

ኃጥዕት
ማሻሻጥ
@OLDBOOKSPDF
ከጀመሩት የማያስቀምጡት ልብ አንጠልጣይ መጽሐፍ!
ደራሲ
አርሺንግ ዋላስ
ትርጉም
ተሾመ ጸምጠው

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved

የመጀመሪያ እትም —— ሐምሌ 1982 ዓ.ም

ድጋሚ እትም —— ሐምሌ 2009 ዓ.ም

ተርጓሚው ከዚህ ቀደም ለአንባቢ ያቀረባቸው ሥራዎች

- እፎይታ
- አመጸኛው
- ጉድ ሲናኝ
- ብው የሚያደርግ ጥቅር

አሣብ አሳታሚ፡-
Hassab Publishers

ስ.ቁ. +251-936 959 644 / +251-923 797 954
+251-965 185 450

Email - hassabpublishers@gmail.com

1

ክፍሉን የፈሳ ሳጥን አቆልቁሎ ተመለከተው። ያስገረመው ነገር አባቱ ያለወትሮው አነስ ማለቱ ነበር። ሟች ምንጊዜም ለኤድዋርድ ግዙፍ እንደሆነ ነው። አሁን ግን በሾጣጣው ሳጥን የተከተተው አባቱ ከመቼውም ይበልጥ አንሶ ታየው። ‹የሕይወት አየር ከላዩ ላይ ስለተገለበ ይሆን?› ሲል አሰበ ኤድዋርድ።

ተቀናቃኝ የለሽና ታላቁ የናፈስ መስፍን ኢዝራ አርምስቱድ ምንጊዜም በሕይወት የተሞላ የንጉስ ምንጭና የማይበገር እንደሆነ ነው። አሁን ግን ግዑዝ ብቻ ላይሆን ትንሽም ሆኗል።

የፈሳ ሳጥኑን ግራ ቀኝ የተደገፉትን የአበባ ጉንጉኖች ሲያስተውል አንድ ነገር ላይ አይኑ ተተከለ። ቡራቡሬው የአሜሪካ ባንዲራ ከአስክሬኑ ራስጌ ይታያል። አም አባቱ ከሚያስተዳድረው ‹‹ሪኮርድ›› ተብሎ ከሚጠራው የኒውዮርክ ዕለታዊ ጋዜጣ ሰራተኞች የተላከ መሆኑን ኤድዋርድ አላጣውም። ምናልባት ከሠራተኞቹ አንዱ ካንበበው ወይም ከሰማው ነገር የኢዝራ አርምስቱድ አስክሬን የአሜሪካን ሰንደቅ ዓላማ ለመሳናፀፍ ብቱ መሆኑን ላይገመግም አልቀረም ይሆናል።

ባለቤቱ ሃና ከአጠገቡ ያንኑ አሰልቺ ልዘናዋን ስታንጓርን ሰማትና ጥላቻ አበግነው። ቢሆንም ፈጠን አለና ወደሷ ቀረብ ብሎ ክንዷን በመደገፍ አይኑት አፈፍ አደረገው። የባለቤቱ ክንድ የክብሪት እንጨት ያህል ተጠነበት። የማታግም ድውይ መሆኗን ያስታወሰው በዚህ ጊዜ ነበር።

ሚስት ረጢብ አይኗን ገለጥ አድርጋ ባሏን ሽቅብ እየተመለከተች

‹‹ሮጀር›› አለች፣ ‹‹ሮጀር የታለ?››

ኤድዋርድ ለእፍታ ሁኔታዎችን ሲገመግም አንድ የረሳው ነገር ትውስ አለው። ሮጀር ለካስ የጣዝ ልጁ ኖሯል። በዚያው ቅፅበት ወደ ኋላው መለስ ብሎ ሲመለከት ሮጀር ረጅም ፊቱን በትካዜ ከስክሶ ከቤተሰቡ ክፍል ወጥቶ ወደ አስክሬኑ ሲያመራ ታየው።

ኤድዋርድ እርምስቲድ ልጁን ጠራና ‹‹እናትህን ጠብቃት›› አለው፣ ‹‹ተሽከርካሪ ወንበሯ ላይ አድርጋት።›› ከዚያ እናትን ለልጅዋ አስረክቦ ኃዘናቸውን ሊገልጡ የመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ ብቅ አለ። ስድስት ሰመጥር አሜሪካውያን ተገኝተዋል። የኢሚሪካ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ሁለት አገረ ገዢዎች፣ ከንቲባው፣ የጠሩ ችፍ አፍ ስታፍ፣ ዝነኛ ጠፈርተኛ ኃዘናቸውን ገለጡ። ኤድዋርድ እርምስቲድ በሰማኒያ አንድ ዓመቱ የሞተው አባቱ ከአይዘንሃወር፣ ከዊንስተን ቸርችል፣ ከቻርለስ ደጎል፣ ከአንዋር ሳዳት፣ ከፍራንሲስኮ ፍራንኮ፣ ከጆን ዋይንና ከተዋናትም በጊዜው ከነበሩ ግናና ሰዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ሲመሰርት የበቃ ብቻ ሳይሆን ከነሱ እንደ አንዱ ሊቆጠር የቻለ ትልቅ ሰው እንደነበር ያስታወሰው በዚህ ጊዜ ነበር።

የቀረውን ኃዘንተኛ ገልመጥ ብሎ ሲያስተውል የራሱን ታማኝ ረዳቶች ሃሪ ዴትዝና ብሩስ ሃርሞስተንን ተመለከታቸው። ብዛት ያላቸው ሴቶችና የአባቱ ጋዜጣ የረከርድ ተቀናቃኝ የሆነው የታይምስ አሳታሚ ሳይቀር ተገኝተዋል። አንድ በታ ችምችም ብለው የሚታዩትን ሴቶች ሲያስተውል ድንገት ከሙ ነሰቢት ትዝ አለችው። ምንም ቢሆን ከሙ ነሰቢት በለቅሶው ላይ እንደማትገኝ አሰበ። እም፣ ሟች አባቱን እንዲጠላ ካደረጉት ሰዎች መካከል አንዷ ከሙ ነሰቢት ነበረች። የጥላቸው መንስኤ እናቱ በሕይወት እያለች አባቱ ከሙ ነሰቢትን ለብዙ ዓመታት በትምጥነት መያዙ ብቻ ሳይሆን ከሙ ነሰቢት ከአባቱ ብቻ ሳይሆን ከእሱ ከራሱ እንኳ የምታንስ ወጣት ቆንጆ በመሆኗ መሆኑን ሲያምን ሞከረ። እውነተኛው የጥላቻ መንስኤ ግን ይህ ሳይሆን ኤድዋርድ የጣዝ አባቱ ምቀኛ መሆኑ ነው። እናም ከሙ ለተበሳ አለመምጣቷ ደስ አሰኘው። እም፣ አለመገኘቷ ለአባቱ እምብዛም የምትጨነቅ አለመሆኗን የሚያሳይ በመሆኑ አስደሰተው።

ኪም ነሰቢትን በዓይኑ ማፈላለጉን እንዳቆመ ጠበቃው ሆራስ ሊዲንግተን ወደሱ ሲመጣ አዩው። ‹‹እጅግ አዝናለሁ ኤድዋርድ›› አለ ሊዲንግተን የአርምስቴድን እጅ በአንድ እጁ እየጨበጠ፣ ሌላውን እጁን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ።

‹‹ምን ይደረግ፣ ጥሩ ሕይወት አሳልፎ ማለፍ መቻልም መታደል ነው›› አለ፣ ‹‹ደስተኛ ሕይወት አሳልፈሃል።››

‹‹እሱስ ልክ ነሁ›› አለ ሊዲንግተን። ከዚያም ‹‹ኤድዋርድ፣ ጊዜ ስታጭኝ—ማለቴ ይህ ሥነ-ሥርዓት እንዳበቃ—ላገኝህ እፈልጋለሁ። እስከዚህ አስቸኳይ አይደለም። ነገ ወይም ተነገ ወዲያ ሊሆን ይችላል። አንድ መስመር መያዝ ያለበት ጉዳይ አለ፤›› አለው።

‹‹ጉዳይ? የምን ጉዳይ?››

‹‹የአባትህ ኑዛዜ ብዙውን ጊዜህን ማባከን የለበትም። አጭር ኑዛዜ ነው። ብዙው ክፍል አንተን ይመለከታል። እንደምታውቀው ሲበዛ ከበርቴ የነበረ ሰው ነው። ታዲያ የሱን ጉዳዮች ከወዲሁ ተረክበ መቆጣጠር ያሻል። ለማንኛውም ሲመችህ እንነጋገርበት። ከቻልህ ነገ።››

‹‹ላፊስ ቢሆን?››

ሊዲንግተን ተግረመ። ‹‹ላፊ? ይሁና። ከዚህ መውጣት የምትችል ከሆነ.....››

‹‹መውጣት እችላለሁ። አባቴ ምን እንደተናዘዘ በቶሎ ማወቅ ያለብኝ ይመስለኛል።››

‹‹ትክክል ነህ፣ በአፋጣኝ ማወቅ አለብህ። በል እንግዲህ ልክ ከግብአተ መሬቱ በኋላ በተጥታ ወደ ቢሮየ ነው የምሄደው።›› ከኑቱ ኪስ የወርቅ ሰዓት አወጣ።

‹‹ስምንት ሰዓት ላይ ቢሮየ እገኛለሁ።››

‹‹በቃ እኔም በሰዓቱ እገኛለሁ፤››

ልክ ሊዲንግተን ከፊቱ ዞር እንዳለ የአባቱ ሞት በሱ ላይ ሊያስከትል

የሚችለው ውጤት በአርምስቱድ አእምሮ ድቅን አለ። ጠበቃው ሊዲንግተን ‹‹ብዙው ክፍል አንተን ይመለከታል›› ብሎታል፣ አባባሉ የአባቱ ኑዛዜ በተለይ የሚያተኩረው በእሱ ላይ መሆኑን ያስረዳል። አም፣ ኤድዋርድ አርምስቱድ ወራሽ፣ የዚያ ግዙፍ ግዛት ወራሽ መሆኑ ነው። አሁን ንጉስ ሞቷል። ከእንግዲህ የሚችን ንብረት ጠቅልሎ የሚይዘው ንጉስ ኤድዋርድ አርምስቱድ ይሆናል። በዚሊዮን የሚቆጠረው ዶላር፣ ጋዜጦቹ፣ የቴሌቭዥን ጣቢያዎችና ከሁሉም በላይ በዚህ ሁሉ ላይ ያለው ስልጣን አሁን ለኤድዋርድ ይሳለፋል። አም፣ ያ የማይቀር ነው። በውርሱ ማንም ተቀናቃኝ የለም። የኤድዋርድ እናት ከሶስት ዓመታት በፊት ሞታለች። በርግጥ የሚች የልጅ ልጅ ሮጀርና በሁለተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ዘመዶች አይጠፉም። ነገር ግን ለእኒህ ሁሉ ሚች ደንታ ያሰው ሰው ስላልነበረ ከውርስ መገኘብ ውስጥ ያስገባቸዋል ተብሎ አይጠረጠርም። የሚች ብቸኛ ልጅ ብቸኛ ወራሽ መሆኑም አይቀርም።

የእንዲህ ዓይነቱን ስልጣን ወራሽነት ለእፍታ እንኳ ከማሰላሰሉ በፊት ስሙ ሲጠራ ሰማ። ‹‹ኤድዋርድ›› ጥሪውን ለሁለተኛ ጊዜ ሲሰማ ድምፁ የሚስቱ መሆኑን ተረዳ። ግልመጥ ብሎ ሲመለከት ሃናን በተሽከርካሪው ወንበሯ እየገፉ ሮጀር ሲያመጣት አየ። ‹‹እንዴት ትቀፋለች›› ሲል አሰበ። እድሜዋ ግና ሃምሳ ስድስት በመሆኑ እቸው ብትሆንም በአቋሟ ግን በእጥፍ ጀጅታለች።

ከጎኑ እንደደረሰች ‹‹ኤድዋርድ›› አለች፣ ‹‹አስከሬኑን ወደ መካነ መቃብሩ እየወሰዱት ነው። እዚያ መገኘት ይኖርብሃል።››

‹‹ጥሩ፣ ሾፌሩን እዚህ ድረስ አምጣልኝ፣›› አለ አርምስቱድ ሮጀርን፣ ‹‹ታዲያ እናትህን ወደኩርባው ውሰዳት።››

ራመድ ሲል ሲጀምር የሃና ድምፅ ዳግመኛ አሰተው። ‹‹ኤድዋርድ፣ ተበሩ እንዳበቃ ቀጥታ ወደቤት መመለስ አለብን። ላትሰማ አልተረዘም፣ መቶ ያህል እንግዶች ሊያስተባብኩ ይመጣሉ። ሁሊታችንም በበታው ተግኝተን ልንተበላቸው ይገባል።››

‹‹እንግሾለን›› አለ አርምስቱድ፣ ትዕግስቱን አጥቶ። ‹‹አንቺና ሮጀር

ከሞብሩ በኋላ በሞጥታ ሂዱ። እኔም እከተላችኋለሁ። መጀመሪያ የምገኝበት አጣዳፊ ጉዳይ ስላለኝ ሽማግሌውን ልቀብረው አልቻልኩም።››

‹‹ጉዳይ? በዛሬው ቀን?››

‹በዛሬው ቀን በሚኙ ንጉሥ ፋንታ አልጋ ወራሹ ዘውድ መድፋት አለበት› ሲል ለአሮጊቷ ሊነግራት ፈልጎ ዋጥ አደረገውና ‹‹በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው፣ እደርስባችኋለሁ.....›› አላት።

* * *

ኤድዋርድ አርምስቱድ በእማካሪ ጠበቃው በሆራስ ሊዲንግተን ቢሮ እንደደረሰ ጠበቃው ከአንድ ሰነድ ጋር ተፋጦ አገኘው። ምናልባት ያው የኑዛዜ ሰነድ-ሳይሆን አይቀርም።

የአርምስቱድን መግባት ሲያይ ጠበቃው ከአንባቡ ቀና ብሎ መነፅሩን አወለቀ።

‹‹አ! ኤድዋርድ በሞጥታ ወደዚህ በመምጣትህ ደስ ብሎኛል›› አለ ሊዲንግተን፣ ‹‹በተለይ አባትህን በቀበርክበት ዕለት መምጣትህ፣ የአባት ሞትክ በሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰት ነገር ነው።››

‹‹ኧረ እኔስ ምንጊዜም አይከሰትም ብየ ሰግቼ ነበር፣›› አለው ኤድዋርድ።

ሊዲንግተን በዚህ አነጋገር ሽምቅት አለ። ኤድዋርድ ፊግማ አለና፣ ‹‹አስደነገጥኩህ? እኔኮ ለውርስ ሳቆበቁብ ዕድሜዬን የገፋሁ ሰው ነኝ። እድሜየ ሃምሳ ስድስት። በውርስ ነገር ተስፋ ቆርጨ ነበር። አሁን ግን ተራየ ደርሷል። አዎ፣ ተራየ ደርሷል›› አለው።

‹‹አ! አዎ—አዎ... እርግጥ ነው፣ ብቸኛ ወራሹ አንተ ብቻ ነህ።››

‹‹ደህና፣ እስኪ በኑዛዜው ላይ እንነጋገርበትና ይፋ እናድርገው።››

ሊዲንግተን ከጠረጴዛው ላይ ያለውን የኑዛዜ ወረቀት ቀረብ አደረገው። ከዚያም ራሱን ለማረጋጋት ለአፍታ ዝም አለና ‹‹እንዳነብልህ ትፈልጋለህ ኤድዋርድ?›› አለው። ‹‹በርግጥ አሮጅ ኑዛዜ ነው። ሰምች እስከ 125 ገጽ

ድረስ ይናዘዛሉ። የአባትህ ግን 37 ገፅ ብቻ ነው። በውነቱ ከንብረታቸው ብዛትና ስፋት ጋር ሲተያይ አጭር ኑዛዜ ነው ለማለት ይቻላል። ላንብልህ እችላለሁ፤›› አለው።

‹‹አይ፣ 37 ገፅ እስክታነብ እንዴት እተመጣለሁ። ፍሬ ሃሳቡን ብቻ ልወቀው። ጠቅላላ ኑዛዜውን ጊዜ ሳጥኜ አነበዋለሁ። አንድ ትጅ ትልክልኛለህ። አሁን ፍሬ ሃሳቡን ብቻ። ለመሆኑ ሁሉንም ነው ወይስ ከፊሉን ያወረሰኝ?››

‹‹እጅግ ብዙውን ንብረቱን ተናዞልሃል። ለልጅህ ለሮጀርና ለባለቤትህ አንዳንድ ነገሮች ትቷል። ከአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ውስጥ ግማሹን ንብረቱን ላንተ ይሁን ብሏል። ግማሹ በርግጥ የሃና ነው፣ በሕጉ መሰረት።››

አርምስቱድ እጁን በንቀት ወደታች ጣል በማድረግ ‹‹የሃና ጉዳይ ችግር የለውም›› አለው ተበል አድርጎ።

‹‹በጣም ጥሩ። ስድስቱንም ቤቶቹን አውርሶሃል። አንዳንድ አነስተኛ ነገሮች በርግጥ ለአቋጥረኛ ዘመዶች ይሁን ብሏል።››

‹‹ሊላስ?›› አለ ኤድዋርድ አርምስቱድ።

‹‹በታ ሊላው በሙሉ ያንተው ነው። ኡታሀና አቫዳ ያሉት የማዕድን ጉድጓዶች፣ አክላሀማና ቴክሳስ የሚገኙት የዘይት ጉድጓዶች ‹‹ኮምር፣ ሁሉም የንግድ ገበያዎች፣ የኒውዮርኩ ክልል፣ የንግድ መርከቦቹ፣ ለብሔራዊ መዛሪያም ከሰጣቸው በስተቀር ሁሉም የስነጥበብ ስብስቦች ሁሉም ላንተ።››

አርምስቱድ ድንገት አንድ ነገር ፍክ አለበት።

‹‹ስለ ኪም ምን አለ?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹ስለ ኪም ነሰቢት?›› ሊዲንግተን አልገባውም። ‹‹ምን ሊል ኖሯል?›› ሲል በጥያቄ መለሰለት።

‹‹ለፀ.ም የተናዘዘው ነገር አለ?››

ጠበቃው ሲያቅማማ ቆየና ‹‹የለም፣ በውል አይታወቅም›› አለው።

‹‹ለምን? እንዴት ገም ሊላት ቻለ?››

‹‹አየህ ኑዛዜኩ በማንም አይን ሊታይ የሚችልና ከማንም ጆሮ የሚገባ ነገር ነው። እንዴት ለትምጡ ውርስ ተናዘ ስሙን ለማጉደፍ ይደፍራል?››

‹‹ኤሮ፣ የእሷን ትምጥንት እንኳ አገር ያወቀው ጉዳይ ነው። አንድ ነገር እንዴት አልተወላት›ም?››

‹‹ምንም ነገር አልተወላትምኩ አላልኩህም›› አለ ሊዲንግተን፣ ‹‹ብቻ በኑዛዜው ላይ የተጻፈላት ነገር የለም።››

‹‹ታዲያ ምን ሰጥታት ይሆን?›› አርምስቱድ ለማወቅ ፈለገ።

ሊዲንግተን ከአፉ ቅጠብ አለና ‹‹አሰን መተንተን የኔ መብት አይመስለኝም ኤድዋርድ። በሁለቱ ግንኙነት መካከል የነበረው ሚስጥር ያግደኛል›› አለው።

‹‹ግባኝ፣ ግባኝ›› አለው አርምስቱድ አቋርጠ፣ ‹‹ማለቴ እንዲያ ሲያስብላት የነበረችው ሴት እንዴት በመጨረሻው ፊቱን ያዞርባታል? ለመሆኑ የሰጣትን አጋርትማስ አወደተላት?››

‹‹አም።››

‹‹አሃ›› አለና አርምስቱድ ሲጋራ አቀጣጠለ።

‹‹እሺ አሁን ወደኔው ጉዳይ እንመለስ። ለመሆኑ ምን ያህሉን ርስት ነው ያወረሰኝ?››

‹‹ነገርኩህ፣ ብዙውን፣ ከሶስት አራተኛ በላይ።››

‹‹እኔ የማውቀው በአሀዝ ሲቀመጥ ብቻ ነው። ምን ያህል?››

‹‹ግምት ልስጥህ። ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ።››

አርምስቱድ አፍታ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ‹‹ግን በርግጥ ያለምንም ገደብ በማያሻማ ታሊ ነው የተናዘዘው? ሊላ ሳላ፣ ሞትሞት ውስጥ የሚጨምረኝ ታሊ የለበትም?›› ሲል ጠየቀው፣ ተጠል አድርጎ ደግሞ ‹‹ስለ ጋዜጣውስ?›› አለ፣ ‹‹በኑዛዜው ላይ ጋዜጣውን ጨምሮልሻል?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹ጋዜጦች›› ሲል ሊዲንግተን አስተካከለው። ‹‹እንደምታውቀው የብዙዎቹን ጋዜጦች ህትመት አቁሚል። ቢሆንም አሁንም አምስት ጋዜጦች

እየታዩለው ናቸው።››

‹‹እኔ የምፈልገው አንዱን ብቻ ነው›› አለ አርምስቱድ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ ‹‹ኒውዮርክ ሪከርድ። የሁሉም የበላይ። ሊሎቹ ሁሉ ትርኪምርኪ ናቸው። እጅግ ጠቃሚው ሪከርድ ብቻ ነው።›› እንዲህ እየተናገረ አርምስቱድ የጠበቃውን ፊት ሊያነብ ሞከረ። ‹‹ሪከርድን አውርሰኸል አይደለም?››

‹‹አ. . . አዎ›› አለና ሊዲንግተን የንዛዜውን ወረቀት ገልበጥ ገልበጥ አደረገ። ‹‹አዎ እስኪ ልመልከተው።››

‹‹ምን የምትመለከተው ነገር ይኖራል?›› አለ አርምስቱድ እየተትበጠበጠ። ‹‹እኔን የሚያስጨንቀኝ የአባቱ ንብረት ሪከርድ ጋዜጣ ብቻ ነው። እሱን ራሱን ዝነኛ ያደረገው ሪከርድ ነው። እኔም ያዳማት በሪከርድ ነው። ከንግዲህ ሪከርድን ምን እንደማደርገው አውቃለሁ። አሁን ሪከርድ የኔ ሆኗል፣ አልሆነም?››

ጠበቃው አሁንም የንዛዜውን ገፆች ያገላብጣል። ‹‹ሆኗልና አልሆነም ነው መልሱ›› አለ በመጨረሻው፣ ከንዛዜው ውስጥ ሰራሱ በድጋሚ የሚያነበው አረፍተ ነገር በማግኘቱ አይኑን አፍጥጦ። ‹‹ኒውዮርክ ሪከርድን በተመለከተ አሻሚ አንቀጽ አለ።››

‹‹ምን አይነት አንቀጽ?››

‹‹ጋዜጣውን በርግጥ ላንተ አውርሷል፣ ግን አንድ ገደብም አድርጎበታል።››

‹‹የምን ገደብ?››

‹‹በእርግጥ... በርግጥ ግራ የሚያጋባ አንቀጽ ነው። በርግጥ ሲናዘዘውም ትዝ ይለኛል። ትርጉሙ ባይገባኝም የታዘዝኩትን መጻፍ ስለነበረብኝ ጥራውን ቃል ነው ያስተመጥኩት።››

‹‹ምን ብሎ ወሽኩቦ ይሆን?››

‹‹በርግጥ ኒውዮርክ ሪከርድን ወርሰሀል። ግን ለአንድ ዓመት የመከራ ጊዜ ብቻ ነው የተፈቀደልህ። በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ በሆነ ነጥብ

ተዋናዮችን ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣን በልጠህ መገኘት ይጠበቅብሃል። በዓመቱ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ታይምስን ከበለጥህ ጋዜጣው ለዘለቂታው ያንተ ይሆናል። ይህ ከተባነህ ግን ሪኮርድ ለታይምስ ባለንብረት ይሸጣል።››

‹‹ውሽ! በለው›› ሲል ሊዲንግተን በተራው አቋረጠው። ‹‹ሰበብ ፈልጎ ሊነጥቀኝ ነው። ጋዜጣው ህይወቱ መሆኑን ያውቃል። ከ1954 ጀምሮ እስከዛሬ ታይምስን እንዳልበለጥን ለቡ ያውቀዋል። ላሚላው የማልችለውን ገደብ ጥሎብኛል። የተረገመ። የምፈልገውን ነገር ነስቶ ጥሩ አባት ተበሎ በዓለም ሊታወት ይፈልጋል። ሁልጊዜ እንደሚያምነው እኔ ተልካሻ፣ ታናሽ ሰው መሆኔን ለዓለም ሊያሳውት ይፈልጋል። ውሽ!››

‹‹ቶይ ታግስ ኤድዋርድ›› ሲል ሊዲንግተን በተራው አቋረጠው። ‹‹ጋዜጣው ያንተ ባይሆን እንኳን የሽያጩ ገቢ ለዘለቂታው ላንተ እንደሚሆን ተናዘልህ። በዘጠው ሊላ ጋዜጣ ልታሳትም ትችላለህ።››

‹‹አልገባህም፤›› አለ አርምስቱድ ቦግ ብሎበት። ‹‹እኔ የማውቀውን ያህል ሰውየውን ኢታውቀውም። እሱ ለገንዘብ ደንታ እንደሌለው ሁሉ እኔም ጉዳየ አይደለም። እሱ የሚያስበው ስለጋዜጣው ነው። እሱን... እሱን በዓለም ዙሪያ ዝነኛ ያደረገው ጋዜጣው ነው። እኔም ስሜን ያነሳሁት በሪኮርድ ጋዜጣ ነው። ከሁሉም በላይ የምፈልገው ኒውዮርክ ሪኮርድን ነው። እሱ በጀ ቢገባ ማንኑን አስመስክርበት፣ ግን መሆኔን አሳይበት ነበር። እሱ ግን አማሩ ወደ ጉድጓድ ሲሄድ የልቡን ሰራ። እድሉን አንኳ እንዳልሞክር ከለከለኝ።››

‹‹ማመጣዘን ያታነህ መሰለኝ ኤድዋርድ። ደግሚ ልንገርህ፣ የራስህን ጋዜጣ ልታሳትም ትችላለህ።››

‹‹ላራ ጊዜ አዲስ ጋዜጣ አሳትመህ ዝና ማግኘት ምን ያህል ከባድ መሆኑን አጥተኸው ነው? ጋዜጣ ሲባል ከዚህ ቀደም ስመን የተከሰ ነገር መሆን አለበት። ጋዜጣ እንደ ሰው ነው፣ ልብና ነፍስ ያለው። ጋዜጠኛ ጓደኛ ነው፣ የእያንዳንዱን አንባቢ ቤተሰብና ሕይወት። ሪኮርድ በሰንት መቶ ሺህ የሚቆጠሩት የዚህ ከተማ ነዋሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ነው። በእጀ መግባት ነበረበት፣ በጀ ገብቶ ከወትሮው ይበልጥ ዝነኛ ጋዜጣ ሆኖ እንኑም ዝነኛ ማድረግ ነበረበት። ምን ያደርጋል፣ ምኞቱን ጉም እደረገው።

ርጉም፡፡››

‹‹ታዲያ አሁንም አልነፈገህም ኤድዋርድ›› አለ ሊዲንግተን ‹‹ለአንድ ዓመት ያንተ መሆኑን ጽፎልሃልኮ፡፡››

‹‹አንድ ዓመት›› ሲል ታሉን ደገመው አርምስቱድ ፊቱን ከስክሶ አድርጎ፡፡ ‹‹እሱ ስንት ዘመን ሞክሮ ያታተውን ባንድ ዓመት እንዳደርግ ተናገረ፡፡ እንደማልችል ያውቃል፡፡ ውሻ!››

ጠቢቃው አሁንም ለማሳመን አንድ የመጨረሻ እድል ሊሞክር ፈለገ፡፡ ‹‹ምናልባትኮ ሰላንተ ያለው ግምት ካሰብከው የላቀ ሆኖ ይሆናል ኤድዋርድ፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉንም ነገር አውርሶሃል፡፡ የቲሊቪዥን ጣቢያዎቹን የኒውዮርኩን ጨምሮ ከመሰጠት ሌላ ምን ያድርግ፡፡ እዚህ ኒውዮርክኮ የቲቪ ተከታታዩ ብዛት ከጋዜጣ አንባቢው በለጠ እንጅ አያንስም፡፡››

‹‹ይዘትህት ቲሊቪዥን፡፡ የማይሞኝና የውለኛት የርዩ ጥርትም፡፡ ባንድ ርዕሰ ሶስት ደቂቃ፡፡ ለማብራሪያ፣ ለትንተና፣ ለአብይ ጉዳይና ለርዕሰ አንቀጽ አምድ የሊለው ግብስብስ፡፡ የኒንዴን ሽተጥ ካለማሻሸጥ የማያውት፡፡ ቲሊቪዥን ያውርሰኝ?››

‹‹ሊላው ሁሉስ፡፡ ስንቱ ሁሉ ቢሊዮን ዶላርሳ?››

አርምስቱድ ሲጋራውን መተርከሻው ላይ ጣል አደረገና ተነሳ፡፡

‹‹የተወልኝ ሁሉ ለኔ ምኔም አይደለም›› አለ አንጀቱ ተኮማትሮ፣ ራሱን ነቀነቀ፡፡ ‹‹ላንተ የሚገባህ ነገር አይደለም›› አለው ቀጠለና በሾርኒ እየተመለከተው፡፡ ቀጥሎም ‹‹በነገራችን ላይ በግሌ የምነጋገረው ጉዳይ አለኝ፣ ስልክህን ብታውሰኝ፣›› አለው፡፡ ‹‹አሁኑኑ ተጠሮ ሰጥቼ በማንባር ላገኘው የምፈልገው ሰው አለኝ፡፡››

* * *

‹‹የላፈው ተጠርሀን ታክብራለሀ ብየ አላሰብኩም ነበር›› አለ ጴትር ሻርፍ የቢሮውን በር ከዚጋ በኋላ ኤድዋርድን ከራሱ ወንበር ትይዩ ባለው

ወንበር ላይ እንዲተመጥ እያመለከተው። ዶክተር ሻርፍ ትሁት፣ ከሁሉም በላይ የተራቀቀና ታላላት የሚባሉትን የኒውሮሎጅ ሰዎች የሚያክም የአእምሮ ስፔሻሊስት ነው። አርምስቱድ ከአባቱ ጉያ ወጥቶ ራሱን ችሎ ነባ ሕይወት እንዲመራ ሊመክረው የሞከረው ከብዙ ጊዜ በፊት ነበር። ዛሬም የወደፊቱን ሕይወቱን አመራር በሚመለከት የሚሰንዝረው ምክር ነበረው። አርምስቱድ ግን በቱላ ታውሯል።

"ዛሬ ለምርመራ ትመጣለህ ብየ አላሰብኩም ነበር" አለ ሻርፍ ነገሩን ሲጀምር፣ ኤድዋርድ ሳምንታዊውን ምርመራ ሊያካሂድ የመጣ መስሎት።

"ምርመራ ገደል ይግባ። ነጩዘው አሮሶኝ የምሄድበት ስፊልግ ነው አንተን ያስታወስኩት።"

ዶክተሩ ፒፓውን ከከንፈሩ አላቀቀ። "ቀብር ላይ አልተገኘህም ልበል ኤድዋርድ?"

"እሱማ እንዴት እቀራለሁ። አለዚያ መሞቱን እንዴት አረጋግጣለሁ?"

"እና አንተም የሚችን መሞት አየሃ?"

"እንደ መድረክ ምስማር መታብር ውስጥ ተቸብችቧል። አርግጠኛ ሆኛለሁ።"

"ታዲያ አሁንም ነፃነት አይሰማህም?"

"እንዴት ሆኖ? የዘረጋው ገመድ አሁንም እንደተብተበኝ ነው። ግናም ይተበትበኛል። በኩዘው ላይ የሰፈረውን ልትሰማልኝ እፈልጋለሁ። ውሻ።"

"እሽ ኤድዋርድ፣ የትኛው ኩዘ ነው ይኸን ያህል ያስከፋህ?"

"ሁሉንም ነገር አውርሶኛል። ከምፈልገው ነገር በስተቀር።"

"ንገረኛ?"

አርምስቱድ የኩዘውን ይዘት በመሉ ተናዘዘለት። ብመጨረሻም ገደብ የተጣለበትን የሪከርድን አንቀጽ ነገረው። ንግግሩን እንደጨረሰም ምላሹን ከሐኪሙ ይጠብቅ ይመስል ሻርፍን አፍጥጦ ተመለከተው።

‹‹በታ ቱጃር ሆነሃል፡›› አለ ዶክተር ሻርፍ፡ ‹‹ሃብታም አድርገውሃል። ይሆን ሁሉ እንዲያደርጉ ማን አስገደዳቸው? አባትነታቸው አይደል?››

‹‹ጋግ አሁን የሱ ተንኮል ጠፍቶህ ነው? ሁልጊዜም አሳንሶ እንደተመለከተኝ ነው። ለምን እንደሁ አላውቅም፡ በኔ ላይ ቅንጣት እምነት የለውም።››

‹‹እንደአባትህ ያሉ ታላላቅ፡ ልምድ ያላቸውና ሁሉንም ነገር በጀኖው ያደረጉ ሰዎች በወለዷቸው ሰዎች ላይ እምነት ሊጥሉ ቢችሩ አያስገርምም።››

‹‹ነገር መዲጋም አልወድም›› አለ አርምስቱድ፡ ‹‹ሰርቶልኝ ነው የሄደው። ከመጀመሪያው ጀምሮ ጋዜጠኛ፡ አሳታሚ መሆን እንደምፈልግ ያውቃል። እሱ ግን አንድም ቦታ አልሰጠኝም። ለመሆኑ ምን የጋላፊነት ቦታ አሰደሰኝ ያውቃል? እሱ የሚተማመነው በሊሎች ነው። እኔንማ የልዩ ፕሮጀክት አፈሰር አድርጎኝ ቁጭ አለ። ሁልጊዜ ተኮጥያ ሥራዎችን ይሰጠኛል። ደግሞ የንቱቱ ንቀት አሁን በአምላ ስድስት ዓመቱ እንኳ ስራውን ገና አልለመድነውም ይለኛል። አሁን በመጨረሻው ምኞቱ ተሳካ ብዩ አሰቢ ነበር። ማንኑን ለዓለም ሳሳይ ነው ብዩ ነበር። ከአንድ ሰዓት በፊት የጣለብኝን ማዕቀብ ሰማሁ፡ የማይቻለውን ነገር ካላደረግሁ በስተቀር ሪኮርድ የኔ አለመሆኑን ተናዘዘልኝ። ይሸጣል አለኝ። ያ ነበር የተወልኝ የስንብት መልዕክት።››

ዶክተር ሻርፍ ሊናገር ቢሞክርም አርምስቱድ አፍ የሚያስከፍት አልሆነም። እሉ ቱማ ይልበታል። የተመረዘውን የሕይወቱን ታሪክ መተንተኑን ሊያቆም አልቻለም። በአንድ ሙያ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ሲጀምር አባቱ ሆን ብሎ ከሥራው እንደሚያገለው አሳወቀ።

‹‹ለዚህ ነው የመጣሁት ካርል›› አለ በመጨረሻ በረጅሙ ተንፍሶ። ‹‹እርዳ ብያለሁ። እርዳታህ ያስፈልገኛል።››

‹‹አዎ።››

‹‹በኔ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንደነበረው ታውቃለህ።››

‹‹ይሆናል።››

‹‹ምርዝ አድርጎ ይጠላኝ ነበር። የሱን ንቀት እያዩ የበታኞቹ እንኳ ከጥፍራቸው ቆሻሻ አይቆጥሩኝም ነበር። ከቺካጎ ሰራተኞች እንኳ ለኔ በጎ አመለካከት የነበራቸው ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። እንዲያውም አንድ ብቻ ነው. . አዎ፣ ረዳት አዘጋጁ ቬሮ ዊስተን። አሁን የፕሬዝዳንቱ የፕሬስ ፀሐፊ ከመሆኑና ከመለያየታችን በፊት ጥቂት አክብሮት ያሳየኝ ነበር። እድል ሊሰጠኝ ይሞክር ነበር። አዎ መሉ ሰውና ችሎታ ያለኝ መሆኔን የሚያውቀው ቬሮ ዊስተን ብቻ ነበር። ታዲያ ምን ያደርጋል፣ ዴኑ አባቴ ወደኒውዮርክ አምጥቶ ከሥራ አገለለኝ። እዚህ ለሪኮርድ አዘጋጅት መጠቃቀሻ አደረገኝ።››

ዶክተር ሻርፍ ፒፖውን አራግፎ ሌላ ትምባሆ ከሞላው በኋላ አቀጣጥሎ ማገለትና በጢሱ አሳልፎ አርምስቱድን ተመለከተው።

‹‹ኤድዋርድ›› አለ ሻርፍ፣ ‹‹አሁንክ የሪኮርድ ባለንብረት ነህ።››

‹‹ለአንድ ዓመት›› አለ አርምስቱድ ግንፍሎ።

‹‹ለአንድ ወርም ይሁን። እኒያ ያንንጠጡህ አዘጋጆች አሁን ያንተ አዘጋጆች ናቸው። አለቃቸው ማን እንደሆነ ልታሳያቸው ትችላለህ።››

‹‹ማለት ጠራርጌ ላባራቸው?››

‹‹ላይሆን፣ የራስህን ታማኝ ሰራተኞች አሰባስብ። እምነት የምትጥልባቸው ልምድ ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ?››

‹‹ሃሪ ዴትዝ ቲጥር አንድ ታማኝ ሰው ነው። ብሩስ ደግሞ ከስ ቱጥሎ፣ ብሩስ ሃርምስተን። ቺካጎ ሳለሁ አብረውኝ ሰርተዋል። እዚህ ኒውዮርክም ልዩ ፕሮግራምች ስሰራ አብረውኝ ነበሩ። በኔ ይተማመናሉ። ለኔ ሲሉ ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ።››

‹‹እንግዲያውስ እነሱን ካንተ ጋር አሳድጋቸውና ስለጋዜጣው አንድ ነገር አድርግ። አዎ፣ ጥንትም ከአባትህ ከምትፈልጋቸው ነገሮች እጅግ በጣም ጠቃሚው ጋዜጣው መሆኑን ስትናገር ነበር።››

‹‹እርግጥ ነው ደጋግሜ ስነግርህ የነበረው ካባቱ ንብረቶች ሁለቱን ብቻ

እንደምወጣ ነው፣ ጋዜጣውንና ኪሜን። ኪም ነሰቢትን።››

‹‹አሁን እንግዲህ ጋዜጣውን ይዘሃል. . .››

‹‹ኪም ደግሞ. . . እም፣ በርግጥ የአባቱ ትምጥ ነች. . .››

‹‹አባትህ አሁን ሞተሞል ኤድዋርድ።››

አርምስቱድ ዶክተሩን በሲጋራው ሞስ አሳልፎ ተመለከተው። ሁለቱም ለረጅም ጊዜ ዝም አሉ። ‹‹ልክ ነህ›› አለ አርምስቱድ በመጨረሻው፣ ‹‹በነገራችን ላይ ኪም ወጻንተ ብት ብላ ታውታለች?››

አርምስቱድ እንደሚያስታውሰው ከአምስት ዓመታት በፊት አልፎ አልፎ ሲያያት ይችል በነበረበት ጊዜ ኪም ነሰቢት የሱን የሞራል ውድቀት የተገነዘች ሰው ነበረች። ብዙውን ጊዜም የአባቱን ድርጊት በመታወም ስለተናገረች አባቱ የአእምሮ ሐኪም እንድታይ አድርጓል። ሚች እንዲያክማት የተላከችበት ዐኪም ሲበዛ አስተዋይና ትህትት የሆነው ዶክተር ሻርፍ ነበር። የዶክተር ሻርፍን ሥነምግባር ያየችው ኪም ነሰቢት ነበረች ኤድዋርድ አርምስቱድንም ከሐኪሙ ጋር ያስተዋወቀችው።

‹‹በርግጥ እዚህ መምጣት ከተወች ቆይታለች›› አለ ዶክተር ሻርፍ፣ ‹‹ለመጨረሻ ጊዜ የመጣችው ከአንድ ዓመት በፊት ነበር። አም ትገ ይለሻል፣ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳልነበረች ታስታውታለች። ብቸኝነት በሽታ ነው። ብዙ የምትጠጣ ትመስለኛለች። ተመላልሳ እንድታነጋግረኝ ፊልጌ ነበር፣ ግን ቀረች።››

‹‹በጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለችም አልከኝ?››

ዶክተር ሻርፕ የጢጉውን ጫፍ ባጥንጫው ጫፍ ጠረግ—ጠረግ አደረገ። ‹‹ለምን እኔን ትጠይቀኛለህ ኤድዋርድ. . .ራስህ አታነጋግራትም?››

* * *

በሩን የከፈተችለት ራሷ ነበረች። አርምስቱድ ለሰላምታ እጁን ሳይዘረጋ ወይም ታል ሳይተነፍስ ተገትሮ ቆየ። ለረጅም ጊዜ ሲመኘው የነበረው ግላ ከፊት ለፊቱ ቆሞ ሲያየው ምን ይበል!?

ደግሞ የቁንጅናዋ ነገር. . . ጥሙም ቁንጅ ነች። ሁድማ የተናገረችው እዩ ነበረች። ‹‹ኤድዋርድ! ፊፅሞ ፊፅሞ ያልተበጠሀ እንግዳ። ሳይህ የተሰማኝን ደስታ ልገልፅልህ አልችልም።›› እጀጀን ስትዘረጋልት በእቅፉ ውስጥ ገባና ሁለቱንም ጉንጮቿን አገላበጠ ሳማት። የገላዋ ጣፋጭ ጠረን ከአከናፍሯ ከሚወጣው የውስኪ ሽታ ጋር ተቀላቅሎ ልዩ መዓዛ ሰጥቷታል። ‹‹ማባ እንጂ፣ ማባ እባክህ?›› አለችው ክንዱን ይዛ በኮሪደሩ በኩል ሰፊ ወደሆነው ሳሎን እየጎተተችው።

ለጥቂት ጊዜ የክፍሉ መብራት ተለም አፍዝዞት ቆየ። አይኖቹ በሰማያዊው ሶፋ ዙሪያ በተቀመጡት ሽጉርጉር መደገፊያዎች በሚያምረው ሲጋጅና በትልቁ ቲያኖ ዙሪያ ተንከራተቱ። ከቢያኖው ጎን የሚታየው ትልቁ ቴሌቭዥን አፍራ ያሳያል። ኪም ነሰቢትን ደግሞ ተመለከታት። በነሱ የውስጥ ልብስ እንዳለች በመምጣቱ ሐፍረት የተሰማት መሆኑን ለማሳወቅ የምትጥር ትመስላለች። ‹‹ይቅርታ ክፍሉ ተመሰቃቅሏል። ሰራተኛየ ስለሌለች ነው›› አለችው፣ ቶጥላም እየተገራገደች ወደ ቴሌቭዥኑ ሄዳ አጠፋችው። ‹‹የሚወሳ ነገር. . . ኤድዋርድ?››

‹‹አንቺም እኔን የምትመስይ ከሆነ. . .›› አላት።

‹‹እንዴታ. . . እኔ ውስኪ ነው የምወስደው። ያንተ ምርጫ ምን ነበር?.....ረሳሁ።››

‹‹እንዳንቺው።››

መጠጡን እየቀዳች ‹‹በጣም ረጅም ጊዜ ሆነንኮ ኤድዋርድ›› አለችው።

‹‹አሥራ አንድ ዋሬ ወራት።››

ትውውቃቸው የጀመረው በአጋጣሚ ነበር። አንድ ቀን የልደት ቀኗ ስለነበር አባቱ ቲያትርና ራት ሊጋብዛት ቀጠሮ ካስያዛት በኋላ በአጋጣሚ አስቸኳይ ሰራ ላይ መግኘት ስለነበረበት ወደ ሎስ አንጀለስ ይሄዳል። ኪም ምሽቱን ብቻዋን እንዳታሳልፍ በማለትም ለኤድዋርድ ይደውልለትና አብሯት እንዲያመሽ ይጠይቀዋል።

ከኪም ጋር ያሳለፈው ምሽት ለኤድዋርድ የተለየ ነበር። ማደጉን

እንዳሳፈጋገጠ ጎረምሳ ሲርበተበት ነበር ያመሸው። ከቲያትር ወጥተው ራት ላይ ተቀምጠው ሁሉ ኤድዋርድ ንፁልል ብሎ፣ አይኑን ከፀ ላይ መንቀል አትችት ነበር ያመሸው። አባቱን ምን ያህል እንደተናበትና እንደተመቀኘው፣ ምን ያህል እንደጠላው ተውሰ አለው። ዚምን የመሰለች ቁንጅ፣ ያን የለተተ የሽማግሌ ቀጻ ስታትፍ ምን ይሰማት?

መቼም ቢሆን እሱን ልትወድ አትችልም ሲል አሰበ አርምስቱድ። አባቱ እፀን በእድሜ ዕሰት ያህል ሳይበልጣት አይተርም። እጁጉም የተወሳሰበ ዘንግ ነበር የሚመስለው። የሱኑቱ መታወቂያ ንያሉ፣ ሀብቱና ዝናው ብቻ ነው።

አርምስቱድ ወደሶፋው ሄዶ ተዝናንቶ ተተመጠ። ባራም እንደያኔው አይኑን ከፀ ላይ ሊነትል አልቻሰም። የውስጥ ልብሷ የሰውነቷን ቅርፅ ያሳያል፣ የአርምስቱድ አይኖች ወደ ጡኖጅ ተጓዙ። ይበልጥ በሰሎ፣ ጎምርቶ ተስታሽ ሆኗል። ዘለግ ያለው ቁመቷ፣ በትክሻዋ በኩል ዘንፈል ካለው የውስጥ ልብሷ ተርፎ የሚታየው ጡቷ ምናብ ይሰርታሉ። አርምስቱድ ስለአባቱ አሰበ። ‹‹ንለሙን የቀጨ ውሻ ነበር፣ የተቀማጠለ ውሻ ነበር፣ ውሻ ነበርኒ ነበር። አም ነበር›› አለ በቀኖተኛ ልቡ።

የዚምን እድሜ ሲገምት ሞከረ። አባቱ መጀመሪያ አይኑን የጣለባት ዳንሰኛ ሆና ነበር። ደጋግሞ ሲንበሻት ከቆየ በኋላ ባንድ የቅንጦት አፓርታማ አስቀመጣት። ያ የሆነው ከአስራ ስምንት ዓመታት በፊት ነበር። ያኔ ዚም የሃያ አንድ፣ አባቱ የሰድሳ ሶስት፣ እሱ ራሱ ደግሞ የሰሳሳ ስምንት ዓመት እድሜ ነበራቸው። አሁን እፀ ሰሳሳ ዘጠኝ፣ እሱ አምሳ ስድስት፣ አባት. . . አባትማ ተሰናብቷል። እፀ ወጣት፣ ከሱ በብዙ እድሜ የምታንስ ሰው ነች። ግን እሱም ከአባቱ በብዙ ዕድሜ ያንሳል።

ከፊት ሰፊቱ ቅማ ውስኪውን ከውሃ ጋር አተረበችለት። ‹‹ይኸው››

አንድ ጊዜ ደህና እድርጎ ተጎነጨለትና ‹‹ተብር አልደረስሽም?›› ሲል ጠየቃት፣ ‹‹አላየሁሽም።››

‹‹ሚዲኤን የሚወድልኝ አልመሰለኝም። እንዴት ነበር?››

ከመጠጡ እንደገና ሳበና ‹‹የተሰከፈ ውሻ ነበር፣ አባቱ›› አለ፣

‹‹አስተዋምኩሽ?››

ከትከሻዋ ነቅነት አለች። ‹‹በጭራሽ። ላንተ ምንጊዜም ጥሩ ሰው አልነበረም።››

ከአርምስቱድ ጥቂት ራት ብላ ሶፋው ላይ ተኮመጠችና ለጠጥ ብላ ትራሱን ተደግፋ እግሯን ሶፋው ላይ አወጣች።

አርምስቱድ እይኑን እንደተከለባት ነው። ‹‹ላንችስ ጥሩ ሰው ነበር?›› አላት።

‹‹ምን አውቅለታለሁ። እም፣ መጀመሪያ ደህና ነበር። ነገር ያመጣው በኋላ ነው፣›› አለችው። አዎ ጊዜ እየረዘመ በመጣ ቁጥር ሚች ኪምን እንዲያውም ከገዛላት አጋርታማ እንዳትወጣ ከልክሏት ነበር። በኋላማ አርጅና ሲጫነው እሷን መጠየትም አቆመ። አርምስቱድ ራሱ እንደሚያስታውሰው አባቱ ኪምን የሚጠይቃት አልፎ አልፎ ነበር። ኪምም ብትሆን ብቻዋን መውጣት ስለምትፈራና ከጓደኞቿ ለረጅም ጊዜ የተለያዩች በመሆኗ ወደ መጠየ ላታዘነብል እንዳልተረች አርምስቱድ አሰበ።

የመለኪያዋን ውስኪ ሰትጨልጥ አያትና ‹‹ኪም›› አላት፣ ‹‹ከአባቱ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ከተገናኛችሁ ስንት ጊዜ ሆናችሁ?››

ልታስብ ሞከረች። ‹‹ወደ ሰባትና ስምንት ወር ላይሆንን አይተርም። እዚህ አካባቢ, ከመጣማ ዓመታት ተቆጥረዋል።››

‹‹ያን ያህል ጊዜ አይተሽው አታውቂም?››

‹‹በጭራሽ። በሳምንት አንዴ ይደውላል። በታ!››

የውስኪውን የመጨረሻ ጠብታ ሞጠችና ‹‹ተጨማሪ ጥያቄ?›› አለች ፈገግ ብላ።

አርምስቱድ አቅማማ፣ ‹‹እም፣ አብራችሁ ከተኛችሁ ስንት ጊዜ ሆናችሁ?››

ዓይኖቿን አርምስቱድ አይኖች ላይ ተከለች።

‹‹ያደረጉችሁ ማለትህ ነው ኤድዋርድ? እኔ እንጃ. . . ረዘም ያለ ጊዜ

ነው። ስድስትና ስባት ዓመት ሳያልፍ አይተርም። ለዚያውም ተደረገ ለማለት አይቻልም። ወትሮም ያው መልፈስፈስ፣ መንፈራፈር ብቻ ነው። አባትህ ሽምግልና ስሚቱን የዘጋው ሰው ነበር።›› ዝም ብላ ቆየችና ‹‹ስላባትህ ይህንን መናገር አልነበረብኝም›› አለችው።

‹‹ታዲያ ስሚትሽን እንዴት ታረክ ነበር?››

‹‹እርጅና ብቻኮ አይደለም ስሚት የሚዘጋው። መጠጥም ፍላጎትን ያጸፍናል።››

‹‹ይገርማል›› አለ አርምስቱድ።

መለኪያውን ጠረጴዛው ላይ አስተመጠችና እግሯን ከሶፋው አወረደች። በዚህ ጊዜ ነበር ሞድ መሉ ለመሉ ተጋልጦ ተግልጦ የታየው። ጡቷንም በድንገተኛ መሉ ለመሉ ተመለከተውና ደረት ምራቁን ዋጠ።

ቆመች። የራሱ ሞን ቱጥር ፈታ አያለ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው። አይኖቹ ከፈት ለፈቱ የቆመውን ማራኪ ትርዕ ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደላይ በጉጉት ታኙ። ‹‹ለወደፊቱ እንዴት ልትጥሪ መስነሻል ኪም? ገና ወጣት፣ ሲበዛ ቆንጆ ነሽ።››

‹‹ለጊዜው አንድ መለኪያ ልጨምር መሰኛለሁ›› አለችውና ፈገግ አለች። ግን አልተነታነቀችም። ‹‹ቆንጆ መሰዬ ታየሁህ? ቁንጅናየ ዛሬ ነው የታየህ?›› ስትል ወረፈችው።

ፈጠን ብሎ ቆመ። ‹‹ስሚ ኪም፣ ስወድሽ ኖሬአለሁ። እወድሻለሁ። ወትሮም እወድሽ ነበር።›› ፈቱ ትዋም አለ፣ እሷም እንደቆመች ተረች። በነ ንዱ አድርጎ ደባበሳት። ጸሰሳው ግን በችኮላ ከመሆኑ የተነሳ የፍትር አሟሟት ሳይሆን የወሪሻ አስተሻሸት አይነት ነበር። በተከፈተው አሴ ውስጥ ከንፈሩን መሉ ለመሉ አሰገባና ምላጋን እስኪያገኘው ድረስ ሞምት አደረጋት።

በብዙ ትግል ከንፈሯን ከከንፈሩ አላቃ ‹‹ኤድዋርድ›› አለች ትንፋሽ እንዳጠራት፣ ‹‹የምታደርገውን አውቀኸዋል?››

‹‹አውቀዋለሁ። ካየሁሽ ጀምሮ ስመኘው የነበረውን ነው የማደርገው።››

ሙሉ ለሙሉ ፈገግ አለች። «አዎ» ከንዶጅ በዝግታ በወገቡ ተጠመጠመ፣ የሷም ከንፈሮች በተራቸው አፉ ውስጥ ተዘርምጠው ምላሱን አገኙ።

ሙቀቫሽቱ እየጠበቀ፣ ከንፈር በከንፈር እየተጨመቀ፣ ግላ በግላ እየሞቀ ሲሄድ አድዋርድ አንድ እጁን ዝቅ አድርጎ የውስጥ ልብሷን ማውለቅ ያዘ።

ጣቶቹ እርቃኑን ሰውነት ነኩ። ያን ሰውነት እየዳበሰ ከትከሻ ወደጡት፣ ወደእምብርትና ከዚያም በታች ወረዱ። በሁሉም ነገር ላይ እንደተባይ ተሯሯጠበት። ሁሉንም ነገር ተመተመት።

እሱን ጆሮው ላይ ለግታ የፍቅር ሲታ አቃሰተችለት። የሷም እጆች ከላይ ወደታች ወርደው ተታራኒውን ገላ ቡሎን እንደሚፈታ ሚካኒክ አሟሟሩት።

«እ. . እኔም ከድሮ ጀምሬ. . . ስፈልግህ ነበርኽ» አለችው በተቆራረጠ እንደበት።

አፈፍ አድርጎ ታተራት፣ ተሸከማት። ወደተንጣለለው መኝታ ቤት እንዲት እንደደረሰ እግዜር ያወቀው። ደብዘዝ ያለው የራስጌ መብራት ሁኔታውን ያመቻቸው ይመስላል። አስተኛት። ኮቱን፣ ክራባቱን፣ ሸሚዙንና የተረፈውን ሁሉ አውልቆ እርቃኑን ሲተር ደቂቃ አልፈጀበትም። በረጅሙ መስታወት ሰውነቱን ሙሉ ለሙሉ ተመለከተው። እድሜው ሃምሳ ስድስት ቢሆንም አይኖቹ ያበራሉ፣ ቆዳው ጥብቅ ነው።

ውፍረት ስላላገረጀፈው ጠንካራ መጠምሻ ነው። ቀጥሎ ከምን በመስታወቱ ከጀርባው ተንጋላ አያት። በአልጋው ጠርዝ ላይ ወጣትነቷን፣ የቆዳዋን ተለምጌ፣ ተጥ ያሉትን ሙሉ ጡቶቿንና በትንሹ እጥረት እየተነሳ የሚወድተውን ባዘር ሆዷን ምራቁን እየዋጠ ተመለከተው።

ወደሷ የሚያደርገውን አረማመድ እያየች ተንጋላ ትጠብቀዋለች። «ዳግሰህ ነበራ የምትጠብቀኝ?» አለችው ሙሉ ለሙሉ ሊማሊም መስላ።

«ለረጅም ጊዜ» አላትና አልጋው ላይ በቁመ ወደተበት። ጡቷን በተሰታ እየደባበሰ ላይዋ ላይ ጉብ አለ። «ሞቼ ከርሜ» አይነት ነበር። . .

ከብዙ ቆይታ በኋላ በጀርባው ተንጋለለና ያደረገው ሁሉ ምን ያህል ያሰደስት እንደነበር አስታወሰው። እግሮቹ እንደበፊቱ ቁጥር ብለው ተንቀጠቀጡበት። አፍላ ጎረምሳነቱ ካከተመ ጀምሮ እንዲህ አድርጎት አያውቅም። አውንም ገና ወጣት ነኝ ሲል አሰበ።

የሞቱ ይመስል ሁለቱም ጎን ለጎን ለረጅም ጊዜ ተኝተው ቆዩ።

እያናወጠች፣ «ከእንግዲህ ብቻየን አትተወኝም አይደል?» ስትል ጠየቀችው።

ጉንጯን ጨምቂ አደረገና፣ «በፍፁም» አላት። እንደተኛ አእምሮውን የሞት ልኩ አያምሰለሰለ ረጅም ጊዜ ቆዩ። በሕይወቱ ሁለቱን የሚፈልጋቸውን ነገሮች ያጣ፣ እድለ-ጎደሎ መሆኑን እያማረረ ለዶክተሩ ነግሮታል። ሁለቱ ነገሮች ሪኮርድ ጋዜጣና ኪም ነበሩ። አሁን ኪም በጀ ገብታ የሰ ሆናለች። የሚቀረው ሪኮርድ ነው። ሪኮርድም ቢሆን ለጊዜው የሰ ነው። ነገ ጧት ወደ አሳታሚው ቢሮ ሄዶ ከሚድግሳው ፎቶዎቹን ነቃቅሎ ሊሎቹንም የአባቱን ቅርሶች ሁሉ ያጠፋል። ለምንም ያህል ጊዜ ይሁን የራሱ፣ የግሉ ነው። እና አሁን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ኪምን ማግኘቱን ሲያስብ «የማይቻል ነገር የለም!» አለ በልቡ።

2

በፀሐያማው ማለዳ ክቺካጎ ዋሽንግተን ብሔራዊ አይሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰች ቪክቶሪያ ዊስተን በቀጥታ ወደ አባቷ ቤት አመራች። አባቷ ዕማ ዊስተን ከስራ ለምሳ ወደቤታቸው ተመልሰው ይጠብቋት ነበር።

ዘበኛው ጉንፉኒ ላይ በመሳም ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ ሻንጣዋን ከትከሻዋ ተቀብሎ ወደ አባቷ ወሰዳት። ቪክቶሪያ አባቷ ላይ ተጠመጠመችባቸው። ከሁለ አብልጣ ከምትወዳቸው አባቷ ጋር ከተገናኘች ወራት ተቆጥረዋል።

ተታቅፈው ከቆዩ በኋላ እንደተላቀቁ አባት ልጃቸውን በሚመረመር አስተያየት አተኩረው ተመለከቷት። ‹‹በውነት እንዴት ተሰማምቶሻል?›› አሏት፡ ‹‹የሃያ አራት ዓመት ወጣት አትመስይምኮ።››

‹‹ምን? ሃያ አራት? ሃያ አምስቱን ደፍኜ ሃያ ስድስተኛዬን ይጦለሁኮ። ያው ለሰላሳ ምን ቀረው?››

እንደግና አስተዋሏት። እጅግ የተዋበች ልጅ ስላለቻቸው ኩራት ተሰማቸው። ደስተኛ ከመሆኗም በላይ አለባበሷ የተለዬ ውበት ሰጥቷታል።

እጅዋን ይዘው ወደ ሳሎን እየወሰዷት ‹‹የቺካጎውን ሂልዴ ጆንሰን ሽልማት በማሸነፍሽ ምን ያህል እንደተደሰትኩ ልነግርሽ አልችልም›› አሏት፡ ‹‹በጃዜጠኝነት መሥያ ታላቅ ውድድር ነው። እንኳን ደስ ያለሽ።››

‹‹አመሰግናሁ፡ አባዬ።››

‹‹ስላንቺ አሸናፊነት የወጣውን ጽሁፍ ቢያንስ ሶስት ጊዜ ሳላነበው

አልተረዙም። በርግጥም አሸናፊነት ይጣፍጣል። ለመሆኑ እናትሽስ? ደስተኛ ናት?››

የሰላሳ ዓመቷ የኸማ ዊስተን ባለቤት ደስተኛ ሰው አልነበረችም። አንድ ልጃቸው በመሆኗ ባልና ሚስት በትዳር አብረው እንዲቆዩ ለማድረግ ያስቻለች ቪክቶሪያ ነበረች። ግን ሊዘልቅ አልቻለም። ከስድስት ዓመታት በፊት ፍቺ ፈጽመው፣ ሚስት የላፉ ሁለት ዓመት አካባቢ አንድ ኑኃዬ አግብታ ትኖራለች።

‹‹እማዬ?›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹ለሁለት ሳምንት እንዴ ብቻ ነው የምንግናኘው። እንተስ አባዬ? ስራ እንዴት ነው?››

ኸማ ዊስተን የአሚሪካው ፕሬዝዳንት የኮሪስ ፀሐፊ ሆነው ከተሾሙ ዓመት ሆኗቸዋል። ከዚያ ጊዜ ጀምረው ነው የቪክቶው ጅርናል ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅነታቸውን ለቀው ተመማድነታቸውን በሞሽንግተን ያደረጉት። ‹‹ሥራዬን አወደዋለሁ። ከታላላት ሰዎች ጋር መዋልና በቴሌቪዥን መቅረብ ቀላል እድል አይደለም። በይ አሁን ለአንድ ሰዓት ያህል ልለይሽ ነው።››

ቪክቶሪያ አባቷን ከላይ እስከታች ያስተዋለቻቸው በዚህ ጊዜ ነበር። ‹‹አሃ. . .ያቲኒስ ቁምላ ነው ወይ የለበስከው? ቲኒስ ለመጫወትም ጊዜ አለህ ማለት ነው? ቲኒስ ስትጫወት ትዝ የሚለኝ ልጅ አያለሁ ነበር። ግን. . .››

‹‹ቪክቶሪያ፣ ፕሬዝዳንቱ እሁድ-እሁድ ቲኒስ መጫወት ይወዳል። በተለይ ከኔ ጋር መጫወት ደስ ይለዋል። በቀላሉ ያሸንፈኛላ. . .››

‹‹በል እስክትመለስ እኔም ግላዬን እታጠባለሁ። ከዚያም ምሳችንን እሰራለሁ።›› አባት ከዜት ሊወጡ በሩ አካባቢ ሲደርሱ መለስ አሉና ‹‹ለመሆኑ በስራ ቀን እንዴት ልትመጭ ቻልሽ?›› ሲሉ ልጃቸውን ይጠይቃሉ።

‹‹ካለፈው አርብ ጀምሮ ስራ ትቻለሁ። እንዲያውም አመሳጠኔ ስለዚሁ ጉዳይ ላኒጣርሀ ነው።››

ራሳቸውን ከፍ ዝቅ አደረጉ ‹‹መልካም፣ በይ ምሳዬን ስሪልኝና እንጫወተዋለን። ከአንድ ሰዓት በኋላ እንገናኝ።››

አባቷ ከወጡ በኋላ ቪክቶሪያ ገላዋን በፍጥነት ታጥባ ልብሷን ለዋወጠችና ምሳ ታበስል ጀመር። ከዘጠና ደቂቃዎች በኋላም አባትና ልጅ ምሳ ላይ ተሰምጠዋል።

‹‹እሺ ቪኪ፣ ሲቲዝን ጋዜጣን ተውኩት ነው የምትይኝ. . . እና ከኔ ጋር ልትነጋገሪ ትፈልጊያለሽ። ምንድን ነበር ነጥቡ?››

‹‹የኔን የወደፊት እኗኗር የሚመለከት ነው።››

‹‹ሎሚይ።››

‹‹አባዬ፣ በዚያ ሳምንታዊ ጋዜጣ አንድ ዓመት መሉ አገልግያለሁ። በጋዜጣው ላይ ምርጥ ጥናታዊ ጽሁፍ አትሬብ. ነበርኩ። ግን ስራው ድግግሞሽ፣ ለውጥ የለሽ ሆነብኝ። እኔ ራሴን የሚለውጥ፣ እውቀቴን የሚያዳብር ስራ ነው የምፈልገው። የተሻለ ስራ ያስፈልገኛል።››

አባቷ አንድ ነገር ይናገራሉ ብላ የራሷን ንግግር ቆም አደረገች። ዝም ማለታቸውን ስትገነዘብ ግን ‹‹ምናልባትም ሌላ ምክንያት ይኖረኝ ይሆናል›› አለች።

‹‹ንገሪኝ?››

‹‹አንደኛው ምክንያት የሙያ ግዴታ ሲሆን ሌላው ደግሞ የግል ምክንያት ነው። በርግጥ ትድሚያ የምሰጠው ለሙያ ግዴታዬ ነው። ሁልጊዜ የምሰራው በሴቶች ዓምድ ላይ ነው። ሰልችቶኛል። በዜና አምድ ላይ መስራት አፈልጋለሁ። አባዬ፣ አሁን የተሻለ ነገር ለመስራት ችሎታውም፣ ልምዱም ያስገድደኛል።››

‹‹ልክ ነሽ›› አሉና አባት ዝም አሉ፣ ‹‹ለውጥ ያስፈልግሻል።››

‹‹ቺካጎም በትቶኛል። ኒውዮርክ መስራት አለብኝ።››

ዊስተን ምግባቸውን እያኘኩ አሰላሰሉ። ከዚያም እፋቸውን ጠራረጉና ‹‹እዚያ ትንሽ መጨናነቅ ይታያል፣ ቪኪ። እስኪ ትንሽ አስቢበት። በመጽሔት ዝግጅት ክፍል፣ ወይም በመጽሐፍ አሳታሚ ድርጅት፣ ወይም በቴሌቪዥን ብትሰሪስ? የማውቃቸውን ሰዎች አፈልግልሻለሁ።››

ቪክቶሪያ ለጠጥ ብላ ወንበሩን ተደገፈች። ‹‹አባዬ፣ አንተን መተካት፣ የጋዜጣ አዘጋጅ መሆን ብቻ ነው የምፈልገው። ያንተ ሕይወት ሁልጊዜ አንዳስተናኝ ነው።››

‹‹ግን በደመወዝሽ አትረኪም።››

‹‹ደመወዝ ገደል ይግባ። ደጀሰላም ውስጥ ወድቄ በቀን አንድ ቲማቲም እየበላሁ የምወደውን ስራ መስራት አመርጣለሁ። ከእውቅ ጋዜጠኞች አንዷ መሆን አለብኝ።››

ኼግ ዊስተንም ለጠጥ ብለው ወንበራቸውን ተደገፉና ‹‹መልካም . . .›› አሉ።

‹‹መልካም ምን?››

‹‹ኒውዮርክ›› አሉ፣ ‹‹ከባድ ከተማ ነው። እሰኪ ላስብበት።››

ብድግ ብለው ኩቲኒስ ጃኪታቸው ኪስ ውስጥ ፒፖ አወጡና ትምባሆ ጨምረውበት አቀጣጥለው እያጨሱ ተመልሰው ተቀመጡ። ‹‹ኒውዮርክ የማውቃቸውን ጠቃሚ ሰዎች እያሰብኩ ነው›› አሉ፣ ‹‹አዝራ አርምስቲድ ትዝ አለኝ። ታስታውሽዋለሽ?››

‹‹አዝራ ጂ አርምስቲድ ማለት ‹ገዘኑ› የሚሉት? በቺካጎው ጋዜጣው ላይ ሰርተህ የለም እንዴ። በዚህ ሳምንት ሞተ ሲሉ የሰማሁ መሰለኝ።››

‹‹ልክ ነሽ። ያ ማለት ኒውዮርክ ሪኮርድ ምናልባት በኤድዋርድ አርምስቲድ ስር ሳይሆን አይቀርም። አዝራ ከኤድዋርድ ሊላ ወራሽ የለውም ነበር።››

‹‹ትዝ ይለኛል አባዬ። አንዳንድ ቀን ቤት አምጥተህ ራት ትጋብዘው ነበር። እንዲያውም እንደራስህ ልጅ ትጨነቅለት እንደነበር ትዝ ይለኛል።››

‹‹ጥሩ ሰው ነበር። ያን ያህል እንኳ በእድሜ አልበልጠውም። ግን ከአባቱ ጋር ስለማይጣጣሙ ብዙ ጊዜ እኔን ይቀርበኝ ነበር። በርግጥ በትርዒቱ ተጣናንቶን አናውቅም፣ ግን በቀላሉ የሚረሳኝ አይመስለኝም. . .››

ቪክቶሪያ እንደማጨብጨብ እየታጣች ‹‹አ አባዬ ከሱ የተሻለ

አላገኝም። ኒውዮርክ ሪከርድ›› ከማለቷ አባቷ አቋረጧት።

‹‹ተስ በይ›› አሉ አባት ኩተተመጠበት እየተነሱ። ‹‹በዓዳናው ላይ አንዳንድ ጋራጣዎች አይጠፉም። ነገሩ የሚሳካው ኤድዋርድ አርምስቱድ እንዳሰብከው ጋዜጣውን የወረሰ እንደሆነ፣ እሱም ደግሞ አዲስ ሰራተኛ ፈላጊ ከሆነ፣ አንችም የሚጠይቀውን መስፈርት ካሟላሽ ነው። ለማንኛውም እስኪ እንሞክራለን።››

ዊስተን ሳሎን ሂደው ወደ ስልኩ ሲያመሩ ቪክቶሪያ የምግብ ሳህኑን ታነሳሳ ጀመር። አባት በረጅም ርቀት ጥሪ ወደ ኒውዮርክ ሪከርድ ደወሉ።

‹‹ሪከርድ ነው? አባከሃ ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቱድን?. . . ኸግ ዊስተን ከሞሽንግተን ዲሲ እንደምፈልገው ይንገሩልኝ. . . እሽ አጠብቃለሁ።››

ስልኩ ከተተመጠበት ሲነሳ ለዊስተን ታወቃቸው። መኒጋሪያውን ይበልጥ ወደ ጆሮአቸው አስጠጉ። ‹‹አም ኸግ ዊስተን ነኝ›› አሉና ያዳምጡ ጀመር። ‹‹ሃሪ፣ ሃሪ ዴትዝ ነህ? ስብአት ለአብ፣ እንዴት ያለ አጋጣሚ ነው ባክህ?. . . እንደምን አለህ?. . . በጣም. . . በጣም ደህና ነኝ። አም ልክ ነህ. . . ኤድዋርድን ፈልጌው ነበር። ላንድ ጉዳይ. . . ምን አልክኝ? እየቀረበ ነው?. . . በጣም ጥሩ።››

ይህ ሁሉ ሲሆን ቪክቶሪያ ከአባቷ ጎን ቆማ ውጤቱን ለማወቅ ልቧ ነጠር ነጠር እያለ ታዳምጥ ነበር። አባቷ የአርምስቱድን መቅረብ ሲያረጋግጡ በፈገግታ ጠቀሰ አደረጓት።

‹‹ሂሎ ኤድዋርድ?. . . እንደምነህ?. . . በጣም ደስ ብሎኛል። ያም ሆነ ይህ ሐዘኔን እገልፃለሁ። ሽማግሌው ረጅም እድሜ ኖረዋል። አንተም ረጅም ጉጉት አሳልፈሃል።. . እ . . . ኤድዋርድ አሁን ምን እንደሚሰማህ ይታውቀኛል። መቼም ጋዜጠኞን ሪከርድን ጨምሮ በቱጥርህ እንዳዋልህ አርግጠኛ ነኝ።›› ንግግራቸውን አቁመው አዳመጡ። ‹‹ጥሩ፣ ጥሩ፣ ጥሩ። ደግሞም በወቅቱ ጋዜጣው ብዙ መሻሻሎች ያስፈልጉታል። የላቀ ስራ እንደምትሰራ እምነቱ ነው። ይህን ከኔ በላይ የሚያውቅ ማንም የለም።››

አቶሙና አጻመጡ። «አመሰግናለሁ ኤድዋርድ በጣም አደንቅለሁ። ግን እኔ አሰከምንጊዜውም ከጋዜጣ ዓለም ተለይቻለሁ። ከሞይት ጎልስ የተሻለ ምን ዐታ ይገኝ ብለህ?» ክት ብለው ሳቁ። «ብርግጥ አሁን የፈለግሁህ እንኳ ደህንነትህን ለማወት ሳይሆን የራስህን ሰራተኞች እያዋቀርህ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።» መኒጋሪያውን ይበልጥ ከጆሮአቸው ጋር አጣበቁት። «በጣም ጥሩ! ያ ማለት እኔ ከምፈልገው ከሌላ ነገር ጋር ተጣጣመ ማለት ነው። አሮጌውን ዊስተን ለመትጠር ከፈተድህ ከአሮጌው የምትበልጥ አዲስ ዊስተን ለስራ ብታመልክት ምን ትላታለህ?»

«አ አሳጌ» አለች ቨክቶሪያ ልትሥህ እየታጣት። «እንደዚያ እንኳ አትበል።»

አባት ቨክቶሪያን በግራ እጃቸው ግፍተር አደረጉና «ማለቴ» አሉ፣ «ልጄን ቨኒን ታስታውሳታለህ?. . . በጣም ጥሩ፣ ይኸውልህ አሁን ሙሉ ሰው ሆናለች። ያውም የታወቀች ዜና ዘጋቢ። ቺካጎ አካባቢ ሶስት ዓመት ሰርታለች። ሁለት ዓመትማ በስሊታዊ ጋዜጣ ታዋቂ ሪፖርተር ነበረች። አሁን ይበልጥ ከበድ ያለ ሥራ ትፈልጋለች። ባለፈው ሳምንት ስራዋን ትታ እዚህ መጥታ ከኔ ጋር ነች። እንኮን አስታወስኩና ጊዜ አግኝተህ እንድታነጋግራት. . .» ንግግራቸውን አቋርጠው ሲያዳምጡ ቆዩና በሰፋት ፈገግ አሉ። «እጅግ በጣም ግሩም ኤድዋርድ፣ በጣም ግሩም። ቅር እንደማትሰኝ አርግጠኛ ነኝ። ምን? ቨክቶሪያ. . . ቨክቶሪያ ዊስተን. . . . መልካም በጣም ግሩም። ለእኑም መልካም እድል ኤድዋርድ። የተታና እድል ይገባሃል። እስኪ ባክህ ወደ ዋሽንግተን ብት ስትል አስቀድመህ ደውልልኝና እንጠያየት ባክህ። በፊ አልሃለሁ። ጥሩ፣ ለቨክቶሪያ እነግራለሁ።»

ሰልኩን ዘግተው ሳት እያሉ ወደልጃቸው ዞር አሉ። «አርምስቱድ የሪክርድን ሰራተኞች ሊበውዝ ይፈልጋል። ሳይተበልሽ አልቀሪም። ነገ በኒውዮርክ ሪክርድ ቢሮው በስምንት ሰዓት ተጠር ይሀልሻል።»

* * *

ከአሥራ ስድስት ሮቱ የአርምስቱድ ሕንጻ በተለይ ትእዛቸኖ

መመሪያዎች የሚተላለፉበት የግንቡ እምብርት በስድስተኛው ፎቅ ላይ ይገኛል። ከዚህ ፎቅ አብዛኛው ለኒውዮርክ ሪኮርድ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተሰጠ ሲሆን የተቀረው የአሳታሚው ዋና ቢሮ፣ የሱ የግል ፀሐፊና እንግዳ ተቀባይ ቢሮ፣ የስብሰባና የኤለክትሮኒክስ መገናኛ ክፍል፣ የማስታወቂያ ዲፈክተሩና የረዳቶቹ ሁለት ቢሮዎችና የምክትል አዘጋጅች ጽሕፈት ቤቶችን ያጠቃልላል።

በእዝራ አርምስቱድ ተብር ሳልስት የሕንፃውና የቢሮው ጊዜያዊ ወራሽ መጠነኛ ለውጦችን አድርጎ ነበር። አድዋርድ አርምስቱድ መጀመሪያ ያዳረገው አርጂደን የአባቱን የግል ፀሐፊና እንግዳ ተቀባይ ጥሩ ጉርሻ ሰጥቶ ከስራ ካሰናበታት በኋላ ኢስቲል ራቭኪን በተባለች የሰላሳ ዓመት ወጣት ቆንጆ መተካት ነበር።

ኢስቲል ራቭኪን በተለይ አርምስቱድ በልዩ ፕሮጄክቶች ስራ ላይ ላለ ለአምስት ዓመታት በታማኝነት አገልግላው ውለታ ጥላበታለች። ሃሪ ዴትዝና ብሩስ ሃርምስተንን ከአራተኛ ፎቅ አውጥቶ ከሱ ቢሮ አጠገብ በማስታወቂያ ዲፈክተሩ ቢሮ አደረጋቸው።

አሁን፣ በአባቱ ሳልስት ከሰዓት በኋላ በአነስተኛ የምሳ ዕቃ የተረበሰችን ምሳ በተለይ በኪም ነሰቢት ፊት ማራኪ እንዲሆን የመረጠውን ምግብ በልቶ ከጨረሰ በኋላ የግል ፀሐፊውን ጠርቶ ሳሁን አሰነሳ።

«እየተዋበ ነው ሚስተር አርምስቱድ» አለችው ኢስቲል ቢሮውን ተገላምጣ ከተመለከተች በኋላ።

አርምስቱድ በአምንታ ራሱን ከፍ ዝቅ አድርጎ «አዎ፣ መልክ እየያዘ ነው፡» አላት።

ፀሐፊው እንደወጣች አርምስቱድ የሚያምረውን ቢሮ ሲቃኘው እርካታ ተሰማው። የአባቱ ማስታወሻ የሆኑት የመጨረሻ ምልክቶች ተወግደዋል። በተለይ የሚያሳዝን ጊዛጊዎችን ባለፉት ሁለት ቀናት ከኢስቲል ጋር ሆኖ ኑታትሷቸዋል። አባቱ ያወዷቸው የነበሩት ባለመስታወት ፎቶግራፎችና ስዕሎች ተሳቡ። ተጥሎ አባቱ ራሳቸው «ገሀነ» ተብለው በሚታወቁበት

የትጽል ስማቸው አይነት እነሳስ ከአምስት የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች፣ ከሙዳ አገር ልዑላውያን ቤተሰቦች፣ ከታወቁ የቤዝቦል ክለብ ተጫዋቾች፣ ከሲኒማና ከቴሌቪዥን እውቅ ሰዎች ጋር የተነሷቸው ፎቶዎች ወረዱ። አንድ ፎቶ ብቻ እንዳለ እንዲቆይ ተፈቀደለት። እሱ ራሱ ከእናቱ ጋር በአስራ አራት ዓመት እድሜው የተነሳው ፎቶ። ባዶ የሆነውን ግድግዳ በአውሮፓ አገሮች ጉብኝት ሲያደርግ የሰበሰባቸውን ስዕሎች ሰቀለበት።

አርምስቱድ ከፍሉን እንደገና ተግሳፀው ቃኘ። በሰፋፊዎች መስኮቶች የሚታዩት አትክልት ልምላሜ፣ የአበቦቹ ተለምና ከማሞቂያው ትይዩ ያለው ባለ ሰባ ሁለት ኢንች ዘመናዊ ቴሌቪዥን ይህ ይውጣላችሁ አይባሉም። ከሰፈው ጠረጴዛ ፊት ሰፊት የተሰደሩት የእንግዳ ወንበሮች አዳዲሶች ናቸው። ዋናው ጠረጴዛ ራሱ ከቶኪዮ በተገዙ የገሆን ጥርስ ጌጣጌጦች፣ ከጋሪስ በመጡ ትናንሽ የወታደራዊ ቅርፃ ቅርጽ ስብስቦች፣ ከትዱስ አንድሩስ በተገኙ የነሐስ ቅርሶችና በማሳዳ ባለመስመር ማሰቀመጫ አሸብርቋል።

የቢሮው ሽብርቅ እንደተጠናቀቀ አርምስቱድ ጠረጴዛው ላይ ያለውን የቀን መቁጠሪያ ሲመለከት ነዘረው። በጊዜ ፍጥነት ላይ ድንጥ እንዲሆን የአባቱ ትዛዜ አሰገድዶታል። በገሆን ጥርስ ተለም ወደተሰራው የኮምፒዩተር ስልክ ሄደና የሃሪ ዴትዝን የስልክ ቁጥሮች ደወለ።

«ሃሪ፣ ለስብሰባው ዝግጁ ነኝ። ብሩስን ሞምር ይዘህ ና።»

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሃሪ ዴትዝ ጥቂት አቃፊዎችን እንደያዘ ብሩስ ሃርምስተንን አስከትሎ ገባ። ሁለቱም በእንግዳ መስተናገጃ ወንበሮች ላይ ተቀመጡ። አርምስቱድ ከወሐፊው ሌላ እምነት የሚጥልባቸው ሁለት ሰዎች ሲመለከት በፊስ የመሠማመን ስሜት መንፈሱን አረጋጋለት። በርግጥ ስልት በመቀዬስና ሃሳብ በማመንጨት ቅልጥፍና ረገድ ሁለቱም ቢሆኑ ከአርምስቱድ ይስተካከላሉ ተብሎ አይታመንም። ነገር ግን ሁለቱም የአርምስቱድን አእምሮ ማንበብ ብቻ ሳይሆን የጀመረውን አረፍተ ነገር መጨረሻ ማወቅ የሚችሉ ሰዎች ናቸው። ኃይለኛ፣ ደፋርና ከሁሉም በላይ እንደ አድዋርድ ሚችን ኢዝራ አርምስቱድን ይጠሉ የነበሩ ሰዎች ናቸው።

‹‹የመጀመሪያ ጉዳይ መጀመሪያ›› አለ አርምስቱድ ለዴትዝ፣ ‹‹የኒውዮርክ ታይምስን አለታዊ ስርጭት አጣራህ?››

ሃሪ ዴትዝ ጠረጴዛው ላይ ክፍት ቦታ ፈልጎ አቃፊዎቹን አስተመጠና የላይኛውን አቃፊ እንስቶ ከፈተው። ‹‹የሥርጭት ክፍል አዲት ቢሮ የላከ አራት ወር ባቀረበው ሪፖርት መሰረት የታይምስ ዕለታዊ ስርጭት 873,255 ነበር። ማለት ቋሚ ደምበኞችን ጨምሮ።››

‹‹የሪኮርድስ?››

‹‹በግምት 533,000።››

አርምስቱድ ሽምቅቅ አለ። ‹‹ያ ማለት ታይምስን ለመበለጥ 350,000 ተጨማሪ አንባቢያን ማፍራት አለብን።››

‹‹እንደዚያ ነው አለቃዬ›› አለ ሃሪ ዴትዝ።

‹‹ውሻ!››

የአርምስቱድ ስድብ በአባቱ ላይ እንደሆነ የገባቸው ዴትዝና ሃርምስተን በመሰማማት አይነት ራሳቸውን ከፍ ዝቅ አደረጉ።

አርምስቱድ ወደኋላው ለጠጥ ብሎ ከራባቱን አላላና ‹‹መቸስ ምን ይደረግ። ጋዜጣውን የግላችን ለማድረግ ያለን አማራጭ የበለጠ መስራት ነው። የገንጅት ሰራተኞችንና የሽግሽግ ሰሌዳውን ሪኮርድ ይዘሃል?››

ሃሪ ዴትዝ ከአቃፊዎቹ መካከል አንዱን መረጠና ‹‹ይኸው›› አለ።

‹‹ጥሩ፣ ወደነሱ በኋላ እመለሳለሁ። አሁን ከሁለታችሁ ልጀምር። በመጀመሪያ ደረጃ ሁለታችሁም ተጠሪነታችሁ በቀጥታ ለኔ ብቻ ይሆናል። አጠቃላይ ትእዛዝን የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ከናንተ ጋር የምነጋገርበት ነጥብ ሁሉ የሚስጥሮች ሚስጥር ሆኖ መጠበቅ ይኖርበታል። ሃሪ! ይህ ታላቅ ስራ ነው፣ በልዩ ጥሮነርምት ስንሰራ ከነበረው ይበልጥ የላቀ ተግባር። በመሆ ኑም ያንተ ስራ ያን ያህል የላቀ፣ የሰፋና የጠለቀ ነው። እንደተለመደው ያንተ ልዩ የሥራ ድርሻ የኔን ሃሳብ ማዳበርና በስራ ሙተርነም ይሆናል። አንተ ደግሞ ብሩስ! እጥፍ ድርብ የስራ ሽክም ይጠብቅሃል። ተግባርህ

ከሁለት ሙቶ የዝግጅት ሰራተኞቼ ጋር ያለኝን ግንኙነት መወከል ብቻ ሳይሆን በተለይ የኔ የግል የሕይወት ግንኙነት ተጠሪ አድርጌም ሾሚሃለሁ።››

‹‹ያንተ የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ ወይስ የጋዜጣው?›› ሲል ብሩስ ሃርምስተን አቋረጠው።

‹‹የኔ፣ እኔ እዚህ ሰልጣን ላይ የወጣሁት የገሠኑ ልጅ በመሆኔ ብቻ እድሉ ተቃንቶ እለመሆኑን፣ የአባቴ ልጅ እለመሆኔን፣ የአፊ ታሪክ የፕሬሰ መስጥን የሸነተሁ ግልሞቲ እለመሆኔን ለማሳዬት፣ እኔ ማለት ማን መሆኔን፣ የራሴ ሰብዕና ምን እንደሆነ ለማስመስከር እፊልጋለሁ።››

‹‹ይሰማኛል፣›› አለ ብሩስ ሃርምስተን ከልቡ በመነጨ አነጋገር።

‹‹ቺካጎ በሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሰርተሃል፣›› አለ አርምስቲድ፣ ‹‹ሰራሀን ለመስራት ልምድ ያለህ ሰው ነህ። ከእንግዲህ የማደርገው ነገር ሁሉ ለኔ ተደማሞንትና ተቀባይነት ማትረፉን መከታተል፣ አትኩሮትና ክብር የሚሰቡ ልኝን ነገሮች ለማጎናፀፍ ፕሮግራም ማውጣት ያንተ ተልዕኮ ይሆናል።››

‹‹በኔ ጣለው›› ሃርምስተን ቃል ገባ።

‹‹እንግዲህ የኛ ታላትነት በጋዜጣው ታላትነት ላይ የተመሰረተ ነው። ጋዜጣውን ታላት ለማድረግ ብቻ ይሁን እንትስታሲያችን። ጋዜጣውን ታላት ለማድረግ ደግሞ ሕዝቡ በሊሎች ጋዜጦች ላይ ሊገኝ የማይችለውን ነገር ልናተርብለት ይገባል። ሃሪ፣ እኔና አንተ ሰራተኛውን እንበውዘዋለን፣ ደካሞችን በጠንካሮች በተለይ በወጣት ጋዜጠኞች እንተካለን። ብሩስ ደግሞ ልዩ ፕሮዠክሞችን እንደገና እንድትተጣል ይሁን። ሠራተኛው ምን ሊያስኝ እንደሚችል አጣራ። ከማክ አሊስተርና ከክሩችፊልድ ጋር ግንኙነት አድርግ። በተለይ ከዚያ የመጨረሻውን ልዩ ፕሮዠክት ይዞ ከመጣው የምርመራ ሪፖርተር ጋር ግንኙነትህን አጥብት። ትገ አይልህም!? ያ የዓለም አቀፍ ሽብር ፊጠራን ተከታታይ መሰረት ይሁ መጥቶ ሽማግሌው አባቱ በተታውሞ ያባረረው? ማ ነበር ያ ሪፖርተር?››

‹‹ኒክ ይባላል። ኒክ ራምሲ›› አለ ብሩስ ሃርምስተን።

‹‹ምላሞ ሰው ነው። እስኪ ስለልዩ ፕሮዠክት አንላበት። ከዚያ

በኋላ.....››

በዚህ ጊዜ የአርምስቱድ ስልክ ጮኸ። በስልኩ የተሰማው ድምፅ የኢስቲል ነበር። ‹‹ሚስተር አርምስቱድ፣ አንዲት ልጅ እግር ሴት በስምንት ሰዓት ተጠሮ አለኝ ትላለች። ወይዘሪት ቪክቶሪያ ዊስተን፣ በማስታወሻ ግን አልያዝኳትም።››

‹‹ወይዘሪት ማን?››

‹‹ወይዘሪት ቪክቶሪያ ዊስተን። ለሪፖርተርነት ታለመጠይት ሊያቀርብላት ሳይቀጥሯት አይቀሩም።››

አርምስቱድ ጥቂት ሲያስብ ቆየና አስታወሰ።

‹‹አም አስታወስኩ. . . የኸግ ዊስተን ልጅ። ጥቂት እንድትጠብቅ ንግሪያት።››

ልክ አርምስቱድ ስልኩን ሲያስቀምጥ ‹‹እኔ ታለመጠይቁን ላቅርብላታ?›› አለው ሃሪ ዴትዝ።

‹‹የለም የለም። ይኸኛውን እንኳ እኔ ብመለከተው ይሻላል። ኸግ ዊስተን ቺካጎ እንዴት ያክብረኝ እንደነበር ትዝ አይልህም? ባለውለታየ ነው።›› ብድግ አለ። ‹‹ለምን እናንተስ ከማክ አሊስተርና ከክሩችፊልድ ጋር በስብሰባ አዳራሽ አትሰበሰቡም? ሰራተኛው ሁሉ በለውጣችን እንዲደናገጥ ያስፈልጋል። እክሌ እክሌ ሳትሉ በሁሉም ባርቁበት። ልጅቷን አነጋግሬ ስጨርስ እኔም እደርስላችሁና በሚያለምጠው ሁሉ አሎህበታለሁ።››

* * *

አርምስቱድ ከወንበሩ ተነስቶ ሶፋው ላይ ተቀምጠ ከሱ ትይዩ ሶፋ ላይ የተቀመጠችውን የኸግ ዊስተንን ልጅ ያስተውላል። በጣም የሚገርመው አርምስቱድ ልጅቷን ልጅ አድርጎ ሲጠብቃት እሷ ግን ሙሉ ሴት ሆና ማግኘቱ ነው። ተለሙ የለቀቀ ሙሉ ራንግለር የለበሰች ቆንጆ ወጣት ሆና አገኛት። ንቁ ዓይኖችና ማራኪ ፊግታ ይታይባታል። ይበልጥ ያስገረመው ግን ፍፁም የዋህና ግልፅ ገፅታ የሚነበብበት ፊቷ ነው።

‹‹ከአባትሽ ጋር የተጣራረበ ግንኙነት እንዳለን ሳታውቂ አትቀሪም›› አላት፣ ‹‹ዊስተን የማከብረው ሰው ነው።››

‹‹እሱም ስለርስዎ እንዲት አይሰለቸውም›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹በደረሰብዎ አክል ሲያዝን ነበር. . .›› ብላ ጥቂት አመነታችና ‹‹ግን ለርስዎ ጥሩ በር እንደተከፈተልዎ ሳይሰማው አልቀረም።››

አርምስቱድ ግልፅነቷን በማድነቅ ፈገግ አለ። ‹‹አዎ አባትሽ ትክክል ነሙቷል። ሲግመንድ ፍሩድ መሰለኝ፣ ‹አባቱ እስካልሞተ ልጅ እዋቂ አይሆንም› ሲል ፅፏል አሉ።››

‹‹አንብቤአለሁ።››

‹‹ለመሆኑ አባትሽ በትርቡ እንዴት ነው? አዲሱ ስራውስ?››

አፍንጫዋን ነፋ አደረገች፣ ‹‹አርግጠኛ አይደለሁም። እሱ ሊጋዜጠኝነት የተወለደ ሰው ነው። በሞሽንግተን የፕሬስ ጉዳይ ፊሚነት የሱ ቦታ አይደለም።››

‹‹ታዲያ አንቺም የሱን ዱካ ልትከተይ ነሞ ያሰብሽው?››

‹‹አይ የሱ እግር ሲበዛ ትልቅ ነው። በእኔ ዱካ የሚሞላ አይደለም።››

ሁለቱም ከልባቸው ሳቁ።

‹‹ግን በርግጥ ጋዜጠኛ መሆን ትፈልጊያለሽ?››

‹‹አሁንም ነኝ፣ ሚስተር አርምስቱድ። ለሶስት ዓመት ነበርኩ። ማስረጃዎቼን ሲያዩ ይረዱታል።››

‹‹አሃ፣ ልክ ነሽ። እሰኪ መጀመሪያ ማስረጃዎችሽን ልያቸው።›› ወረቀቶቹን ገላልጦ በጥንቃቄ ካነበባቸው በኋላ መልሶ አጣጠፋቸው። ‹‹ማሩም። የልብ የሚያደርስ ልምድ። ዝንባሌሽ ወደ ምርመራ ሪፖርት ያደላል። ጥሩ የስራ መስክ ነው።››

‹‹የኦሊ ቢሊን ምላሽ ለመከተል እመኛለሁ›› አለችው።

‹‹ያቺ. . . ዓለምን በሰማኒያ ቀናት የዞረች ጋዜጠኛ. . . በስንት ዓመት

ምሀረት ነበር ባክሽ?››

‹‹በ1889ዓ.ም ታዲያ ለኒውዮርኩ ወርልድ ጋዜጣ ስትሰራ ሳለ በ72 ቀናትኽ ነው ጉዞዋን ያጠናቀቀችው። ጉዞዋን የጀመረችው አሙንሰን ሽነዮራያ በተባለች መርከብ ነበር። ምላሌዋን የምኩራል ይመስለኛል።››

‹‹ያለጥርጥር›› አለ አርምስቱድ አሁንም ፈገግ እንዳለ፣ ስሚድና ሰሰራዋ ያላት ፍቅር በእያሌው አስደስቶታል። ‹‹ካሁን ጀምሮ የኒውዮርክ ሪኮርድ ባልደረባ ነሽ።››

‹‹እኔ አላምንም›› ከደስታ ብዛት ከሶፋው ዘሳ ልትነሳ ምንም አልተራት። ሰውዬውን ሳሚው ሳሚው የሚሳት መጥቶ ድንገት ስሚድን ገታች። ‹‹የሚያስደስት ነው ሚስተር አርምስቱድ። እንደማሳስፍርዎ አርግጠኛ ነኝ።››

‹‹እተማመንብሻለሁ። ወደፊት ካንቺ ብዙ ቁምነገር እጠብቃለሁ።›› ብድግ ሲል እሷም በፍጥነት ተነሳች። ‹‹የምርመራ ሪፖርተር በመሆራት እንፈልግ ነበር›› አለ አርምስቱድ፣ ‹‹በተለይ ሴት። ያሉት ሁለትና ሶስት የምርመራ ሪፖርተሮች ሁሉም ወንዶች ናቸው። ከነሱ የላቀው ታሞቂ ሪፖርተራችን ኒክ ራምሲ ይባላል።››

‹‹ሥራውን እንብዘለታለሁ። የሚደንት ሰው ነው።››

‹‹በተለይ በማይጠብት ጊዜ›› አለ አርምስቱድ፣ ‹‹እንቺን ሊተናቀን የሚችለው ሳበገ ሰው እሱ ብቻ ነው።›› ከከፍሉ ሊያስወጣት ከንዲን ያዝ አድርጎ መራት። ‹‹ነገ ልክ በሶስት ሰዓት ስራ ትጀምሪያለሽ። የፕርሶኔል ዲፈኩራችን ወይዘሮ ከሮም ትባላለች። ሂጂና አነጋግሪያት። ስለጀመወገሽ ከሷ ጋር ትደራደራላችሁ። በክፍያችን በኩል ቅሬታ እንደማይሰማሽ እርግጠኛ ነኝ። እሷ ጉዳይሽን ወደ ኦሊማክ አሊስተር ትመራልሻለች። እሱ ደግሞ ቢሮ ይሰጥሻል። አሁኑኑ ሪዳቱን ከዚያም የኔን ሁለት ረዳቶች እንድታነጋግሪ ወደሚቀጥለው ክፍል ልወስድሽ ነው።

‹‹የሪኮርድ አሳታሚ ከሆንኩ ጀምሮ የተጠርኳትን የመጀመሪያዋን ሰው እንዲያነጋግሩልኝ እፈልጋለሁ። እየሽ፣ ያንቺን ጉዳይ በግል መከታተል አለብኝ። ነገ ምንም ስራ አትሰሪም። ቀኑን ከኒክ ራምሲ ጋር እንድታሳልፊ

እፈልጋለሁ። የስራውን ፀባይና ጠቅላላ መስሪያ ቤታችንን ያስገነዝባል።››

በስብሰባ አዳራሽ መግቢያ ሲደርሱ አርምሶቴድ አቆማት።

‹‹አንድ ነገር ትዝ አለኝ›› አላት፣ ‹‹ይቺ በሰባ ሁለት ቁጥር ዓለምን የሠረጭ ኔሲዚሊ ያልሽኝ ሴት መሳሪያ ትይዝ ኖሯል?››

ቪክቶሪያ ደንግጣ አለች፣ ‹‹እኔ. . እኔ አንጀ።››

‹‹መቼም ከነበረችበት ስራ ጋር ስናስተያይ መሳሪያ መታጠቅ እንዳለባት ይሰማኛል። እስኪ ነገ ከኒክ ራምሲ ጋር ስትውይ ይህን ጥያቄ አንሽበት። እሱ ሳያውቅ አይቀርም። ምናልባት እሱም ራሱ ሳይታጠቅ አልቀረም። አንቺም በርግጥ የምርመራ ሪፖርቱን መሆንሽ ከሆነ አንድ የንፍስ ወከፍ መሳሪያ መታጠቅሽ አይቀርም።››

* * *

በማግስቱ ጧት ቪክቶሪያ ዊስተን ለአዲሱ ሥራ የነበራት ጉጉት የቅጥር ፎርማሊቲ በማጓላቱ አሰልቺ ስራ ተጸክሞ ነበር ያረፈደው። ወይዘሮ ከሮው ከደመወዝ አንስቶ እስከ ጤና ኢንሹራንስና ማኅበራዊ ደህንነት ቅጾች በዝርዝር ስትሰራ ቁጭ ብላ መጠበቅ ነበረባት። በምክትል አዘጋጁ በአለ ማክ አሊስተር ቢሮ ስትገባ ለምሳ ሃያ ደቂቃ ጉዳይ ሆኗል።

አለ ማክ አሊስተር በሃምሳዎቹ መካከለኛ ዕድሜ የሚገኝ ጋማርት ቢጤ ነበር። ቅናቱን ባገኘችው ጊዜ ያልወደዳት መስሏት ተጨንቃ ነበር። ዛሬ ግን ዝምተኝነቱ ተፈጥሮው መሆኑን ተረድታለች።

በሩን ከፍታ ስትገባ የቴሌክስ መልእክት በማንበብ ላይ ስለነበር ከአንገቱ እንኳ ቀና ሳይል እንድትቀመጥ በእጁ ወደ ወንበሩ ጠቆማት።

‹‹ርርማሊቲዎችሽን አጠናቀቅሽ ወይዘሪት ዊስተን?›› አላት ንባቡን እንደጨረሰ።

‹‹ይመስለኛል›› አለች፣ ‹‹ከኒክ ራምሲ ጋር እንድሰራ ተነግሮኛል።››

‹‹ቆይ እስኪ ላግኘው›› አለና ማክ አሊስተር ስልኩን አነሳ። ብዙ ከደወለ

በኋላ ሊያገኛው ባለመቻሉ የሚያሳውን ሰዓት ተመለከተ።

‹‹አ፣ ለስድስት ሩብ ጉዳይ። ቢሮው እንደማይገኝ ማወቅ ነበረብኝ። የምሳ ሰዓት ደርሷል። ከዘጠኝ ሰዓት በፊት አናገኘውም።››

‹‹እስከዘጠኝ ስራ የለም?! ለምሳ ሶስት ሰዓት?!›› አለች ቪክቶሪያ ተገርማ።

‹‹ማለቴ ለጊዜው ሥራ የለውም፣ ኒክ ራምሲ ስራ ከተሰጠው ያለ ዕረፍት ይሰራል። ስራ ከሌለው ደግሞ አትቆጣጠሩኝ፣ እንደፈለግሁ ልግባ ልውጣ ባይ ነው። ባሬ ስራ ስለሌለው ቶሎ እይመለስም።››

‹‹እስከዚያ የሚሰጡኝ ስራ ይኖርምታል ሚስተር ማክ አሊስተር?››

‹‹ምሳሽን ብይ። ከዚያም በኋላም ቢሆን ለኒውዮርክ ከተማ እንግዳ ነሽና የግል ስራዎችሽን ጨራርሽ።››

‹‹በርግጥ›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹ትናንት ማታ አንዳንድ ጓደኞቼን ሳጠያይቅ እንድ ኢንቨታማ ሳያገኙልኝ አልተኙም። ሂጂ ባየው ደስ ይለኛል።››

‹‹እይው፣ እስክ ዘጠኝ ሰዓት ነፃ ነሽ።››

ቪክቶሪያ ብድግ አለች። ‹‹ቢሮ እንደሚሰጠኝ ተነግሮኝ ነበር።››

‹‹እንዴታ!›› አለ ምክትል አዘንጂ። ቀደም ብሎ በሩን ከፈተላትና ወደሰፊው የመዋዕለ ዜና ክፍል ወሰዳት። መለስተኛ አዳራሽ የመዋዕለ ዜና ክፍል ግማሽ በሰዎች የተያዙ እጅግ ብዙ ጠረጴዛና ወንበሮች ሞልተውታል። ‹‹ይሀን ያህል ብዙ ጠረጴዛዎች የሞሉት ክፍል አይቼ አላውቅም›› አለች ቪክቶሪያ የማለዳው የሥራ ጉጉት እየተቀሰቀሰባት።

‹‹እዚህ ክፍል ሁለት መቶ ሠራተኞች አሉን›› አለ ማክ አሊስተር፣ ‹‹ክፍሉም ቢሆን ሰፊ ነው።› ክፍሉን ቃኘና አንድ ባታ ላይ ጣቱን ቀሰረ።

‹‹በዚህ ረድፍ ወደግራ ተመልከች። አሥረኛው መደዳ። ልትረሽው አትችይም። በዚህ ክፍል ያለው ንፁሕ ጠረጴዛ እሱ ብቻ ነው። በይ እንግዲህ

መልካም ምሳ ቪክቶሪያ።››

ተፈላጊነቷን ያረጋገጠችው ቪክቶሪያ በትክሻዋ ያነጣጠችውን በርካ በእጅዋ አንጠልጥላ የወጣት ሪፖርተሮች ዓይኖች አንዳተኩሩባት ወደራ ጠረጴዛ አመራች። ስልኩና የዝና የወሮ ደብዳቤ ማስቀመጫዎች ያሉት በሩማ የብረት ጠረጴዛ ነበር። አሁን ቦታዋን አውታለች። ከእንግዲህ የሚተራት ምሳ መብላት፣ የመኖሪያ አፓርታማዋን መከራየትና አለቁ ያደነቁትን ኒክ ራምሲን ማግኘት ነበር።

* * *

ኒክ ራምሲ ተደም ብሎ ይጣ ይሆናል በማለት ቪክቶሪያ ከሰዓት በኋላ የተመለሰችው በስምንት ተኩል ነበር። አሱ ግን ገና አልገባም።

ምሳዋ ምሳ አልነበረም። እየተዋከበች የሰጋ ሳንድዊችዋን በልታ አንዲት የኮሌጅ ጓደኛዋ የጠቆመቻትን አፓርታማ ተጽሩላ መከራየት ነበረባት።

አሁን ወንበሩ ላይ ተቀምጣ ገና አረፍ ሳትል መልኩን የማታውሰውን ኒክ ራምሲን በዚያ ሰፊ የመዋዕለ ዜና አዳራሽ መፈለግ ያዘች። በመጨረሻ ግን ራምሲ ራሱ እሷን ፍለጋ እንደሚመጣ ስለተገነዘበች ተረጋግታ ተቀመጠችና በሰለቱ ታትሞ የወጣውን የሲቱን ሪከርድ ጋዜጣ ታነብ ጀመር። በጋዜጣው ላይ በተለይ ኒውዮርክ ከተማን በሚመለከት ያገኘችው ዜና ግን በአብዛኛው በወንጀል በተለይም በነፍስ ግድያ ላይ ያተኮረ ነበረ። የተሰላቸ ንባቧን ተጥላ ሳለ ትክሻዋን እንድ እጅ ቸብ አደረጋት።

ከማየቷ በፊት ሰማችው።

‹‹መደበሪት ኒሊ. ብሊ. መሰልሽኝ?›› አለ ወፍራም ድምጽ።

ቪክቶሪያ ከአንገቷ ሠር ሰትል ያ ወፍራም ድምጽ ‹‹ኒክ ራምሲ ነኝ፣ ምንጊዜም ታዛርሽ›› አላት።

ገጽታው ያሰደንግጣት ይመስል ፈንጠር ብላ ተነሳች።

አርምስቱድ ምርጥ የምርመራ ሪፖርተር ያለው ኒክ ራምሲ እንደጠበቀችው ዓይነት ሰው ሳይሆን ከልጅነረዱት ጋር ተጻርቶ ያላበ

የክሊጅ ተማሪ መስሎ አገኘችው። ሰፊ ትከሻ ያለው ወልገድጋዳ ረዣርም ወጣት ነው። ፊቱ ደስተኛ ይመስላል። ወደ አንድ ጎን የላገው ጥቁር ፀጉር ፊቱ ላይ ድፍት ብሎ ልዩ ውበት ሰጥቶታል። አለባበሱ ደማሞ እጅግም ያልተሽቀረቀረ የወንዳወንድ አለባበስ ነው። እድሜው ከሰላሳ አምስት እንደማይበልጥ ቪክቶሪያ ገመተች። ትንሩሽ ትኩሳት ያጋየው ይመስላል።

‹‹ቪክቶሪያ እባላለሁ. . . ቪክቶሪያ ዊስተን›› አለች ቪክቶሪያ ሃሳቧን ልታሰባስብ እየሞከረች።

‹‹አ ኒሲ ብሊ መስለሽኝ›› ሲል ኮመካት።

‹‹ምን?›› አለችው ግራ ተጋብታ።

‹‹መሳሪያ። ኒሲ ብሊ መሳሪያ እንግባ አታውትም። አንቺም ብትሆኝ በጓሮ ድመቶች ላይ ልትተኩሽ ካልፈለግሽ በስተቀር ማንገብ የለብሽም። በመለስተኛ ደረጃ የምርመራ ሪፖርተርነት መተጠርሽ ተነግሮኛል። ኒክ ራምሲ እባላለሁ።››

‹‹አመሰግናለሁ›› አለችው ነገሩን ባጭር ለመቅረጥ። ኒክ ሰዓቱን ተመለከተና፣ ‹‹የሁለት ሰዓት ጊዜ አለን። የሴቶችን መፀዳጃ፣ የቡና ማሽን ክፍሉንና ጠጥተሽ ካደርሽ በማግስቱ ሳትታይ ቢሮሽ የምትገቢበትን ድብቅ መንገድ ላሳይሽ።››

‹‹በጣም ጥሩ።››

‹‹ከጎኔ እንዳትራመጅ›› አላት፣ ‹‹ራስ ራሴን እያየሽ ተከተይኝ። ትንሽ ጠጥቼ ነው የገባሁትና እንቺንም እንዳላስፎግርሽ።››

‹‹ግን ራስህን ስተሃል?››

‹‹ያንቺ ዓይን ሚዛኑን ያስጠብቀኛል። በይ እንግዲህ ተዘጋጅ። ጉብኝትሽን ከዚሁ ክፍል አስጀምርሻለሁ።››

እነጋገሩን ወደደችለት። ‹‹ገማጯ ነኝ ኒክ›› አለችው።

ኩተንጣለለው የመዋዕለ ዜና አዳራሽ አስገብኝነቱን ጀመረ። በክፍሉ

ያሉትን ሰራተኞች ስም እየጠቀሰ፣ የክፍሉን አደረጃጀት አስረዳት።

የኒውዮርክ አካባቢ አዘጋጆችን፣ የቪሌራዊ አዘጋጆችን፣ የሙዚ አዘጋጆችን፣ የስፖርት ዝግጅቱን፣ የፋይናንስ ዝግጅትንና የባህል ዝግጅትን ስፍራዎች በጣቱ እየጠቆመ አሳያት። በአሶሼትድ ፕሬስ፣ ከሮይተር በዶ ጅንስና በሊሎች የዜና ምንጮች ሪኮርድን በወከሉ ዘጋቢዎች የሚደርሱ ዓለም አቀፍ መራጮች የሚተናበሩበትን ሰላሳ አምስት የቴሌክስ ሰራተኞች የታመቁበትን ክፍል በእድናቆት አስተዋለች። እጅግ የሚያስደንቅ ውስብስብ አሰራር ነበር።

ከዚያ በኋላ በተለያዩት ክፍሎች እያዞረ ከሠራተኞቹ ጋር አስተዋወቃትና ወደ ቤተ መፃሕፍት ወሰዳት።

ጉብኝቱን እንዳጠናቀዱ ራምሲ ቪክቶሪያን በእትኩሮት ሲመለከታት ከቆየ በኋላ «ትንሽ ሳትደክሚ አልተረሽም» አላት። ቀጥሎም ሰዓቱን አየ። «አ! አሥራ ሁለት ሊሞላ አይደለም እንዴ። በይ እንግዲህ ልለይሽ ነው። በአስራ አምስት ደቂቃ ውስጥ የምገኝበት አንድ ተጠሮ አለብኝ» አላት።

«በጣም አመሰግንሃሁ ኒክ።»

«ክፅ ከመለየቱ በፊት ሲጋራ አቀጣጠለና ለመራመድ አመነታ። «ግን አሁን ምን ስራ አለሽ?» አላት።

«ማሮሰራ ሄጀ ጥቂት የሚበላ ነገር መግዛትና ቤቱ ገብቼ ማብሰል አለብኝ።»

«አ! ጀማሪ ሰራተኛ እንደመሆንሽ የመጀመሪያውን ምሽት ስታብስይ ማሳለፍ የለብሽም።»

«ታዲያ ምን ልስራ?»

«ለምሳለ ከአስተባባሪሽ ጋር የራት ፕሮግራም መያዝ። እንቺ ከቻልሽ ተጠሮየን ልሰርዝልሽ እችላለሁ።»

ፊቷ ፈነ። «ደስ ይለኛል፣ ወቴ ከየራሳችን ኪስ ከሆነ?»

«በጣም ጥሩ፣ በሁለት ተኩል አዚሁ እንገናኝና የት እንደምናለፍ

እንወስናለን።››

በሰዓቱ ተገናኝተው በታውን ወሰኑ። የራምሲ እጅት ለደቂቃ እንኳ አለመባዘናቸው ቪክቶሪያን ሲያስገርማት ነበር ያመሸው። ተኝ እጹ ከጂንና ከቶኒክ፣ ግራው ደግሞ ከሲጋራ ሊለዩ አልቻሉም።

እሷ እንዴን እንኳ ሳትተምስለት እሱ ሶስቱን አጋብቶታል። በመጨረሻ ቪክቶሪያ ጠኔ ሲያገላብጣት ራምሲ የሷን ምርጫ እንኳ ሳይጠይት ራት አዘዘ። በትእዛዙ ተደስታ ሳታበቃ አራተኛውን ጂን ሲያዝ አይታ መንፈሷ ተረበሸ። በመጠጥ ኃይል ተግፋፍቶ ሊያመጣ የሚችለው አደጋ ታይቷት ተፈራት። እሱ ግን ብዙም ለውጥ አላሳየም። እንዲያውም ረጋ እያለ መጣ።

የሱ ረጋና ዝም ማለት ደግሞ እሷን ያለወትሮዋ ምላሳም አደረጋት። ስለተከራየችው አፓርታማ፣ ስለከፈለችው ኪራይ፣ ከቫካን ስላመጣችው ጓዝ፣ አባቷ ቤት ዋሽንግተን ስልክ ስለመደወሏ፣ ለእናቷ ደውላ ስራ መጀመሯን ስለመንገሯ፣ ተጥላ ሰውነቷን ስለመታጠቧ፣ ተጥላ ልብስ ስለመቀየሯና ታክሲ ይዛ ስለመምጣቷ፣ የዋጠችው ቅቤ አልተራትም።

ራምሲ የሰማት መልስ ግን ‹‹ጋዜጠኝነት አስተያየቷ ስራ ነው። በተለይ ሴቶች የሚሰሩት የሙያ መስክ አይደለም። እውነትን ጠርቦና ቦርቾ ለትረካ ማቢያትን ይጠይቃል። እንዴት እዚህ ሜጥ ውስጥ ልትገቢ ቻልሽ?›› የሚል ጥያቄ ነበር።

ግዴለሽ ከሚመስለው ገጽታው ያልጠበቀችውን ቁጡ ንግግር በመስማቷ የደነገጠችው ቪክቶሪያ የሕይወት ታሪኳን ሙተረኳን ቀጠለች። አባቷ፣ የአባቷ ብልሀትና ቆራጥነት የሷን ሙያ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው። ነገር ግን ከሁሉም በላይ ቪክቶሪያን ወደጋዜጠኝነት ሙያ እንድታዘነብል ያደረጋት ለጋዜጠኞች፣ ለሚቆፍሩት ምርጥ ዜናና ወሬ በማቀናበር ረገድ ላላቸው ጥበብ የሚሰማት አድናቆት ነበር። በሰሜን ምዕራብ ዩኒቨርስቲ አምስት ዓመታት አሳልፋ፣ በኮሌጅ ጋዜጣ ሰራተኛነት ከመስራቷም በላይ በጋዜጠኝነት የማስትሬት ዲግሪ ከተቀበለችበት ጊዜ አንስቶ በሳምንታዊ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሠርታለች። ከዚያ ጊዜ አንስቶ ቪክቶሪያ በመዋዕለ ዜና ክፍል አገልግላለች።

‹‹በፍቅር ዓለም ያላለፍሽው ሕይወት አለሽ?›› ሲል ገለማዋን ድንት አቋረጣት።

‹‹ያ ያንተ ችግር አይደለም፣ ግን አሱንም አይቸዋለሁ›› አለችው።

‹‹ከጋዜጠኛ ጋር ፍቅር አይተሻል?››

‹‹የለም፣ ግን. . .››

‹‹ግን አትችይም።››

‹‹ለምን አልችልም?››

‹‹እንደተዋንያንና ደራሲያን ሁሉ ጋዜጠኞችም በግል ጉዳይ የተጠመዱ ናቸው። ዊልሰን ሚዝነር ‹‹ሕይወቱ ካሳለፍኳቸው የፍቅር ገጠመኞች ሁሉ ትልቁ ከብቸኛ ጋዜጠኛ ጋር ያሳለፍኩት ነው›› ብለዋል።››

ከጋዜጠኛ ጋር፣ በተለይም ከዕድሜና ከአመለካከት አኩያዋ፣ በተለይም ደግሞ ኒክ ራምሲን ከሚመስል ወንድ ጋር ፍቅርን መስራት ምን እንደሚመስል በተመለከተ አሰበች።

በርግጥ ለፍቅር አዲስ አይደለችም፣ ያሳለፈቻቸው ሁሉ ፍቅር የሚባሉ ከሆነ። በሕይወቷ አራት ወንዶችን አይታለች። አራቱም የአጭር ጊዜ ኮንትራቶች ነበሩ። የመጀመሪያው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለች ያየችው ሲሆን ነጣሩን ያደረገችው ያን ‹‹ጋሬጣ›› ከብረ ንጽህናዋን ለማስወገድ ስትል ነበር። ሁለተኛውና ሶስተኛው ኮሌጅ ገብታ ያሳለፈችውና አስደሳችነቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማጣጣም ያደረገችው ነበር። (ከሁለቱ አንደኛው ትንሽ ደስታ የሰጣት ቢሆንም ደስታዋ ከአሌን ላይ ደስታ አልፎ ሊዘልትላት አልቻለም።) አራተኛውና ለእባቷ ገልፃ የነገረችው ግን ከኮሌጅ የምረቃ ጽሑፏን ለማተናበር ታለመጠይቅ ካደረገችለት ባለትዳር ጠበቃ ጋር ያሳለፈችው ነው። ጠበቃው መላ ፍትሩን ከመለገስ አልፎ ሚስቱን ፈቶ ሊያገባት ቃል ቢገባላትም ከራስ ወዳድነቱ የተነሳ ባለቤቱን ፈቶ ሊለያት አልቻለም።

ኒክ ራምሲ ምንም ይበል፣ ግን ጋዜጠኛ ቢያፈቅሩት ያን ያህል ይጎዳል? ስትል አሰበች።

በዚህ ቅጽበት የሞቱሉ አስተናጋጅ ለራምሲ አዲስ መለኪያ ጅን ሞላለት። ወዲያውኑ ራምሲ መለኪያውን ብድግ አድርጎ ባንድ ትንፋሽ ካጋመሰለት በኋላ ‹‹የዊልሰን ሚዝነርን አባባል ልድግመልሽና ‹አኔ ታላቅ ተማሪ ነኝ። ከዓረፍተ ነገሮች ሁሉ የምወደው አንድ ለመንገድ የተባለውን ነው› ብሏል›› አላት።

‹‹ይሽ ዊልሰን ሚዝነር ማነው?›› አለች ቪክቶሪያ ሹካዋን ወደ አፏ ለግታ።

‹‹ዊልሰን ሚዝነር ማነው?›› ሲል ራምሲ ታሉን በማሾፍ ደገመው። አፉ ግን መያያዝ የጀመረ ይመስላል። ‹‹ለመልስ የቸገረ ጥያቄ አቀረብሽልኝሳ። ዊልሰን ሚዝነር ደራሲ፣ ቱማርተኛና ሁሉንም ልሁን ባይ ነበር። ይህንን ባህርዩን እወድለታለሁ። በችሎታው ሙሉ ያልተገለገለ ሰውም ነበር። ይህንን ወላይም እወድለታለሁ። አንድ ቀን አንድ ሰው ከአትሙ በላይ ተሸክሞ ሲንገላገል አይቶት ‹አንተ ድመት ልትሆን የምትጥር አይጥ ነህ› አለው።››

ቪክቶሪያ ከት ብላ ከመሳት ሊላ ምርጫ አልነበራትም። ሳቋን ስትጨርስ ከምግቧ በሹካዋ ጠቆም አድርጋ ‹‹አንድ ነገር ጠይቀኸኝ ነበር›› አለችው፣ ‹‹ድርሻየን እኔም ልጠይቅህ። እንተስ ምን የፍቅር ገጠመኝ አለህ?››

‹‹ድምጽ ከመስጠት ተቆጥቤአለሁ›› አላት።

‹‹ልክ አይደለህም።››

‹‹የፍቅር ሕይወት አልሞክረኝም›› አለ፣ ‹‹የወሲብ ሕይወት ብቻ። በኔ ግምት ፍቅር የሶስት ፊደላት ታሪ ነው። በናትሽ የተበላሸውን የሕይወት ታሪኬን እንዳበራራ አትጠይቂኝ። የፍቅር ሰው አድርገሽ ግመተሽኝ ከሆነ እርሽኝ። ፍቅርና ጋዜጣ፣ ሁለት ባለሶስት ፊደላት ታሉኛ።››

የጎሪጥ ተመለከተችው። በዝግ እንዳለ መጠጡን ይጨልጣል።

‹‹ታዲያ ጋዜጠኝነትን ይህን ያህል ከጠላኸው›› አለችው፣ ‹‹እንዴት ሙያህ አደረግኸው?››

‹‹ሽርሙጣ እንዴት ትሸረሙጣለች?›› ሲል በጥያቄ መለሰላት።

‹‹እሱ መልስ አይደለም።››

‹‹ጥያቄሽም ጥያቄ አይደለም።››

‹‹ማለቴ ወደመጣያው እንዴት አዘነበልህ? ምን ገፋፋህ?››

‹‹እሱ ነው ጥያቄ›› አላት፣ ‹‹በስፖርት ደካማ ነበርኩ። ጽሑፍ ብቻ አሞካክር ነበር። መቼም ጽሑፍ፣ የተፈጥሮ ተሰጥኦ ነው። እኔም መጽሐፍ ልደርስ አሰብኩ። ግን ደራሲያን ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ጥሩ ኑሮ መኖር አለባቸው፣ ነፃነትም ሊሰማቸው ያስፈልጋል። እኔ ግን በመለስተኛ ክሊጅ ሁለት ዓመት እንዳሳለፍኩ ባቋራጭ የጋዜጠኝነት ነፃ ትምህርት እድል አግኝቼ ዩኒቨርስቲ ገባሁ። ያ የሕይወቴ ውድቀትና የመጨረሻው ክስረት ነበር።››

የምጣብ ሳህናቸው ተነስቶ ራምሲ የመለኪያውን አልኮል ሲጨልጥ ንግግራቸው ተቋርጦ ስለነበር ከጥቂት ዝምታ በኋላ፦

‹‹የት ላይ ነበርኩ?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹ዩኒቨርስቲ ገባሁ›› አለችው።

‹‹አዎ። በዚያ ዩኒቨርስቲ የደይሊ ካርዲናል ጋዜጣ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢ ነበርኩ። እጅግ፣ እጅግ በጣም ከፍተኛ ተሰጥኦ ነበረኝ፣ እንዲያውም አልነግርሽም። የትርፍ ጊዜ ስራ ሰጥቶኝ ነበር። በኋላ ደግሞ በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ተቀጥሬ ሰርቻለሁ። ይኸውልሽ ከዛሬ አስር ዓመታት ጀምሮ ወፍራም ደመወዝ ለሚከፍለው ‹ዝሆኑ› ኢዝራ አርምስቴድ ለሚያሳትመው ሪከርድ ጋዜጣ እየሰራሁ ነኝ።››

‹‹ታዲያ ምንድን ነው ያስከፋህ?›› ቪክቶሪያ ልታውቅ ፈለገች።

‹‹መፃሕፍት›› ነበር መልሱ። ‹‹ሁልጊዜ መጽሐፍ መድረስ እንደ ተመኘሁ ነኝ።››

‹‹ታዲያ ምን አገደህ?››

‹‹ምንም አላገደኝ። አንድ ጽፌአለሁ።››

‹‹እውነት?!›› ሲበዛ ተደነቀች፣ ‹‹እንተ መጽሐፍ ጽፈህ አሳትመሃል? ስለምን ነበር?››

‹‹ስለጂን ጃክ ሩሶ። በ1910 ስለሞተው የፈረንሳይ ሰዓሊ። ስለታወተው ተቆጣጣሪ፣ በኋላ ፖስተኛ ሆኖ በመጨረሻ ወደተለም ትብ ስላዘነበለው ስለጂን ጃክ ሩሶ ነበር።››

‹‹ላንበው እፈልጋለሁ። ርዕሱን ንገረኝ?››

‹‹ርዕሱ ‹ፖስተኛ ሁልጊዜ ሁለቱ ያንኳኳል› ይላል። የለም ስተልድሽ ነው። ስለርዕሱ አትጨነቂ።››

‹‹ላንበው እፈልጋለሁ፣ ኂክ።››

‹‹አታገኘውም። በምርጥ መጽሐፍት መደብር እንኳን አይገኝም። 344 ቅጅ ብቻ ነው የተሸጠው።››

‹‹ለምን ሌላ መጽሐፍ አትጽፍም?››

‹‹አንቺ እኔን ብትሆኚ ትታመጭለሽ?››

ቪክቶሪያ በታላት ስሜት ራሷን ነቀነቀችና ‹‹በሕይወቱ የምፈልገው ድርሰት ከሆነ ለምን አላደርገውም?›› አለችው።

አፍንጫውን ነፋ አድርጎ ‹‹አንቺ ትችያ ይሆናል፣›› አላት፣ ‹‹አንቺማ እውቅ ዜና አጠናቃሪ ለመሆን የሚያግደኝ ነገር የለም የምትይ ጅግና ነሽ፣ አይደለሽም?››

‹‹አም አምንበታለሁ። ጋዜጠኝነት ከተከበሩ ሙያዎች ውስጥ የሚመደብ መሆኑን ማን ይክዳል?››

‹‹የኔ አመቤት፣ ዛሬ ጊዜው የተራቀቀ ነው። የጥድፊያ ጊዜ ነው። የን ግድ ጊዜ ነው። የጋዜጠኝነት ክብር ድሮ ቀረ። የወጣትነት ጊዜሽን በከንቱ አታባክኚ። በጋዜጠኝነት የወደፊት ሕይወቴን አላምራለሁ ብለሽ አትድከሚ። በኔ ይሁንብሽ ጋዜጠኝነት እጅግ አሰልቺ ከሆኑ ሙያዎች አንዱ ነው።››

‹‹ተሳስተሃል›› አለችው አጽርጣ።

‹‹እንግዲህ እንዳልሽ ይሁንልሽ›› እንዳላት በአጠገባቸው የሚያልፈውን አስተናጋጅ ባዶ መለኪያውን ከፍ አድርጎ ‹‹አንድ ለመንግድ›› አለው። አይኑን ካስተናጋጁ አንሶ ቪክቶሪያን ሲመለከት በትዝብት እንደምትመለከተው ተረዳ።

‹‹ኒክ›› አለችው፣ ‹‹ለምን ይሆን ያህል ትጠጣለህ?››

ካለልቡ ፈገግ ብሎ ‹‹ምን አውቃለሁ?›› አላት፣ ‹‹የምርመራ ሪፖርተር በመሆንሽ እንቺው ድረሽበት።››

* * *

በማግስቱ ጧት ቪክቶሪያ ዊስተን ስሚ በድምጽ ማጉያው ሲጠራ በሰማችው ወቅት ስለኒክ ራምሲ በማሰብ ላይ ነበረች። ከምክትል አዘጋጁ የተላለፈላት ጥሪ ነበር። የማስታወሻ ደብተሯንና ብእሯን እንስታ ወደ ማክ አሊስተር ቢሮ ለመሄድ ተነሳች።

ማክ አሊስተር የእንድ አታፊ ጽሑፎች እያግላበጠ እንድትቀመጥ ጋበዛት።

‹‹የመጀመሪያ ተልእኮሽ›› አላት።

‹‹ዝግጁ ነኝ›› አለች ተበል አድርጋ፣ ትእዛዙን በማስታወሻ ልታሰፍር እየተዘጋጀች።

‹‹ኤድዋርድ አርምስቱድ ቦታውን የያዘው በትርቡ እንደመሆኑ ምን አይነት የምርመራ ታሪክ ማግኘት እንዳለብን ገና አልወሰንም። ሆኖም ስራ እንዳትፈች አንዳንድ ጥናታዊ ዜናዎችን እንድትሰራ አዘጋጅተንልሻል። በተለይ አሁኑኑ የምትሰሪው አንድ ሥራ አለ።››

ቪክቶሪያ ምንነቱን ለማወቅ ጓጓች።

‹‹ለመሆኑ ሳም ይንገር ሲባል ሰምተሽ ታውቂያለሽ?››

‹‹እሱን የማያውቅ ማናለ? እኒያን ሕፃናት የፈጀው ነፍሰ-በላ።››

‹‹ይኸውልሽ ከሁለት ቀናት በኋላ በኤሊክትሪክ ወንበር ላይ ተቀምጦ

እንዲሞት ተፈርዶበታል። አየሽ፣ የፊጸመው አሰቃቂ ወንጀል ሕዝቡን ሰለሱ መጨረሻ ለማወቅ እንዲጓጓ አድርጎታል። በተለይም የሕይወቱን የመጨረሻ ቀናትና የመጨረሻ ሰዓቶች እንዴት እንደሚያሳልፋቸው ለማወቅ ሁሉም ይፈልጋል። አሁን እኛ የምንፈልገው እውነተኛ የሆነ ግሳፄ ታሪክ ማተናበር ነው። ዴዝ ሮው በተባለው የመጣደያ ስፍራ የሚኖን ይህዮት በታ የተፈረደበት ወንጀለኛ በሕይወቱ የመጨረሻ ሰዓቶች ምን ይሰማዋል? ምን ያደርጋል? ምን ያስባል?››

‹‹ግባኝ›› አለች ቪክቶሪያ።

‹‹አንድ ጽሑፍ እንደምታዋርቢልን ተስፋ አለን። በርግጥ አኛ እና ሁሉም የማስታውቂያ ድርጅቶች ታለ መጠይት እንዳናዋርብ ተከልክለናል። ይንግርን በግንባር ማነጋገር አልቻልንም። አሁን እንደደረስንበት ግን ይንግርን በተዘዋዋሪ መንገድ መጣናኘት ይቻላል።››

‹‹እዚህ ላይ አልግባኝም፣›› አለች ቪክቶሪያ አቋርጣ።

‹‹አየሽ›› አለ ማክ አለስተር በሰፋት ሲተነትን፣ ‹‹እዚህ የሪኮርድ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በማዘጋጀ ቤት፣ በዓለቢ ሕግ ጽሕፈት ቤት ቢሮና በአስተዳደር ጽሕፈት ቤት አካባቢ አንዳንድ ጆሮ ጠቢዎች አሉት።›› ንግግሩን ቅም አድርጎ ቀየና ‹‹ከሽብር ፈጣሪዎች ላይ ወሬ የሚያቀብሉንም አሉ›› አላት።

ቪክቶሪያ አልተደነቀችም። ነገር ግን ‹‹ኧረ? ግን የጠ ባልደረቦቻቸውን ሲሰልሉ ትንሽ አያስጋቸውም?›› አለችው።

‹‹በርግጥ ይሰጋሉ። ግን ገንዘብ ስለሚፈልጉ ራሳቸውን በሚያስገኛቸው መንገድ የሚለትመውትን ወሬ ያቀብሉናል። ከፋኖዎች ላይ ወሬ በማቀበል ከሁሉም የሳቀው ጆሮ ጠቢአችን ጉስ ፓጋኖ ይባላል። ስለጉስ ፓጋኖ ከዚህ በፊት የሰማሽው የለም?››

‹‹አልሰማሁም።››

‹‹በርግጥ ያኔ አንቺ ቺካጎ ስለነበርሽ ጉስ ፓጋኖን አታውቂው ይሆናል። ከሰሰት ዓመታት በፊት ጉስ ፓጋኖ መለሰተኛ ወንጀል ፊጽሞ ነበር። ግድያ

ሳይሆን ስርቆት። አንድ ምሽት የአንድ ሆቴል ግንባብ ያዥ ሲባ ሲዘርፉት ሲሞክር ደርሳበት ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ደውላ ኖሮ ሁለት ፖሊሶች በመኪና ይደርሱላታል። ሌባው ግን ሁለቱንም ፖሊሶች ገድሎ ያመልጣል። እንደም ታውቂው ፖሊስ የፖሊሰን ጥቃት በቀላሉ አይመለከተውም። የወንጀል ምርመራው በስፋትና በጥልቀት ተጥሎ ተጠርጣሪዎች እየተያዙ ይታሰሩ ጀመር። ጉሰ ፓጋኖ አንዱ ተጠርጣሪ ነበር። ወዲያውኑ ሶስት ምስክሮች ነፍሰ-ገዳዩ ጉሰ ፓጋኖ መሆኑን ማየታቸውን ይመሰክራሉ። እሱ ቢምልና ቢገዘትም ለንጽሕናው ማረጋገጫ አልነበረውም። ፓጋኖ ክስ ይመሰረትበትና በኤሌክትሪክ ወንበር ተቀምጦ እንዲሞት ይፈረድበታል። ፓጋኖ ንፅሕናውን እያስመለከተ ለብዙ የኒውዮርክ ጋዜጦች በመፃፍ አቤቱታውን እንዲያሰተጋ በሶት ይማፀናል። የሪከርድ ጋዜጣ አዘጋጅች በጉሰ ፓጋኖ ደብዳቤ ከተመሰጡት መካከል ነበርን። ባደረግነው ርብርቦሽ የሞት ቅጣት የሚፈጸምበት ቀን በተድጋጋሚ ይተላለፍ ጀመር። በመጨረሻ ግን ቁርጠኛ የፍርድ መፈጸሚያ ቀን ይወሰንበታል። ወደ ዴዝ ሮው ተወስዶ የመሞቻውን ሰዓት በመቁጠር ላይ ሳለ አትላንታ ላይ አንድ ነፍሰ ግዳይ ይያዝና ጉሰ ፓጋኖ የተወነጀለባቸውን ፖሊሶች መግደሉን ያምናል። በርግጥ ወንጀለኛው ጉሰ ፓጋኖን ይመስል ስለነበር ምስክሮቹ ወንጀሉን በጉሰ ፓጋኖ ላይ መለደፋቸው አስደናቂ አልነበረም። ያም ሆነ ይህ ፓጋኖ በነፃ ይለቀቃል።››

‹‹ታዲያ አሁን ለናንተ እያገለገለ ነው?››

‹‹አዎ። ነገሩ የሆነው በእጣፈንታ ነበር። ከእስር ከተፈታ በኋላ አንድ ቀን ነፃ እንዲወጣ ላደረግንለት ጥረት ምስጋና ሊያቀርብ ወደ ቢሮአችን ይመጣል። በርግጥ አንዳንድ መለስተኛ ወንጀሎችን ይፈጽም እንደነበርም ጨምሮ ይገልጽልናል። በጆሮ ጠቢነት እንድንቀጥረው ያመለከተንም ራሱ ነበር። በሱ ላይ እምነት ባይኖረንም በመጨረሻው ብቃቱን ልንሞክር ተስማማን። መጀመሪያ የሚያቀርብልን መረጃዎች ይህን ያህል ባይሆኑም በኋላ ግን በጣም ጠቃሚ ዜናዎችን ያቀርብልን ጀመር። እሱ በሚያቀርብልን ጥቆማዎች እየተመራንም ብዙ ታላላቅ ወፈፎችን ማቀናበር ቻልን። ከዚያ ጀምሮ በደመወዝ ሰነዳችን ላይ ተመዝግቦ ይገኛል አልሻለሁ።››

‹‹ታዲያ ከሳም ይንገር ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?›› ስትል

ጠየቀች ቪክቶሪያ።

‹‹ከሁለት እንዳቸው ወህኒ ከመውረዳቸው በፊት ፓኃኖ ይንገርን ያመለው ነበር። ከሁለ ይበልጥ ጠቃሚው ነጥብ ግን ይንገር አሁን ሞቱን እየተጠባበቀ የታሰረባት ክፍል ጉስ ፓኃኖ ነፃ ከመወጣቱ በፊት ሲገደል ሲል የታሰረባት ክፍል ነበረች።››

ማክ አለስተር የቪክቶሪያን ገጽታ ሊያነብ ንግግሩን አቆመ፡ የቪክቶሪያ ፊትም ወዲያውኑ ተለዋወጠ። ‹‹ባባኝ›› አለች፣ ‹‹ይንገርን በቀጥታ ማግኘት እስካልቻልን ድረስ አሁን እሚሰማውን ስሜት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በዚያው ክፍል የሞት ቅጣቱን ሲጠባበቅ ከነበረው ከጉስ ፓኃኖ ልናውቅ እንችላለን።››

‹‹ደርሰሽበታል። የጉዳዩ ምንጭ ጉስ ፓኃኖ ይሁን። የፓኃኖ ፍንጭ ሲይንገር ይሞል።››

‹‹ጉስ ፓኃኖን መቼ ላገኘው እችላለሁ?››

‹‹በማናቸውም ጊዜ። አሁን እንዲያውም ወደዚህ እየመጣ ነው። እሱ ራሱ ከሱ ምን እንደምንፈልግ ያውቃል። በሚቀጥለው ክፍል በሚገኘው የስብሰባ አዳራሻችን ውስጥ ልታነጋግሪው ትችያለሽ። ስለይንገር ወንጀሎች የሚያትት ፋይል ይኸውልሽ። ስለሱ ለማወቅ ይረዳሻል። ጉስ ፓኃኖን አነጋግረሽ እንደጨረስሽ ታሪኩን ዋፊ። ታዲያ ከስምንት መጭ ኃላት እንዳይበልጥ። ዛሬውኑ ከሰዓት በኋላ ለኔ አትርቢልኝ።›› ወደበሩ እንድትወጣ አሰናበታት። ‹‹መልካም እድል እንግዲህ፤ ወጣቷ እመቤት።››

* * *

ጉስ ፓኃኖ የሰላሳ አምስት ዓመት ልጅ እግር፣ ሎጋ ቁመና ያለው የፊልም ተዋናይ ይመስላል። ከተገለጠው ሸራቡ ላይ ጡቱ አካባቢ መነጽር አንጠልጥሏል። አፈኛና የባንኮኒ ሰው መሆኑን ከከንፈሩ ድርቀት፣ ከአመ ዳግሙ መልኩና የዝንጀሮ ቲየ ከመሰሉት ቀይ አይኖቹ መረዳት ይቻላል።

ልክ ቪክቶሪያን ሲመለከት ሾጠጥ ያለውን ባርኔጣውን አውልቆ በክቡ የስብሰባ አዳራሽ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳ። ‹‹ጉስ

ፓኃኛ እባላለሁ›› አለ፣ ‹‹በሪኮርድ ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ ካቀረቡልኝ ውስጥ አንቺን አይቸሽ አላውቅምሳ?››

‹‹አዲስ ነኝ፣ ሚስተር ፓኃኛ፣›› አለችው ቪክቶሪያ። በክቡ ጠረጴዛ ዙሪያ ስምንት ወንበሮች ቢኖሩም ጉስ ፓኃኛ ግን ከቪክቶሪያ ቀጥሎ ባለው ወንበር ላይ ጉብ አለ።

‹‹ስለ ላም ይንገር እየፃፍሽ ነዋ?›› አላት፣ ‹‹ለመሞት መዘጋጀት ምን እንደሚመስል ልትነግረኒ ነው አሉ?››

‹‹የኤሊክትሪኩን ወንበር መጠላበት፣ ሞትን ማሰብና የዴዝ ሮው የእስር ክፍል ምን እንደሚመስል ለመዘገብ አፈልጋለሁ።››

‹‹ነም ይንገርን ሊያጣፍት ስለማይችሉ እኔ የማውቀውን ሊያቀናብሩ ይፈልጋሉ።››

‹‹ልክ ነሙ፣›› አለችው።

‹‹የሞት ፍርድ ተላልፎብኝ በዴዝ ሮው ክፍል ከታሰርኩ በኋላ መፈታቴን ነግረውሻል። አይደል?››

‹‹ሰምቻለሁ።››

‹‹አም፣ አሁን ይንገር የታሰረላት ክፍል የኔዋ ክፍል ነበረች። እዪሽ፣ ያኔ እኔን ከሚሰማኝ ስሜት ተነስቼ ዛሬ ይንገር ምን እንደሚሰማው ልነግርሽ አልችልም። የኔው የተለዩ ነበር። እኔ ባልፈጸምኩት ወንጀል የታሰርኩ ሰው ስለነበርኩ ስሜቴን ይህንኑ ፍርደ ገምድልነት የሚመለከት ነበር። ሁለመናየ በእርሮ ተኮማትሮ ነበር። የይንግሩ ደግሞ ሊላ ነው። እሱ ወንጀለኛ ነው። የፈፀመውን ወንጀል ታውቂያለሽ፣ አይደለም?››

‹‹የተመሰረተብትን ክስ ከሪኮርድ ጋዜጣ አንብቤአለሁ›› ስትል ባጭሩ መለሰችለት። ፓኃኛ ራሱን ነቀነቀ። ‹‹የተለከፈ ቀውስ። መጀመሪያ ከዚያች ሴት ጋር መጨመቱ። ማ ነበር ስሟ. . . ?››

‹‹ካሮሊን።››

‹‹አም መምህርት ካሮሊን። ይንገር ሁለት ጊዜ ካወጣት በኋላ በዘነጠቁን

አይታ ሠር በል ትለዋለች። ሲደውልላት ትዘጋዋለች። አንድ ምሽት ካንድ ወንድ ጋር እጉል ቦታ ያያትና ትናት ይፈሰፍሰዋል። በማግስቱ ስድስት ሕፃናትን እንግሊዝኛ ከምታስተምርበት ትምህርት ቤት ይሄድና ካሮሊንን ብቻ ሳይሆን ስድስቱንም ሀፃናት ጨምሮ በአውቶማቲክ ይገድላቸዋል።››

‹‹ሁሉንም አውታለሁ›› አለችው ቪክቶሪያ።

ጉሰ ፖጋኖ ቪክቶሪያን ችላ ብሎ ትረካውን ቀጠለ። ‹‹አምልጦ ነበርኮ። ብቻ አንዱ ሰንበትበት ብሎ አየው።›› ፖጋኖ አሁንም ራሱን ነቀነቀ። ‹‹ልክ እኔ እንደተፈታሁ እኔው እስር ቤት ታሰረ። እሱኮ የሁላችንንም ሰም የበከለ አረመኔ ነበር።››

‹‹የኑሮው ሁኔታ ምን ይመስላል? እንዴት ይኖራል? ጊዜውን እንዴት ያሳልፋል?››

ጉሰ ፖጋኖ ጋዜጠኛዋ ቪክቶሪያ ማስታወሻዋን ገልጣ ብዕሯን እስከታዘጋጅ ዝም ብሎ ቆየና ገለጣውን ቀጠለ። ‹‹ዴዝ ሮው ኪ ጋለሪ ከሚባለው አዳራሽ ጎን ነው የሚገኘው። ያ እኛና አሁን ሳም ይንገር ያለበት ክፍል። ምን ብየ ልንገርሽ፣ እስር ቤት ያው እስር ቤት ነው። ምን እንደሚመስል በፊልም እንኳ ሳታይ አልቀረሽም።››

‹‹አዎ፣ ግን እርስም እንዲገለፁልኝ አፈልጋለሁ።››

‹‹ጠበብ ያለ ደብዛዛ ክፍል ነው። መተሙጫ የሌለው ሽንት ቤት አለው። ውሃና ሊሎች አንዳንድ ነገሮችም አሉት። ክፍሉ መፈት ውስጥ የተቆፈረ እንደመሰሉ ዘበኛው የሚቆጣጠርሽ ከጣራሽ ላይ እየተንሳደደ ነው። ታዲያ አንቺን ቁልቁል የሚመለከትባት ቀዳዳ ከጣራሽ ላይ አለች። በርግጥ ሊሎች እሥረኞች የሚያገኙትን አንቺ አታገኝም።››

‹‹ማለት እንዴት?›› ቪክቶሪያ አቋረጠችው።

‹‹ማለት ምግብሽን ከሊሎች ጋር በምግብ ክፍል አትበይም። ራሽንሽ ራስሽ ክፍል ድረስ ነው የሚመጣልሽ። ሲጋራ ይሰጥሻል፣ ከብራት ግን አይፈቀድልሽም። የሚለኩስልሽ ዘበኛው ነው። ቁምጣ እንጅ መሉ ሱሪ አይፈቀድም። ፎጣ የምታደርጊው ያለእግር ሽራብ ነው። ለሊትሽ ምላጭ

ልትዋሽ ትችያለሽ፣ ግን ኩነላጪሽ በኋላ መመለስ ግዴታሽ ነው።››

‹‹ዘበኖቹ ከክፍላችሁ እንድትወጡ ፊቅደውላችሁ ያውቃሉ?››

‹‹በቀን አንድ ሰዓት ለመፍታታት፣ እና ጠያቂ ሲመጣ።››

‹‹ጠያቂም ይፈቀድላችኋል?››

‹‹አሮጊቷ እመቤቴና ታላች እህቴ ይጠይቁኝ ነበር። ጠበቃየም እንዲሁ ብቅ ይላል። ደሞም ሐኪምና የአሮጊቷ እመቤቴ የነፍስ አባት። ሌላ ጠያቂ ግን የፍርድ ቤት ፈቃድ ያስፈልገዋል።››

‹‹ጊዜዎን እንዴት ያሳልፉ ኖሯል ሚስተር ፖጋኖ? ማለቴ የተወሰነብዎ የሞት ቀን ከመድረሱ በነበሩት ቀናት?

‹‹እኔ? እኔ እንኳ የተለየሁ ነበርኩ። መጻሕፍትን በአብዛኛው የሕግ መጻሀፍትን አነብ ነበር። አንዳንድ ነገሮችን፣ ማመልከቻዎችንና ደብዳቤዎችን ለፕሬስ እጽፍ ነበር። ለሌላ ነገር ጊዜ አልነበረኝም። ሳም ይንገር ግን አንድም መጽሐፍ እንደማያነብና አንድም ነገር እንደማይሰራ ይሰማኛል።››

‹‹ጋዜጣስ የሚያነብ ይመስልዎታል?››

‹‹ጋዜጣ አይፈቀድም። እንደምገምተው ብዙ ጊዜ ቴሌቪዥን ይመለከት ይሆናል።››

‹‹ቴሌቪዥን?›› ጠየቀች ቨኑቶሪያ፣ ‹‹ቴሌቪዥን ክፍላችሁ ድረስ ያቀርቡላችኋል ማለት ነው?››

‹‹እንዴታ። አልነገርኩሽም? እስር ቤቱኮ የሰለጠነ ሲኦል ነው። ወደ ነጥቡ እንመለስና ትርፍ ጊዜየን በሙሉ እንዴት እንደማሳልፍ አልጨረስኩልሽም።››

ቅንድቧን ከፍ አድርጋ ‹‹አልገባኝም። የምን ትርፍ ጊዜ?›› ስትል ጠየቀችው።

‹‹ጥቂት ትርፍ ጊዜ ነበረኝ›› አላት በሚስጥራዊ አነጋገር። ‹‹ለመሆኑ ባፈሰስ ትፈቅጅልኛለሽ?››

የክብራቱን ነበልባል ወደሲጋራው ሲያስጠጋ እቧም መኮርኮሻውን ገፋ አደረገችለት። ሲጋራውን በጥልቀት ማገና አንድ ነገር ለመናገር ሲያትማማ ቆይቶ በመጨረሻ ተንፍሶት አረፈው። ‹‹አንድ ኮሚክ ነገር ላልነግርሽ›› አለ። የአነጋገሩ ቃና ከስተር ማለቱ ያስታውቃል። ‹‹ኮሚኩ ነገር እኔ ብፈልግ አሁን ላም ይንገርን እንዲያመልጥ ላደርገው እችላለሁ።››

‹‹ይችላሉ? እንዴት?››

ፓጋኖ ጥቂት አመነታ። ከሲጋራው ማገና ቪክቶሪያን የጎረጥ ተመለከታት። ‹‹በኔና ባንቺ ብቻ የሚቀር ሚስጥር ነው›› አላት ቀስ ብሎ፣ ‹‹ድምጽ መቅጃውን አጥፊውና ሚስጥር ላለማውጣት ቃል ግቢልኝ።››

‹‹ቃል ገብቻለሁ፣›› አለች እየተደነቀች።

‹‹በጣም ጥሩ፣ እነግርሻለሁ›› አለና ቪክቶሪያ ብዕሯንና ማስታወሻዋን እስክታስቀምጥ ይጠብቅ ጀመር። ከዚያም ፈጠን ብሎ በቀስታ ድምጽ ግለፃውን ቀጠለ።

* * *

ከሁለት ሰዓት በኋላ ለምሳ ሰዓት ጥቂት ሲቀረው ቪክቶሪያ ማክ አሊስተር ቢሮ ተቀምጣ የትርብ አለቃዋ ያቀረበችለትን የላም ይንገርንና የዲዝ ሮው ጥናታዊ ሪፖርት ሲያነብ የሚነበብበትን ገጽታ ታስተውላለች። ምክትል አዘጋጁ ማክ አሊስተር ማን ፊቱ ላይ ምንም ለውጥ ሳይታይ ንባቡን ጨርሶ ማስታወሻዋን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው።

‹‹በርግጥ ደሀና አቀናብረሽዋል›› አለ፣ ‹‹ማን. . .›› ያ ‹ማን› ያለው ቃል አየር ላይ ተንጠልጥሎ የቀረ ይመስላል።

‹‹. . .ይህ ነው ልልሽ አልችልም›› አለ ማክ አሊስተር ሲያጠቃልል። ‹‹በመሠረቱ ደካማ ጽሑፍ ነው። ነፍስ ያለው መረጃ አይደለም።››

‹‹ፓጋኖ የነገረኝን ሁሉ እንድም ሳላስቀር አቀናብሬአለሁ›› አለች ቪክቶሪያ በተከላካይ አነጋገር፣ ‹‹ችግሩ የፓጋኖ ነው። የሚነግረኝ ሁሉ በቂ አይደለም። በጭራሽ ላም ይንገርን የሚያውቀው አይመስለኝም፣ ስለሱ

ስሜትና ድርጊት ሊገልጽልኝ ይቅርና ስለእስር ቤቱም ምንም የተሰየ ነገር አልነገረኝም። በርግጥ አንድ ከሁሉም የሳቀ መረጃ ሰጥቶናል፣ ግን ልንጠቀምበት አንችልም።››

‹‹ልንጠቀምበት አንችልም? ለምን?››

‹‹ጋጋኖ ለህትመት እንዳይውል ብሏል። እንዳንጠቀምበት ቃል አስገብቶኛል››

‹‹ምኑን ነው እንዳንጠቀምበት ቃል የሚያስገባሽ?›› ማክ አሊስተር አፈጠጠ።

‹‹ከይንገር ክፍል በታች በእስር ቤት ዓሮ በኩል ስለተቆፈረው የማምለጫ ቱቦ›› አለችው።

‹‹ቱቦ ነው ያልሽኝ?›› ጆሮውን ተጠራጠረው።

‹‹አዎ፣ ከዴዝ ሮው ወደ ውጭ የሚያስወጣ ቱቦ።››

‹‹እውነተኛ ቱቦ?››

‹‹ብጉስ ጋጋኖ ገለባ መሰረት እውነተኛ ቱቦ ነው። ወህኒ ቤቱ እንደተሰራ የመጀመሪያው የዴዝ ሮው አስረኛ አንድ ሊገነጠል የሚችል የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ ያገኛል። ያ አስረኛም ያንን ቀዳዳ ተከትሎ ባገኘው አሮጌ መገልገያ እየቦረቦረ፣ ቆሻሻውን ባጠገቡ ባለው የመጋዘን ክፍል እየከተተ ይሞክራል። ግን ብዙም ርቆ ሳይቆፍር ይገደላል። ነገር ግን የሱ ክፍል ቀጥሎ ለሚታሰረው አስረኛ አንድ መልእክት ሊያስተላልፍ ችሎ ነበር። በዚህ አይነት እያንዳንዱ አስረኛ የበኩሉን መከራ በማድረግ እየቆፈረ በመጨረሻው ጉስ ጋጋኖ እዚያች ክፍል ይገባል። ጉስ ጋጋኖ በታሰረበት ጊዜ ቱቦውን ለማጠናቀት የሚቀረው ትንሽ ነበር። ጋጋኖ ደግሞ የሞት ቅጣቱ ብዙ ጊዜ የተላለፈለት ሰው ስለሆነና ጊዜውን የሚያሳልፈው በቡርቦራ ስለነበር ቱቦውን ሊያጠናቅት በቃ። በነፃ ካልተለቀቀ ቱቦውን ሊጠቀምበት ወሰኖ ነበር። ነገር ግን በነፃ በመለቀቁ ቱቦውን መገልገሉ አስፈላጊ አልነበረም። የሚተካው አስረኛ ሳም ይንገር መሆኑን ሲረዳ ለይንገር ምንም ፍንጭ ላይተውለት ይወስናል። ይንገር መሞት አለበት

የሚል አምነት አለው።› ቪክቶሪያ ትንፋሿን ዋጥ አደረገች። ‹ይንገር የማምለጫ መንገድ አለለት፣ ግን መንገዱን አያውቅም። እንዴት ያለ ታላቅ ታሪክ ነበር! ልንጠቀምበት አለመቻላችን እንዴት ያሳዝናል?›

የማክ አሊስተር አይኖች ተቀክለውባት ቀሩ። ‹ያሳዝናል› አለ እሱም፣ ‹ታዲያ አንችም እንደማንጠቀምበት ለፓንኖ ታል ገብተሽለታላ?›

‹አዎ፣ ምየለታለሁ።›

ፈገግ አለ። ‹መልካም፣› አለና ብድግ አለ፣ የቪክቶሪያን ሪፖርት ከጠረጴዛው አያነሳ። ‹የጻፍሽውን ሪፖርት ለኤድዋርድ ልዩ ረዳት ለሃሪ ዴትዝ ማሳየት አለብኝ› አላት፣ ‹ሪፖርትሽን ምን ማድረግ እንዳለብን አስተያየት ይሰጠኛል። ለጥረትሽ ላላመሰግንሽ አላልፍም። ነገ ሲላ የምትሰሪው ነገር እናዘጋጅልሻለን።›

ቪክቶሪያ እንደወጣች ማክ አሊስተር ስልኩን አንስቶ ደወለ።

‹አሲ ነኝ› አለ፣ ‹ለሁለት ደቂቃ መኖቼ ላንጋገርህ እችላለሁ?›

‹ጥቂት ልትቆየኝ ትችላለህ?› ሲል የሃሪ ዴትዝ ድምጽ በጥያቄ መለሰለት። ‹በጣም ስራ ይበዛብኛል።› ጥቂት ዝም ብሎ ቆዬና፣ ‹አስቸኳይ ነው?› ሲል ጠየቀው።

‹አስቸኳይ› አለ ማክ አሊስተር።

‹እሽ። አሁኑኑ እንገናኝ።›

ማክ አሊስተር ሃሪ ዴትዝ ቢሮ ሲገባ ሃሪን ያገኘው በስራ ተወጥሮ ሳይሆን ከማድማው መስታወት ፊት ለፊት ቆሞ ወጉሩን ሲያበጥር ነበር። የአሊስተርን መግባት ሲያይ ዴትዝ ማበጠሪያውን በኪሱ ከተተና ወደ ወንበሩ ተመለሰ።

‹እሽ አሲ?›

ምክትል አዘጋጁ የቪክቶሪያን ሪፖርት አቀረበ። ‹ከቪክቶሪያ ዊስተን የተረበ የመጀመሪያ ዝግጅቷ መሆኑ ነው። የሪፖርቱ ምንጭ ጉስ ፓንኖ ነው። እንድትመለከተው አፈልጋለሁ።›

ሃሪ ዴትዝ ማክ አሊስተርን እንዲቀመጥ ጋብዞት ሪፖርቱን ገረፍ ገረፍ አድርጎ ካነበበ በኋላ በቅፌታ ቡኮጨማደደ ፊት ሪፖርቱን መለሰለት።

‹‹የማይረባ ነው›› አለ ዴትዝ፣ ‹‹በርግጥ መጣፍ ትሸላለች። ምንም ጥንቡ እንዳላቀበላት ያስታውሳል። ግን ፓጋኖ መቼም ይህን ሪፖርት አስቸኳይ ብለህ ልታቀርብልኝ እንዳልመጣህ እርግጠኛ ነኝ።››

‹‹እርግጠኛ ሁን›› አለ አሊስተር ኮራ ብሎ፣ ‹‹በሪፖርቱ ያሳስቀመጠችውን አንድ ነገር ልነግርህ ነው የመጣሁት።››

ሃሪ ዴትዝ ትኩረቱን አሰባሰበ። ‹‹ቀጥል።››

‹‹ከሰም ይንገር ዴዝ ሮው ክፍል ጎን ለጎን የማምለጫ ዘዘ በድብቅ ሲቆፍሩ ከነበሩት መካከል አንዱ እሱ ራሱ መሆኑን ጉስ ፓጋኖ ነግሯታል። ይንገር ግን ስለ ዘዞው የሚያውቀው ነገር የለም። በርግጥ ፓጋኖ ሚስጥሩን ለቨክቶሪያ ያጫወታት መሀላ አስደርድሮ ነው።››

የሃሪ ዴትዝ አይኖች የበለጠ ጎለ። ‹‹ቀጥል ባክህ አሊ?››

አሊ ማክ አሊስተር በቨክቶሪያ በኩል ከፓጋኖ የተሳለፈውን ሚስጥር አንድ ባንድ ዘከዘከው። ትረካውን ሲያጠቃልቅም ከትከሻው ሽምቅቅ ብሎ ‹‹አንተ ልታውቀው የሚገባ ነገር መሰለኝ›› አለው እያመነታ።

ዴትዝ ተገናንቶ ተቀመጠ። ‹‹ትረካህን ጨረስህ?››

‹‹ከሰማሁት ያስተረፍኩት የለም።››

‹‹የሚገርም ነው›› አለ ሃሪ ዴትዝ፣ ቀጥሎም ከልቡ ፈገግ ብሎ፣ ‹‹አንተም በበኩልህ እንደሰማህ ወደዚህ መምጣትህ የሚያኮራህ ነው፤›› አለው።

‹‹አንተና ሚስተር አርምስቱድ ልታውቁት የሚገባ ነገር መሰለኝ።››

‹‹አዎ፣ እሱም ፍንጩን እንደሚያደንቀው እርግጠኛ ነኝ። ያንተን ፈጣንነትና ታማኝነትም እንደሚያደንቀው አልጠራጠርም።››

‹‹ከፍንጩ መረጃነት ምንም እንደማታደርጉ አውቃለሁ፤›› አለ ማክ

አሊስተር፣ «ግን ሁሉም ፍንጭ ሊደርሳችሁ እንደሚችል ገመትሁ።»

ሃሪ ዴትዝ ከፊት ስፊቱ የተገተረውን ምክትል አዘጋጅ አየት አደረገና «መቼም አንተና ሌላውም ሁሉ እንደሚጠብቀው የሪከርድ ጋዜጣ አመራር በመለወጡ የሰራተኛ ሹም ሽር መደረጉም የማይቀር ነው። አም፣ አንዳንድ አበይት ለውጦች መደረጋቸው አይቀርም። ሚስተር አርምስቲድ ቤቱን ሊያዘጋ፣ ማለትም አባቱ ሸፋፍናቸው የነበሩ ደካማ ሰራተኞችን ከሪከርድ ሊጠርግ ይፈልጋል። በዚህ እጀንዳ ስር የሰራተኛው የስም ዝርዝር ሲቀርብ የነፊውን አስተዋጽኦህን ከግምት ውስጥ አስገባዋለሁ። በርግጥ አንተው እንደ ጨረስከው አስተዋጽኦህ ወፊ ከማቀበል ሳያልፍ ይችል ይሆናል። ሆኖም ሆኖም፣ ትኩሳ ወፊ ማቀበል የምናደንቀውና የምንፈልገው ብቃት ነው። አዲስ ወፊ ሹክ ማለት በኛ ግምት ንቁነትን ማስመስከር ነው። ከኛ ጎን መሰለፍህን የሚያሳይ ምስክርም ነው። በዚህ መልኩ፣ ማለትም አይኖችህንና ጆሮዎችህን ለኛ ዓላማ ክፍት ማድረግህን ተጥል። በርግጥ በአፋጣኝ ሚስተር አርምስቲድ ነገሩን እንዲያውቅ አደርጋለሁ።»

እንጀራ ጋጋሪው ማክ አሊስተር የሚለው አልነበረውም። «አመሰግናለሁ ሃሪ፣» አለና በረጅሙ ተነፈሰ።

* * *

ኤድዋርድ አርምስቲድ ግዙፉን የቢሮ ጠረጴዛ በክርኑ ተደግፎ ግድግዳው ላይ የተሰቀለትን የዩኅዝላቪያ ጥንታዊ ሰዕሎች እየተመለከተ ሃሪ ዴትዝን ያዳምጣል።

ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ሃሪ ዴትዝ ሹክ የሚለውን ወፊ ጨርሶ አርሳሱን የላከ ቀለሀ መስሎ ተቀምጧል። «ይኸው ነው አለቃ፣» አለና ነገሩን እንደነገሩ ቋጨው።

አርምስቲድ በጆሮው የሰማውን በአእምሮው እያዋዛ ስዕሎቹ ላይ እንዳፈጠጠ ተረ። ቆይቶ ግን ፊቱ ፈገግ፣ ወግ ይል ጀመር። ወደ ሃሪ ዴትዝ መለስ አለና «ግሩም» አለ፣ «በጣም ግሩም ሃሪ።»

«ጋጋኖ የተናገረው ለሪከርድ እንዳልሆነ፣ ነገሩን በሚስጥር

እንድትጠብቅ ልጅነን እንዳስማላት መዘንጋት የለብንም›› አለ ሃሪ ዴትሚ እየተቆናጠረ።

የአርምስቱድ ፈጣሃትና ወጣታ በትጽበት ጠፍቶ የልዩ ረዳቱን ገጽታ አስተውሎ በመመልከት ሰውየው የሚናገረው ከልቡ ይሁን ቀልዱን የሚመራመር ይመስል ጀመር። ‹‹ጋጋኖ ከሪኮርድ የተደበቀ ነው አለ? ከልብህ ነው ሃሪ? የማናውቱ ነው ጋጋኖ? ትናንት አንተን ከጣጂ ያወጣነው ሽለመጥማጥ። ይዘትበት ጋጋኖ። ‹ከሪኮርድ የተደበቀ› እያለ ወሬ የሚያቀብለውን ከዛሬ ጀምሮ ልክ አስገቡልኝ።››

‹‹ታዲያ ፍንጩን ልታሳትመው ወሰንክ?›› አለ ሃሪ ዴትሚ የአለቃውን አይን ማየት ፈርቶ እየተሸኮረመመ።

‹‹ማሳተም ጀነብ ይግባ›› አለ አርምስቱድ ‹ከዚያ የበለጠም አለ›› የሰማውን ፍንጭ በአእምሮው አሰላሰለ፡ ‹‹መነሻው የሳም ይንገር እስር ክፍል፡ መድረሻው ነባነት የሆነ ጥቅም ላይ ያልዋለና ያልታወቀ የማምለጫ ቱቦ። ሳም ይንገር ነገ ይሆን ቢያውትስ?›› አርምስቱድ መንፈሱ ሁሉ ይትበጠበጥ ጀመር። ‹ተግባር፣ ተግባር፣ ተግባር! ‹‹የሚባክን ጊዜ የለም፣ ሃሪ። በእስቸኳይ የሳም ይንገር ጠበቃ ማን እንደሆነ አጣራ። ባስቸኳይ ደውልለትና ዛሬውኑ ማታ ባንድ ሰዓት ፔሪ ጉርድ መናፈሻ ድረስ ልጋብዘው እንደምፈልግ ንገረው። ኘሮግራም አለኝ ካለህ ሰርገህ በለው። የእው ቀጠሮ እንደሚበልጠው ንገረው።››

* * *

የይንገር መከላከያ ጠበቃ፣ ጆርጅ ታተም በተጠሮው ቦታ ፔሪጉርድ መናፈሻ ከመግቢያው በር በስተግራ በሚገኘው ባዶ ክፍል ብቻውን ተቀምጦ አሳታሚውን ኤድዋርድ አርምስቱድን ይጠባበቃል። አርምስቱድ የሳም ይንገር ፋይል ደንታው እንዳልሆነ ሁሉ ጠበቃው ጆርጅ ታተምም እንዲሁ የአለባበሱን ነገር ከጉዳይ የማይጥፍ ምሁር ይመስላል። እንዲያውም በእንዲህ ያለ ትልጥጥ ያለ ምግብ ቤት ሲገባ የመጀመሪያው ምሁር የመሰለው ይመስል ራሱን የታዘበው ይመስላል።

አርምስቱድ መጀመሪያ ራሱን እንደነገሩ አስተዋወቀና በንይል

አጨብጭቦ ጥንድ ዊስኪ በቀዝቃዛ ውሃ እዝዞ ከጠበቃው ትይዩ ተቀመጠ።

ጆርጅ ታተም ራሱ ስላዘዘው መጠጥ ሃፍረት የተሰማው ይመስላል። ‹‹ልጠጣ ስል ነበር የመጡት›› አለ፣ ‹‹ጥቂት ጠበቅሁ።››

‹‹ለመሆኑ ለምን እንደፈለግሁህና እንዴት እንደፈለግህህ አውቀሃል?›› አለ አርምስቱድ ፈጠን ብሎ።

‹‹የፊለጉኝ የሳም ይንገርን ጉዳይ በሚመለከት እንደሆነና ጉዳዩ ጥብቅ እንደሆነ ብቻ ነው የተነገረኝ›› አለ ጠበቃው ራሱን እየተጠራጠረ።

‹‹ትክክል ይመስላል›› አለ አርምስቱድ መጠጡን ከአስተናጋጁ እየተቀበለ። መጠጡን ቀመስ አድርጎ እያጣጣመ ከጠበቃው ጋር የሚያደርገው ውይይት በምን ዘዴ መካሄድ እንዳለበት ይተይስ ጀመር። ቀጥሎም ሲጋራ አቀጣጥሎ ማገና ከሮሱ አወጣጥ ጋር በተዋሃደ ታና ‹‹ለምን እንደፈለግሁህ ሳታውቅ አትቀርም›› አለው፣ ‹‹የኒውዮርክ ሪኮርድ ጋዜጣ አሳታሚ እንደሆንክ ማወቅህን አልጠራጠርም።››

‹‹በርግጥ አውቃለሁ።››

‹‹እንዲያው ለመሆኑ ከዚና ዘጋቢዎቹ አንዱ ወይም አንዷ ጉዳያቸውን ከምትከታተሉላቸው ተከሳሾች ባንዱ ወይም ባንዷ ላይ ያተኮበረችው ወይም ያተኮበረው የዜናዎች ዜና፣ አርእስተ ዜና እንዳለው ብነግርህ ምን ይመስልሃል? ይህ ዜና የተጠናቀረው ያ ባለጉዳይህ ከመገደሉ ከጥቂት ሰዓቶች በፊት ቢሆን ምን ይመስልሃል?››

የጆርጅ ታተም ምላሽ ፈጣን ነበር። ‹‹እኔ እንጃ›› አለ እያመነታ፣ ‹‹የማይቻል ነገር ነው የምለው።››

‹‹ጥቡም የማይቻል?››

ጆርጅ ታተም ወረድ ያለውን መነጽሩን ይበልጥ ወደ አይኑ አስጠጋና ‹‹ሚስተር አርምስቱድ›› አለ፣ ‹‹የሚናገሩት ፍፁም እንቆቅልሽ ነው።››

አርምስቱድ የጠበቃውን መልስ ያውቅ ስለነበር ለአነጋገሩ አዲስ አልሆ ነም። የሲጋራው ጭም የአምበላንስ መብራት እስኪመስል ምጓ አምበለጠጠ

ውና ‹‹ሠልካም›› አለ፤ ‹‹ባለጉዳይህ ነፃ ቢወጣ ምን ያህል ትፈልጋለህ?››

‹‹ነፃ ቢወጣ? ነፃ ሊወጣ አይችልምኮ። ይመሓት በቃ ተፈርዶበታል። ከነገ ወዲያ በኤለክትሪክ ወንበር ላይ ይቀመጣል። ሦኑን መሉ አገረ ገዢው የሚስተር ይንገርን ፍርድ ከሞት ቅጣት ወደ እድሜዘ ይፍታህ እንዲያሻሽሉት ለማድረግ ሰሯሯጥ ነበር የሞከሁት። አገረ ገዢው ግን አልተቀበሉንም። በኤለክትሪክ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ተፈርሞበታል።››

አርምስቱድ የሚናገራቸውን ታላት መግምግ ብቻ ሳይሆን ለካቸውና ‹‹ሚስተር ታተም›› አለ ፊጠን ብሎ፤ ‹‹የምጠይቅህ ባለጉዳይ ነፃ ይውጣ አይውጣ የሚለውን ጉዳይ አይደለም። ነፃ እንዲወጣ ምን ያህል ትፈልጋለህ? የሚል ነው የኔ ጥያቄ።››

ጆርጅ አሁንም እንደተምታታበት፣ እንደተወናበደ ነው። ‹‹ምን እንደሚሉኝ አልገባኝም ሚስተር አርምስቱድ። እኔ የሚስተር ይንገር ጠበቃ ነኝ። ወንጀሉን እከላከላለሁ። ተግባሬም እሱን ነፃ ማውጣት ነው፤ ስተፈረደበት አንተጽም ይግባኝ ብያለሁ። እስከ አገረ ገዢው ደርሻለሁ። ተግባሬን ፈጽሚአለሁ።››

‹‹ያንተን ተግባር እርሳው›› አለ አርምስቱድ። ‹‹ባለጉዳይህ በኤለክትሪክ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ትፈልጋለህ?››

‹‹በርግጥ አልፈልግም። መሞትም የለበትም። ጥሩና ንፁህ ሰው ነው ማለቱ ሳይሆን በምስክሮቹ ገለፃ መሰረት ወንጀሉን የፈፀመው በድም ፍላት እንጅ በቂም በቀል ባለመሆኑ ሊሞት አይገባውም። የተበየነበት ፍርድ ከሰብአዊነት ውጭ ነው።››

‹‹እና ነፃ ቢወጣ ፍላጎትህ ነው፤ እ?››

ታተም የሚሰጠውን መልስ አሰበበትና ‹‹እንዲገደል አልፈልግም›› አለ።

‹‹ከሞት ለማትረፍ በሚቻልህ ሁሉ ትደክማለህ?››

‹‹እሱማ ምን ጥያቄ አለው?›› የታተም ፊት ቁጥር ፊታ እያለ ነገሩ እንቆቅልሽ እንደሆነበት መሰከረበት።

‹‹አልጣኝም ሚስተር አርምስቱድ›› አለ።

አርምስቱድ ሲጋራውን መተርከሻው ላይ አስተመጠና ‹‹በቀላሉ እንዲህ ነው። የያንዣርን የሞት ፍርድ ልታከሽፍ ትፈልጋለህ። እኔ ቀረጻህ እችላለሁ። ላወጣው እችላለሁ›› ብሎት አረፈው።

‹‹ከኤሌክትሪክ ወንበር ሊያድኑት ይችላሉ?››

‹‹ከእስር ቤትም ላወጣው እችላለሁ።››

ጆርጅ ታተም ፈጽሞ ሊያምን አልቻለም። ‹‹እውነትዎን ነው?››

‹‹በጣም።››

‹‹ደግሚ ልንገርዎ መሰለኝ። አገረ ገዢው የሞት ቅጣቱን ቀን ጥቂት ፈቀቅ ለማድረግ እንኳ እምቢ ብሏል። ያንዣርን ከነገ ወዲያ የኤሌክትሪክ ወንበር ይጠብቀዋል። አማራጭ የለም።››

‹‹ልድግመልህ፡ ማምለጫ አለ።›› አርምስቱድ ቀልዱን ሊያቆም ፈለገ። ሲጋራውን አቀጣጠለና ቁርጥ ያለውን አረፍተ ነገር አስተመጠለት። ‹‹ወንጀለኛውን ከእስር ቤት የሚወጣው ከሆነ ቀደም ብለህ የኔ ሪፖርተር ከታሰረበት ክፍል ገብቶ እንዲያነጋግረው ልታደርግ ትችላለህ?››

ጆርጅ ታተም ራሱን ከፍ ዝቅ አደረገ ‹‹በዚህ ሁኔታ በርግጥ እችላለሁ። ሁኔታዎችን ላመቻችለት እችላለሁ። ዘወቹም ሆኑ ያንዣር ራሱ ለታሰ መጠያቂ እንዲተባበሩ አደርጋለሁ።››

‹‹ለዚህ ዋስትና ትሰጠኛለህ?››

‹‹አሰላለሁ። ግን የእርስዎ ታሳል ፈጽሞ የሚታመል አይደለም። ፈጽሞ የማያሠንና የማይመስል ነገር ነው።››

‹‹የማያሠነውና የማይመስለው ሚስጥሩን ለማያውቀው ነው›› አለ አርምስቱድ ፈርጠም ብሎ። ከዚያም ድምፁን በመጠኑ ዝቅ አደረገና ‹‹ሚስተር ታተም ቀረብ በልና በጥሞና አዳምጥ። ልብ በል፣ ሚስጥሩን አንድም ሳታሰቀር ለሳም ያንዣር ትነግራለህ፣ ለሌላ ሰው ትንፍሽ ብትል ግን

እኔን ጨምረህ ችግር ውስጥ ትከተኛለህ። መልካም፣ እንተ እስረኛህ ከሠኔ እንዲወጣ እኔ ደግሞ ሪፖርተሬ ወሰኔ ቤት እንዲገባ አፈልጋለሁ። ባጭሩ ይኸውልህ። ክሳም ይንገር ክፍል ጎን ቁልቁል አስወርዶ ወደ ውጭ የሚያዳርስ ዙሀ አ.ሠ አለው። ከዚያም ድምፁን የበለጠ ዝቅ አድርጎ ገሰፃውን ያለማቋረጥ ይዘረግፍለት ጀመር።

3

ሄራ ዴትዝ በግል የስጣት ስራ ቪክቶሪያ ዌስተንን ሲበዛ ረብሿታል። በረዘርድ ጋዜጣ ኮንትራትነት የተክራየችውን ቺቭሮሌት መኪና እየነዳች ሁለት ሰዓት የሚፈጅውን ጉዞዋን ተያያዘችው። ከሳም ይንገር ጋር ተግናኝታ ኦለመጠይቋን ለማትረብ ተጠር የተያዘላት ለዘጠኝ ሰዓት በመሆኑ ሰፊ ጊዜ ስላላት የጥያቄዎቹን አይነት ለማተናበር ተመችቷት ነበር። ግን ምን አይነት ጥያቄዎች ናቸው የሚተናበሩት? የረበሻት ይህ ነበር። በደምና በስጋ ቅሞ ከሚንጠባጠብ፣ ነገር ግን ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ ከቆሙት በታች ከሚሆን ወንጀለኛ ጋር በሕይወቱ የመጨረሻ ሰዓቶች የሚተርቡ ጥያቄዎች ይዘት ጋዜጠኛዋን ግራ አጋብቷታል። ይህም መኪና ከመንዳቱ ተግባር ጋር ተዳምሮ ጥያቱ ለማውጣጣት አስቸግሯታል። በዚያ ላይ የገጠሩ ውበት፣ ኮረብታና ሸንተረሩ፣ ሚዳና ደኑ ትኩረቷን እየተጋራ ጉዞዋን ሳይተር አሰቸጋሪ አድርጎባት ነበር። ካሰበችው ጊዜ በፊት «ማሪን ሃሸን ማረሚያ ቤት» የሚል ሰፊ ጽሑፍ በትልቁ የተፃፈበት የበር ትስት ከጉዞዋ ገታት። ይህ ነበር ሳም ይንገር የታሰረበት ወህኒ ቤት።

መኪናዋን በእንግዶች መኪና ማቆሚያ አቁማ ከዋናው በር አጠገብ የሚገኘውን ደረጃ ሽቅብ እየወጣች ወደ ባለመሰታወት በሩ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገሰገሰች። መጀመሪያ መታወቂያ ካርዷን ማሳየት ነበረባት። ቁጥላ የጉሁ ሻንጣዋን አስፈትሻ በልዩ የመፈተሻ መሳሪያው በኩል አለፈች። የግራ እጅዋን አሻራ በሰውር ተለም አስመዘገበች። በመጨረሻ የተመደበላት ዘብ እየመራት ብዙ ጨለማ ክፍሎችን አልፈው ወዳንድ የጎብኝዎች ክፍል ደረሱ። እዚያ ደግሞ ሌላ ሽምበል ባሻ ግንባሩን ከስክሶ ተቀበላት። ከአጠገቡ

የእንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ቲሊቪዥን ካሜራ አየች።

‹‹እዚህ ተተምጠሽ እንድትጠባበቂ ነው መመሪያ የተሰጠን›› አላት የተመደበላት ዘብ፣ ከዚያም ወደ ሻምበል ባሻው አያመለከተ ‹‹እሱ ያንቺንና የእስረኛውን እንቅስቃሴ ይከታተላል። ማለቴ ምንም ነገር ለወንጀለኛው አለማተበልሽንና...›› እዚህ ላይ ዘቡ ንግግሩን ቆም አድርጎ ሲያቅማማ ከቆየ በኋላ ‹‹. . አዎ፣ ፍትር አለመስራታችሁን ይቆጣጠራል›› ብሏት አረፈው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሳም ይንገር ቀርቦ ከተደገፈችው ጠረጴዛ ትይዩ ባለው ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ታዘዘ። ይንገር ሁለቱም እጆቹ በካቴና ታስረው ከእግሩ ጋር የተቃፈዱበት ያነሰው ይመስል ሁለት ግዙፍ ዘቦች ተቸብበውታል። ይንገር በሁለቱ ዘቦች ቁመና እይነት ስላንዣበረችው ይሁን ከጠበቀችው አነስ አለባት።

ይንገር ከሙቦ ሲመለከቱት የከሰረ ሱቅ በደረቱ ከመምሰሉ በስተቀር ሰድስት ሀሳናትን ካስተማሪዎቻቸው ጋር የፊጂ ነፍሰበላ መሆኑን ማመን ይቸግራል። ይሁን እንጅ ገና ሁለቱ ዘቦች ለቀቅ አድርገውት እንደተመለሱ ካንደበቱ የወጡት የመጀመሪያ ቃላት ብቻዋን የምታነጋግረው እንደግስላ የተቆጣ አረመኔ መሆኑን ለቪክቶሪያ መሰከሩላት። ቁጭ እንዳለ ‹‹አነጋግር የተባልኩት አንቺን ነው እንዴ?›› አላት።

‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን እባላለሁ። የኒውዮርክ ሪኮርድ ሪፖርተር ነኝ። ታለመጠይቅ እንዳደርግልህ እንደምትፈቅድልኝ ተነግሮኝ ነበር።››

‹‹ፈቃደኛ አይደለሁም። ብቻ ለጠበቃዬ ስል እሺ።›› ይንገር አዝገመገመ፣ ‹‹ለምን እዚህ እንዳመጡኝ አይገባኝም። ለኔ ምናባቱ ያደርግልኛል? እግዜር ያሳይሽ ለማታነቢው ጋዜጣ ታልሽን ስም ብትባይ ምን ይለማሻል?››

‹‹ምናልባት እስከ ጧት እንድ ተዓምር ልታይ ትችል ይሆናል።›› ቪክቶሪያ ተባጠረች።

‹‹ወይጅ ባክሽ። ምንም ተአምር እንደማይፈጠር አንቺው ታውቂያለሽ። ያሰው አድል አገር ገዢው ነበር። አሱም ፍርዱን አጽድቆ ፈርሞበታል።

በቃ እንደሞትኩ ቁጠሪው። ሞቻለሁ።››

ቪክቶሪያ ነገሩን እንዴት መቀጠል እንዳለባት ቸገራት። በዚያም በዚህ ብላ የቃለመጠይቁን አስፈላጊነት ማሳመን ነበረባት። ‹‹አየህ ሚስተር ይንገር፣ በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ያለብን ሁላችንም ሟች መሆናችንን ነው፤ እንዲያውም እንተ በኔ አማካይነት ከመሞትህ በፊት ስሜትህን ለሕዝብ ማስተጋባት መቻልህ ሁላችንም ያልታደልነው ትልቅ እድል ነው። አንተኮ ስሜትህን ለጓደኞችህ፣ ለዘመዶችህና ለዓለም ማሳወቅ መቻልህ ነው። መቼም ጓደኞችና ዘመዶች ሳይኖሩህ አይቀሩም።››

‹‹እህት ብቻ። ለሊላ ለማንም ደንታ የለኝም።››

‹‹ፍቅረኛም?››

‹‹ለማንም ደንታ የለኝም። ካሮሊን ነበረች ሞታለች።››

‹‹ስለገደልካት እዝንሃል?››

ይንገር መልስ ከመስጠት ተቆጠበ።

ቪክቶሪያ ፊሯ ተላ እያለች ምሬቋን አዋዋጠችና ‹‹ሕፃናቱ. . . ለመሆኑ ስለሕፃናቱስ ምን ይሰማሃል?›› ስትል ጠየቀችው።

‹‹ማድረግ ነበረብኝ›› አለ ድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ።

‹‹ማድረግ ነበረብህ? ለምን?››

‹‹እንዴት ይጠፋሻል? የአይን ምስክሮች ሆነው እንዳይቀርቡ ነዋ። ግን ምንድን ነው ልዩነቱ። እነሱ ደሞ ኖሩ አልኖሩ ምን ዋጋ አለው? ምን እንደመታቸው እንኳ የማያውቁ. . . .››

ቪክቶሪያ ወንጀለኛው የሚናገራቸውን ታላቅ በማስታወሻ በማስፈር ስራ ላይ ስትጥለቀለቅ እሱ አፍጥጦ ተመለከታት።

‹‹ሰማሽ ወይ አመቤት፣ አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ። ልታላትሚው ትችያለሽ። ከሳም ይንገር አንደበት የወጣ ብለሽ ልታስለፍፊ ትችያለሽ። ስለሞት ጉዳየ አይደለም። ይህ አለም ስለቀረብኝ ምን

ይከፋኛል? ከሞትስ ባመልጥ የእድሜ ልክ እስራት ተፈረደልኝ ብዬ ልፈነጭ ማለት ነው? እማዬር ያሳይሽ፣ ሰው እንዴት እድሜህን በሙሉ ሁለት ባራት ሜትር ክፍል ቤት ውስጥ ታጉረህ ማሩ ሲባል ደስ ይለዋል? ሞት ማለትኮ ረጅም እንቅልፍ ነው። ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ምን እንደሚደረግ የማይታወትበት፣ እንቅልፍ። አይን የተጨፈነ፣ ጆሮ የተደፈነበት፣ ጠቅላላ ሕዋሳት ስራቸውን ያቆሙበት ሕይወት ነው። ሞት፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ፣ ድብን ያለ ረጅም እንቅልፍ። ሕልም የለ ሃሳብ የለ። ሁለመናው እረፍት... እርይታ። ሞ... ሆ፣ ሞትን እንዴት እፈራለሁ? ሳም ይንገር ሞትን ትንሣኤ እንደማይፈራ ንገረልኝ። ምን ይመስልሻል እመቤት?››

‹‹ጥሩ ፍልስፍና ነው።›› ቪክቶሪያ ማስታወሻዋን እያሣደፈች።

‹‹አም›› አለ ይንገር። ጥቂት አሰበና ደግሞ ‹‹ከሞት የከፋ ነገርም አለ። መኖርም አለ›› ካለ በኋላ ንግግሩን ገታና ‹‹ሕይወቱ ንውዚ ነበር›› አላት።

‹‹እንዴት?››

‹‹እኔ እንጃ።›› ሆን ብሎ ትውስታ ውስጥ ገባና ትረካውን ቀጠለ። ወላጆቹን አያውታቸውም። በእንለ ማውታ ልጅነቱን ፈጀው። አድጎም አልሆነለት። በትርምስናው ወደ ማጅራት መቺነቱ ሞካክሯል። በተረፈ የድለላ ስራ ነበር ክፍት ባጀቱ። ያም ሆኖ ራሱን ለማሻሻል የማታ ትምህርት መከታተሉን አልተወም። ትምህርት ግን ኑሮን ለማሻሻል አላገለገለውም። ደግት ከተማ እንደገባ የከባድ መኪና ሾፌር ሆኖ ተቀጠረ። ገንዘብ ሲያገኝ ደግሞ አያውትበትም። መዝናኛቱን፣ ሲኒማ ቤቱንና በተለይ ሴቶችን ያለትጥ፣ ያለመጠን ያበላል። ከሴቶች ያገኘው ቢኖር የአባላዘር በሽታ ነበር። ልቡ የፈተጻትና የወደዳት ብትኖር መምህርት ካሮሊን ነበረች፣ እሷንም ከወንድ ያላት። በታ፣ እሷም ሽረሞጠች ማለት ነው። የተረገመች የውሻ ልጅ...!›› እዚህ ላይ ንግግሩን አቋረጠና ‹‹የተገረመ ሕይወት ነበር›› አለ ቀጠለና፣ ‹‹ሊላ የምትፊልጊው መረጃ ይኖርሻል ወይዘሪት?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹አንድ ጥያቄ ይቀረኛል።››

‹‹ቀጥይ።››

‹‹ይገርመኛል። ስለውቺው ዓለም ዛሬ ምን ይሰማሃል? ሳላጠናቅቀው

ቀረው እያልህ የምትቆጭበት ነገር አለህ?››

‹‹ምንም። ሴት ማደን እንኳ በትቶኛል። አንቺን ራስሽን ወርት አልብሰው ቢያቀርቡልኝ እንኳ በሊላ መልኩ አልከጅልሽም።››

ቪክቶሪያ ሆን ብላ በዝምታ ቆየችና ‹‹እና ምንም የምትቆጭበት ነገር የለህም?›› አለች።

ያንገር በሃሳብ ተመሰጠ ቆየና ‹‹አዎ.. ኧም አንድ ነገር ነበረኝ›› አሉ። ሆኖም ምን እንደሆነ ከመናገሩ በፊት ረጅም ዐጥቃ ሰፈነ።

ብዕሩን ወረቀቷ ላይ እንዳሾለች ‹‹ልትነግረኝ ትፈልጋለህ?›› አለችው።

‹‹አንድ ነገር። ለአንድ ሰዓት አንኳ ብፈታና በከሱ ወቅት ያመናጨቁኝን ሁሉ ዋጋቸውን ብሰጣቸው አመኝ ነበር። በተለይ አንድ ሰው። ማለቴ የወረዳው አቃቤ ሕግ። ማ ነበር ስሙ?››

‹‹ሻን ዱሰንን ማለትህ ነው?››

‹‹አ.. ዎ አሉ። ረካሽ ዲቃላ። ፍርድ ቤት መጀመሪያ እኔን ሲያነጋግረኝ፣ በኋላ ደግሞ ለፖሊሮቹች መግለጫ ሲሰጥ ብትሰሚው ደምሽን ያፈላዋል። ትናንት እንኳን ለአገረ ገዢው የተናገረው.. ›› ከንፈሩን ነከሰ። ‹‹አዎ፣ ሻን ዱሰን። ምናምን ይተርፋውና ሳም ይንገር ከሕብረተሰቡ መተርፉት አለበት አለኝኮ። በኋላማ ይባስ ብሎ እንሰሳ አለኝ እንጂ። እግዜር ያሳይሽ እንሰሳ። ጸጋመኛ ሊላ ተከሳሽ ላይ እንደለመደው እንዳያንዛርጥ ባፍጢሙ በዘነበልኩት። በቃ መፈታትን የምሻው ለዚህ ብቻ ነበር። ያን ቀሽሽ ዱሰንን ለመግደል።››

ቪክቶሪያ በጽሑፏ ላይ እንዳተኮረች ብትሆንም ጭንቅላቷ ተወጥሮባ ታል። ስድስት አፈር ከእህል ያልለዩ ሕፃናትን ጭንቅላት በጥይት የፈረከሰ አረመኔ አሁን ደግሞ ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ የሚሰማኝ ቱሎት እንሰሳ ብሎ የሰደበኝን አቃቤ ሕግ አለመግደሉ ብቻ ነው ሲላት እንዴት ትቻለው?

‹‹ሊላስ?›› ጠያቂው ጭራሽ ይንገር ሆኖ ቱሎ አለ።

ቪክቶሪያ መጻፉን ጨርሳ ማስታወሻዋን በማጠፍ ላይ እንዳለች

ከጀርባዋ አንድ ድምጽ በመሰማቷ ደንግጣ ዞር አለች። ሻምበል ባሻዉ ነበር። «ስማ ሳም ይንገር፣ ለላ ጎብኚ ይጠብቅሃል።»

«ዞሀ . . . እገሪ ግርሙ ይሆናል።» ይንገር አሽሟጠጠ።

«ጠበቃህ ነው፣ ጅርጅ ታሁም። ሲሰናበትህ ሳይሆን አይቀርም።»

በዚህ ጊዜ ቪክቶሪያ ብድግ አለች። «መልካም። እንግዲህ ለጠበቃዉ ቦታውን ብለት ይሻላል። አመሰግናለሁ ሚስተር ይንገር።»

* * *

ቪክቶሪያ ወደ ግሪን ሃቨን መሀኒ ቤት የገባችው በብዙ ችግር ነበር። አልጣፊ የበለጠ አሰቸገራት። መጀመሪያ የለከፈቻት መኪናዋ ነበረች። ሞተር አልነሳ አላት። ባትሪዋን መጨረሷን ተረዳች። በመሀኒ ቤቱ ችግሩን የሚያቃልልላት አልነበረም። በስቶርምቪል ከሚገኘው ጋራዥ እርዳታ ማግኘት ይኖርባታል። ሞከረች። ነገር ግን ሁሉም የስቶርምቪል የጣና መኪናዎች ለስራ ወጥተዋል። በእማን ከተባለው ስፍራ ለሚገኝ ጋራዥ ደውላ እርዳታ እንድትጠይቅ ተነገራት። እዚያ ደግሞ ያለው የጣና መኪና አንድ ብቻ ሲሆን እሱም ለስራ ወጥቷል፣ ሆኖም ዶሎ ይመለሳል። እንደተመለሰም ይደርስላታል። እንድትታገስ ተነገራት።

ሁለት ሰዓት ጠብቃ መኪናው ሲደርስላት ጨለምለም ማለት ጀምሮ ነበር። እገሪ መንገዷን የሳም ይንገርን ታለመጠይቅ እያነበበች፣ መልሳም በእእምሮዋ እያመነገበች ለጽሑፉ የምትሰጠውን ርእሰ ሰታሰላስል ቆየች።

ከጣና መኪናው ጋር የመጣው ወጣት መኪናዋን ሲትረጉር ትእግስቷን አስጨረሳት። በመጨረሻ ሞተሩ ተነሳ። የተትበጠበጠችው ቪክቶሪያ እሁን የቀራት መሸምጠጥ ብቻ ነው። ሆኖም «ልሄድ እችላለሁ አይደል?» ስትል ወጣቱን ጠየቀችው።

«አይ፣ ከጓላየ ብትከተይኝ ይመረጣል። መኪናሽ ተጥታ ወደ ኒውዮርክ የሚያደርስሽ አይመሰለኝም፣» ብሎ ወሽመጣን ቆረጠው።

«ታዲያ ከጓላህ ብከፋልስ ምን ያደርግልኛል?»

«ጋራዥ እንደደረስን ባስቸኳይ ባትሪውን እሞላልሻለሁ።»

በዚህ ጊዜ ነበር ተልእኮዋ እንዳልተሳካላት የተረዳችው። ለጊዜው እንደነገሩ የተጠገነውን መኪናዋን ከከባድ መኪናው ጎላ እያስከተለች ወደ ጋራዥ ታዘግም ጀመር። ባትሪ መሙላት ብቻ እርባ አምስት ደቂቃ እንደሚፈጅባት ትገ አላት። በብሽቀት ብው አለች። አዲስ ባትሪ መግዛቱን መረጠች። ባካባቢው ያለው ብቸኛ የባትሪ መሸጫ ዘግ ነው። ምን ታድርግ? እም. . . ሪኮርድ ጋዜጣ ለማክ አሊስተር ለመደወል ወሰነች።

በብዙ ችግር መስመሩን እንዳገኘች በተትበጠበጠ መንፈስ የመኪናውን ብልሽትና የተልእኮውን መዘግየት አሰረዳች።

ማክ አሊስተር ቀዝቀዝ እንዳለ ካዳመጣት በኋላ «ለመሆኑ ምን ዓይነት ሪፖርት ብታገኝ ነው? ይንገር ጠቃሚ ነገር ነገረሽ?» ሲል ጠየቃት።

ስልኩን በጆሮዋና በትከሻዋ አጣብቃ ከበርሳዋ ማስታወሻዋን አወጣችና አልር አልር፣ ገረፍ ገረፍ አድርጋ አነበበችለት።

«ሙጥር አይደለም።» ምክትል አዘጋጁ መለሰላት። «ሆኖም ብዙም የሚጠቅም አይደለም።»

«በጣም ጠቃሚ ይመስለኛል» አለች ገንፍለባት።

«አይመስለኝም» አላት ረጋ እንዳለ። «ያም ሆነ ይህ ጥቂት ሳትዘገይ አልተረሽም። ብቻ አትጨነቂ። በቃ ስልክም አትደውይ። በደረስሽ ጊዜ ድረሽ።»

«እሺ ቶሎ እመለሳለሁ። ብቻ የሳም ይንገር ፎቶዎች ተፈልገው ተዘጋጅተው ይጠብቁኝ። መንገድ ላይም ቢሆን ወሬውን አቀናብረዋለሁ። ለሊሊቱ ጋዜጣ እንኳ ሊደርስ ይችላል።»

«ፎቶዎቹ ጠረጴዛሽ ላይ ይገኛሉ።»

«በጣም ጥሩ። አሁኑኑ እደርሳለሁ።»

ግን አልተቻለም። ቪክቶሪያ በስልክ ወሬውን እንዳታሰራጭ መከልከሏ

ያስደሰታት ቢሆንም ወዲያውኑ ደግሞ የጉዞዋ ዳተኛነት ይበልጥ አበሽቃት። የመኪናዋ ባትሪ መሞላት ትልቅ ግልግል ነበር። ጉዞዋን አጣዳ ከተማ ስትገባ ግን ፍጥነቷን እንድትቀንስ የትራፊክ ሕግ ያስገድዳታል። በዚያ ላይ ልክ ሃርለም የተባለውን ወንዝ ድልድይ እንደተሻገረች ጥልፍልፍ መንገድ አትጣጫዋን አሳታት። ደጋግማ መንገዱን በሳተች ቁጥር ወደ ድልድዩ መመለስ ነበረባት። መጨረሻ ላይ አንዱን አትጣጫ ይዛ ከነፈች።

ከተማ እንደገባች ካንድ ሳዕሠን ጥያ የእግረኛው መከማቸት ትኩረቷን ሲረብሸው። ከመኪናዋ ወረደች። ብዙ እስር ወረቀቶች ግራ ቀኝ የሚያከፋፍል ሰው ከዘ የቆመው ሕዝብ ብዛት ለጉድ ነው። እየሮኸ የሚናገረው ነገር በደንብ ባይሰማትም የይንገርን ስም የጠራ መሰላት። እየተጣደፈች ወደ ሰውየው ተጠጋች። ሰውየው የሚሸጠው ኒውዮርክ ሪከርድ ጋዜጣን ሲሆን በፊት ለፊቱ ገጽ ላይ በትልቁ የተፃፈውን ርእስ ዓይኗን ጎልጉላ አነበበችው።

ይንገር ከእስር ቤት አመለጠ። አንቀጠቀጣት። ተዋክባ ጋዜጣውን ለመግዛት አዲስ የተሰራውን ሰልፍ ያዘች። ከሪከርድ አጠገብ የሚታየው ታይምስ ጋዜጣ የይንገርን ስም ሞራሽን አልጠቀሰም። ከሪከርድ ዘግይተው የወጡት ኒውዮርክ ኒውስና ኒውዮርክ ፖስት ጋዜጦች እንኳ ይህ ወሬ እንዳልደረሳቸው አወቀች።

ኒውዮርክ ሪከርድ ብቻ ትኩሱን ዜና ተልዕኮል፣ ተራዋ ደርሶ አንድ ቅጅ እግኝታ ጣች።

አዎ! የይንገር የማይታመን ማምለጥ እውነትም ተጽፏል። በራት ሰዓት ላይ ክፍሉ ባዶ ሆኖ መገኘቱ፣ ማምለጡን በማስመልከት ቶሎ ሪፖርት ባለመደረጉ ብዙ ሐሜት እንደሚናፈስ፣ ዘበኞቹ በዴዝሮው የታሰረ ሁሉ ማምለጫ እንደለለው በመተማመን መዘናጋታቸው፣ ወንጀለኛው ግን እንደ የአየር ማናፈሻ ገንዋሎ እንደወጣ፣ ከወህኒ ቤቱ ጎን የሚገኝ ብዙ በማግኘቱ ተሸሎክሉኩ ሳያመልጥ እንዳልቀረ የተረበውን ዘገባ ላፍ አድርጋ አነበበችው። በዜናው መሰረት ይንገር መሳሪያም ሊይዝ እንደሚችልና ለሚቀርቡት ሁሉ አደገኛ ሳይሆን እንደማይቀር ታትቷል። አፈሩ ላይ የሊላ ሰው እግርና የወገንጃ ሰደፍ ጹላ ተግኝቷል። ሊላው ማስረጃ ደግሞ የይንገር የእግር ጹላ

ከወህኒ ቤቱ ግቢ ውጭ በደበብ በኩል ወደ ኒውዮርክ ከተማ ማምራቱን መጠቆሙ ነው።

ቪክቶሪያ ተበሳጨች። ይንገር ያን የማምለጫ ቁፋ እንዴት ሊያውቀው ይችላል? ከሪኮርድ ጋዜጣ ሰራተኞች ሚስጥሩን የሚያውቁ አሷና ማክ አሊስተር ብቻ ናቸው። ማክ አሊስተር ደግሞ ሚስጥሩን ከሪኮርድ መጠበቅ እንዳለበት ራሷ ነግራዋለች። ደግሞም ሚስጥሩን ለይንገር ለመንገር ምክንያትም ሆነ ችሎታ ሊኖረው አይችልም። እንዲህ ስታስብ ለሷ ለራሷ ሚስጥሩን ያተበላት ጉስ ፓጋኖ መሆኑ ትዝ አላት። አዎ፣ በርግጥም ጉስ ፓጋኖ። ድሮስ ፓጋኖ ወንጀለኛ እንደነበር እንዴት አጣችው? አዎ፣ ለገንዘብ ሲል ጉስ ፓጋኖስ ሚስጥሩን ሊያወጣ ይችላል፣ ያ ሚስጥር ደግሞ ለይንገር ለራሱ በተጥቃ ባይሆን እንኳ መጀመሪያ በዴዝ ሮው ለሚገኝ ለሊላ ወንጀለኛ ሊተላለፍና ያ ወንጀለኛም ለይንገር ሽክ ሊለው ይችላል። ይንገር በፍጥነት አጋጣሚውን ተጠቅሞበታል፣ ተሳክቶለታልም። ይህ ወሬ ደግሞ በሆነው መንገድ ለሪኮርድ ደርሷል።

በሊላ ማዕዘን የሚገኘውን የጋዜጣ ማከፋፈያ ተመለከተች። የበለጠ ሕዝብ ከዩታል። የበለጠ ጋዜጣ ይሸጣል። ሆኖም የሚሸጠው ታላቁን ዜና የያዘው ጋዜጣ ነበር። ኒውዮርክ ሪኮርድ የላፊን ምሽት ገበያ ለብቻው እድርጎታል።

የሪኮርድ ጋዜጠኛ በመሆኗ ኩራት ሊሰማት ሞከረ። ወደ መኪናዋ እያዘገመች አሁን በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ከይንገር ጋር ያደረገችው ቃለመጠይቅ ምን ጠቀሚታ እንዳለው አሰላሰለች። ከመግደሉ በፊት የሰጠው ቃል አሁን ነፃ በመውጣቱ ፉርሽ ሆኗል። አዎ፣ ከእንግዲህ ቃለመጠይቁ ተንባቢ ዜና ባይሆንም ወሳንድ የምርምር ጽሑፍ የሚያንደረድር ዘገባ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ስለዚህ በፍጥነት መሄድና ታሪኩን ማቀናበር ይኖርባታል።

ታሪኩን ለማቀናበር እንደቋመጠች ጋዜጣው ትኩሱን ወሬ ከየት እንደ ቀለበው ለማወቅ እንደጓጓች መኪናዋ ውስጥ ዘው ብላ ኩርባውን በፍጥነት አሾረች። ወዲያው ግን የተጨናነቀው ትራፊክ በዝግታ እንድታሽከረክር

አስገደዳት።

ወደ አርምስቱድ ሕንጻ ስትቃረብ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሊሞላ ምንም አልቀረውም። ከይንገር ጋር ያደረጥችውን ታለመጠይቅ አርእስት ዜና በአእምሮዋ ደጋግማ ጽፋው፣ በአዲሱ የይንገር ሁኔታ እንኳ የሷ ጥንቅር ሊሰራ እንደሚችል አምናበታለች። ሰውነቷ በመላሉ ብዙም አልተረበሸችም።

ወደ አርምስቱድ ሕንጻ ከመድረሷ በፊት ያሰቆማት ቀይ የትራፊክ መብራት ታለመጠይቋን ለመጨረሻ ጊዜ በአእምሮዋ እንድትጽፈው ጊዜ ሰጣት። በሃሳቧ ከመጨረሻው አንቀጽ ላይ ደረሰች።

«ወንጀለኛው ከእስር ቤት ቢወጣ ሊሰራው የሚፈልገው ያልተጠናቀቀ ተግባር ይኖር አይኖረው እንደሁ ላቀረብንለት ጥያቄ ሲመልስ «ብፈታና በዘው ወቅት ያመናጨቁኝን ሁሉ ዋጋቸውን ብሰጣቸው አመኝ ነበር። በተለይ አንድ ሰው። ማለቴ የወረዳው አቃቤ ሕግ። . . አዎ፣ ቫን ዱሰን። ምናምን ይቀርፋውና ሳም ይንገር ከሕብረተሰቡ መቀርፋት አለበት አለኝኩ። በኋላማ ይባስ ብሎ እንሰሳ አለኝ አንጂ . . ዳግመኛ ሊላ ተከሳሽ ላይ እንደለመደው እንዲያንዛርጥ ባፍጢሙ በከነበልኩት። በታ መፈታትን የምሻው ለዚህ ብቻ ነበር። ያን ቆሻሻ ቫን ዱሰንን ለመግደል።» በእነዚህ የመጨረሻ ሰኮንዶች የቪክቶሪያ ጀርባ በተዝታባ ላብ ተዘፈቀ።

አሁን ይንገር ነፃ ሰው ነው። መሳሪያ እንደያዘና አንዳዙም ወደ ኒውዮርክ ሳይሆን እንደማይቀር ከሪኮርድ አንብባለች። ልክ ነው፣ ይንገር የሚታመን ሰው ከሆነ ወደ ኒውዮርክ የሚሄድበት አንድ የአነሳስ ዓላማ አለው። ለመግደል። በመግደል ለመበቀል። የወረዳውን አቃቤ ሕግ ቫን ዱሰንን ለመግደል። ይህን ሚስጥር የምታውቀው ደግሞ እሷ ብቻ ነች። አቃቤ ሕጉ ቫን ዱሰን ራሱ እንኳ የሚያውቀው ሚስጥር አይደለም።

ልክ የትራፊኩ መብራት አረንጓዴ ሲያበራ ቪክቶሪያ አትጣጫዋን ቀየረች። መኪናዋን በዝግታ እየነዳች የሕዝብ ስልክ ፍለጋ ግራ ቀኝ ታማትር ጀመር። ከብዙ ደቂም በኋላ በአንድ የምግብ አዳራሽ መግቢያ በር ላይ ሁለት የሕዝብ ስልኮች አዩች። አሁን ደግሞ ለመኪናዋ ማቆሚያ ቦታ ለማግኘት ትእግስት አስፈራሽ ፍለጋ ይቀራታል።

የመኪናዋን ሞተር አጥፍታ ዘላ ወጣችና ወደስልኩቹ ሮጠች። አንደኛው ስልክ አልተያዘም። ብዙ ዝርገር ሳንቲሞች በኪሷ እንዳሉ አርግጠኛ ነች። የቫን ዱሰንን አድራሻ አፈላልጋ ለሕይወቱ እንዲጠነቀቅ ማድረግ አለባት። በዚህ ሰዓት ደግሞ ቫን ዱሰንን ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

ወደ ማሠሪያ ደወለች። ስልኩ ሲነሳ ይሰማታል። ሆኖም የኦፕሬተሮች ማንብ እንዳገዳት ተሰማት። የሰው አጣዳፊ ተማባር የማይማባቸው ዳተኛና ብማን የሚያደርጉ ኦፕሬተሮች።

በመጨረሻ ከመንጀለኛ ፍርድ ቤት ሕንፃ ኦፕሬተሮች ጋር ተገናኘች።

‹‹የወረዳውን አቃቤ ህግ ቢሮ አግኙን እባክም?›› ቪክቶሪያ ለመነች። ‹‹ሚስተር ቫን ዱሰንን ማነጋገር አፈልጋለሁ። በጣም አስቸኳይ ነው።››

አብሻቂ ድምጽ መልሱን ነገራት። ‹‹የለም። ማንም የለም። እንዴ፣ ለመሆኑ በስንት ሰዓት ነው የሚደውሉት? ነገ ይሞክሩ።››

‹‹ነገ ምናልባት ጊዜው ያልፍ ይሆናል። እባክም የአንድ ሰው ህይወት አደጋ ላይ ሆኖ ነው።››

‹‹እሽ. . . ምናልባት የሚያነጋግርም ሊላ ሰው ላገኝልም እችል ይሆናል። በእቤቱታ ክፍል ከተቆጣጣሪው ጋር ላገናኝም። ይጠብቁ።››

የደወል ምልክት ይሰማታል። በመጨረሻው የወንድ ድምጽ ተሰማት። የተዳከመ ድምጽ። ‹‹በርግስ ነኝ። ከአቤቱታ።››

ቪክቶሪያ ድምጽዋን ሰክን ለማድረግ እየሞከረች ‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን እባላለሁ። የኒውዮርክ ሪኮርድ ዜና ዘጋቢ ነኝ። እጅግ በጣም አስቸኳይ ለሆነ ጉዳይ አቃቤ ሕጉን ማነጋገር አለብኝ።...››

አላስጨረሳትም። ‹‹አዝናለሁ የኔ እመቤት፣ የደወልሽው በስህተት ነው።››

‹‹እሪ ባክም ሚስተር ቫን ዱሰን ማግኘት አለብኝ። በጣም አሳሳቢ ነገር ነው። በእውነት።››

‹‹የምመክርሽ ነገ ጧት ቢሮአቸው እንድትደውይ ነው።››

‹‹ከመንገዱ በፊት ሊሞቱ ይችላሉ።››

‹‹ሁላችንም የመሞታችንን ቀን አናውቅም አመቤት›› አለ ሱፐርቫይዘሩ እየሳቀ፣ ‹‹በርግጥ የሚያሳምን እቤቱታ ካለሽ. . .››

በተራዋ አቋረጠችው። ‹‹የኔ እቤቱታ አታቤ ሕጉን ለማግኘት የሚተባበረኝ ማጣቱ ነው።››

‹‹ዛሬ አግኝቸዋለሁ ብለሽ እንደሁ ከንቱ አትድከሚ። ፕላዛ ሆቴል በከንቲባው የራት ግብዣ ላይ ናቸው።››

‹‹የት?››

ያንኑ ደገመላት። ፕላዛ ሆቴል።

ቪክቶሪያ በትዙ ምስጋና ለማቅረብ እንኳ ጊዜ አልነበራትም። ሰልኩን በታይል ዚንችና አሰበች። ወደ ፕላዛ ሆቴል በእግሯ ለመሮጥ እንኳ ሩቅ አይደለም። በእንዲህ አይነቱ የጥድፊያ ጊዜ ግን አገር አቋራጭ ርቀት ከመሮጥ አይተናነስም። ወደ መኪናዋ ስትንደረደር ሄደችና ወደ ፕላዛ የሚያደርሳትን አቅራራጭ መንገድ ልታግኝ ሞከረች።

በአስራ ሁለት ደቂቃዎች ውስጥ መንገዱን ፉት ማለት ብቻ ሳይሆን መኪናዋን አቱማ በሆቴሉ መግቢያ በር ላይ ናት።

ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ነው። የከንቲባው ግብዣ እየተጠናቀቀ ሳይሆን አይተርም፣ ተጋባዥ በመውጣት ላይ ነው።

በደመ ነፍስ የምታውቀው ሰው ፍለጋ አማተረች። በተለይ የታወቀ ሰው ብታገኝ ትመርጥ ነበር። የደንብ ልብስ የለበሰ ፖሊስ ላይ አይኖቿ አረፉ። ወጋ አለችና፣ ‹‹እባክሞ ይተባበሩኝ?›› አለችው።

የሚርበተበተው ገጽታዋ ፖሊሱን ሳያስገርመው አልቀረም።

‹‹ምን ችግር አለ ወይዘሪት?››

‹‹የወረዳውን አታቤ ሕግ፣ ቫን ዴሰንን ማነጋገር እፈልጋለሁ።››

‹‹እትዮልጅ አመቤት። ከከንቲባው ጋር መድረክ ላይ ናቸው፣ ማንም እንዳያናግራቸው ከልክለዋል።. . .››

‹‹እባክም ይስሙኝ?. . .››

‹‹አዝናለሁ ወይዘሪት።።።››

ቪክቶሪያ ታክታት። በረጅሙ ተነፈሰች። በዚያው ቅጽበት ማን እንደ እድል ሆኖ አንድ ወጣት ሲመለከታት አየች። አረማመዱም ወደሷ መሆኑን አረጋገጠች።

‹‹ይቅርታ አድርጊልኝ፣ የሪኮርድ አዲስ ሪፖርተር ቪክቶሪያ ዊስተን እንቺ መሰልሽኝ፣ እ?››

‹‹አዎ።።››

‹‹ትናንት ከኢከ. . . ኢከ ራምሲ ጋር አግኝቻችሁ አስተዋውቆን ነበር። ልድገምልሽና ጄም ፐርዲ እባላለሁ። በዚያው በሪኮርድ የከተማ ዝማጅት ክፍል ውስጥ ነኝ። እዚህ ምን ትሰሪያለሽ?››

ወጣቱ የሞት ማርከሻ እንደሆነ ሁሉ ከንዱን አፈፍ አደረገችው። ‹‹ስማኝ ጂም፣ ልትረዳኝ ትችላለህ። ባሁኑ ደቂቃ ቫን ዱሰንን ማግኘት አለብኝ. . .››

‹‹አሁን እንኳ የሚቻል አይመስለኝም። ልትቆይ አትችይም?››

‹‹የለም አልችልም። ምን እንደተፈጠረ ትሰማኛለህ?›› ስለ ሳም ይንገር የተከሰተውን ሁሉ ከትንፋሿ ጋር እየታገለች ዘበዘበችለት።

ጂም ፐርዲ ወዲያው ሃሳብ ገባው። ‹‹በርግጥ አቃቤ ሕጉን እንደሚፈልጋቸው ራሱ ተናግሯል? አመንሽው? ምናልባት ለዘገባሽ ሲል ደስኩሮልሽ እንዳይሆን።።››

‹‹አንተ በስፍራው ኖረህ ብትሰማው ኖሮ ታምነው ነበር። ያም ሆነ ይህ ቫን ዱሰን ሊሰሙት ይገባል። እሳቸውን ሊያነጋግር የሚችል ሰው ታውትልኛለህ?››

‹‹እስኪ ላስብበት።።።››

ጂም ፐርዲ ወደ አዳራሹ በር ሄዶ ከፖሊስ ዘቦች ጋር ሲያንሾካሾክ፣ በር ሲከፈትለትና ወደ ውስጥ ሲመለከት ቪክቶሪያ አስተዋለችው። ጥሩ ጥሩ

የለበሱ ሰዎች አዳራሹን ሞልተውታል። ራት ካለው መድረክ አካባቢ ያሉ ሰዎች ቆመዋል።

ጂም ፐርዲ ወደ ቪክቶሪያ መለስ አለና፣ «ቫን ዱሰን ከንቲባውን ተሰናብተው ከመድረኩ እየወረዱ ናቸው። እስኪ ሳኒማግራቸው እችል እንደው ልሞክር፣ ጠብቂኝ» ብሏት ወደ ፊስጥ ገብቶ አቃቤ ሕጉ ሳይሆን እይተርም ተጠን ብሎ ዘለግ ያለ አንድ ሰው ከብዙ ሰዎች ጋር ሰላምታ እየተለዋወጠ ከወደ መድረኩ ወደ መጨረሻው በር ወደሚያመራበት አትጣጫ ገሰገሰ። አዳራሹ መሃል ላይ ቁሞ ሰላምታ እንደማትረብ አይነት እየተሽከረመመ ሲቅበጠበጥ ቫን ዱሰን ሳንበሰ አለና የሚናገረውን አዳምጠ ሳይሆን አይተርም፣ ቪክቶሪያ ወደቆመችበት አትጣጫ ተመለከተ።

ዓቃቤ ሕጉ ወደ ቪክቶሪያ ሄዶ «ቪክቶሪያ ዊስተን አንቺ ነሽ? ጂም ፐርዲ ከኔ ጋር አንድ አሳሳቢ ጉዳይ እንዳለሽ ነግረኝ። ሳም ይንገር እኔን ሊገድል ይፈልጋል? አልገባኝም. . .»

«ይንገር ማምለጡን ሰምተዋል?»

«ከወህኒ ቤቱና ከናንተው ጋዜጣ ወሬው ደርሶኛል፣» አለ።

«ላፊ ከሰዓት በኋላ ለወንጀለኛው ቃለመጠይቅ እድርጌለት ነበር። ከእስር ቢወጣ ምን ማድረግ እንደሚመኝ ጠየቅሁት። ለነፃነቱ የሚቆምበት አንድና ብቸኛ ምክንያት እርስዎን ለመግደል መፈለጉ መሆኑን ነግረኝ።»

ቫን ዱሰን ኮስተር አለ። «በርግጥ ይህን ተናገረ?»

«ማስታወሻየን ላሳይዎ እችላለሁ። ከራሱ አፍ የወጣውን ቃል አሰፍሬዋለሁ።»

«ከልቡ ይመስልሻል?»

«ይመስለኛል። ስድስት ሕፃናትን ያረደ አረመኔ ነውኮ።» ቪክቶሪያ እምነቷን ለማሰላሰል ሞከረች። «ከልቡ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ። ፍርድ ቤት እንሰላ ብለው ስለጠሩት መርዞ ይዘምታል።»

«እውንም ቢሆን መታገ አህያ ነው፣» አለ ቫን ዱሰን።

«ታዲያ እውንኮ ከእስር ወጥቷል» ቪክቶሪያ መለሰች።

የወረዳው ዓቃቤ ሕግ ከአዳራሹ በመውጣት ላይ ወዳለ አንድ ሰው ተመለከተና የቪክቶሪያን እጅ በምስጋና ጨብጠ ‹‹ላላመሰግንሽ አላልፍም ወይዘሪት። የፖሊስ አዛዡ እየመጣ ነው። ጥበቃውን እጥፍ ያደርግልኛል። ዋቂት ተጨማሪ ጊዜ ልታጠፊልኝ ትችያለሽ? ለኔ የነገርሽኝን ለፖሊስ አዛዡም ብትደግሚለት። አሁንም አመሰግንሻለሁ። ሕይወቴን አትርፈሽልኛል።››

* * *

የሰራ አካላቷ በጥድፊያ ብዛት የደከመው ቪክቶሪያ በአርምስቱድ ሕንፃ ደርሳ ሰራተኞች አልፎ አልፎ ተንጠባጥበው ከሚገኙበት የሥራ ክፍል ስትገባ መንፈቱ ሊሊት ሊሆን የቀረው በጥቂት ደቂቃዎች የሚቆጠር ጊዜ ነበር። ጊዜው ከማለፉ በፊት የይንገርን ታሰመጠይት ለማጠናቀር ጥንካሬውን እንዲሰጣት እየፀለየች ማስታወሻውን ከቦርሳዋ አወጣች።

መቀመጫዋ ላይ ስትደርስ ወንበሩ ተይዞ አገኘችው። ያ ግዴለሽና ምናልባትም መጠጥ ያነፈዘው ኒክ ራምሲ እንድ እግሩን እጅ መደገፊያው ላይ አውጥቶ ከወንበሩ ጋር ግራ ቀኝ ይናጣል።

‹‹ለክብርት ሎይስ ሌን ወንበሩን አሙቱ ልጠቁት ብየ ነው›› ሲል ተለጻት።

‹‹አመሰግናለሁ›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹አሁን እስኪ ላስቸግርህ። የማጠናቅረው ታሰመጠይት ነበረኝ።››

‹‹አሱን ተይው፣›› አላት እያሾፈ።

የቪክቶሪያ ትንድቦች ተነሱ። ‹‹ምን ማለትህ ነው?››

‹‹ታሰመጠይትሽ ተሰርሟል›› አለና ገላገላት።

‹‹ለምን?››

‹‹የበለጠ ትኩስ፣ የሚፋጅ ዜና ሲገኝስ። ያንቺው ታሰመጠይት አሁን ጊዜ ያለፈበት አሮጌ ሆኗል።›› ራምሲ እንዲህ እየተናገረ እግሩን ከመደገፊያው አወረደና ተስተካክሎ ተቀመጠ። ‹‹ሳም ይንገር ሞቷል።››

‹‹ምን?›› ቪክቶሪያ ጆሮዋን ተጠራጠረች።

ራምሲ ብድግ አለ። ‹‹ጂም ፕሪዲ ከአቃቤ ሕጉ መኖሪያ ቤት ከአምሳት ደቂቃዎች በፊት ደወለልን። ቫን ዱሰን ከከንቲባው ግብዣ በመመለስ ላይ ነበር። ሳም ይንገር ጠመንጃውን አነጣጥሮ በደረቱ ተኩሶ ይጠብቅ ኖሯል። የዓቃቤ ሕጉ ዘበኞች ቀድመው ነፋት። በደረቱና ባናቱ ከደርዘን በላይ ጥይቶች ሳያከቡበት አልቀሩም።›› ራምሲ ፈገግ አለ። ‹‹አመሰግናለሁ›› ነበር የመጨረሻው ቃሉ።››

ቪክቶሪያ የነገሮች ተደራርቦ መከሰት ሲበዛ አስደንቋት ራሷን ግራ ቀኝ ነቀነቀች።

‹‹በጂም ፕሪዲ አምድ ላይ ሰፍሯል። ‹የሪከርድ ልጃገረድ ዘጋቢ የአቃቤ ሕጉን ሕይወት አዳነች› ይላል፣ ቫን ዱሰን ምስጋናውን በግል ላንቺ አትርፏል።››

‹‹ግን ቃለመጠይቁስ? አሁንም ቢሆን የማጠናቅረው ዝግጅት ይኖረኛል።››

‹‹አሮጌ ዜና ውድ ቪኪ። ካንቺው ቃለመጠይቅ በኋላ ይንገር አመለጠ። ይንገር ዓቃቤ ህጉን አድፍጦ ጠበቀው። ቪክቶሪያ ዌስተን አቃቤ ሕጉን አስጠነቀቀችው። ይንገር ከተፈረደበት ጊዜ ጥቂት ሰዓቶች ቀደም ብሎ ተገደለ። ደሞ ሁን ይንገር። አሮጌ ዜና።››

‹‹አሮጌ ዜና!›› አለች ቪክቶሪያ ተሰፋ በቆረጠ ቃና። ‹‹ምናልባት ቀደም ብየ ባለመድረሴ ይሆናል። ሚስተር ኤድዋርድ ምን የሚያድርጉ ይመስልሃል?››

‹‹እኔ እንጃ። ቫን ዱሰን ግን አንቺን ቆራጥ አርበኛ ብሎሻል። ኤድዋርድ አርምስቱድ. . . ወይ ከስራ ያባርርሻል፣ ወይም እድገት ይሰጥሻል።›› ኒክ ራምሲ በመጨረሻ ከንዱን በከንዱ አገባና ‹‹ባሁኑ ደቂቃ ምን እንደማስብ ልነግርሽ ነው። ጥቂት መለኪያ መጠጥ ብትቀምሽ የሚበጅሽ ይመስለኛል።››

4

አብረው መዋል በጀመሩባቸው ዓመታት ውስጥ ሃሪ ዴትዝ ኤድዋርድ አርምስቱድን እንዲህ ፍንድቅድት ብሎ አይቶት አያውቅም።

በጊማጌጥ ያሸበረቀውን የአሳታሚው ቢሮ እስከ በረንዳው በረዘመውና መሉ በመሉ በተከፈተው በር የሚገባው የፀሐይ ብርሃን ይበልጥ አስውበ አናት ተፈጥሮ በኤድዋርድ አርምስቱድ ላይ ወርታማ ውበቷን ለማንፀባረቅ ታጥታ የተነሳች አስመሰሏታል። ኤድዋርድ በቆዳ በተለበደው ተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ በኩራት ለጠጥ ብሎ ተቀምጠ ወገግ ያለውን ፊቱን ፀሐይዋ እንድታሞቅለት እያመቻቸ ከጠረጴዛው ባሻገር የተቀመጠውን ልዩ ረዳቱን በተመስጠ ተመለከተና «እስኪ እንደገና ንገረኝ፣ ሃሪ» አለው።

ሃሪ ዴትዝ ከፊት ለፊቱ የታጠፈውን ወረቀት በድጋሚ ዘርግቶ «ልብ በል፣ አሃዞቹ ይፋ ያልሆኑ ናቸው። ሆኖም እስከዚህ አጠያያቂዎች አይደሉም። አለታዊው ኒውዮርክ ታይምስ ትናንት የሸጠው ከ860,000 ቅጅ አይበልጥም።» ሃሪ እዚህ ላይ ጉሮሮውን ሳል አደረገ። «ኒውዮርክ ሪኮርድ 940,000 ቅጅ አግለብልቦ ሸጧል። ተቀናቃኞችህን ደምስሰሃል። እንደፎከርክ አድርገኸዋል» ሲል አዘነበለት።

«ይኸ. ነው።» ሥዩ አርምስቱድ፣ «ተስፈንጥረናል። የይንገር ማምለጥ ሳድል አብትዮናል። ወንድ ወንድ ወንድ!»

አርምስቱድ የውስጥ ስልኩ ሲያንቋርር ተሰማው። ድምጹ የፀሐፊው የኢስቲል ነበር። «ሦስ ሊዲንግተን ተርበዋል» አለችው።

‹‹ሠራስ ነህ?››

‹‹ሂሎ ኤድዋርድ፣›› አለ ሲዲንግተን። ‹‹እንደምነህ?››

‹‹ከብሩ ይስፋ። ለመሆኑ ትናንት ገበያ ላይ ሪኮርድ የተቀዳጀው ድል ዜና ደርሶሃል?››

‹‹ጭምጭምታው ብቻ. . . .››

‹‹ምኑ?››

‹‹ምን እንደተደረገ ስገምት ነበር። በማታው ቴሌቭዥን የዜና ፕሮግራም ያንተውን ጋዜጣ በዜና ምንጭነት ሲጠቅስ ሰሰማ የበለጠ በዝርዝር ለማወቅ እኔ ራሴ ጋዜጣህን ልገዛ ከቤቴ ወጣሁ። ይገርምሃል አንድ ቅጅ ለማግኘት ሶስት የሽያጭ ጣቢያዎችን ማሰስ ነበረብኝ። ሕዝቡ በሽሚያ ሲገዛው ነበር። እንኳን ደስ ያለህ. . . ከልቤ የምስራች አልሃለሁ።››

ኤድዋርድ የሰልኩን መናገሪያ በእጁ አፈነና ለሃሪ ዴትዝ ‹‹ያባቴ ጠበቃ ስገምተው የነበረ ድል ነው እያለኝኮ ነው። በሱ መኖሪያ ሰፈርም ህዝቡ ተረባርቦበታል ይለኛል። የምስራች አለኝ›› አለውና እጁን ለቀቅ አደረገ።

‹‹በጣም ደስ ብሎኛል፣›› ሲዲንግተን ተጠለ።

‹‹አመሰግናለሁ ሠራስ፣ አመሰግናለሁ።››

‹‹እረ ለመሆኑ ምን ያለኸው ሳተና ብትሆን ነው ወሬውን ለእፍታው ለጥብስ ያደረስከው?››

‹‹ስለሱ አትችገር። አባቱ በኑዛዜ የጣለብኝ ማዕተብ በይንገር ከወሂ ማሽቀብ ተበጥሷል።›› እንደጥሩ ቅኔ ዘራፊ ማዕተብንና መሸቀብን ጥበት አደረገው። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል፣ ‹‹እስከ የትናንቱ ሽያጭ እሃዝ ልንገርህ።››. ከሃሪ ዴትዝ አንድ ወረቀት ነጠት አደረገ። ‹‹ኒውዮርክ ታይምስን በ80,000 አስከንድተነዋል። ምን ይመስልሃል?›› አለው ወንበሩ ላይ እየተፍነሸነሸ።

‹‹የተሳካልህ ትመስላለህ።››

‹‹እንደተሳካልኝ አረጋግጫለሁ?››

‹‹በርግጥ ያባትህን የኑዛዜ አደራ ማሟላትህን ለማረጋገጥ ኦፊሴላዊ ማረጋገጫ ማግኘት አለብኝ። አይመስልህም?››

‹‹ልክ ነህ። ኦፊሴላዊ አሠራን ልክ ከቺካጎው የሰርግ ድግስ ኦዲት ቢሮ እንደተቀበልኩ አልክልሃለሁ። ግን ነገሩ አጠያያቂ አይደለም. . .››

ጠቢቃው አቋረጠው። ‹‹የምናገረው ከሕጋዊነት አኳያ ነው፣ ኤድዋርድ። በማንኛውም መንገድ የተጠየቅኸውን ለማሟላትህ እኔ ራሴ እማኝ ነኝ።››

‹‹ጥሩ ጥሩ፣ ይህን ካንተ አፍ መስማቴ ብቻ ያረካኛል›› አሰ አርምስቱድ። ‹‹ኔዛዜው የጠየቀኝን ቅድመ-ሁኔታ አሟልቻለሁ። ከዛሬዋ ዕለት ጀምሮ ሪኮርድ የኔ የግል ንብረት ነው።››

‹‹ብዚህ ሲበዛ እንደተደሰትኩ ደግሜ አረጋግጥልሃለሁ።››

‹‹አመሰግናለሁ ሆራስ። ግን አመነኝ ሆራስ፣ ይህ ግና የመጀመሪያው ነው። ከዛሬ ጀምሮ እንቅስቃሴዬ ሁሉ መደፈት ነው።››

‹‹እኔና ባለቤቴ በሚቀጥለው ሳምንት አንተንና ሃናን ጋርቲ አዘጋጅተን ልንጠራችሁ አትደናል። ለድልህ የምናነሳው ጽዋ ቀላል እንዳይመስልህ።›› አርምስቱድ ፈንቅሎት የሚወጣውን የተፍነሸነሸ ሳቅ ሊገታም ሆነ ሊደብቅ አልቻለም። ያባቱ ጠቢቃ የሆነው ሆራስ ነገሮችን ለማዘዘር ካለው ጥበብና ተሰጥኦ የበለጠ በየትኛውም ስፍራ ተደማጭነት ስላለው የኤድዋርድ አርምስቱድን ምኞት ሊገድልም ሆነ ነፍስ ሊዘራ አይሳነውም።

‹‹አመሰግናለሁ ሆራስ›› አለ ኤድዋርድ ከመሉ ፈገግታ ጋር፣ ‹‹ጋርቲውንና ሻምጋኖን ተቀብየዋለሁ። በትርጡ እንግናኛን።››

ኤድዋርድ ስልኩን ዘግቶ ደቂቃ እንኳ አልቆየም። ዐሐፊው አሲቲል አውንም ደወለችለት። ‹‹ይሄ ስልክ አውንሰ አበባው ሚስተር አርምስቱድ። ሁሉንም ጥሪዎን ወደርስዎ እያስተላለፍኩ አልረብሽዎትም። መልእክት እቀበልልዎታለሁ። ብቻ ይሸኛውን ይፈልጉት ይሆናል። ከከንቲባው ነው፣ ከከንቲባው ከራሳቸው›› አለችው ዐሐፊው።

አርምስቱድ ስልኩን ገልመጥ አያደረገ፣ ‹‹አግናኟኝ›› አለ። ተጥሎም

የሚያዘጋጁትን ጥያቄ ምልክት መሬን አያርፅ ብሎኛል። . . ኤድዋርድ አርምስቱድ ነኝ። አንድምን ከሰ እጋብ . . . አመሰግናለሁ። እጅግ በጣም። . . ሕመምተኛ ሆኖ ከሆስፒታል ሰዎችን ነን፣ ለሕዝቡ። . . ልክ ነው፣ ፍላጎታችን በመሳካቱ ብቻ ነው የምንደሰተው። አሁ በሚቀጥለው ሳምንት ቢሮው ድረስ መጥቼ ምነ አብረን ብንበላ እጅግ በጣም ደስ ይለኛል።››

በደስታ ላይ ደስታ። አርምስቱድ ስልኩን ዘጋና ሃሪ ዴትዝን በእይታ ዙሪ እየተመለከተ፣ «ከሁርኒታቸው፣ ከንቲባው ናቸውኮ አንኳን ደስ ያለህ የሚሉኝ። ሰምት አንደሆነ ኅብዮሃል? ይንገር ላንናወፈን ድል እንዳደመሰልህ። የወረዳው አታቢ ሕግ የጠመጠሙን አደጋ በማስታወት የሻን ዱሰንን ሕይወት ለማጸን የበታች ጀግና ሪፖርተር ስላለችኝ ኩራት እንዲሰማኝ ነውኮ ሃ. . . ሃ! ቪክቶሪያ ዊስተንን ማለታቸው ነውኮ። ምን ያመሰልሃል ሃሪ?››

«እኔ እንጃ!» አለ ሃሪ ዴትዝ በግልጽነት።

«ዚኦ፣ አፏን እንዲት መያዝ አንዳለብኝ እኔ አውቃለሁ። በል እንግዲህ በርታ ሃሪ፣ . . እና አፏን ቶሎ ላክልኝ።››

* * *

ቪክቶሪያ ቢርውን ከበሩ አስከ ጠረጴዛው አጭርማ ስትጣ ኤድዋርድ አርምስቱድ በአትኩሮት ተመለከታት። አንደወጉሯ ዘለማ ያለች፣ እንደ እድሜዋ ፈካ ያለ መልክ ያላት፣ ከማራሚው ሽራፊ ጋር አርምጃዋን ተከትለው ወዲያ ወዲህ የሚሉ ውብ ጡቶቿ በወብቷ ላይ ውበት የጨመሩላት ትንሽዬ ያለች ከሁሉም በላይ ትኩስ ልጃገረድ መሆኗን ያስተዋለው ግን ብሬ ነበር። የኪም ነስቢትን ያህል ያልበሰለች የቧን ያህል ሙሉነት የሚጎድላት፣ ጎያል የተሞላች ሴት ሲል አሰበ።

ሁኔታዋ ግን ሳበው። ቀለል ያለችና ለሁሉም ነገር ዝግጁ ነች። የገረመው ግን ፈጣን መሆኗን እያየ ረጋ ያለች መሆኗንም ሊነድ አለመቻሉ ነው። ‹‹ሁሉም ነገር የተደበላለቀባት ሁለገብ ሲል አሰበ። ምንም ቢሆን ሰራተኛው ናትና ለቴመናዋ፣ ለገጽታዋና ለድርጊቷ ተንበርክኮ ፊት ሊሰጣት እንደማይገባው ተገንዘና ግምግማውን ከሊላ አትጣጫ አደረገው። አም፣

ልጅቷ አንደኛ ደረጃ ዜና ዚጋቢ ይወጣታል። ሊሎች ወንዶችን ልታሳብልና ልትገራ የምትችል ልጅ ነች። የሪኮርድ ጋዜጣ ቁጣ ቅርስ እንደምትሆን አድርጎ አሚት። ያም ቢሆን እሱ ሰፊ ኮስታራ መሆን አለበት። እውነተኛ ሪፖርተሮችን የማነው፣ የመቅረፁ ተግባር ሳይውል ሳያድር ዛፈኑ መጀመር አለበት።

የሚሰራበት ጠረጴዛ ከሚለያዩቸው በስተቀር የተቀመጡቸው ከፊት ለፊቱ ነበር። ‹‹የምስራች ሚስተር አርምስቱድ። ኒውዮርክ ሪከርድ ትናንት ሊሎችን የኒውዮርክ ጋዜጠኞች በመሊ መብለጡ ሰፊ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል። በስራተኛው ዘንድ ታላቅ ድል!››

‹‹አዎ ልክ ነሽ። አመሰግናለሁ ቨክቶሪያ። እየመራ ነው፣ ወደፊትም ይሆንን ቦታ መነጠት የለብንም።

‹‹እንዴት ቀደማችሁ? ማለቱ የይንዝርን ማምለጥ እንዴት ደረሳችሁበት? ከሁሉም በፊት የናንተ ዜና እጅግ ቀድሞ ነው የደረሰ።››

እዚህ ላይ ሁለቱ ሰዎች አደገኛው ጠረፍ ላይ ይረሱ። ያሁንና ጨለሊው አርምስቱድ ቀስ ብሎ ጠረፉን ተሻገረው። ‹‹የወሀኒ ቤቱን ማምለጫ ቁበ ማለትሽ ነው?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹ይንዝር ሚስጥሩን እንዴት እንደደረሰበት እንቦትልሽ ነው የሆነብኝ።››

‹‹መልካም፣ አንቺ ሚስጥሩን ከጉሰ ጋጋኖ አግኝሽ። ጉስ ጋጋኖ ሚስጥር እንዳታወጭ ያስጣሽን ታልም ጠብቀሽ ነበር። ግን ሊሎች እንዳንቺ ታማኝ መሆናቸውን እጠራጠራለሁ። ባጭሩ በወሀኒ ቤቱ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ሚስጥሩን ለይንዝር ነግረው። በዚያው ደቂቃ ደግሞ አንድ ሰው ይንዝር በቁጣው በማምለጥ ላይ መሆኑን ለኛ ሽክ አለን። እንደሚመስለኝ ልክ ይንዝር በማምለጥ ላይ እንዳለ፣ እኛ ዜናውን ለማደያ አደረስነው። ሊላ ዝርዝር መረጃ እንዳልሰጥሽ ጠቅቱ ግና አይፈቅድልኝም።››

‹‹አ! ያን ያህል ሚስጥር ላስፈለፍልም አልፈልግም ሚስተር አርምስቱድ።››

‹‹ማስፈልፈል አይደለም ቨክቶሪያ። ነገሩ ሙያሽ እስከሆነ መጠየቅ

አለብሽ። ግን አየሽ ማንም ሰው በጋዜጣችን ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባብን አልፈልግም። ባንቺ ላይ ግን ጽኑ እምነት ሲኖረን እንደሚገባ ተረድቻለሁ።››

‹‹ሙቅ በሙቅ ሚስተር አርምስቱድ፡›› አለች።

ሆን ብሎ ሲጋራ አቀጣጠለ። ‹‹ከይንገር ጋር ያደረግሽው እጅግ በጣም ጠቃሚ ቃለመጠይቅ እንደነበረሽ ይሰማኛል።››

‹‹እ… እም እጅግ ጠቃሚ ነበር›› አለች በታክቱ ድምጽ።

‹‹በትክክ መጠየቁ ጊዜ ወንጀለኛው አቃቤ ሕጉን ሊገድል እንደሚፈልግ ነግሮሽ ነበር፣ ታዲያ ይንገር ማምለጡን ስትረጅ አቃቤ ሕጉን ለማስጠንቀቅ ብዙ ጥረት አድርገሻል፣ በርግጥ በጥረትሽ የሰውየውን ሕይወት አትርፈሻል።››

አውንም እንድታብራች፣ ‹‹ይመስለኛል›› አለች።

‹‹ለሰብአዊነትሽና ለጥሩ ዜግነትሽ የተሰማቸውን እድናቆት የሚገልፁልኝ ብዙዎች ናቸው። አንቺን ለማድነቅ ከንቲባው ሳይቀሩ ደውለው ነበር። ግን ያንቺን ድርጊት የሚያደንቅ አንድ ሰው አለ። ሰማሽ፣ ያ ሰው እኔ ነኝ። አትጥረጅብኝ፣ ያላልኩሽን ስታደርጊ ደስ ሊለኝ አይችልም።››

አርምስቱድ የሚናገረው ለልጅቷ ግልጽ እንደሆነ ቢረዳም እሷ ግን ነገሩ ስለገባት ዝም አላለችም። ‹‹ምን ማለትዎ ነው?›› ስትል ጠየቀችው።

አሳታሚው የሲጋራውን ጭስ ቁማ አድርጎ ጭሱ ሲቦን፣ ሲሟሟና ሲጠፋ አስተዋለው። ‹‹አባባሌን የማብራራልሽ ባንድ ቦታ ያነበብኩትን ትንግርት በመተረክ ይሆናል። ታሪኩ የአንዲት ሴት ሪፖርተር ነው። ስሟን ረሳሁ፣ ግን ለኒውዮርክ ደይሊኒውስ ትሰራ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ባንድ ወቅት የዊልስ መስፍን ጉብኝት በሚያደርግበት ጊዜ ደይሊኒውስ ወጣቷ ሪፖርተር የመስፍኑን የግል ሁኔታ፣ ሃሳቡንና ስሜቱን እጥንታ እንድታብርብ ይልክ ታል። ታዲያ አየሽ ተልእኮዋ ባንድ በኩል ሲሳካ ባንድ በኩል ደግሞ ከሽፏ። እያጸመጥሽኝ ነው ቪክቶሪያ? ምን ስሀተት እንደተፈጠረ ብነግርሽ ይጣፍሻል። ወጣቷ ሪፖርተር መስፍኑን በወበቷ ማርከ በጥቅር ልቡን አጥፍ

አብራው እስከመደነስ ደረሰች። ልቡን ሰልባ ስሜቱንና ፍላጎቱን ከማንም ይበልጥ የሚል ሚስጥሩን ሁሉ አስወትውታው ትመለሳለች። ነገር ግን ሪፖር ታን ልታሳትመው ይሳናታል። መስፍኑ ጓደኛዋ በመሆኑ ልትከዳው አትች ልም፣ የጓደኛዋን ሚስጥር በማውጣትም የተላከችበትን ሪፖርት ልታቀርብ አትችልም። በርግጥ አንድ ነገር ጽፋ አቀረበች፣ ግን ከእውነተኛው ፍፁም የራቀና ከተልእኮዋ አላማ ጋር የማይጣመድ ነበር። በመጨረሻ የፀ ታማኝነት ለምታገለግለው ጋዜጣ ሳይሆን ለምትወደው መስፍን ዋለ። የሪፖርተርነቷን ኃላፊነት ዘንግታ አሳታሚዋን ጉድ አደረገችው። ነገሩ ይታይሻል?››

‹‹ይታየኛል›› አለች ቪክቶሪያ በዝግታ።

‹‹እንቺም በተመሳሳይ ሁኔታ እኔን ጉድ አድርገሽኛል። ለኛ የምታቀርቢልን ታሪ መጠይት ነበረሽ። ጽሁፍሽን ባስቸኳይ በማጠናቀር ፋንታ ስለወረዳው አታቢ ሕግ ሀይወት ትጨነቂ ጀመር።››

‹‹ግን ሲገደሉ ዝም ብየ ማየትም አልነበረብኝም›› አለች ቪክቶሪያ።

አርምስቱድ የሲጋራውን ቁስ ፊቷ ላይ ቁማ አደረገው። ‹‹ሕግን አትውጂ። በማናቸውም ሁኔታ ደንገር አታቢ ሕጉን ለመግደል የነበረው እድል በጣም ጠባብ ነበር። የመረዳው አታቢ ሕግ ሁልጊዜም ደህና ጥቢት የሚደረግለት ሰው ነው።››

‹‹ታድያ አታቢ ሕጉ ራሳቸው ለምን አመሰገኑኝ?››

‹‹እንዲሁ፣ እንዲሁ ቪክቶሪያ። እንደ ልጅ ሲተልድሽ ነው። የለም፣ አትሚችኝ። ትድሚያ ለምትሰጪው ጉዳይ ትድሚያ አለመስጠትሽን እንድታስተባብይኝ አልፈልግም። የተኮመርሽበት ተግባር የሕዝብ አገልግሎት ሰጭነት አለመሆኑን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንድታውቂ። ሩጫና እሽቅድምድም በሞላበት የጋዜጠኝነት ሙያ ላይ የተሰማራሽ መሆንሽን መዘንጋት የለብሽም። የመጀመሪያውና ብቸው ጉዳይሽ እኔና ይሆን ጋዜጣ ማገልገል ብቻ ነው። በብዙ መከራ ከወንጀለኛው ጋር ለመጣናኘት በንበታ ኃላፊነቱን ላንቺ መስጠታችን አደራሽን በብታት ትመጫለሽ በሚል እምነት ነበር። አዎ፣ ጥሩ ታሪ መጠይት አድርገሽ ነበር። እንዲያው እንዴት ያለሽው ብትሆኝ ይሆን ያን የመሰለ ታሪክ በቦርሳሽ

ታትፈሽ አቃቤ ሕጉን ፍለጋ ስትሠራ ያመሸሽው? አም፣ በተጭ- እዚህ መጥተሽ የተላከሽበትን ታሪክ ብታተናብሪ ኖሮ ለሁለተኛ ጊዜ የበላይ የሚያደርግንን ምርጥ ዜና እናትም ነበር። ርእሱን ምን ብለን እናወጣው እንደነበር አሁን እንኳ ይታየኛል። ‹ያመለጠው ነፍሰ ገዳይ ቫን ዱሰንን ለመግደል ምሷል› እንለው ነበር። ጋ፤ በእንዴት ያለ ሽሚያ የሚሸጥ ጋዜጣ ይኖረን ነበር? ይንገር በመሞቱ ያንቺ ታለመጠይትም ውዳቂ ሆነ። የይንገር ሞት ደግሞ ሁሉም ያወቀው ዜና እንጂ የኛ ብቻ አልሆነም። የምታስተድሚውን ነገር አላስተደምሽም። ተግባብተናል፡ ቪክቶሪያ?››

‹‹ይ. . . ይሆናል። ሚስተር አርምስቱድ፡ አዝናለሁ።››

‹‹የወረዳው አቃቤ ሕግ ምናልባት ሚዳሊያ ይሸልምሽ ይሆናል። ኤድዋርድ አርምስቱድ ግን ጋዜጣውን ለማያስተድምለት ሰራተኛ ቆርኪ አይሸል ምም። ከእንግዲህ እንዲህ ያለው ታላቅ ታሪክ በጅሽ እንደገባ ወዲያውኑ ከእጅሽ ወጥቶ ለሪኮርድ መድረሱን ማረጋገጥ ይጠበቅብሻል። ከዚያ በኋላ ትክክለኛውን ሚዳሊያ ትቀበያለሽ።›› መረበሽን ከፊቷ በማንበቡ የበለጠ ሊረብሻት አልፈለገም። ‹‹መልካም፡ ትምህርት መውሰዴ ነው ዋናው ቁም ነገር። ካሁን በኋላ ስሁትሽን እንደምታርሚ ተስፋ አደርጋለሁ›› አላት።

ከክፍሉ ስትወጣ ምን ያህል እንደጨከነባት አሰበ። ይህን ያህልም አልጠረጣት። ትምህርት ከመስጠቱ በስተቀር። ካሁን በኋላ ተጥ ያለች ሪፓርተርና የአሸናፊው የሪኮርድ ቡድን ጥሩ ባልደረባ ይመጣታል።

* * *

ኤድዋርድ አርምስቱድ ድል አድራጊ ቡድን ሊያዋቅርና የመሪነት ስፍራውን ምንጊዜም የማይለቅ ጋዜጣ አሳታሚ ሊሆን ከወሰነ ሰው አድሯል። ይህን ምኞቱን ለማሳካት ለሚተጋለት ተናት ሊታተሙ የተዘጋጁ ወረቃችን ፋይል አስተርቦ ያመረምራል። ሁሉም እርባና የላቸውም።

አሱን የበላይ የሚያደርገው ሌላ ይንገር ፊለግ። የበፊቱን የሚመስል ይንገር።

ሃሳቡ ፍክ እንዳለበት ማክ አሊስተርን ጠርቶ ኋክ ራምሲ

እንዲቀርብለት አዘዘ።

ኒክ ራምሲ በስልኩ መስመር ቀረበ። «አርምስቱድ ነኝ ኒክ።»

«አቤት ጌታዮ?»

«ያን ቢጋራ የወጠንከውን የመፈረሻውን ልዩ ፕሮጀክት ታስታውሳለህ? ያ እንኳ አባቱ የቀታወመው?»

«በሚገባ። ያ የፋኖምች ታሪክ ተከታታይ ጽሁፍ አድርገን ልናትመው ነበር። ርእሱ እንኳ «የፋኖምች ዘመን» ይል ነበር።»

«ጎሽ ጎሽ በደንብ አስታውሰኸዋል። መሰረተ-ዜናውን በከፊል እንዳቀናበርከው ትዝ ይለኛል። ማስታወሻህ አሁንም ይኖር ይሆን?»

«እኔ ማስታወሻዮን ጥየ አላውቅም።»

«በጣም ጥሩ። ለፀሐፊዬ ስጣት። እንደገና ላነባቸው ፈለጋለሁ። ምናልባት ፕሮጀክቱን እንደገና መቀጠል ያስፈልገን ይሆናል።»

«ትልት ሃሳብ።»

«እሰኪ እናያለን። መጀመሪያ ጽሑፍህን ለመልከተው።»

ኤድዋርድ የስልኩን መነጋገሪያ ከማስቀመጡ እንደገና በመደወሉ ደግመኛ ማንሳት ነበረበት።

«ጉስ ፓጋኖ ቀጠሮ አለኝ ይላል።» አለችው ኢስቲል። አርምስቱድ ቀጠሮውን ረስቶት ነበር። «አስገቢው።» አላት።

«ግሩም አቀማመጥ» አለ ፓጋኖ ባርኔጣውን አውልቆ እንደገባ ለቢሮው አዘገጃጀት ያለውን አድናቆት ሲገልጽ።

አርምስቱድ ከዚህ በፊት ከፓጋኖ ጋር ተነጋግሮ አያውቅም።

አርምስቱድ ጊዜ ሳያጠፋ ወደ አርዕስተ-ጉዳዩ ገባ። «ስለእስር ቤቱ የማምለጫ ዘዴ ለሰጠኸኝ መረጃ የከፈልንህ ጉርሻ ደጎስ ያለ ነበር። አይደለም?» አለው።

«ተጠቀመበት አላልኩም ነበር» አለ ፓጋኖ። አነጋገሩ ከብስጭት

አልነበረም። «ነገሩ ሚስጥር ነበር» አለ ተጠለና።

«ሰማህ ወይ ሚስተር ፓጋኖ፣ ካኖ የልጣ ነገር ሁሉ ሚስጥር አይደለም። ይህ መታወቅ አለበት።»

«እንዳታሳትሙት ብየ ታስቢያት ነበር።»

«ታዲያ ሙች ታተመ» አለ አርምስቱድ ቀለል አድርጎ «የይንገር ግምለጥ እስኪረጋግጥ ድረስ አላተምነውም። አሁን ወደ ዋናው ቁምነገር ሚስተር ፓጋኖ። በጥሞና አዳምጠኝ። አንድ በተለይ ሳንተ ያዘጋጀሁልህ ሰራ አለ። የሰራውን አይነት ከመግለጼ በፊት ግን የኔን የግል ፖሊሲ በሚያሻማ መንገድ ላነጋግርህ። እኔ እንደማምነው አንድ ጊዜ ለረዥድ እስከደረሰ ድረስ በዚህ አለም ላይ የማይታተም ነገር የለም። በኛ አመለካከት በዚህች ምድር የሚከሰት ነገር ሁሉ ይታተማል። ለመሆኑ ስለይንገርና ስለአሰር በቱ ለሪፖርተራችን በማሰረዳትህ ምን ያህል ጉርሻ ነው የተከፈለህ?»

«ሁለት መቶ ሃምሳ ዶላር።»

«በቲ አይደለም» አለ አርምስቱድ፣ «ሲያንስህ ነው። በል እኔ ጉርሻውን አንድ ሺህ ዶላር አድርጌልሃለሁ። ታዲያ ደግሞ አዲስ የሰራ መስክም ከፍቼልሃለሁ። ይመወዝህን በሳምንት ወደ አንድ ሺህ ዶላር ከፍ ባደርግልህ ምን ይመስልሃል?»

ፓጋኖ ያርባውን ከመንበሩ መደገፊያ አስልትቶ ወደፊት አሰገገ። ትንሽ አትማማ። «ምን ሰርቼ?» አለ በመጨረሻ።

«እንደሰሞኑ አይነት። ማለቴ እንደበፊቱ፣ እንደ ይንገር ምንቺ ስታገኝ ማሳወቅ።»

«እንደ ይንገር አይነት ሁኔታ ቶሎ ቶሎ አይፈፀምም።»

«ሰማ፣ ትንሽም ቢሆን ስላንተ አውቃለሁ። ደህና ኑሮ መኖር የምትፈልግ ሰው ነህ። ሁልጊዜ የገንዘብ እጥረት አለብህ። የኔ ደመወዝ ምኞትህን ያሳክልሃል፣ ችግርህን ይቀርፍልሃል። እኔ ደግሞ ከሰዎች ጋር ተግንና ወሬ አቀብልኝ ስልህ የወትሮውን በመሳሪያ እያስፈራሩ መዝረፍ ተጥልበት ማለቴ

አይምሰልህ። በበፈት ጓደኞችህ ላይ እያንጮበብህ ጅሮህን ከፍተህ ድርጊታቸውን በትኩስ አሳውሎኝ። ግን ግን በነሱ ተማባር አትሳተፍ፣ ወይም ራስህን በሚያስበላ መንገድ አትትረባቸው። አባባሉ ግልጽ ነው?››

‹‹አሃ. . . የሰማሁትን ማሳወት ነሞ?››

‹‹ጠቃሚ ከሆነ አምና. . . .››

‹‹ግን እኒያን ሰዎች ማስበላትም የለብኝም።››

‹‹የለብህም። አንተ የምትነግረንኩ እነ እከሌ እያልህ አይደለም።››

ፓጋኖ ያተጣጠለውን ሲጋራ በሐሳብ ተመስጠ ማኖና ‹‹ቢሆንም አደገኛ ስራ ነው›› አለ፣ ‹‹ጓደኞቼም ቢሆኑ ከጀርባቸው የሚያተሰትሰ ሰላይ መኖሩን ካወቁ ደስ አይላቸውም።››

‹‹ሰለላ አይደለም ያንተ ተግባር። ማንንም ሳትጎዳ ብዙ ማዳመጥ፣ ካዳመጥከው ውስጥ ጠቃሚ ጠቃሚውን መርጠህ ለኛ መንገር ብቻ።››

‹‹ጥሩ።››

አርምስቱድ ብድግ አለ። ‹‹ምን አልከኝ ፓጋኖ?››

ጉስ ፓጋኖም ተነሳ። ‹‹ተስማምቻለሁ።››

ለሚስተር አርምስቱድ መሉ ቀን ነበር። ነገሮች በዐይናቸው እየተዘጋጁ ናቸው። የፓጋኖን ከንድ ያዝ አድርጎ ወደ ውጭ እየመራው ‹‹ና›› አለው፣ ‹‹ዝርዝሩን ከሃሪ ዬትዝ ጋር መነጋገር አለብህ። አሁን ሃሪ የኔ ረዳት ስለሆነ አንተም ከንግዲህ ግንኙነትህ ከሱ ጋር ይሆናል። ሁለታችሁ እቅድ እንድታወጡ አፈልጋለሁ። እሽ?››

‹‹እሽ።››

* * *

አርምስቱድ የቢሮ ልብሱን እየለወጠ ነው። ሶስት ፕሮግራሞች ተደትነውበታል። ነገር ግን ከቢሮው ልብስ ለመቀየር ሲያማድፍ ያመጣው ከኪም ነሰቢት ጋር ያደረገው ቀጠሮ ነው። በወጣት አለባበስ ቱር ካለ በኋላ ረጅም መስታወት ፊት ለፊት ቆመ። አም ከብዙ አመታት ወዲህ እንዲህ

አምርባት አያውቅም።

ቀጠሮው እየደረሰ በመሆኑ የቀረችውን አምስት ደቂቃ ሳሎን ተቀምጣ ከምትጠብቀው ሚስቱ ከሃና ጋር ሊያሳልፍ ሄደ። ሃና ለምን እንደፈለጋችው ሊገባው አልቻለም፣ በተለይ እንዲህ ጊዜ አጥሮት። በይንገር ማምለጥ ምክንያት ፈልገድ ስለተቀጻጀው ድል ጧት ቁርስ ላይ ነግሯታል። ሌላ ምን የሚያነጋግር ነገር አለ? ወቼም ሃና በአእምሮዋ የሚጉላላባት ነገር ካለ ያ ነገር ጥሩ አይሆንም።

‹‹በዚህ ሙሉ ቀን ባልለከፈችኝ›› ሲል አሰበ።

ያለወትሮዋ ፈታ ፈታ ያለው ሃና ያለ ወትሮዋ ከተሸከርካሪ መንበሯ ወርዳ ሶፋ ላይ ተቀምጣለች። ወደቧ እያመራ ከጎኗ ሊቀመጥ ከዳዳው በኋላ ተጠጋ። መቀናጣት ሚስቱ ብዙ እንድታወራ መጋበዝ መሆኑን ተገንዝቦ እንዲቆም ተረ።

‹‹እንኳን ደስ ያለህ አዲ፣ በድሉ ተደስቻለሁ፣›› አለችው።

‹‹እንደማይርገው አውቅ ነበር፣ አደረግሁት›› አለ ከኪሱ ሲጋራ አውጥቶ እያቀጣጠለ። ‹‹እሽ ሃና፣ ምን ልርዳሽ?››

‹‹ስለ ሮጀር ነበር፣›› አለች።

‹‹ሮጀር ምን ሆነ?››

‹‹ከሣራን ባይ ሆስፒታል ደወለልኝ።››

‹‹ሆስፒታል? ምን ማለትሽ ነው? ምን ነካው? ከባድ ነገር ነው? የለም ከባድ ቢሆን ለደውልልሽ አይችልም ነበር።››

‹‹ከባድ እንኳ አይደለም። ተራራ ሲወጣ እንሸራተት ወደተ።››

‹‹ተራራ ሲወጣ? በይ ተይኝ። ማሪን ባይ ውስጥ ተራራ የለም።››

‹‹ኮረብታም ሊሆን ይችላል›› አለች፣ ‹‹ምናልባት ሰሰማ ተሳስቼ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ተጎድቷል። ሁለቱም እግሮቹ ተቀጥቅጠዋል። ሪጅም ጊዜ ሳያስተኙት አይቀሩም።››

‹‹ዮታባቱ፡ እሱ ብሎ ተራራ ወጣ።››

‹‹ከስራው ጋር ለተያያዘ ጉዳይ መሰለኝ።››

‹‹ደደብ›› አለ አርምስቱድ። ‹‹ሞጋሙን አገኘ።› ጥቂት ወየቃ ሰፈነ።

‹‹ጥሩ፡ ለነፉ የማይስጠው ከሆነ ሁኔታውን ደውየ አከታተላለሁ። ሰዚህ ነበር የፈለግሽኝ?››

‹‹አይ›› አለች ሃና፡ ‹‹ኢዲ ለሳምንቱ እረፍት ወደ ሣሪን ባይ ይዘኸኝ ብትሄድ?››

አርምስቱድ በረጅሙ ተነፈሰ። ‹‹ለምን? ሂጅና ጡትሽን አጥቢው። ስሚ፡ ሃና። እሱኮ ከንግዲህ ህጻን አይደለም። በዚህ ላይ ህክምና እያደረገ ነው። ብዙ ጓደኞችም አሉት።››

‹‹እንደቤተሰብኮ አይሆንም ኢዲ። የወለድነው ልጅ ሆስፒታል ተኝቶ እንዴት ወላጅነን ይናፍቅ?››

አርምስቱድ ተስላችቶ ሲጋራውን አወጣወጠ። ‹‹ስሚ ሃና፡ የሽማግሌውን ሀታ የያዝኩት አውን ነው። ማን መሆኑን ያስመሰክርኩትም አውን ነው። በሰራ ተውጨ፡ በስንት ነገር ተከብቤ፡ ዘጠኝ ሙቶ እትድ እያራመድኩ፡ ግና የዚናውን ሞግድ ላንኮጠትዋ እየተሰናዳሁ. . .››

‹‹ላንድ አሁድ እንኳ ጊዜ ጠፋ?››

‹‹በፈጠረሽ ሃና፡ እኔን ተይኝ። ሮጀር ሰው ያስፈልገዋል ካልሽ አንቺ አሁድ ሂደሽ ጠይቂው። አብራሽ የምትሂድ ነርስ ላዘጋጅልሽ እችላለሁ።››

ሃና ብዙ ስታጣጥር ቆይታ ‹‹ልጅ የሚፈልገው ወላጆቹን ነው ኢዲ። በይንገር ጉዳይ ሪከርድ ሰላገኘው ድል እዚያ ከሚወጣ ጋዜጣ ማንበቡን ነገረኝ። አንተ ባደረግኸው መከራቱን ሁሉ እየተናነከነከ ነገረኝ።››

አርምስቱድ እየተገረመና ደስታው እየታወቀበት ‹‹እዚህ ላይ ልጅ ትንሽ ነፍስ ያወቀ ይመስላል።› አለ። ሙዲያው ደግሞ ሰዓቱን ተመለከተና፡ ‹‹ልንገርሽ፡ አውን የምሮጥበት ጉዳይ አለኝ። የሮጀርን ሰልክ ቁጥር እዚው ተይልኝ። ከራት በኋላ ብዙም ሳልቆይ እመለሳለሁ። አንቺ ወደ ሮጀር ሂጂ።

ሰለያሽ አገናለሁ፣ ግን ምን ይደረግ፣ እሱ ደግሞ ከኔ ይበልጥ ይፈልግሻል። በይ እንግዲህ እንዳልዘገይ። ድሳችንን በሚመለከት ሃሪንና ብሩስን የፍንጥ ልጣቸው ነው።›› ወዮቅ ተፈተለከ።

ልክ አሳንሰሩ ላይ ሲደርስ ግን አንድ ሃሳብ ድቅን አለበት። እሱ ራሱ ለረጅም ጊዜ የአባቱ ልጅ ሆኖ የኖረ ሰው ሲሆን እሱ ግን በተራው የልጁ አባት ለመሆን ጊዜ ማጣቱ አሰገረመው።

* * *

ኤድዋርድ በኪም ነሰቢት አጋርታማ በውሃ አረንጓዴው ሶፋዋ ላይ ተንሰራፍቶ ተኮምጠ ከወዲያ ወዲህ ስትንሳፈድድ በአይኑ ይከተላታል። የወጣትነት፣ የትኩሰንት፣ የንደል ስሜት እንዲሰማው ስለሚፈልግ ወጣት ትኩስና ንደል የሚያቅበጠብጣት ሴት ማግኘት ይፈልጋል። ሚሰቱ ከተዘቀዘቸውና ከደረቀችበት አመታት ተቆጥረዋል። ዛሬ ሃና ለበሽተኛው ሰውነድ ሌት ተቀን ከመጨነት በተረፈ አልፎ አልፎ ልጃቸው ሮጀር ያላስባት እንጂ የማብረ ስጋ ማንኑነት ነገር ለአእምሮዋም ሆነ ለገላዋ ባዕድ ነው። ኪም ነሰቢት በጎ ያልጠገቸች፣ ደስታ ሰጥታ ደስታ የምትቀበል ሰው ነች። ይቺን ሴት ሲመኛት ኖሯል። በመጨረሻም ያለተቀናቃኝ አግኝቷታል፣ ወደፊትም ደግሞ ደጋግሞ ያገኛታል።

‹‹ውስኪ በውሃ?›› ስትል ጠየቀችው ኪም።

‹‹ትክክል።››

‹‹ወላይህን እያጠናህ ነው›› አለችው መለኪያውን እያቀበለችው፣ ‹‹በሁሉም መንገድ ላስደስትህ አፈልጋለሁ፣ አዲ።››

‹‹ያለጥርጥር።›› እሷ ባዶዋን መሆኗን አየ። ‹‹እንቺስ?››

‹‹ለኔ አንተ አለኸኝ፣ የኔ ጌታ›› ራሷን ወደሱ አስጠግታ በክንዱ አቀፈችው። ርጥብ ከንፈሮቿን በዳበሳ አገኘ። ምላሷ ዳሰሰው። የውጭ ልስላሴ ተሰማው።

መሳሳማቸውን እንዳበቁ የተገለጠችን ጡቶቿን ሲያይ ሰውነቱ ጋለ።

‹‹አሁንም ቂት ስትደውልልኝ እንደነበርክው ደስተኛ ነህ?›› አለችው።

‹‹ደስታ የሚሰጠኝ ምን እንደሆነ ጠንቅቁ የሚውቅ ሰው ነኝ። አለ እየተነሳ፡ አፏንም ከፊት ለፊት እያቆማት።

‹‹የኔ ፍቅር›› አለችው ወደ መኝታ ቤት ሲያመሩ።

አልጋው ላይ ሲወጣ እግሯን ግራና ቀኝ አሰማርታ ጠበቀችው። በጥጥነት ላይዋ ላይ ጉብ አለባት።

ተፋጠፋጠሁ። አበዱ። በመጨረሻም በረዱ።

እሱም በጀርባው ተንጋለለ። ትንፋሻቸውን መቆጣጠር ቻሉ።

ዐጥታ ሠነ።

‹‹አስከመቼ ይሆን የምታፈቅረኝ?›› ስትል ጠየቀችው።

‹‹እስክ ምንጊዜም።›› ቃል ገባ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንቅልፍ እያናወጣት አይኖቿን ስትከድን እሱም ከአልጋው ተነስቶ ለባበሰ ለመውጣት ሲዘጋጅ በመጨረሻ የተናገራት ቃል የይስሙላ መሆኑን ልቡ አወቀው።

አፏን ማፍቀር ያስደስታል፡ አፏን ማማኘትም ትልቅ ድል ነው። ሆኖም እሱ የሚፈልገውና አይነተኛ አቅዱ ይህ አይደለም።

የግብረ ስጋ ግንኙነት አንደኛ ምርጥ ነገር ላይሆን ሁለተኛ ምርጥ ነገር ነው። ስልጣን ግን ከሁሉም ይመረጣል።

ሁሉንም እና ምንንም ለመግዛት፡ ለመቆጣጠርና ለማዘዝ ስልጣን። ከንግዲህ ርካታው ከወሲብ አይደለም፡ አለምን ከመቆጣጠር እንጂ። በርግጥ አደገኛ፡ በጣም አደገኛ ይሆንበት ይሆናል፡ ይህ ሀይወትን መጻፈር። ግን ይሞክረዋል እንጂ አይተወውም። የመጨረሻውን እርካታ መርካት አለበት።

5

እንዳለፉት ቀናት የዛሬውም ብሩህ ሆኖ ያልፍ ዘንድ ኤድዋርድ አርምስቱድ ታጥቆ ተነስቷል። እሱ ራሱ እንኳ ከሰታራና ተጥታፋ ሰራተኛ ሊሆን ወስኗል።

በጥሪያቸው መሰረት ኒክ ራምሲና ቪክቶሪያ ዊስተን ቢሮ ሲገቡ በስርዓት ተቀበላቸውና እንዲቀመጡ ጋበዛቸው፡ ትናንትና ኒክ ራምሲ የተወሰኑን ቢታይም የተጸፈ ወረቀት አነሳ።

ማስታወሻውን ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ያነበበው ቢሆንም እውን ይሞ እንደግና ይመለከተው ጀመር። ‹‹ግልጽ ትችላለህ›› አለ አርምስቱድ ቀና ብሎ ሳይመለከት። ሰበብ ፊላጊው ራምሲ ወዲያውኑ ሲጋራውን አቀጣጠለ። ቪክቶሪያ ግን አጀንን ግራ ቀኝ እንዳወላለፊች ናት።

አርምስቱድ ማስታወሻውን አስተመጠ። እውነት ለመናገር እሱ የሚፈልገው የንግግራቸውን ርዕስ ከይንገር ማምለጥ ጋር ለማያያዝ ነው። ደረጃ በደረጃ መደዘው አርእስተ ጉዳይ ሊያነሱቸው ፈለገ።

የመጀመሪያው ርምጃ።

‹‹የፋናዎች ዘመን› በሚል ርዕስ ያቀረብካቸውን ማስታወሻዎች ሳነብ ነበር፡ ራምሲ›› አለ ኤድዋርድ፡ ‹‹ጥሩ ጽሑፍ አትርበህ ኖሯል?››

‹‹በውነት የተደሰትኩበት ጽሑፍ ነበር›› አለ ራምሲ።

‹‹የሚታተም ቢሆን እንዴት ደስ ይለኝ ነበር።››

‹‹ማን ያውቃል?›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹አንድ ሃሳብ ይመላለስብኛል። የሁላችሁንም ትብብር የሚጠይቅ ነገር ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ስለዚህ ማስታወሻ ከራስህ የበለጠ በዝርዝር መስማት እፈልጋለሁ ኒክ። ለጊዜው ቪክቶሪያ የሚለበትብሽ ማጻመጥ ብቻ ነው።››

‹‹የሚረዳም እስከሆነ ድረስ በማስታወሻየ ያላሰፈርኩትንና በግል የማውቀውን አንድም ሳላስቮር ልነግርም ዝግጁ ነኝ ሚስተር ኤድዋርድ።››

‹‹የራስህን ግምገማ ልትነግረኝ እፈልጋለሁ ኒክ›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹በአካባቢያችን ብዙ የፋኖ ቡድኖች እየተንቀሳቀሱ ናቸው፣ ግን የትኞቹ ናቸው በጣም አደገኞቹ?››

‹‹አደገኛነት ከምን አኳያ?››

‹‹ሰናንጻጽራቸው ብዙዎቹ ተራ ማጅራት መቺዎች፣ ለሎቹ ደግሞ ሰርሳሪዎች ይሆናሉ። አነሱን ተዋቸው። በጣም ጎጂዎቹና ተልጣሮቹ የትኞቹ ናቸው?››

‹‹አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ካሉት ማለትም ነው?››

‹‹አሁን›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹በጣም ጎጂዎቹ፣ በጣም ተልጣሮቹ. . .›› አለ ራምሲ የአለታውን አገላለጽ በመድገም ኢያሰበ። ከጥቂት ቆይታ በኋላም በአለም ዙሪያ በጥናት ደረስኩባቸው የሚላቸውን የየአገሮቹን ቡድኖች ስም ዘረዘረለት።

‹‹የጋራ አላማ የሚሉት ነገር የላቸውም?›› አለ ኤድዋርድ፣ ብዛታቸው አስገርሞት።

‹‹ሀገር ጎሳዝም ይውደም›› ይላሉ ብዙዎቹ። በግለሰብ ደረጃ ብዙዎቹን የፋኖ ቡድኖች የሚያስተባብረው የሁሉም የበላይ የሆነው ካርሎስ የተባለው አውት ፋኖ ነው።››

‹‹አሃ ካርሎስ›› አለ ኤድዋርድ የራምሲን ማስታወሻ እየነካ። ‹‹ነፍስ ገዳዩ ቪኤዙዌላዊ? የሰበሰብካቸውን የሱን ፎቶግራፎች ተመልክቻቸዋለሁ። ሲያዩት ጨዋ ይመስላል።››

"መልኩ እንዳያሞኝም" አለ ራምሲ፡ "ካርሎስ ሲበላ ቆራጥ ነው። የሰው ህይወት ለሱ ምኑም አይደለም። ታሞቲ ከመሞኑ በፊት ካርሎስ ጦሩን በሳቲን ሰፊር ሩ ቱሲ ውስጥ በሳቲን ሰፊር ሩ ቱሲ ውስጥ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ያኖር ነበር። መኻርቤል የተባለ ሊባኖሳዊ ጓደኛው በፊረንሳይ የስለላ ድርጅት ጀኮ መሪ እንዲሆን ከተገደደ በኋላ ሶስት የፊረንሳይ ስለላ ሰራተኞችን ወደ ካርሎስ መርተዋ ነበር። በታለ መጠይቁ ወቅት ካርሎስ ሽንት ቤት ደርሶ ለመመለስ ፈቃድ ይጠይቃል። ከሽንት ቤትም አንድ አውቶማቲክ መሳሪያ ይዞ ይመለስና ሁለቱን ሰላሞች ገድሎ ሶስተኛውን በጽኑ አቁስሎ የመሪነትን ጓደኛውን ማንባሩ ላይ መቶ ያገድልና ያመልጣል። ይህ ሁሉ የተፈጸመው በአሰር ሰከንዶች ውስጥ ነበር። ካርሎስ የፈጸማቸው ሌሎች ድርጊቶችም ማስታወሻየ ውስጥ ይገኛሉ።"

"ዝርዝራቸውን ማስታወስ አልችልም" አለ ኤድዋርድ፡ "ብዙ ጀብዱዎች ናቸው።"

"ካርሎስ የጂጎን ሽፍቶች በእስራኤል ሶድ አውሮፕላን ማረፊያ የፈጸሙትን ሞፍጨፋ ለማቀናበር ረድቷል" አለ ራምሲ፡ "ጎሪስ ውስጥም ባንድ መድኃኒት ቤት ፈንጅ አጥምዶ ሁለት ሰዎች ሲገድል አሰራ ሁለቱን አቁስሎ መድኃኒት ቤቱ በእሳት እንዲጋይ አድርጓል። በአርሴ አውሮፕላን ጣቢያ ደግሞ ፔፐር መኪናውን ወደ ማኩበከቢያ ስፍራው እያሽከረከረ ተጠግቶ የእጅ ርኪት ተወንጫፊውን 136 መንገደኞች ባሳፈረ የያንግ 707 አይሮፕላን ላይ ተኩሰ። ሆኖም አውሮፕላኑን አሳጥንውም። አቴንስ ላይ ወደ ኢንቴሊ ይበር የነበረ የፊረንሳይ አውሮፕላን እንዲጠለፍ አድርጓል። በሚሉ እንደማስበው ካርሎስ በተሳካ ሁኔታ የተካሄደለት ጀብዱ በ1975 ቪየና ላይ ከአምስት ጓደኞቹ ጋር መንገድ ላይ የቆሙት መኪና አስነስቶ ወደ ነዳጅ ሳዚ አገሮች ድርጅት ዋና ጽህፈት ቤት ሲወስድ ነበር። ካርሎስና ቡድኑ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ገብተው ሶስቱን ዘቦች ከገደሉ በኋላ አስራ አንድ የነዳጅ ዘይት ሚኒስትሮችን አፍነው ወደ አልጀርስ ከወሰዱ በኋላ የጠየቁትን አስፈጽመው ለቀቁ። ይህ ሁሉ ብልሃትና ወኔ ይጠይቃል። ካርሎስ በጣም ከባድ ሰው ነው።"

"አንጋዠህ ካርሎስ አሁንም እዚህ አካባቢ እንዳለ አስመስለህ ነው።

በትርብ አለ እንዴ?››

‹‹እኔ እንጃ›› አለ ራምሲ፣ ‹‹ጋሪስ ላይ ታሪኩን ሰጽፍ ሳለ በርግጥ ሰውየው ነበረ። ስለሱ በሕይወት መኖር የሰማሁትም ያኔ ነው።››

‹‹በሕይወት መኖሩን አታውቅማ?››

‹‹በውነቱ አላውቅም። ግን ያለ ይመስለኛል። ምክንያቱም ስለመሞቱ የተነገረ ነገር የለም። በ1982 ሆላንድ አካባቢ ሆኖ በርሱ የጣት አሻራ ፊርማ ለፊረንሳይ የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ማስጠንቀቂያ ልኮ ነበር።››

‹‹አሁን የት ያለ ይመስልሃል?››

ራምሲ ትከሻውን ሰበቅ አደረገ። ‹‹ለንደን፣ ቦን ወይም ደማስቆ ሊሆን ይችላል። ይበልጥ የሚታመነው ግን ጋሪስ እንደሆነ ነው።››

የኤድዋርድ አይን ከኋላ ራምሲ ወደ ቪክቶሪያ መልሶም ወደ ኋላ ራምሲ ተሽከረከረ። ‹‹ይህ ሁሉ ምን ይመስልሃል ኒክ? ይህ ካርሎስ የሚሉት ኮሙኒስት ይሆን?››

ራምሲ ራሱን በአሉታ ነቀነቀ። ‹‹አይመስለኝም። በማስታወሻየ ላይ ከሰፈረው ማብራሪያ በርግጥ ሊመስልም ይችላል። አባቱ ኮሎምቢያዊ ሲሆን ወደ ቬኔዙዌላ ተባውሮ_ሚሊዮነር ሊሆን የበቃ ሰው ነበር። አባቱ ሶስት ወንድ ልጆች ሲኖሩት ስማቸውን በሊኒን ስም ነበር የሚጠራቸው። አባቱ ማርክስ ሶት ነበር። ካርሎስን በሊኒን ሁለተኛ ስም ኢሊች ብሎ ሰየመው። ካርሎስ በሃቫና የኮሙኒስት ሰልጠና እንዳገኘ ይገመታል። በኋላ ደግሞ ሞስኮ ውስጥ የጋትረስ ለመምህ ወዳጅነት ዩኒቨርስቲ ተማረ ነበር። ግን በጠላትነትና በሴሰኛነት ወቀፍ ከትምህርት ተባረረ። ኮሚዩኒስት እንኳ አይመስለኝም። ቪየና ላይ የነዳጅ ላኪ አገሮች ድርጅት ሚኒስትሮችን ሲጠልፍ ከተጣላፊም እንዱ የላውዲ አረቢያው የነዳጅ ሚኒስትር ነበሩ። በኋላ ሳውዲ ዓረቢያ ከካርሎስ ጋር ድርድር ባደረጉበት ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ካርሎስ የኮሚዩኒስትም ሆነ የፍልስጥኤምን አላማ አያራምድም።››

ኤድዋርድ አውንም እንደተወናበደበት ነው። ‹‹ግን ለምንድን ነው ከአገር አገር እየዞረ የሚጠልፈውና የሚገድለው?››

ራምሲ ትከሻውን ነቀነቀ። ‹‹የተረጋገጠ ነገር የለም። የማኦን ፍልስፍና በመከተል በአለም አቀፍ አብዮት እንደሚያምን ይገመታል። ግን ከአላማዎቹ ሁሉ ተልቁ ጀብዱ መፈጸም ሳይሆን አይተርም። ምናልባት ገንዘብ ፍለጋም ሊሆን ይችላል። አሰቢያም ስልጣን ያምረው ይሆናል። ከጀርመኖቹና ከአረቦች የተመለመለ የራሱ ቡድን ሳይኖረው አይተርም።››

አሳታሚው አዲስ ሲጋራ አውጥቶ ካቀጣጠለ በኋላ ለአፍታ አያቅማማ ‹‹ይህን ሁሉ፣ በተለይ ስለካርሎስና ስለቡድኑ ፍንጩን ከየት አገኘኸው?››

‹‹ብዙ ፍንጮች›› አለ ራምሲ፣ ‹‹ዋናው ምንጭ የካርሎስ ቡድን አባል የሆነ ወሬ አቀባይ ነው። ይህ ሰው በእርግጥ በካርሎስ ቡድን ውስጥ ደህና ቦታ ያለው ሰው አይደለም። ፖሪስ ሳለሁ ለወሬ አቀባዮች ምላሽ በምሰጥበት ወቅት ይህንን ሰው አግኝቻት። ሰውየው የካርሎስ ቡድን አባል የሆነች ፍቅረኛ ነበረችው፣ ታዲያ ለሷ አንዳንድ ወሬ ያቀብላት ነበር። አሁን ያነበብኸውን ዘገባ ላቀናጅ የበቃሁት ይህ ወሬ አቀባይ የጠየቀኝን አንድ ሺህ ዶላር ከሚስተር ሃሪ ዴትዝ ተቀብየ በመስጠት ነው።››

‹‹የበለጠ መረጃ እፈልጋለሁ›› አለ አርምስቱድ ብድግ ብሎ ሲጋራውን እያቀጣጠለ።

ራምሲ ተደነቀ ‹‹ስለካርሎስ?››

‹‹ስለ ካርሎስና ስለቡድኑ።››

‹‹የሚቻል አይመስለኝም›› አለ ራምሲ።

‹‹የማይቻል ነገር የለም›› አለ አርምስቱድ። ተጥሎም በእያንዳንዱ አርምጃው ልክ እያወራ በዚያው ከጻር ጻር ተንማለለበት። ‹‹የፋኖምችን ዘዛ በሚመለክት ባሳቱ ጊዜ ተጀምሮ የተጨናገፈውን ፕሮጀክት ልተዋልበት እፈልጋለሁ። ዋናው ዒላማም ካርሎስ መሆን አለበት። ስለዚህ ባሰቸኳይ ወደ አውሮፓ ትመለሳለህ። ከቨኮዶሪያ ዊስተን ጋር ፖሪስ ትሂጻላችሁ። የምትፈልጉት እርጻታ ሁሉ ይደረግላችኋል።››

ራምሲ የቨኮዶሪያን አደኖች ተመለከተና ሽምትት አለ። ‹‹ይሽ የሴት

ስራ አይመስለኝም. . .›› ብሎ ከመናገሩ ቪክቶሪያ አቋረጠችው።

‹‹ገና ኒክ፣ የወንድ ትምክህተኝነት እዚህ ላይ አይሰራም። ፊሪንሳይኛ መናገር እችላለሁ። ፓሪስን ደግሞ ሰስት ጊዜ ስላየሁዋት መግቢያ መውጫዋን አውቀዋለሁ። በዚህ ስራ ትልቅ አርዳታ ላደርግ እችላለሁ።››

‹‹እኔም። እስማማለሁ›› አለ ኤድዋርድ ነጠት አድርጎ፣ ‹‹በዚህ ስራ ላይ እጂ ታስፈልግናለች። ምክንያቱም ወንዶችን ብቻ ሳይሆን ሴቶችንም ሙምር የሚነካካ ታሪክ እንዲጥርብልኝ እፈልጋለሁ።››

ዋናውንና ለሃራ ዴትዝ የገለጸለትን ምክንያት ግን ካፉ ሊያወጣው አልደፈረም። ለኸግ ዌስተን ልጅ አንድ ነገር አድርጎ አባቷን የበለጠ ሊያስደስተው ይፈልጋል። ኸግ ዌስተን አሁን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የፓሪስ ፀሐፊ ነው። አንድ ቀን ኸግ ዌስተን አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል። ‹‹በዚያ ላይ ቪክቶሪያን ለዚህ ስራ የምልክበት ሌላ አነስተኛ ምክንያትም አለኝ›› አለ ኤድዋርድ ሰስለስ ብሎ። ‹‹ሁለታችሁ ፓሪስ ላይ ስትታዩ ባልና ሚስት ቱሪስቶች ልትመስሉ ትችላላችሁ። በርግጥ ሦስል የማስመሰግባችሁ ለየብቻ ነው። ደግሞም በናንተ ስራና በሪኮርድ ጋዜጣ መካከል ግንኙነት የሌለ መምሰል አለበት። ስትሰሩ ጋዜጠኝነታችሁ መታወቅ የለበትም›› ካሸ በኋላ ወደ ወንበሩ ተመለሰና ‹‹እንደሚመስለኝ ኒክ ስራህን ከሀርሎስ ወሬ አቀባይ ጋር በመግናኘት ልትተዋወል ትችላለህ። ስመ ማን ነበር?››

‹‹አዘጦት።››

‹‹መልካም፣ አዘጦት በመጀመሪያ አሁንም ፓሪስ ውስጥ መኖሩን አረጋግጥ። ይህን ማድረግ ትችላለህ?››

‹‹አሱን ማግኘት የሚችል የእንድ የሦቱል አስተናጋጅ ደላላ አለኝ።››

‹‹አደራህን በርታ›› አለ ኤድዋርድ ‹‹አየህ ካርሎስ በትርቡ የሚያደርገው ጠፋ፣ ዘረፋ ወይም ተመሳሳይ ተግባር ይኖረው እንደው ሳውቅ እፈልጋለሁ።››

‹‹እዚህ ላይ በኳ›› አለ ራምሲ እየተጠራጠረ።

‹‹እኔም የምከፍለው ብዙ ነው›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹አሀመት ላልከው ወራ አቀባይ አስር ሺህ ዶላር ልትከፍል ትችላለህ። የበለጠ ፍንዮ ሲሰጡ ለሚችሉ ደግሞ የበለጠ እከፍላለሁ።››

ራምሲ በሃሳብ ተዋጠ። ‹‹ደግሞም አህመት ስለካርሶስ ሊሰጠን የሚችለውን ፍንዮ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ አላውቅም። ግንዘብ እዚህ ቦታ አይሰራም። በርግጥ ፋኖዎች ግንዘብን ይጠቀማሉ፣ ግን የእንቅስቃሴያቸው አላማ ግንዘብ አይደለም። ፍላጎታቸው ርዕዮተ ዓለማዊ ነው።››

‹‹በኔ አመለካከት ርዕዮተ አለም ማለት ግንዘብ ነው›› አለ ኤድዋርድ በፍጥነት፣ ‹‹ግንዘብ ሁሉም ነገር ነው። አሁን ትረዳዋለህ። ለጊዜው ግን ከአህመት እንጀምር። በሉ ለጉዞው ተዘጋጁ። ጉዞ ነገ ነው። ጋሪስ እንደደረሳችሁ ደጎል አውሮፕላን ጣቢያ የሚተበላችሁ ማርቸዲስ መኪና ከነሾፌሩ ይዘጋጅላችኋል። የምትሂዱት የአንደኛ ማዕረግ አገር ጎብኚዎች ሆናችሁ ነው። አዲስ ዜና ስታገኙ በግል ስልክ ደውሉልኝ። ከዚህ በኋላ ሃሪ ዴትዝ ወይም እኔ የሚተላለፉን ሰራችሁን እናሳውቃችኋለን። መልካም ጉዞ።››

* * *

ከአውሮፕላን ወርደው መኝታ ቤታቸው ሲደርሱ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሆኖ ነበር። በጉዞው የተዳከሙት ቪክቶሪያ እንደተጋደመች እንቅልፍ ወሰዳት፣ ከረጅም ጉዞ ጋር የተላመደው ኒክ ራምሲ ግን ከመተኛቱ በፊት መኝታ ክፍሉ ውስጥ ውስኪውን እየተጎነጨ የወትሮውን በፋኖዎች እንቅስቃሴ ላይ ያጠናቀረውን ማስታወሻውን ሊያገላብጥ ችሎ ነበር።

በማግስቱ እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ። ከሦቱላቸው ወጥተው በኒክ ራምሲ መሪነት ግማሽ ሰዓት እንደተጓዙ አንድ ሦቴል በር ላይ ሲደርሱ ‹‹ወደ ውስጥ እንግባለን። እኔ ላነጋግራቸው። መጠጥ እገዘሽ በወታ ጠብቂኝ›› አላት።

‹‹ምንድነው የምጠጣው?››

‹‹የፈለግሽውን።››

ራምሲ የሚያሳያት ንቀትና በተደጋጋሚ እያን እንደማይፈለግ ተቀጥላ መመልከቱ አብግኗታል። በደመነፍስ ጥርያን ነክሳ እየተከተለችው ወደ ውስጥ ገባች።

ራምሲ አንድ በርጩማ ላይ ሲቀመጥ ቨክቶሪያም ከጎኑ ቁጭ አለች። አንድ ጎባጣ አስተናጋጅ እጅቹን ወደኋላ አጣምሮ ትእዛዞቹውን የሚጠባበት ይመስል ከፊት ለፊታቸው ቆመ። ራምሲ ሲጋራውን አቀጣጥሎ ‹‹ውሰኪ›› አለ።

ቨክቶሪያ ራምሲ ያዘዘውን በማዘዝ እያም ከሱ አኩል መሆኗን ልታሳየው ወስና ነበር። ግን በዚህ ሰዓት ከባድ አልኮል መጠጣቱ ከእኩልነት ይልቅ የበታችነት ምልክት መሆኑን እምና ተወችው። ያለጥርሃት፣ ‹‹ኮካ›› አለች።

አስተናጋጁ መጠጣቸውን በማቅረብ ላይ እንዳለ ራምሲ ወደፊት አስግጎ ‹‹መሴ፣ ባለፈው እዚህ ሳለሁ፣ ማለቴ ካንድ አመት በፊት ሂንሪ የተባለ አስተናጋጅ ወዳጄ ነበር። አውን. . . ››

አስተናጋጁ አቋረጠው። ‹‹አለ፣ ጓዳ ልብስ እየተየረ ነው።››

‹‹እንግዳ እንደሚፈልገው ልትነግርልኝ ትችላለህ?››

ጎባጣው አስተናጋጅ በቡና ቤቱ በአንደኛው በር በኩል ከወጣ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከትከሻው ሰፋ ያለ መልከ ቀና ሰው የነጭ ጃኬቱን ቁልፎች እያስተካከለ ብቅ አለ።

‹‹ሃይ ሂንሪ›› አለ ራምሲ፣ ‹‹አስታወስከኝ?››

ሂንሪ ቀስ በቀስ ፈገግ እያለ በመምጣት ‹‹መሴ ኒክ እንደምነህ?›› አለው።

‹‹በጣም ደህና ነኝ። እንደምታየኝ በትርቡ አግባ፣ ከባለቤቴ ጋ ተዋወቁ።›› ሂንሪ ጥቅ ባለ ሰላምታ ከቨክቶሪያ ጋር ተጨባበጠ።

‹‹የአብርሃምና የሳራ ጋብቻ። ኧረ ለመሆኑ ይህን ጉዳት ሽማግሌ

እንዴት ልታገኚ ቻልሽ?›› ሲል ቀለዳት።

‹‹ለግንዘብ›› አለች ቪክቶሪያ ሙሉ ለሙሉ ፈገግ ብላ።

‹‹እሽ ሄንሪ፣ ደህና ነህ ወይ?›› ጠየቀ ራምሲ።

‹‹እኔማ የልጅ ልጅ አድርሻለሁ›› በማለት ሄንሪ ከኪሱ ቦርሳ አንድ ፎቶ ግራፍ አውጥቶ ሰጣቸው። ራምሲና ቪክቶሪያ ፎቶውን ተጠጋግተው ተመለከቱት።

‹‹አንኳን ደስ ያለህ ውድ ኢያት›› አለ ራምሲ ፎቶውን እየመለሰ።

‹‹አናንተም ለኤጉላ ነዋ የመጣችሁት?››

‹‹ለሥራ›› አለ ራምሲ።

የሄንሪ ገጽታ ኩፍትርትር አለ ‹‹የበፊቱ አይነት ስራ?››

‹‹የበፊቱ አይነት›› አለ ራምሲ ድምጹን ዝቅ አድርጎ።

‹‹አጅሬ አሁንም ፓሪስ አለ?››

‹‹አዎ።››

‹‹ሳነጋግረው እችላለሁ?››

‹‹መቼ?››

‹‹በተቻለ ፍጥነት።››

‹‹የት ነው ያረፋችሁት?››

ራምሲ ያረፉበትን ሆቴል አድራሻ ሰጠ።

‹‹በአንድ ሰዓት ውስጥ እንዲደውልላችሁ አደርጋለሁ።››

‹‹አመሰግናለሁ›› ራምሲ ከበርቴጣው ተነስቶ ለመጠጡ ከከፈለ በኋላ ለሄንሪ 500 ፍራንክ ሸኘጥ አድርጎ ከቪክቶሪያ ጋር ከሆቴሉ ወጣ።

ባቆራረጡ መንገድ እየተጣደፉ ወደ ሆቴላቸው ተመልሰው የሚያወልላቸውን ስልክ በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር።

ስልኩ የተደወለው ከሃምሳ ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ነበር። ራምሲ አፈጥ አደረገው። «ሂድ?»

«ሚስተር ራምሲ?»

«ነኝ።»

«አዘመት ነኝ።»

«ታዲያስ አዘመት። በመደወልህ ደስ ብሎኛል። ልታነጋግረኝ ትችላለህ?»

«አይሆንም፣ አሁን አልችልም። በሴን ዳርቻ፣ የሞንቱቢሉ መዋኛ ስፍራ አሳ አጠምዳለሁ። ማለቱ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እዚያ እንነጋገር።»

«ጥሩ፤ ልክ በዘጠኝ እንዳላጣህ።» ራምሲ ስልኩን ዘጋ።

«ምን ጊዜ?» አለች ቪክቶሪያ የንግግራቸው ፍጥነት አስገርሟት። «ጥሩ ውጤት ተገኘ?»

«ሁኔታው አላመቸውም። ሊያነጋግረኝ አልቻለም። ተጠሮ ሰጠኝ። በሴን ዳርቻ አሳ እንደሚያጠምድ ነግሮ የምንገናኝበትን ቦታ ጠቁሞኛል።»

«እውነት አሳ ያጠምዳል ማለት ነው?» አለች ቪክቶሪያ ግራ ተጋብታ።

«የኮድ ንግግር ነው። ስፍራው አመቺ ስለሆነ ንግግራችንም ሆነ እኛ ራሳችን ልንጠለፍ እንችልም። አየሽ ካርሎስ የራሱን ቡድን አባላት እንትስታሲ ሳይተር በጥብቅ ስለሚከታተል አዘመት ሲበዛ ጠንቃቃ ነው።» ራምሲ ሰዓቱን ከተመለከተ በኋላ «ጥቂት ሰዓቶች አሉን። በፓሪስ የራኮርድ መኪና የሆነውን ሲድ ሉታስን ማነጋገር አለብኝ። አንቺስ ምን ስትሰሪ ትቆያለሽ?»

«ትንሽ ልተኛ» አለች ቪክቶሪያ፣ «ወደ አዘመት ስትሄድ ቀስቅሰኝ።»

ከምሳ በኋላ ቪክቶሪያ እንቅልፏን ጨርሳ ፊቷ እያበራ አዘመት ወደ ተቀጠረበት ስፍራ ከራምሲ ጎን ትገባለች።

‹‹በዚህ ታች›› አለ ራምሲ፣ ከመንገዱ ተገንጥለው ወደ ሲን ወንዝ ዳርቻ በሚያስወርዱት የድንጋይ ደረጃዎች እየተጠመዘዘ። ቪክቶሪያ ተከትላው ወረደች። ደረጃውን እንደጨረሱ ከወንዙ ጎን ሰጎን በተዘረጋው የድንጋይ ንጣፍ ይጓዙ ጀመር። ከበስተቀኛቸው ከተንጣለለው ወንዝ ጠርዝ ላይ እራት ወይም አምስት አሳ አስጋሪዎች ፈንጠር ፈንጠር ብለው ይታያሉ።

‹‹አጠገባችን ያለው ነው አህመት፣ ባለ ባርኔጣው›› አሳት ራምሲ። አህመት ቀጠን ያለ ወጣት ሲሆን ከአጠገቡ ትርጫት አስቀምጦ የቅርዛ መንጠቆውን ወንዙ ውስጥ እየጨመረ ነው።

ራምሲ ሲጋራ የሚያያይዝ በመምሰል ቆም አለና በዝግታ ለቪክቶሪያ ‹‹ልትከተይኝ ትችያለሽ፣ ግን በጣም አትጠጊኝ። ደሞ አትነጋገሪ ሚስቴ መሆንሽን እንግረዋለሁ። እሺ እንሂድ›› አሳት።

ከአህመት ትርጫት ትይዩ ሲደርስ ራምሲ ቆም አለ። መጀመሪያ ወዲያ ወዲህ ተግላመጠ። ሊሎች አሳ አስጋሪዎች ራቅ ራቅ ያሉ በመሆናቸው ንግግራቸውን ሊሰሙ አይችሉም። ራምሲ ወደ ትርጫቱ አመለከተ። ‹‹ባሬ ስንት አሳ አሰገርህ አህመት?›› ጠየቀ ራምሲ።

‹‹እንደምታየው ነው።›› መለሰ አህመት። ራምሲ በርከክ ብሎ ትርጫቱን ከፈተው። ባዶ ነበር።

አህመት ፈጠን ብሎ እየተቆናጠረ ‹‹ሲድ ደግሞ ማናት?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹ባለቤቴ።››

‹‹ጥሩ፣ በል ፈጠን አድርግው።››

‹‹እንደበፊቱ ነው።›› አለ ራምሲ፣ ‹‹አንድ መረቧ እፈልጋለሁ፣ ክርሶስ ፓሪስ አለ?››

‹‹ሊሆን ይችላል።››

‹‹በትርቡ አንድ እንትስታሲ አትዶ እንደሁ ማወቅ እፈልጋለሁ።››

‹‹አይቻልም። ሂድ ከዚህ።››

ራምሲ ግን ንትንት አላለም።

‹‹አስር ሺህ ዶላር እከፍላለሁ።››

ለመጀመሪያ ጊዜ አህመት ራምሲን ገልመጥ አድርጎ ተመለከተው፣ የሰማው እውነት መሆኑን ሊያረጋግጥ የፈለገ ይመስል።

‹‹አስር ሺህ ዶላር›› ራምሲ ደገመው።

አህመት ወደ አሳ ማጥመዱ ተመልሶ ጥቂት ካትማማ በኋላ በከንፈሩ ጠርገ እየተናገረ፣ .

‹‹ዛሬ ማታ እኩለ ሌሊት ላይ እደውልልሃለሁ። ደህና ሁን›› አለ ባሎሩ። ራምሲ መለስ ብሎ የቪክቶሪያን ክንድ ጨብጠ በመጣበት ተመለሰ።

‹‹እሽ?›› ጠየቀች ቪክቶሪያ በሹክሹክታ።

‹‹ግና ነው›› አላት ራምሲ። ምሽቱን ያሳለፉትና ራት የበሉት በእንድ የቻይና ምግብ አዳራሽ ነበር። ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከመሆኑ በፊት ወደ ሆቴላቸው ተመለሱ።

ለስድስት ሰዓት ስምንት ደቂቃ ሲቀረው ስልኩ ጮኸ።

‹‹ራምሲ ነኝ።››

‹‹አህመት ነኝ፣ ከዋናው ምንጭ ምንም መረጃ ላገኝ አልቻልኩም።››

‹‹በጣም ያሳዝናል።››

‹‹ግን ሌላ ነገር አለኝ።››

‹‹እሺ, ቀጥል፣ ቀጥል።›› ራምሲ ተቁነጠነጠ።

‹‹በግንባር ይሻላል። አሁን አይመችም። ነገ ከሰዓት በኋላ በአስራ አንድ ሰዓት፣ ካሊፎርኒያ ሆቴል የመኝታ ቁጥር 110 ውስጥ። በሩን አልቆልፈውም›› አለ አሁንም ባሎሩ።

‹‹እገኛለሁ።››

‹‹አንተ አታስፈልግም። ባለቤትህን ላክት። ግንዘቡን ይዛ መምጣት አለባት። በዶላር ነው የምቀበለው።››

‹‹ችግር የለም። አመሰግናለሁ አህመት።››

‹‹አንድ ጥንቃቄ ላናግኝ አልቀረንም›› አላት ቪክቶሪያን፣ ስልኩን ከዚያ በኋላ።

‹‹አህመት እንደሚለው ከሞናው ምንኛ ምንም መረጃ ሊያገኝ አልቻለም። ዋና ምንጭ የሚላት የካርሎስ ቡድን አባል የሆነችው ጥቅሻው ናት። ግን በግንባር የሚነግረን ሊላ መረጃ አግኝቷል። ካሊፎርኒያ ሆቴል ቁጥር 110 በ11 ሰዓት ይጠብቅሻል። ቂት ላይ የጠየቀውን ገንዘብ ከባንክ አውጥተን ይዘሽ ትሄጅና አህመት የሚነግርሽን ካዳመጥሽ በኋላ ትሰጭዋለሽ።››

‹‹ግን ያገኘው መረጃ ምን ይመስላሃል?››

‹‹ካርሎስ ሰሞኑን ሊያደርግ ያቀደውን የሚመለከት።››

‹‹አምላኬ፣ እኔስ ጭንቅ ጭንቅ አለኝ›› አለችው።

* * *

በካሊፎርኒያ ሆቴል መግቢያ በር ላይ የደረሱት ከሰዓት በኋላ አስራ አንድ ሰዓት ሊሞላ አምስት ደቂቃ እንደቀረው ነበር። በቀጥታ ወደ አሳንሰሩ አመሩ።

‹‹እንግዲህ›› አለ ራምሲ የአሳንሰሩን ቁልፍ ጫን እያደረገ። ‹‹ቁጥር 110 የሚገኘው በሚቀጥለው ፎቅ መሆኑ ነው። በሩ ክፍት ነው የምታገኘው። በቀጥታ ግቢ። ለመሆኑ ገንዘቡን ይዘሻል?››

‹‹ይኖለሀ። ግን ኒክ፣ ስውየውን ባጣው ምንድነው የማደርገው?››

‹‹ዶሎ ተመለሽ። ግን አታስበ. አህመት ያለጥርጥር ይጠብቅሻል።››

‹‹ገንዘቡን ከመክፈሌ በፊት የሚነግረኝን መጻፍ አለብኝ አይደል?››

‹‹ጎሽ፣ ገብቶሻል በቃ።››

‹‹የሚሰጠኝ ጥንቃቄ የማይጠቅም ቢሆንስ?››

‹‹ያም ሆነ ይህ ገንዘቡን ስጭው። ከሰውየው ጋር ግንኙነታችንን መቀጠል አለብን።››

አሳንሰሩ ተከፈተ። «የት ነው ታዲያ ሰመለስ የማገኘህ ኢነ?»

«ቡና ቤቱ ውስጥ እጠብቅሻለሁ፤ መልካም እድል።» አሳንሰሩ ውስጥ ገብታ ወደ ላይ በጓንች መጠን ራምሲ ወደታች ሲተር አየችው። ወዲያው እንደኛ ፎት ደርሳ በመጠኑ ጨለም ባለው ኮሪደር በኩል ወደ ቁጥር 110 ታመራ ጀመር።

በሩ ዝግ ነበር። ማንኳኳት ይኑር አይኑርባት ስታመነታ ቆየችና እጇታውን ወደ ታች አለችው። ተከፈተ። ገባችና ከውስጥ ዘጋችው። ክፍሉ ጨለም በማለቱ ለአይን ያዝ ያደርጋል። ለክፍሉ ደብዛዛ ብርሃን ሊሰጠው የቻለው በበሩና በትልቁ ጥንድ አልጋ መካከል የቆመው የራስጌ መብራት ነበር።

ሰውየው ያለበትን ቦታ ለመለየት ጊዜ አልወሰደባትም። ከአልጋው በወዲያኛው ጠርዝ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተቀምጧል። የሚታየው ግን ጀርባው ብቻ ነው። ጫማውን እያሰረ መሆን አለበት።

«አሀመት» ተጣራች፤ «እመቤት ራምሲ መጥቻለሁ።» አልጋውን እየዞረች ወደ ሰውየው እየተጠጋች ቦርሳዋን ከፍታ ብዕርና ማስታወሻዋን ታወጣ ጀመር። ግን ቀረብ ስትል ድንጉት ትጥፍ አላት። መልሰ አልሰጣትም።

«አሀመት» እንደገና ተጣራችና ወደ ሰውየው በመሄድ ፋንታ መልስ አስኪሰጣት ቆም ብላ ጠበቀችው።

ዐጥታ።

አልተንቀሳቀሰም፤ ወይም ሰላምታ ሊሰጣት ቀና አላለም። አይንቀሳቀስም፤ ግዑዝ ነው።

ቀስ እያለች ቀረበችው፤ አሁን በግልጽ ይታያት ጀምሯል። እናቱና ትከሻዎቹ ተለዩዋት።

አሁንም ተጠጋች። የፊቤ እጇታ ጀርባው ላይ ታያት። ጨቤው ራስ ግን ተሰክዩበታል።

ጨነቀድን ልትለቀው ስትል ለጥቂት ዋጠችው። ሰውነቷ ራደባት። ተንዘፈዘፈች። በክፍሉ የሚሰማው ድምጽ የሚደልቀው የልቧ ትርታ ብቻ መሰላት።

«ስብእት ለአብ» አይኗን ጨፈነች።

ራሷን ማወቅ ስትጀምር ፍርሃት ዋጣት። ሊላ ሰውስ በክፍሉ ይኖር እንደሁ? ምናልባት አህመትን የገደለው ራሱ ቢኖርስ? በደመነፍስ ዙሪያዋን ተገላመጠች። ከቧና ከራሳው በስተቀር ማንም የለም። እንደምንም ተጠግታ የሆነውን ለማወቅ ወኦዋን አሰባሰበች። የጨቤው ስለትና የተቀደደው ሹሺ በደረቱ ደም ተበክሏል። እዚህም እዚያም ሰውነቱን ጨቤ ሸርክቶታል።

መለሰ ብላ በማጎንበስ መልኩን ለመለየትና በህይወት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ ፈለገች። የአይኖቹ ብሌኖች ከመሰርጎጻቸውና ከመግለበጣቸው ብዛት ሞራው ብቻ ነበር የሚታየው። አፉ የተከፈተ ሲሆን ወፈር ያለ የደም አረፋ በከንፈሩ ጠርዝ ወደ ጉንጩ ወርዷል።

የሰራ አካላቷ በጥርሃት እየዘፈነ ካጎነበሰችበት ቀና አለች። የሚባክን ጊዜ አልነበረም። ወደ በሩ ተንደረደረች። በመጨረሻው ቅጽበት የግድያ ሚስጥር ያዘሉ ፊልምና መጻሕፍትን ስትከታተል የኖረች ስለነበረች እንድ ነገር ትዝ አላት። በሚንቀጠቀጡ እጆቿ ከቦርሳዋ መሃረብ አውጥታ የእጅዋን አሻራ ከበሩ እጀታ ላይ ጠረጋ አጠፋች። ከዚያም በሩን በትከሻዋ ገፋ አድ ርጋ ከፍታ በኮሪደሩ ግራና ቀኝ ተገላመጠች። ማንም የለም። ሸመጠጠች።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ድንጋጤዋ ያለቀታት ቢሆንም ከራምሲ ጋር በቀጠሮዋ ቦታ ተገኝታለች። በተቆራረጠ ትንፋሽ የገጠማትን ነግራው ለድንጋጤዋ ማብረጃ ከማቀዝቀዣው ደረት ጅን አውጥታ ተጎነጨች።

የራምሲ መልሰ ፈጣን ነበር። ጊዜ ሳያጠፋ ኒውዮርክ ለኤድዋርድ አርምስቱድ ደውሎ ከእንትልፉ አስተስትሶ የወራው ምንድ ተግድሎ ማግኘታቸውን አረጻው። ቪክቶሪያ ያለወትሮዋ መጠጡን እንደተያያዘችው ናት።

ራምሲ ስልኩን ከመዝጋቱ በፊት «እሺ, ሚስተር አርምስቱድ ከርስም

ተለሞድ ትዕዛዝ እስኪደርሰን ባለንበት እንጠባበቃለን። ሰላም ያግናኝን›› ሲል ሰማችው።

‹‹እ. . እሱኮ በህይወቱ አስከሬን አይቼ አላውቅም›› አለችው።

ራምሲ ሶፋው ላይ ተንሰራፍቶ ተቀምጠ ሲጋጃውን እየተመለከተ፣ ‹‹መልሱን የሰጠው ካርሎስ ይመስለኛል›› አላት፣ ‹‹አርምስቱድ ደግሞ ሲላ ስራ እስክንሰማችሁ ስለሊሎች የፋኖ ቡድኖች አጥኑ ነው የሚለን›› አላት። ከዚያም አይን አይኗን እየተመለከተ ‹‹እስክ አሁን አስከሬን አይቼ አላውቅም አልሽኝ? ከእንግዲህ ግና ብዙ ታያለሽ›› አላት።

* * *

በፓሪስ የተፈጸመው ግድያ እውነት ከዚያ ቀን የራት ግብዣ በፊት የኤድዋርድ አርምስቱድን ሞንትላት አልመታውም ነበር። ሃሪ ዴትዝን በኢጣሊያው ምግብ ቤት በናኔ እል ባሉቦ ተጠሮ ሰጠው። በግል ለመነጋገር አመቺ ሰፍራ ሲሆን ኤድዋርድ ደግሞ ባሬ በዚህች አለም ከሁሉም አብልጦ ከሚያምነው ሰው ጋር ሊነጋገርበት የሚፈልገው አጀንዳ ነበረው። ይህ አጀንዳም በሕይወቱ ከማንም ጋር ከተነጋገረባቸው አርእስተ ጉዳዮች ሁሉ የላቀው እንደሆነ ገምቷል።

ሃሪ ዴትዝ ለሱ ታማኝ የሆነው የግል ሕይወቱን ለማበጀት ሲል እንደሆነ ኤድዋርድ ጠንቅቆ ያውቃል። ወዳዘጋጀው ወሳኝ ውይይት ከመግባቱ በፊት የሃሪ ዴትዝን ታማኝነትና የማንኑነታቸውን ጥብቅት ለመጨረሻ ጊዜ ሊገመግም አሰበ።

ከልጅነቱ ጀምሮ ብቻውን ያደገው ዴትዝ ከሊሎች ሰዎች ጋር ሊቀራረብ ያበቃው ኤድዋርድ ቺካጎ ላይ በሰጠው ስራ አማካኝነት ብቻ ነው። በዚህም የተነሳ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሃሪ ዴትዝ እንደሚወደው ብቻ ሳይሆን እንደሚያመልከውና እሱን ለማስደሰት የጣ እናትህን ግደል ቢለው እንኳን ወደኋላ እንደማይል ኤድዋርድ በፅኑ ያምናል።

እም፣ ያወጣውን እቅድ ሚስጥር ለሃሪ ዴትዝ ቢያዋየው ከሁሉቱ እንደማያልፍ ኤድዋርድ አረጋገጠ።

ያዘዘውን ስጋጌቲ እያሞሞጠ በኒክ ራምሲና በቪክቶሪያ ዊስቲን ላይ ጋራስ ስለደረሰው ነገር ተረክለት።

የግሪ ዴትዝ ቅንድቦች ከፍ አሉ። «ምን ትተልዳለህ? ወሬ አቀባዩን ቪክቶሪያ ተገድሎ አገኘችው?»

ኤድዋርድ የአምንታ ምልክት አሳየ «ብዙ መልእክት ያዘለ ግድያ ነው የተፈጸመው። ካርሎስ ራሱ ከተከታተልኸኝ ዋጋህን ነው የምሰጥህ እንዳሰኝ ነው የምቆጥረው።»

ዴትዝ በተራው የአምንታ ምልክት አሳየ።

«ሊሎች ፋኖምችም ቢሆኑ ተመሳሳይ መልእክት እንደሚልኩብን ነው የምጠብቀው።»

«ያለጥርጥር» ዴትዝ ተስማማ።

«ያ ሃሳብ ነው ሊላውን ታላቁን ሃሳቤን ያመነጨልኝ» አለ አሳታሚው፣ «ለዚህ ነው ባራ ካንተ ጋር ልነጋገር የፈለግሁት።»

«ያሰብክው ምንድን ነው አለታ?»

«ታላቅ ሀሳብ በርግጥ ሃላፊ የተጠነሰሰብኝ በይንገር ማምለጥ ላይ ያን ድል እንደተቀዳጀነው ነው። ይንገር ያተዳጀን ድል ትክሰ ወሬምች ራሳቸው እኛ ጋ እንደማይደርሱ ነው የሚያስተምረን። ልክ ያኔ እንዳደረግነው ትክክ ዜናምችን ራሳችን መፍጠር ይኖርብናል። አየህ ሃሪ፣ ራምሲንና የዊስተንን ልጅ ጋራስ ሰልካቸው እንኳ ከነሱ ምርምር ምንም የረባ ነገር ሊገኝ እንደማይችል አውቀው ነበር። ማንኛውም የሩኖ ቡድን ቢሆን ምንም ነገር ሊያሳውቀን እንደማይችል ወዲያውኑ ነበር የተረዳሁት። ግን ላረጋግጥ ፈለግሁ። ለዚህም ነበር ሪፖርተሮቹን ጋራስ የላክሁዋቸው። ይኸውልሃ ግምቱ ትክክል መሆኑን አረጋገጡልኝ። አየህ፣ ፋኖምች የራሳቸውን ሽብር የሚያካሂዱት ለራሳቸው አላማ ነው። የኛ ችግርና ጥላት ሊገቧቸው አይችልም። በርግጥ እቅዳቸውን ከፈጸሙ በኋላ ያደረጉት ነገር ዜና፣ ያውም ታላቅ ዜና ነው። ነገር ግን የኛ የግል ዜና ሳይሆን በአለም የሚኖች ማንኛውም ጋዜጣና ሬዲዮ ያተመውና ያናፋው ዜና ነው የሚሆነው።

ፋኖዎች ለማንም ቢሆን እንዲህ ልናደርግ ነው ብለው አስተድመው አይናገሩም። ተግባባን?››

‹‹ተግባባን›› አለው ሃሪ ራሱን እየነቀነቀ።

‹‹አየህ ሃሪ፣ ትናንት ሰሞኑን ጋዜጣችን ላይ ምን ልናሰፍር እንደምንችል ፋይል ላዘጋጀት ነበር። በርግጥ ብዙ የሚታተም ነገር አለ። የሲፖኛ ንጉስ በባስክ ግጠር ጉብኝት ያደርጋል። በስዊዘርላንድ የኑክለዬር ጦር መሳሪያ ትኦ ስብሰባ ይካሄዳል። የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር በካይሮ ሌላ ስብሰባ እያካደ ነው። በሎርድስ ደግሞ ጳጳሱ ንግግር ያደርጋል። ይህ ሁሉ ዜና ነው። ግን ሁሉም ትኩስ ዜና አይባልም። እኛ እናትመዋለን፣ ኒውዮርክ ታይምስ ያትመዋል፣ ሁሉም ያትመዋል፣ ቴሌቪዥኑ አሞናብሮ ያቀርበዋል፣ ራዲዮውም እንዲሁ›› ኤድዋርድ ሲጋራ አውጥቶ ሰኮሰና ‹‹በእጠቃላይ ሃሪ፣ እውነተኛ ዜና የሚባል ነገር የለም፣ አንተ ራስህ እስካልፈጠርከው ድረስ›› አለው።

‹‹እየሰማሁህ ነው አለቃ።››

‹‹በጥሞና እዳምጠኝ። ባለፈው ምሽት ከዚም ጋር ተኝቼ ልነሳ ስል አንድ ድንቅ ሃሳብ ጭንቅላቴን መታው። የይንገር ማምለጥ እንዴት የማላችን ዜና ሊሆን ቻለ? ራሳችን ስለፈጠርነው አይደለም? አሞ እኛ የሰራነው ክስተት ስለነበር ከሁሉም በላይ አደረግነ። አሁንም ከቆምንበት እንድንተጥል ነው ፍላጎቱ። ካንድ ዝንኛ የሽብርተኛ ቡድን ጋር ልሰራ አፈልጋለሁ። ታዲያ ታሪክን ራሳችን አቀናጅተን የምንሰራው ከሆነ ያ ታሪክ የማላችን መሆኑ አይቀርም። አባባሌ ገብቶሃል ሃሪ?››

‹‹ግን እንዴት?. . . እንዴት ነው ታሪክን ራሳችን የምንሰራው?››

‹‹ታሪክ እንዲሰራ የምትልከው የራስህ የፋኖ ቡድን በማደራጀት›› አለ አርምስቱድ በዝግታ፣ ‹‹በርግጥ አሁን ያሉት ፋኖዎች አልተባበሩንም። ስለዚህ የራሳችንን ቡድን እኛ እንመድናለን። ያ ቡድን እኛ ያዋቀርነው በመሆኑ እኛ ያዘዝነውን ብቻ ይፈጽማል። ያ ቡድን የፈጸመው ተልዕኮም እኛ ያሰራነው ታሪክ በመሆኑ የኛ የግል ዜና ይሆናል። ይህ ሂደት ነው በኒውዮርክ ቁጥር አንድ የሚያደርገንና በአለም የታወቅን ጋዜጠኞች

የሚያሰኝን። ምን ይመስልሃል ሃሪ?››

‹‹ታላቅ ሃሳብ አለኝ፣ የታላቆች ታላቅ! ፍፁም የጠራ ዕንስ ሀሳብ ማለት ይኸ ነው። አጓጓህ በትክክለኛው ፊር ነው። ግን?. . .›› ሃሪ አትማማ።

‹‹ግን ምን?›› ኤድዋርድ ሊያውቅ ፈለገ።

‹‹በርግጥ ሊደረግ ይችላል?››

‹‹ተደርጓል። በይንገር ጊዜ።››

‹‹ማለቴ የሩኖውን ቡድን ማግኘት እንዴት ይቻላል?››

‹‹በጉሰ ፖጋኖ በኩል›› ኤድዋርድ በትጽበት መለሰ።

* * *

በማግስቱ ጧት ኤድዋርድ ፖጋኖን ቢሮ ውስጥ ተቀበለው። ለፖጋኖ ግልፅ በመሆን ሁለንም ነገር እፍረጥርጠ ሊነግረው ኤድዋርድ ወስኗል። ነገር ግን መጀመሪያ ፖጋኖን በጓደኝነት ማትረብ እንዳለበትም ተገንዝቧል። ቡና አዘዘለት። በርግጥ ሁለቱ የሚያወሩት የጋራ ጉዳይ ሊኖራቸው ስለማይችል ኤድዋርድ በቀጥታ ወደ ነጥቡ ሊገባ ፈለገ። ቡናውን ጨልጠ አስቀመጠና ‹‹ጉስ›› አለ፣ ‹‹አንድ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ላዋይህ ፈለግሁ። ግን ከመነሻው እንስቶ ለኔ ስላለህ ታማኝነት ላረጋግጥ እወዳለሁ።››

ፖጋኖ ግንባሩን ሸበሸበ። ‹‹ወጥራም ደመወዝ ይከፍሉኝ የለም እንዴ? ያ ነው እኔን ታማኝ የሚያደርጉኝ።››

‹‹የበለጠ ልከፍልህ እችላለሁ›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹ፍፁም ታማኝም ነኝ። ግን የሚያዋዩኝ ነገር በሁለታችን የሚቀር ሚስጥር ከሆነ በፍፁም አይጠርጥሩኝ።››

‹‹ሙቶ በሙቶ ላምንብህ እፈልጋለሁ።››

‹‹ኧረ ሙቶ በሙቶ ይመኑብኝ።››

‹‹ማለቴ ማንንም ቢሆን ስንቀጥር ፋይል እናዘጋጅለታለን። ታዲያ ያ ፋይል በለውየው ላይ ቢ‘ግኘው የእለት ተእለት መረጃ ይጠናከራል።

እንቶንም ስንቀጥርህ እንዲሁ ፋይል ከፍተንልህ ነበር። ያ ፋይልም በለት ተለት መረጃ የተጠናከረ ነው።› ንግግሩን ጊታና ፓጋኖን ተመለከተው። ‹‹ከሁለት አመታት በፊት በልክሲንግተን የተደረገው ተኩስ ትዝ ይልሃል፣ በእንጥረኛች ላይ?››

ፓጋኖ መልስ አልሰጠም። በድንጋጤ አሳታሚው ላይ አፈጠጠበት።

‹‹ቢተኩሱ ወቅት አንድ የእንጥረኛው ደንበኛና እንዲት የመጥ ሚስት ሲገደሉ ዘበኛው ቆስሎ ነበር።››

‹‹ምን ማለትም ነው?›› አለ ፓጋኖ ‹‹በህይወቱ እኔ ማንንም ገድየ አላውቅም።

‹‹እኔም አልወጣኝም›› አለ አርምስቱድ፣ ‹‹የምናገረው የሆነውን ብቻ ነው። ታሪኩን ፈልፍሎ ያወጣው አንድ ያጣቱ ሪፖርተር ነበር። ያ ሪፖርተር ለቆሰለው ዘበኛ ብዙ የሚጠረጠሩ ሰዎችን ፎቶ ግራፎች እያቀረበ አሳየው። ታዲያ ዘበኛው የአንድ ሰው ፎቶ ሲያይ ወንጀለኛው እሱ መሆኑን አስረዳ። በፎቶው ላይ የሚታየው ሰው ሰም ጉስ ፓጋኖ ነበር።››

ፓጋኖ መልስ አልሰጠም። ትክዝ ብሎ ቀረ።

‹‹ይህን ሃት ለፖሊስ ማቅረብ እንችል ነበር›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹በማድረግም በጋዜጣችን ለህትመት የሚበቃ አንድ ወሬ እናገኝ ነበር። አባቱ ግን የራሱ ሰራተኛ የሆነ ሰው በእንዲህ ያለ ወንጀል ሲከሰስ ሊያይ ስላልፈለገ መረጃው በዚህ ፋይል ውስጥ ተቀብሮ እንዲቀር ተደረገ። እኔም ጉዳዩን ከዚህ ፋይል የማወጣው አይመስለኝም፣ ያንተ ትብብር ከታከለበት።›› አርምስቱድ ምላሹን ከፓጋኖ ይጠብቅ ይመስል ዝም አለ።

ፓጋኖ ሲጋራውን ከዚሱ አውጥቶ አቀጣጠለ። ከሲጋራው ምሳ ሞሱን በረጅሙ ዙግ አደረገና በከፈል ፈገግ አለ። ‹‹ግባኝ ሚስተር ኤድዋርድ፣ የሚፈልጉት መፅ በመፅ ታማኝ መሆኔን ለማረጋገጥ አይደለም? ሁለት መፅ በመፅ ታማኝ ነኝ›› አለ።

አርምስቱድ ከልቡ ፈገግ አለ ‹‹ጥሩ፣ በጣም ጥሩ›› ፋይሉን ወደ ጻር ገፋ አደረገ። ‹‹ከንግዲህ ይህን ጉዳይ ከወሬ አናገባውም።›› ከዚህ በኋላ

ኤድዋርድ የሚፈልገውን ለፓኦሎ ከመናገር የሚያግደው ነገር ሊኖር አይችልም።

‹‹የምታውቃቸው ወንበዴዎች ይኖሩህ ይሆን?›› አለውና አረፈው።

‹‹ወንበዴዎች?›› ያልተጠበቀውና የሆነ ልጅ የመሰለው ጥያቄ ፓኦሎን አስገረመው። ‹‹በተለያዩ ስፍራዎች ከወንበዴዎች ጋር ነው ያደግሁት።››

‹‹የለም፣ የለም›› ኤድዋርድ አቋረጠው፣ ‹‹የመንግድ ማጅራት መቺዎችን ማለቴ አይደለም። ስለአለም አቀፍ ወንበዴዎች ነው የማወራው።››

‹‹አ. . . አልገባኝም።››

ኤድዋርድ እንደገና ሞከረ፣ ‹‹በውሃ አገር ሥምር የሚንቀሳቀስ ሽብርተኛ አይነት ወንበዴዎችን ማለቴ ነው።››

‹‹አ፣›› አለ ፓኦሎ ‹‹አኒያ ተዘዋዋሪ ማፊያዎች? ኧረ የለም ማንም አላውቅም።››

ኤድዋርድ በትጽበት ፈቱ ተለዋወጠ። ፓኦሎ ግን ንግግሩን ቀጠለ። ‹‹ግን ያሉዋቸውን አይነት አለም አቀፍ ፋኖዎች፣ አሞ አንድ ቡድን አውቃለሁ።››

‹‹አቨ, ቀጥል።››

‹‹የሚገኙት ለንደን ነው። በርግጥ ሽብርተኞች የሚባሉ አይነት አይደሉም።››

‹‹ታዲያ ምንድናቸው?››

‹‹ለገንዘብ የሚሰሩ ምርጥ ሰዎች።››

‹‹ምን ሥራ?››

‹‹እንደ ዝርፊያ ያለ።››

‹‹ምን አይነት ዝርፊያ?››

‹‹ማንኛውንም አይነት።››

‹‹እና አንተ ከነሱ ጋር በርግጥ ግንኙነት አለህ?››

«በርግጥ ግራን ሃቨን መሀረ እያለሁ ክሩጊንስኪ የተባለ አሰረኛ ጓደኛ ነበረኝ። ክሩጊንስኪ በጥሩ ወላይ ተመርጠ የንልበት ስራ እንዲሰራ ከመሀረ ቤቱ ውጭ ይወስዱት ነበር፣ አንድ ቀን አመሰጣቸውና በብዙ መከራ ለንደን ገባ። ታዲያ ግንዘብ ይቸግራው ሰለነበር ከኩፐር የመንበዴዎች ቡድን ጋር ይገናኛል። አሁንም ክሩጊንስኪ ለንደን ሲሆን እንዲያውም አኔንም ጠርቶኝ ነበር።»

«ታዲያ ልትሂድ አስበህ አታውትም?»

«በፍጹም። በርግጥ ህጋዊ ፖስፖርት አግኝቻለሁ፣ ግን ከውጭ ሰዎች ጋር ልለምድ አልችልም። በዚያ ላይ የርስም ቋሚ ሰራተኛ ነኝ። ምን ያንተዝትዝኛል?»

አርምስቲድ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በሃሳብ እንደተመሰጠ በክፍሉ ተንሳፈፈ። በመጨረሻም ወደ መንበሩ እየተመለሰ «ጉስ» አለው «ይህ ቡድን ከሰራቸው ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ብትጠትስልኝ?»

«በእንግሊዝና በፈረንሳይ ብዙ ታላላት ስራዎች ሰርተዋል። በቦስተን ለምሳሌ የብራክን ዝርፊያ የፈጸሙት እነሱ ናቸው። ከዛላስ ጎው ወደ ለንደን በሚጓዘው ባቡር ላይም ታላት ዝርፊያ ፈጽመዋል። በፈረንሳይ የሶሲቲ ጀኔራልን ባንክ መልሎ አድርገው ዘርፈዋል። ያን ጊዜ ወደ ባንኩ የገቡት መሬት ውስጥ በተተበረ የጭነሽ ቱቦ ተሽሎክሉክው ነበር። ከባንኩ የዘረፉት አስራ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ነበር።»

«ለመሆኑ ይህ የኩፐር ቡድን ሰንት አባላትን ያቅፍ ይመስልሃል?» ጠየቅ ኤድዋርድ።

«ክሩጊንስኪ ባለፈው ዓመት እንደነገረኝ ከደርዘን ይበልጣሉ። ያውም አስር ቤት የገቡት ሳይቆጠሩ። ተመሳሳይ ፖስፖርትና ቪዛ መስራት፣ መጥ ለፍ፣ ፈንጂ ማጥመድና መዝረፍ ለነሱ እንደ ህፃን ጨዋታ ነው። ፖሊሳ ምናቸውም አይደለም። የሚፈልጉት ግንዘብ ብቻ ነው፣ ብዙ ግንዘብ።»

ኤድዋርድ ሳቅ አለ። «ሞልቶኛል።»

ፖጋሞም እንዲሁ ሳቅ አለ «እም ሰምቻለሁ።»

«ሕክምና ገና ሚስጢር ነው። እኔም እንደሪሉ ፖለቲካ አልወድም።»

ዮሃንስ አይኖች ጠበብ ብለው አባታቸውን ተመለከቱት። «ታዲያ ምንድነው የፈለጉት?»

«ዜና።»

«ዜና?» ጆጋኖ አስተጋባ፣ «አልገባኝም።»

«የምፈልገው ዜና መስራት ነው። ዜና መፍጠር. . . ለጋዜጣና ለቴሌቭዥን ጣቢያዎች። ወንበዴዎች ምን ሊያደርጉልኝ ይችላሉ።»

ጆጋኖ ከራሱ ዘንበል አለ። አሁን ሚስጥሩ ተግለጧል።

«የሃላቡ ምንጭ አንተ ራስህ ነህ አቶ ኤድዋርድ፣ «የይገዙ የሚመለሟቸው ብዙ ትልቅ ትምህርት ነው የሰጠኝ። ታሪኩን ፈጠርክ፣ ሰራህ፣ ማለት ይንገርን በቴክው አሸለኩና የግሌ ዜና ሰርቼ ኒውዮርክን እንቀጠቀጥኳት። ሊሎች ጋዜጦችን አበትኳቸው። አናታቸው ላይ ወጣሁ። ያ ነበር ዜና የመፍጠርን ሃሳብ የሰጠኝ። ታማለህን ግስ?»

«አዎ» አለ ጆጋኖ፣ «እየገባኝ ነው።»

«አየህ» ኤድዋርድ ሊያብራራ ሞከረ፣ «ባሁኑ ጊዜ ይህን ያህል ጠቃሚ ዜና የለም። አብዛኛውን ጊዜ ተኮናታኙቼ የኑን ያህል ጋዜጣ የመሸጥ አቅም አላቸው። ታዲያ አሁን የግላችን ዜና ያስፈልገናል። ያ ዜና ደግሞ ራሱ አስካለተፈጠረ ድረስ ራሳችን መፍጠር አለብን። ያ ነው የኔ ታላቅ ሃሳብ።»

«ባድና ለዚህ ጉዳይ ወንበዴዎች ያስፈልጉዎታል ማለት ነው?»

«አዎ፣ ሪከርድ ጋዜጣ ብቻ የሚያውቁና የሚያትመው ታላቅ ታሪክ የሚሰሩ ወንበዴዎች። በግልፅ ለማስተመጥ መሉ ጊዜአቸውን ለኔ የሚሰሩ የተደራጁ ጉልበተኞች አፈልጋለሁ። ዜና እንዲሰሩልኝ አፈልጋለሁ። ነፍስ ግጥፋት ላይሆን ጠለፋ፣ ሲሰሙት አለበጀሁ የሚያስኝ ዘረፋ እንዲያደርጉ ልሞላላቸው አፈልጋለሁ። ታዲያ በከፍተኛ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ልምድ ያላቸው ወንበዴዎች መሆን አለባቸው። የነሱ ሰራ ሁልጊዜ በሪከርድ የመጀመሪያ ገፅ ላይ የሚታተም ታላቅ ተግባር መሆን ይኖርበታል።»

ጋጋኖ አውን ሙሉ ለሙሉ ተገለፀለት። ‹‹ደህ እንኳ አደገኛ ሳይሆን አይቀርም›› አለ፡ ‹‹በዚህ ተግባር ላይ ሰምች ዜና ለመስራት ሲሉ ህይወታቸውን አደጋ ላይ ሲጥሉ ነው።››

‹‹አዎ፡ ለግንዘብ›› አለ ኤድዋርድ ጠበቅ አድርጎ። ‹‹የሁለቱ ሀገሮን ግንዘብ ያፈልጋል ብለዝቨዋል። እኔ ደግሞ ያን ግንዘብ አሰጣለሁ።››

‹‹ምን አይነት ግንዘብ ነው የሚሉት?››

‹‹ምናልባት ላንድ ተልዕኮ ሶስት ሚሊዮን ዶላር።››

ጉስ ጋጋኖ የቀስታ ፉጨት አመለጠው።

‹‹የሚያቅማሙ ይመስልሃል?›› ጠየቀ ኤድዋርድ

‹‹ሶስት ሚሊዮን ከተቀበሉ አይናቸውን አያሻሹም።››

‹‹ታዲያ ማን እንደሆንክ እንዲያውቁኝ አልፈለግህም። ስራችውን ራሱን ለማን ወይም ለምን እንደሚሰሩ ማወት የለባቸውም። ስራቸውን የማዝባቸው ባንተ በኩል ይሆናል። ምንም ጥያቄ እንዲኖሱ አልፈቅድላቸውም። ለእያንዳንዱ ተልዕኮ ግንዘብ ይከፈላቸዋል። አምቢ የሚሉ ይመስልሃል?››

‹‹ምን ቆርጢቸው።››

‹‹ታዲያ በርግጥ ታግኛቸዋለህ?››

‹‹አዎ።››

‹‹በል ስራህን ጀምር›› አለ ኤድዋርድ። ነገሩ ትዕዛዝ ነበር። ‹‹ላንተ ያሰብኩትን ክፍያ ደግሞ ጊዜው ሲደርስ አሰጣለሁ። አውን ግን በተጭታ ለንደን ሂደህ እሺና እምቢታቸውን አሳውቀኝ።››

‹‹አውኑን?››

‹‹ላሬ ሚታ የጉዞ ቲኬትና መስናዱ በሙሉ ይዘጋጅልሃል። መልሱን በእርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ እጠብቃለሁ።››

* * *

ከሁለት ተናት በኋላ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ኤድዋርድ የስልክ ጥሪ

ደረሰው። ስልኩን አንስታ ያቀበለችው ሚስቱ ሃና ነበረች። «ከለንደን ይፈለጋለ›› አለችው።

ኤድዋርድ ልቡ በኃይል ሲመታ ተሰማው፣ «በግል መስመሬ እንዲደውሉልኝ ንገሪያቸው›› አላት።

ወደ ጥናት ክፍሉ ሲንደረደር ሄዶ ግባና ከውስጥ ቆለፈው። ከሱ በቀር ሌላ ሰው ነክቶት ወደማያውቀው ነጭ ስልክ ተረብ አለ። ብዙም ሳይጉላላ ስልኩ አቃጨለ።

«ሂሎ?››

«ሚስተር አርምስቱድ?›› የሴት ድምጽ ጠየቀው።

«ነኝ።››

«ሚስተር ጋጋኖ ከለንደን ይፈልጉዎታል።››

«እሺ, አገናኝኝ።››

የጋጋኖ ድምጽ በመስመር፣ «አርስዎ ነዎት አለታ?››

«ሃይ ጉስ፣ እሽ መልሱን።››

«ኩፐር ተስማምቷል›› አለ ጋጋኖ፣ «ግን አንድ ነገር ብቻ።››

«ተስማምቷል ካልህ የምን አንድ ነገር ነው?››

«አርስዎን ራስዎን እዚህ መጥተው ሊያግኙም ይፈልጋሉ። እንደሚመስለኝ ሊያገዙዋቸው የሚፈልጉትን ነገር በግልጽ እንድትነጋገሩበት ሳይሆን አይቀርም። ማንነትዎን እንዳይለይ መፍትሄ እንፈልግለታለን።››

«ከፈለጉኝ ችግር የለውም›› ኤድዋርድ ቀልጠፍ ብሎ ተጠለ፣ «በታ እመጣለሁ።››

«ነገ ሊደርሱ ይችላሉ?››

«እችላለሁ። የመጀመሪያውን በረራ እይዛለሁ።››

«ልቀበልዎ እችላለሁ።››

‹‹ማንንም እንዲታሰክሉ።››

‹‹በፍፁም! ብቻዮን እጠብቅሻለሁ።››

ቀሰ ብሎ ስልኩን ዘጋው፣ አድዋርድ።

6

ጉስ ፓጋኖ እንግዳውን አውሮፕላን ማቢያ ከተተበለው በኋላ በቀጥታ በራሱ ስም ወደተመዘገበለት ሆቴል ወሰደው። አምስተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው የመኝታ ክፍል እስኪደርሱ ድረስ ኤድዋርድ ትዕግስቱን አጥቶ ይትበጠበጥ ነበር። አውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ በግል ለመነጋገር አመቺ አልነበረም። ኤድዋርድ ወደፊት የሚጠብቀው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ቸኩሏል።

‹‹ከልብ ተስማምተዋል?›› ሲል ገና መኝታ ቤት እንደገቡ ጠየቀው።

‹‹ኩፐር መስማማት ብቻ ሳይሆን ቋምጧል። ሶስት ሚሊዮን ዶላርኮ ቀላል አይደለም።››

‹‹ይህን ከፍያ ወደፊትም በሰራልኝ መጠን እንደሚቀጥል ነግረሀልኛል?››

‹‹በሚገባ! እሱኮ ነው ያጓጓው። ግን አላመነም። እርስም ራስም እንዲያነጋግሩት ይፈልጋል።››

‹‹በዘኩሌ ዝግጁ ነኝ›› አለ ኤድዋርድ፤ ‹‹መቼ ነው የምታገናኘን?››

‹‹አሁኑኑ።››

‹‹የት?››

‹‹እዚሀ›› አለ ፓጋኖ፤ ‹‹በሚቀጥለው ክፍል እየጠበቁም ናቸው።››

እኒያን በመላው አለም የሚፈሩ፤ ብዙ ጊዜ የተሳካላቸው ሀያው

ወንጀለኞች የማዩቱ ጉጉትና ከነሱ በላይ ሆኖ እነሱ በአክብሮት የታዘዙለት ሰው የመሆኑ ሀሳብ በአእምሮው ተደበላለቆ የሚሆነውን አሳጣው።

«ስንት ናቸው?» ሲል ፓጋኖን ጠየቀው።

«ምናልባት ኩፐርና ከረዳቶቹ ሁለቱ። ግንኩ መጀመሪያ ጥቂት ደቂቃ ልኝ ቢያርፉ ነው የሚሻልዎ. . . ማለቴ ግና ከመንግድ መግባትዎ ስለሆነ።»

«እሱን ተወውና ባክህ ቶሎ አግናኘን. . .»

ፓጋኖ እጁን ተወጥሮ ወደነበረው ኪሱ ሰዶ አንድ የታሰረ የሚመስል ጨርቅ አወጣና ለኤድዋርድ ሰጠ።

«ምንድነው እሱ?» አለ ኤድዋርድ ጨርቁን እየዘረጋጋ። «አይነርግብ ነው?»

«አዎ። እነ ኩፐር ማንኩን አይወቁ ካሉ ቢያጠልቁት ይመረጣል። እየሩ በርግጥ ሞቃት በመሆኑ ሊያፍንዎ ይችላል። ግን ፊትዎን ይከልል ዎታል።» ኤድዋርድ ፓጋኖን በአድናቆት እየተመለከተው ከሱፍ የተሰራውን አይነርግብ አጠለቀው። ከአይኖቹ በስተቀር ፊቱ ሙሉ ለሙሉ ተሸፍኗል።

«አሸ. እንግዲህ እንሂድ» አለ ፓጋኖ።

ወደ ሁለተኛው ሙኝታ ቤት የሚያስገባውን በር ቁልፍ ከፍቶ በሩን ገፋ አደረገው። ኤድዋርድ ወደ ክፍሉ ገብቶ ዙሪያውን ሊታኝ ሞከረ። ሰፊው ክፍል በጨለማ የተዋጠ ነው። ከአልጋው አለፍ ብሎ ሁለት ፈንጠር ያሉ ታላፊ ወንበሮች ይታያሉ። ከወንበሮቹ ትይዩ ባሉት ሶፋዎች ላይ ሰዎች ተኮምጠዋል። ሁለቱም የለበሱት ጃኬት ቢሆንም ከራባት አስረዋል።

በጥማ በኩል ቆሞ የነበረ ኤድዋርድ ያላየው ሶስተኛ ሰው ወደፊት ተራምዶ እጁን ለሰላምታ ዘረጋ። «ኩፐር እባላለሁ።»

ፓጋኖ ቀልጠፍ ብሎ አለታውን አስተዋወቀ። «አሊታየ እላቸው ናቸው።»

«ዋልተር ዚበርግ እባላለሁ» አለ ኤድዋርድ ከኩፐር ጋር እየተጨባበጠ። ኩፐር ሶፋው ላይ ወደተቀመጡት ረዳቶቹ እያመለከተ

መለየት የሚያዳግተውን ስማቸውን ተናገረ። ‹‹ክሩጊንስኪና. . . ኩግ ይባላሉ።›› ከዚያም ተጠል አደረገና ‹‹አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ሌሎቹን ዴ ሳልቮ፣ ቪልድስና ሳፈር የተባሉትን አባላት የሚያቅፈውን የዲሬክተሮች ቦርድ ሊተዋወቁ ይችላሉ። ለጊዜው ግን ወደ ጉዳያችን ብንገባ›› ብሎት ወደ ሶፋው ሂዶ ተቀመጠ። ኤድዋርድና ፓጋኖ በታጣፊዎቹ ወንበሮች ላይ ጎን ለጎን ተቀመጡ።

ኤድዋርድ ጉሮሮውን ጠራረገ፣ ‹‹የዚህ ስብሰባ አጀንዳ ለሁላችሁም ግልፅ ይመስለኛል።››

‹‹እስኪ በግልፅ ፊት ለፊት እንወያው?›› አለ ኩፐር ‹‹እንደሰማነው፣ የተለያዩ ተልዕኮዎች እንዲፈፀምልን የሚያዝዙት የተደራጀ ቡድን አያፈላስን ነው። ለእያንዳንዱ ተልዕኮም ሶስት ሚሊዮን ዶላር ለመክፈል ዝግጁ ነዎት።››

‹‹ትክክል›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹እዚህ ተልዕኮዎች ለምን ማስፈጸም እንደፈሚፈልጉ አንጠይቅም።› አለ ኩፐር ‹‹ያ የርስዎ ጉዳይ ነው።››

‹‹ከፖለቲካ ጋር የሚገናኝነ አይደለም›› አለ ኤድዋርድ ፈጠን ብሎ።

‹‹የፈለገው ይሁን።›› መለሰ ኩፐር፣ ‹‹ለርስዎ መስራት እንደምንችል ውሳኔ ከመስጠታችን በፊት የሚያስፈጽሙትን ተልዕኮ በግልጽ ማወቅ አለብን። ነፍስ ማድያም አለበት?››

ኤድዋርድ ሽምትት አለ ‹‹በጭራም›› አለ ፈጠን ብሎ። አይኑርግብ ሳይተር ሲንቀሳቀስ ይሰማ ጀመር። ሳይታወቀውም ሳድጉን በእጁ ጭብጥ አደረገው። ነፍስ ማድያ የሚባለውን ቃል እንደተላለ ነገር መጠቀሙ እስከ ጥፍሩ ድረስ ጠረረው። ብቻ ለማንኛውም ሃሳቡን አሰባስቦ ፍላጎቱን መግለጽ እንደሚያስፈልገው ተገነዘበ። ‹‹የኔ ፍላጎት አፈና ነው፣ ጠለፋ›› አለ፣ ‹‹ምናልባት ከጊዜ በኋላ ዝርፊያ። ግን የመጀመሪያው ስራ ጠለፋ ነው። አንድ ታዋቂ ሰው እንድታጥልኝና ለሁለት ሳምት ደብቃችሁ እንድትይዙልኝ፣ ከዚያም የመደባ ግንዘብ እንድትጠይቁ እፈልጋለሁ።

ታዲያ የምትጠይቁት የመያዣ ግንዘብ ተለል ያለና ሰውየውን በምክንያት እንድትለቁት በተላለ የሚከፈል መሆን አለበት። እንደነገርኳችሁ የምሰጣችሁ ተልዕኮ ከፖለቲካ ጋር የተገናኘ አይደለም። ግን ሆን ብላችሁ ፖለቲካ ብታስመስሉትና ምናልባትም ለጠለፋችሁት ሰው መለቀት በግንዘብ ፋንታ አንድ የፖለቲካ አስረኛ እንዲፈታ ብትጠይቁ የበለጠ ያመረጣል። ታዲያ እንዲፈታ የምትጠይቁት ሰውም እንዲሁ ጠቃሚ ያልሆነና ተጠያቂምቹ ያለማመንታት የሚፈቱት ሰው መሆን አለበት። የጠለፋችሁትን ሰው በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ እንድትለቁት አፈልጋለሁ፣ ምክንያቱም ታድናችሁ እንድትያዙ መሆን የለበትም። በሣም ጠቃሚው ነጥብ ደግሞ ጉስ ፓጋኖ እኔን በመወከል የቦርዳችሁ አባል ቢሆን ደስ ይለኛል።››

‹‹ለመሆኑ የመጀመሪያው ተልዕኮ የምንፈጽመው የት ነው?›› ኩፐር ጠየቀ።

‹‹ስፓኝ ነው፣ ሳን ሴባስቲያን›› ኤድዋርድ መለሰ።

‹‹መቼ?››

‹‹የነገ ሁለት ሳምንት።››

ለአፍታ ዝምታ ሆነ። ‹‹የምንጠልፈው ማነው?›› ኩፐር ጠየቀ።

ኤድዋርድ ትንፋሽን አምቆት ቆይቶ ሲለቀው በአይነ-ርግቡ ላይ ያስታውት ነበር። ድምጹን ሊያስተካክል እየሞከረ፣ ‹‹የስፓኙን ንጉስ ትጠልፋለኛላችሁ›› አለ።

የሚደፈርስ የማይመስል ፀጥታ ነገሰ።

ፀጥታውን የሰበረው ኩፐር ነበር። ‹‹እንነጋገርበት። እርስም ወደ መኝታ ክፍልም ይመለሱ። ውይይታችንን ስንጨርስ እንጠራዎታለን።››

* * *

ለኤድዋርድ አርምስቱድ ጊዜ የቆመ መሰለው። መኝታ ክፍሉ እንደግባ አይነ-ርግቡን አውልቆ አስተናጋጅ ጠርቶ የሚጠጣ ነገር ሊያዝዝ ፈለጎ ነበር። ጉስ ፓጋኖ ግን አስተናጋጅ በአካባቢያቸው መታየት እንደማይገባው

አለቃን አሳመነ። ኤድዋርድ ልብሱን አወላልቆ ሰውነቱን ታጠቢ ሙልዕ ለበሰ። ተጥሎም ከቢሮ ቦርሳው አንድ ሰነድ አውጥቶ እነ ኩፐር የተጠየቁትን ተልዕኮ ለመፈጸም ቢታወሙ ሊላ አማራጭ ይኖር እንደሁ ይመራመር ጀመር። እምብዛም ጠቃሚ ተልዕኮ በትርቡ ሊፈጸም እንደማይችል ሲገነዘብም እነኩፐር ፈታዲኛ ይሆኑ ዘንድ በልቡ ተማፀነ። በመጨረሻም ወደ ኩፐር ክፍል የሚያስገባው በር ተንኳኳ።

‹‹ኩፐር›› አለ አንድ ድምፅ በተጥታ ‹‹ሊመጡ ይችላሉ።››

ኤድዋርድ አያነ-ርግቡን አጥልቶ ወደ ሳሎግው ክፍል ገባ። ኩፐር አሁን አንድ ፈርጠም ያለ አሮር እንግሊዛዊ ሰው ጨምሯል። ‹‹ኩግ ይባላል። እንደምታስታውሱት በሰጋኝ ላይ ብዙ ልምድ ያካበተ ሰው ነው። እንዲያውም እዚያ አንድ የክረምት ማሳለፊያ ቤት አለው። ተልዕኮውን የሚመራው እሱ ይሆናል። ግን አንዳንድ ጥያቄዎች አሉት።››

ኩፐር ወደ ሶፋው ተመለሰ። ኩግ ኤድዋርድ ሰፍራውን እስኪይዝ ጠበቀና አንድ ሊላ ታማፊ ወንበር ስቦ ካጠገባቸው ተቀመጠ።

‹‹ተልዕኮው ቀላል አይደለም›› ሲል ጀመረ።

‹‹ኤክስፐርቶች የፊለግሁትም ለዚህ ነው።›› ኤድዋርድ አቋረጠው።

‹‹ጠለፋ ሁሉ ከባድ ነው ማለቱ አይደለም›› አለ ኩግ በባለሙያ ልበ ሙሉ አንደበት፣ ‹‹በተሳሉ የሚጠይቀው ጠንቃቃ ዝግጅት ነው። በቦታቸው ሆነው የንይል አሰላለፍን የሚያስተካክሉ፣ መንግድ የሚይዙ፣ ተጠላፊውን ወዳዘጋጀንለት ተሽከርካሪ የሚወስዱ፣ ወስደውም ወዳዘጋጀንለት መደበቂያ የሚያደርሱ፣ እዚያም የሚጠብቁና በመጨረሻም የሚደራደሩ አባላት ያስፈልጋሉ። ግን አርስዎ የጠየቁት ተልዕኮ ደግሞ የበለጠ አስጊና አደገኛ ነው።››

‹‹አስጊ ያልሆነ ጠለፋ አለ?›› ኤድዋርድ ተከራከረ። ኩግ ግን የሚቀመስ አልሆነም። ‹‹ይህን ተልዕኮ ከሌሎቹ የበለጠ አደገኛ የሚያደርገው የራሱ ምክንያት አለው። ተልዕኮው የሚፈጸመው በባሰነ ገጠር መሆኑን ልብ እንበል። ታዲያ ንጉሱ ከባሰነ ተገንጣዮች ጥቃት እንዳይታጣባቸው ከፍተኛ

ጥበቃ ሊመደብላቸው ይችላል።››

‹‹ያ ታዲያ ለናንተ ጥሩ አይደለም?›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹የስፓኝ ፖሊስ ከትትል የሚያተኩረው በባስክ ተገንጣዮች ላይ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ለውጭ አገር ጎብኚዎች ብዙም ትኩረት አይሰጡም። እንግሊዛውያን አገር ጎብኚዎች ጉዳት ያደርሱብናል ብለው መቼም አይጠረጥሩም።››

ኩግ ተስማማ። ‹‹አዎ፣ ይሆን ሁሉ ተነጋግረንበታል›› ካለ በኋላ ጥቂት ሲያመነታ ቆይቶ ‹‹የብላንኮን ፍጻሜ ያውቃሉ?›› ሲል ኤድዋርድን ጠየቀው።

‹‹ኧረ አላውቅም።››

‹‹የባስክ ተገንጣዮች የፈጸሙት የተሳካ ተግባር ነበር›› አለ ኩግ፣ ‹‹ያን ተግባር በንጉሱ ላይ ለመድገምና ነፃነን በባስክ ተገንጣዮች ለማላክክ አስበን ነበር።››

‹‹ግን ምንድን ነው እሱ፣ የብላንኮ ፍጻሜ?›› ጠየቀ ኤድዋርድ።

‹‹አድሚራል ብላንኮ የስፓኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ነበር። የባስክ ተገንጣዮች ደማሚት አጥምደው ከነመኪናው አጋዩት። እጅግ በጣም የተሳካ ቅንብር ነበር። ማለቴ ለኛም ከጠለፋ ይልቅ እንዲህ አይነቱ ተልዕኮ ይቀለን ነበር።››

አርምስቱድ የሰማውን ሊጠራጠር ምንም አልተረዳም። የሚነጋገረው ከተራ ቀማኞች ጋር አለመሆኑን የተረዳው ግና አሁን ነበር። የሚደራደራቸው ሰዎች ደመ-ተዝታዛ ነፍሰ-ገዳዮች መሆናቸውን ተገነዘበ። ሞኑ ተንቀጠቀጠበት፣ ‹‹እስኪ አንዴ ታገሱኝ›› አለ የግዴን፣ ‹‹የስፓኙን ንጉስ በፈንጅ ብንገድል ይሻለናል ነው የምትሉኝ?››

‹‹አስተያየት ብቻ ነው ያቀረብነው›› አለ ኩግ።

‹‹በስመአብ አያቻልም›› አለ ኤድዋርድ ልቡ ነጠር ነጠር እያለ። ‹‹ከመጀመሪያው ነግሬአችኋለሁ፣ ነፍስ ግድያ አልፈልግም። የምፈልገው ጠለፋ ብቻ ነው።››

‹‹ግን እንደግና ልንገርምና ጠለፋ የበለጠ አደገኛና የበለጠ ውስብስብ

ነው። እንደተነጋገርንበት ለሶስት ሚሊዮን ዶላር ጠለፋ ማካሄድ ሲበዛ አደገኛ ነው።››

‹‹እሃ መልካም፣ ምን ያህል ግንዘብ ነው አደገኛነቱን የሚተንሰው?››

‹‹አምስት ሚሊዮን›› አለ ኩማ።

‹‹ለአንድ ተልዕኮ አምስት ሚሊዮን ያስፈልጋችኋል›› አለ ኤድዋርድ፣ የሰማው ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ።

‹‹ከርስዎ የሚጠበቀው ይህ ግንዘብ ብቻ አይደለም›› አለ ኩማ፣ ‹‹ሊሎች ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው።››

‹‹የምን ቅድመ-ሁኔታዎች?›› አለ ኤድዋርድ ፈጠን ብሎ።

ኩማ መደንጓለው ዞር ብሎ ‹‹ሰፍራውን ልልተቅለህ ኩፐ›› አለ። ከዚያም ኩፐርና ኩማ ቦታ ከተለዋወጡ በኋላ ኩፐር ገለፃውን ቀጠለ። ‹‹ለንደን ላይ አሰራ ሁለት ሰዎችን ያቀፈ ኃይል አለን›› አለ ኩፐር፣ ‹‹ለእንዲህ አይነቱ ተልዕኮ ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎች ሊያስፈልጉን ነው። ሰዎችን ከየት እንደምን መለምል እናውቃለን። እነሱን ከየሃገሩ ለማሰባሰብ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር ያስፈልገናል። በርግጥ ይህ ወሮ ሊላ ጊዜ የሚደገም አይደለም። ማለቱ አንድ ጊዜ ሰዎቹን ካሰባሰብን ለሚቀጥሉት ተልዕኮዎችም በሂችን ናቸው።››

‹‹ሊላስ?›› ኤድዋርድ ጠየቀ።

‹‹መሳሪያዎች›› አለ ኩፐር፣ ‹‹በርግጥ እኛም መጠነኛ ትጥቅ አለን። ግን አርስዎ ለሚያዝዙን ተልዕኮ ከባድ መሳሪያዎች ሁሉ ያስፈልጋሉ። ቀለል ያሉ ሠነው ግን እጅግ በጣም ዘመናዊ መሳሪያዎች ሊኖሩን ይገባል። ይሆንን ወሮ ሽፍነው የሚገዙልን አርስዎ ይሆናሉ። ይህም የሚያጓጓም ወሮ ነው።››

ኤድዋርድ በረጅሙ ተነፈሰ ‹‹የሚያስፈልጋችሁ ይህ ብቻ ከሆነ ቀላል ነው›› አለ።

‹‹የምንፈልጋቸውን ነገሮች ዝርዝር የምንቀበልበትን ቦታና ጊዜ ለሚስተር ጆንሳ እናሳውቃለን።››

ኤድዋርድ የተጠየቀውን መሳሪያ ከየት ሚገኝት እንደሚችል ሲያለላበል

ጉሪስ የሚገኘው ኒክ ራምሲ ትውስ አለው። ያለጥርጥር ኒክ ራምሲ ይሠንን ችግር ይፈታዋል ሲል አሰበ።

«ይኸው ነው?»

«ይህ ብቻ አይደለም» አለ ኩፐር፡ «በርግጥ እንዴት እንደምንሳሳሰ የምንሄደው ራሳችን ነን። ግን ተልዕኮአችንን ለመፈጸም የተረን ጊዜ አሞር በመሆኑ አንድ ኑሮብ ላይ የርስዎ ርዳታ ያስፈልግናል። ስራችንን የምናከናውንበትን ስፍራ ለመወሰን እንዲያመቸን የንብሱን የጉብኝት ፕሮግራም በዝርዝር አስጠንተው ያቀርቡልናል። ይሠን ለማድረግ ይቸግርዎታል?»

«ችግር የለውም» ኤድዋርድ ታል ግባ።

«አንድ የመጨረሻ ነጥብ። ለኛ ከሚከፈለው አምስት ሚሊዮን ዶላር ውስጥ ግማሹን በትድሚያ እንፈልጋለን።»

«ተላል ነው» አለ ኤድዋርድ፡ «ሁለንም በጥጋ በኩል ታገኛላችሁ። ይኸው አይደለም?»

ኩፐር ፈገግ አለ «ይኸው ነው። ይበሉ እንግዲህ መሰናበቻችን ነው።»

ኤድዋርድ ብድግ አለ «ጀሚ ደንበኞች ለመሆን ያብቃ።»

* * *

ቨኩዩሪያ ከመኝታ ክፍሏ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ኢንተርናሽናል ሄራልድ ትሪቡን ጋዜጣ አንብባ እንደጨረሰች ከሚቀጥለው ክፍል የኒክ ራምሲ ድምጽ ይሰማት ጀመር። የሚነጋገረው ከማን ጋር እንደሆነ ስላልገባት ወደሱ ስትሄድ ስልክ ይዞ አገኘችው። ራምሲ ደግሞ አፏን ሲያዩ የስልኩን መነጋገሪያ በመያዙ እሩጫ እንድ የተጻፈ መልእክት እየጠጣ «ስንደን መጥቷል» አላት።

«ማ?» የጥያቄዋን መልስ ከመስማት አገኘችው። ኤድዋርድ ከስንት በኋላ ደውሎ ስላጣቸው የተወሳቸው መልእክት ነበር። «ስንደን ምን ያደርጋል?»

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ የኤድዋርድ ሻካራ ድምጽ ተሰማ። «ሂድ»

«ሚስተር ኤድዋርድ? ኒክ ራምሲ ነኝ። ከፖሪስ አውን መግባትን ነው። በሊሎች ቡድኖች ላይ ምርመራ ስናካሂድ ነበር የቆለነው።»

«ላንድ ጉዳይ ወደ ለንደን መጣሁ» አለ ኤድዋርድ፣ «በፋሞስ አሰራር ላይ ጥናት ባካሂድክበት ጊዜ አንድ ጥያቄ ሳትመልስ እንዳልቀረህ እርግጠኛ ነኝ። ለመሆኑ እኔህ ፋሞስ መሳሪያ ከየት ነው የሚያገኙት?»

«አለም አቀፍ ደላሎች አሏቸው፣» አለ ራምሲ።

«እባክህ አንዱን ደላላ አግኝቼ ላነጋግረው እፈልግ ነበር?» አለ ኤድዋርድ፣ «ለጀመርነው ፕሮጀክት ይረዳኛል።»

«አይጨነቁ ሚስተር ኤድዋርድ፣ እኔና ቪኪ አንዱን አትርፈን እናነጋግረዋለን።»

«የለም፣ ራሴ ላነጋግረው ነው የምፈልገው።»

ራምሲ ንግግሩን ሳያቆም ቪክቶሪያን ተመለከታት «መልካም፣ የመሳሪያ ነጋዴ ግለሰብ ልናገናኝም ይፈልጋለ፣ የት ና ማቼ?»

«የትም ቦታ። በተቻለ ፍጥነት። ከተቻለም በሁለትና በሶስት ቀናት ውስጥ።»

«መጀመሪያ እንዳንድ መጠይቆችን አድርገን ይበልጥ የተሻለውና በቀላሉ የሚገኘው ነጋዴ ማን እንደሆነ ማወቅ አለብን።»

«ጥሩ» አለ ኤድዋርድ፣ «ታዲያ ፈጠን አድርጉት። ደሞ እኔ ማን እንደሆንኩ፣ ነገሩ ጋዜጣን የሚመለከት መሆኑን እንዳትነግሩት። ስሙ ካለታወቀ መሳሪያ ገዥ ጋር ልታገናኙት እንደምትፈልጉ ንገሩት። እንዲ ያውም ዋልተር ዚምበርማ የተባለ አሜሪካዊ ነጋዴ ወኪሎች ነን በሉት።»

«ዋልተር ዚምበርማ፣ መልካም ሚስተር ኤድዋርድ። ነገ እኔና ቪኪ ስራውን እንጀምራለን። ውጤት እንዳገኘን እደውልልዎታለሁ።»

«አይሆንም። ከእንግዲህ የስልክ ግንኙነት አያስፈልግም» አለ ኤድዋ

ርድ፣ ‹‹ነገሩን እንደጨረሳችሁ እዚሁ ለንደን አጠብቃችኋለሁ። በሁለት ቀናት ውስጥ እንደምትመጡ ተስፋ አለኝ።›› ኤድዋርድ አድራሻውን ሰጠ።

ራምሲ ስልኩን እንደዘጋ የተነጋገረውን ሁሉ ለቪክቶሪያ ተረከላት። ‹‹ታዲያ ይህን የመሳሪያ ደላላ የት የምናገኘው ይመስልሃል?›› ቪክቶሪያ ግራ ተጋብታ ጠየቀች።

‹‹ችግሩ እሱ አይደለም። የሚያስጨንቀኝስ እኛ ስለ ፋሞስ የጀመርነው ጥናት ገና ሳይጣደድ በመሳሪያ ንግድ ላይ ታሰመጠይት ማድረግ ለምን አሰፈለገ? ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጥድፊያ?››

* * *

በማግስቱ አመሻሽ ላይ ራምሲና ቪክቶሪያ ለንደን ገብተው ኤድዋርድ በፈጣንነታቸው እየተደነቀ በደስታ ሊቀበላቸው በታ።

‹‹ሁኔኛውን ሰው እንዳገኛችሁ አልጠራጠርም›› አለ ኤድዋርድ በሶፋው ዙሪያ እንደተቀመጡ።

‹‹ከአንድም ሁለት አማኑኤን ነበር›› ሲል ራምሲ መለሰ። ‹‹ግን እርስዎ የሚፈልጉት ትክክለኛ ሰው ቪኪ ያገኛችው ይመስለኛል።››

ቪክቶሪያ ጣልቃ ገባች። ‹‹ፍራንከፈርት የሚገኝ ሂልመት ሚደንዶርፍ የተባለ እውቅ ነጋዴ ነው። በስልክ አነጋግራዋለሁ። እውነትምን ከሆነ ሊያገኙት እንደሚችሉ ተናግሯል።››

‹‹እውነቱን መሆኑን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?››

ራምሲ ጣልቃ ገባ። ‹‹ማረጋገጫው በስዊዝ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እንዳለም ማሳየት ነው። ሁሉም መሳሪያ ነጋዴዎች ይህንን ይጠይቃሉ። በስዊዝ ባንክ ሂሳብ ሊከፍቱ ይገባል።››

‹‹አለኝ›› አለ ኤድዋርድ በጥድፊያ።

‹‹በራስዎ ስም?›› ራምሲ ጠየቀ።

‹‹በዋልተር ዚምበርማ።››

‹‹ቪክቶሪያ የርስዎ ስም ምልተር ዚምበርግ መሆኑን ለነጋዴው ነግረዋለች።››

‹‹በጣም ጥሩ።››

‹‹ታዲያ መቼ ነው ፍራንክፈርት የምሄደው?››

‹‹መሄዱ እስፈላጊ አይደለም›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹ነጋዴው ራሱ ዛሬ ለእረፍት ወደ አንቲብስ ይሄዳል። እዚያ እንግናኝ ነው ያለው።››

ቪክቶሪያ የቀጠሮውን ቦታ ጨምራ ተናገረች።

‹‹መቼ? በስንት ሰዓት?››

‹‹ከነገ ወዲያ ጧት በአምስት ሰዓት። ቀኑ ጸሐይማ ከሆነ በመዋኛ ስፍራ ይገኛል። ከመዋኛው ከለብ መግቢያ በር በስተግራ በካፍቴሪያ ወንበር ላይ ተቀምጠ ያግኙታል። ከጎኑ ጠረጴዛ የገለጠች ልጃገረድ በጀርባዋ ተንጋላ ፀሐይ ትሞቃለች። ሰውየው የራሱን ምልክት ሲናገር ራሴ በራ ነው፣ ወፍራም ነኝ፣ ጥቁር መነፅር አደርጋለሁ፣ ፒፖ አጨሳለሁ ብሏል። የስዊዘርላንድ መጽሔት እንደሚያነብ ጨምሮ ተናግሯል። በቀጥታ ወደሱ ሲጠጉ ልጃገረዷ ከቦታው ተነስታ መንገድ ትለቅልዎታለች። ካጠገቡ እንደተሳመጡ በስዊዝ ባንክ ሂሳብ የከፈቱበትን ደብተሮ ያሳዩት። ከዚያ በኋላ የሁለታችሁ ውይይት ይጀምራል።››

‹‹ጥሩ አድርገሻል ቪክቶሪያ›› አለ ኤድዋርድ በእርካታ።

‹‹ሚስተር ኤድዋርድ›› አለ ራምሲ ነጠቅ አድርጎ። ‹‹እኛም ካጠገብዎ ባንርቅ ጥሩ ነው። ላንዳንድ ጉዳዮች ልናስፈልግዎ እንችላለን።››

‹‹የለም አመሰግናለሁ›› አለ ኤድዋርድ በድንጋጤ፣ ‹‹እንደ እውነቱ ላንተና ለቪክቶሪያ ያተድኩት ሌላ ስራ አለኝ። ነገ ስንኝ ሄዳችሁ ላን ሴባስቲያን ላይ እንድትገኙልኝ እፈልጋለሁ። ላን ሴባስቲያ በባስክ ክፍለ ሀገር የምትገኝ የጠረፍ ከተማ ነች።››

‹‹አንድ ከረምት አላልፈባታለሁ›› አለ ራምሲ።

‹‹የስጋኙ ንብስ በላን ሴባስቲያን ያንድ ቀን ጉብኝት ያደርጋል።

እንደሚወራው የባስክ ተገንጣዮች ሳያንጥብቡበት አይተራም።››

‹‹አይመስለኝም›› አለ ራምሲ።

‹‹ያም ሆነ ይህ ማርማር ሊፈጥሩ ይሞክሩ ይሆናል።›› ኤድዋርድ ኮስተር አለ።

‹‹በድራሽ›› አለ ራምሲ፣ ‹‹የአካባቢው ፀጥታ በእጥፍ የተጠናከረ እንደሚሆን የተረጋገጠ ነው። ለዜና የሚበቃ ነገር ይፈጠራል ብየ አላምንም።››

ኤድዋርድ በቁጣ ገነፈለ። ‹‹አትከራከረኝ ኒክ፣ ቢያንስ እንኳን ንጉሱን ለአደጋ የሚያጋልጠው ስፍራ መንገዱ ላይ አለ ምይ የሚለውን ጥያቄ አስቀድመን መመለስ አለብን። አንተና ቨክቶሪያ እዚያ እንድትሄዱ የምፈልገው አደጋ ሲደርስ እንድትመለከቱ ሳይሆን በጉብኝቱ ሁለት ገጽታዎች ላይ ለሪኮርድ የትደሚያ ማቴሪያል እንድታቀርቡ ነው።››

‹‹እንደመሰለም ሚስተር ኤድዋርድ›› አለ ራምሲ እያመነታ።

‹‹አንተ፣ በሳን ሴባስቲያን ለንጉሱ ጉብኝት የተዘጋጀው የፀጥታ ጥበቃ ምን ያህል እንደሆነ እንድታጠና ይሁን። አግረ መንገድህንም የባስክ ተገንጣዮች ሊያደርጉ ያቀዱት ነገር ይኖር ይሆን የሚለውን ታጣራልኛለህ። እነሱ እንቅስቃሴያቸውን ይነግሩሃል ማለቴ አይደለም። ብቻ አንተ በዙሪያቸው እያንጎራበብህ የሚወራውን ሰብስብልኝ።››

‹‹የተቻለኝን አደርጋለሁ፣ ሚስተር ኤድዋርድ።››

‹‹አንቺ ደግሞ ቨክቶሪያ፣ በሳን ሴባስቲያን የጉብኝት ፕሮግራም ታጣራያለሽ። በሰንት ሰዓት የት ይደርሳል? ኦፊሲዮላዊ ጉብኝት ነው? ከተማዋን ተዘዋውሮ ይጎበኛል? የት የት ቦታ ቆይታ ያደርጋል? ከአካባቢው የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ጋር የሚያደርገው ስብሰባ ይኖራል? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ላንቺ የተተወ ነው። ችግር ከገጠመሽ በማድሪድ ከሚገኝ የመንግስት ቢሮ ጋር ግንኙነት አድርጊ።››

ቨክቶሪያ ‹‹እሞክራለሁ›› አለች።

‹‹የመሳሪያውን ንግግር እንደጨረስኩ እዚሁ እመለስና ሳምንቱን ቀሪ ቀናት አሳልፋለሁ። ሁለታችሁም ሪፖርቶቻችሁን ትጻፋለ ከሰዓት በኋላ በስልክ ታቀርቡልኛላችሁ። ኒክ በተለይ የምታቀርበውን ሪፖርት እኔ በመር መሳሪያ ካደረግሁት ታለ መጠይት ጋር ወደ ኒውዮርክ እልካለሁ። ሁሉም ነገር ግልፅ ነው?››

‹‹ከአርብ በኋላስ ምን እንሰራለን?›› ቨክቶሪያ ነበረች።

‹‹አ! ንጉሱ ከጉብኝቱ እስኪመለስ ድረስ በሳን ሲባስቲያን ትቆያላችሁ። ምናልባት አንድ ነገር ቢከሰት። ከዚያ በኋላ፣ እኔ ወይም ሃሪ ዴትሺ ከኒውዮርክ ደውለን የሚቀጥለውን ሥራችሁን እንነግራችኋለን።››

ኤድዋርድ ሁለቱን ጋዜጠኞች መልካም እድል እንዲገጥማቸው እየተመኘ ከሸኛቸው በኋላ በቀጥታ ወደ ስልኩ አመራ። ለፓጋኖ ነበር የደወለው። ፓጋኖ ባስቮኳይ መልስ ሰጠ።

‹‹ጉስ፣ ሁሉም ነገር ተስተካክሏል። ባስቮኳይ የኤር ፍራንስ ትኬት አዘጋጅልኝ። ደግሞም በዋልተር ዚምበርግ ስም በአንቲብስ ሆቴል ሁለት መኝታ ቤቶች እንዲያዝልኝ አድርግ›› ሲል ከመሳሪያ ነጋዴው ጀርመናዊ ጋር የሚጠበቀውን ቀጠሮ አዘጋጀ።

7

ሳን ሴባስቲያን ሲደርሱ መሸትሸት ብሎ ስለነበር በዚያ አለት ሰራቸውን ለመጀመር አልቻሉም።

በማግስቱ ራምሲ የከተማውን የተለያዩ ስፍራዎች ለቪክቶሪያ ሲያስጎበኛት አረፈደ። ከዚያም አንድ ምግብ ቤት ገብተው አረፍት ካደረጉ በኋላ ሲወጡ ‹‹ከዚህ በኋላስ?›› ስትል ቪክቶሪያ ራምሲን ጠየቀችው።

‹‹ከእንግዲህ ራስሽን ችለሽ መንቀሳቀስ ትችያለሽ። በበኩሌ ወደ መኝታየ ተመልሼ ትንሽ እተኛለሁ፣ ከዚያም ስልክ እየደወልኩ አንዳንድ ቀጠሮዎችን እይዛለሁ። ስራው ለሁለታችንም ቢሆን ቀላል አይሆንም። መቼም ማንኛውም ባለስልጣን ቢሆን ስለንጉሱ የጥበቃ ሁኔታ ጥንቁቅ ሊሰጠን አይፈልግም።››

‹‹ግን ለኔ የንጉሱን የገብኝት ፕሮግራም ለማግኘት ከማድሪድ ይልቅ በሳን ሴባስቲያን መሞከሩ ይቀለኝ አይመስልህም?››

‹‹አይመስለኝም፣ በመሰረቱ በሁለቱም ከተሞች ብትሞክሪ የሚሳካልሽ አይመስለኝም። አየሽ ቪኪ፣ በባስክ ክልል ማንኛውም የሰጋኝ ሙሪ የተቃዋሚዎች ኢላማ ነው። ማን ሞኝ ነው ታዲያ የገብኝቱን ፕሮግራም አውጥቶ እያቀበለ ንጉሱን ለአደጋ የሚያጋልጠው?››

የጎረጥ ተመለከተችው። ‹‹አስተያየትህን አልቀበልም። ታያለህ ዝርዝር ፕሮግራሙን ካላገኘሁ እኔ አይደለሁም።›› ቦርሳዋን ከፍታ የከተማዋን ካርታ የሚያሳይ ጥራዝ አወጣች። ‹‹አዎ፣ ከማዘጋጃ ቤት እጀምራለሁ። ከንቲባውን

አነጋግራለሁ።››

‹‹መልካም እድል፣›› አላት።

* * *

ከእንቅልፉ እንደነቃ ራምሲ ፊቱን በቀዝቃዛ ውሃ ታጥቦ አደረቀና ከአልጋው አጠገብ ወደሚገኘው ስልክ አመራ።

ጆሱ የተባለውን የባስክ ፋርማሲስት ጓደኛውን ለማግኘት ነበር መጀመሪያ የወሰነው። ጆሱ በሚስጥር የሚንቀሳቀሰው የባስክ ተቃዋሚ ቡድን አባል ሲሆን የንጉሱን የጥበቃ አደረጃጀት በተመለከተ ፍንጭ የሚያውቅ ሰው ካለ የመጀመሪያው ጆሱ መሆን አለበት።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ራምሲ በጆሱ መድኃኒት ቤት ገብቶ ስሙን ጠራው።

‹‹ኒክ›› ሬሚ ጆሱ በድንጋጤ። ዘለሎ ተጠመጠመበት ‹‹ስንት ጊዜ ሆነን ባክህ? . . . አሰኪ ና ለማንኛውም በስተጀርባ ባለው ክፍል ጥቂት ወይን ጠጅ አለኝ።››

ከመድሃኒት ቤቱ በስተጀርባ ወደሚገኝ የተገለለ ክፍል ሄደው እንደተቀመጡ ጆሱ ወይን ጠጁን እየቀዳ ‹‹ምርጥ ጠጅ ነው›› አለ ራምሲን፣ ‹‹በተለይ የሀረ ድምር ለመጥረግ።››

‹‹ልክ እኔ የምፈልገው መጠጥ ነው›› አለ ራምሲ እየተጎነጨ፣ የሚተጥለውን የጭውውት ርዕስ የከፈተው ጆሱ ነበር።

‹‹ሰሞኑን ደግሞ እዚህ ምን አመጣህ ኒክ? ሌላ መጽሐፍ እየፃፍክ ነው?››

‹‹በወፍራም ደመወዝ ሰራ ጀምሬአለሁ። እንደገና ጋዜጠኛ ሆኛለሁ። ለኒውዮርክ ሪኮርድ እየሰራሁ ነኝ። የሰሞኑን ንግላችሁን ጉብኝት ለመከታተል ነው የመጣሁት።››

ጆሱ ባንድ ትንፋሽ ወይን ጠጁን ጨልጦ እንደገና ሞላው። ‹‹ንጉሥ ነኝ ስለሚለው ሰው ጉብኝት ልትከታተል ነዋ?›› አለው በማሾፍ።

«የስጦኝ ንጉሰ በባስክ. . . አንድ የሚገፍ ታሪክ ሳይሰራ አይቀርም ይሆናል።»

ጆሱ ራሱን በትራታ ነቀነቀ። «አሁን እንኳ የሚሰራ ታሪክ የለም። ከበድ ያለ ጥበቃ ሳይደረግለት አይቀርም።»

«ምን ያህል?»

«እሱንማ ማን ያውቅ ብለህ ነው?»

«ካንተ የተሰወረ ሊሆን አይችልም ጆሱ፣ እስኪ ግምትህን ንገረኝ። ከማን እንደሰማህት እንደማልናገር የምታውቅልኝ ይመስለኛል።»

ጆሱ ጉንጩን አከክ አከክ ሲያደርግ ቆየ፣ አሁንም የጥርጣሬ ምልክት ይነበብበታል።

«ጓደኛህ የነበርኩ መሰለኝ።» ግፋ፡ው ራምሲ።

ጆሱ ያልሰማ መስሎ ጥቂት ቆየና በዝግታ ይናገር ጀመር።

«በርግጥ ሁሉንም የማድሪድ ባለስልጣኖች ንጉሱን ፈምሮ በትርብ እንከታተላቸዋለን። ንጉሱ የትኛውንም ስፍራ ሲጎበኝ ስድስት የግል ጠባቂዎቹን አስከትሎ ነው። የሚታጠቁት የነፍስ ወከፍ ጠመንጃ ብቻ ነው። የላን ሴባስቲያን ከንቲባ ንጉሱን የሚቀበለው በወታደራዊ ሾፌሮች በሚነዱ ሶስት መኪናዎች ይሆናል። ንጉሱ የሚተመጥባት መኪና የመካከለኛዋ ነች። ከጓላዋና ከፊቷ ያሉት መኪናዎች ስድስቱን ዘቦች የሚይዙ ናቸው።»

«ዘቦቹ ስድስት ብቻ ናቸው ማለት ነው?»

«ሊላ የታወቀ ነገር የለም» አለ ጆሱ፣ «ንጉሱ ለተጠናከረ የጥበቃ ኃይል በጀት የለውም። ግን በጀት ቢኖረውም፣» አለ ጆሱ፣ «ግን በጀት ቢኖረውም አይጠቀምበትም። ስጦኝ ንጉሷን እንደ ላንቲካ ያስቀመጠች ዴሞክራሲያዊ አገር መሆኗን ለማሳየት የምትሞክር አገር ነች። በርግጥ ንጉሱ ላን ሴባስቲያን እንደደረሱ በየመንገዱ ቆመው የሚጠብቋቸው ነዶ ለባሾች ሳይኖሩ አይቀሩም።»

ራምሲ ነዶ ለባሾች የተባሉት ልዩ ስልጠና የተከበሉ፣ ልዩ ዩኒፎርም

የለበሱና ልዩ አውቶማቲክ መሳሪያዎች የታጠቁ፣ ልዩ ዘቦች መሆናቸውን አላጣውም።

‹‹ምን ያህል ይሆኑ እነሱስ?›› ሲል ጆሱን ጠየቀው።

‹‹ይህን እንኳ እንጃ፣ ግን በእንዲህ አይነቱ ልዩ ጉብኝት ግፋ ቢል ከሃምሳና ከስድሳ የማይበልጡ ግን በስትራቴጂያዊ ሰፍራዎች የቆሙ ዘቦች ይኖሩ ይሆናል። ከዚህም ሌላ ባለህ ከፍለ ሃገር ራዲዮ በየመንገዱ፣ በየህንፃው ጣራና በተራሊኒው በታ ሁሉ የምትመድባቸው ወታደሮች ይኖሯታል።››

‹‹ይኸው ነው?››

‹‹እስከማውቀው ድረስ። በተጨማሪ ደግሞ ህዝቡ እንዳያውክ የሚቆጣጠር የተለመደ የፖሊስ ኃይል መመደቡ አይቀርም።››

‹‹ከዚህ አይነት የንጉሱ ጥበቃ ከባድ አይደለማ?››

‹‹ከባድ አይደለም፣ ግን አይበገርም።››

‹‹ግን እኔ የተቃዋሚ ቡድን መሪ ብሆን ኖሮ በተላሉ ጉዳት እንደማደርስበት ነበር የምገምተው።››

‹‹ተሳስተሀል ኒክ፣ የንጉሱ ጥበቃ በተጠንቀቅ በሚገኝበት ሁሉ አደጋ መጣል የማይታሰብ ነው።››

‹‹ስለዚህ ተቃዋሚ ቡድን እርምጃ አይወስድማ?››

ፋርማሲስቱ ፈገግ አለ። ‹‹በኔ ግምት ምንም ርምጃ አይወስድም።››

* * *

የጋበዛትን ራት በተከፈተ የምግብ ጥላጎት ብትመገብም ቪክቶሪያ ደስተኛ እንዳልነበረች ለማወቅ ራምሲ አላስቸገረውም። እንዲያውም መረበሿን የሚመሰክረው ገፅታዋ ሰላም ነሳው። እንዴት ሳቲት እንደሚያደርጋት አሰበ።

‹‹ቪክ፣ መቼም በእንቲባው ቢሮ የንጉሱን የጉብኝት ፕሮግራም ላንቺ ለማሳወቅ ተዘጋጅቶ የሚጠብቅሽ ሰው እንዳልነበረና ከዚህ ስትነሺ ታውቂ

የነበረ መሰለኝ፤›› አላት።

‹‹የሚገርመው እንዳንዴ ይባስ ብለው ግልምጫቸው ነው›› አለች እንዳጎመዠት።

‹‹በቀላሉ መግመት ትችያለሽ›› አለ ራምሲ ‹‹የንጉሳዊውን ጉብኝት ፕሮግራም ለውጭ ሰው ማቀበል በነሱ አመለካከት ንጉሱን ለግድያ አሳልፎ መስጠት ነው።››

‹‹አውቃለሁ›› አለች ቪክቶሪያ፣ ‹‹እኔ ግን የሆነ ነገር አነስተኛም ቢሆን ዋሽተው ቢሆን እንኳ አንድ ሁለት አንቀጽ ያህል እንድጽፍ ይነግሩኛል ብዬ ጠብቂ ነበር።››

ራምሲ ፈገግ አለ። ‹‹ለመሆኑ ከማዘጋጃ ቤት በኋላ ሌላ ቦታ ሞክረሽ?››

‹‹ፖሊስ መምሪያ ሂጀ ነበር፤ ስጠይቃቸው እንዲያውም ሳቁብኝ። በኋላማ እንዲያውም እሽቀንጥረው ሊወረውሩኝ ዳድቷቸው ነበር።››

‹‹የከተማዋን ጋዜጣ ዝግጅትስ ሞክረሻል?››

‹‹አዎ። አዘጋጆቹ በርግጥ ትህትኞች ነበሩ፤ ግን ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነገሩኝ። እኔን ያስጨነቀኝ ለሚስተር ኤድዋርድ ምን እንደምለው ነው። ሪፖርታችንን እስክ ከነገ ወዲያ ይጠብቃል። አንተስ ኒክ፣ ተሳካልህ?››

‹‹እኔ እንዳንቺ ወደ ባለስልጣኖች ቢሮ አልሮጥም›› አላት፤ ‹‹መጠነኛ መረጃ አግኝቻለሁ። እንደተረዳሁት በንጉሱ ላይ ምንም የታቀደ ተንኮል የለም።››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹ከሞላ ጎደል።››

‹‹ታዲያ ወደ ባለስልጣኖች ቢሮ ካልሄድክ መረጃውን ከሚስጥራዊ ፍንጮች አገኘኸው ማለት ነው።››

‹‹እንደዚያ ነው።››

ለመጀመሪያ ጊዜ ፊቷ በፈገግታ ወጣ አለ። ‹‹እኔም ነገ ይህንኑ

አደርጋለሁ ኒክ። አንድ ነገር ቆፍሬ ማውጣት አለብኝ፣ አመሰግናለሁ ኒክ።››

* * *

የተጠሮው ቀን ደረሰ። ኒክ ራምሲ ለንደን የሚገኘውን አለቃውን በስልክ ተገናኝቶ የንጉሱን የጥበቃ አደረጃጀት የተመለከተውን ሪፖርቱን በቃል አሰምቶ እንደጨረሰ ለንደን የሚገኘው የአለቃው ድምፅ ‹‹አመሰግናለሁ ኒክ›› ሲል ተሰማ። ‹‹ቪክቶሪያን አትርሳት።›› ቪክቶሪያ ከስልክ መነጋገሪያው ጎን በሚገኘው ወንበር ላይ እየተቀመጠች ማስታወሻዋን ጭኗ ላይ ካደረገች በኋላ ሪፖርቱን ታዘንብ ጀመር።

‹‹ይፋዊ ምንም ማግኘት አልቻልኩም ሚስተር አርምስቲድ። ሁሉንም ቦታዎች ሞክሬ ነበር፣ የሚተባበረኝ አልተገኘም። በመጨረሻም ግን ይፋዊ ካልሆነ ምንጭ የጉብኝቱን ፕሮግራም ላገኝ ችያለሁ።››

‹‹ይፋዊ ያልሆነ?›› አለ አርምስቲድ ከለንደን፣ ‹‹ምንድነው ደግሞ ይፋዊ ያልሆነ?››

‹‹አፈሲላዊ መረጃ ማግኘት መቼም የሚታሰብ አልሆነም።›› አለች ቪክቶሪያ። ‹‹ነገር ግን ንጉሱ ከሰዓት በፊትና ከሰዓት በኋላ እዚህ መዋላቸው ከታወቀ አንጻንድ ቦታዎችን መጎብኘታቸው እንደማይቀር ተሰማኝ። ከዚያም ሊጎበኙዋቸው ይችላሉ ብዬ የገመትኩዋቸውን ስፍራዎች በማስታወሻዬ ያዝኩና ወደነዚህ ስፍራዎች በመሄድ የሚመለከታቸውን ሰዎች ማነጋገር ያዝኩ። እነዚህን ሰዎች ማግኘትና ማነጋገር ቀላል ነበር። ካነጋገርኳቸው መካከል መዚየም ተቆጣጣሪ፣ የመንገድ ጽዳት ሰራተኞች፣ ሱፐርቫይዘር በትልቁ ቤተክርስቲያን የጳጳሱ ረዳትና የመሳሰሉት ይገኛሉ። ከመካከላቸውም አንዳንዶቹ የንጉሱን ጉብኝት አስመልክቶ ተዘጋጅተው እንዲጠባበቁ መመሪያ ተላልፎላቸዋል። በዚህ መሰረት መመሪያ የተሰጣቸውን ድርጅቶች በመግፍ ንጉሱ የሚጎበኟቸው ስፍራዎች ዝርዝር ሊኖረኝ ችሏል።››

‹‹ጎበዝ፤›› ሲል ተሰማ የአለቃዋ ድምጽ።

ቪክቶሪያ በደስታ እየፈነደቀች የስልኩን መነጋገሪያ ይበልጥ ወደአፏ አስጠጋችው። ‹‹ዝርዝሩን ላንብልዎ እችላለሁ፣ ሚስተር ኤድዋርድ።››

‹‹ለመረጃሽ ትክክለኛነት እርግጠኛ ነሽ?››

‹‹መቶ በመቶ።››

‹‹ቀጥይ።››

ከጧቱ በሰስት ሰዓት የሚጀምረው የንጉሱ ጉብኝት ከሰዓት በኋላ በ8፡30 እስኪጠናቀት ድረስ የሚጓዝባቸውን ስፍራዎች በጠራ ድምጽ አንድ ባንድ ከማስታወሻዋ በአለቃዋ ማስታወሻ አስገለበጠችው።

* * *

ለንደን ላይ ጀምበር እያዘቀዘቀች ናት። ኤድዋርድ አርምስቱድ ባረፈበት ሆቴል መኝታ ክፍል አይነ-ርግቡን አጥልቶ እንደጨረሰ ‹‹ስንት ናቸው?›› ሲል ጉስ ፓጋኖን ጠየቀው።

‹‹ሁለት ብቻ፣ ኩፐርና ኩግ። ኩፐር ወደ ተልዕኮው ከመሄዱ በፊት የመጨረሻውን ሪፖርቱን ሊያሰማም ይፈልጋል።››

ኤድዋርድ ፓጋኖን እየተከተለ ወደሚተጣለው ክፍል ሄዱ። ከሁለቱ ደብዛዛ መብራቶች በስተቀር ከፍሉ ጨለማ የዋጠው ነበር። በክፍሉ መካከል ባለው ሰፊ ጠረጴዛ ዙሪያ ከሚገኙት ስድስት ታጣፊ ወንበሮች በሁለቱ ኩፐርና ኩግ ተቀምጠዋል።

ኤድዋርድ ፊጠን ያለ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ከፊት ለፊታቸው ባለው ወንበር ፓጋኖን ከጎኑ አድርጎ ተቀመጠ።

ኤድዋርድ መቀመጫውን እንደያዘ ወደ ሁለቱ ፋኖዎች ሲመለከት ባየባቸው የተከሰከሰ ገጽታ ቅስሙ ተሰበረ። አንድ ችግር ተከስቶ ይሆን? እኒህን ሰዎች የገጠማቸው እንቅፋት ይኖር ይሆን?

ነገር ግን የኤድዋርድ ፍንጥት ከአእምሮው ሲቀረፍ ደቂቃ እንኳ አልወሰደም።

‹‹ባንድ ሰዓት ውስጥ መጓዛችን ነው›› ሲል ኩፐር ጀመረ። ‹‹ከመሄዳችን በፊት ትንጅታችን ምን እንደሚመስል ልናብራራልም ፈልጌ ነው። ሁሉም ነገር በእቅድ መሰረት እየተጓዘ ነው።››

ኤድዋርድ በእፎይታ በረጅሙ ተነፈሰ።

‹‹ቡድናችን የተተበላቸውን መሳሪያዎች ይዞ በተመደበለት ስፍራ ተሰማርቷል። የጠየቅንም መሳሪያዎች በክፈል ደርሰውናል። በርግጥ ሄሊኮፕተር ገና አልደረሰችልኝም፣ ሆኖም አሰከሚቀጥለው ሳምንት ስለማታስፈልገን ጊዜ አለን። ሌሎች እቃዎች ከእንግሊዝ ዌልስ ወደ ፈረንሳይና ወደ ስፓኝ ጠረፍ እየተጓዝሁልን ናቸው።››

‹‹ብዙዎቹን መሳሪያዎች ተተብላችኋላ? እንዲህ በፍጥነት?››

‹‹ያፈጠነው የክፈሉን ገንዘብ ደንስ ያለ በመሆኑ ነው›› አለ ኩፐር፣ ‹‹በሚቀጥሉት አርባ ስምንት ሰዓቶች ውስጥ በስፓኝ ክልል እንገባለን። ቀጥለን ከንጉሱ የጉብኝት ስፍራዎች ጋር ራሳችንን ስናለማምድ እንቆያለን።››

‹‹ብቻ ንጉሱ የጉብኝቱን ፕሮግራም እንዳይለውጡ›› አለ ኩማ ማልቃ ግብዶ።

‹‹የፈለገ ይለወጥ›› አለ ኩፐር ወደ ኤድዋርድ ዞር ብሎ። ‹‹እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ የፕሮግራሙን ትክክለኛነት በራሳችን ስልት እናረጋግጣለን። በጉብኝቱ ላይ ለውጥ ከተደረገ ወዲያውኑ እትዳችንን ከአዲሱ ፕሮግራም ጋር እናተናጀለን።››

‹‹የጥበቃ ሪፖርታችንስ አርከቲችኋል?›› ኤድዋርድ ሊያውት ፈለገ።

‹‹በጣም ጠቃሚ ሪፖርት ነው›› አለ ኩፐር፣ ‹‹የንጉሱን ጥበቃ አደረጃጀት ባናውቅ ኖሮ እትዳችንን መንደፍ ያስቸግረን ነበር።››

‹‹እንደሚሳካላችሁ ተስፋዬ ነው›› አለ ኤድዋርድ በመጨረሻው።

ኩፐር ከመተመጫው ተነሳ። ‹‹እንደሚሳካልን ተስፋችን ነው›› አለ፣ ‹‹ግን ዋስትና እንስጥም። የምናደርገው መከረ ነው። አሁንት መሄድ አለብን። ሚስተር ፓጋኖ አብሮን እንዲጓዝ ይፈልጋሉ?››

ኤድዋርድም ብድግ አለ። ‹‹የፓጋኖ መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው። ለተግባራችሁ ሁሉ የኔ አምባሳደር ነው። እኔም ነገ ከለንደን እለቃለሁ።

ፓፓኖ አድራሻዬን ስለሚያውቅ በፈለግን ጊዜ ሃሳብ መለዋወጥ እንችላለን። ለመሆኑ ለጉዞው ተዘጋጅተሃል፣ ጉስ?››

‹‹ገዛኽ ነኝ›› አለ ፓፓኖ።

‹‹እንግዲህ ሁሉንም ካንተ ነው የምሰማው።››

‹‹ነገሩ በሆነበት ደቂቃ ጆሮም ውስጥ እንዲገባ አደርጋለሁ።›› ፓፓኖ ቃል ገባ። ‹‹ልክ መሳሪያዎቻችንን ባስገባንበት ስልት እኔም እንደ ኮንትሮባንድ በድብቅ በፈረንሳይ ጠረፍ በኩል ስጋኝ እገባለሁ። ነገሩ እንደተፈጸመ እደውልልዎታለሁ።››

‹‹መልካም›› አለ ኤድዋርድ በእርካታ፣ ‹‹መልካም እድል።›› ኤድዋርድ ለሱቱም ሰዎች ከክፍሉ ሲወጡ እንደቆመ ከተመለከታቸው በኋላ የሚኮሰኩሰውን አይነ-ርግብ እውልቅ ወደ ክፍሉ ተመለሰ።

አልጋው ላይ በቱመሙ ዘሮድ ሲለበት ለመጀመሪያ ጊዜ ውስጣዊ ደስታ በአእምሮው ተሰራመሰ። አንዳች ውስጣዊ ስሜት ከውስጥ ተሰማው። ያለው ኒውዮርክ አለመሆኑንና በቱጥታ ወደ ኪም ነሰቢት ሂዶ ስሜቱን ማርካት አለመቻሉ ቆጨው። ነገር ግን የእውነተኛ ስሜቱን ርካታ የሚያገኘው ከኒውዮርክ ሳይሆን ከሳን ሲባስቲያን መሆኑ ወዲያውኑ ትውስ ብሎት ሳቅ አለ።

* * *

ሳን ሲባስቲያን ላይ ንጋቱ ተገለጠ ነበር። የስጋኝ ንቅሥ በፕሮግራሙ መሰረት ከነተከታዮቻቸው ደረሱ።

የከተማዋ ህዝብና የንጉሱ አጀቢዎች ከፖሊሱ ጋር ተዳምረው የፈጠሩት ትርምስ እንቅፋት ቢሆንባቸውም ራምሲና ቪክቶሪያ የንጉሱን እንትስታሴ በተከራዩት አዲስ ሬኖ መኪና ለመከታተል ችለው ነበር። በፕሮግራሙ መሰረት ከእንድም ሁለት ቦታዎችን ሲመለከት አይተዋል።

አራት ሰዓት ላይ ንጉሱ በፖሊስ ዴ አየት ጉብኝት-ማድረግ ሲጀምሩ ራምሲ ትእግስቱን ማጣት ጀመረ። ቪክቶሪያ ግን ጉብኝቱ በፕሮግራሙ መሰረት በመካሄዱ ደስታዋ ልክ አልነበረውም። ልክ አራት ሰዓት ተኩል ላይ

ቪክቶሪያ ወደ ራምሲ ጠጋ ብላ፣ ‹‹አራት ተኩል ሆነ ኒክ፣ በፕሮግራሙ መሰረት ንጉሱ አሁን ወደ ማዘጋጃ ቤት ይጓዛሉ። ወደ መኪናችን እንሂድ›› አለችው።

‹‹ከመሰለሽ›› አያለ ራምሲ ሀገሩን እየሳሰ ከቪክቶሪያ ጋር ወደ መኪናው ጉዞውን ቀጠለ።

መኪናቸው ውስጥ እንደገቡ ልዑላዊዋን መኪና እየተከተሉ ወደ ሳን ሴባስቲያን ማዘጋጃ ቤት ገሰገሱ። ማዘጋጃ ቤት እንደደረሱ ሬኖ መኪናቸውን ከመኳኳላቸው የተነሳ ባልተፈተደ ክልል አቆመውና ከበፊቱ የበለጠ በተጠቀጠቀው ህዝብ እየሳሱ ንጉሱና አብረውት የመጡት ጎብኚዎች ከከንቲባው ጋር ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ሕንጻ ሲገቡ አዩ።

ንጉሱ ህንጻው ውስጥ ገቡ፤ው ሃያ ደቂቃ ያህል እንደቆዩ ራምሲ ይበልጥ ግድ የለሽና ተበጥባጣ እየሆነ ይመጣ ጀመር። በመጨረሻም የቪክቶሪያን ኮት እጅጌ እየሳበ ‹‹ምን እያደረግን ነው ቪኪ?›› አላት።

‹‹እስካሁን ምንም›› አለችው።

‹‹ንጉሥ አንድ ከፍለ ሀገር ሲጎበኝ አይቼ አላውትም እንዴ? በይ ቻው።. . .››

‹‹መሄድህ ነው?››

‹‹ሄድኩልሽ፣ ወደሆቴል ሄጀ ትንሽ ልተማምስና ልተኛ። ስለጉብኝቱ ሪፖርትሽን አጠናትረሽ ስትጨርሽ ተሰትሽኝ። የሞራል ድጋፍ እሰጥሻለሁ።››

የሚናገራት እያሾፈ መሆኑ አልጠፋትም። ይባስ ብሎ የመኪናውን ‹ቁልፍ እየሰጣት ‹‹ጥናቱን ይስጥሽ እንግዲህ ሃቀኛዋ ጋዜጠኛ›› ብሏት በተጨናነቀው ህዝብ መሃል ገብቶ ተሰወረ።

በኒክ ፈገግ በማና፣ በራሷ መጀመል ራሷን ታገባ፣ ልትከተለው ብትፈልግም አንዳች ነገር እግሯን ስለተበተባት ልትንቀሳቀስ አልቻለችም። ራሷን ልታጽናና እየሞከረች ‹‹ሽ.. . .ት ከዚህ ጉብኝት አንድ የሚከሰት ነገር ይኖር ይሆናል፣ እኔ ደግሞ ሪፖርተር እንደመሆኔ ከዚህ ስፍራ መራቅ የለብኝም። ኒክ ደግሞ ማነው? ከመለዚያው ጋር የተቆራኘ ጣዜ›› አለች

በልቧ።

አምስት ሰዓት ከሩብ ሲሆን እንኳ ንጉሱ ከማዘጋጃ ቤቱ ሀንጻ አልተመለሱም። ይህ ማለት ደግሞ ፕሮግራሙ እየተጣበበ ነው ማለት ነው።

አስር ተጨማሪ ደቂቃዎች እንዳለፉ የሕዝቡ ሁከትና ጮቤረገባ የቪክቶሪያን ትኩረት ሰረቀው። በእግሯ ጣቶች ቆማ ስትመለከት የንጉሱን ገጽታ ልታይ ቻለች። ንጉሱ ወደ መኪናቸው ከመግባታቸው በፊት ከሳን ሴባስቲያን ከንቲባ ጋር ይጨባበጣሉ። አጃቢዎቻቸውና ጠባቂዎቻቸው ከበዋቸዋል።

ቪክቶሪያ ሕዝቡን እየንሰነሰች ሰንጥቃ ወጣችና ወደ መኪናዋ አመራች። መኪናዋ ውስጥ እንደገባች የሳን ሴባስቲያንን አቀማመጥ የሚያሳየውን ካርታ አገኘችው። በካርታው ላይ ንጉሱ ጉብኝት የሚያደርጉባቸውን ስፍራዎች ምልክት አድርጋባቸው ነበር። ስለዚህ አሁን ከማዘጋጃ ቤት ጉብኝታቸው ቀጥሎ ወዴት እንደሚጓዙ ለማወቅ አላስቸገራትም። ንጉሱ አሁን የሚያመሩት ወደ ቡን ፓስቶር ቤተክርስቲያን ነው። የመኪናዋን ሞተር አስነስታ መንገዱን ያዘች።

ቤተክርስቲያኑ ከፊት ለፊቷ መታየት እንደጀመረ መኪናዋን ማቆሚያ ፍለጋ ታማትር ጀመር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከማርገጃው ትይዩ ከሚገኘው ድልድይ አጠገብ መኪናዋን ልታቆም ቻለች።

አሁንም ሊላ የሕዝብ ትርምስና ሁከት ቤተክርስቲያኗን አሰጨንቋታል። መግቢያውን በር የከበበው ሕዝብ ፖሊስ ባይኖር ኖሮ የቤተክርስቲያኑ መቅደስ እንኳ ባላገደው ነበር። ቪክቶሪያ አካባቢውን በግልጽ የሚያሳይ ጉብ ያለ ቦታ ብትፈልግም አልቻለችም።

ሕዝቡ እይታዋን የከለለው ቢሆንም ቪክቶሪያ ንጉሱ ከመኪናቸው ወርደው ከባለሥልጣኖቻቸው ጋር ወደ ካቴድራሉ መግቢያ ሲያመሩ ይታዩዋታል። ቀጥሎም የንጉሱ አጃቢዎች ከግራ ቀኝ ቀረት ሲሉ፥ ንጉሱ ግን በሁለቱ የግል ጠባቂዎቻቸው እንደታጀቡ ወደ አንድ ቁስ ሲያመሩ አየች። አራቱ ሰዎች ባንድነት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገቡ።

ንጉሱ ሁለት አጃቢዎችን ብቻ አስከትለው ወደ ካቴድራል መግባቱ

ያልተለመደ በሆነም ቪክቶሪያ ምን እየተደረገ እንደሆነ ወዲያውኑ ተረዳች። ይህ የካቴድራል ጉብኝት ለአምድር ጊዜ የሚቆይ መሆኑንና ንጉሱ ወደ መቅደስ የሚገቡት ንስሐ ለመግባት መሆኑን ተገነዘበች።

ቪክቶሪያ ፈገግ አለች። ከዚህ ጉብኝት ለህትመት የሚበቃ ዜና አግኖለሁ ማለት እውነትም ኒክ አንዳለው ሞኝነት ኖሯል። ያም ሆነ ያህ ምንም ያህል ቢታክታት ለመጨረሻ ጊዜ በትእግስት ለመጠበቅ ወሰነች።

* * *

የካቴድራሉ ውስጣዊ ክፍል ቀደም ሲል ከቱሪስቶችና ከአማኞች የፀዳ ከመሆኑም በላይ በተወሰኑ ስፍራዎች ላይታዩ ተርተው አሁንም ሲሰግዱ ከሚገኙ ቀሳውስት በስተቀር በመላው ካቴድራል የሚታዩት ንግሥቲ አስተናጋጇ ቄስና ሁለቱ ጠባቂዎች ብቻ ነበሩ። በመጨረሻው ንጉሱ፣ ጠባቂዎቹና መሪው ቄስ ባሉበት እንዲቆዩት ምልክት ሰጥተው ብቻቸውን ወደፊት ተራመዱ።

በመቅደሱ ውስጥ ግርማ ሞገሱ ከሚያሰፈራው ክፍልና ከትዳላን ስፅሎቹ በታች የስጋቸው ንጉሥ ሰፋ ያለውን ባዶ ክፍል እቅርጠው ወደ ኑዛዜ ተቀባዩ ሰግነት አመሩ። በመጋረጃ ወደተከለለው መግቢያ ሲደርሱም ከዚያ ሁሉ የሕዝብ ሀብት የተገለለበት፣ ከዚያ አስጨናቂ የፖለቲካ ስራቸው የተወገዱበት የእርያታ ትጽበት በመሆኑ ንጉሱ ሃሳባቸውን ለማሰባሰብና የነፍሳቸውን ሽግን ለመጉመጥመጥ ወደሚንበረከኩበት ስፍራ ተጠጉ።

ንስሃ ከሚገቡበት ስፍራ ገባ ብሎ ኑዛዜያቸውን አጸምጦ የምሀረት ታሉን በፈጣሪ ስም የሚያሰማቸውን ቄስ የሚከልል ሌላ መጋረጃ አለ። በዚያ መጋረጃ ተከልሎ ሃጢአታቸውን ሲናዘዙ የሚያጸምጣቸው ያ ቄስ ጳጳሱ ራሱ እንደሆኑ ንጉሱ ያውቃሉ።

ንጉሡ በጉልበታቸው ተንበርክከው ራሳቸውን ሥጋጃው ላይ ደፋ አድርገው. ፊታቸውን በመጸፋቸው እንደከለሉ ዝት ያለ ቢሆንም በጥራት በሚሰማ ድምጽ ኑዛዜአቸውን ቀጠሉ።

‹‹አባቴ፣ በድየሃለሁ።››

«አዎ፣ ልጅ።»

«ያትር በለኝ. . .»

በዚህ ቅጽበት መጋረጃው ግራ ቀኝ ተበረገደ። ንጉሡ በዚህ ተደንቀው አላቆሙም። የጳጳሱ መልክ አልታየም። እንዲያውም አንድ ዓንት ያጠለቀ ፊት በተበረገደው መጋረጃ መሃል ባለ 9 ካሬ በር ሽጉጥ ደግኖ አፈሙዙን ከንጉሡ ግንባር ላይ አሳረፈው።

«አጅ ወደ ላይ!» ስትጥጥ የሚያደርግ ድምጽ አዘዘ። «የታዘዝከውን ትፈጽማለህ ወይም ትሞታለህ።»

ንጉሡ እንደተንበረከኩ ቀሩ።

መጋረጃው ሙሉ ለሙሉ ተገለጠ። ከውስጡ የቁስ ልብስ የለበሰ ሰው ጠመንጃ ደግኖ ሲዘልት፣ ወዲያው ደግሞ የጳጳሱ የራስ ጥምጥም በራሳቸው ዙሪያ ሲጠመጠም እንደገና የጳጳሱ መጎናጸፊያ በትከሻቸው፣ በክንዶቻቸውና በመላ ሰውነታቸው ዙሪያ ሲያርፍ ግብናቸውን አስተዋሉ።

«ተነስ!» ሲላ ጨካኝ ድምጽ በስጋትና ቁንጽ ጆሮአቸው ላይ አምባረቀ። ንጉሡ ራሳቸውን ችለው ለመነሳት አትም ማጣታቸው ያስታውሱ ሲል የጳጳሱን ረዳት መጎናፀፊያ የለበሰ፣ ግን አውቶማቲክ መሳሪያ የታጠቀ ቁስ ብቅ አለ።

ሁለቱ ቀሳውስት ንጉሡን አፈፍ አድርገው አነሱና ከንስሃ መግቢያው ክልል አሳልፈው ወደ ውስጥ እየገፈተሩ ወሰዷቸው። እኒህን ሁለት ቀሳውስት ከውስጥ ሊለዩ ጥንድ ምስመናን ይጠብቋቸው ኖሯል። ንጉሡ በአራት የታጠቁ ቁሶች ተከበቡ።

አራቱ ቁሶች ንጉሡን ይዘው ወደመጡበት ወሰዷቸው። ከመቅደሱ ሲወጡ ንጉሡ የራሳቸውን በወጉና ብዙ ቁሶችን ሊመስኩ ቢችሉም, ከአንደበታቸው አንድም ቃል ሊወጣ አልቻለም። አስመሳዮቹ ቁሶች ንጉሱን በአውቶማቲክ መሳሪያ ከበው ይዘዋቸዋል።

የበለጠ አረመኔአዊ ቅላጼ ያዘለ ድምጽ ወደ ንጉሡ ጆሮ ጠጋ ብሎ፣ «ወደ ውጭ ወሰደን በሰተጀርባ ወደምትገኘው መኪና ልንወስድም ነው።

ጸባይም ካሳመሩ ይድናሉ። አንድ ታል ከተነፈሱ ግን ይሞታሉ፡፡ አላቸው።

ንጉሡ በእምነታ ራሳቸውን እየነቀነቁ እንደሚታረድ ከብት ከመነጫጨ በስተቀር የሚናገሩት አልነበራቸውም።

* * *

ቪክቶሪያ የካፑድራሉን መግቢያ በመመልከት አይኗን ብቻ ሳይሆን የሰራ አካላቷን ታክቲታል።

ሊሎች አስራ አምስት ደቂቃዎች ቢያልፉም ንጉሡ ብቅ አላሉም። የኒክ ራምሲ ግምት ትክክል ለመሆኑ ቪክቶሪያ ልትመሰክርለት ተቃርባለች። ይህ ቀን እሷን ብቻ ሳይሆን የኒውዮርክን ኤድዋርድ ሳይቀር ቅር የሚያሰኝ ቢና አልባ ቀን እንደሆነ ለታምን ምንም አልተራትም።

በዚያው ቅጽበት ግን አንድ የተንከለከለ የጩኸት ድምጽ ከፊት ለፊቷ ተሰማት።

የሆነውን ለማወቅ ከፊት ለፊቷ የቆመችን ገበሬ ባልና ሚስት በርቅሳ ከፖሊሶች አጠገብ እንዴት እንደደረሰች ራሷም አታውቅም። በደቂቃ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑን በር መሉ ለመሉ ማየት ከምትችልበት ቦታ ደርሳ ስትመለከት ይበልጥ የሚያስገርማት ነገር ገጠማት። በሩ ላይ መትናፀፊያውንና ቀምጣሙን የተላማ ሰው፡ ጳጳሱ ራሳቸው ሳይሆኑ አይቀሩም፡ በጥቢቃ ወታደሮችና በንጉሡ ዘቦች ላይ ያምባርቃሉ። የወታደሮቹ አለቃ የሚመስል መኮንን ጳጳሱን ደግፎ አድርጎ ይዞ ሊያፅናናቸው ይሞክራል።

የፖሊሱ መኮንን ወደ ኋላው መለስ ብሎ ከህዝቡ እንደሚቀላቀል ሁሉ ፊጠን ብሎ ይራመድ ጀመር። ፖሊሱ በዚያው ደቂቃ ለወሬ ባቆበቆበው ህዝብ ባይከበብ ኖሮ ቪክቶሪያ ዘላ ከፊት ለፊቱ ገሮ ብላ በጥይቱ ባዋከበችው ነበር። የካቴድራሉ በር በወታደሮች ተጣበበ። ብዛት ያላቸው ፖሊሶች ወደ መኪናዎች ሲሮጡ ተሳፍሰቱ ደግሞ ጳጳሱን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ ይገፋፋሉ።

በእፍታ አካባቢው በዙትና በመኪናዎች ሞተር ጩኸት ተጨነቀ። ያለ

ምንም ጥርጥር እንድ አሸባሪ ነገር ተከሰቷል፣ ቪክቶሪያ ግን የስጋኛ ቋንቋ ባለመቻሏ የሆነውን ነገር ለማወት አልቻለችም። በደመነፍስ ድምጿን ከፍ አድርጋ በዙሪያዋ በሚተራመሱት ሰዎች ላይ ጮኸች። "ምንድነው የሆነው? ምንድነው እሱ? እንግሊዘኛ የሚናገር የለም?"

ራት ብሎ የነበረ ተማሪ የሚመስል ወጣት ወደፊ ቀረብ ብሎ ትከሻዋን ነንቶል አደረጋት "እንግሊዘኛ እችላለሁ" አላት፣ "ንጉሡን ከቢተክርስቲያን መቅደስ ሽበር ፈላሪዎች በመሳሪያ አስገድደው አፍነው ወስደዋቸዋል። መጀመሪያ ጳጳሱን የፍዮኝ አስረው በሳቸው ቦታ ተተክ። የቀሩት ደግሞ የቄስ ልብስ ለብሰው ነው የመስዲቸው።"

ጆሮዋን ልታምን አልቻለችም። ወጣቱ እንዳይሄድባት ክንዱን ሙጭጭ አድርጋ ያዘች። "ንጉሡ ተጠለፉ?" ስትል ጮኸች። "እርግጠኛ ነህ?"

ወጣቱ በአምንታ ራሱን ነቀነቀ። "አውነት ነው ተጠልፈዋል።" ቪክቶሪያ ክንዱን የበለጠ ሞምድድ አድርጋ ያዘችው፣ "ማነው የጠለፋቸው?"

ወጣቱ ራሱን በአለታ ነቀነቀ። "ይህን የሚናገር የለም. . ግን ያለጥርጥር የባስክ ተገንጣዮች መሆን አለባቸው።"

ለተግባር እንጂ ለሃሳብ የሚበክን ጊዜ አልነበረም። ቪክቶሪያ የሚተራመሰውን ህዝብ በረቃቅሳ እየተጣደፈች ወደ መኪናዋ በረረች።

በቢተክርስቲያኑ በመዶየቲ ደስታ ተሰምቷታል። ኒክ ራምሲ የሚፈጠር ነገር የለም ብሎ ወደ መኝታው በመሄዱ ለራሱ ትልቅ ነገር ተርፎበታል። ታላቅ ዜና የሚሆን ነገር ተከስቷል፣ ሲከሰትም ከሞላ ጎደል በአይኗ ተመልክታለች። ትኩሱን ዜና ከሁሉ አስቀድማ ያወቀችው እሷ ነች። ይህን ትኩስ ዜና ከነእንፋሎቱ እያግለበለበች ለሪኮርድ ጋዜጣ ታተርባለች። ከይንዝ ማምለጥ በኋላ ለሪኮርድ ሊላ ታላቅ ድል ልታቀዳጅ ነው። ኤድዋርድ አርምስቱድ በደስታ ይሰክራል። እሷንም የሚያደርጉት ይጠፋዋል።

የአሁኑ ደቂቃ ተግባሯ ወደ መኝታ ሆቴል መበረርና እንግሊዝኛ መናገር በምትችለው የሆቴሉ ስልክ ኦፕሬተር አማካኝነት አገር አቋራጭ ጥሪ

ማድረግና ትኩስን ዜና ለሚሰተር ኤድዋርድ ማብሰር ነው።

የሲንን ንጉሥነ ተጠለፉ።

ፈናዋን አያስንሳረች ወደ ሆቴሏ ሸው አለች።

* * *

ሆቴሏ እንደገባች የኒውዮርክ መስመር እንድታገናኛት ለሆቴሉ ሪፖርተር ደወለችና የኒውዮርክ ሪኮርድን የሰላክ ቁጥር በጥንቃቄ አጻፈቻት።

‹‹ይጠብቁ›› አለቻት ኦፕሬተሯ፣ ‹‹መስመሩን እንዳገኘሁ እደውልልዎታለሁ።››

ቪክቶሪያ ተማፀነች፣ ‹‹እባክዎ የኔ እመቤት በተቻለ መጠን ፈጠን ቢያደርጉልኝ?››

ኦፕሬተሯ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር በድንጋጤ በመናገር ‹‹መስመሩን እንዳገኘሁት እደውልልዎታለሁ›› አለችና ጆሮዋ ላይ ዘጋችባት።

ቪክቶሪያ ከመጠባበቅ ሌላ አማራጭ አልነበራትም። የጠለፋውን ታሪክ በምን ቅደም ተከተል ለኤድዋርድ እንደምትተርክለት በአእምሮዋ ታውጠነጥን ጀመር።

ደግነቱ ሰላኩ ሁለት ደቂቃ የሞላ ጊዜ እንኳን ሳትቆይ አታጨለ። ቪክቶሪያ ደግሞ አስኪያስጮል ፋታ አልሰጠችውም፣ አፈፍ አደረገችውና ‹‹አቤት?›› አለች።

የኦፕሬተሯ ተገራገጭ ያለ አነጋገር ያሳበዳል። ሞራሹን ‹‹ወይዘሪት ዊስተን ያስመዘገቡትን ሰላክ ባሁኑ ሰዓት ማግኘት አንችልም›› አለቻትና አረፈችው።

‹‹ምን?››

‹‹ምናልባት ቆየት ብለው፣ ወደ ማታ አካባቢ እንደገና ቢያስመዘግቡን እንሞክርልዎታለን።››

‹‹ኧረ እባክሞ. . . ››

‹‹አስቸኳይ የፖሊስ ትእዛዝ ተቀብለናል። ከሳን ሲባስቲያን ውጭ የሚደረግ የሰልክ ጥሪ በሙሉ ለጊዜው ታግዷል። እንደተፈቀደ ራሴ ደውየ እነግርዎታለሁ።

ልመናውን መተጠሉ ዋጋ እንደሌለው ቪክቶሪያ ወዲያውኑ ተገነዘበች። ወሽመጡ በተበጠሰ ሰው እንጋገር ‹‹እጠብቃለሁ›› ብላ ስልኩን ዘጋች።

ትስሟ እንደተሰበረ አልቀረችም። አንድ ሃሳብ ድቅን ብሎላት ፈገግ አለች። አዎ፣ የውጭ ሰልኩ ጥሪ ተከለከለ ማለት ሊሎች ተቀናቃኝ መገናኛ ብዙሃንም ተመሳሳይ ችግር ይገጥማቸዋል ማለት ነው። ማንኛውም የስጋኝ ጋዜጣ ዝግጅት ወይም የዜና ወኪል ከሳን ሲባስቲያን ዜና እንዳያስተላልፍ ተከልክሏል ማለት ነው። በዚህ አይነት ደግሞ የስጋኝ ራዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ዜናውን እንዳያሰራጭ እንደተከለከለ ቪክቶሪያ እርግጠኛ ሆነች። በሌላ መልኩ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የንጉሥ ጠበልፍ መቆ በሙቦ እርግጠኛ መሆኑን ነው።

ታዲያ ምን መደረግ አለበት?

እም ኒክ ራምሲ፣ ጉድ አልሰሚ ኒክ፣ ብቻዋን የታቀፈችውን ታላቅና ትኩስ ዜና አያውቅ፣ በሚተዋለው ክፍል በጀርባው ተንጋሎ ቀን አለቀን እንቅልፉን እየለጠጠ ነው። ዜናውን ወዳ ኒውዮርክ እንዴት በፍጥነት ማድረስ እንደሚችሉ ኒክን ማማከር አለባት።

ከነጥሏ ስትንደረደር ወጥታ ኮሪደሩን አቋርጣ ወደ ራምሲ ክፍል ገሰገሰች። ያ ንውዚ በድንጋጤ ከእንቅልፉ እንዲባንን በሩን በእግሯም በቡጢም ነጠረቀችው። በሩ በትጽበት ተበርግዶ ተከፈተ።

‹‹ኒክ. . .›› ስሙን ጠርታ አልጨረሰችም፣ ወይም የተከፈተውን አፏን አልከደነችም። ያልተጠበቀ አስደንጋጭ ነገር በማየቷ ከው ብላ እንደ ተገተረች ቀረች።

ዩኒፎርም የለበሰ ወታደር መሳሪያ ደግኖ በሩ ላይ ቆሞ አፈጠጠባት። በሩን የከፈተው እሱ ኖሯል። ከውስጥ ራምሲ አልጋው ላይ ያለጫማ ደረቱ እንደተግለጠ የቤት ሱሪውን ለብሶ ተቀምጧል። በግራና በቀኝ ሊሎች ሁለት ወታደሮች ጠመንጃ ደግነውበታል። ራት ብሎ በሚታየው ጠረጴዛ አካባቢ

አንድ ሴላ ወታደር ሰልክ ይዟል። ይህ ሰው ምናልባት መኮንን ሳይሆን አይቀርም።

ቪክቶሪያ ራምሲን ተመለከተችው። ሰክሮ ያደረ ሰው ከመምሰሉ በስተቀር የድንጋጤ ምልክት አይታይበትም። የአለጋው ምንጣፍ ተመሰቃቅሏል።

አንድ እጁን ከፍ አድርጎ ፊጥ እያለ ሰላምታ ሰጣት። ‹‹ሄይ ቪኪ››

‹‹ምንድነው ነገሩ?›› ወደ ራምሲ እየተራመደች ጠየቀች። መሳሪያ ከደገነበት ሁለት ወታደሮች መካከል አንደኛው በስጋንቲኛ አንድ ነገር ተናገራት። ቋንቋው ባይገባትም መረመዲን ትታ ቆም አለች። ‹‹ኒክ. . . ንጉሡ ተጠልፈዋል።››

‹‹አውን ሰማሁ›› አለ ራምሲ ‹‹አንዲያውም ከጠላፊዎቹ መካከል አለሀበት እየተባልኩ ነው።››

‹‹ምን? እዚሁ አይደለም እንዴ የዋልከው? በምን ጠረጠሩህ?››

‹‹ባለፈው ሳምንት ሲከታተሉኝ ኖሯል። የባስክ ተገንጣዮች በሚያስተዳድሩት መድሃኒት በት ስገባ ታይቻለሁ። መግባት ብቻ ሳይሆን ምንም ነገር ሳትገዛ እንዴት ወጣህ ይሉኛል። የጠለፋውን ሴራ አብረህ ጠንስሰሃል ተብያለሁ።››

‹‹እንዴት የሚያስት ሞኝነት ነው›› አለች ቪክቶሪያ ራሷን እየነቀነቀች።

‹‹ሞኝነታቸውን ንገሪያቸው›› አለ ራምሲ እየሳቀ።

‹‹ስማ ኒክ እርዳታህ ያስፈልገኛል. . .››

በትጽበት ኮስተር አለ ‹‹መጀመሪያ እኔ ያንቺ እርዳታ ያስፈልገኛል›› አላት፤ ‹‹ፈጠን ብለሽ ለሚስተር ኤድዋርድ ይውደና ከአምባሳደሩ ጋር ተነጋግሮ እንዲያስለቅቁኝ ንገሪው።››

‹‹ችግሩ እሱ ላይ ነው›› አለች ቪክቶሪያ ፈጠን ብላ፤ ‹‹አንተን ለመርዳትም ሆነ ዜናውን ለማስረዳት ኤድዋርድን ማግኘት አልችልም። የውጭ ጥሪ ሁሉ ታግዷል። ሌላ ምን መፍትሄ አለ?››

«ወጥታ» ከጠረጴዛው አካባቢ ድምጽ ተሰማ። ሰልክ ይሆ የነበረው መኮንን ስልኩን ዘግቶ ባርኔጣውን አደረገና ወደ አልጋው አመራ። ቀጥሎም ወደ ራምሲ እየተመለከተ፣ «ልብስህን ልበስ» አለው። «ከአለቆቹ ጋር ተነጋግሬ መመሪያ ተቀብያለሁ። ነገሮች አስኪጣሩ በቁጥጥር ስር ትውያለህ። ታልህን ስለምተበልህ ወደ ጣቢያ እንሂዳለን።»

«ይኸውልሽ» አለ ራምሲ በረጅሙ ተንፍሶ የሸሚዙን ቁልፎች እየቆለፈና ተስፋ በቆረጠ አስተያየት ወደ ቨክቶሪያ እየተመለከተ፣ «ሁላችንንም በቀላሉ የሚለቁን አይመስለኝም» አላት።

መኮንኑ ቨክቶሪያን እንዲያስወጧት ለወታደሮቹ የትእዛዝ ምልክት ሰጠ።

«ምንም አንሆንም ኒክ ስማኝ» አለችው ቨክቶሪያ፣ «በተጥታ በፈረንሳይ ክልል መዳለችው ወደ ቅድስት ጂን ደ ሉ እበራለሁ። ከዚህ ርቀቷ ሃያ ማይል አይበልጥም። ከዚህ በፊት ቦታዋን አውታታለሁ። በባቡር ወይም በተገኘው እንባለሁ።»

«ግን ያስወጣሻል. . .?» አላት።

«የአሜሪካ ፓስፖርት አሳያቸዋለሁ። ኒክ ተጥ ብየ ቻንታክ ሆቴል እገባለሁ። ግቡ የፈረንሳይ ስለሆነ የኒውዮርክ መስመር አግኛለሁ። ኤድዋርድን መስመር ላይ እንዳገኘህት ዜናውንና ያንተን ሁኔታ እነግረዋለሁ።»

ሁለቱ ዘቦች ቨክቶሪያን ወደ ሙጭ ወሰዷት። ኮሪደሩ አካባቢ ሰትደርስ ቆማ ወታደሮቹ ራምሲን እየገፈተሩ ከክፍሉ ሲያስወጡ ተመለከተች። ኮሪደሩ ሲደርስም ዙሪያውን ከበውት ወደ ደረጃው ይዘውት ሄዱ። ጥቂት ፈተት እንዳለ ራምሲ ከእንጉቱ ዞር ብሎ ባሰተለለ ሀዘን አስተያየት ቨክቶሪያን ተመለከታት።

ከአይን ተሰወረ።

እንደገና ወደ ሃሳቧ ስትመለስ ወደ መኝታ ክፍሏ እየሮጠች ሄደች። መንፈሷ እየተትበጠበጠ እያንም ሆነ ማንኛውንም ሰው፣ በዚያ የተበጠበጠ

ሥን ከሳን ሲላስቲያንም ሦነ ከስጋኘ መውጣት ይፈትዱ እንደሁ ታውጠንጥን ጀመር።

* * *

በተከሰቱባት ተደራራቢ ነገሮችና እንደፈለጋት እንዳትንቀሳቀስ በገመዧት ተደራራቢ ችግሮች የተነሳ ቪክቶሪያ የልብ ትርታዋ ሲቆም አስኪደርስ ስትጥት ነበር የሞለችው። ራምሲን ለመርዳት ትችል ዘንድ ስልክ በእጓጣኘ ለማግኘት እንደተጣደፈች፣ የንጉሥን መጠለፍ ከሁሉ ቀድሞ ለአሰራዋ ለማሰማት እንደጅመጠች ሰዓቶች እንደሴኮንድ ከነፉ።

ለሦቱሉ ተቆጣጣሪ ደህና ጉርሻ ሰጥታ የመጓጉጥ ተሽከርካሪ አፈላልጎ እንዲያግኘላት ለመነቸው። በባቡር ከተጓዘች የሚወስድባት ጊዜ ረጅም እንደሚሆንባት ነግራት። በመጨረሻ ግን ተቆጣጣሪው በሁለት ሰዓት ውስጥ ፈረንሳይ ከልል የሚያደርሳት አንድ የመኪና አከራይ ድርጅት ጥሩ መኪና እንግሊዝኛ አጣርቶ ከሚናገር ሾፌር ጋር አዘጋጅቶ ማግኘቱን አወሳላት።

ካሁን አሁን የተባለላት ሾፌር መኪናውን ይዞ ደረሰልኘ እያልኝ በየደቂቃው የሚጣደውን ሰዓት እየተመለከተች በንጉሡ አጠላለጥ ላይ የምትዘግበውን ጽሁፍ ረቂት ማዘጋጀቷን ተጠለች። ኤድዋርድን ልክ በስልክ ባገኘችበት ደቂቃ ትኩሱን ዜና ባንድ ጊዜ እንደ ደፍ ልታዘንብለት ፈልጋለች። በመጨረሻም የንሞዋን ንድፍ የሚያሳይ ጥራዝ በረንዳው አካባቢ አግኝታ ከግቸት በኋላ መደ ከፍቷ ጉብታ ተቀመጠች። የንሞ ዐርሳዋን አዘገጃጀታ ከከፍሉ ልትወጣ ጥቂት እንደቀራት ቀና ብትል የፖሊስ ዩኒፎርም የለበሰ ሰው በሩ ላይ ቆሞ አየች።

አም፣ ሁለት እንግሊዘኛ መናገር የሚችሉ ፖሊሶች ቆመዋል። ከሁለቱ መካከል ይበልጥ ግርማ ሞገስ ያለው የሚመስለው አንደኛው ፖሊስ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ መታወቂያውን ካሳያት በኋላ ቪክቶሪያ ዊስተን በርግጥ እዩ መሆኗን አረጋግጠ ጋስፖርት ጠየቃት። ቀጥሎም ታስመጪት ለማትረብ በይበልጥ ቀረብ ብሎ በእለቱ በዘጠማዋ ሽብር ፊጠራ እንደተከሰተ ከገለፀላት በኋላ እዷ የምታውቀው ነገር አለ እንደሁ ጠየቃት።

ከፈለን በአይኗ መመልከቷን በግልጽ ነገረችው። በኩድራሉ እንዴት

ልትገኝ ቻለች? በቱሪስትነት ንጉሡን ለመጠልከት? ሲል ላቀረበላት ጥያቄም፣ አይደለም፣ ስትል መለሰችለት። በቱሪስትነት ሳይሆን ጋዜጠኛ በመሆኗ የንጉሱን ጉብኝት በተመለከተ የሚዘጉ ነገር ታገኝ እንደሁ ለመከታተል በካቲድራሉ መገኘቷን ፊት ለፊት አሰረዳችው። ይህን በምን ልታረጋግጥለት እንደምትችል ፖሊሱ ከመጠየቁ ቪክቶሪያ ከኒውዮርክ ሪኮርድ የተሰጣትን የይለፍ ወረቀት አሳየችው።

ፖሊሱ ግን በይለፍ ወረቀቱ አለመርካቱን በመግለጽ መለሰላት። እሷም የሚያሰራትን የኒውዮርክ ሪኮርድ ቢሮ በሚችለው መንገድ ሁሉ ተግናኝቶ በመጠየቅ ማረጋገጥ እንደሚችል ነገረችው። በሴላ ታለምልልሰ ትነትኩ ቸጠለ።

ንጉሡ በሳን ሴባስቲያን ጉብኝት ከማድረጋቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ቪክቶሪያ በከተማዋ ስትዘዋወርና በተለይም ንጉሡ የሚጎበኟቸውን ስፍራዎች አስቀድማ ስታጠና እንደሰነበተች ተደርሶባት ኖሯል። ከዚያ በፊትም ንጉሡ የሚጎበኟቸውን ቦታዎች ለማወቅ ስታፈነፍን እንደነበር ማስረጃዎች ተጠቅሰውባታል። ለምን? የሚለው የፖሊስ ጥያቄ ቸጠለ። ቪክቶሪያም በበኩሷ ከኒውዮርክ የተላከችበት ስራ መሆኑን በድፍረት ገለጸች።

ከኪክ ራምሲ ጋር ለምን ስትዘዋወር እንደሰነበተችና ከሱ ጋር ያላት ግንኙነት ምን እንደሆነ ተጠየቀች።

ታለመጠይቁ ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ቀጥሎ ቆየ። በመጨረሻው ግን ፖሊሶች ቪክቶሪያ ምንም ሚስጥር አዘል ተልእኮ እንደሌላት አረጋገጡ።

ከላን ሴባስቲያን የወጣችው እጅግ ዘግይታ ነበር። ኪራይ መኪናዋ ውስጥ ከገባች በኋላ እንኳ በጉዞዋ ላይ ሶስት ጊዜ አስቁመዋታል። ከከተማ ውጭም ያንኑ ያህል በየቦታው ትእግስት የሚያስጨርስ ተደጋጋሚ ታለመጠይት። ስፖኘ ጠረፍ ላይ ሲደርሱ የጉምሩክ ፍተሻ ከማግሽ ሰዓት በላይ አቆማቸው። ፈረንሳይ ከልል ከገቡ በኋላም ቢሆን ሁኔታው እምብዛም የተሻለ አልነበረም። የመንገድ ሰራው፣ የትራፊኩ መጨናነቅና የመሳሰሉት እንቅፋቶች እንደልባቸው አላስንዟቸውም።

የኔቭል ወንዝ ድልድይ ተሻግረው ቅዱስ ጂን ዲ ሉ ከተማ ሲገቡ ቪክቶሪያ እፎይታ ተሰምቷት ፈገግ አለች። የወደፊ ከተማ ቀለል ያለች እንግዳ ተቀባይ ከተማ ነበረች። ቪክቶሪያ ግን ከተማዋ ሌላ ትኩረቷ የሚሳብበት ቀልብ አልነበራትም።

መሃል ከተማ ሊገቡ እንድ ማይል ሲቀራቸው ከታውቦው ከቻንታክ ሆቴል ደረሱ። የሆቴሉ የመናፈሻ ስፍራ ውበትና ማራኪው ህንጻ አይነግቡ ቢሆንም ለቪክቶሪያ ምኗም አልነበረም። እዷ የምትፈልገው አንድ ጥያቄ እንደሚመለስላት ብቻ ነው። የጣላ መታጠቢያና ስልክ ያለው የመኝታ ክፍል አላቸው?

አላቸው።

መኝታ ክፍሏ ውስጥ እንደገባች በረሃብ የታጠፈውን አንጀቷን ቢሞረመረውም አእምሮዋ ለምግብ ቦታ አልሰጠውም። ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ኒውዮርክ ከተማ ጥሬ አድርጋ በአምስት ደቂቃ ውስጥ የሪከርድ ጋዜጣ አሳታሚ የሚስተር ኤድዋርድ አርምስቲድን መስመር አገኘች። የአሳታሚው ፀሐፊ ኢስቲል ራብኩን ስትተርብ ቪክቶሪያ ጉጉቷ የመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። እጅግ በጣም ባስቸኳይ ከሚስተር ኤድዋርድ ጋር መነጋገር አለባት። የተሰጣት መልስ ግን ከዚሮ የወጣና በትርብ የማይገኝ መሆን ሲሆን መቼ እንደሚመለስም ኢስቲል የምታውቀው ነገር የለም።

ወሽመጫ ተቆርጦ ሚስተር ሃሪ ዴትዝን እንድታገናኛት ጠየቀች፣ ቪክቶሪያ። እሱም ወጥቷል። ሌላ ወሽመጥ በማሽ መልስ።

ተስፋ ቆርጣ ሶስተኛውን ሰው ጠየቀች፣ ምክትል አዘጋጁን አለ ማክ አሊስተርን። አለ መስመር ላይ ተገኘ። ‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን ነኝ። ከሰዓት በኋላውን በመሉ እናንተን ለማግኘት ስደክም ነው የዋልኩት. . .››

‹‹እንደምነሽ ቪኪ?›› ከልክ ያለፈ ደስታ የተሰማው ሰው ለመሆን ከድምፁ ተረዳች። ‹‹ለመሆኑ የት ነሽ?››

‹‹የምደውለው ከቻንታኮ ሆቴል ነው. . . ቅዱስ ጂን ዴ ሉ።››

‹‹የት?››

‹‹ክሳን ሴባስቲያን በስፓኝ ጠረፍ በኩል በምትገኝ የፈረንሳይ ኩጦ ቻንታኩ ሆቴል ውስጥ ነኝ።››

‹‹እም ሚስተር ኤድዋርድ እሷን ከጦማ ሲጠቅስ ሰምቼዋለሁ. . .››

‹‹እጅግ የሚያስደንቅ ትኩስ ዜና አግኝቻለሁ። ማንም ሰው ክሳን ሴባስቲያን አውጥቶ ሊያስተላልፈው ያልቻለው አስገራሚ ድርጊት ተከስቷል። ክሳን ሴባስቲያን ወደ ውጭ መደወል ስለተከለከለ ነው እዚህ የመጣሁት። ዘራ ጧት የስፓኙ ንጉስ ተጠልፈዋል። ዜናውንም ማንም አልተደመጠም።››

‹‹እም ማንም አልተደመጠም ቫኪ›› ማክ አሊስተር መለሰ፣ ‹‹የግላችን ዜና ሆኗል! ታላቅና አስደናቂ ትኩስ ዜና። በዚህ ዜና ከአንድ ሰዓት በፊት የኒውዮርክ መንገዶች በረኮርድ አምበሽብሸናቸዋል። ‹የስፓኙ ንጉስ በሳን ሴባስቲያን ቤተክርስቲያን መቅደስ ውስጥ እንደገሙ በሚስጢር ሽብርተኞች ቡድን ተጠለፉ። ጠፈሙዝ የታሰሩት አልባሳት ለብሰው ነበር። ያሰምንም የተኩስ ድምፅ ንጉሱን ሊጠልፉ ችለዋል። በረኮርድ ጋዜጣ የመጀመሪያ ገፅ ላይ የወጣ አርእስተ ዜና ነው። ሬኮርድ በይንገር ጊዜ የነበረውን ያህል በወረሩ እየተቸበቸበ ነው. . .››

‹‹አሊ›› ቫኮቶሪያ በብሽቀት አቋረጠችው፣ ‹‹በትክክል የማናምጥ አይመስለኝም። ከጅሮየ ነው ወይስ ስለንተሱ ጠለፋ በውነት ሰምታችኋል?››

‹‹እየነገርኩሽ? በመጀመሪያው ገፅ ላይ ወጥቷል።››

ከጓላጥ በነበረው ሶፋ ላይ በቁሚ ወደቀችበት።

‹‹ግን አሊ፣ ነገሩን ያየሁትና የማውቀው እኔ. . . እኔ ብቻ ነኝ። ማንም ከስፓኝ ሊያወጣው ያልቻለ ዜና ነው።››

‹‹አንድ እድለኛ ካልተደመሽ ከየት አገኘነው ብልሽ ነው? በጣም ጥሩ ሞከረሽ ናሯል ግን. . .››

‹‹ማነው እሱ የተደመኘ?›› ሥቫት፣ ‹‹እንዴት?››

‹‹ከርዕሱ ስር የዜናው ዘጋቢ ማርክ ብራድሾ መሆኑን ጋዜጣው ላይ አንብቤአለሁ። እንደተነገረኝ ሰውየው ሚስተር ኤድዋርድ በአውሮፓ ዜና

ዘጋቢነት በኩንትራት የቀጠረው እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ ነው።››

‹‹እኮ እንዴት ወሬውን ከስጋኝ ሊያወጣው ቻለ?››

‹‹በሙነቱ እኔ አላውቅም ቨኪ። ወሬው የደረሰን በለንደኑ ቢሮአችን በኩል ነው። ማርክ ብራድሾ ዜናውን ሊያስወጣ የሚችልበት አንድ አማራጭ አግኝቶ ይሆናል። ምናልባት ልክ አንቺ በሞከርሽው አይነት. . .››

‹‹ግን ሌላ ተቀጣሪ እንዳላቸው ሚስተር ኤድዋርድ ከዚህ በፊት አልነገሩንም።››

‹‹ይህ የኢላታሚዎች ፀባይ ነው። ሁሉንም ነገር ለሰራተኞቻቸው አይነግሩም።››

አሁንም የተታውሞ ጥያቄዋን ልታሰማ ፈለገች።

‹‹ግን ኒክ ራምሲና እኔ. . .›› ይህን እንደተናገረች አንድ ነገር ታወሳት። ‹‹ሙይ አምላኬ፣ ሚስተር አለ አንድ የረሳሁት ነገር ትዝ አለኝ። ዛሬ ረፋዱ ላይ ኒክ ራምሲን የስጋኝ ፖሊሶች ይዘውታል። ከሥቱሉ እየገፈተሩ አውጥተው ወሰዱት። ሰለጠለፋው እንደተጠረጠረ ራሱ ነግሮኛል። ከተጎንጣዮች አባል ጋር ሲነጋገር አይተውት ነበር››

ማክ አሊስተር በግድየለሽነት ንግግሯን አቋረጣት፤ ‹‹እሱ ደግሞ በየሂደበት ፖሊስ እንዳፈሰው ነው›› አላት።

‹‹ታስሯልኮ አሊ።››

‹‹ልማዱ ነው።››

‹‹ሚስተር ኤድዋርድ ከግድሪዱ የአሜሪካ አምባሳደር ጋር እንዲነጋገሩና አንድ ነገር እንዲያደርጉለት ይፈልጋል። . .››

‹‹ጥሩ፤ እንደሚሆን እናደርጋለን።››

‹‹እኔም እዚው ሆቴል እንድጠብቀው ተነጋግረናል። ሚስተር ኤድዋርድ የሚተማመኑን ሰራችንን እንዲሰጡንም ማነጋገር አለብን።››

‹‹አትጨነቂ፣ ቨኪ። እየተንሸራሸርሽ ጠብቂው፣ ኒክን በተ

ታገኝዋለሽ። ስለሚተዋለው ስራችሁም እንደውልላችኋለን።››

ስልኩን እንደዘጋች ቪክቶሪያ ድካምና የብሽቀት ሲታ ጉሮሮዋን ተናነቃት። እንባዋ ቸርፈፍ አለ። የአንድ ቡድን ተጫዋች እንደመሆኗ የግው ግብ የዜናው ባለቤት የፃ ቡድን የሆነው ሪኮርድ መሆኑ በደስታ እንድትፈነድት ለማድረግ በቂ ነበር። ነገር ግን ግቡን ያገባችው ራሷ ባለመሆኗ፣ በራሷ ቡድን ተጫዋች በመቀደሚ አንጀቷ አሯል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከተመሰጠችበት የእልህ ሰመመን ብንን ስትል እንደገና ስልኩን አነሳችው። አሁን የምትደውለው ግን የሞቱለ አሰተናጋጅች ምግብ እንዲያቀርቡላት ለማዘዝ ነበር።

* * *

የሚቀጥለውን ቀን በአብዛኛው የኒክ ራምሲን የስልክ ጥሪ ስትጠባበቅ በመኝታ ክፍሏ እንደተጋደመች ነበር ያሳለፈችው።

ስልኩ ባቃጨለበት ጊዜ በንጉት ስታነሳው ያገኛችው ግን ኒክ ራምሲን ሳይሆን ከአሀጉር አቋራጭ ጥሪ የቀረበላትን ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቱድን ነበር።

‹‹ትናንት ስለጠለፋው ደውለሽልኝ እንደነበር ሰማሁ›› አላት ኤድዋርድ፣ ‹‹ጥሪትሽን ማድነቁን ልነግርሽ ነው የደወልኩት።››

ከንፈሯን ነክሳ እንደምንም ታገሰችና ‹‹ለማንኛውም ከኑ በፊት ዜናውን በመቀበልም እንኳን ደስ ያለም። በጣም ደስ ሲልም ይገባል›› አለችው።

‹‹ጥሩ አጋጣሚ ነበር›› አላት ኮራ ብሎ፣ ‹‹ኒውዮርክ የሚታተመውን ማንቸውንም ጋዜጣ በልጠናል። አጠገባችን የደረሰ የለም። የሚገርምሽ ዛሬ ጧት ደግሞ ሌላ ዜና ብቻችንን አገኘን።››

‹‹ምንድነው እሱ?›› ለስለስ ብላ ጠየቀች።

‹‹ጠላፊዎቹ ያቀረቧችውን ጥያቄዎች ዝርዝር ማርክ ብራድሾ ልኮልናል። ልትሰሚው ትፈልጊያለሽ?››

‹‹አዎ፣ በጣም እንጂ››

‹‹ላንብብልሻ፣›› አለ ኤድዋርድ አሁንም በኩራት፣ ‹‹ይኸው‚ልሽ ‹የባህሳ ብሔራዊ አርነት ንቅናቄ (ኢ.ብ.ኤ.) በሰ'ኙ ንጉሥ ላይ ለተካሄደው ጠለፋ ተጠያቂ መሆኑን አስታወቀ›።››

‹‹ጠላፊዎቹ ተገንጣዮች ናቸው ማለት ነዋ?›› ቪክቶሪያ አቋረጠችው።

‹‹ያለጥርጥር›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹ሊላ ማን ይሆናል ብለሽ ነው›› ንባቡን ተጠለላት። ‹‹በንጉሡና በሰ'ኛ መስተዳድር ላይ የምናደርገው የተቃውሞ እንቅስቃሴ በብሔራዊ ነፃነታችን የሚደረግብን ሞቶና እስከሚወገድ ድረስ ይቀጥላል›› ካሉ በኋላ ‹‹ንጉሡን ለመልቀቅ አንድ ጥያቄ አቅርበዋል። ማለት ስድስት ያህል የባስክ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱላቸው ጠይቀዋል። ‹ያዘ መደረጉን ካረጋገጥን› ይላሉ ኢ.ቲ.ኤዎች ‹ንጉሡን ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው እንለቃቸዋለን›።››

‹‹ምንም ግንዘብ አልጠየቁም ማለት ነው?›› ጠየቀች ቪክቶሪያ ከልክ ያለፈ ተደንቃ።

‹‹በመሠረቱ ጠለፋው የፖለቲካ ጠለፋ ነው›› አለ አርምስቱድ ባጭሩ። ‹‹ብንገራችን ላይ የኒክ ራምሲን ጉዳይ ስክታተለው ነበር። ከማድሪዱ የአሜሪካ አምባሳደር በስልክ እንደተነገረኝ ፖሊሶች ራምሲን ዒት እንደሚፈቱት ቃል ገብተዋል። ነገ ታገኝዋለሽ።››

‹‹ትልቅ ግልግል!›› ነበር መልሷ።

‹‹ልክ እንደተገናኛችሁ ደውሉልኝ። የሚተዋለተውን ስራችሁን አዘጋጅቼላችኋለሁ።››

* * *

የምትፈልገውን ያህል እረፍት አድርጋ ስለነበር ቪክቶሪያ በማግስቱ ዒት ሰውነቷን ተጣጥባ እንደጨረሰች ቀለል ያሉ ልብሶችን ለብሳ በቅንቃኑ ሆቴል የምግብ አዳራሽ ተቀምጣለች። የተረበሳትን ቡና ጨርሳ ኒውርክ ሪኮርድን በዚና ምንጭነት ጠቅሶ በንጉሡ አጠላለፍ ላይ ዝርዝር ዘገባ ያቀረበውን የኢንተርናሽናል ሄራልድ ትሪቡን ጋዜጣ በማንበብ ላይ ሳለች ስሟ ሲጠራ ሰማች።

ሎና ስትል ኒክ ራምሲ ሙሉ ለሙሉ ፈጥን እንዳለ ወደፊ ሲራመድ ተመለከተችው።

ግንባሯ ላይ ስሟት ተኮመጠጠ። ተጥሎም አስተናጋጅ ጠርቶ የአሳማ ስጋ፣ ከእንቁላል ጋር እና ጥቁር ቡና አዘዘ።

ቪክቶሪያ አተኩራ መመልከቷን አላቋረጠችም። ‹‹ኒክ፣ በሰላም ተመለስክ?›› ስትል ጠየቀችው።

ራምሲ ክንዶቹን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ እያጣጣመ ከመረመራቸው በኋላ፣ ‹‹ሁሉም ነገር በቦታው ነው። ፖሊሶች ዴላ አላሳሪፉብኝም፣ የተለመዱው የታሰሙበት ድግግሞሽ ብቻ›› አላት።

‹‹ወሀኒ አስገብተውሀ ነበር?››

‹‹ለዚህ እንኳ ሳልታደል ቀረሁ። ምንም አይን የሚያርፍበት ነገር ሳላይ አሳደሩኝ። በመጨረሻው በወሰዱኝ ሁኔታ በመታደር እንደታጀብኩ ከነበርኩበት ሆቴል መለሱኝ። ለጥረትሽ ሁሉ አመሰግናለሁ። ግን አንቺም በዜናሽ የአለምን ጆሮ ሳታርገበገቢ አትሁሪም።››

ታላት ከመደርደር ይልቅ ስታነበው የነበረውን ሄራልድ ትሪቡን ጋዜጣ ገፉ አደረገችለት። ወዲያው ደግሞ በጠለፋው ታሪክ ላይ የተጻፈውን አምድ አያሳየችው፣ ‹‹ተመልከት›› አለችው።

ፀጥ ብሎ ታሪኩን አነበበው።

‹‹ያንቺ ዘገባ አይደለም ማለት ነው?›› አለ አንብቦ እንደጨረሰ፣ ግራ ተጋብቶ። ‹‹ማነው ደግሞ ማርክ ብራድሾ?››

‹‹አንተ ራስህ የምታውተው መስሎኝ ነበር።››

‹‹ይሀን ስም በህይወቴ ሰምቼው አላውቅም።››

‹‹ኤድዋርድ በአውሮፓ የተከናነረው ሰው ነው አሉ፣ ከአሊ እንደሰማሁት።››

‹‹በጣም ይገርማል፣ ብራድሾ እንዴት ካንቺ ሊተርም ቻለ?›› በማለት ራሱን ሲነቀንቅ ቆየና፣ ‹‹ብቻ ያም ሆነ ይህ ኤድዋርድ ዜናውን የማሉ

ማድረጉም አንድ ነገር ነው። ጋዜጠኞቹን አንድ ነገር ይፈጸማል ብሎ በሚጠረጥርበት ስፍራ መላኩም ጉብዝናውን ያሳያል›› አላት።

የሆቴሉ የድምጽ ማጉያ የጥሪ ምልክት አሰማ። ወዲያው ደግሞ ወይዘሪት ቪክቶሪያ ዊስተን እንግዳ መቀበያ ክፍል ድረስ እንድትቀርብ በድምጽ ማጉያው ተጠየቀች።

ፊጠን ብላ ወደ እንግዳ መቀበያው ሄደች። ከኒውዮርክ የስልክ መስመር ክፍት ሆኖ እንደሚጠብቃት ተነገራት።

በእገር አቋራጭ ጥሪ የፊለጋት ሃሪ ዴትዝ ነበር።

‹‹ሄሎ ቪክቶሪያ›› አለ ሃሪ፡ ‹‹እናንተ ጋ ገና ጧት መሆን አለበት፡ መኝታ ክፍልሽ ደውየ አጣሁሽ።››

‹‹እዚህ ነኝ›› አለችው ቁርጥ አድርጋ።

‹‹ኒክ ራምሲ እንቺ ጋ መድረሱን እንዳረጋግጥ ጠይቆኝ ነበር።››

‹‹አውን ደርሷል በደህና ገብቷል።››

‹‹ጥሩ›› አለ ሃሪ ዴትዝ።

‹‹እዚህ ሃራልድ ትሪፀንን ሳንብ ነበር። የዜና ምንጭ አድርጎ ኒውዮርክ ሪከርድን ጠቅሷል።››

‹‹በጣም ግሩም፡ ለሚስተር ኤድዋርድ እንግረዋለሁ። በነገራችን ላይ በኢቲኤ ጠለፋ ላይ ሌላ ትኩስ ዜና በግላችን ማግኘታችንን ላብስርልሽ። በመያዣው ጥያቄ ላይ የስፓኝ መንግስት መስማማቱን አስታውቆ እስረኞቹን ፈቷል። በምላሹም ንጉሡ ተፈተዋል። ኢቲኤዎች በሂሊኮፕተር ንጉሣን ከሳን ሴባስቲያን ውጭ ባንድ ኮረብታ ላይ እጃቸውን የፍተኝ አስረው አይናቸውን በጨርቅ ሸፍነው ጣሏቸው። ሂሊኮፕተሯ ከአካባቢው ከተሰወረች በኋላ ፋኖዎቹ ለስፓኝ ባለስልጣኖች ስልክ ደውለው ንጉሣን የት እንደሚያገኙአቸው ነገሩአቸው። ባለስልጣኖቹም ንጉሱ ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው አግኝተዋቸዋል። ዜናውን ያገኘነው እኛ ብቻ ነን፡ የኒውዮርክ ጓዳኖቻች ዛሬም በሪከርድ ተጥለቅልቀዋል። ሪከርድን ለመግዛ

በየማዕዘኑ የሚታየው ሰልፍ ለኑድ ነው።››

‹‹እንኳን ደስ ያላችሁ›› አለች ቪክቶሪያ።

‹‹ሌላ ሚስተር ኤድዋርድ ላንቺና ለኢክ ንግሬቸው ያለኝ ነገር አለ። ሁለታችሁም ዛሬውኑ ጋሪስ ትሄዳላችሁ። እንደበፊቱ በፕላዛ ሆቴል ታርፋላችሁ። ነገ ሚስተር ኤድዋርድ በስልክ ይገናኛችሁና የምትሰሩትን ይነግራችኋል።››

‹‹የምንሰራው ምን ይሆን?›› ቪክቶሪያ በንዴት ጠየቀች።

‹‹ለሁሉም መጀመሪያ ጋሪስ ሂዱና ተጠባበቁ።››

ልክ ስልኩን ስትዘጋ ቪክቶሪያ ሃሪ ዴቭዝን አንድ ነገር ሳትጠይቀው በመቅረቷ ተቆጨች። ማነው ማርክ ብራድሾ? ለማንኛውም ጋሪስ እንደደረሰች ስለሰውየው ሊታወቅ እንደምትችል ገምታ ተጽናናች።

8

‹‹ኤድዋርድ›› አለ ዶክተር ሻርፍ፡ ‹‹የሚገርመኝ እስካሁን ብዙ ጉዳዮችን አንስተን ስንወያይ አንድ ጊዜ እንኳ አባትህን አለማንሳትህ ነው።››

ኤድዋርድ ሃኪሙን ለአፍታ አተኩሮ ሲመለከተው ከቆዬ በኋላ ‹‹አባቴማ ሞቷል›› አለ ከትከሻው ነቅነቅ እያለ። ‹‹ከእንግዲህ እሱ በኔ ሕያውት የሚገባበት አንድ ጉዳይ የለም።›› ንግግሩን ጥሏት ሲያጤን ቆየና ኤድዋርድ ቀጠለ። ‹‹በርግጥ ላንድ ነገር ሳላመሰግነው አላልፍም። ለወለደው ልጅ ትንሣት ክብር ባይሰጥም ለስልጣን ታላት አክብሮት አለው። የጨዋታው ስም ሁልጊዜም ድል መንሳት መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። እምነቱ ትክክል መሆኑን የተረዳሁለት አሁን ነው። እም፡ የጨዋታው ስም ድል መንሳት ነው። እሱ ነው አውነተኛው ርካታ።››

‹‹ግንኮ ለሁለቱም አርካታዎች ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል።›› አለ ሻርፍ ሰክን እንዳለ። ‹‹ሁለቱንም እንዳግባቡ ማስተናገድ የህይወት ግዴታ ነው።››

‹‹በኔ እምነት›› አለ ኤድዋርድ ሲመልስ፡ ‹‹የአልጋ ላይ ርካታ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ማንኛውም ሰው ሊያገኘው የሚችል ዝቅተኛው የእርካታ አይነት ነው። ትልቁ እርካታ ምንጊዜም ድል መንሳት ነው።››

‹‹መልካም።›› አለ ዶክተር ሻርፍ በመጨረሻው፡ ‹‹ራስህን ደስተኛ ለማድረግ ሰለተሳክልህ ደስ ብሎኛል።››

ኤድዋርድ ከመተመጫው ለመነሳት ካሽቆጠቆጠ በኋላ ተመልሶ ተቀመጠና ‹‹ይህ የበሰበሰ አረፍተ ነገር ነው።›› አለ፡ ‹‹ማንም ሰው ሪከርድ

ጋዜጣ ላይ እንደኔ ድል ሊነሳ አይችልም። በርግጥ በራሴ ስራ ራሴን ደስተኛ አድርጌአለሁ። አም፣ አድሉ ከተሰጠኝ ድል የምነሳበት ታላቅ ጥበብና ኃይል እንዳለኝ እምነት ነበረኝ። ጊዜው ሲደርስ እምነቴን እውን አደረግሁ። ስማ ካርል፣ የአጋጣሚ ነገር እንዳይመስልህ፣ የሙያ ብቃትና የተሰጥኦ ጉዳይ እንጂ።››

‹‹እውነት ነው፣ በሙያህ ላይስ እጠብህ የሚደርስ አለመኖሩን ስጠላትም ለወዳጅም አሳይተሃል።››

‹‹ግና የመጀመሪያው ነው ካርል፣ ግና መነሻው። ወደፊት ደግሞ እርምጃየ ይተጣል። የሚያግደኝ ነገር ስለሌለ መቆም አልሻም።››

‹‹ግን እንዴት? አንድ ነገር የሚከሰት መሆኑን እንዴት አስተድመህ ብትገምት ነው ሰዎችህን በዚያ ቦታ ላይ አዘጋጅተህ የምትገኘው?››

ኤድዋርድ አፍንጫውን ነፋ። ‹‹እድልና ተሰጥዎ›› አሰኖ ፊቱን ከስከስ አድርጎ፣ ‹‹የለም፣ ሊላም ነገር አለበት። ታላላት ሰዎች ያለቦታቸው የሚገኙበትን አጋጣሚ የመጠንበይ፣ ለጠላቶቻቸው ቀርበው የሚገኙበትን ወቅት ከነሱ የበለጠ የመገመት፣ ጠላቶቻቸው ምን እንደሚያስቡ የማወቅ፣ በሌላ አባባል እግዚአብሔርን የመሆን፣ ማለት ከደመናው በላይ ሆኖ ከፍጡራን ጎዳና ፊት ለፊት ምን ተደትኖ እንደሚጠብቃቸው የማሳየትና ከተደሞው እንቅፋት አጠገብ ተተምሎ የመገኘት ልዩ ችሎታ ተጠቀጅቻለሁ።››

‹‹ከምርህ ነው የምትናገረው?!›› አለ ይስሀቦር ሻርፍ የታካሚው አነጋገር አስገርሞት።

‹‹ምን?›› አለ በሽተኛው ቆጣ ብሎ።

‹‹እንደ እግዚአብሔር ከሰዎች ሁሉ የበላይ ነህ?››

ኤድዋርድ ከትከሻው ነትነት በማለት ለይስሀቦር የአምንታ ምልክት አሳየው። ንግግሩን ሲቀጥል ግን፣ ‹‹የለም፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ማለቴ እንኳ አይደለም። አባባሉ ቢገባህ ትንቢያን በተመለከተ የሚስተካከለኝ የለም ማለቴ ነበር። የሲጋኖ ንጉሥ ምን እንደሚጠብቀው አውቅ ነበር፣

የጠረጠርኩትም ተፈጸመ። ከሁሉ በፊት በሆታው በመጥቱም የዜናው ባለቤት ሆንኩ። ባድ ብዙ የሚለውን ታል በኋላ ለማስተመጥ ከሁሉም ተደምኩ። ይኸው ነው። አሁን የሰልጣኔ ቀጥተኛ ተጠቃሚ መሆን ሲያንሰኝ ነው።› ንግግሩን አቋረጠ ሰዓቱን ተመለከተ። «በል እንግዲህ ልሂድልህ።»

«ምን አስቸኮለህ?» አለ ዶክተር ሻርፍ የሚሄድበትን ሰዓት እየተመለከተ። «ጊዜ አለን። የምትሄድበት ጊዜ ሲደርስ እነግርሃለሁ።»

ኤድዋርድ ዶክተሩን አላሳመጠውም። ብድግ አለ። «በጣም ስራ ይበዛብኛል። ፓሪስ የማነጋግረው ስልክ አለ።» ንግግሩን ጉዮ ሲያትማማ ከቆየ በኋላ፣ «እንዲያውም የዛሬው አመሳጠኔ ለህክምና ሳይሆን ከንግዲህ በወትሮው ጥርግራም መሰረት በሳምንት ሶስት ቀን ልመጣ አለመቻሌን ልነግርህ ነበር። ሀይውቱ በስራ ተወጥራለች። ስለዚህ ከንግዲህ የምንገናኘው በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል።»

«ከመሰለህ...»

«ይመስለኛል።»

ዶክተር ሻርፍ ብድግ አለ። «በጣም ጥሩ፣ በሳምንት አንድ ጊዜ አድርገን እንሞክረዋለን። በዚህ ቀንና በዚህ ሰዓት በየሳምንቱ እንገናኝ።»

«በጣም ጥሩ» አለ ኤድዋርድ፣

ሻርፍ ኤድዋርድን ወደ በሩ እየሸኘው፣ «ለሁሉም ግን ሪኮርድን በጅህ ለማስገባት በርትተህ እንድትሰራ የረዳኸ ኑዛዜ የተጠለሀን አባትህን ልትዘነጋቸው አይገባም» አለ።

«ተዘንግቷል በለው» አለና ኤድዋርድ በሩን በሃይል በርግዶ ከፍቶ ወጥ በመኪናው ተፈተለከ።

* * *

ቢሮው እንደደረሰ ኤድዋርድ ኮቱን አውልቆ ካንጠለጠለ በኋላ ወደ ወንበሩ በማምራት ላይ እንዳለ በሩ ተከፍቶ የሃሪ ዴትዝ ሞንትሳት ታየ።

«መመለስህን ኢስቲል ነግረችኝ» አለ ዴትዝ።

«ከራምሲና ከሚስቱን ልጅ ጋር ተነጋግሬአለሁ። ፓሪስ ገብተዋል። ጥሪህን እየተጠባበቁ ናቸው።»

«መስመር አግኛኝ» ኤድዋርድ አዘዘ፣ «መጀመሪያ ራምሲን ላነጋግረው።»

«አሁኑኑ» እያለ ዴትዝ በሩን ዘጋው።

ኤድዋርድ ወንበሩ ላይ ተቀምጠ አይኖቹን ጠረጴዛው ላይ እንደተከለ ወጥቶ እስኪመለስ ድረስ የቆዩትን የስልክ መልእክቶች የጋዜጠኞችና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ የጋዜጣና መጽሔት አዘጋጆች በስጋኝ ንግግሥ ያልተጠበቀ ጠለፋና በተከተሉት ድርጊቶች ወቅት ኤድዋርድ ያሳየውን ተልሳፋ የወሬ አትርቦት አስመልክቶ ያስተላለፉት የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት ነበሩ። በመልእክቶቹ ለተሰማው ደስታ ፊታ ያለው ግንባሩ ይመሰክራል።

የኮምፒዩተር ስልኩ ድምጽ አንቋረረ። ወዲያው ደግሞ የሃሪ ዴትዝ ድምጽ ተሰማ። «ኒክ ራምሲ መስመር ላይ ነው ኤድዋርድ።»

«ጥሩ» ካለ በኋላ ኤድዋርድ የወደፊት እቅዱን አጠቃላይ ግዕታ የሚመራመር እየመሰለ ለአፍታ ተመስጠ ቆየ። ከዚያም ፈጣን እንዳለ መነጋገሪያውን አነሳ። «ሂለ፣ ኒክ።»

«ጨና ይስጥልኝ ሚስተር ኤድዋርድ፣ በሰላም ስላስፈቱኝ አመሰግናለሁ።»

«አደገኛ ቦታ ላይ ሰራተኞቻችንን ካስተመጥን ለደህንነታቸውም ኃላፊነት ይሰማናል» አለው ኤድዋርድ።

«በንጉሡ አጠላለፍ በመትደምም እንኳን ደስ ያለም።»

«ግና የመጀመሪያው ነው።» ኤድዋርድ ቃል ገባ።

«በሚተጥሉት ሁለት ሳምንታት ደግሞ ሁለት ነገሮች ይደረጋሉ። ለሁለቱም ከባድ ትኩረት ልሰጣቸው እፈልጋለሁ። እንደኛውን አንተ ትከታተልልኛለህ። ሊላውን ቪክቶሪያ። ለእሮር ጊዜ ላለያያችሁ ነው።»

‹‹ስራችን ምንድነው ሚስተር፣ ኤድዋርድ?››

‹‹አንተ ቁል አቪዝ ሄደህ በእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትርና በግበፅ ፕሬዝዳንት መካከል ካይሮ ላይ ስለሚደረገው ስብሰባ አላማ አስቀድመህ ታጠናልኛለህ።››

‹‹ስብሰባውኮ የዛሬ ሁለት ሳምንት ነው›› አለ ራምሲ።

‹‹መጀመሪያ እስራኤል እንድትሄድ ነው የምፈልገው። ምናልባት ወሳኝ ስብሰባ ይካሄድ ይሆናል። ምናልባትም አንድ ሽብር ተወጥኖ ይሆናል።››

ራምሲ የተቃውሞ ንግግር ያሰማ ይሆናል ብሎ ሲያዳምጥ ቆየ። ራምሲ ግን ‹‹ይሆናል›› ከማለት ሌላ አልተናገረም።

ኤድዋርድ ለራሱ ረጋግ አለ። ራምሲ ተገርቷል።

‹‹እንግዲህ የሚኮኮሰብን ሁለት ሳምንታት በሁለቱ ከተሞች ስታንዛብብ ታላልፋለህ።›› አለው ኤድዋርድ፣ ‹‹የኛ ቢሮ ብዙ ጊዜ ዋናው ዜና ላይ ያተኩራል። ጥቂት የመንደርደሪያ ሃተታ ያስፈልግናል። ለሁለቱ የሳምንት መጨረሻ አርዕስተ-ጉዳዮች እንደመግቢያ የሚያገለግል ዕውቅ ካንተ እንጠብቃለን። ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለራሱ፣ በካቢኔ አሱን ስለሚቃወሙ ሰዎች፣ በእስራኤል ስለሚሰማው የህዝብ አስተያየትና በመረጃ አሸንጸነት ይቀርባሉ ስለሚባሉ የመወያያ ርዕሶች ልትፅፍ ትችላለህ። ተማባብተናል?››

‹‹ተማባብተናል›› አለ ራምሲ።

‹‹መልካም. . .እንግዲህ ልክ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከቴልአቪቭ ሲነሳ አንተም አብረኸው ካይሮ ትሄዳለህ። በጥሬስ አውሮፕላን ቦታ አስይዘልሃለሁ። ካይሮ ስብሰባውን በሚመለከት ልታገኝ የምትችለውን መረጃ ሁሉ ታጠቀብለናለህ። ከሁለቱ የመካከለኛ ምስራቅ ስብሰባዎች በኋላ የት እንደምመድብህ ወደፊት እወሰናለሁ። ቪክቶሪያን አትርሳልኝ።››

ኤድዋርድ ቪክቶሪያ አስከትላርብለት ከሱቱ ኪስ ሲጋራ አውጥቶ ለማቀጣጠል ጊዜ አገኘ። ቪክቶሪያ ምንነቱን በውል ሊሰማ ያልቻለው ነገር ለራምሲ ስትናገር ይሰማታል። ወዲያው ቀረበች።

‹‹አዘት፣ ሚስተር ኤድዋርድ?››

‹‹ስሚ ቪክቶሪያ፣ አንድ አሰቸኳይ ስራ ይጠብቅሻል። ማለቱ ለሚመጡት ሁለት ሳምንታት ብቻሽን ልትሰነብት ነው። ራምሲን ወደ እስራኤል መላኬ ነው፣ አንቺን ደግሞ ነገ ስዊዘርላንድ እንዳገኝሽ እፈልጋለሁ። ስዊዘርላንድ ሰልሽ፣ ጂኦቭ።››

‹‹በጣም ጥሩ›› አለች ቪክቶሪያ ተበል አድርጋ።

‹‹ክራምስ, መለያየትሽን ትር አላስገኘሽም ማለት ነው?››

‹‹በብዙ ነገር ረዳቱ ነበር። ግን ቢሆንም በግሌ የተሳከሁበትን ስራ ለማከናወን ራሴን የምፈትንበት አጋጣሚ ስላገኘሁ ደስ ይለኛል።››

‹‹ጥሩ ይገባውልሽ። በሚቀጥለው ሳምንት መግቢያ ጂኦቭ ላይ ኑክሊየር አምራች ያልሆኑ አገሮች ስብሰባ እንደሚያካሂዱ ሰታውቂ አትቀሪም።››

‹‹አውታለሁ።››

‹‹የስብሰባውን ዝርዝርና ያንቺን ስራ በተለይ የሚመለከት ሰነድ ረቫጅ ሆቴል ይጠብቅሻል። ስብሰባው ከአራት ቀናት በኋላ በጂኔቭ የተባበሩት መንግስታት ቢሮ ይጀምራል። ከስብሰባው አንድ ቀን ቀደም ብሎ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ጂኦቭ ይገባሉ። በሚቀጥሉት አምስት ወይም አስር አመታት ውስጥ ኑክሊየር ጠር መሳሪያ ማምረት ይጀምራሉ የሚባሉት ሃያ አምስት አገሮች መልእክተኞችም በዚሁ ቀን ጂኦቭ ይገባሉ። የስብሰባውን እጀንዳና አንዳንድ መረጃዎችን የያዘ ሰነድ እንደነገርኩሽ በተያዘልሽ ሆቴል ውስጥ አዘጋጅተንልሻል።››

‹‹በጣም አመሰግናለሁ›› አለች ቪክቶሪያ።

‹‹በተረፈ አሰፈላጊውን ነገር ሁሉ ዙሪክ የሚገኘው ቢሮአችንን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጉቦቱክል ክፍል ያቀርብልሻል። አሁን እኛ ለሪከርድ የምንፈልገው ሁለት የመንደርደሪያ ዕሁፎችን ነው። አንደኛው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጂኦቭ መስሪያ ቤትና በተለይ መልእክተኞች የሚተመጡበት ሀንባ ምን ይመስላል? ስብሰባው የሚካሄድበት ቦታስ? የሚል ይሆናል። ቀጥሎ ደግሞ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል ዙሪያ

ዘርዝር ንብኝት አድርገሽ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሐፊና ረዳቶቹ የሚያርፉበትን የየግላቸውን ክፍል የሚመለክት ዝርዝር ጥያቄ ዕሁፍ ታዘጋጅና ከነገ በስቲያ በስልክ ለኔ ወይም ለሃሪ ዴትዝ፡ ለምታግኚው ሰው እንደተሰመደው ከግስታወሻ ደብተርሽ ታስገለብጫለሽ።››

‹‹ዝርዝር መግለጫ?›› ቪክቶሪያ ጠየቀች።

‹‹ዝርዝር መግለጫ። ታዲያ ልድገምልሽና መግለጫሽን የምንጠብቀው ከነገ ወዲያ ነው። በእኛ የጊዜ አቆጣጠር አመሻሽ ላይ ሊሆን ይችላል የምትደውይልን። እንግዲህ አንቺ መረጃውን በሰጠሽን ማግስት ዋና ጸሐፊው ጀኔቭ ይገባል ማለት ነው። የዋና ጸሐፊውን መግባት የሚመለከተው ዕሁፍ ያንቺ ድርሻ አይደለም። ሌሎች ሰራተኞች ከኔ በፊ አመድባለሁ።››

‹‹ላገኛቸው እችላለሁ?››

‹‹የለም፣ የለም። አንቺ የምትሰሪው በግልሽ መሆን አለበት። ያልኩሽ ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ በጀኔቭ ያቆየሁዋቸው ናቸው። በዚያ ላይ እነሱ የሚያውቁት ነገር ባንቺ ስሚት ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር አልፈልግም። ያንቺ ዕሁፍ በራስሽ አይን ምስክርነት ላይ የተመሰረተ ወጥና አዲስ መሆን ይኖርበታል። እንግዲህ በሁለቱ ተናት ስራሽን ጨርሰሽ ሶስተኛውን ቀን እንደ ሌሎች ቱሪስቶች ወይም የስብሰባው መልእክተኞች ከተማዋን በመጎብኘት እንድታሳልፊው ይሁን። በአራተኛው ቀን ግን በስብሰባው አጻራሽ ለጋዜጠኞች በተዘጋጀው ስፍራ ተገኝተሽ ስብሰባውን ትከታተያለሽ፣ የሚፃፍ ነገር ካገኘሽም ታዘጋጅልኛለሽ። ከተናገርኩት ያልገባሽ ነገር ካለ ሆቴልሽ ከሚገኘው ሰነድ ተረጅ። መልካም ዕድል።››

* * *

ኒክ ራምሲና ቪክቶሪያ ዌስተን ሁለቱም ያን ምሽት ያለወትሮአቸው ጋሬት እንደሆኑ አምሽተው ነበር የተሰነባበቱት። ቪክቶሪያን ያስከፋት ድንገት መለያየታቸው ሲሆን ራምሲ ደግሞ ወደመከለኛው ምስራት መሄዱ ሳይሆን እንደማይተር ገመተች።

አመሻሽ ላይ ሁለቱም በቪክቶሪያ የመኝታ ክፍል በረንዳ ላይ ቆመው

ሳለ ቪክቶሪያ አንድ ውስጣዊ ስሜት ድንገት ነዘራት። ራምሲን ከፍሷ ውስጥ፣ አልጋዋ ውስጥ፣ ሰውነቷ ውስጥ እንዲገባ ልትጋብዘው ፈለገች። ወሲብን በተመለከተ ራምሲ ብዙም ትኩረት እንደሌለው የምታውቅለት ቢሆንም ከሷ በብዙ መንገድ የተለየ ሰው መሆኑ የገባት ግን ዛና ዛሬ ነበር። አብረው በቆዩባቸው ብዙ ሳምንታት ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እየሳባት፣ ሰልካካ መልኩ እየማረካት፣ ወንዳወንድ ሁኔታው ልቧን እየሰረቃት፣ ከፈቱ የማይለየው ፊግታው ወለዘ እያደረጋት መጥቷል። የሷ ልታደርገው፣ በጅግ ልታስገባው ትፈልጋለች፣ እፍ አውጥቶ ማነጋገርና መጠየቁን ለመድፈር ግን አልቻለችም። ጥያቄው ከሱ ይነሳል የሚል የማይሞት ተስፋ ነበራት። አንድ ቀን ወደ መኝታው ይወሰደኛል፣ ወደአልጋው ይገፈትረኛል፣ ወይም ቢሆንስ በከንፈሮቹ ጉንጨን ይዳስሳል ብላ በጉጉት መጠበቅ ከጀመረች ውላ አድራለች። አጅሬ ግን ፓሪስም ሆነ ሳን ሴባስቲያን በመጨረሻም በትንሿ የፊረንሳይ የጠረፍ ከተማ በቻንታኮ ሦቱል ለዚህ አይነቱ ነገር ፈት የማይሰጥ መሆኑን አሳይቷታል። ሲሳሳሙ አምሽተው የመኝታ ጊዜ ሲደርስ ግንባሯን ላም፣ ትከሻዋን ችብ አድርጎ ወደ መኝታዋ ያሰናብታታል። በመጨረሻዋ የስንብት ምሽት ብቻ ‹‹በትርቡ እንገናኛለን›› አላት ወደክፍሷ ሲሸኛት።

አልጋዋ ላይ ወጥታ ልብሷን ስታወላልት የራምሲ ሁኔታ ድቅን አለባት። ለምን ችላ ይላታል? በበኩሷ አንድ ጊዜ ከተረባት በኋላ ያልተመ ኛት ወንድ የለም። ይህ ሰው የመጀመሪያው ነው። እሷ ደግሞ ተልዚን አሳድራበታለች። ፈልጋዋለች። እንዲህ ሲያደርጋት፣ ለወንድ ልሷ ሲረታም የመጀመሪያዋ ነው። እናም ለምን ችላ እንደሚላት ምክንያቱን እስካልደረ ሰችበት ድረስ እረፍት እንደማይኖራት አንዳች ውስጣዊ ስሜት ነገራት።

ስለራምሲ የሚጉላላባት ሃሳብ ገለል ማለት የጀመረው እንትልፍ አእምሮዋን እያዳከመው መጣል ስትጀምር ነበር።

* * *

ረፋዱ ላይ ጀኔቭ ደረሰች። ከአውሮፕላን እንደወረደች ታክሲ ይዛ ወደ ሪቫጅ ሦቱል ስታመራ እንኳ የራምሲ ነገር እንደገና ድቅን አለባት። ደግሞ መሳል ከጦማ መግባት ስትጀምር ጀብዱ ልትፈጽምበት የምትችለው አዲስ

የጂኤቮ ስራዋ እየታወሳት በመምጣቱ ያን አመሻሽ ትረሳው ጀመር።

ሦቱል እንደገባች ወደ ሳም ከመሄዷ በፊት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጂኔቭ ቢሮ የነበራትን ሽሙን ፀሐፊ በስልክ ተጣናታ ስብሰባውን የሚመለከት ጥያቄ ማቅረብ ትችል እንደሁ ጠየቀች። ከሰዓት በኋላ በሰምንት ሰዓት በድርጅቱ ጽ/ቤት ብትኖኝ ለለሎች አለምአቀፍ ጋዜጠኞች የሚሰጠውን መግለጫ መከታተል እንደምትችል ተነገራት።

እስከ ስምንት ሰዓት ያለውን ጊዜ ምሳ ከበላች በኋላ ገላዋን ታጥባ ለለች ዝግጅትን ስታደርግ አሳለፈች። በመጨረሻም ወደ ጽ/ቤቱ ለመሄድ ቲሸጣዋን አወላልቃ ልብሷን ለመልበስ ራቁቷን እንደቆመች በክፍሉ ሳጥኑ መስታወት ውስጥ የሚመረገረገው የራሷ ሰውነት ታያት። ተረበሸች፡ ተረበሸች። ረጅሙን ፀጉሯን፡ ሰሰ ከንፈሮቿን፡ አጥንታቸው ወጣ ወጣ ያሉ ሰፋፊ ትከሻዎቿን፡ የተወላወሉ ጡቶቿን፡ የተሰለበውን ባህር ሆዷን፡ ግራ ቀኝ የተገለጠውን ዳሌዎን፡ በሲጋ የተሞሉ ጭኖቿን፡ ያማረውን እግሯን፡ የሰፊ አካላቷን በጥንቃቄ ተመለከተችው።

ኒክ ራምሲ ችላ ያላት ሕዋን አድርጎ በመገመት እንዲልቀን አረጋገጠች።

እንዴት ያለ ገላ እንደተረበት እንዳላገናዘበ ገባት።

ሃሳቧን እንደገና ወደ አለታዊ ሰራዋ መለሰ አድርጋ ታሰላስል ጀመር። በዚህች የተዋበች ከተማ ኑክሊየር ጠር መላሪያ ለማምረት አትም ያላቸው ብዙ አገሮች ተሰብሰበው ቴክኖሎጂያቸውን ለልማት ሰራ ብቻ ለማዋል ቃል እንዲገቡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ማዕከልነት ያወያያሉ። አም፡ ደህ ራሱ ዜና ነው፡ ግን ብዙ ስው ተሰብብግበ የሚሰማው ጆሮ ኮርኒራ ዜና እንደማይሆን ግልፅ ነው። ቨ.ክቶሪያ የምትመኘው የኒውዮርክና የመላው አለም ህዝብ ትንግርት ብሎ የሚያጸምጠው አዲስ አስደናቂ ዜና ማግኘት ነው። ግን ስዊዘርላንድን በመሰለች ገለልተኛ ሀገር ምን አዲስ ነገር ይፈጸማል?

* * *

የተከራየችውን ጅንር መኪና ከመንገዱ ዳር አቁማ በድርጅቱ መማሪያ በር በቂኬት መቁረሚው መስኮት ስትደርስ የይለፍ ካርዷን አሳየች። ከውስጥ ብዛት ያላቸው አገር ጎብኝዎች ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ሲገቡ ከጀርባቸው ደረሰችባቸው።

በእንግዳ መቀበያው ክፍል ብዙ ጋዜጠኞች ተሰምጠዋል። ስለስብሰባው በተለያዩ ጠቅላላ ጉዳዮች ላይ አንዲት ፈረንሳዊት ሴት ገለፃ አደረገች። ገለፃው እንዳበቃ የሀንግሙን የተለያዩ ክፍሎች በተለይም የተለያዩ አለም አቀፍ ስብሰባዎችን የሚያስተናግዱ በሶሩ የተሞሉ አዳራሾችንና በተለይም መጀመ ስብሰባ የሚካሄድበት ሰፊ አዳራሽ፡ በዚህም አዳራሽ ተርንሚዎች፡ ጋዜጠኞች መልእክተኞችና ስብሰባውን የሚመሩት የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ፊሳቸው የሚቀመጡበትን ሰፍራ አንድ ባንድ ጎበኙ። ጉብኝቱ ሲፈፀም ፈረንሳዊቷ ትብንምቱ ያልገባቸው ነገር ካለ ሊጠይቁ የሚችሉ መሆናቸውን አስታወቀች። ቨክቶሪያ ግና ከጅምሩ የተገላላባትን ጥያቄ አንሳች። ጥያቄዎቹም ተነሰተው እንደነገሩ መልሳቸውን አገኙ። ያየችውንና የሰማችውን ሁሉ በማስታወሻዋ አሰፍራ ነበር ቨክቶሪያ ወደ መኪናዋ የተመለሰችው።

ወደ ሆቴሏ በመመለስ ላይ እንጨለች አንድ የተምታታ ነገር አእምሮዋን ወሰጨጨው። የተሰማት ሰራ ስሜት የማይሰዋ ነው። እም ኤድዋርድ ሃሰበ ጠፋብ ሸው ነው።

በፍጹም ስሜት የማይሰዋ ውሰን ሰራ ነው።

በመጨረሻ ወደ መኝታ ክፍሏ ስታመራ ግን የተሰማት ሰራ ትዕዛዝ በመሆኑ ያየችውን ሁሉ ኒውዮርክ ደውላ መንገር እንዳለባት ተረዳች። የነገው ሰራዋ የተሻለ እንድሚሆን ተሰፋ አደረገች።

* * *

የማማቱ ስራዋ ግን እንደጠበቀችው ሊሻል ይትርና የባሰ ሆኖ አገኘችው።

ቫክቶሪያ በማንኛውም ግዑዝ ነገር በማንኛውም ስውር ነገር ላይ ቢሆን

አንድ ተንባቢ ዕሁፍ ማቅረብ የሚችል የተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ እንዳላት ራሷ በኩራት የምትመሰክር ጋዜጠኛ ናት። ይህችው፣ ሁለተኛው የኤድዋርድ ትዕዛዝ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ስብሰባ አስመልክቶ በጀኔቫ አንተርከንቲኔንታል ሆቴል ዕሑፍ የማቅረብና የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ ዘሆቴሉ በሚቆዩበት ወቅት ስለሚደረግላቸው መስተንግዶ ሃተታ የማዘጋጀት ሃላፊ ግን ፍፁም የማይንቀሳቀስ ሆኖ ታዮት። ብዕሯ በማስታወሻዋ ላይ እንደ ወትሮው ሊንደረደርበት ስላልቻለ አንድ ቦታ ተተክሎ ለራሷ ጥያቄ አቀረበላት።

እንደምንም ከማዘሙ ጀመረች። የበሩ ዘብ የትና እንዴት እንደቆመ አለባበሱን ሳይተር አንድ ባንድ ዓረች። ሰፈሙን የሞቴሉን በረንዳ የእንፃ መቀበያውንና ግባ ብሎ የሚገኘውን አሳንሰር በማስታወሻዋ አሰፈረች።

ራሷ አሳንሰሩ ውስጥ እንደገባች በተጥታ ዋና ፀሐፊው ወደሚያርፉበት ክፍል አመራች። ሰፈና የተዋበ የመኝታ ክፍል ነበር። በስተግራ በኩል ቡድን የተከፈለ ትላልቅ ሶፋዎችና አራት ሊሎች መንበሮች ይታያሉ። በስተቀኝ ትልቅ ጊያኖ በለሎች መንበሮች የተከበበ ጠረጴዛና ሌላ አትክልት የያዘ ሳህን የተቀመጠበት አነስተኛ ጠረጴላ አለ።

ክፍሉን አጥንታ እንደጨረሰች በገባችበት በመውጣት ላይ ሳለች ለመጨረሻ ጊዜ ዞር ብላ ተመለከተች። በአይነ-ህሊናዋ በክፍሉ ሀያሉት ዘራችበት። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊን በሃሳቧ ክፍሉ ውስጥ አስቀምጣ ሳለቻቸው። ዋና ፀሐፊው ከተለያዩ አገሮች መልእክተኞች ጋር የግል ውይይት ሲያደርጉ ታዩዋት።

ሃሳቧ ግን እውን አልሆነም። የተንጣለለው የመኝታ ክፍል ሳሎን እና እንደሆነ ከሃሳቧ ስትመለስ ተረዳች።

ግና ዒት በመሆኑ ለኤድዋርድ ስልክ ለመደወል ጊዜው ግና ነው። የሰስትና የአራት ሰዓት ነፃ ጊዜ አላት። በዚህ ጊዜ ለነገ ያተደችውን ከተማሞን የመጎብኘት ተግባር ዛሬ ልታደርገው አሰበችና ተመችው። ፍላጎቷ ከኩማ ለጠቃሚነትና ወደ ገጠሩ ጎራ ለማለት ነበር። መኪናዋ ውስጥ እንዳለች ከነኗ ባለው መቀመጫ የሚገኘውን የስዊዘርላንድ ካርታ ታጥፎ

ተቀምጦ አየችው። ግላሲያ ስትመለከተው N1 በሚል ምልክት በተሰመረው ከጀኔቭ ወደ ላውላን ከተማ በሚወስደው አውራ ጎዳና ላይ አደጋ አረፈ። ያንድን አስነሲዮ N1 የሚለውን ምልክት ለማግኘት ከሞቱሉ ወጣች።

እንደጠበቀችው ጉሞ ዶሰ የሚል የገጠር ህብረተሰም ያለው ሆኖ አገኘችው። በዝግታ እየነዳች ንፁህ የገጠር አየር እየሳበች ለግማሽ ሰዓት ያህል እንደተጓዘች በሃያ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ኒዮን ከተሰኘችው ጥንታዊ ከተማ ደረሰች። ያህችን ታሪካዊት ከተማ በዚህ አጋጣሚ ተዘዋውራ ለመጎብኘት ወሰነች።

ሁለት ጎዳናዎች ከሚገናኙበት መስቀለኛ መስመር አጠገብ መኪናዋን ለማቆም ስፍራ በማግኘቷ ላይ ሳለች ድንገት አይኗ አንድ ነገር ላይ ተተክሎ ቀረ።

ሞቱል ሳይሆን አይቀርም፣ ባንድ ረጅም ሀንግ በር አካባቢ ደርሶ መሰሰ የሚል ሰው ተመለከተች። ሀንግው ሞቱል መሆኑን ወዲያውኑ አረጋገጠች። አልጎስ ሞቱል የሚል ፅሁፍ ይነበባል። ሰውየው ላይ አይኗ ተተክሎ የቀረው ግንቱን የምታውቀው መሆኑን በማመኗ ነበር። ለመሆኑ ሰውየውን የት ነው የምታውቀው? በዚህች ትንሽ የስዊዝ ከተማስ ምን ያደርጋል? ጥያቄዋ በአእምሮዋ ተጉላላ።

በሞቱሉ በር ሁለት ሶስት ጊዜ ሲንጎራደድ ቆይቶ ወደ ውስጥ ገባ። የምታውቅበትን ስፍራ ልታስታውስ ሞከረች። ቁመናው ዘለግ ያለ ለግላጋ ወጣት የሚመስልና ከፈቃ ጠበብ ያለ ባርኔጣ ጥቁር ጠጉር ባበቀለ አናቱ ላይ የደፋ፣ አፍንጫው የማንቆርቆሪያ ሻንጣ የመሰለ፣ ከንፈሩ ጸጉስ ያለ ባጠቃላይ በሰኒማ ከተመለከተቻቸው ብዙ ማጅራት መቺዎች እንዱን የመሰለ ፍጥንግል፣ ማነው እሱ?

እም፣ መጀመሪያ ባየችው ጊዜም ይህን ሰው ከከተማ ወንበዴዎች እንደ አንዱ አድርጋ መገመቷ ትዝ አላት። ወዲያው ደግሞ ይህ ሰው እንዴት እንደተዋወቃት ታወሳት።

ጉስ ፖጋኖ!

ልክ ነው፣ ጉስ ፖጋኖ። ባንድ ወቅት ቤት ሰርሳሪ ሊባ ተጥሎ የቸጦር

ነፍሰ ገዳዮች ጅሮ ጠፊ የነበረው፣ በኋላ በኢሙዮርክ ሪከርድ የመጀመሪያ ስራዋ ታሳሚነት ያደረገችለት ጉስ ፓጋኖ።

ጉስ ፓጋኖ ከሊሎች አሚሪካውያን ሁሉ በዚህች የስዊዘርላንድ አነስተኛ ከተማ በኢዮን ምን ያደርጋል?

መኪናዋን አቁማ ልታገኘው ፈለገች። ባዶ ጉጉት እንጅ የምታጣራው ጉዳይ ኖሯት አልነበረም። የሚያውቁትን ሰው በሰው አገር ሲያገኙ የሰላምታ ልውውጥ እንኳ ታላቅ ተስፋ ነው። ቪክቶሪያ ግን ፓጋኖን ሻይ ወይም ምሳ ለመጋበዝ የሚያስችል ትውውቅ ስላላት በፈገግታ ሰላምታ ልታቀርብለት ትችላለች።

ከመኪናዋ የወረደችው በዝላይ ነበር። አልጎስ ሆቴል ውስጥ ዘው ብላ ገባች። የእንግዳ መቀበያና ሶስት የበረንዳ መንበሮች ከመኖራችው በስተቀር ሆቴሉ የሚያደናግር የቁሳቁስና የመስታወት ሽብርት ያጣበቀው ድርጅት አልነበረም። ይላስ ብሎ በውስጡ የሚስተናገድ አንድም ሰው አለመኖሩ ቪክቶሪያን አስገረማት። ጉስ ፓጋኖም ሆነ ማንም ሰው የለም። ፈጠን ብላ ወደ እንግዳ መቀበያው መንበር አመራች። ግን እሱም ባዶ ነው። በሃሳብ መደጣጠሪያው አጠገብ አንድ ደወል አየች፣ እርዳታ ለመጥራት የተተከለ ደወል መሆኑን ገምታ ደወለች።

በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ ኢጣሊያዊ ዓይነ የሚንዘባበት አስተናጋጅ ከምግብ አዳራሽ አትጣጫ ብቅ ብሎ ቪክቶሪያን ተመለከተና፣ አሜሪካዊ መሆኗን በመገንዘብ ሳይሆን አይተርም በጠራ እንግሊዝኛ «ይቅርታ» አላት። «በምግብ አዳራሽና በእንግዳ መቀበያ ክፍል ደርቤ ነው የምሰራው። ሊመጠጡ ይፈልጋሉ?»

«የለም» አለች ቪክቶሪያ። «ጓደኛየ የሆነ አንድ እንግዳ እዚህ አርፋለች። ላነጋግረው አፈልጋለሁ። የመኝታ ክፍሉን ቁጥር ልትነግሪኝ ትችላለህ?»

አስተናጋጅ ከእንግዳ መቀበያው መንበር ወደፊት ተራምዶ የእንግዳ መመዝገቢያውን ቅጽ እያሰሰ «ስማቸውን ማን ልበል?» አላት።

«ሚስተር ፖንቲ። ጉሰ ፖንቲ ይባላል። ከኒውዮርክ ነው የመጣው።»

አስተናጋጁ በብስሩ ከላይ ወደታች እየወረደ ኢያንዳንዱን ቱፐር አይቶ ከጨረሰ በኋላ ስሙን ሊያገኝ ባለመቻሉ ገጽኑን ማዛባቡ ያዘ። በመጨረሻም «ስሙን በፈደል ሊነግሩኝ ይችላሉ?» ሲል ቨክቶሪያን ጠየቃት።

«ፖ-ንቲ፡ ፖንቲ።»

አስተናጋጁ እንደገና ገፅ በገፅ፡ መስመር በመስመር ስሙን ቢፈልግ ሊያገኘው ስላልቻለ ራሱን እየነቀነቀ «አዝናለሁ፡ ፖንቲ የተባለ ስም የለም» አላት።

«እስኪ መዝገቡን እኔ ልየው» ጠየቀች ቨክቶሪያ። አስተናጋጁ መዝገቡን አስጠጋላት። በጥንቃቄ መረመረች። ፖንቲ የሚል ስም አልተጻፈም። ግራ ገብቷት «ደቂቃ እንኳ አይሞላም፡ እዚህ ሲገባ አይቸዋለሁ» አለች።

«አልተመዘገቡም ማለት ነው።» መለሰ አስተናጋጅ።

«ምናልባት ምግብ ቤት ገብቶ እንደሁ?»

«የለም፡ ምግብ ቤት ለማግኘ ሰዓት ያህል የመጣ ሰው የለም። እንደሚመስለኝ ምናልባት ሰውየው አልጋ የያዘ ሌላ ሰው ሊጠይቁ መጥተው ይሆናል። እንዲያ ከሆነ ደግሞ የግድ ስማቸውን እንመዘግባለን።»

ይህ ሬጽሞ ያልጠረጠረችው አማራጭ ነበር። ከአማራጭ በላይ ሊሆን የሚችል ትክክለኛ ግምት መሆኑን ወዲያውኑ አመነች። አስተናጋጁን አመስግና ከሆቴሉ ወጣች።

ወደመኪናዋ ስትመራ ሰዓቷን ስትመለከት ካሰበችው የበለጠ ጊዜ ማባከኗን ስለተረዳች ወደ ጀኔቭ ለመግስገስ ትጣደፍ ጀመር። ያስቸኳት የምትሰራው ስራ በመኖሩ አልነበረም። ለኤድዋርድ ስልክ ከመደወሏ በፊት ያዘጋጀችውን ዕቅድ እንደገና መገምገም ነበረባት።

* * *

ከሰዓት በኋላ ቨክቶሪያ ከኒውዮርክ ሪከርድ አሳሚ ፀሐፊ ከኢስቲል

ራቭኪን ጋር በስልክ ተገናኝታ አለቃዋን ለማነጋገር መጠባበቅ ጀመረች።

ከማስታወሻዋ ግንባሳ የያዘችው የኢንተርኮንቲኔንታል ሞቱልን ሀገሳ ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታ የሚያትቱ ገጾቿ ሙኗ ላይ ተኮምጠዋል። ለአራት ጊዜ እየገመገመቻቸው ነበር።

"ኤድዋርድ ነኝ። እንዴት ነሽ ቨክቶሪያ?"

"አቤት ሚስተር ኤድዋርድ፣ በኢንተርኮንቲኔንታል ሞቱል ላይ ሃተታ አዘጋጅቼ እንድልውልዎ እዝዘውኝ ነበር።"

"በትክክለኛው ሰዓት ነው የደወልሽው። ለመሆኑ ዋና ዐሐፊው የሚያርፈው በርግጥ በዚያ ሞቱል መሆኑን አረጋግጠሻል?"

"ነገ በሞቱሉ ይገኛሉ" ካለች በኋላ ጥቂት አትማማችና ምራቋን ውጣ፣ "ሚስተር ኤድዋርድ መቼም የተጎለኙን ሁሉ ነው ያደረግሁት። ያውም ከረጻት ሰራ አስኪያጁ ጀምሮ ሁሉም የሞቱሉ ሰራተኛ በጣም ነው የተባበሩኝ" አለች።

"ልክ ነሽ። ሰራተኞች ተባባሪዎች ናቸው። በሱ ሞቱል ብዙ ጊዜ አርፈበታለሁ።"

"ግን እነሱ ምንም ያህል ቢተባበሩኝ ምንም ያህል የውስጡንና የውጪውን እንደፈለግሁ ቢያስጎበኙኝ ሃተታ የምፅፍበት ምንም ነገር አላገኘሁም።"

"ስለሁተታሽ ጠቅሚነት አስተያየቱን ለኔ ተይልኝ።"

"እሱስ ልክ ነው። . . ግን ለመጀመር ያህል ባለአምስት ሚዕዘን ሞቱል ነው። ምንም የተለየ ነገር አላየሁበትም።"

"የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ዐሐፊን ያህል ትልቅ ሰው ሲያርፍበትም ልዩ ዝግጅት አልተደረገበትም?"

"እኔ የማየው ምንም ዝግጅት አልተደረገበትም።"

"መልካም በይ ቶጥይ። ያየሽውንና የሰማሽውን በሙሉ አስገልብጭ።"

«ሁሉንም ቃል ሊሰጡ ይፈልጋሉ?››

«የለም፣ አትጨነቂ። ኢስቲል መስመር ላይ ናት። እኔ ለመስማት ብቻ ስልኩን ከፍት አተወዋለሁ። ቸጥ ይ።››

ለእስር ደቂቃዎች ያህል የማስታወሻዋን ፅሁፍ ለኢስቲል አስገልብጣ እንደጨረሰች የአለቃዋን ድምጽ ሰማችው።

«ይቅርታ እንግዲህ›› አለች ቢቸግራት። «ይህን ያህል የሚሰብ ፅሁፍ አይደለም። ያበሳሸው ርዕሱ ነው።››

«የለም የለም›› አለ ኤድዋርድ ተበሳል አድርጎ። «ይህንኑ ብቻ ነው የምንጠብቀው። እሮጮር ጥናታዊ ፅሁፍ ይወጣዋል። *ሶዋና በሐፈው የጀኔቭ ቆይታ በስብሰባው ዋዜማ* በሚል ርዕስ እናትመዋለን። በጣም ጥሩ ፅሬሻል ቪኪ . በይ እንግዲህ ግዳጅሽን በብቃት ስለተወጣሽ ነገን አረፍት አድርገሽ ከነገ ወዲያ በስብሰባው አዳራሽ ተገኚ።››

«ኦ! አንድ ተሳል ነገር ሳልነግርም ሚስተር ኤድዋርድ›› ስትል ድንገት አለቃዋን አቋረጠችው። «ለርስም ከመደወሉ በፊት ጥቂት ትርፍ ጊዜ ስለነበረኝ ከጀኔቫ ወጣ ብዬ ነበር። አንድ ሰው ያየሁ መሰለኝ፣ ግለቱ ከባልደረቦቻችን አንዱን. . .››

«ከምናቻችን አንዱን? ከሰራተኞቻችን?››

«ጉስ ፓጋኖን›› አለችው ባጭሩ።

«ማንንም?››

«ጉስ ፓጋኖን። ኢያስታውሱም በድርጅትም እንደተተጠረኩ መጀመሪያ ቃለመጠይቅ ያቀረብኩለት ሰው? በይንገር አስር ቤት ታስሮ የነበረው የመሰሪያ ቢታችን ቃል አቀባይ? ስሙን ረስተውት ይሆናል። ፓጋኖ ይባላል።››

«ኦ አስታወስኩት። ምን ሆነ ታዲያ?››

«ከሰዓት በፊት ወደ ገጠር ወጣ ብየ ነበር። ኒዮን በተባለች ትንሽ ከተማ ስደርስ ፓጋኖ አንድ ሆቴል ሲገባ አየሁት። ሰላም ልለው ገባ ብዬ

ስጠይት አልተመዘገበም። ሰውዬው ፖጋኖ መሰለኝ። ብቻ ይህን ያህል ጠቃሚ ወሬ አይደለም።››

‹‹ፖጋኖ ሊሆን አይችልም›› አለ አርምስቱድ ቀልጠፍ ብሎ። ‹‹ተሳስተሻል።›› ተጥሎም ደረት ሳት አደሰማ ‹‹ባንድ ጊዜ ሁለት ቦታ እንዴት ሊታይ ይችላል? ከማማሽ ሰዓት በፊት እኔና ሃሪ ዴትዝ አይተነዋል። ያንቺው ፖጋኖ አምሳያ መሆን አለበት።››

‹‹ወይኔ ጉዴ . . . ልክ ራሱን ነውት የሚመስለው። በዚህ አይነቱ የማይረባ ወሬ ጆሮዎን በማደንቆራ ይቅርታ ሚስተር ኤድዋርድ።››

‹‹ምንም አይደለም። በይ እንግዲህ በጀኔቭ መልካም እረፍት። ከነ ወዲያም ከሰብሰባው አዳራሽ እንዳትለይ። ደህና ሁኚ።››

* * *

ለደቂቃ ያህል ኤድዋርድ እንደ ተክል ድንጋይ ድርት ብሎ እንደቀረ ቆየ። ከውስጥ ቆሽቱ በብሽቀት እርር ብሏል።

የውስጥ ስልኩን መደወያ ሜን አደረገ። ‹‹ሃሪ››

‹‹አቤት አለቃ? . .››

‹‹ዮሎ ና!›› ኤድዋርድ አዘዘ ‹‹አሁኑኑ!››

ሃሪ ዴትዝ በድንጋጤ ትንፋሹ ቱርጥ ቱርጥ እያለ አለቃው ቢሮ ሲገባ ደቂቃ እንኳ አልወሰደበትም። ‹‹ምን ችግር አለ፣ አለቃ?››

‹‹ምን ችግር አለ?›› ኤድዋርድ ባረቀ ከንፈሩን በሽሙጥ ገለጠ። ‹‹ያ ሽፋፋ ድካማችንን ሁሉ አፈር አስጋጠው።››

ሃሪ ወደፊት አሰገግ፣ ከመጀመሪያው ይበልጥ ተወናብዶበታል። ‹‹አ. . . አልገባኝም።››

‹‹ያ ደደብ ፖጋኖ ተደበቅ በተባለበት ቦታ እንደውሻ ከወዲያ ወዲህ ሲልከፈከፍ ሰው አይቶታል።››

‹‹የት?››

"የቅሰ ቢሆን። እንዳትታይ ተጠንቀቅ

"ግን እንዴት?" ጠየቀ ሃሪ ረጋ አደረ።

"ያቺ የዊስተን ልጅ . . ለሽርሽር ወደ [illegible] ኒዮን ከተማ ፓታናን አየችው። እንዲያውም በጣም [illegible] ነበር። ደግነቱ አላገናኝችውም። ደግነቱ አልተመዘገበችም።

"የተመዘገበው ጀምስ ፈርግሰን ቢሆን [illegible] አሰብ አደረግና "እኔ እንጃ አሰቃ፣ እኔን [illegible] ፈምሲን ባንድ ጊዜ ወደ ውጭ መላኩ፣ [illegible] ጥሩ ሃሳብ አይመስለኝም። እንዲህ [illegible] እሰጋለሁ። . ."

"ሁለቱ እዚያ መሆናቸውን እርግጠኛ [illegible] ጠቃሚ ጋዜጠኞች ናቸው። ቅናረው [illegible] ይህ የሣራው ማን እንዳልከው [illegible] የሚሰማ ቢሆን ኖሮ. . ." ኤድዋርድ [illegible] አሁኑ ፓታናን አግናኘኝ። ዋጋውን [illegible] ከቨክቶሪያ የተቀበለችውን ሃሳብ [illegible] ንገርልኝ። ለፓታኖ ሃሳቡን [illegible] ዝቅዝቅ መስመር ላይ አቅርብልኝ።"

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሃሪ [illegible] የአገር አቋራጭ መስመር እየተጠበቀ [illegible]

ኤድዋርድ ላቡን ከግንባሩ ላይ [illegible] ጠረጴዛው በዙጠ እየደለዘ [illegible] ድምፅ ይሰማ ጀመር።

"ጉሰ?" ኤድዋርድ ፈሯ

"ምን መጣ ጌታዮ?"

"አንተ የተለከፍክ. . አንተ ቀለብላባ [illegible]

ታይተሃል።››

ፓኃኖ ተምታትቦበት ተርበተበተ። ‹‹አ . . . አልገባኝም።››

‹‹አንድ ሰው አይቶሃል።›› የኤድዋርድ ድምጽ ከኒውዮርክ የአውሮፓውን ፓኃኖ ጆሮ ታምቡር አርገበገበው። ‹‹የድርጅታችን ሠራተኛ የሆነች ሴት፣ ሪፖርተራችን . . አወቅሃት ልጅቷን? ቪክቶሪያ ዊስተን። አንድ ጊዜ ታልሀን የተቀበለችው?››

‹‹ኧረ አላስታወስኳትም. . .›› ማን እንደሆነች ልቡ አላጣውም። ‹‹አሃ ያቺ ስለይንገር ያነጋገረችኝ ደልዳላ ልጃገረድ?››

‹‹እሷ ነች በኢንተርኮንቲኔንታል ላይ እንድትጽፍ ጀኔቭ የላከውት። ሽርሽር ወጥታ አንተን ሆቴልህ ውስጥ ስትገባ አይታሃለች።››

‹‹እዚህ መጥታ ነበር?››

‹‹ደደብ። ለሽርሽር ነው የመጣችው ነውኮ የምልህ። አሁን ነጥቡ ቀን ለቀን ሰው በሚያይህ ወቅት ምናባትህ ልትሰራ ከመኝታህ ክፍል ወጣህ ነው። አላስጠነቀቅንህም?››

‹‹ይሰመኛል ጌታዬ . . ላስረዳም . . ኩፐር?››

‹‹ይህ ስም ለመሆኑ በሰልክ የምትጠራው ስም ነው እንተ ቅድ አፍ?››

‹‹ቆይ እንጂ ላስረዳም?››

‹‹በቃህ . . . ሁለተኛ እንዳይደገም!››

‹‹ግን እኮ እንዳንድ ጊዜ የሚያስወጣኝ የስራችን ጉዳይ ይኖራል።››

‹‹ይህ ከሆነ ዒምህን አሳድግ፣ ጥቁር መነፅር ግዛ። የለም ዒምም ቢሆን እስክታሳድግ ጊዜ የለንም፣ ግዛ። ወይም ሌላ ዘዴ ፈልግ።››

‹‹እሺ ጌታየ›› ከማለት ሌላ ፓኃኖ የሚናገረው አልነበረም።

‹‹የኢንተርኮንትኔንታልን ፅሁፍ ተተብየልሃለሁ።››

‹‹ጥሩ፣ ግን ኩፐር ብዙም ፅሁፉን የሚፈልግ አይመስለኝም። ከወንጭ

አንዱን በሦቱሉ አስገብቦ ከላይ እስከ ታች አሳይቷል። ለማንኛውም የርስዎንም ላቀብለው።››

ሶስት ገፅ ተኩሉን የታይፕ ዕሁፍ በጥንቃቄ ለፓኃና አነበበለት። ፓኃና በብዕርና በወረቀት እያንዳንዱን ታል ተቀበለው።

በመጨረሻ ኤድዋርድ ‹‹ለመሆኑ ፕሮግራሙ በፕሮግራም መሰረት እየሄደላችሁ ነው?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹ምንም ለውጥ የለም። የተነገ ወዲያውም ፕሮግራም በእትድ መሰረት ነው።››

* * *

ከነገ ወዲያ በጁኔቭ።

ከጧቱ ሶስት ሰዓት ከሃያ አምስት።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስፓኝ አዳራሽ በተለይም የጋዜጠኞች ችና የትቢኝች የመቀመጫ ስፍራ ጢም ብሎ ሞልቷል። ለእይታዋ ከሁሉም ይበልጥ አመቺ ስፍራ ለማግኘት ስትል ቨ/ኮተሪያ ወደ አዳራሽ የገባችው ከብዙዎቹ ተደም ብላ ነበር። በማንኩኒው የመጀመሪያው ረድፍ ቢታ አገኘች። የማንኩኒውን ጠርዝ ተደግፋ ወደፊት በማጎንበስ ከምድር-ቤት የተንጣለለው አዳራሽ ምን እንደሚመስል አተኩራ ተመለከተች። አዳራሹን የመንግሥታቱ መልእክተኞች ሞልተውታል። ብዙዎቹ በተዘጋጁላቸው ስፍራ ተቀምጠዋል፣ ጥቂቶቹ ወዲያ ወዲህ ይመላለሳሉ፣ ሌሎች በየአገራቸው ቋንቋ ይወያያሉ።

ለአይን እጅግ የሚማርክ ስነ ስርዓት ከመሆኑ የተነሳ ቨ/ኮተሪያ የስብሰባው ፕሮግራም እስኪጀምር ቸኮለች። ጊዜ እያዘገመ ወደ ሶስት ሰዓት ተኩል በተጠጋ መጠን ብዙዎቹ የስብሰባው ተካፋዮች በማናቸውም ሴኮንድ በዋና ፀሐፊው በሚያዘው የሊቀመንበር መድረክ ላይ አይናቸውን አሳረፉ።

ሶስት ተኩል።

ቨ/ኮተሪያ ማስታወሻ ደብተሯንና ብዕሯን እዘጋጅታ ትጠባበቅ ጀመር።

ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አምስት።

[illegible] ነገር አልነበረም ብዙ ነው።

ሰውዮ ከሥራ [illegible] መሆኑ ከአርባ አምስት።

እንዲያውም ረዘም አለ፡ አምስት ደቂቃዎች አለፉ። ዋና ፀሐፊ እዙንም ጥቂ እሳ[illegible]

[illegible] ሲቸገሽ መልእክቶችን ሲቀበሉ ሲቸነጠሩ [illegible] አገልግሎት ከተቀመጠበት ይነሳሉ፡ ሌሎች በተቀመጡበት እያገለግሉ ይዘገያሉ። በቪክቶሪያ ግምት የዋና ፀሐፊው መሥሪያ ያልተለመደ ሰዓት ነው። የአመራር ሰዎች ምንጊዜም በታላላቅ ጉዳዮች ስለሚመሩ ብዙ ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ መፈፀም ይኖርባቸዋል። ዋና ፀሐፊውም ተመሳሳይ አንድ ጉዳይ አዘግይቷቸዋል። በአጭር ጊዜ በሰፍራቸው እንደሚገኙ ለቪክቶሪያ እመነች።

ሌሎች አምስት ደቂቃዎች እንዳለፉ አዳራሹ ትዕግስቱን አጥቶ በማጉረምረሙ ላይሆን አይቀርም አንድ ድምጽ በድምጽ ማጉያ «ዋና ፀሐፊው በአንቱርኩዲኤንታል ሆቴል ከመኝታ ክፍላቸው መውጣታቸውና ወደዚህ በማምራት ላይ መሆናቸውን እንገልጻለን» ሲል ተሰማ።

ይህ ግለሰብ ለተቂት ጊዜ አዳራሹን አረጋጭ ሊያደርግ ቻለ።

ይሁንና ጊዜ አያዘገመ ቢንዝም ዋና ፀሐፊው በአዳራሹ ሊታዩ አልቻሉም። ቪክቶሪያ ትዕግስቷ በመሟጠጡ በደመነፍስ ከመቀመጫዋ ተነስታ ከጋዜጠኞች ክፍል ጠጣች።

በአዳራሹ በረንዳ የሰሚዝ ፖሊስ ሰልፈኞች ተሰብስበው ይታያሉ። ቪክቶሪያ ወደ አንደኛው ጠጋ ብላ «ይቅርታ ብታደርጉልኝ የኔ ወንድም፡ እንግሊዘኛ መናገር ትችላለህ?» ስትል ጠየቀችው።

«አዎ፡ እመቤት።»

«ዋና ፀሐፊው እስካሁን አልመጡም?»

«እስካሁን ግና ናቸው። እየጠበቅናቸው ነው።»

ዋና ፀሐፊው የዘገዩበትን ምክንያት በመዘርዘር ይቅርታ ጠይቀው

ስብስባውን የሚጀምሩበት ጊዜ ሩት እንደማይሆን ግምታ ከአካባቢው ላለመራቅ ወሰነች። ቶስ እያለች ወደ መውጫው በሚወስዱት ደረጃዎች ስትመላለስ ቆይታ በመጨረሻ ወደ መኪናዋ አመራች። የዋና ዐሐፊው በፕሮግራም አለመገኘት ግራ የሚያጋባ ነው። እንዲያውም ጥሩ ዜና ሊወጣው ይችላል።

መኪናዋ ውስጥ ስትንደረደር ገባች። ኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል ለእግር ጉዞ ሩት ባይሆንም የጊዜ እጥረት መኪናዋን ባለው ፍጥነት እያንሳረች ገሰገሰች። ብዙ ሃሳብ ይዘበራረቅባት ጀመር። ህመም አጥቶአቸው ይሆናል። ሊላስ? ምን ምክንያት ይኖር ይሆን? ባስቸኳይ ልትደርስበት ቱርጥ ሃሳብ አደረገች።

በሆቴሉ መግቢያ መኪናዋን አቁማ ወደ ውስጥ ገባች። በእንግዳ መቀበያውና በአሳንሰሩ መካከል አይኗ ዋሸ። ብዙ ሰዎች አንዳንዶቹ የደንብ ልብስ የለበሱ፣ ሌሎቹ በፕሮቶኮል ሠነው በአሳንሰሩ አጠገብ ተኮልኩለዋል። የዋና ዐሐፊው ደህንነት ጠባቂዎች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ቪክቶሪያ ብትገምትም እርግጠኛ ለመሆን ፈለገች።

አይኗ በድንገተ ወደ እንግዳ መቀበያው ወንበር መለሰ አለ። ሆቴሉን ለመጎብኘት መጥታ በነበረበት ወቅት ያስጎበኛትን ረዳት ስራ አስኪያጅ አየችው። ፊጠን ብላ ወደሱ ሄደች።

‹‹ሰላም›› አለች። ‹‹ያስታውሰኛል?››

ረዳት ሥራ አስኪያጁ ጥቂት አሰበና ‹‹አዎ፤ እንዴታ። ጤና ይስጥልኝ ወይዘሪት ዊስተን›› አላት።

‹‹ይቅርታ ያድርጉልኝና ዋና ዐሐፊው ምን ሆነዋል?››

ረዳት ሥራ አስኪያጁ ትከሻውን ሰበት አድርጎ ‹‹አላወትንም›› አላት።

‹‹አስካሁን መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ናቸው?››

‹‹ስልክ ደውለን ነበር። መልስ አላገኘንም።››

‹‹ምናልባት ታመው እንደሁ?››

ሩየለም ወይዘሪት፣ ክፍላቸው ውስጥም ገብተን ነበር፣ ባዶ ነው። ከክፍላቸው ወጥተዋል።››

‹‹ግን. . .››

በዚህ ቅጽበት ረዳት ስራ አስኪያጁ ከቪክቶሪያ በስተጀርባ አንድ ነገር በማየት መሆን አለበት፣ ከእንባቱ ሰግማ ብሎ ይመለከት ጀመር። ቪክቶሪያም ሰውየው ወደሚመለከትበት አቅጣጫ ዞር አለች። ያደረገው ጥቁር መነፅር አፍንጫውን ሙሉ ለሙሉ ሊሸፍነው የደረሰ አንድ ረጅም ሰው ከኋላዋ ቆሚል። ረዳት አዘጋጁ ከተቀመጠበት ተነሳ። ‹‹አንድ ጊዜ ይቅርታ ወይዘሪት›› አለ ረዳት ስራ አስኪያጁ። ‹‹ዋና ስራ አስኪያጁ ናቸው ሊያነጋግሩኝ የሚፈልጉት።›› ረዳት ስራ አስኪያጁ ቪክቶሪያን አልፎ ወደ አለታው እንደሄደ አለታው ከንዱን ትከሻው ላይ ሲያሳርፍበት ቪክቶሪያ ተመለከተች። ዋና ስራ አስኪያጁ እጁን በረዳቱ ትከሻ ላይ ሚሳረፍ ብቻ ሳይሆን ራት ወዳለ ምሰሶ እየጎተተ ወሰደው።

ረጅሙ ስራ አስኪያጅ ወደ ረዳቱ ጎንበስ ብሎ አንድ ሚስጥር ሹክ ይለው ነበር። ወደ ምሰሶው መደበት ሲጀምሩ የቪክቶሪያ አእምሮ በሞያቂ ተመጠረ፣ ወደ ምሰሶው ሬመድ አለች። የሚያወሩት ስለሆቴሉ አስተዳደር ሊሆን ቢችልም ንግግራቸው ሊያመልጣት አልፈለገችም። በምሰሶው ጥቃራኒ ጎን ተክለላ ታዳምጣቸው ጀመር።

ዋና ስራ አስኪያጁ በጥሞና ይናገራል። የሚናገረው ፈረንሳይኛ ቢሆንም ቋንቋው እንግዳዋ አልነበረም። የሰማችው ግን በቆመችበት ክው ብላ እንድትቀር አደረጋት።

ጆሮዋን አቁማ ስታዳምጥ ዋና ስራ አስኪያጁ ‹‹አዎ፣ ልክ ነው፣ በሱን ቃል ከሚቀበሉት ከሦሊስ ጠቅላይ መምሪያ የደረሰኝ ሚስጥር ነው። እንደተረዳሁት ዋና ዐሐፊው ከዘጥቱ ጋር በግል ወዳዘጋጁላቸው አላንበር ይሄዳሉ። አላንሰሩ በተጥቃ መኪናቸው ከቆመችበት ቦታ ነበር የሚያወርዳቸው። ነገር ግን ባልሆነ መንገድ አላንሰሩ መሃል ጎዳና ላይ ቆሞ ይከፈታል። የታጠቁ ሽብርተኛ ፋኖዎች አሁን እንደ ደረሰንበት የካርሶስ ሞፍሮች አላቸውን ከንዘባቸው አፍነው አይኖቻቸውን በሐር ጨፍነው

ከሦቱሉ ሲያንደረድሩ ያወጡአቸውና ወደ አንድ ትልቅ አውቶሞቢል ይወስዷቸዋል። ከዚህማ ውጭ።››

‹‹አይደረግም›› ሪዳት ስራ አስኪያጁ ሲያንቋርር ሰማችው። ‹‹የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ጀኔቭ ላይ ተጠለፉ፡ በድራሽ አይደረግም።››

ዋና ሥራ አስኪያጁ ንግግሩን ቀጠለ። ‹‹ተደረገ እንጂ ወዳጄ፡ የጣዛ ዘቸው ነውኮ የተናገረው። ካርሎስ ዘቡን ጠለፋውን ለፖሊስ ሪፖርት እንዲያደርግለትና የመያዣ ጥያቄውን እንዲገልጽለት አሰረው። የመያዣ ጥያቄውን በርግጥ አላወቅሁም። የካርሎስ ቂፍቦች ዘቡን አይኑን መጨፈን ብቻ ላይሆን እጁንም የፊጥኝ አሰረው። በመኪናቸው በግምት ሃያ ወይም ሃያ አምስት ደቂቃ ያህል ከመሰዱት በኋላ ዘቡን ብቻ ከኋላው መቀመጫ አውርደው አውላላ ሜዳ ላይ ጥለውት ይበራሉ። ሆን ብለው ያሰሩት ላላ አድርገው ስለነበር ከተቂት ጊዜ በኋላ በራሱ ጥረት እስሩን ሊፈታ በመቻሉ የአይኑን ሽፋን ገልጦ ወደ አውራ ጎዳና ይሮጣል። አንድ ሞተረኛ አሳፍሮት ወደ አንድ መንደር እንዳደረሰው ዘቡ ስልክ ደውሎ ሁኔታውን ለፖሊስ ሪፖርት ያደርጋል። ጠላፊዎቹ የካርሎስን ስም ሲጠሩና ካርሎስ ጠለፋው መሳካቱን ሲሰማ እንዴት ደስ እንደሚለው ሲያውሩ መስማት ቸን ጨምሮ ተናግሯል። ፖሊሶቹ ትብብር እንዳደርግላቸው ጠይቀውኛል።››

‹‹ማን እንዴት?››

‹‹የዋና ፀሐፊው አጃቢዎች ሰውየውን በመጠበቅ እንዳይጉላሉ ነግሬ አንድ ሰበብ መፍጠር እንዳለብኝ ጠይቀውኛል።››

‹‹ዋና ፀሐፊው ታመዋል፡ ለሁለትና ለሶስት ቀናት ያህል ታመው ስለሰነበቱ እረፍት እንዲያደርጉ በሃኪም ታዘዋል ብንል. . .››

‹‹ልክ ነህ። እንዲያውም ይህንኑ አንተው ራስህ ንገራቸው። እኔ ደግሞ ለስብሰባው አዳራሽ ደውዮ ፀሐፊው በጤና መታወክ የተነሳ ሊገኙ ስለማይችሉ የላሬ ሚቱ ስብሰባ ሙሉላለቃን መንገር አለብኝ።››

ቪክቶሪያ በዚህ ጊዜ ሽምቅቅ አለች። ሚስጥር ስታዳምጥ መያዝ

የለባትም። ይህን አስደናቂ ዜና፣ ይህን ትንግርት በተቻለ ፍጥነት ኒውዮርክ ማድረስ ይኖርባታል።

በእግሯ ጣት እየተራመደች ከምሰሶው ራት ካለች በኋላ ጉዟዋ በጉጉት እየተንቀጠቀጡ፣ እግሯ እየተብረከረከ ቢያስቸግራትም ራሷን ለመቆጣጠር እየታገለች በመጣችበት ተመለሰች።

በሴኮንድ በሚቆጠር ጊዜ መኪናዋ ውስጥ ገብታ በታላቅነቱ በህይወቷ የመጀመሪያው የሆነውን ጀብዱ መቀጸጀቷን ትንጣት ሳትጠራጠር ወደ ሆቴሏ ከነፈች።

* * *

ረቫጂ ሆቴል ውስጥ በመኝታ ክፍሏ ገብታ ከውስጥ እንዳቆለፈች ባሁኑ ጊዜ ኒውዮርክ ጊዜው ምን እንደሚሆን ልትገምት ሞከረች። ኒውዮርክ ውስጥ ጊዜው ግና ንጋት ላይ ሳይሆን አይቀርም፣ በዚህም የተነሳ ከሪኮርድ ሰዎች ውስጥ ልታገኘው የምትችል ደህና ባለስልጣን ስራ ላይ እንደሚይኝ ተገነዘበች። የተቀጸጀችው ጀብዱ፣ ለሣሏ የያዘችው ትንግርተኛ ዜና ደግሞ ከታላቅነቱ የተነሳ ለአልባለ ሰው ጆሮ የሚነገር አይደለም። ዜናዋ በቀጥታ ከቴንሬሙው ላይ መድረስ አለበት።

የኤድዋርድ አርምስቱድን የቤት ሰልክ አታውትም። ረጋ ብላ ስታስብ ሃሪ ዴትዝ አስቸኳይ ጉዳይ ካጋጠማት ቤቱ ልትደውልለት እንደምትችል ጠቅሶ የሰጣት ቁጥር ትዝ አላት።

የሃሪ ዴትዝ መኖሪያ ስልክ አገናኝ አያጓጋች ጥቂት ካላዘነችባት በኋላ አገናኟቻት።

‹‹ሂለሙ ማን ልበል?››

የቪክቶሪያ ልብ ዘለለ። የሰማችው ድምጽ የሃሪ ዴትዝ ለመሆኑ አልተጠራጠረችም።

ቪክቶሪያ ዜናዋን እያምባረቀች ልትነግረው፣ ጆሮው ላይ ልታፈነዳበት ፈለገች። ነገር ግን ረጋ እንድትል ሙያዋ አስገድዷት ልብ ገዛች።

«ሚስተር ዴትዝ፣ ቪክቶሪያ ዊስተን ነኝ፣ ከጂኦቭ» አለች ትንፋሿን መለስ አድርጋ። «በፊት ስለተሰናበትኩም ይቅርታ ግን. . .»

አላስጨረሳትም። «ምንም አይደለም» አላት፣ «በውነቱ እስካሁን አልተኛሁም» ከአንጋፋ ጥቂት መጠጥ ሳይተርስ እንዳልቀረ ያስታውቃል።

«ኤድዋርድና እኔ አሁን ገና ከቢሮአችን መውጣታችን ነው። እንዴት የተመጠረንበት ሊሊት ነበር መሰለሽ፣ ግን ደግሩ ኒውዮርክ ውስጥ የሁሉም የበላይ የሚያደርግን ታላቅ ነገር አገኘን። ከማግኘትም አልፈን አሳትመነዋል። እስካሁን የከተማው መንገዶች በጋዜጣችን ሳይጥለቀለቁ አይቀሩም።»

እቺም እንዲሁ አለታዋ ንግግሩን እስኪጨርስ ልትታገስ አልቻለችም። «ግን ይሰሙሻል?. . .»

ሃሪ ዴትዝ ከጉዳይ አልጣሩትም። ንግግሩን ቀጠለ «በርግጥ ከአጠገብሽ ነው የተነጠቅሽው፣ ታላቅና ትንግርተኛ ዜና። የሚያስደንቀው ደግሞ መሉ ለመሉ የግላችን መሆኑ ነው። ማንም ሰው፣ ማንም ድርጅት ይሁን ዜና ሊጋራን አልቻለም። እንዴት ያስደስታል? የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ተጠለፉ። ከሥልጣናቸው ወጥተው ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሲያመሩ ታፈኑ. . .»

«ከርሰሰ ሞኖሮች» አለች፣ ቪክቶሪያ በሰለለ ድምጽ። አልሀ ንቦዋን አንቋታል። አልጋዋ ላይ በቁሟ ወደቀችበት። ውጋት የጠበሰታት መሰላት። ጨጓራዋ ሳይተር እየተፋፋ አዝጫጫ።

ሃሪ ዴትዝ የሰማት አይመስልም «ከካርሎስና ከሞኖሮቹ። ኤድዋርድና እኔ ወደ መኝታችን ለመግባት ስንሰናበት የጠላፊዎቹ የመያዣ ጥያቄ ዜና ደረሰን። አሁን ሰራተኞቻችን ይህንኑ ዜና በማተም ላይ ናቸው። በነገው እትማችን ላይ ሌላ ትንግርት አውጥተን የኒውዮርክ ነዋሪ ህዝብ ለንበሸበሽ ነው. . .»

«የመያዣ ጥያቄያቸው ለመሆኑ ምን ነበር?» ጠየቀች ቪክቶሪያ መሸመጧ ተቆርጦ።

‹‹የማይረባ ነው ባክሽ፣ በውነቱ የማይረባ። ግን እንደ ካርሎስ አይነቱን ሰው የምታውቂ ከሆነ ከሱ የሚጠበቅ ጥያቄ ነው ያቀረብው። መጥፎው የጉክሊዩር ጦር መሳሪያ የሚመለከተውን ስብሰባ አቋርጠ የየመንግስታቱን መልእክተኞች ወደየአገራቸው መመለስን የሚጠየቅ ነው። ምክንያቱም ስብሰባው ጎያላን መንግስታት ደካሞቹን አጥሮ ያልታጠቁና ደካሞች አድርገው ለማስቀረት ያለሙት የተንኮል ስብሰባ ነው ይላል ካርሎስ። ስለዚህ ይህ መድልኦ የሚያደርግ ስብሰባ ብዙሃኖ ተወካዮች አገሮቻቸው መሳሪያዎቹን እንዲያጠርቱ ተፈትዶላቸው በየመጡበት እንዲመለሱ ይፈልጋል። በዚህም መሰረት የስብሰባው ተካፋዮች ወደየአዘጋቻቸው ከተመለሱ ዋና ዓሐፊው ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ይለቀቃሉ።››

‹‹በትርቡ ሌላ ስብሰባ ሲጠራ አይችልም ታዲያ?››

‹‹ይችላል ግን ካርሎስ እንዲህ አይነቱ ስብሰባ ጸጋመኛ የሚከሂድ ከሆነ እንደነና ሽብር እንደሚለቅበት አስጠንቅቋል። ካርሎስ እንዲህ ማድረግ ልማዱ ነው። ይኸውልሽ ሪኮርድና ማርክ ብራድሾ ዛሬም የአሜሪካና የመላው አለም ኢንፎርሚሽን ቴንሎጂዎችውን ደግመው አልሻለሁ። ሁሉም አዲሱን ዜና የሚያገኘው ከሪኮርድ ብቻ ይሆናል። በይ እንግዲህ ትንሽ ሳሸልብ፣ ስለደመልሽልኝ አመሰግንሻለሁ፣ ቪኪ።››

ለምን እንደደወለች ለመጠየቅ እንኳ ሳይጨነት ጆሮዋ ላይ ስልኩን ጠረቀመባት።

እንደተቀመጠች ደርሶ ተረች። ትንግርተኛ ዜና ዛሬም ከአሷ ላይ ተነጠቀ። በማን? ዛሬም በሪኮርድ ብርቅ ልጅ፣ በማርክ ብራድሾ።

እንዴት?

የሰዓድ ደወል፣ ጠለፋው ከተካሄደ ሶስት ሰዓት ብቻ እንዳለፈው አሰረዳት። የማሷ፣ የብቻዋ ዜና ነበር፣ ግን ብትታገልም አልታደለችም። ከጂ ቀድሞ ሌላ ሰው ዘግቦ አትርቦስታል፣ ኒውዮርክም ይኸኔ በጎድጓዳማው ዜና ተመታለች። መንገዱጅ ብቻ ሳይሆኑ የአየር ሞገዱ ሳይቀር በትንግርተኛው ዜና እየተርገበገበ ነው። ታሪክ በተፈጸመበት በጀኔቭና በሰፊው አለም ግን ድርጊቱን ግና ማንም አላወቀውም። ማንም ቢሆን ሊያውቀው የሚችለው

ተአምረኛው ሪከርድ ጋዜጣ ሲነግረው ብቻ ነው።

እንዴት?

ምናልባት እንደ ኒክ ራምሲ ያለ ልምድ ያካበተ ጋዜጠኛ ሚስጥሩን ያውቅ ይሆናል። አም፤ ራምሲን ማግኘት፣ መንገርና የሚላትን መስማት አለባት።

9

ያለፉት አሥር ቀናት ለኒክ ራምሲ አታካች ሆነው ነበር ያሰፉት። ከፖሪስ ግና ቱልአቪቭ ከመግባቱ ከኒውዮርክ አሊ ማክአሊስተር ደውሎ አንድ አስቸኳይና ቅድሚያ የሚሰጠው ስራ እንደተዘጋጀለት አስረዳው። የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ግብፅ የሚያደርጉትን ጉዞና በዚያም ከግብፅ አቻቸው ጋር የሚያካሂዱትን ውይይት መከታተል እንዳለበት ተነገረው። የአምስት ቀናት ስራ። በስድስተኛው ቀን ኢየሩሳሌም በሚገኘው የመጓጉ ባህር ቅርሳቅርስ መዘያም ተገኝቶ ስመጥር አለም አቀፋዊ አርኪኦሎጂስቶችን በሚያሰባስበው በመዘያሙ አመታዊ ክብረበአል ላይ ይገኛል።

አምስቱን ቀናት ከአእምሮ ይልቅ በጉልበት ሥራ ተጠምዶ ነበር ያሳለፈው። በስድስተኛው ቀን የመጓጉ ባህር መዘያምን ክብረ በዓል ሊመለክት ኢየሩሳሌም ገባ። ሰላቱን ወደር የሌላቸው የእስራኤል ብርቱ ትርሶች የሳበኘው በታላቅ ጉጉትና እርካታ ቢሆንም ስለመዘያሙ ሊያቀርብ የሚችለው ዕውቅ ግን ከጣናው ኒውዮርክ ሪከርድ አንባቢ የሚጠበቀውን ማራኪ ቁምነገር እንደማያዝል ተገነዘበ። ለማንኛውም የመዘያሙን ውጫዊ ትርዕ ጨምሮ በውስጥ የሚገኙትን የብራና ጥንታዊ ዕቁሮችና በእስር የመስታወት ሳጥኖች ውስጥ ለጎብኝዎች እንዲታዩ ሆነው የተቀመጡት አሪጅናልና ፎቶ ኮፒ ታሪካዊ ትርጸች የሚያካትት ሰፊ ዘገባ አዘጋጀ። በዚያው ምሽትም ካረፈበት ሆቴል ሆኖ ኒውዮርክ ደወለና በተቻለው መጠን ያቀናበረውን ዘገባ ታል በታል ለአለቃው አስገለበጠው።

ሀፊ ቂት ራምሲ በኢየሩሳሌም የሚያደርገውን ስራ አጠናቶ በታክሲ ወደ ቴልአቪቭ ተመልሷል። ልብስ ለመቀየር፣ ቁርስ ለማድረግ፣ ግላውን ለመሊኮስት ጊዜ ሳያገኝ በጥራስ አውቶብስ ተሳፍሮ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ሄደ።

* * *

ጀምበር ከአናት ወደ ምዕራብ ዘንበት ግለት እንደጀመረች በመካከለኛ ፍጥነት የሚንዝ መለስተኛ አውቶቡስ በኢየሩሳሌም ኘሬዝዘል ጎዳና ታየ።

በዚህ የኪራይ አውቶቡስ ውስጥ የአገር ጎብኚ ነጋዴ ሞዴል የያዘው ኩፐር ነጣ ባለ የቢጋ ሸሚዝ ላይ ጠባብ ክራባት አስሮ አፍንጫው መስታወቱን እስኪነካው ድረስ ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ውጭ-ውጭውን ይመለከታል። በስተቀኙ የኘሬዝደሪው ዩኒቨርሲቲና የዩኒቨርስቲው ስታዲየም ከመሊናው አንገዝ ጋር ወደኋላ ሲቀሩ ይታዩታል። የእስራኤሉን ፓርላማ አልፈው ጥቂት እንደተጓዙ የመጥ ባህር ቅርሳቅርስ መዚየም ለእይታ በቃ። «ኮቃርበናል» አለ ኩፐር አቀማመጡን እያስተካከለ። በአውቶቡሱ ያሉት ሰባት ጓዶቹ እንዲሰሙት ድምፁን ከፍ አድርጎ ነበር የሚናገረው። «ሁላችሁም እትጣጫችሁ ወደ መዚየሙ መሆን አለበት። ተልዕኮአችሁ ለእያንዳንዳችሁ በግልፅ ተነግሯል።»

«በግልፅ» አለ፣ ከፊት ለፊት ወንበር ላይ የተቀመጠው ኩግ ተበል አድርጎ።

ለግማሽ ደቂቃ ያህል የፀጥታ ጉሀ ሆነ። ከዚያም ኩፐር ዘና እንዳለ ንግግሩን ቀጠለ። «ከፍጥንስኩ አውቶቡሱን ከመዚየሙ ጎን በሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ያቆምልናል። ቀጥሎም ከአውቶቡሶች ወርዶ ከጋጋኖ ጋር ፈቀቅ ብለው ወደቆመት ሁለት ባዶ ፎርዶች ይሄዳሉ። ከመኪናቹ አጠገብ ቆመው ሲጋራ እያቀጣጠሉ ሰዓታቸውን በጠመልከት በሸፈር መቀመጫዎቹ ላይ የሚቀመጡበትን ጊዜ ያመቻቻሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ስድስታችን ከዚህ አውቶቡስ እንወርዳለን፣ ከሊቨርፑል የመጣን የጎብኚዎች ቡድን አባላት መሆናችንን እንዳትዘንጉ። መዚየሙ መግቢያ ላይ ልክ የመግቢያ ትኬት መቁረጫው ላይ ስንደርስ ቲኬት ለመግዛት እንሰለፋለን። አንድ ጊዜ

መግቢያውን ካለፍን ወደ እስራኤል መዚያም የሚያመራ የጭብ መንገድ እናገኛለን። መንገዱን ትተን ወደ ቀኝ አጠፍ ስንል የመሓት ባዘር ትርሳ ትርስ መዚያም የሚል ዕሁፍ ይነበበናል። የምንፈልገው እሱ ነው። ረጋ እንዳላችሁ ወደዚያ ትሂዳላችሁ። ሩጫ የለም። ጉብኝዎች መሆናችሁንና ግራ ቀኛችሁን እየታኛችሁ መራመድ እንደሚጠበቅባችሁ ልብ በሉ። በመሠረያው በኩል ደረጀዎች ታገኛላችሁ። አራት ደረጀዎች እንዳሰፋችሁ ጥቂት ትራመዱና እንደገና ሁለት ደረጀዎች ይጠብቋችኋል። ከዚህ በኋላ ቁልቁል የሚያስወርድ ደረጃ አለ። ይህን ደረጃ ወርዶን እንደጨረስን ጉዟችን ተጣባደደ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ የሚተረን ሥራችንን መስራት ብቻ።››

ላፈር እጅን አነሳ ‹‹ለሎች ቱሪስቶች፡ እውነተኛ ቱሪስቶች ቢያጋጥሙን ምን እናደርጋለን?››

‹‹ይህ ከሆነ›› ኩፐር መለሰ፡ ‹‹አሰቱማቸው። በፍፁም ከዘር እንዳይወጡ አስገድዳቸው።›› ከዚያም ወደ ሌሎቹ ዞር ብሎ ‹‹ሌሎቻችን ግን ጉዟችንን እናቆምም። ፊጠን እንላለን። ከመግቢያው እስከ መውጫው ድረስ የምፈትድላችሁ ጊዜ ሶስት ደቂቃ ብቻ ነው። ተግባባን?››

‹‹ተግባብተናል።› መለሰ ኩማ።

‹‹ጥያቄ አለ?›› ጠየቀ ኩፐር።

ጥያቄ ግን አልነበረም።

‹‹አንድ ጥንቃቄ›› አለ ኩፐር። ‹‹ዘግየት ብሎ ከፓጋኖ በደረሰን ጥቆማ ላይ የተመሰረተ አንድ ጥንቃቄ።››

ከሾፈሩ በቀር አውቦቡሱ ውስጥ ያሉት በሙሉ አይኖቻቸውን ኩፐር ላይ ተከሉ።

‹‹ታስታውሱ እንደሁ ከመግቢያው አጻራሽና ከትርሳትርስ ክፍል በመስታወት ሳጥኖች ውስጥ የተቀመጡ ለእይታ የተዘጋጁ ታሪክዊ እቃዎችን የያዘ ሰፊ ቤዕ መኖሩን ገልጨላችኋለሁ። እዚያ ውስጥ ያሉትን ቁሳቁስ በፍፁም እንዳትነኩ። በመስታወት ሳጥኖቹ ውስጥ ያሉት ያልታተሙ ታሪክዊ ዕሁፎች ትርፃ ትርስ፡ ሳንቲሞች፡ የሽክላ ስራዎችና ሌሎች ትርስት ናቸው

የምንፈልጋቸው። ታላላት ንብረቶች እነሱ አይደሉም። እነሱን አልፋችሁ ወደሞናው ክብ መደሀነው ማዕከላዊ አዳራሽ ሂዱ። እንደደረሳችሁ በአዳራሹ ሜጫጫ ዙሪያ ወዳሉት አሰር የማእያ ሳጥኖች በተጥታ ተጠኑ። ከቱምራን ቀሽ የተገኙት የሙት ባህር ጥርስ ጥርስ ማለት እነሱ ናቸው። የማሳያውን መስታውቶች ለመስበር እንዳትታከሙ። መስታወቶቹ ምን ያህል ወፍራም እንደሆኑ የምናውቀው ነገር የለም። በዚያ ላይ መስታውቶቹ ወደውጭ ማስወንኮቢያ የሚያኮብል መሳሪያ ተያይዛባቸው እንደሁም አናውቅም። ስለዚህ ብቸኛ ተማባራችሁ ያራባንሳችሁን ተመሳሳይ ቱልፎች መጠቀም ነው። ቱልፎቹን ስትጠቀሙ ጥቂት ደቂቃዎች ሊባክኑባችሁ ይችላሉ፣ ነገር ግን ስራችሁ አስተማማኝና ዋስትና ያለው ነው። እያንዳንዱ የመስታወት ሳጥን የራሱ የቱልፍ ተጻፃ ከሰሩ ባለው የእንጨት ከፈጥ ላይ ይገኝበታል። ቱልፉን አስገቡ፣ ተከፋቹን አንሱ፣ ትርዕቹን አውጡ። ከዚያ መውጣት ይህን ያህል ቀላል ነው።።

በዚህ ጊዜ አውቶቡሱ ለመዞር ይጠመዝዝ ጀመር። ኮፐር በመስኮቱ ወደ ውጭ ተመለከተ። ።ደርሰናል። የተዘጋጁልንን ሁለት ፎርዶች ማየት ትችላላችሁ። ከሩጉንስኪ ወደ ጎላ ሂደህ አቁም።።

አውቶቡሱ ወደ ማቆሚያው ሲያዘግም ሁሉም ተሳፋሪዎች ውጥረት እየተንበዘበዛቸው እንደተቀመጡ በመኪና ማቆሚያው ስፍራ የሚታዩት ሶስት ባዶ አውቶሞቢሎች ብቻ መሆናቸውን አስተዋሉ።

ልክ መኪናው እንደቆመ ኮፐር ንግግሩን ተጠሰ። ።ስለአወጣጣችን።። አለ፣ ።ሁሉም ነገር በሰላም በእቅዳችን መሰረት ከተከናወነ አመጣጣችን እንደ አገባባችን ረጋ፣ ቀስ ያለ ይሆናል። ከመዚያ እንደወጣን አራታችሁ ሃይፋ ወደብ ወደምትጠብቃችሁ መርከብ ትሄዳላችሁ። ታዲያ ጥርሳ ጥርሱን የያዛችሁባቸውን እቃዎች ለኔ ትተጢልፉኛላችሁ። እኔና ፓኦሎ ወደ ኢያሩሳሌም ተመልሰን ከእስራኤል ከመውጣታችን በፊት ልናደርግ የሚገቡንን ነገሮች እናከናውናለን። በእቅዳችን ላይ እክል ከተደቀነና ጉልበት እንድንጠቀም ከተገደድን ግን ኃይላችንን በትልጥፍና ተጠቅመን በሁለተኛው እቅዳችን መሰረት ሌላ የጉዞ መስመር በመከተል እናንተን ጥንድ ጥንድ አድርገን በምትገኙበት ቦታ ላይ እንወስዳችሁና ልብሳችሁን እንድትቀይሩና

ከአገር እንድትወጡ እናደርጋለን።›› ንግግሩን ወደ ክሩፕንስኪና ወደ ጋጋኖ በማዞር ቀጠለ። ‹‹በሁላቹም እቅድ ብንስማማስ ይህን ግዙ ስንለት መኪናዎቻችሁን የምታሽከረክሩት በተረጋጋ መንፈስ ይሆናል። ፍጥነት ወይም ቀይ መብራት መጣስ አይቻልም። አስራአሌች በየአራት መንታ መንገዶቻቸው ላይ ሀግ የሚተላለፉትን የሚያነሱ የፎቶ ሳጥኖች አሏቸው። አንድ ጊዜ ተልዕኮአችንን ከፈፀምን የምንገናኘው በተነጋገርነው መሰረት ጋራስ ይሆናል።››

ኩፐር አውንም ወደ ውጭ ተመለከተ። አውቶቡሱ ቆሞ ሞተሩ ጠፋ። ‹‹በሉ እንግዲህ ልጆች›› አለ ኩፐር ረጋ ባለ ድምፅ፣ ‹‹ስራችንን መጀመራችን ነው። እንውጣ።››

የአውቶቡሱ በር ተከፍቶ ክሩፕንስኪ ወረደ፣ ጋጋኖ ተከተለው። ሁለቱም ወደ ርቀዶቻቸው ሲያመሩ ኩፐር አያቸው። ከዚያም ራሱ ከመቀመጫው ተንስቶ ከንደኞቹ ጎላ ከአውቶቡሱ ወጣ።

እንደወጡ በሁለት በኩን ተከፍለው የሞቀ ጨዋታ የከፈቱ እየመሰሉ ‹‹የቲኬት በር›› የሚል ፅሁፍ ወደሚነበብበት ክፍል አመሩ። በክፍሉ በር እንደደረሱም አንድ መስመር ሰርተው ሁሉም ዝርዝር ሳንቲም ፍለጋ ኪሶቻቸውን ይዳብሱ ጀመር።

ኩቲኬት ግዢ በጎላ በኩፐር መሪነት ወደ መግቢያው በር ተጠጉ። ከመግቢያው በር በስተውስጥ አንድ የተሰላቸ መልክ የሚታይበት የአስተናጋጅ ምልክት ኩፉ ላይ የለጠፈ ወጣት ከእንዲት ወፍራም ልጃገረድ ጋር በእይሁድ ቋንቋ ያወራል። ወጣቱ የትዝታዎቹን ቲኬት በፍጥነትና በቸልተኝነት እየቆጠ አሳለፋቸው።

የመግቢያውን በር እንዳለፉ ሁሉም ተሰባሰበ። እንደገና በኩፐር መሪነት ጉዟቸውን ቀጠሉ። የመጀመሪያውን መተላለፊያ ቀኞቹን ትተው በግማት ሲያዘግሙ እንደቆዩ ከፊት ለፊታቸው የመጓጉ ባዘር ቅርፅርስ መሀያም የሚል ፅሁፍ ተነበባቸው።

ልክ ፅሁፉ ላይ ሲደርሱ ሁሉም ከኩፐር ጀርባ ተከልከሉው ወደ ሌላ መተላለፊያ በርፍ ኩፐር የገለፀላቸውን ደረጃዎች ከወጡ በኋላ ቁልቁለቱን

ከመውረዳቸው በፊት እንደገና ተሰባሰቡ። የተረፉት እውነትና ቱሪስቶች በአካባቢው አስመኖራቸውን ያረጋጠት እዚህ ሰፍራ ሆነው ነበር።

በዚህ ቅፅበት ኩፐር ሰዓቱን ተመልከቱ ወደ ሚኖርቸው ቦር አሰና ሚቀሩ፡፡ አለ። ‹‹ተሞሉ፡፡ አንድ የሚስዋር ምልክት ሳይሆን እያተርምሱ ስድስቱም ከሱፍ የተሰራውን ቫንኑርንሩን የፊት ሽፋን ከየኪሶቻቸው አውጥተው አጠለቁ። ያዘ በእንዲህ አንዳለ ኩማ በትከሻው ካንተው የጉዞ ሻንጣ ውስዋ ኮች የተባለውን አውቶማቲክ መሳሪያ አውጥቶ በተጠንቀት ያመ። በዚያው ቅጽበት የተቀሩት በሙሉ የጎረሱ አውቶማቲክቻቸውን አውጥተው በደረጃው ወጂታች ወርደው በዘረንዳው ወለል ላይ በረድፍ ሲቆሙ ለተመለከታቸው አንድ የመዚቃ ትርኢት የሚያሳዩ ተዋዋጮች ይመስሉ ነበር። በተንደርደር በረንዳውን አልፈው ወደ መዚየሙ በሚያስገባው በዋናው በር ትይዩ ቀጥ አሉ። ፈት ለፈት የሚመራቸው ኩፐር በበሩ አቨልኮ ሲመለከት ይኖራሉ ብሎ የጠበቃቸውን የመዚየሙን ሰራተኞች ተመለከተ። ከመግቢያው በር በስተመስዋ በተከፈተ የብረት በር አጠገብ አንድ ቲኬት ተቆጣጣሪ ይታያል። የኒዮርም መሰል ንግር የለበሰ ጠና ያለ ዘብ የሽጉጥ ማፋጸ አንግቶ ቆሟል። በስተጀርባቸው ብዙም ሳይርቅ ጋዜጣ የሚያነብ ሌላ ሰራተኛ ተቀምጧል።

በደግቱ ብርሃን የሚፍለቀለት አውቶማቲክ የደቦንሙና በአሰፈራ የእያንት ቀዳዳ በተንደሉ የፊት ሽፋን የተሸፈነው ኩፐር ድንገት ከፊት ሰፈታቸው ገቦ ሲል ሶስቱ ሰራተኞች የተሰማቸውን ድንጋጤ መገመት አያስቸግርም።

ኩፐር በሩን በርግዶ ዘው ሲል አምስቱም ሚኖርቸ ተከተሉት። በሴኮንድ ውስዋ ቲኬት ተቆጣጣሪውና ጋዜጣ ሲያነብ የነበረው እጃቸውን ወደላይ አደረጉ። ጥቂት ሊታወም የነጀለው ጠና ያለው ዘብ የሚንቀሳቀሰ እጁን ወደ ማፋጸው ሰደደ። በዚያው ሴኮንድ ኩፐር ዘሎ የዘቡን አናት በመላሪያ ሰደፍ ሲወታው ዘቡ ጥቂት ሊያንጋርር ሞክሮ ወዲያው ዝልፍልፍ ብሎ ወደቀ። ሙሉ ለሙሉ መሬት ላይ ከመዘረሩ በፊት ግን ኩፐር ዘቡን አፈፍ አድርጎ ሽጉጡን ከማረከው በኋላ ወለሉ ላይ ዘረረው። ኩማ በበኩሉ በሴኮንድ በሚቆጠር ጊዜ ከትኬት ተቆጣጣሪው ጀርባ ላይ አውቶማቲኩን ደቅኖ ትጥቁን ከሰፈታው በኋላ ከኩቱ ከስ ባለጣው ቀሚን ገመድ ሁሰት

እጅን የፊጥኝ አስሮ ወለሉ ላይ አስተኝውና ከሱሪው ኪስ መሃረብ ካወጣ በኋላ በእስረኛው አፍ ውስጥ ጠቀጠቀበት። በዚያው ጊዜ ኩፐር ራሱን የሳተውን ዘብ እጅ የፊጥኝ ጠፍሮ ጨርሷል። አዘርለ. የተባለው ጓደኛው ጋዜጣ ሲያነብ የነበረውን ሰራተኛ እንዲሁ አድርጎታል።

ትንሣት የመረበሽ ምልክት ያሚይታይበት ኩፐር ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ኩሳ ከመግቢያው በር ሳይንቀሳቀስ እንዲጠባበት ምልክት ከሰጠው የጉሠ ሻንጣዎቹን ከተተበለው በኋላ ለጓደኞቹ እንድ እንድ ያድል ጀመር። ይህ እንደተጠናቀቀ ወዲ ቅርሳ ቅርሱ ክፍል በሩጫ ዘው አሉ። በዚህ ጊዜ ግን ኩፐር የሚሮጠው ከኋላቸው ነበር። ወደ ዋናው የቅርሳ ቅርሰ ክፍል ሊገቡ ጥቂት ሲቀራቸው ኩፐር በተመለከተው ነገር ለጊዜው እጢው ጹብ አሰ። እንደመጀመሪያው ዩኒፎርም መሰል ልብስ የለበሰ የመዚየም ዘብ በሩ ላይ ቆሟል። ይሁንና ኩፐር በትዕበት ዘው ያልታጠቀ መሆኑን ተረዳ። እንዲያውም ዘው አሰቀድሞ እጅን ወደላይ አንከርፍቷል። ኩፐር ከዮፍሮቹ አንዱ ይህን ዘብ እንደለሎቹ የፊጥኝ እንዲታፍዱት የሚያዝዝ ምልክት ሰጠ።

ወዲያው ደግሞ ጊዜ ሳያጠፉ ኩፐር የመዚየሙ ኤግዚቪሽን ክፍል ሰው አለበት እንደሁ ለማረጋገጥ በትጽበት ተመለከተ። ከመካከል አካባቢ ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም እድሚያቸው በሰድሳምቹ የሚገመቱ ወንድና ሴት ጎብኝዎች ቅርሳ ቅርሰን በታላት ተመስጠ ይመለከታሉ። አሳውንቶቹ ምን እንደገጠማቸው ከማወታቸው በፊት የኩፐር አብረቅራቂ አፈሙዝ ተጸዳ አተኩሮባቸው ተመለከተ። ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማሰብ እንኳ ፋታ አልነበራቸውም። ኩፐር እየገፋተረ ወደዮፍሮቹ ወሰዳቸው፣ ደቂቃ ሳይሞላ የፊጥኝ ታስተው ከዘቡ ጎን በደረታቸው እንዲተኙ በአስፊሪ ታና ታዘዙ።

የኩፐር አባላት ሴኮንድ እንኳ ሳያባክኑ በግድግዳው ዙሪያ ባሉት የመስታወት ሳጥኖች ስር ቁልፎቻቸውን እያስገቡ ይከፍቱ ጀመር። አምስት የመስታወት ሳጥኖች በትጽበት ተከፍተው የመት ባዘር ቅርሶች ጥንታዊ የብራና ፅሁፎችና ሌሎችም ቅርሶች እየተንሰሳሱ ከወው በኋላ በንሥ ሻንጣዎች ውስጥ ይታጨቁ ጀመር። በሁለተኛው ዙር የተቀሩት አምስት ሳጥኖች ተከፍተው በተመሳሳይ ፍጥነት ንብረቶቻቸውን አስረከቡ። ተልዕኮው

ማን ሊመታ ይሆን? በራሬም ቸር በጀርባ በር ለመጠጣት ተዘጋጀ።

* * *

ወደ እስራኤል ሙዚየምና ወደ ሙት ባህር ቅርሳ ቅርስ ኤግዚቢሽን በሚያስገባው በር የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር የግብፅን አምባሳደር ከጎናቸው አድርገው በጥድፊያ ከመኪናቸው ከወረዱ በኋላ ዋናውን የመግቢያ በር ችላ ብለው እንግዳቸውን ከጎን በሚገኘው የእግረኛ በር እየመሩ አስገቧቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰባ ሁለት ዓመት አዛውንት ቢሆኑም በሳርባማው የጠብ መንገድ በኩል በፍጥነት ሲራመዱ ለተመለከታቸው አትሌት ይመስላሉ። የግብፅ አምባሳደር ሶስቱ ወጣት ኮማንዶ አጃቢዎቻቸውና ሁለቱ እስራኤላውያን ጠንቋዮች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ርምጃ እኩል ለመፍጠን የሚያትት-ተውን ትንፋሻቸውን ለመቆጣጠር መታገል ነበረባቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅግ፣ እጅግ በጣም ዘግይተዋል። ለአንድ የፖለቲካ ሰው ምንጊዜም ፕሮግራም ከማፋለስ የበለጠ ይቅርታ የሚያሰጥ ወንጀል የለም። በካይሮ ጉብኝታቸው ላይ አብረው ለመገኘት ከዚህ የሚነሱት ረዳቶች፣ አማካሪዎችና የፕሮቶኮል ሰዎች አውሮፕላን ውስጥ ተቀምጠው የእሳቸውን መምጣት በተሰላቸ ሁኔታ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አልጠፋቸውም።

ያም ሆኖ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአምባሳደሩ የዝቡት ታሪክ ነውና በሙት ባህር የቅርሳ ቅርስ ኤግዚቢሽን አዞር ጉብኝት ለማድረግ ጥቂት ጊዜ መግደላቸው የግድ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀስ በቀስ ፍጥነታቸውን መቀነስ ጀመሩ። ‹‹ቅርሶቹ እንዴት እንደተገኙ ያውቃሉ?››

‹‹እንዴታ፣ ዝርዝር ታሪኩን አንብበአለሁ።›› አምባሳደሩ መለሰ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአምባሳደሩን መልስ ያልሰሙ ይመስል ቅርሶቹን የፈላቸው አባት እንዴት እንደገኟቸው በኩራት ያብራሩ ጀመር። ‹‹የሁለት ሺህ አመት እድሜ ያላቸው ቅርሶች ናቸውኮ፣ ክሰ በመጨረሻው።

ይህ በእንዲህ እንዳስ መንገዳቸውን ወደማገባደዱ በመቃረባቸው

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእጃቸው ወደ አንድ ጎን እያመለከቱ፡ ‹‹አቋራጩን መንገድ እንያዝ። በጀርባ በር በኩል ብንገባ ጊዜ ስለምንቆጥብ ትርአቺን በዝርዝር ለመመልከት ጥቂት ደቂቃዎች ይኖሩናል፡፡ አሉ።

* * *

በትርሳ ትርሰ ኤግዚቢሽኑ ክፍል ውስጥ ኩፐር በሩጫ ወደከፍቱ መሸለኪያ ኩቲጋ በኋላ በከፍተኛ ድምጽ ሶስት ጊዜ አፏጭቶ ሲያጸዳም ኩማ ሶስት የመልስ ቃጨት አሰማው። ከግቢው ለመውጣት የተሰጠ ምልክት ነበር። በእድር ጊዜ ኩማና አሙቶማቲኩ በፍጥነት ወደሱ ሲቀርቡ ተመለከተ። ኩማ ከአጠገቡ ሲደርስ ኩፐር ሥጋ ብሎ ለሊሎች ሞፍሮቹ ‹‹ካርሎስ በፍጥነት እንውጣ ይላችኋል›› አለ። ንግግሩ ግን ከሞፍሮቹ ይልቅ የፊጥኝ የታሰሩት የሙዚየሙ ሠራተኞች እንዲሰሙት ሆን ተብሎ የተቀናበረ አረፍተ ነገር ነበር።

ኩፐርና ኩማ እየሮሩ ከሊሎች ጎደኞቻቸው ጋር በቀድፊያ በስተኧርባ ወደሚገኘው ኮሪደር ወደሚወስደው በር ሲሞክሙ በድንገት፡ ባልጠበቁት ሁኔታ በሩ በሰዎች፡ በእንግዳ ሰዎች ወደሙዚየሙ የሚያመሩ በሚመስሉ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት፡ አምስት ሰዎች፡ ሁለቱ ሲቪል፡ ሶስቱ ዩኒፎርም በለበሱ ሰዎች መሞላቱን ተገነዘቡ። አምስቱም መሳሪያ ታጥቀዋል። ኩፐር የሰዎቹን ግራ የተጋባ መልክ ሲያንብ እሱ፡ ኩማና ሊሎቹም ሞፍሮቹ የፊት ሽፋን ማጥለቃቸውና ያለጥርጥር ሽብርተኞች መሆናቸው በግልፅ እንደሚታወቅ ትውስ አለው። ደሀ በእንዲህ እንዳለ ዩኒፎርም ከለበሱት መካከል አንደኛው በፍጥነት መሳሪያውን አውጥቶ ጥሯል፡ ወዲያው ተኩስ ከፈተ። የመጀመሪያዎቹ ጥይቶች ከኩፐር ሞፍሮች መካከል ሺልድስ የተባለውን በታትነው ዘረሩት። በዚያው ሴኮንድ ኩማ አሙቶማቲኩን እያንፈተፈተው መሆኑን ኩፐር አየ። የኩፐር አሙቶማቲክ በመሣባት ላይ ያሉትን ሰዎች በግራ ወደ ቀኝ እንደግናም ከቀኝ ወደግራ አጨዳቸው። አምስቱም ተነጠፉ። ወለሉን የደም ጅኖ አለበሰው።

አጨዳው በሴኮንድ ተጠናቀቀ። የተኩስ ድምጽ ከአዳራሹ ውጭ የተሰማ አይመስልም። ኩፐር በትልጥና የተረፉት አባሎች እንዲወጡ የሚያዝ

ምልክት ሰጠ። የሚኖችን አስከሬኖች እየዘለለ በበከተፈርባው ኮሪደር አድርገው በቀኝ በኩል በሚገኘው የመጨረሻ በር ለመጠባት ይራኩ ጀመር። እግረ መንገዳቸውን የፊት ሽፋናቸውንና መሳሪያዎቻቸውን ወደ ሻንጣዎቻቸው መመለስ እንዳለባቸው አልዘነጉም።

ከኤግዚቪሽኑ ክፍል ከመትለበት ወጥተው በትርቡ ወደሚገኘው የመዚ የመ መወጫ ተጣደፉ። ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ ከፊት ለፊት በሚመራቸው በኩፐር አካሄድ መሰረት ፍጥነታቸውን ቀንሰው በተቻላቸው መጠን ምንም አዲስ ነገር እንዳልተሰራ ራሳቸውን እያረጋገ የቪዲዮ መቅረጫውን ያለ ችግር አለፉ። በቪዲዮ መቅረጫው ከሚገኙት መነከል ያደረጉትን መጠር ጠር ቀርቶ ቀና ብሎ ያያቸው እንኳ አልነበረም። ኩፐር ረጅም የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰ። የተከስ ድምፅ እንድም ከርቀት የተነሳ አልተሰማም፣ ወይም ሰዎቹ ቢሰሙም በግዚ ውስጥ መተከሱ አልተጠረጠረም።

ርጋታቸው ሳይለያቸው የአትክልቱን ስፍራ ተሻግረው ሁለት ፎርድ አውቶሞቢሎች ወደቆሙበት አመሩ። ተውኑቱን በሾፌርነት የሚሰሩት ጆጋናና ከሩፐንስኪ መኪናዎቹን ተደግፈው በግዴለሽ አኳኋን ቆመዋል።

ኩፐር ከለሎቹ ተደም ብሎ ሾፈሮቹ ወደ መኪኖቻቸው እንዲገቡ ምልክት አሳያቸው። ከኤግዚቢሽኑ የወጡት ጎብኚዎች ለሁለት ተከፍለው በሁለት አውቶሞቢሎች ሲገቡ አፍታ አልፈጀባቸውም።

ጆጋኖ በጥንት የመኪናውን ሞተር ሲያስነሳ ከጎኑ የተቀመጠው ኩፐር ከኋላ ወደተቀመጡ ሾፍሮቹ ዞር ብሎ ‹‹እኔያ ከወታደሮቹ ጋር የነበሩት ሁለት ሰዎች እንማን ናቸው?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹አንደኛው የእስራኤልን ጠቅላይ ሚኒስትር ይመስላል›› አለ ላፈር የተባለው።

‹‹የታባቱ›› አለ ኩፐር ‹‹በዚያ ላይ ሽልድስን ማጣታችን። ጆጋኖ ፍጥነት። ትርስ አልባውንና ደም ያዘለለትን መዚያም ከጀርባቸው ጥለው ገሰገሱ።

ተልዕኮው ግቡን መታ።

* * *

ካይሮ ላይ ጊዜው ሰአይን መያዝ ጀምሯል። በካይሮ አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የኮፊሰ ቢሮ የተቀመጠው ኒክ ራምሲ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር አውሮፕላን እስካሁን ባለመድረሱ መገረም ይዟል። ሰንቱ ላይ ሆኖ የማዕዕ ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ የንግድ ሚኒስትሩና ባማረ ዩኒፎርም የተንቆጠቆጠው የክብር ዘብ ለረጅም ጊዜ እንግዳውን በመጠባበቅ ተግተረው መቆየታቸውም አስደንቆታል። በመጨረሻው ግን ፕሬዝዳንቱና ሌሎች ባለስልጣኖች ስፍራቸውን እየለቀቁ መሆናቸውንና በተጠንቀቅ የነበረው የክብር ዘብም ዘና ማለት መጀመሩን አስተዋለ። ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ አለመድረስ እስካሁን የተሰጠ መግለጫ የለም። የጊላ ጓላ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአገራቸው የተነሱት ከተያዘላቸው ፕሮግራም ሁለት ሰዓት ዘግይተው መሆኑና በአሮር ጊዜ ካይሮ እንደሚገቡ ሰማ። ሌላ አንድ ሰዓት አለፈ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አውሮፕላን ግን ዳናው ጠፋ።

ያልተለመደ ነገር ነበር። ለጋዜጠኞች የተረበ ሌላ መግለጫ የለም።

ራምሲ ከኮፊሰ ቢሮው ወጥቶ ወደ ኩጣ ለመሄድና በተያዘለት ሆቴል እረፍት ለማድረግ ሊወሰን ምንም ያህል አልተረዳም። ድንግት ‹‹እንተንክ ነው ኒክ?›› አለው አንድ ድምፅ። ዞር ሲል አንድ ፊቱ ትጭጭ ብሎ የተጨማተረ ወጣት ወደሱ ሲያመራ አየ። ከወጣቱ ጋር ባንድ ወቅት እንደተዋወቁና ለንደን የሚታተመው ታይምስ ጋዜጣ ሪፖርተር መሆኑን ስመ-ም ብረያን ኢንደርስ እንደሆነ አስታወሰ።

ኢንደርስ መ-ሰ ለመ-ሰ ፊግግ ብሎ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ ‹‹እንኳን ቶናችሁ. . . ባልደረባችህ ኒውዮርክ ላይ እንደግና የኮፊሰ ቁንሙ ሆነዋል›› አለው። ራምሲ ነገሩ ስላልገባው እንግሊዛዊውን በጥያቄ አስተያየት ተመለከተው።

‹‹ኒውዮርክ ሪከርድ ላተመው ዜና እንኳን ደስ ያለህ። ከአፍታ በፊት በቴሌግራም ነው የሰማሁት። እስካሁን የሆነውን አታውትም ማለት ነው?››

‹‹ምኑን ነው የማውተው?››

‹‹አሃ፣ አታውቅማ. . . እንግዲያውማ ላንተ ለማብሰር የመጀመሪያው ልሁን። ዛሬ ረፋዱ ላይ የእየሩሳሌሙ የሙት ባህር ትርሳትርስ ኤግዚቪሽን በካርልሶስ ፋኖዎች ተወሮ ነበር። ትርሱን በሙሉ ዘርፈውታል። እጅግ የሚያስደንት ጀብዱ ነበር። መቼም በህይወቱ እንዲህ ያለ ወኔ የተሞላበት ጀብዱ ሲፈፀም ሰምቼ አላውቅም።››

ራምሲ ከመገረሙ የተነሳ ሳይታውቀው ከተቀመጠበት ብድግ አለ ‹‹አያታመንም›› አለ።

‹‹በግዛ ራስህ ጋዚጣ የመጀመሪያውን ገፅ የሞላው ትኩስ ዜና የቱ ሆነና ነው የማታምነው? የዜናው ብቸኛ ባለቤት ሪኮርድ መሆኑ በአለም ዙሪያ እያስተጋባ ነው።››

ራምሲ በመስኮት ወደውጭ እየተመለከተ ራሱን ከፍ ዝቅ እያደረገ ‹‹ለዚህ ይሆናል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያልመጡ›› አለ፣ ‹‹ምናልባት ዝርፊያውን ሲሰሙ ጉብኝታቸውን አስተላልፈውት ይሆናል።››

‹‹አይመስለኝም፣ ግብጾች እንደነገሩኝ እንግዳው ከአንድ ሰዓት በፊት ጉዞ ሳይጀምሩ አይቀሩም።››

‹‹ምናልባት ድርጊቱ አውሮፕላናቸው ላይ እንዳለ በቴሌግራም ተነግሮአቸው ለመመለስ ወስነው እንደሁስ?››

ኢንደርስ በጥርጣሬ ፊቱን ቁጥር አድርጎ ‹‹እኔ እንጃ›› አለ።

‹‹እኔም እንጃ›› ብሎ ራምሲ በተልድ የእንግሊዛዊውን ሪፖርተር ትከሻ ቸብ ካደረገው በኋላ በሰገነቱ ለመውረድ ጉዞ ጀመረ። ‹‹ምን አይነት ጎደሎ ቀን ነው? የሙት ባህር ትርሶች መዘረፍ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አድራሻ መጥፋት የነገሩ ስር ምን ይሆን?››

እንድ የመጭትሄ ሃሳብ ብልጭ አለበት። የነገሩን ሥር ምናልባት ኤድዋርድ አርምስቱድ ያውት ይሆናል።

* * *

‹‹ምን ምን ምን?›› አለ ኤድዋርድ አርምስቱድ፣ ጆሮዎቹን

እስኪጠራጠር ድረስ በሰማው ነገር ከመደንገጡ የተነሳ ፊቱ ቲማቲም መስሎ ከወንበሩ እየተነሳ።

ሃሪ ዴትዝ የአለቃው ድንጋጤ ሳይገባበት አልተረፈም፣ ከወንበሩ ተፈንጥሮ ሊነሳ ምንም አልተረፈውም።

‹‹ተኩሰው መቱት?››

‹‹የእስራኤሉን ጠቅላይ ሚኒስትር በጥይት መቱት ነው የምትለኝ? አቆሰሉት?››

‹‹ያለጥርጥር። የአገራቱ መንግስታዊ መግለጫ ቁስለኛው ወደ ሆስፒታል መወሰዱን አስታውቋል። መንግስታዊ መግለጫ ዝርዝር ዘገባ ባያቀርብም ራሴ ባገኘሁት ምንጭ መሰረት ግን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁስለት ከባድ ሳይሆን አይቀርም።››

‹‹ይህን የሰማኸው ከፓኖኛ ነው?››

‹‹አዎ ከጉስ ፓኖኛ። የቅርሳ ቅርሱን መውጣት ሲያትትልኝ ስለተኩሱ ሊነግረኝ አልፈለገም ነበር። ባንድ በኩል ከፋኖዎቹ አንዱ ለኛ ሪፖርት እንደሚያደርግ እንዳይታወት በመስጋት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተኩሰው የጣሉት ማንን እንደሆነ በውል ባለማወቃቸው ሊሆን ይችላል። የእስራኤልን መንግሥታዊ መግለጫ እንደሰማ ግን እንደገና ደውሎ አንዳንድ ዝርዝሮችን አቀረበልኝ።››

‹‹ምን አይነት ዝርዝሮች?›› ኤድዋርድ ጠየቀ፣ ‹‹እንዴት ሊሆን ቻለ?››

ሃሪ ዴትዝ ጉርሮውን ሰሎ ከፓኖኛ የሰማውን ተረከለት። በመጨረሻም፣ ‹‹ስንቱ ሞተው ስንቱ እንደቆሰሉ ኩፐር በውል የሚያውቀው ነገር የለም ይላል ፓኖኛ። ነገሩ የተፈጸመው እጅግ በፍጥነት ነበር።››

‹‹እና ከሽልድስ በስተቀር ኩፐርና ጓደኞቹ በሰላም ወጡ?››

‹‹ያለጥርጥር!››

ኤድዋርድ ራሱን ነቀነቀ። ‹‹ትልቅ ግልግል። ግን ሽልድስን ትተው መውጣታቸው. . .››

«አማራጭ አልነበረም። እያንዳንዷ ሰከንድ ዋጋ ነበራት።»

«ለመሆኑ መታወቂያ ነገር ይዘው ጥሯል?»

«በፍራሽ። ማናቸውም ቢሆኑ መታወቂያ የሚሉት አልያዙም።»

ኤድዋርድ አሁንም ራሱን ነቀነቀ። «ደም እንዲፈስ አልፈለግም ነበር።»

«አማራጭ አልነበረም። ራስን ማዳን የግድ ነበር» ሃሪ መለሰ።

«ግን ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን ይሆናል?»

«የእስራኤል መንግሥት ካርሎስን ተጠያቂ አድርጓል።»

ኤድዋርድ ከንፈሩን ነከሰ። «ያሳዝናል። የጠቅላይ ሚኒስትሩን መቁሰልም ቀደም ብለን ለብቻችን ማተም አለመቻላችን ያሳዝናል። ግን የተከሰተን ዝርዝር በሚመለከት ማንም ሊያውቅ አይችልም አይደለም?»

«ከቮ በስተቀር ማንም» አለ ሃሪ፡ «ግን ይፋ መግለጫ ከመሰጠቱ በፊት ካወጣን ሊያስጠረጥረን ይችላል።»

ኤድዋርድ ጠረጴዛውን በቡጢ ደልሀ አጽረጠው። «አትቀልድ፡ ከኛ ቀድሞ ማንም እንዲያትም አልፈቅድም። ጊዜ የምንሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ ሊላ ኮከብ ኤድዋርድ፡፡ ሊላ ኮከብ ሪኮርድ። ሊላ ኮከብ ሞግድ። *የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር አጅባሰል በዝርዝር*፡፡ በጋዜጣየ የመጀመሪያ ገጽ ላይ የአጭር ታሳች ዜና፡

ከወንበሩ ተነስቶ እየተንጎራደደ ጠረጴዛውን ሲዞር ሃሪ ዴትዝም ብድግ አለ። ኤድዋርድ የሃሪን ክንድ ጭብጥ አድርጎ «ንቢችንን አናቱም ሃሪ፡ ይህች ምድር ከእግራችን ስር ናት። ምን ጊዜም ከእግራችን ማፈንገጥ የለባትም» አለው።

«እንዳልከኝ አደርጋለሁ አለቃ፡ ግን ዘጋቢ የማደርገው አሁንም ማርክ ቭራድኖን አይደለም? በቅርብ ትርስ ዝርፊያ ላይ ዘጋቢአችን እሱ ስለነበረ በተከሰም እሱን ማድረግ ይበልጥ ያሳምናል።»

‹‹ጎሽ ሃሪ፣ ማርክ ብራድሾ ኮከብ ሪፖርተራችን እንደሆነ ማቆየት አለብን።››

‹‹እሽ። ግን አንድ ሌላ ነገር. . .››

‹‹ምን?›› ኤድዋርድ በጥርጣ አይኑን አፈጠጠ።

‹‹ራምሲን ምን እንበለው?››

‹‹አሃ፣ እሱን ከካይሮ ብናወጣው ይበጃል። ባስቸኳይ ፓሪስ ሂዶ ከቨክቶሪያ ዊስተን ጋር ስራ እስክንሰጣቸው እንዲጠብቅ ደውልለት። በትርቡ አንድ አዲስ ኮከብ ዜና ለማምረት አስቤአለሁ።››

ሃሪ ዴትዝ እንደማትማማት አያለ ‹‹አንድ ነገር ሳስብ ነበር፣ አለቃ›› አለ፣ ‹‹በምርቶቻችን መካከል ጥቂት ጊዜ መስጠት አይገባንም? ማለቴ እንዲህ የተከታተለ ነገር. . .››

አለቃ አላስጨረሰውም። ‹‹ደሞ ከመቼ ወዲህ ነው ይህ ማመንታት የሚሉት በሽታ የጀመረህ ሃሪ?›› አለው በንቀት።

‹‹በእውነት ማመንታት አይደለም። ግን. . .›› አሁንም አለቃ አቋረጠው።

‹‹እትዱን ለኔ ተውልኝ›› አለው፣ ‹‹አለምን አንድ ጊዜ እንደትርጓት ኳስ ማንቀርቀብ ከጀመርክ እረፍት ልትሰጣት አይገባም።››

10

‹‹ኒክ›› አለች ቨክቶሪያ ራምሲ አጠገቧ እንደደረሰ። ቢጮሩ ቻርልስ ደኅል አውሮፕላን ማረፊያ ቨክቶሪያ ልትተበለው መምጣቷን ሲያይ ደስታ አስፈንድቆት በሚፍለቀለት የናጥቆት ፈገግታ ለስማት ተንደርድሮ ከሄደ በኋላ ፊቷ ላይ ባነበበው ኮስታራ ገጽታ ደንግጥ ብሎ ቆመ።

‹‹ምን ሆነሻል?››

‹‹ኒክ፣ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር. . . ሞቱ።››

‹‹ሞቱ?››

‹‹ቀዶ ጥገና ሲደረግላቸው ሞቱ።››

‹‹ወቸ ጉድ!›› አለ ራምሲ በረጅሙ ተንፍሶ። ‹‹ከየት ሰማሽው?››

‹‹የፈረንሳይ ቱሊቪሽን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆስፒታል ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ራሳቸውን ማወቃቸውን አውርቷል። የመጣ ባሀር ቅርሶች በመያዣነት መዘረፋቸውና ዘራፊዎቹ ቅርሶቹን ለመመለስ አምስት የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት አስረኞች እንዲፈቱላቸው መጠየቃቸው ይነገራቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን ‹በጭራሽ! በሚሊዮን አመት ውስጥ እንኳ የማይሞከር ጥያቄ ነው። ቅርሶቹ ለሁላችንም አንጡራ ንብረቶች ናቸው፣ የሕገባችን ደህንነት ግን ከሁሉም የላቀ ብርቅ ንብረታችን ነው። ዛሬም ሆነ ወደፊት በዚህ ጉዳይ አንደራደርም› አሉ። ከዚያ በኋላ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ወሰዷቸው፣ ወዲያው ሞቱ።››

‹‹ጠቅላላ ታሪኩ ይኸው ነው?››

‹‹የፊረንሳይ ቴሌቭዥን መዘየሙ ውስጥ የተፈጸመውን ድርጊት በዝርዝር አትቷል። የዜናው ምንጭ ተደርጎ የተጠቀሰው የአሜሪካ ጋዜጣ ነው።››

‹‹ማለት ኒውዮርክ ሪኮርድ?››

‹‹አም።››

‹‹ዜና ዘጋቢ ማርክ ብራድሾ?››

‹‹አም።››

‹‹አሃ›› አለ ራምሲ። የገባው ሚስጥር ግን አልነበረም።

‹‹ግራ የሚያጋባ ነው›› አለች ቪክቶሪያ ከመናኸሪያው ወደ አግረኛው መንገድ በማምራት ላይ እንዳሉ።

‹‹በዚህች አለም እየተፈፀመ ያሉ ብዙ ነገሮች ግራ የሚያጋቡ ይመስለኛል›› ሲል መለሰላት።

ጥቂት ራቅ ብሎ ሲጋራ ወደሚያጨስ ሾፌር በእጅዋ እያመለከተች ‹‹ተደም ብየ ልጠብቅህ ስለፈለግሁ ሚርሴደስ ተከራይቼ ነው የመጣሁት›› አለች።

‹‹ግንዘብ አባክኛ ሆነሻላ›› አላት፣ አነጋገሩ በፈገግታ ነበር። እዩ ግን አሁንም ገጽታዋ እንደተከሳተረ ነው።

‹‹የኤድዋርድ ግንዘብ ነው። እሱ ደግሞ በሪኮርድ ገዘ. በግንዘብ ላይ ግንዘብ እየቆለለ ነው።››

‹‹ግንዘብ ሲያንሰው ነው›› አለ ራምሲ ሳቅ ብሎ።

‹‹ኤድዋርድ አርምስቱድ፣ በጠሩት የማይሰማ ዝነኛ፣ የሁሉም ሰው መነጋገሪያ እየሆነ ነው።››

‹‹ይህም ይገባዋል።››

‹‹እድሜ ለማርክ ብራድሾ።››

ጫን ያለው አኒንግሯ ትኩረቱን ስለሳበው አፍጥጠ ተመለከታት። ቪክቶሪያ የራምሲን ክንድ ያዝ አድርጋ ‹‹ኒክ ይሀን ሁሉ የተምታታ ነገር ልንወያይበት እፈልጋለሁ። ብንነጋገርበት አይሻልም?›› አለችው።

የመነጋገሪያቸው ርዕስ ምን እንደሆነ መጠየቅ እንዳለበት ቢያውቅም ራምሲ ጥያቄውን ለማቅረብ በአካልም ሆነ በመንፈስ የተዘጋጀ ሰው አልነበረም።

መኪናዋ አጠገብ ስለደረሱ መነፈር ነበረባቸው። ራምሲ የጓለኛውን በር ለቪክቶሪያ እየከፈተ ‹‹ጥሩ›› አለ፣ ‹‹እንነጋገርበታለን። ግን አሁን አይደለም። የካይሮን አቧራ አራግፌ ልብስ መተየር አለብኝ።››

‹‹እውነቱን ነው የምልህ ኒክ።››

‹‹አኔም።››

‹‹ግን አሁን በሪኮርድ ወኪል ቢሮ አንድ ጉዳይ ስላለኝ መንገድ ላይ እወርዳለሁ። አንተ ሆቴልህ ገብተህ ተጣጥበህ ልብስ ተይረህ በቻምፕዝ-ኤሊስ ካፍቴሪያ በረንዳ እንገናኝ። የተደመ ይጠብት።›› አለችው።

* * *

በካፍቴሪያው በረንዳ ቀድማ የተገኘችው ቪክቶሪያ ነበረች። ከበረንዳው ብዙም ሳይርት በሚያድርጠው ሰፌ አውራ ጎዳና ጠርዝ ባለው የእግረኛ መንገድ ወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡለው ህዝብ ብዛት እያሰገረማት ፊነ ስትመለከት ትቆይና ሃሳቧ ሲመሰስ ከኒክ ራምሲ ጋር ልትነጋገርበት ስላሰበችው ጉዳይ ታሰላስላለች።

ብዙም ሳይዘግይ ኒክ ራምሲ ምንም እንኳ ሩት ቢሆንም ከፊት ለፊት ከሚጓዙት ፊረንሳውያን እግረኞች ዘለግ ያለ ስለነበር ወደቧ ሲመጣ ለየችው። ራት እንደሚጋብዛት ብትጠራጠርም እቧ ግን ሆድ ሆዷን የሚበላትን ጉዳይ እዚው ቦታ ላታማክረው የትም ላትሄድ ወሰናለች።

ከእግረኛው መንገድ በመውጣቱ ሳይሆን አይተርም ለአፍታ ልብሱንና ጽዳቱን አስክትለየው ድረስ ቀረብ ብሎ ታያት። ይሁንና ወደቧ እየመጣ

አለመሆኑ ታወቃት። ቆሚል ወይም ሰዎች አስቱመውታል። እንድ ግዙፍ ሰው አስቱሞ እያነጋገረው መሆኑን ለማወት ጊዜ አልወሰደባትም። እንዲያውም ሊላ አጠር ያለ ደንደሳም ሰው ከጀርባው በኩል እየተረበሙ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በክርኑ እየጎሸመው መሆኑን ተረዳች። ከዚህ በኋላ የሚደረገው እንዱም አላመለጣትም። ሁለቱ ሰዎች የራምሲን መንገድ በግተው ከእግረኛው መንገድ ወደ መኪናው ጎዳና ይገፈትሩታል። ድርጊታቸው ግልጽ ባይሆንም ሰዎቹ ራምሲን በግድ ወደ እንዲት መኪና እየወሰዱት ይመስላል።

ሁኔታው አላምርሽ ያላት ቪክቶሪያ ከቦርሳዋ ብዙ ዝርዝር ሳንቲሞች አውጥታ ጠረጴዛው ላይ ከዘረገፈቻቸው በኋላ የጓደኛዋን ሁኔታ መከታተል ያዘች።

ራምሲና ሁለቱ ጉልበተኞች መኪናዋ ጎን ደርሰዋል። ራምሲ ያለጥርጥር መኪናዋ ውስጥ እንዲገባ እየተገደደ ነው። ምናልባትም መሳሪያ ተደቅኖበታል። ራምሲ እየታፈነ ነው።

እግረኞች እንደልቧ ባያራምዱትም ቪክቶሪያ ወደመኪናዋ በሩጫ ታመራ ጀመር። ደረሰችባቸው።

ከፊት ወንበር ቮፌሩ ተቀምጧል። ከኋላ ደግሞ ራምሲን ከግራና ከቀኝ አድርገው አየቻቸው። ነገር ግን ልትጣራ አፏን ለመክፈት እንኳ ጊዜ ከማግኘቷ በፊት ውሃ ሰማያዊዋ ሲትረን አውቶሞቢል ባለ ኃይሏ እየጓሪች መንገዱን ይዛ ተፈተለከች። ምን ማድረግ እንዳለባት በሃሳቧ ተደበላለቀባት። ለወታደር ለመንገር ወሰነች። መንገዱ ላይ የሚታይ ግን አልነበረም። እንድ ነገር ትዝ አላት። በሪኮርድ ጋዜጣ ስራ እንደጀመረች ሚስተር ኤድዋርድ ምንም ይሁን ምን አዲስ ነገር ስታይም ሆነ ስትሰማ ወዲያውኑ፣ ከሁሉም በቅድሚያ ለሚያሰራት ድርጅት ለኒውዮርክ ሪኮርድ ማስታወት እንደሚጠበቅባት ከወቀሳ ጋር ያስጠነቀቃት ታወሳት።

ወዲያው ግን ሊሉኝ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ተተራመሱ። ኒክ ራምሲን ሊጠልፉ የሚፈልጉት እነሱ እንማን ናቸው? በምን ምክንያት? በመያዣ ለማሰር? ከሊላ ሰው፣ ለምሳሌ ከእንድ ሃብታም አሜሪክዊ ጋር ተምታ

ቁባቸው ይሆን? ለመሆኑ እነሱስ እንማን ናቸው? የሚወስዱትስ የት ይሆን?

እኒህ ጥያቄዎች ነበሩ ባንድ ውሳኔ ላይ እንድትሆና ያደረጓት። እንደእድል ሆኖ በዚያው ቅጽበት አንድ ታክሲ ከአጠገቧ አንድ ተሳፋሪ ለማውረድ ቆሞ አለ። ባለታክሲውን የት እንደሚሄድና ምን ያህል እንደምትከፍለው በመጠየቅ የሚባክን ጊዜ አልነበረም። ከውስጥ የነበረው ተሳፋሪ የጓለኛውን በር ከፍቶ ከወረደ በኋላ በሩን መልሶ ከመዝጉቱ በፊት ቪክቶሪያ በፍጥነት ዘው ብላ ገባች።

ሪዙ የተንሸራተተው የታክሲ ሾፌር ከአንጉቱ ሠር ብሎ በፈረንሳይኛ «የለም የለም፣ አይሄድም» አለ፣ «ለዛሬ በትቶኛል። ከእንግዲህ ወደቤቱ ነኝ።»

ቪክቶሪያ ወደፊት አሰገገች። ከንዱን በሁለቱም እጇ ጨብጣ እያወዛወዘች ተማፀነችው። «መጀመሪያ አዳምጠኝ ሙሴ፣ ነገሩ እጅግ በጣም አስቸኳይ ሆኖብኝ ነው። ሃምሳ ፍራንክ እከፍላለሁ።» እንዲህ እየተናገረች ወደፊት አመለከተች። «እዚያ መብራት ያለቆማት ሰማያዊ ሲትሮን ትታይሃለች? ሶስት ሰዎች ጓደኞቼን ይዘውታል። ጠልፈውታል።»

ሾፌሩ ወደፊት ተመለከተ። «ይሀን ጉዳይ የሚከታተለው ፖሊስ ነው.....»

አላስጨረሰችውም። «ልክ ነህ፣ ግን ጊዜ የለም። መጀመሪያ የት እንደሚወስዱት ማወቅ አለብኝ። ባክህ፣ ሙቶ ፍራንክ ተጨማሪ እከፍላለሁ።»

የታክሲው ሾፌር እጁን ሰጠ። «መቼስ ላንቺ ስል አመቤት፣ አብረን እንከተላቸዋለን።»

«አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ። ግን አደራ እየተከተልናቸው መሆናችንን እንዳያውቁብን።»

«ባኔ ይሁንብሽ፣ አመቤት።»

* * *

ይሆን ያህል ለረጅም ጊዜ መጨፈን አያንን መረበሽ ብቻ ሳይሆን አእምሮንም ያውክል።

ከተጠለፈበት ደቂቃ አንስቶ አሁን በማያውቀው ሰፍራ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ኒክ ራምሲ ለቅጽበት እንኳ ከመገረምና ከግራ ከመጋባት በስተቀር ትንሣት የፍርሃት ምልክት አልታየበትም። ጠለፋው የተፈጸመበት በስህተት እንደሆነና ጠላፊዎቹ ማንኑቱን ሲረዱ እንደሚለቁት ሙሉ ለሙሉ አምኗል። በመኪናቸው አስገብተው ሰፈሙን አውራ ጎዳና ተንዘው እንደጨረሱ ጠላፊዎቹ ራምሲን ከወንበሩ ስር እንዲተኛ አዘዙት። ትዕዛዙን ለማክበር ቢያመነታም ብብቱ ስር በደቸንበት ሽጉጥ አስገዳጅነት ከእግራቸው ስር ተኛ። ወዲያውኑ በጥቁር ጨርቅ አይኑን አጥብቀው አሰሩት።

ጥቁም መሳሳታቸውን ለማስረዳት በሞክረበት ጊዜ ሁሉ ማስፈራሪያ በተተላተለበት ኮና ካፈኑት ሰዎች አንደኛው በእንግሊዘኛ አፉን እንዲዘጋ ያዝዘዋል። በዚህ ሁኔታ ከኋለኛው መቀመጫ ግራ ቀኙን ከተቀመጡት ከሾፌሩ መካከል አንዳቸው እንኳ ከሱ ጋር ቀርቶ እርስ በርሳቸው ሳይነጋገሩ ነበር የተጓዙት። በጉዟቸው ወቅት በመንገዱ ዳር የነበረው የሰው ድምጽ እስከመጨረሻው ድረስ ዐጥ ባለማለቱ ራምሲ ከመሃል ከተማ ብዙም እንዳልራቁ ገምቷል። ቪክቶሪያ ምን ያህል በተጠሮው ቦታ ልትጠብቀው እንደምትችልና ከምን ያህል ትዕግስት በኋላ የተረበችን ምክንያት ለማወት እንደምትሞክር ሲገምት ሞክረ። እሱ በያ ቦታ ቢሆን ምን ያደርግ እንደነበር አሰላሰለ። ተጠለፈ የሚል ሀሳብ ምንም ቢሆን በአእምሮዋ አይጣም። ለምን ጉዳይ ይጠለፋል ብላ ትጠራጠራለች?

ከመኪና አውርዶው ጥቂት ካስጓዙት በኋላ ሶስት የድንጋይ ደረጃዎችን ወደ ላይ አወጡት። ከአየሩ መሞቅ መሰወጥ ከውጭ ወደቤት መግባቱን ተረዳ። ከዚህ በኋላ ብዙ ክፍሎችን ያለፈ ይመስለዋል። በመጨረሻው በአንድ ክፍል ውስጥ አስገብተው እንጨት ወንበር ላይ አስቀመጡት።

ከዚህ በኋላ ነበር አይኑን የጨፈኑበትን ጨርቅ የፈቱለት። በብርሃን ነፀብራቅ አታወራለሁ ብሎ ሰግቶ ነበር። አይኑ ሲገለጥ የጠበቀው ግን ከተሸፈነበት እምብዛም የማይሻል ጨለማ ነበር። ሰፋ ላለው አና ክፍል

ብርሃን የምትሰጠው የራስን መብራት የመሰለች አንዲት አነስተኛ አምፑል ብቻ ነች። በደብዛዛው ብርሃን እየታገዘ ራምሲ በተጥታ ከፊት ለፊቱ የቀመጠ አንድ ሰው በፈገግ እየሳቀ ሲመለከተው አየ። ቀስ በቀስ ከዚህ ሰው ግራና ቀኝ የተቀመጡ ሰዓት፣ አራት ሰዎች መኖራቸውን ሊለይ በቃ።

የራምሲ አይን ከፊት ለፊቱ ወደተቀመጠው ሰው መለሰ አለ። በሰላሳዎቹ መካከለኛ ዘመናት የሚገኝ ተጥ ብሎ ሰፋ ያለ አፍንጫ፣ የሳጂታዱ ጉንጮችና ደንስ ያሉ ከንፈሮች ያሉት ሰው ነው። ፊቱ ከሻዋ ከመሠኑ የተነሳ በትርቡ ብዙ ክብደት የቀነሰ ይመስላል።

ይህ ሰው ረጋ ባለ ወፍራም ድምፅ «እንኳን ደህና መጣህ ሚስተር ራምሲ» አለው። «ብዙም እንዳላስከፋንህ ተስፋ አለኝ።»

«ምንድነው ይህ ሁሉ? ምን እያነት መተለድ ነው?» ራምሲ ትንጣት ሳይረበሽ ጠየቀ።

«ቀልድ እንኳ አይመስለኝም» ነበር የሰውየው መልስ።

«ምንድነው የሚሰራው? እናንተ እነማን ናችሁ? የት ነው ያመጣችሁኝ? ከኔ የምትፈልጉት ምንድነው?»

«አንድ ጊዜ መመለስ የምችለው አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። መጀመሪያ ራሴን ላስተዋውቅህ። ኢሊች ራሚሬ ሳንቺ ማለት እኔ ነኝ።»

ይህን ስም ሲሰማ ራምሲ ጥቂት ጊዜ ተምታቶበት ከቆየ በኋላ ወዲያው ትውስ አለው። «ካርሎስ» ሲል ሥጋት—ሳይታወቀው።

«ሽበርተኛው ብለህ ሙሉ ስሜን ተናገር» አለ ሰውየው እሁንም የፈገግ ስቱ ሳይለየው። «ካርሎስ ሽበርተኛው አይደለም እናንተ ጋዜጠኞች ሙሉ ስሜን ስታስቀምጡ የሰማችሁኝ ማዕረግ?»

ራምሲ ይህን አለምን የሚያንቀጠቅጥ አለም አቀፉ ፋኖ በአድናቆት ተመስጠ ተመለከተው። «ግን ከኔ የምትፈልጉት ነው ያልጣኸኝ?»

«ሚንጋገር ብቻ፣ በቃ ሚንጋገር ብቻ» አለ፣ ካርሎስ።

ራምሲ ግን አላዳመጠውም። «በመያዣ ወይም በተመሳሳይ ነገር

የምትፈልጉትን አግኝን ብላችሁ ከሆነ ተሳስታችኋል። የያዝኸውት ሰው አሜሪካዊ ጋዜጠኛ እንጂ የሚረባችሁ ሰው አይደለም።››

‹‹ማነና ምን እንደሆንክ አማርተን እናውቃለን።››

‹‹እንግዲያውማ ለጨዋታ ነው የያዛችሁኝ። ከኔ ምን ልታገኙ ትችላላችሁ?››

‹‹ነግሬሃለሁ።›› ባረተ ካርሎስ። ‹‹አሮር ታለምልልስ ከምናደርግበት ወሳኝ ወቅት ላይ ነን።››

‹‹ስለምን ጉዳይ?››

‹‹ዘዚያ የግብስብስ ጥርትም፣ በኒውዮርክ ሪከርድ ላይ ስለምታሳሂደው ርካሽ ስራህ።›› የካርሎስ ፊገግታ እንደ እንፋሎት ተነነ። ገራገሩ ፊትና ለሰላሳው እንደበት ኮስታራና ሻካራ ሆነ።

‹‹የኔ ስራ?›› አለ ራምሲ ተምታትበት።

‹‹ያንተ ትጥፈት፣ ሚስተር ማርክ ብራድሾ።››

የራምሲ አፍ ፭ ብሎ ተከፈተ። ‹‹ብራድሾ? ብራድሾ እኔ መስያችኋለሁ? ተሳስታችኋል። ፍፁም ተሳስታችኋል። እንተ ራስሀ ሰላምታ ያቀረብክልኝ ራምሲ ብለሀ ነው። ራምሲ መሆኔን በደንብ ታውቃላችሁ። ካለ በኋላ ጥቂት እትማምቶ ‹‹ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። ፓስፖርቴን ላሳያችሁ እችላለሁ›› አለ።

‹‹ማንም ሰው በፓስፖርቱ ላይ የፈለገውን ስም ሊያስትምጥ ይችላል። እኛ ለምሳሌ ደርዘን የሚሞላ ስም የተጻፈባቸው ደርዘን የሚሞሉ ፓስፖርቶች አሉን። እንተ ማንነታችንን እንደምትመረምር ሁሉ እኛም ማንነትህን መርምረን ደርሰንበታል። የምታደርጋቸውን ታለ መጠይቆች፣ ጉዞዎችና የምትጽፋቸውን ታሪኮች ተከታትለናል። በትርቡ እየተፈጸሙ ያሉትን ተደጋጋሚ ሽብር ፈጠራዎች ካርሎስ ፈፀማቸው እያልክ የምትለክከብኝ ሁሻ ጋዜጠኛ ማርክ ብራድሾ ማለት በርግጥ አንተ እንደሆንክ በተጨባጭ እንዳምን ያደረጉ አያሉ ማስረጃዎች አሉኝ። እጅግ

ብዙ። ለዚህ ነው ካንተ ጋር ጥቂት የምጨዋወትበት ጊዜ መድረሱን ወሰኔ ያመጣህ።››

ፊምሲ ወደኋላው ለጠየ ብሎ ከመቀመጥ ሌላ የሚያደርገው አልነበረውም። ‹‹እመኑኝ፣ እኒያን ዘጣምች በረከርድ ጋዜጣ ላይ ያስፈርኳቸው በጭራሽ እኔ አይደለሁም።››

‹‹የለም፣ የለም›› አሰ ካርሎሰ ነጠት አድርጎ። ‹‹ታሪክቹማ ተፅፈዋል። እንዲያውም የጋዜጣችሁ አዚያ ዜናምች ሆነው ነው ሲወጡ የሰነበቱት። በአለም ዙሪያ ተሰራጭተዋል። ካርሎሰ ለስፖኙ ንጉሥ ጠላፊምች መሰረያ አዘዘ። ካርሎሰ የተዛበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊን ጠሰፈ። ካርሎሰ የሙት ባዘር ቅርሶችን ዘረፈ። አንዳቸውንም እኔ አላደረግሁም። አንዳቸውም የኔን ሰልት አያንፀባርቁም። አንዳቸውም ተቀባይነት ያለው መያጣ አልጠየቁም።››

የፊምሲ የጋዜጠኛ አንደበትም እንዲሁ ተባ።

‹‹የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር አግደዋልስ?›› አለ። ‹‹ቀደም ሲልም የዘኔ ሚኒስትሮችን አፍናችሁ መስጸችሁ ነበር። ምን ማፈን ብቻ፣ ገድላችሁማል።››

‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት ላይ የኔ እጅ ሊኖርበት ቀርቶ አሚኒቡን ያወቅሁትም ከናንተው ጋዜጣ ነው። መያጣ መከፈል በማያውቅ ሀገር ዝርፊያ አዛሂዶ መያጣ መጠየቅ የሞኞች ተግባር ነው። እስራኤል ትርሶቿን ለማስለቀቅ ስትል የተጠየቀችውን መያጣ አልተከበለችውም። ዛሬ ጧት ሊበቹ ጥያቂያቸውን ማንሳታቸውን የእስራኤል መንግስት ትርሶቹን ከሃይፋ ወደብ አጠገብ ከአንድ የፋብሪካ ማጠራቱሚያ በርሜል ውስጥ ሲያገኛቸው እንደሚችል ደውለው አስታወቁ። ጠቅላላ ድርጊቱ የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት ስራ ይመስላል። ነገር ግን በግልፅ ለመናገር በትርቡ ከተፈፀሙት የሽብር ፈጠራ እንቅስቃሴምች መሀከል አንዳቸውም የፖለቲካ አላማ ያዘሉ አይደሉም። ይህም የፖለቲካ ድርጅቶች ያንተሳተሱዋቸው ተግባራት ላስመሠገናቸው አይነተኛ ምልክት ነው። ድርጊቱን የፈፀመው ከፍል አላማው ከፖለቲካ ውጭ ነው። ግንኙቸውም በሆኑ የካርሎስ ድርጊቶች አይደሉም።

ፈጣጣው ሃት ይህ ሆኖ እያለ ማርክ ብራድሾ አስካውን የተፈፀመት ተራ ውንብድናዎች በሙሉ በካርሎስ የተተናበሩና የተሰሩ አድርጎ ዘግቺዋል። ማርክ ብራድሾ አንተ ለመሆንህ የጥፍሬን ቁራጭ ያህል አልጠራጠርም።››

‹‹ሙሉ ለሙሉ ተሳስተሃል ነው የምለው።››

‹‹መቺም አንተና ረዳቱ ናት የምትላት ሴት ሁለታችሁም የኒውዮርክ ሪከርድ ሪፖርተሮች መሆናችሁን አትክዱኝም። እያንዳንዱ ጠለፋና ዘረፋ በተፈጸመበት ወቅት በቦታው እንደነበራችሁም የምትክደበት አፍ የለህም።››

‹‹እኔ የምክደው ማርክ ብራድሾ መሆኔን ብቻ ነው። በርግጥ ድርጊቶቹን ሪፖርት ያደረገው እሱ ነው። እኔ አይደለሁም። የድርጊቶቹ ተጠያቂ አንተ እንደሆንክ ያተተው እሱ ነው። እኔ አይደለሁም።››

ካርሎስ ለጥቂት ጊዜ ዝም ለማለት ተገደደ። ‹‹እንግዲያው ማርክ ብራድሾ አንተ ካልሆንክ ማነው እሱ? ልትጠቁመኝ ትችላለህ?››

‹‹በእውነት አልችልም። እኔ ራሴ አላውቅም።››

‹‹ደኽ እንኳ የማይመስል ነው።››

‹‹ኧረ እውነቱን ነው።››

‹‹እንዴት ልመንህ?›› አለ ካርሎስ፣ ‹‹ወደ መደምደሚያው እንማጣና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንደሰጠሁህ አወቅልኝ። ማርክ ብራድሾ አንተ ካልሆንክ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያየን እንድትነግረው አዝዘሃለሁ›› ካለ በኋላ ካርሎስ የሚተዋለትን ታላቅ ተጠቃሚ ባለ እንደበት ተናገራቸው። ‹‹ከእንግዲህ በፊጠራ ውሸትህ የኔን ስም እንድ ጊዜ እንኳ ብታስገባ እንድ ሐሙስ በህያወት እንደማላቆይህ አወቅልኝ። ሚንትላትህን አፈንድቼ አይብህን አይልሃለሁ። ያንተን ብቻ አይደለም፣ የምታስክትላትን ሴትህን እንጎል ባልፈጠፍጠው እኔ አይደለሁም። እያጸመጥክኝ ነው?››

‹‹ሰማሁ›› አለ ራምሲ በረጅሙ ተንፍሶ። ‹‹ግን ማርክ ብራድሾ እኔ ባልሆንስ?››

‹‹እሱ የራስህ ችግር ነው። ብልህ ከሆንክ ግን እኔ የምመክረህ ሰውየውን

አማኑዝ ማስጠንቀቂያዎን እንድታስተላልፍ ነው። በማንኛውም መንገድ ቢሆን የኔ ስም ከንግዲህ በቶሻሻው ጋዜጣችሁ ብትጠቀስ በሀያውት የለሀም። አንተና ሴትህ።››

‹‹የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ›› ከማለት ሌላ ራምሲ ምን ሊናገር ይችላል? ‹‹የሚተዋወሱ ምንድን ነው?›› ሲል ጠየቀ ተጠለና።

‹‹እንዴት ማለትን?›› ካርሎስ አልገባውም።

‹‹አሁን ምን ልታደርጉኝ ወሰናችሁ?››

‹‹ከንግዲህ አንተን አልፈልግህም። ፍላጎቱ መልእክቱን በግንባር ማስተላለፍ ነበር። እንደግና አይንህን ትጨፍንና ትለተታለህ። ደሞ ይህን ያውነን ሙይይታችንን ቢጋዜጣህ እንዳታሳትመው እጥብቱ እመክርሃለሁ።››

ካርሎስ ከመተመሟው ብድግ ሊል ሲዳዳው የራምሲ ጥሪ ተመልሶ እንዲቀመጥ አደረገው። ‹‹ካርሎስ?››

‹‹ምን ነበር?››

‹‹አንድ ጥያቄ›› ራምሲ ዝም ሊል አልቻለም። የሰውየው ስነ ምግባርና ከአንግሩ የሚሰግመገመው የአመለካከት አቅጣጫ እጅግ የሚያስደንቅና የማይታመን አይነት ነበር። ‹‹አንተ መቼም ሰቱዋር የሚያስቸግሩ ሽብር ፈጠራዎችን የፈፀምህ ወንጀለኛ መሆንህን ጠላው አለም ያመነበት ጉዳይ ነው። ከተወያየንበት ወንጀሎች ጋር የሚያገናኝህ ነገር እንደሌለ አምርረህ እንድትከራከር ያደረገህ ምንድን ነው?››

‹‹የመሥያ ግዴታ›› አለ ካርሎስ ያለወትሮው ኮራ ብሎ። ‹‹የመሥያ ኩራት፣ ይገባሃል? የተፈጠመት ወንጀሎች ከኔ አላማ ጋር የሚገናኙበት ነጥብ የለም። ስሜ እንዲጠራ የምፈልገው ስም ሊያስጠራ በሚገባ ክቡር ጅብዱ ብቻ ነው። የዘመናችን ትክክለኛ ታሪክ የሚፃፍበት ጊዜ ሲደርስ በመሥዋው ዘመን ግንባታ ላይ የተሣፈጥኩት ሚና በአግባቡ እንዲመዘገብ እፈልጋለሁ። ተግባብተናል?››

ራምሲ በአምንታ ከራሱ ከፍ ዝቅ አለ። ካርሎስ ብድግ አለ። ‹‹እንግዲህ

የመጨረሻ ታሊን ልብ በል ሚስተር ራምሲ። መሃል አናትህን በጥይት እርሳስ ሳታስበጠርት ለመሰንበት ልቡና ይስጥህ። ደህና ሁን።›› ከማላሪኒያው የስንብት ታል ጋር ወደጨለማው ገቡ። ተሰወረ።

* * *

ስልኩ ባታጨለበት ወቅት ቪክቶሪያ በጥሳዛ ሠቱል የእንግዳ መቀበያ ክፍል ሁለተኛዋን ኮክቴላ በመጨለጥ ላይ ነበረች። በረጅ ማራቱል ጎዳና የራምሲ ጠላፊዎች የተደበቱበትን ህንፃ አይታ ከተመለሰች በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል ኒውዮርክ ከተማ አሰሪዋን ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቱድን በስልክ ለማግኘት ስትሰፋ ቆይታለች። ኤድዋርድ በሪክርድ ቢሮው የሚገባ የሚወጣበት ሰዓት በውል የሚታወቅ ካለመሆኑ ባሻገር ዐሐፊውም ሠንቾ ረዳቱ ማክ አሊስተር አሳታሚው የት እንዳለ የሚያውቁት ነገር የለም።

‹‹ምናልባት ሃሪ ዴትዝ ያውቅ ይሆናል›› ብሳታል ማክ አሊስተር። ‹‹ሚስተር ሃሪ ከኤድዋርድ ጋር አብሮ ሲመሳ አይቼዋለሁ። ሃሪ ብዙም ሳይቆይ እንደሚመለስ እርግጠኛ ነኝ። ሲመለስ የኤድዋርድን አድራሻ ይነግረኛል።››

የሚታገስ ተልብ ባይኖራትም ቪክቶሪያ ለጥቂት ጊዜ እየተቁነጠነጠች መጠበቅ ግዴታዋ ነበር። ግማሽ ሰዓት ቆይታ ራሷ ሃሪ ዴትዝ ቢሮ ደወለች። አሁንም አልገባም። በራምሲ ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ስላሰበት ለፈረንሳይ ፖሊስ ጣቢያ ደውላ ለማስታወቅ ወሰና ነበር። ከዚያ በፊት ግን ለመጨረሻ ጊዜ ሃሪ ዴትዝ ቢሮ ልትሞክር አሰበች። በሶስተኛ መክፈዋ ላይ የሃሪ ዴትዝን ድምፅ በስልኩ መስመር ስትሰማ ረጅም የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰች።

ነገሩን አጠር በማድረግ ከሚስተር ኤድዋርድ ጋር የምትነጋገርበት እጅግ በጣም አጣዳፊ ጉዳይ ስላላት ያለበትን ቦታ እንዲነግራት ጠየቀችው። ሃሪ ዴትዝ ግን ጥያቄዋን ለመመለስ ሲያቅማማ ከታላት አጣጣሉ አወቀ ችበት። ‹‹አይ እርግጠኛ አይደለሁም፤ ጉዳዩን ለኔ ብትነግሪኝ?›› አላት።

ዘርዝራ ልትዘረግፍለት ከጓጓት በኋላ ድንገት በደመነፍስ ጉዳዩን ከኤድዋርድ በስተቀር ለማንም እንዳትተነፍስ አንዳች ውስጣዊ ውላኑ አሰ

ያጣት።

«ለራሳቸው ባብራራ የሚሻል ስለመሰለኝ ነው» አለችው።

«ሠ. . . ግን ነገሩ አሰቸኳይ ለመሆኑ እርግጠኛ ነሽ?»

«እጅግ በጣም አሰቸኳይ. . . ይመኑኝ።»

«መልካም ቪክ. . . እሰኪ ልሞክር።»

«ያለብትን ቢነግሩኝና እኔ በተጥታ ብደውልላቸው? ማለት ጊዜ ለመቆጠብ።»

«የለም፣ የለም። እኔው ብሞክር ይሻላል። ሊያነጋግርሽ ፈቃደኛ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት መልሶ እንዲደውልልሽ አነግረዋለሁ።»

እመታት የመሰለ ብዙ ደቂቃዎች ካዘገመ በኋላ ነበር የቪክቶሪያ ስልክ ያቃጨለው። መነጋገሪያውን በትጽበት አፈፍ አደረጎችው።

የአለታዋ ድምፅ ቀስ ቢልም ቁጣ የተቀላቀለበት መሆኑ ያስታውቃል። ለሰላምታ እንኳ አልተጨነቀም። «ምንድን ነው እሱ ቪክቶሪያን ምን ይሆን ያህል የሚያሳስብ ጉዳይ አገኘሽ?»

«ስለረበሽኩም በጣም አዝናለሁ ሚስተር ኤድዋርድ፣ ግን አማራጭ በማጣቴ ነው። እዚህ አንድ ችግር ተከስቷል። ኒክ ራምሲ ተጠልፏል።»

«ምን ሆኗል. . . ተጠልፏል?» የቁጣው ቃና በሴኮንድ ለመጀመሪያ የድምፁ ቃና ይመሰክራል። «ምን ምን አልሽኝ?»

«ኒክ ተጠለፈ። በአይኖቼ እያየሁ ከሁለት ሰዓት በፊት ታፍኖ ተወስዷል። ዝርዝሩን በዝርነት ላስረዳም።»

ትንፋሽ በሚቆራረጥ ድምጽ ሁለት ሰዎች በምን ሁኔታ አስገድደው በመኪና እንደወሰዱትና እንዴት ሰዎቹን ተከታትላ ራምሲን ያስገቡበትን ሠንሣ ልትደርስበት እንደቻለች አተተች።

አላታመጣው ጸጥ ብሎ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ በረጅሙ ተንፍሶ

‹‹ጠላፊዎቹ እንማን ይመስሉሻል?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹በፍፁም ላውቃቸው አልችልም።››

‹‹እስካሁን ከጠላፊዎቹ የሰማሽው የለም?››

‹‹አንድም ቃል። ምናልባት ጊዜው አጭር በመሆኑ ይሆናል። ለፈረንሳይ ፖሊስ ባስታውቅ ይሻል ኖሯል? ከሁሉም በፊት አርስዎ ይወቁት ብየ ነው።››

‹‹ፍፁም ትክክለኛ ተግባር ነው ያደረግሽው።››

‹‹አሁንሳ ፖሊስ ማዚያ ላመልክት? የጠላፊዎቹ አድራሻ አለኝ። ሬዩ ማርቱል ጎዳና ህንፃ ቁጥር 12 ነው። ፖሊሶች ነገሩን ሊጨርሱት ይችላሉ...››

ቪክቶሪያ ንግግሯን ጥና ሳትጨርስ፣ ኤድዋርድም ጥና መልስ ሳይሰጥ በመካከላቸው ሶስተኛ ድምጽ ጣልቃ ገባ። ቪክቶሪያ ከአንገቷ መለስ ስትል ራምሲ ራሱ ወደ ክፍሏ ሲገባ አየችው።

‹‹ሚስተር ኤድዋርድ ናቸው?›› ራምሲ ሊያውት ፈለገ። ‹‹ሊለቁኝ ሲሉ ወደ ሌላ አገርታማ እንደሚላወሩ ሲነጋገሩ መስማቱን ንገሪልኝ። እንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ የሚተመው አይመስለም።››

በራምሲ ድንገተኛ አመጣጥ የተወናበደችው ቪክቶሪያ፣ ኤድዋርድ በስልክ ምን እንደሚል ለመስማት ሳትጨነቅ አፏን እንደከፈተች ተጠላፊው የሚለውን አዳመጠች። በመጨረሻ ግን አለቃዋ መስመር ላይ መኖሩ ትውስ ሲላት መነጋገሪያውን አስጠግታ፣

‹‹ሚስተር ኤድዋርድ ራምሲ አሁን መጣ! ይህና ነው›› አለች።

‹‹ምን? መጣ?›› አለ ኤድዋርድ ተምታቶበት።

‹‹ሊያነጋግርዎ ይፈልጋል።›› መነጋገሪያውን እያቀበለችው ቦታ ስትለቅለት ራምሲን ጉንጩ ላይ ሳመችው። ራምሲ መነጋገሪያውን ቸኩ ከድኖ ወደ ቪክቶሪያ ዞር አለና፣

‹‹ዮት መስያውኝ እንደነበር በደንብ አይተሻል ማለት ነው?›› አላት።

‹‹ካንተ ይበልጥ›› አለችው በፈገግታ።

በአድናቆት አፍጥጠ እየተመለከታት ‹‹ምርጥ ልጅ ነሽ›› አላት፡ ‹‹ሻምፓኝ እጋብዝሻለሁ።›› ከዚያም እጁን ከመኪኖገሪያው አንስቶ ወደ ጆሮ ማንዴ አስጠጋው። ‹‹ጤና ይስጥልኝ ሚስተር ኤድዋርድ፡ የደረሰብኝን ከቪክ የሰሙ መሰለኝ።››

‹‹ሰማሁ›› አለ አለታ፡ ‹‹ግን እንደገና ከራስህ ለሰማ አፈልጋለሁ። ማን ነበር የፈለገህ? እንዴትስ ተለተኮህ?››

‹‹ለማመን ያስቸግርሃል›› አለ ራምሲ። ‹‹በካርሎስ ትዕዛዝ በካርሎስ ጭፍሮች ታፍኜ ካርሎስ ራሱ ፊት ተርቢ ነበር።››

‹‹ማን?›› ኤድዋርድ የግላ ራሱን ጆሮ ተጠራጠረው።

‹‹ካርሎስ። ካ—ር—ሎ—ስ።››

‹‹ፋኖው?››

‹‹ቀጥር አንድ ራሱ። ያስጠለፈኝ እሱ ነበር። እንዳነጋግረው ፈልጎ ኖሯል።››

‹‹ብፈጠረህ ለምን?››

‹‹ማርክ ብራድሾ እኔ መስየው ኖሯል። ለጠለፋዎች ተጠያቂው ካርሎስ መሆኑን እየገለጽኩ መጻፌን የምተጥል ከሆነ አንጎሌን እንደሚያፈነዳው ለመንገር፡ ለማስጠንቀቅ ነበር የፈለገኝ።››

ኤድዋርድ ጥቂት ሲያስብ ከቆየ በኋላ ‹‹የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊን መጥለፉንና የመሳት ባህር ቅርሶችን መዝረፉን ይከሳል ማለት ነው?›› አለ።

‹‹በአንዳቸውም እጁ እንደሌለበት ነው የሚናገረው። እንዲያውም እንዲህ ያሉትን ሽብር ፈጠራዎች ተራ ውንብድናዎች ነው የሚላቸው። ይበልጥ ያስቆጣውም በእንዲህ ያለው ርካሽ ተግባር ስሙ መጠፋቱ መሆኑን ጨምሮ ነግሮኛል። ተጀምሮ እስኪጨረስ የሆነውን አንድ ባንድ ባስረዳም ይሻላል›› ካለ በኋላ ራምሲ ከካርሎስ ጋር ያደረገውን ውይይት በዝርዝር

ለአለቃው ይገልፅ ጀመር።

አሳታሚው አፉን እንደከፈተ እያዳመጠ የራምሲን ትረካ ካሰፈረሰው በኋላ ‹‹ይኸው ነው?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹ይኸው ነው።››

‹‹የሚደነቅ ታሪክ›› አለ ኤድዋርድ። ‹‹በዕውፍ ሪፖርት አድርገህ ብታቀርበልኝ በጣም ጥሩ ነው። ባስቸኳይ ለህትመት መብቃት አለበት።››

‹‹በደስታ›› ነበር ራምሲ በሳቅ የመለሰው። ‹‹ግለት፣ እናቱ በጥይት እርሳስ የተበጠረቀ ጋዜጠኛ ሊኖርም ከፈለጉ። አንድ ታል ብተኩስ ግንባሬን እንደሚያበጋልኝ ካርሎስ ታል ገብቶልኛል።››

‹‹የለም፣ የለም፣ ህያውነህ አደጋ ላይ እንዲወድቅ አልፈልግም።››

‹‹በለላ በዙል ግን ካርሎስ የሚገኝበትን ቦታ ለፖሊስ ጠቁመን ካስያዝነው አኔና ቪኪ ሁሉንም ነገር ዘግበን ልናቀርብልዎና ሊያትሙት ይችላሉ።››

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሆነ። ‹‹የለም። ይሀም ጥሩ አይደለም›› ሲል ወሰነ ኤድዋርድ በመጨረሻው። ‹‹ፖሊስ ጆሮ ውስጥ የገባ ወሬ በማግስቱ ህዝቡ ጆሮ ውስጥ ይገባል። ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ አዚያ ቤና አጣን ማለት ነው። የካርሎስን ነገር በታ ለኔ ተውልኝ። የራሴ የግል የፖሊስ ግንኙነት አለኝ።››

‹‹እሽ፣ ራስዎ ይጨርሱት።›› ራምሲ ተስማማ። ‹‹ግን ፈጠን ካላሉ ካርሎስ ያለበትን ቦታ ይተይራል። ሽርታታ ቢጤ ነው።››

‹‹ግዴለህም። ለኔ ተውልኝ።››

‹‹መልካም›› አለ ራምሲ እያመነታ፣ ‹‹ግን በዘኩሊም አንድ የማደርገው ነገር አለ። ምናልባት ካርሎስ አድራሻውን ከለወጠ. . .››

‹‹ነግርኩህኮ ለኔ ተውልኝ።››

‹‹አይታወቅም፣ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው በፍጥነት አድራሻውን ቢለውጥ እኔ ደግሞ ማርክ ብራድሾ ማን እንደሆነና የት እንዳለ ማወቅ አለብኝ። በካርሎስ ላይ ከንግዲህ ዕሁፍ ካሳተመ ለህይወቱ እንደሚሰጋው

መንገር ይገባኛል። ብራድሾን የት ላገኘው እንደምችል ሊነግሩኝ ይችላሉ።››

እንደገና ፀጥታ ሆነ። ‹‹የብራድሾንም ሆነ የካርሎስን ጉዳይ ለኔው ብትተውልኝ ይሻላል።›› አለ ኤድዋርድ በመጨረሻ።

‹‹እንግዲህ እንዳሻም ጌታየ።››

‹‹ሁሉንም ነገር በኔ ላለው›› አለ ኤድዋርድ ቁርጥ ባለ አነጋገር።

‹‹በል እንግዲህ አንተንና ቨክቶሪያን በዓንተ ሰዓት አቆጣጠር ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ መኝታ ክፍላችሁ እንዳገኛችሁ። ነገሩ ከምን እንደደረሰና አዲሱ ስራችሁ ምን እንደሚሆን እደውልላችኋለሁ።›› የራምሲን የመልስ ድምፅ ለመስማት ሳይጨነት ስልኩን ዘጋው።

ራምሲ ስልኩን ሲዘጋ ፊቱ ላይ የሚነበበውን ትራታ ቨክቶሪያ አነበበች። ወደሱ ጠጋ አለች። ‹‹ምንድን ነው እሱ ኒክ? ምን ነበር የሚያወራው?››

‹‹ሁሉንም ነገር ራሱ ሊጨርስ ይፈልጋል። ያለጥርጥር የግሉ የፖሊስ ግንኙነት ሳይኖረው አይቀርም። እኛ ፖሊስ ጣቢያ ካመለከትን ችኩሱን ዜና እንደምናበላሽበት ሰግቷል። እሱ የተጨነቀው ለሚያሳትመው ወሬ ብቻ ነው።

‹‹እኔ የምጨነቀው ደግሞ ላንተ ብቻ ነው›› አለች ቨክቶሪያ ግንባሯን ከስከሳ። ‹‹በካርሎስ ዙሪያ መንከባለል በጎላ ሁጨት አያምረኝም። እራሳችን በቀጥታ ለፖሊስ ሂደን ብናመለክት ነው የሚሻለን።››

‹‹እና ከሰራ መባረር?›› አለ ራምሲ ከተቀመጠበት እየተነሳ። ‹‹የለም፣ አይመስለኝም ቨክ። ኤድዋርድ ራሱ በካርሎስ ዙሪያ ሊንከባለል ከመሰነ ሁጨቱ ምን እንደሚሆን መታዘብ ብቻ ነው ምርጫችን።››

‹‹ብበኩሌ አልስማማም።›› ተቃወመች ቨክቶሪያ።

‹‹ወደድንም ጠላን ምርጫችን ይኸው ነው። እኩለ ሌሊት ላይ እደውልላችኋለሁ ብሏል›› አላት ራምሲ። ‹‹እስከዚያ ምድር ቤት መርዶን የሚጠጣ ልጋበዝሽ?››

‹‹እኔ መጠጥ አልፈልግም። ርበኛል።››

‹‹እንግዲያውስ እንቺ ራት ትበያለሽ። በበኩሌ ከወደ ውሃው ነው ያሰኘኝ።››

* * *

በኪም ነሰቢት አፓርታማ የተንጣለለ ሳሎን ውስጥ ረጅም ጊዜ ሳይንቀሳቀስ ተቀምጠ ያሳለፈው ኤድዋርድ አርምስቱድ ሲነጋገርበት ቆይቶ የዘጋውን ስልክ ግብኑን ይመለከታል። ሃሳቡ ግን ከቪክቶሪያ ዊስተንና ከኪራምሲ ጋር ያደረገውን ንግግር በማውጣትና በማውረድ ላይ ያተኩረ ነበር።

በብዙ ተናት ውስጥ ከኪም ነሰቢት ጋር ፍትር የመሰራት ነገር ድንገት መንፈሱን ስለኮረኮረው ነበር ያለፕሮግራም ከቢሮው ተነስቶ የመጣው። ምኞቱ የተሳካለት የድል ሀይወት ስለተጎናፀፈ ደስተኛ ሰው ነው። የነፈሱ አለም ዛሬ ከኤድዋርድ አርምስቱድና ከተቀጻጮቸው የመ.ያ ጀብዱዎች በስተቀር የሚነጋገርበት ርዕሰ የለውም። እንዲያውም ታይም መፅሔት በሽፋኑ ላይ የዚህን ታሳት የነፈሰ ንጉስ ፎቶ ለማውጣት ጠይቆታል። ይህ ድል፣ ይህ የሀይወት ሰከት ሳይሆን አይቀርም ደስታን አጎናጽፎ ኪም ነሰቢትን እንዲያስታውሳት ያደረገው። ግና ከወጻጁ መኖሪያ ከመግባቱ ሰብሰብ ያለው ነው የሃር ቀሚስ ያጋለጠው ምራት የሚያስውጥ ሞን ተቀበለው። ግና ከመግባቱ ቀዝቅዝ የነበረው ስሜቱ በትዕበት ፈላበት። ይባስ ብሎ ወጻጁ ግና ስታየው ከተጋደመችበት ሶፋ ዘላ በመነሳት ከሙሉ ፈጣታ ጋር በእንዴ ሙሉ ስትታቀፈው ስሜት ሊያሳብደው የደረሰ መሰለ።

ደስተኛ፣ በጣም ደስተኛ፣ እጅግ በጣም ደስተኛ ልታደርገው እንደተዘጋጀች ተሰማው። ይሁን እንጂ ጃኪቱን፣ ሱሪውንና፣ ሻሚውንና ሽሚዙን እስኪያወልቅ ድረስ እሷም ወደገላ መታጠቢያው ሂጻ ሰውነቷን መለታለትና ይበልጥ ዝግጁ መሆን ነበረባት።

ሽሚዙን በግራሱት ላይ ሳለ ድንገት ስልኩ ጮኸ። ሃሪ ዴትዝ ነበር።

ኤድዋርድ በዚያ ሁኔታ ላይ ሁኖ ያን በመሰለ ጊዜ የቪክቶሪያን የስልክ ጥሪ ለመቀበል ተታውሞ ነበር። ሃሪ ዴትዝ የነገሩን አስቸኳይነት ስለነገረው

ብቻ መልሶ ፓሪስ ደወለ፣ እናም እሷን ብቻ ሳይሆን ራምሲንም ሊያነጋግር በታ።

ጋዜጠኞቹ የነገሩት የራምሲ መጠለፍ ጉዳይ ፍፁም ያልተጠበቀ ክስተት ነበር። እናም ምን ማድረግ እንዳለበት ተምታቶበት በአካል ብቻ በወዳጁ ሳሎን ተወዛዥል።

ኪም ቶሎ እንደማትመጣ ለማረጋገጥ ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ተመለከተ። ሽቶው፣ ቅባቱ፣ ሰውነት ማድረቂያና መኳኳሉ ባሞር ጊዜ እንደማይጠናቀቅ ሲረዳ ሌላ የሰለከ ጥሪ ለማድረግ ወሰነ።

ሃሪ ዴትዝ ወደሚኖርበት ሆቴል ደወለ። ወዲያውኑ አገኘው።

«ቪክቶሪያ ዊስተንን ደውየ አነጋገርኳት ሃሪ።»

«እሽ፣ ለመሆኑ ምን ጭጋል ያን ያህል ያጣደፋት?»

ኤድዋርድ ድምፁን ዝት አደረገ። «ነገሩስ እውነትም አጣዳፊ ነበር።»

«ኧረ?»

«ኒክ ራምሲ ፓሪስ ገብቷል። የካርሎስ ሰምች ጠልፈውት ጭጋል።»

«ምን ትተልዳለህ?»

«ቪክቶሪያ ተከታትላቸው ነበር። ካርሎስ የመሸገበትን ህንፃ ደርሳበታለች።»

«ውይ፣ እንዴት የሚገርም ጉድ ነው። ለፖሊስ ብንጠቁም. . .»

«በምድር ላይ ለሚታተም ጋዜጣ ሁሉ ጠቅምን ማለት ነው።» ኤድዋርድ ረዳቱን አቋርጦ ባረተ። «ራምሲም ነገሩን ለፈረንሳይ ፖሊስ ሹክ ሊል ሲል በብዙ ልፋት ነው የከለከልኩት። ይኸማ ጅልነት ይባላል።»

«ፍፁም ትክክል ነህ፣ አለታ። ግን አሁን በካርሎስ ላይ ምን እንሰራ?»

«እስካሁን አልወሰንኩም» አለ ኤድዋርድ ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ። «ለጊዜው ግን ምን እንደምናደርግ እስክንወስን ድረስ ካርሎስን በአይነ-

ቁራኛ መጠበቅ አለብኝ። ለመሆኑ ጉሰ ጥጋኖ የት ነው ያለው?››

‹‹ጥሪሰ ገብቷል።››

‹‹በጣም ጥሩ። አሁኑኑ ደውልለት። ካርሎስና ጀሊቃቹ በረዩ ማርቱል ሀንፃ 12 እንደሚገኙ ንገረው። ከእኩለ ሌሊት በፊት ሀንፃውን ሊለቁ ይችላሉ። ጥጋኖ በሀንፃው አካባቢ እያንዣበበ የካርሎስን ቁራ መከታተል እንዳለበት ትነግረልኛለህ። ታሪኩን ሳይታሰብ በራኮርድ አውጥቼ አዝናን ጉድ በማሰኝበት ወቅት ካርሎስ የት እንደሚገኝ ማወቅ እፈልጋለሁ።››

‹‹አሁኑኑ እደውላለሁ›› አለ ሃሪ፡ ‹‹ግን ያልነገርከኝ ነገር. . ለምን ነበር ካርሎስ ራምሲን ያስጠለፈው?››

‹‹ማርክ ብራድሾ መስሎት። ማርክ ብራድሾ ባልሰራው ድርጊት ስሟን አንስቷል ብሎ ተቆጥቷል። ነገሩ ጸጥመኛ ከተደገመ ራምሲን ወይም ብራድሾን እንደሚገድል ምሏል አለ።››

ሃሪ ክት ብሎ ሳቀ። ‹‹ብራድሾን ሊገድል?›› አለ።

‹‹አለዚያ ራምሲን›› አለ ኤድዋርድ። ‹‹አልሰሚ ራምሲ ብራድሾን ፈልጎ ለማግኘትና ማስጠንቀቂያ ብቻ ሳይሆን ከካርሎስ አካባቢ እንዲርቅ ለመምከር ታጥቆ ተንስቷል። እኔም እንዳሳየው ወጥሮ ጠይቆኝ ነበር።››

‹‹ምን አልከው?››

‹‹የብራድሾን ጉዳይ እኔ ራሴ እንደምከታተለው ነገርኩት። አየህ ሃሪ፡ የራምሲ ነገር ትንሽ አሳስቦኛል። የብራድሾን ነገር እኔ እከታተላለሁ ማለቴን አልደገፈውም። እንዲያውም ተጠራጣሪ እየሆነ ሳይሄድ አልቀረም። ምናልባት በግሉ የነገሩን ውስጠ-ሚስጥር ለማወቅ ይጣጣር ይሆናል። ይሽ ደግሞ ችግር ይፈጥርብናል። ምን ይመስልሃል?››

‹‹ባስቸኳይ ኪጥሪሰ ብታወጣው ይመረጣል፡ እንዲያውም ከአውሮፓ ወደዚህ ብትመልሰው ይሻላል።››

‹‹ልክ እኔ እንዳሰብኩት›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹እንዲህ እናድርግ። ራምሲን ካረፈበት ሆቴል ከሊሊቱ ስድስት ሰዓት

ላይ እንደምደውልለት ነግሬዋለሁ። በኔ ፋንታ አንተ ደውልለት።››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹ፓሪስ ባሉኝ የፖሊስ ግንኙነቶች አማካኝነት ሞክሬ እንደነበር፣ ነገር ግን ካርሎስ አድራሻውን በመለወጡ ሊያገዝ እንዳልተቻለ ትነግረዋለህ። ስለዚህ ሁላችንም ስለራምሲ ህይወት እየተጨነትን ነው ትለዋለህ። ከሰራተኞቻችን የአንዳቸውም ህይወት አደጋ ላይ እንዲወድቅ እንደማንፈልግና ተቀጻሚ ተግባራችን የሪፖርተሮቻችንን ደህንነት ማረጋገጥ እንደሆነ ታስረዳዋለህ። በዚህም መሰረት ለራሱ ደህንነት ስንል ከፓሪስ እንደምናነሳውና ከነገ ጧት ጀምሮ ወደ ዋሽንግተን እንደሚበር ትነግረዋለህ። በዋሽንግተኑ ቢሮአችን ወደ ልዩ የስራ መደብ ልናዛውረው መወሰናችንን፣ በሁለት ሳምንታት ውስጥ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ከእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር የሚያደርጉትን ስብሰባ እጀንዳ በሚመለከት ዘገባ እንደሚያቀርብልንና ከፕሬዝዳንቱም ጋር በሪፖርተርነት ላንልከው እንደማንቀር ታብራራለታለህ። አይመስልህም?››

‹‹ቪክቶሪያ ዊስተንስ? ምናልባት እሷንም ከፓሪስ ብታነሳት ላይበጅ አይቀርም። ጉስ ፓጋኖን ፓሪስ ካስተመጥነው ድንገት ልታየው ትችላለች።››

ኤድዋርድ ጥቂት አሰላሰለ። ‹‹የለም፣ እዚያው ትቆይ። እዚያው ፓሪስ ሆና በቅርቡ ጳጳሱ በሎርድስ የሚያደርጉትን ጉብኝት የተመለከተ ዕውቅ እንድታዘጋጅ እዘዝልኝ። ተግባብተናል አይደለም?››

ሃሪ መልስ አልሰጠም። የትዕዛዙ ብዛት ሳይሆን አይቀርም ‹‹ተግባብተናል›› የሚለውን ቃል ተናግሮ ለሚፈጠረው ችግር ተጠያቂ ሊሆን ባለመፍቀዱ ነው አለ።

‹‹በቃ፣ ለማንኛውም በሃያ ደቂቃ ውስጥ እኔ ቢሮ ድረስ እንገናኝና በሰፈው እንምከርበት›› ብሎ ስልኩን ዘጋው፣ ኤድዋርድ።

የስልኩን መነጋገሪያ ወደ ስፍራው በመመለስ ላይ ሳለ ኪም ነሰቢት ከመታጠቢያ ክፍሏ ወጥታ ወደሱ ካመራች በኋላ በፈገግታ ስትመለከተው አያት።

ኤድዋርድ ወዳጁን ብቻ ሳይሆን እዚህ ቤት ውስጥ ለምን እንደመጣ

ሳይቀር ፍፁም ረስቶ ነበር።

የተከፈተ ሽሚዙን ጥሎ እያለ እየቆለፈ ከራሻቱን መልሶ አጠበቀና ወደ በሩ አመራ።

ኪም እርቃኗን ተንጋላ ጥሬ የሚያቀርብ ገላዋን ልትለግሰው መዚንጀቷን አሳየችው። ከአልጋዋ ተነስታ እጅጉን እንደዘረጋች ሳት እያለች ልትጠመጠምበት ስትቀርበው ‹‹እስካሁን አላወለቅህም የኔ ፍቅር?›› አለችው፣ ‹‹ይሀን ያህል ያስቸልሃል አላልኩም ነበር። ሳይህ እንዴት ደስ አለኝ መሰለህ? ከተማናኘን ስንት ጊዜአችን. . .››

ሊያቅፈው የተዘረጋውን እጅጉን ወደጎን ፈቀቅ አድርጎ ጥፏት ሲያልፍና ጃኬቱን አውልቆ ወጻስተመጠበት ሲያመራ ከተተመጠበት የተነሳው ለፀ አለመሆኑን በመረጻጅ ንግግሯ ምላሽ ላይ እንደሳሙና አረፋ ሙሽሽ አለ። ገፅታዋ ተለዋወጠ። ‹‹ምን እያደረግህ ነው?››

‹‹እዝናለሁ፣ ኪም። ወደ ቢሮ መሮጥ አለብኝ። አሁን እንድ አስቸኳይ ንገር ገጠመኝ።››

ስትንደረደር ሄዳ ተጠመጠመችበት። ‹‹ውይ የኔ ፍቅር፣ እባክህ አትሂድ? ጥቂት ጊዜ ስጠኝ? ተው ጥቂት ጊዜ እንኳ አብረን እናሳልፍ? በሰንት ቀንህ መጣህና? ባክህ በጣም ታስፈልግኛለህ?››

‹‹ሊላ ጊዜ›› አለ የግልምጫ ገፅታ በተሞላው አኒጋገር። ‹‹ቅድሚያ የምሰጠው ጉዳይ ይጠብቀኛል።› በጉልበቱ እጅጉን ከትከሻው አላቆ በቸኮላ ወደ በሩ ሄደ።

አላስቻላትም። ተከትላው ሄዳ ከኋላው ደረሰችበትና እንደገና ተጠመጠመችበት። ‹‹የኔ ጌታ ባክህ፣ ባክህ ይህች አለምኮ ያላንተ ፈሊማ ናት።››

‹‹ይሀን ካወቅሽ ለቀቅ አድርጊኝ›› አለና ይበልጥ በተቆጣ ሁኔታ እጅጉን መንዛቱ አስለቀቀና ወጥቶ ተፈተለከ፣ በሩን ከጀርባው በኃይል ዘግቶ።

* * *

ታሪክ ላይ ጊዜው ከሊሊቱ ስምንት ሰዓት ሊሞላ ነው።

ቪክቶሪያ ቄስቲን ባረፈችበት ጥላዛ ሆቴል መኝታ ክፍሏ ውስጥ ጥቅጥቅ ባለው ሶፍለማ በጀርባዋ ተንጋላ በተከፋ ሀሊናዋ ከኒክ ራምሲ ጋር ያሳለፈችውን ሌሊት ትገመግማለች።

ራት የበሉት ባንድ ጠረጴዛ ቢሆንም ቪክቶሪያ ደስተኛ አልነበረችም። ኒክ ግን እንደተለመደው ከእሀሉ ይልት ውሃው ላይ ኦተኩሮ ነበር ያመሸው።

በቆይታቸው ወቅት ብዙ ጊዜ አእምሮዋን እረፍት ነስቶ ሲበጠብጣት ስለነበረው ጉዳይ፣ ስለ ሚስተር ኤድዋርድ አጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ ስለ ማርክ ብራድሾ ሚስጥር፣ ለቧና ለራምሲ ስለሚሰጡት ግራ የሚያጋቡና ከሙያቸው ጋር የማይገናኙ ስራዎች ትዕዛዝ ሊታኒጋረው ያላደረገችው ሙከራ አልነበረም። ግን አልተሳካላትም። ራምሲ የቧን ነገር ከመስማት ይልቅ ራሱ መናገርን እንደመረጠ፣ የሚናገረውም ስለግብፅና እስራኤል ሆኖ አመሸ። ዚቻራት ስለሱ ማሰብ፣ ለምን ብዙ እንደሚጠጣ መጨነትና ለምን እሷን ችላ እንደሚላት ማሰብ ጀምራ ነበር።

ከሊሊቱ ስድስት ሰዓት ከመሆኑ በፊት ከአለታቸው የሚተላለፈውን የስልክ ጥሪ ለመተበል ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ። ካርሎስ ፖሊስ ሳይደርስበት መኖሪያውን ለውጦ እንደተሰወረ፣ ራምሲ ዚት ወደ ዋሽንግተን እንደሚጓዝ፣ ቪክቶሪያ ፓሪስ ቀርታ ከጳጳሱ ጉብኝት አስተድሞ በሎድረስ ላይ እንድትፅፍ መወሰኑ በስልክ ተግለፀላቸው።

ከስልኩ በኋላም ቢሆን ቪክቶሪያ ጠቅላላውን የተወሳበደ ሁኔታ ከራምሲ ጋር ልትነጋገር ሳትሞክር አልቀረችም። ኒክ ግን ለዋሽንግተን ጉዞው ሲሰናዳ የሚያመሽ በመምሰል ተፍ ተፍ ሲል ብዙውን ጊዜ አጠፋው። በዚያ ላይ ገደብ የለሽ ፣አንድ ለመንገድ፣ ልታናግረው ከመቻሏ በፊት ራምሲን ሰብ አደረገው። በመጨረሻም ተስፋ ቆርጣ ወደ መኝታዋ ሂዳ ተጋደመች።

እንቅልፍ ግን በቀላሉ እንደማይጎበኛት ወዲያውኑ ተገነዘበች። የአካል ዝለት። አእምሮዋ ግን ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች በፈጠሩት ውጥረት ተሰቅሏል። ራምሲ ምን አይነት ሰው ነው? ሚስተር ኤድዋርድ ምን ይመስላል? ብራድሾስ? ሶሞኑን እንድታዘጋጅ የታዘዘችውን ፅሁፍ በፓሪስ

የሬዛሪድ መዘል በር ሊያዘጋጀው ቢችል ኖሮ ለምን ተመረጠች?

ጥያቄዎቹን ልትመልስ እንደማትችል ስታውቀው ሁሉንም ሃሳቧን ከአእምሮዋ አውጥታ እንቅልፍ እንዲወሰዳት ለማድረግ ወሰነች። እንቅልፍ ግን የለም።

ዘመዷ ሬዛሪ ከሄደ ጀምሮ ልትወሰድ መስና ሳለ በሙታ ክፍሉ መተላለፊያ የእንድ ክፍል በር ሲከፈት ተሰማት። ራምሲ ከቦና ቤት ወጥቶ ሙታ ክፍሉ እየገባ መሆኑን ጠረጠረች።

ራምሲ ቂት ወደ ዋሽንግተን መሄዱ ነው። ከዚያ በፊት ያልተመለሱ ጥያቄዎቿን አውጥቶ አንሲታ ግማዘር አለባት። መኖሲ ቂት ወደ አውሮፕላን ጣቢያ ስትሸኘው ታንብበት ነገ መንገዲኛ ሰለሆነ ጊዜውም አይኖረውም። አውን ግን ሊያመልጥ በማይችልበት ሙታ ክፍሉ ከልትው እንዳለ ሁሉንም ነገር ለመስማት ይገደዳል።

ምን ጊዜ ምንጣሬን በረታትሳ፣ መብራቷን አብርታ የሊሊት ልብሷን ደርባ ወደበሩ እንዳመራች ራሷም አታውቀውም። ከራምሲ ክፍል ከመግባቷ በፊት ግን ምንም ቢሆን ፊቷን በመስታወት ላትመለከትና ወጉን ላታስተካክል ከራሷ ክፍል ልትወጣ አልደፈረችም።

ራምሲ ክፍል በር ላይ ስትደርስ ቆም አለች፣ አመነታች። ልፍለፋዋን ለመስማት ፈታኟ ባይሆንስ?

‹‹ምንም አይደለም፣ ኤሞ›› አለች ለራሷ። ከዛሬ ያለፈ ነገር ሁሉ ዋጋ የለውም።

ሁለት ጊዜ እንዳኳኳች የጓደኛዋን ድምጽ ሰማች። ‹‹ይግቡ››

ከፍታ ገባች።

ክፍሉ ባልተነጠፈው አልጋ ግራና ቀኝ ባሉት የራሷ መብራቶች ደብዘዝ ያለ ብርሃን ይታይበታል። ኒክ ፊት ለፊት ታያት። ከውስጥ ሙታንታ በቀር ራቁቱን ነበር።

ራቁቱን ስታየው ደንግጥ ብላ ‹‹ሙይ ይቅርታ፣ አላወትሁም›› አለችውና

ለመመለስ ዞር አለች።

ራምሲ ግን «ወግኛ» ብሎ አስቆጣት። «ወንድ እንዲህ ሆኖ አይቼ አላውቅም ለማለት ነው ወይስ አቋሜ የወንድ አይመስልም?»

ከአግሯ በታች መሬት ውስጥ የተተከለ ስር ያላት ይመስል ቪክቶሪያ ተገትራ ቀረች። እንደቆመች ከላይ አስከታች ስታስተውሰው ቁመናው የወንዶች ወንድ ሆኖ ታያት። ዐንር የለበሰው ደረቱና የተቆጣጠረ ጡንቻ የበዛበት ሞኑ የወንድነት ምልክት አሰመሰሎታል። ወደፊ ራመድ ሲል ግን ሚዛኑን ከመሳቱም በላይ ሲናገር ምላሱ የተሳሰረ ነው። «አንድ መለኪያ አብረሽኝ ልትወስጅ ነው?» አላት፣ የጨበጠውን የብራንዲ መለኪያ ከፍ እያደረገ።

«አይ ይቅርብኝ ኒክ፣ አመሰግናለሁ። በውነት የመጣሁት ከዚህ ከመሄድህ በፊት ጥቂት ላነጋግርህ ብየ ነው። ምን ጊዜ ነው የምትወጣው?»

«ከሦቲል? በአምስት ሰዓት» ክላት በኋላ በጥንቃቄ ወደአልጋው ተራምዶ ዙሮ አለና አልኩሱን ሞልጥ አድርጎ በመለኪያው አሻግሮ ተመለከታት።

«እንግዲያውስ ጊዜ አለን» አለች፣ «ጥቂት ጥሮ። ጧት ልንነጋገር እንችላለን። አሳሳበ. ጉዳይ ሆኖብኝ ነው።»

«የለም ቪክ» አለ መለኪያውን ጠረጴዛው ላይ እያስተመጠ። «እንነጋገርበት። ለረጅም ጊዜ ላነጋግርሽ ስፈልግ ነበር።»

«ጥሩ፣ እንተም እንደኔ አስበህበት ከሆነ።»

«እንዳንቺ አስበበታለሁ» አለ፣ «በግሌ ጠቃሚ የሆነ ነገር ላነጋግርሽ ስሙኝ ነበር» ክላት በኋላ የአልጋውን ፍራሽ መታ መታ አደረገና፣ «እዚህ ተቀመጪ» አላት።

«እሺ» ብላ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጠች።

«ግን መጀመሪያ እኔ ልንገርህና አንተ ትቀጥላለህ።»

በዓዘዙ አይናቸው ሊያያት እየሞከረ «የለም» አላት፣ «መጀመሪያ እኔ።

የእው የበለጠ አሳሳቢ ነው። ሁለታችንን ይመለከታል።››

አይኖቿ ፈጠጡ። በትዕበት ጓንች፣ ተገረመች።

‹‹ስለሁለታችን›› አለ እንደገና፣ ‹‹ላፊ ነገ ሰል አስካሁን ያልገለፅኩልሽ ነገር አለ፣ ላብራራልሽ።››

‹‹አያስፈልግም ኒክ›› አለችው ሆዷን ባር ባር ቢላት።

‹‹አያስፈልግም። ምክንያቱም. . .›› በመጠጥ ብዛት አፉ እየተንተባተበ እንዳስቸገረው ያስታውቅበታል። ‹‹ወንደላጤ ነበርኩ። ከስድስትና ሰባት ዓመታት በፊት ካንዲት ሴት ጋር ግንኙነት ጀመርኩ። በሚም ከመተራረባችን የተነሳ መዘዙን ፊርቼ ሳርታት ወሰኜ ነበር። እዩ ግን ከእ ፍቅር ይሄታል ብየ ገመትኩ፣ አሰብኩ። እና ተጋባን። ወዲያውኑ ግን ግና ጓንላችንን ሳንጨርስ ከሌላ ወንድ እንደኔ ለይስሙላ ሳይሆን በውነት ከምታፈቅረው ወንድ ማርዝን ደረስኩባት። ለካስ ለውየው ልጅን ስላለተቀበላት ኖድል ለልጅዋ አባት ፍለጋ እኔን ያገባችኝ። እቧን ወይም ራሴን ለመግደል ፈለግሁ፣ ወሰንኩ. . .››

ቪክቶሪያ የራምሲን ንግግር እቋርጣ እጁን እያነታነተች፣ ‹‹በጣም የሚያሳዝን ታሪክ አለህ ኒክ›› አለችው።

‹‹አሮጌ ታሪክ ነው፣ ያረጀ። ግን ግድያውን መፈፀም አልቻልኩም። ለምን? ብየ ራሴን ጠየቅሁና በተላሉ ፈታኝት፣ ተውኪት፣ አውልቂ ግልጓት አንደ አሮጌ ጨርቅ። ከዚያ ወዲህ ሌላ ሴት ላላምን፣ ለማንም ልቤን ላልሰጥ በልቤ ማልኩ፣ ተገዘትኩ። ይሁንና የተከተለው ብቸኝነትና ተስፋ መቁረጥ ስለነበር መጠጣት ጀመርኩ፣ ከዚያ ወዲህ ጓደኛየ መለኪያ ሆኖ ተረ። አልፎ አልፎ ፍላጎቴን ለማርካት ካልሆነ በስተቀር የምሽት ጓዴ አልኮል ነው። ከዚያች ርክሰ በኋላ ማንንም ደጋግሚ ላላወጣ፣ ማንንም አምኜ ላላፈቅር ወሰኜ ነበር አልሻለሁ። እውነትም ከማንም ጋር ፍቅር ይዞኝ አያውቅም. . . አንቺን ከማግኘቴ በፊት።››

ቪክቶሪያ ልቧ በመደሻ የተቀጠቀጠ መሰላት።

‹‹አንቺን ላለማፍቀር ብዙ ታግየ ነበር›› አላት ተጠለና፣ ‹‹ከማንም ጋር

እንዴት በፍትር አጠድቃለሁ?››

‹‹እኔ ላንተ እንደማንም ነኝ እንዴ?››

‹‹ኤዲያ፣ ያም ሆነ ይህ በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አንቺን ከልቤ ለማፍቀር ተጣድፌለው ቪኪ፣ ከንግዲህ ደግሞ ካፈሌ ጠጥቼልና ወደኋላ አልመለስም።››

‹‹አ ኒክ›› ከተቀመጠችበት እንዴት እንደተነሳች አያም አታውትም። ላዩ ላይ ተከመረችበት። እንባ ተናነቃት። ከንፈሮቹን ፊልጋ ደጋግማ ሳመቻቸው። ፈመፈመቻቸው መጠመጠቻቸው። ነከሰቻቸው። ‹‹አኑም ከየህህ ጀምሮ በፍትር ስፈኔትልህ ነው የኖርኩት።››

ከንዶቹን በዙሪያዋ ጠምጥሞ ወደ ደረቱ ሞምት እያደረገ ተራውን መሟጠት።

‹‹ቪኪ፣ አልጋ ላይ እንውጣ?››

የሰራ አካላቱ ጡንቻዎች ቱጦርጦር ማለታቸው ታወቃት። የራሷ ጉሰኛ፣ ጠቦችና የሞኗ የውስጥ ክፍልም የትንታግ ወላፈን የጸሰሳቸው እስኪመስላት ድረስ ተታጠለ፣ ነደዱባት። ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ ስሜቷን ለማጠት ታገለች። ‹‹ትጠይቀኛለህ ብየ አላሰብኩም ነበር›› አለችው በታፋነ ድምፅ።

አልጋው ላይ ሊያስተኛት ጎንዶል አደረጋት። ‹‹አሁኑኑ የኔ አመቤት።››

ጥቂት ራት አለችውና ‹‹አም አሁኑኑ›› አለችው አፍ አውጥታ። ከዚያም ብድግ ብላ ‹‹መጀመሪያ ልታጠብ፣ ሁለት ደቂቃ አልቆይም›› አለችውና በባዶ እግሯ፣ ወደሱ መታጠቢያ ክፍል ጉበታ የሊሊት ሞሚቧን ስታወልትና ውሃውን በሰራ አካላቷ ስታርከፈክፈው ደቂቃ እንኳ አልፈጀባትም። ሰውነቷ በስሜት ይወዛዞል። ልቧ ላይቀር ደስታዋን የሚካፈል ይመስል ደረቷ ላይ ሥቧ ይረግጣል። ለካስ ራምሲ ያፈቅራታል! ለካ ይፈልጋታል! ከንግዲህማ ምን ጎይል ይነጥላቸዋል።

ከፈት ለፈቷ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን መስታወት አየችው። ሽኖ

ቅባትና ሌሎች የውበት መዋመሪያዎችን ብትተባባ በወደደች። ግን ምንም አይደለም። ራምሲ መጀመሪያ አይኑን የት ላይ እንደሚጥል የገባ ራፒ ምስል ነገራት። ራቱቷን ከፊቱ ግቡ ስትል ራምሲ አስተድሞ የሚያየው በመጫና በዳሊዋ መካከል ያለውን ክልል ነው። በዚያ በጥቅር በነደደ ጥብት የወጣት ገላ ተማርኮ ምራቱን ከመዋጡ በፊት ለሽዮና ለትባቱ ተልብ አደናረሙም።

ታስደስተዋለች። እም፣ በበኩሷም በሱ ለመደሰት ለወራት ያለመችውን ፍላጎት እውን ታደርጋለች።

ይህ የተቀደሰ፣ የተወደሰ፣ የተባረከ፣ የተመረቀ፣ የታደለ ቀን ያመጣው ደስታ አሁኑኑ በተግባር መታየት ይኖርበታል።

ከመታጠቢያው ወጥታ መበራቱን አጠፋችና በተጎማለለ አረማመድ እርታኗን ወደ መኝታ ክፍሉ አመራች። አልጋው ላይ ተጋድሞ ሲጠብቃት አየችው።

እጅጅን ከጎንና ከኋኗ ከርፊፍ እንጸደረገች ወደ አልጋው ጠርዝ እስክትጠጋ ድረስ ከእርምጃዋ ጋር ጡቶቿ በራሳቸው ሰልት ይነሱ ይወድቁ ነበር።

አሁን ራምሲ ሙሉ ለሙሉ ይታያታል። በጎኑ ተጋድሟል፣ አሁን በውስጥ ሙታንታ ነው። ራሱን ደግሞ ትራሱ ውስጥ ተብሯል።

ተጠጋችው። አይኖቹ ተክድነዋል። እንዲያውም ሲያንኳርፍ ሰማችው። እም፣ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዶታል።

ቁልቁል እየተመለከተችው እንደደረቀች ቀረች። የምትሠነው ጠፋት። እሪ ብላ ልታለትስ ፈለገች፣ ሳቂ ግን ተደማት። ሁለቱም ተደበላለቁባት፣ ለትሶና ሳት!

ዝርግትግት ያለውን ሰውነቱን እንደገና እያስተዋለች ከደቂቃዎች በፊት የዘበዘበላትን ኑዛዜ ልትገመግም ሞከረች። ጊሾ ባተባው አፍ ደብቶት የኖረውን ጥቅሩን ነው ገልጾ የነገራት? ወይስ ሲሰክር የፈለገውን የሚተፋ ባዘታም ነው?

ሙልሱ?

ሬንድ ወቅት ግና ታዳጊ ህጻን ሳለች ከአባቷ ጋር የድምፅ የለሽ ፊልሞች ፌስቲቫል ሲከበር ተከታትላ ነበር። በፌስቲቫሱ የተረዙት ፊልሞች በመሉ አንድ ተመሳሳይ ባህርይ ነበራቸው። ሁሉም አንድ ታሪክ አንድ የተንጠለጠለ ነታ ሲደርስ የተመልካቹን ልብ እንዳንጠለጠሉ ይፈጠማሉ። «ይቅጥላል!» ነበር ሁሉም ፊልሞች በመጨረሻ የሚያሰሙት ድምፅ።

ቪክቶሪያ፣ በምሬት ፊገማ አለች ለራሷ።

«ይቀጥላል» ስትል ተናገረች ለራሷ።

ተመልሳ መታጠቢያ ክፍሉ ግባችና የሊሊት ልብሷን አውርዳ ለብሳ እንደገና በመኝታ በኩል ወጥታ በመጣችበት ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

እናም፣ ምንም እንኳ ልሷ እንደተንጠለጠለ ቢሆንም ለጊዜው የፊለገችው እንትልፍ ወሰዳት።

ቀሪው? ይቀጥላል!

11

ከጧቱ አራት ሰዓት ተኩል ነው። ቪክቶሪያ ከመኝታ ክፍሏ ወጥታ በሆቴሉ የእንግዳ ማረፊያ አዳራሽ ማዕዘን ይዛ አንድ ወንበር ላይ ተቀምጣ ጋዜጣ ታነባለች። በጋዜጣው በከፈለ ራሷን ከልላ በአዳራሹ የሚያልፉ የሚያገድሙ ሰዎችን በቲቪረጅታ ትመለከታለች። ራምሲን መኝታ ክፍሉ ውስጥ ልታገኘው ስላልቻለች አምስት ሰዓት ሆኖ ወደ ቻርልስ ደጎል አውሮፕላን ማረፊያ ለመሄድ ከመነሳቱ በፊት ሳታገኘው እንዳይሄድ ሰግታ ነበር። ይሁን እንጂ ሻንጣውና የዕሀፈት መሳሪያዎቹ መኝታ ክፍሉ ውስጥ መኖራቸውን ሰላየች ከሆቴሉ ግና እንዳልወጣ እርግጠኛ ሆና ነበር የምትጠብቀው።

ጋዜጣውን የሚያዩት አይኖቿ ብቻ ናቸው። ሃሳቧማ ግና ትናንት ማታ ላይ፤ ትናንት ማታ ከደረሰባት ለወሬ የማይመች ታሪክ ላይ ተነስቶ ከሂዜ ጋር መራመድ አትችልም። አእምሮዋ የሚያሰላስለው የትናንት ማታውን ብቻ ነው። ራምሲ እንደሚያፈትራት ገልጸላታል። ገልጸ ነግሮኛል ብላ እንዳትረጋጋ ደግሞ የጠላው መጠጥ አንኳን አእምሮውን ምላስንና አግሩንም አሳልድፎአቸው ነው ያመሸው።

ነገር ግን ምናልባት ካፉ የወጡትን ታላቅ ጠንቱቹ የሚያውቅ ሊሆን ይችላል። ለሁሉም እርግጠኛ የምትሆነው ለአፍታ አግኝታ ስታጫውተው ከገፅታው በማንበብ ወይም የሚታውን ደፍሮ በድጋሚ ሲነግራት ብቻ ነው። ብቻ ሳታገኘው እንዳይሄድ።

አምስት ሰዓት ሊሆን ዘጠኝ ደቂቃ ሲቀረው ራምሲ ሻንጣውን በእንድ

ፈጠሉ አሸከሙ ወደ ተሽከርካሪው በር ሲጣደፍ በአይኗ ተብ አደረገችው።

በሩን አልፎ ሲወጣ ሲል ድግሞ በእጅዋ ተብ አደረገችው።

ራምሲ ቪክቶሪያን ድንገት በማየቱ በመገረም አይኑን ጎላ አድርጎ "ሄይ!" አላት፤ "እንደምሄድ እንዴት አወቅሽ?"

ወሽመጥ የሚበጥስ ሀረግ ነበር። በታ፣ ማታ የተናገረውን ፊጽሞ እያስታወሰም ማለት ነው።

"በስን ልበና" አለችው። ራምሲን ከሚጠብቀው የኪራይ መኪና ውስጥ አብረው ገብተው ጉዟቸውን ሲቀጥሉ ደግሞ፤ "የለም፡፡ አለችው፤ "ትናንት ማታ በአምስት ሰዓት እንደምትወጣ ተጫውተናል።" ድውውታቸውን ለማውጣጣት ሞከረች። "አታስታውሰም?"

ገፅታውን ሲያንበት የተምታታበት ይመስላል። "ትናንት ማታ? ተጫውተን ኖሯል? ወደ ዋሽንግተን እንድመለስ መታዘዜን ካወቅሁ በኋላ? ከሦቱል ከወጣሁ በኋላ የማስታውሰው መተኛቴን ብቻ ነው።"

"በመከከሉ ተጫውተናልኮ" አለችው እየተቅለሰለሰች።

ራምሲ ግንባሩን ቋጥር አደረገ። "ይሆናል፡፡ አለና ፈገግ ሲል ሞከረ። "ምናልባት ከወደውሃው ስለወሳሰድኩ ዘንግቸው ይሆናል።"

"ይሆናል" አለችው፣ ያለ ልጊ ደረት ፈገግታ ልታሳይ እየሞከረች፣ የአንጀቷን ማረር ይብታ።

የጠጣው አልኮል ጠዝሚራውን አዙሮት እንደነበርና ትውስታውም ዜሮ መሆኑን አወቀችለት።

ያችን አሮር የጭኮር የመተቃቀፍና የመሳሳስ ደቂቃ፣ የተመረቀች መሰላ የተረገመች፣ የተባረከች መስላ የተለከፈች፣ የተቀደሰች መስላ የረከሰች፣ የታደለች መስላ የጎደለች ቀን መለስ ብላ አሰበቻት። እንዴት እንጸጸሽ ራምሲን ማስታወሱ ዋጋ የለውም። እንዲያውም አሳፋሪ ሊሆን ይችላል። ጣቢው ራምሲ አእምሮውን ሲጥ ለዋላ ፈዛዘ፣ ለሴትና ለወሲብ፣ በታ የማይሰጥ ልበ-ድፍን ቢሆንስ? አመድሻለሁ ብለኸኛል ስትለው ከት

ብሎ በስቅባትስ?

‹‹ግደል ይግባ›› አለች በመጨረሻ በልቧ፣ ብዙ ሴቶች ሲፈቱ እንደሚያደርጉት።

‹‹በውነቱ ኒክ፣ ከመሄድህ በፊት የማማክርህ ጉዳይ አለኝ ብየህ ነበርክ። ብዙ ጊዜ ሞክሬ ነበር፣ ትናንት ማታም ራት ላይ ነገሩን ላነሳልህ ነበር፣ አልቻልኩም።››

‹‹ራት ላይ?›› አላትና አረፈው። ‹‹አዝናለሁ›› አለ ቀጠለና። ከወደ መተመሚዋ ወደሱ ዞር ብላ፣ ‹‹ኒክ አንድ እንግዳ ነገር አእምሮየን እየረበሸ አስቸግሮኛል። የነገሩን ስር ካላገኘሁ እረፍት የለኝም። ያንተ ምክር ይጠቅመኛል።››

‹‹እሽ፣ እስኪ ልሰማው። ምንድነው የሚረብሽሽ?››

‹‹አውሮፓ ከመጣን ጀምሮ የሚታየው የሽብር ፈጠራ ማስበል።››

‹‹ቪኪ፣ አውሮፓኮ ለዘመናት በሽብር የተናጠና የሚናጥ አህጉር ነው።››

‹‹በዚህ መልኩ ግን አይደለም›› አለች በአለታ፣ ‹‹ይህን ያህል የጠነከረ፣ ይህን ያህል አንዱ በአንዱ ላይ የተደገሙ ነበር እንዳትለኝ። ይህን ያህል የአለምን ህብረት ትኩረት የሳበ ሽብርም ታይቶ አይታወቅም። እስኪ አስበው፣ የሲኖ ንብስ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሐፊን፣ የእስራኤልን ጠቅላይ ሚኒስትር በሚያህሉ ሰዎች ላይ ማን ሽብርተኛ ድፍረት ፈፅሞ ያውቃል? የመት ባህርን ትርሶችስ ማን ልብ ያለው ሽብርተኛ ነው የሚዘርፈው? የለም፣ የዘንድሮው ሽብርስ የተለመደው አይነት አይደለም።››

‹‹ግን ልታግዝኸኝ የፈለግሽው ምንድነው?›› ሲል አቋረጣት።

‹‹ሰማ፣ ለእኒህ ሁሉ ድርጊቶች ተጠያቂው ካርሎስ እንደሆነ ተደርጎ ተፅፏል። አንተ ደግሞ ትናንት የካርሎስን እቅም ሰምተሃል።››

‹‹ካርሎስ የሚያደርገውንና የማያደርገውን በተመለከተ ማስረጃው ካርሎስ ነው የሚል እምነት የለኝም›› አላት።

«እንደሚመስለኝ ግን ካርሎስ እውነቱን አናውቀው ነገሮሃል። እዚሁ አፍንጫችን ላይ ከሚፈፀሙ ሽብሮች ጋር ካርሎስ ግንኙነት ያለው አይመስለኝም።» ቪክቶሪያ ስለተፈፀሙት ጠለፋዎች፣ ዝርፊያዎችና ግድያዎች ነጥብ ለራምሲ ካስረዳች በኋላ አስተያየቷን ስትቋጭ «ካርሎስ እውነት ተናግሯል» አለች፣ «እንዳቸውም የሱ ስልቶችና ተግባር አይደሉም፣ ድርጊቶችም ሆኑ የመያዣ ጥያቄዎች። ባጠቃላይ ተጠያቂው ሌላ ክፍል ነው። ሌላ ኃይል።»

«ካርሎስ ካልሆነ ማን?» ጠየቀ ራምሲ።

«እኔ እንጃ፣ እስኪ አንተ ግምት?»

«በአለማችን በመሬቱ የሚቆጠሩ የተደራጁ ሽብር ፈጣሪ ቡድኖች ይንቀሳቀሳሉ።» አብራራ ራምሲ። «አንዳንዶቹ ይካማ፣ አንዳንዶቹ ብርቱ። ምናልባት ከኢህ መከከል አንዱ ይሆናል ተጠያቂው። ወይም በትንጅት፣ በህብረት የሚፈጽሙዋቸው ወንጀሎች ይሆናሉ።»

«የሰሞኑን ሽብሮች የሚፈጽመው ግን አንድ ቡድን ብቻ ነው» አለች፣ ቪክቶሪያ ቁርጥ ባለ ቋንቋ።

«ይሀን ያሳመነሽ ምንድን ነው?»

«ማርክ ብራድሾ» አለች ቪክቶሪያ በቀላሉ። «የሽብሮቹ አንቱና ብራድሾ ነው። አንድ ነገር ይከሰት፣ ሁሌም ብራድሾ በዐታው አለ። እንዴት?»

«እኔና አንችም በብዙዎቹ ቦታዎች ነበርን።»

«እሱ ግን ሁልጊዜም ከኛ ቀድሞ ይገኛል። ለሪከርድ የመጀመሪያው ጠሬ አቀባይ ሁሌም እሱ ነው። ፊጽሞ የማይታመን ነገር። ሽብር ፈጠራዎቹ የትና መቼ እንደሚፈፀሙ እንዴት ከሁሉም ሰው በፊት ሊያውት ይችላል?»

«ምናልባት በግል ግምቱ» አለ ራምሲ ትከሻውን ሰብቆ።

«አይመስለኝም» አለች ቪክቶሪያ። «እንደምገምተው ግን ብራድሾ የዘንድሮውን ሽብር ፈጠራ ከሚፈጽመው ቡድን ጋር አንድ ግንኙነት ያለው

ሰው ነው። ምናልባት ከሽብር ፈጣሪው ቡድን አባላት አንዱን ያውቅ ይሆናል። በተጭኑ የቡድኑ አባል ሊሆንም ይችላል።››

‹‹ትንሽ አልተጀልሽም ቪኪ? ሰውየውኮ ልክ እንደኔና እንዳንቺ ለሚስጥር ኤድዋርድ ያደረ ተኮላሪ ነው።››

ቪክቶሪያ አይኖቿን በራምሲ ላይ አፍጥጣ ‹‹አረጋግጠልኝ እስኪ?›› አለችው።

‹‹ምኑን?››

‹‹ማርክ ብራድሾ የኒውዮርክ ዜጋዊ መሆኑን።››

ራምሲ አሁንም ትከሻውን ሰበቀ። ‹‹ምን ማረጋገጫ ያስፈልጋል? እኔኮ መሃይም አይደለሁም። እንደማንኛውም አሜሪካዊ ያነበብኩትን ነገር ሁሉ አምናለሁ። ማርክ ብራድሾ ደግሞ የጋዜጣችን ዜጋዊ መሆኑን ካቀረበው ሪፖርት አንብቤአለሁ። ሌላ ምን ማረጋገጫ ልስጥ?››

‹‹እሱ የወረቀት ታል እንጂ በህይወት ያለ ሰው አይደለም።›› ቪክቶሪያ ክርክሯን ቀጠለች።

‹‹በሌላ ሰው ላይ የቀረበ ዕሁፍ አንብቤ አላውቅም።›› ራምሲ በተጭውሞው ገፋ።

ቪክቶሪያ እጅዋን ልትሰጥ አልፈለገችም። ‹‹ማርክ ብራድሾ በርግጥ ሰው ከሆነ የታለ? ማነው? እሱን ያገኘ፣ ባይኑ ያየ፣ ያነጋገረው ሰው አይተህ ታውቃለህ? የሌሎች ጋዜጠኞች አሳታሚዎች ስለብራድሾ ጥያቄዎችን ያዘንባሉ። እስካሁን መልስ አላገኙም። በርግጥ ሲደረግ ለከረመው ሁሉ ቁልፉ እሱው ነው። እውነቱን ነው የምልህ፣ ማርክ ብራድሾን ያገኘህ እለት በዘንድሮዎቹ ሽብር ፈጠራዎች ላይ የቀረቡ ብዙ አከራካሪ ነጥቦችን መመለስ ትችላለህ።››

‹‹ቪኪ፣ ምናልባትኮ እንቺ እንደምታስቢው ምንም አከራካሪ ነጥብ የለም ይሆናል።››

‹‹ባይኖር ደስታውን አልችለውም። ግን በእሱ ላይ ትስማማለህ ብዬ

አበበ ነበር። ያም ሆነ ይህ አሁን አንተ መሄድህ፣ እኔ ደግሞ እዚሁ መቅረቴ ነው። በሎርደስ የጳጳሱን ጉብኝት አስመልክቶ ዕሁድ እንዳተርብ ታዝጋለሁ፣ እቀርባለሁም። ግን ማርክ ብራድሾን ማሳደዴንም አልተውም። ማን እንደሆነ ሳላውቅ ላልመለስ ወሰኛለሁ። በውሳኔየ እንደምትስማማ ተስፋ አለኝ።››

ራምሲ መልስ አልሰጠም። በመኪናዋ መስታወት ወደ ውጭ ያመለክት ጀመር።

መኪናዋ እውሮፕላን ማረፊያው ደርሳ ስትቆም ብቻ ነበር ራምሲ የተናገረው። ‹‹አስማማለሁ›› አለ። ‹‹ግን ሰውየውን ልታገኘው ካልቻልሽ የሰርድን የሰራተኛ ጉዳይ ዲሬክተር - ወይዘሮ ከዚን ክሮው ትባላለች - ለማነጋገር ሞክሪ። የቆየች ሽርኪ ናት። ሚስጥር ልታጥያት ትችያለሽ። ስለብራድሾ የበለጠ ዝርዝር ማግኘት ካለብሽ ደግሞ ከሪክርድ ሰራተኞች ውጭ ያለ ሰው ብታማክሪ ነው የሚሻለው። በተለይ በንዲህ አይነቱ ጉዳይ የውጭ ሰው ይመረጣል። እና የቴሌግራፉን ሰራተኛ ሆዊ ዲትማንን አነጋግሪ። በእንዲህ አይነቱ ተግባር የተዋጣለት ፊልፊላ ነው። የኔን ስም ከነገርሽው የጠየቅሽውን ሁሉ ያደርግልሻል።››

ይሀንን ከተናገረ በኋላ ራምሲ እጇ የመኪናውን በር መክፈቻ ፍለጋ እየተራወጠ፣ ‹‹ትናንት ማታ ጀምሬልሽ የተረፈ አንድ ነገር ነበር፣›› አላት፣ ‹‹ግን ለጊዜው ልናቆየው እንችላለን። በትርቡ አንድ ቀን ተገናኝተን በሰፈው እንጫወትዋለን። መጭው ጊዜ የኛ ነው።››

* * *

ቨክቶሪያ በጥንታዊቷ አነስተኛ ከተማ በሎድሪስ ላይ እንድታተርብ ከአለታዋ በታዘዘችው መሰረት ለዕሁዱ ምንጭ የሚሆኑ ዋቢ መዛግብት ፍለጋ የጀመረችው በንሪስ የኒውዮርክ ሪኮርድ ወኪል ቢሮ ቤተ መጽሐፍትን በመጎብኘት ነበር።

በጽሕፈት ቤቱ እንደተገኘች በቀጥታ ወደ ጎላፊው ቢሮ አመራች።

‹‹ብሎድሪስ ላይ ለሪኮርድ ዘገባ ማቅረብ አለብኝ። ፋይሎችሀን እየጎሰጎስኩ የማገኘውን ሁሉ ልጭር ነው። እይፈተድልኝም?›› አለችው ሲድ

ሉቃስ የተባለውን የጽሕፈት ቤቱን ኃላፊ።

‹‹ምንም ችግር የለም። ግን ብዙም የሚጠቅምሽ ምንም የምታገኝ አይመስለኝም›› አላት ሲድ ሉቃስ።

እውነትም ለብዙ ሰዓቶች ደክማ ያገኘችው መረጃ ሲበዛ ትንሽብ ነበር። የካቲት 11 ቀን 1858 የተቆረቆረችው ሎድረስ ከአመሰራረቷ ጋር የተያያዘ ስለሚባለው አንድ ተንኮራዊና መንፈሳዊ ትንግርት ብቻ ነበር ብዙም መረጃዎች የሚያትቱት።

ከጽሕፈት ቤቱ ከመውጣቷ በፊትም እንደገና ወደ ኃላፊው ቢሮ ጎራ ብላ ነበር። ‹‹አመሰግናለሁ ሲድ፣ ግን እንዳልከው ብዙም አላገኘሁ።››

‹‹በዚህ የኮምፒዩተር ዘመን የሎድረስን ታሪክ ማን ከቁጥር ያስገባ ብለሽ ነው?››

‹‹ጻጻሱ ናቸው። በትርቡ በሎድረስ ጉብኝት እንደሚያደርጉ አልሰማህም?››

‹‹አሱማ እንጂራው ነው።››

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ተጨዋውተው ሊለያዩ ሲሉ ሲድ ሉቃስ አንድ ጠቃሚ ነገር ለቨክቶሪያ ጠቆማት። ‹‹የሶርቦን ዩኒቨርስቲ መምህሩን ዶክተር ሌክሌርን ብታነጋግራ ስለሎድረስና የጻጻሱን ጉብኝነት በተመለከተ ከምትፈልጊው በላይ መረጃ ይሰጥሻል›› በማለት የዶክተር ሌክሌርን አድራሻ ነገራት።

በመጨረሻ ልትወጣ በሩ ላይ እንደደረሰች ቆም አለች። ‹‹አ ሲድ ባትሰለቺኝ አንድ ሌላ ጉዳይ ላስቸግርህ ነው።››

ወንበሩ ላይ ወደኋላ ለጠጥ ብሎ ‹‹ምንድን ነው እሱ?›› ሲል ጠየቃት ሲድ።

ማርክ ብራድሾን ለማወቅ የምታደርገውን ጥረት አብራርታ ከዚህ በፊትም የሰውየውን ማንነት እንዲያፈላልግላት ጠይቃው እንደነበረ ካስታወሰችው በኋላ ፍለጋውን ከምን እንዳደረሰው ጠየቀችው።

«አልዘነጋሁትም» አላት ሲድ፣ «በማውቃቸው ሰዎች ሁሉ አጠያይቄአለሁ። አንድ ሞብዋ ላይ ደርሻ ቢሆን ኖሮ ደውየ አነግርሻ ነበር። ግን እስካሁን የማርክ ብራድሾን አይን አይቻለሁ የሚል ሰው አልተገኘም።»

«እንግዲያውስ አንድ የመጨረሻ ነገር ላስቸግርህ። ከሰንደን እስከ ባግዳድ ያሉትን የወኪል ዕሀፊት ቤት ኃላፊ ጓደኞችህን እየወደወልክ ያውቱት እንደሁ ብትጠይቅልኝ?»

«ከተቻለ ወደ ኋላ አልልም። ግን በበኩልሽ አንድ ሁለታ ዋይልኝ?»

«ምን?»

«ማርክ ብራድሾን ራስሽ ካገኘሽው በጣም የማክብረው የጦራስ ጀግና መሆኑን በኔ ሰም ነግረሽ አድናቆቱን ግለጭልኝ።»

«የሚደንት ችሎታ ተርቶ የሚጨበጥ እጅ ያለው ሰው አይደለም» ልትለው ከጸጸት በኋላ ከእሷ ላይ መልሳ «የኔንም ያንተንም አድናቆት አገልዕለታለሁ» ብላው ወጣች።

* * *

ፕሮፌሰር ሊክሊርን ለማግኘት ብዙም አልተቸገረችም። ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ፕሮፌሰሩ ለቨክቶሪያ ያደረጉላት ግለፃ ያስገኛላት ሞብዋም ከግሙቶችው በላይ ዝርዝርና በምትፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነበር። በመጨረሻ በትርቡ ጸጸሰ በሚያደርጉት ጉብኝት ላይ ለመገኘትና ለመስገድ እንደተለመደው በብዙ ሺህ የሚቆጠር አማኝ ህዝብ ከአለም ዙሪያ ወደ ሎድረስ መጉረፍ መጀመሩን አስረዳት።

ቨክቶሪያ እጅዋ እስኪዝል ድረስ ግለጻውን በማስታወሻዋ ገልብጣለች፣ ረክታለችም። ግለፃው ተግባዱ ሲሰነባበቱም፣ «ከጠበቅሁት በላይ ነው ያስረዱኝ። እንዴት ደሰ እንዳለኝ በታላት ልነግርም አልችልም» ከማለት ሌላ የምትናገረው አልነበራትም።

ፕሮፌሰር ሊክሊር ግን የጋዜጠኛዋን ያህል በዝ ግለፃቸው የልባቸው የደረሰ አይመስሉም። «ጥቂት ቀደም ብትይልኝ ኖሮ» አሉ ራሳቸውን

በትራታ እየነቀነቁ። ‹‹እጅግ ምርጥ የሆነ የሎድረስ ካርታ አሰጥሽ ነበር። ትናንት አንድ ሊላ አሜሪካዊ መጥቶ ስለጠየቀኝ ሰጠሁት።››

ቪክቶሪያ ወዲያውኑ ትኩረቷ ተሳበ። ‹‹ሊላ አሜሪካዊ አሉኝ?››

‹‹አዎ፣ ግን ስጋት አይደርብሽ፣ የሚቀናቀንሽ ጋዜጠኛ አይደለም። በአለም መንፈሳዊያን ኩነኖች ላይ ጥናት የሚያካሂድ የታሪክ ተመራማሪ መሆኑን ራሱ ነግሮኛል።››

ቪክቶሪያ ግን ጥርጣሬዋ አልለቀቃትም። ‹‹ግን. . .ግን ስሙን ነግሮዎታል? ማርክ ብራድሾ ይሆን ስሙ?››

‹‹የለም፣ የለም›› ካሉ በኋላ ፕሮፌሰሩ ጥቂት በተመሰጠ አሰብ አደረጉ። ‹‹ኧ. . .አዎ ፈርግሰን፣ ጀምስ ፈርግሰን ይባላል። ከኒውዮርክ ዩኒቨርሲቲ ያመጣ ነው። ፀጉሩ ቁጥርጥር ያለ ሆኖ ጥቁር፣ ፂሙ የተንዠረገገ፣ አፍንጫው ወጣ ያለ፣ በውፍረትም ሆነ በቁመቱ መካከለኛ የሚባል ይመስላል። ምናልባት ታውቂው ይሆን? ብታውቂው ካርታውን እንዲያውስሽ ትጠይቂው ነበር።››

‹‹ባውቀው ጥሩ ነበር። ግን አላውቀውም።››

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ግን ቪክቶሪያ ፕሮፌሰሩን ተሰናብታ ወደ መኪናዋ ስታመራ ስሙ በማይረሳ ቦታ እንደተሰማ ሙዚቃ ትዝታ አእምሮዋን ይረብሽ ጀመር። ሚስተር ጀምስ ፈርግሰንን በአካል ባታውቀው እንኳ ስሙ ከዚህ በፊት የሰማችው መሆኑን ልትጠራጠር አልቻለችም።

ግን የት?

በዚያው አለት ከሰዓት በኋላ ቪክቶሪያ በሎድረስ ላይ ያጠናቀረችውን አመርቂ ጽሁፍ አቀናብራ፣ የኩነማዋንና በተለይም ጳጳሱና ከአለም ዙሪያ የሚመጡ ብዙ ሺ ሃይማኖተኞች ለስግደት የሚሰበሰቡበትን በምድር ውስጥ የተሰራ የፀሎት ቦታ አቀማመጥ ትርፅ ስፋት ላይቀር በሰፈው በማተት ኒውዮርክ ሪኮርድ ቢሮ ደውላ ላገኘችው ለጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ ለማክ አሲስተር አስገለበጠች።

ሰልኩን ከማስቀመጧ ወዲያውኑ ሥዝ። የደወለላት የፓሪሱ ሪኮርድ

ቢሮ ኃላፊ ሲድ ሉታስ ነበር። ማርክ ብራድሾን ማስፈለግ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ተጥረው አሰርተውት እንደሁ ፋይሎቻቸውን እንዲመረምሩ በመላ አውሮፓና በመካከለኛው ምስራቅ ከተሞች የሚገኙ የወኪል ቢሮዎች ኃላፊዎችን ጠይቶ ከአንዳቸውም የአምንታ መልስ እንዳላገኘ፣ ብዙዎቹ እንዲያውም ስለሰውየው ለማወቅ ያላቸውን ጉጉት በትሬታ ገለፀላት።

‹‹አንድ ሰው የህዝብ አይን ሲያርፍበት ብዙ ጊዜ ስሙን ይለውጣል›› አላት። ‹‹ራሱን ብረቅና ፊድ ለማድረግ ብራድሾ ራሱ ወይም የሪኮርድ ባለስልጣኖች ስሙን ለውጠው ያሰሩት ይሆናል።››

‹‹ይሆናል›› አለችና ቪክቶሪያ ሉታስን አመሰግና ሰልኩን ዘጋችው። የብራድሾ ነገር ደብዛው ያልተያዘ ቢሆንም ቪክቶሪያ ሽንፈቱን ተቀብላ ተስፋ የምትቆርጥና ደካማ ሆና አልተገኘችም። እንዲያውም ነገሩ እልህ አጋብቶ ከመደበኛ ስራዋ ጎን የምትሟሟትበት ተግባር አድርጋ ለመያዝ እንድትወስን አደረጋት።

ራምሲ ወደ አገሩ ከመመለሱ በፊት ምናልባት ችግር ቢገጥማት በኒውዮርክ ሪኮርድ የሰራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል የምትሰራ የቅርብ ጓደኛ ስላለችው እሷን ደውላ ማነጋገር እንደሚጠቅማት መከሮ የሴትየዋን ስም ሰጥቷት ነበር። ወይዘሮ ከሮው ነበር የሴትዮዋ ስም።

በዚያው እለት ለሴትዮዋ ደወለች። እንዳገኛቻትም ቪክቶሪያ መጀመሪያ ራሷን አስተዋውቃ የኒክ ራምሲን ስም አነሳችላት። ‹‹ራምሲ የሚስጥር ጓደኛው እንደሆኑ ነግሮኛል። የኔንም ጉዳይ በሚስጥር እንደሚይዙልኝ ገልጸልኛል›› አለች ቪክቶሪያ ቀጥላ።

‹‹ሚስጥር ይጠበቃል።›› አለች ወይዘሮ ከሮው።

‹‹የደወልኩልዎ በኛ መሰሪያ ቤት ስለሚሰራ አንድ ሰው ሳነጋግርዎ ነው። ማርክ ብራድሾን ማለቴ ነው። በጥበት እፈልገዋለሁ። እንዴት እንደማገኘው. . .››

‹‹እንዴት ያለ አጋጣሚ ነው?›› አቋረጠቻት ወይዘሮዋ።

‹‹ለብዙ ሳምንታት በየቀኑ ስለሱ የሚጠይት አንድ ሰው ሳይደውልልን

ውሎ አያውቅም። ጋዜጣ እዘጋጅና የዜና ማሰራጫ ሳቢያምኽ እሱን አግኝተው ለማነጋገር ይወተውቱናል። በበኩላችን ግን ማርክ ብራድሾ የሚባል ጋዜጠኛ በሰራተኛው ዝርዝር ላይ የለንም።››

‹‹ግን የግድ መኖር አለበት።›› ተቃወሙት ቪክቶሪያ።

‹‹ይሰማኛል›› አለችና ወይዘሮ ክሮው ዝም አለች። ‹‹ቆይ እስኪ። እንድ ነገር አስታወስኩ፣ መስመር ላይ ጠብቂኝ›› አለች ተጠለችና።

ቪክቶሪያ ወይዘሮ ክሮው ምን ልታደርግ እንዳሰበች ግራ ገብቷት የስልኩን መነጋገሪያ ይዛ ትጠባበቅ ጀመር።

‹‹ወይዘሪት ዊስተን?›› አለች ክሮው ከአንድ ደቂቃ ቆይታ በኋላ። ‹‹አልሆነም። ከኛ ውጭ ማርክ ብራድሾን ልታውቅ ትችላለች የምላት ኤድዋርድ ዐሐፊ ኢስቲል ራበኪን ነበረች። ነገሩ እንዲከበዳት ብየ አንቺ ከፓሪስ ደውለሽ የብራድሾን አድራሻ በጥብት እንደምትፈልጊው መጠየቅሽንና አሁንም መስመር ላይ እንደምትጠኝ ነገርኳት። እሷ ግን ሚስተር ኤድዋርድ በመደበኛ ሰራተኛነት ከሚያሰራቸው ውጭ በግል ኮንትራት የቀጠራቸውን ሰራተኞች አውቃለሁ፣ ማርክ ብራድሾ የሚባል ሰው ግን የኤድዋርድን ቢሮ ረግጦ አያውቅም፣ በስልክም ከአለቃየ ጋር እንዲህ ያለ ሰም አስከዛሬ አላገኘሁም ነው የምትለኝ። ኢስቲል ሚስጥር አትደብቀኝም፣ እምናታለሁ›› አለቻት።

ቪክቶሪያ ፈገግ አለች። ‹‹በጣም አመሰግናለሁ ወይዘሮ ክሮው›› ብላ መነጋገሪያውን አስቀመጠችው። አሁን ጥረቷ ባለመሳካቱ ብቻ ሳይሆን በሌላ ነገርም መረበሽ ሊኖርባት ነው። ከመሰንባበታቸው በፊት ራምሲ ማንሻውም ነገር ከወይዘሮ ክሮው አልፎ ሶስተኛ ሰው ጆሮ መድረስ እንደሌለበት የመከራት ታውሳት። አሁን የአለቃዋ ዐሐፊ ጆሮ ውስጥ ገብቷል፣ ምናልባት ኢስቲል ነገሩን ሰራ በዝቶበት ለሚዋከበው አለቃዋ ሽክ ለማለት የሚዘው ጠቃሚ ነገር አልመሰልሽ ብሎ ካልታያት በስተቀር የቪክቶሪያ እንቅስቃሴ አራተኛ ሰው ሊሰማው ይችላል፣ ያ ሰው ደግሞ ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቴድ ሊሆን ነው። ያም ሆነ ይህ ቪክቶሪያ ጭንቀቷን ወደጎን አድርጋ ወደ ፊት ምን መስራት እንዳለባት ማሰላሰል ያዘች።

* * *

ዛሬ ሊሊቱን መሉ እንትልፍ እንደማትተኛ ቪክቶሪያ አስተድማ ተገንዝባለች። ከወይዘሮ ከሮው ተጥሎ ራምሲ አሜሪካ ሲመለስ እንድታነጋግረው ጠቁሟት ለነበረው ሁለተኛ ሰው አመሻሽ ላይ ደውላ የማርክ ብራድሾን አድራሻ እንዲያስፈልግላት ጠይቃው ነበር። ከማማሽ ለዓት በፊት ሰውየው ደወለላት። መልሱ ግን ያው የተለመደው አይነት ነበር። ‹‹ትሰሚኛለሽ? ማርክ ብራድሾ የሚባል የሪኮርድ ጋዜጠኛ የለም፣ ሊኖርም አይችልም›› አላት ቁርጥ አድርጎ።

ጥያቄው ግን አሁንም አልተመለሰላትም። በአእምሮዋ እየተመላለሰ እረፍት ማሳጣቱን እንደተጠለ ነው። እናም ይህን ያልተመለሰ ጥያቄ በሀሊናዋ እያንጓለለች፣ እያመነገፐከች እንትልፍ ልትተኛ አትችልም።

እስከ እኩለ-ሌሊት ድረስ አልጋዋ ላይ ስትገላበጥ አምሽታ በመጪረሻው በገዛ ፈቃዷ ተነሳች። እንትልፍ ለነሳት ነገር ጊዜያዊ መፍትሄ ማግኘት ነበረባት።

በቀጥታ ወደ ዋሽንግተን ደውላ በዚያ ከሚገኘው የኒውዮርክ ሪኮርድ ብሔራዊ የፕሬስ ህንፃ ጋር ተገናኘች። እንደ እድል ሆኖ ኒክ ራምሲ ስራ ላይ አለ። በስልክ አነጋጋዋ አማካኝነት መስመር ላይ ጓደኛዋን ስታገኘው የቸኮነት ሽክም ከላይዋ ላይ የወረደ መሰላት። ‹‹ኒክ፣ ቪኪ ነኝ›› አለችው ፈጠን ብላ።

ራምሲ ከልቡ ደስ እንዳለው በድምፁ ያስታውቃል። ‹‹የት ሆነሽ ነው?›› አላት።

‹‹ፓሪስ።››

‹‹እስካሁን ላትተኚ?››

‹‹ሃሳብ በዛብኝ። እንተን ማነጋገር እፈልጋለሁ። አንድ የምነግርህ ነገር አለ. . .››

‹‹መጀመሪያ እኔ ልንገርሽ።›› አቋረጣት። ‹‹በሎድሪስ ላይ ያተረብሽው

ዕሁፍ እጅግ የሚደነት ነበር። እጅግ በጣም። መቼም ትናንት ማታ ሎድሬስ ላይ የደረሰውን ነገር ሳትሰሚ አልተረሽም።››

አፏ ያለወትሮው ፈጠነ። ‹‹ኧረ የለም። ምን ተደረገ?››

‹‹አዲጋ›› አለ ራምሲ። ‹‹ጳጳሱ ብዙ ሺህ ሀገብ ሲሰግድ ወደነበረበት የመራት ውስጥ ጸሎት ቤት በመሄድ ላይ ነበሩ። መፀለያው ውስጥ የነበረው ሀገብ ከመብዛቱ የተነሳ ግፊያውና ትርምሱ ከቁጥጥር ውጭ በሆነበት ደቂቃ ድንገት መብራት ይጠፋል። ያተረፋቸው እጅግ የተጠናከረው ዘቫቸው ያደረገላቸው ጥበቃና ክለላ ነው። መጨረሻ ላይ መብራት ሲበራ በ,ያንስ አርባ ሰዎች የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው ተገኙ። ብዙዎቹ ሳይሞቱ አይቀሩም. . .››

‹‹ግን ጳጳሱ ሳይጎዱ ተረፉ?››

‹‹ነገርኩሽ፣ ጠንካራ ጥበቃ ስለተደረገላቸው በሰላም ወጥተዋል።››

‹‹ኒክ እውነቱን ነው የምልህ፣ እኒያ. . . እነማንም ይሁኑ. . እኒያ ልማደኞች ናቸው ሆን ብለው መብራቶቹን ያጠፉአቸው። አልተሳካላቸውም እንጂ ጥንሰሳቸው ጳጳሱን ለመጥለፍ መሆን አለበት።››

‹‹አ! እዚህ ላይ አበሳሽው፣ ቨኪ። የምትይውን በተመለከተ የተገኘ ማስረጃ የለም። ተደም ብሎ የታቀደ ነገር ቢሆን ኖሮ እንደተለመደው ማርክ ብራድሾ ዘግቦውን ይሆ በሪከርድ የመጀመሪያ ገፅ ላይ ብት ይል ነበር። ትክሱን ዜና ሪኮርድ አላገኘውም ማለት አስተድሞ የተወጠነ ታሪክ የለም ማለት ነው።››

ቨክቶሪያ እየር ወደ ውስጥ ስባ በረጅሙ ከተነፈሰችው በኋላ ‹‹ኒክ›› አለች። ‹‹ይኸ የምትለው ዘግቦ፣ ፍፁም ውሸት ነው።››

‹‹አልገባኝም።›› አላት።

‹‹ይኸ በሁሉም አቢይ ዜና ላይ የብራድሾ ዘጋቢ ሆኖ መትረብ ፍፁም ውሸት ነው። ስለመጥ ባህር ቅርሶች ዘረፋ የገፈው ነገር የለም። ሌሎቹንም ቢሆን እሱ የጻፋቸው ዘግቦዎች አይደሉም። ባጠቃላይ ማርክ ብራድሾ

የሚባል ጋዜጠኛ የለም።››

ከዋሽንግተን በኩል የመልስ ድምጽ ጠፍቶ ጥቂት ከቆየ በኋላ ‹‹ቪኪ፣ ምንድን ነው የምታወሪው?›› አለ ራምሲ።

‹‹ሰሞኑን ብራድሾን በተለያየ መንገድ ሳስስው ነበር የሰነበትኩት። እነግሪ ያልከኝን ሰዎች ሁሉ ጠይቂአለሁ። ብራድሾ የሚባል ጋዜጠኛ አውንም ሆነ ከዚህ በፊት ሪከርድ ጋዜጣ እንደማያውቀው አረጋግጫለሁ። የደወልኩልህም ለዚህ ነው። ነገሩን እያምሰለሰልኩ ልቀውስ ምንም አልቀረኝም። ምን ይመስልሃል?››

ራምሲ ጥቂት ሲያሰብ ቆይቶ፣ ‹‹እኔ እንኛ ቪኪ›› አለ፣ ‹‹ምን እንደሚሰማኝ እርግጠኛ አይደለሁም።››

‹‹ግን እኒያን ሁሉ ዜናዎች ከኛ ቀድሞ የሚዘግብ አንድ ሰው መኖር አለበት። የኔ ጥያቄ ያ ሰው ማነው የሚል ነው።››

‹‹እኔ እንኛ ቪኪ›› አለ ራምሲ አውንም።

‹‹የስፓኙን ንጉስና የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ዐሐፊ መጠለፍ፣ የእስራኤሉን ጠቅላይ ሚኒስትር መግደልና የትሪሶቫን መዘረፍ ሁሉንም ከሁሉ ሰው በፊት ደርሶባቸው ለሪከርድ ያቀበለው አንድ የሪከርድ ሰው ነው። ግን ማነው እኒህን ሁሉ ነገሮች ልክ ሲፈፀሙ በቦታቸው ተገኝቶ ዘግቦ በዚያው ትጽበት ለሪከርድ የሚሰጠው? ሰማ ኒክ፣ አንድ አማራጭ ይታየኛል። ሚስተር ኤድዋርድ ከሽብርተኞቹ ጋር ግንኙነት አለው። እንዲያውም የሽብርተኞቹ የራሳቸው አባል ከሆነ ሰው ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል። ያ ሰው ደግሞ ሽብሮቹ በተፈፀመበት ትጽበት ድርጊቶቹን በተመለከተ ለኤድዋርድ ሰነድ ይሸጥለት ይሆናል። ምን ይመስልሃል?››

‹‹የለም። ይኸ እንኳ አያመስልም።››

‹‹እሽ. እንግዲያውስ እኔ ሌላ መልስ የለኝም። መልሱን ካንተ ጠብቁ ነበር።››

‹‹ለጊዜው መልስ የለኝም። እስኪ ላስብበት። አውን ግን ወደ ዋይት

ሐውስ ሄጀ ፕሬዝዳንቱ በለንደኑ ውይይታቸው እጀንዳ ላይ የኑክሊየር መሳሪያዎችን ቅነሳ ጉዳይ ጨምረውበት እንደሁ ዝግ ዊስኮን የሚሰጡትን መግለጫ ለመስማት ችኩያለሁ።››

‹‹ይሁን›› አለች ቨክቶሪያ እንደተከፋች፣ ‹‹ለአባቴ ሰላምታ አትርብልኝ።››

‹‹ስሚ ቨኪ፣ በነገሩ አስበበታለሁ። በትርቡ ፕሬዚዳንቱ ከእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ለንደን ላይ ይገናኛሉ። አባትሽ በሪፖርተርነት ስለመረጡኝ እኔም ለንደን መምጣቴ አይቀርም። እንደምንም ሾለክ ብየ ከለንደን ወዳንቺ ለመምጣትና ነገሩን በስፋት ለመነጋገር እሞክራለሁ። ምን ይመስልሻል?››

‹‹እሰከዚያ መጠበት አልችልም፣ ኒክ።››

‹‹ታዲያ ምን ልታደርጊ ወሰንሽ?››

‹‹ይሀን ጥያቄ ለመመለስ ያለ አረፍት እደክማለሁ። የፊለገው ይምጣ።››

* * *

ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቱድ ቀደም ሲል በደዘው ቀጠሮ የተደወለለትን ስልክ ለአስር ደቂቃዎች ያህል አነጋግሮ ወደመጨረሱ ነው።

‹‹እሽ፣ አግባብ ነው ፓጋኖ›› አለ፣ ‹‹ቢሳካ ደስ ይለኝ ነበር። ግን አልሆነም። ኩፐር እንደሚለው ሁሉንም ዘዮች ማሸነፍ እንደማይችል ተረድቶታል። በነገራችን ላይ ቅሬታ እንዳይሰማው በኔ ስም ንገርልኝ። ምናልባት የሚቀጥለው ተልዕኮ ቀለል ይለው ይሆናል። በተጠንቀት እንዲጠብቀኝ ንገረው።››

ኤድዋርድ ስልኩን እንደዘጋ ቀና ሲል ሃሪ ዴትዝ በሩ አጠገብ ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ ቆሞ ተመለከተው።

‹‹ሄይ ሃሪ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ? ዛሬ እረፍት ልታደርግ አልነበረም?››

‹‹እፈልግህ ስለነበር ከዚህ አካባቢ አልራትሁም። የያዝከው ስልክ

ከፖሊኖ ጋር እንደሆነ ስላወቅሁ እስክትጨርስ ስጠብቅ ነበር›› አለና ሃሪ ወደ ውስጥ ገብቶ በሃሳብ እንደተመሰጠ ከኤድዋርድ ጠረጴዛ ፊት ለፊት ወዳለው ወንበር ተራምዶ እንደተሸማቀቀ ተቀመጠ። ‹‹ሎድረስ የተሰራውን ስህተት ነግረህ?››

‹‹ስህተት ሳይሆን ከመነሻው የማይቻል ሙከራ ነበር። መብራቱን አጥፍተው ሰዎቻቸውን በትክክለኛው ቦታ መድበው ነበር። ግን የሰው ብዛትና ግፊያው ከቁጥጥር ውጭ ሆነ። በዚያ ላይ በጸጸት ዙሪያ የነበረው የደህንነት ጥበቃ እጅግ የበዛ ኃይል ነበር። የነገሩ መሳቅት ስላጠራጠረው ኩጦር ተልዕኮው እንዲጨናገፍ አደረገ። የዚህ አመቱ ስራችን እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ግብ ባለመምታቱ ብዙም በድል የማይወጡትን ተማባር እንዲሞክሩ አልፈልግም።››

‹‹ትክክል›› አለ ሃሪ ዴትዝ።

ኤድዋርድ የረዳቱን ግዕታ ሲያነብ አንድ ምልክት ያነበበ መሰለው። ‹‹ፈትህን ሳየው ነገር የረበሸህ ትመስላለህ ሃሪ። ምን እያሰብክ ነው?››

‹‹ያች አዲስ ተቀጣሪ፣ ቨክቶሪያ ዊስተን ከክልሷ ውጭ እያነፈነፈች መሆኗን ሰምተሃል?››

‹‹እንዴት?›› ኤድዋርድ አልገባውም።

‹‹ማርክ ብራድሾን ውለዱት እያለች ሰምትን ታሳጥጣለች።››

ኤድዋርድ ትከሻውን በንቀት ሰበቀና ‹‹የትም አትደርስም›› አለው።

‹‹ከፖሪስ እዚህ እየደወለች ወይዘሮ ከሮውንና የራስህን ዐሐፊ በጥያቄ አስጨንቃቸዋለች።››

‹‹ይህ አዲስ ነገር አይደለም፣ ምቀኝነት ነው። ብራድሾ ከእሷ ላይ ብዙ አዚይ ወሬዎችን እየነጠቀ ስላስቸገራት ትናት ፈጥርቅታል። ሰውየውን አግኝታ ከዒ የበለጠበትን ጥበብ ለመቅሰም ትፈልጋለች ማለት ነው። ሞትኩ ላወራ በላት። የትም አትደርስም።››

‹‹ግን. . .›› ሃሪ ነገሩን በአምንታ ሊያልፈው አልፈለገም። ‹‹ይህን

ማነፍነፍ እኔ አልወደድኩትም። ጠንቀቅ ማለት አለብን። ስራችን ሁሉ አደገኛ ነው። ጥቂት ጋብ ብንል?››

‹‹ምንድን ነው እንዲህ የሚያንበቀብቅህ ሃሪ? የአለም እንቁ፣ የሰው ልጅ ምርጥ ዘር መሆንህን ካረጋገጥህ በኋላ ማፈግፈግ የማይሞከር ነው።››

‹‹ላልመከርህ እንዳልተር ብየ ነው፣ አለቃ›› አለ ሃሪ እየተፈፈው።

ኤድዋርድ የረዳቱን የተጨፈገገ ፊት ሲያይ ጥቂት በረድ ብሎ በአምንታ ራሱን ነቅንቅ አደረገና፣ ‹‹መልካም ሃሪ›› አለ፣ ‹‹እስኪ ከራሴ ጋር ልምከር። ነገ ምን እንደሚያመጣ እንጠብቅ።››

* * *

ነገ ታይም መጽሔትን ይዞ ነጋ።

ፊቱ እንደ ቂት ዐሐይ የሚያበራው ኤድዋርድ አርምስቱድ የታይም መጽሔትን አንድ ቅጅ ይዞ ነበር ቂት ቢሮ የገባው። ሃሪ ዴትዝ እንግዳ መኮመኛው ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ፣ ይጠብቀው ኖሯል።

ኤድዋርድ እየተፍለቀለቀ መጽሔቱን ከፍ አድርጎ ይዞ በፊት ለፊት ሽፋን ላይ የሚታየውን የራሱን ጉልህ ፎቶግራፍና ከጎላው የተላለውን መልኩ በውል የማይለየውን—ምናልባትም ማንነቱ ያልታወቀውን ማርክ ብራድሾን ለማመልከት የተነደፈውን—ምስል በእጁ ይጠቁማል። በሽፋኑ ላይ ከኤድዋርድ ምስል ጋር ‹‹ምንሰናት›› የሚል ጽሁፍ በትልቁ ይታያል።

‹‹አይተኸዋል ሃሪ?›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹መጥፎ አይደለም፣ አይደለም?››

ሃሪ ራሱ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን መጽሔት ብድግ እያደረገ ‹‹አይቸዋለሁ። ፅሑፉንም አንብቤአለሁ›› አለው።

ኤድዋርድ ወደ ወንበሩ ሲያመራ ደስታው ከግንባሩ ይነበብ ነበር። ‹‹ፎቶው እኔን ይመስላል አይደል። ጥቂት አስገልጭሻል ልበል?››

‹‹ፎቶው እንከን አይወጣለትም።›› ሃሪ አረጋገጠለት። ‹‹ጠንካራ፣ ትኩስና አርቆ አሳቢ አድርጎ ነው ያቀረበህ።››

«ከዚህ የተሻለ ልነሳ አልችልም» አለ ኤድዋርድ ወንበሩ ላይ እየተቀመጠ። የመጽሐፉን ሽፋን ፈገግ እንዳለ መመልከቱን ግን አላቋረጠም። «ምንተሰኘት» ሲል የሽፋኑን ርዕስ አነበበው። «ምንተሰኘት እንዴት ይመስለሃል?»

«እውት ምን ይሳንሃል!» ሃሪ ተበሳጨ አድርጎ መለሰ። ኤድዋርድ በእድናቆት ራሱን ነቀነቀ፣ «አባቱ እንኳ ያን ያህል በመን ይሆን መሳይ ስም ወጥቶለት አያውትም።»

«ከውስጥ የተጻፈልህን ዕሁፍ አንብበኸዋል፣ አለታ?»

«እንዴታ! በሚገባ አብራርተውሻል። ሃና እንኳ ወዳዋለች።»

ሃሪ ለአፍታ ተምታቶበት ነበር። ወዲያው ግን አስታወሰ። «ባለቤትህም አንብባዋለች?»

«ስለኔ ማወት ፈልጋ ነበር።» ኤድዋርድ ከት ብሎ ሳቀ። «አሥ፣ አሮጊቷም ወዳዋለች። ምን ይመስልሃል ሃሪ?»

«ግሩም ዕሁፍ ለመሆኑ ጥያቄ የለውም። ጥቂት ብራድሾን በሚመለከት ሰውየውን በሌላ የዜና ድርጅት እንዳንነጠት ሆን ብለን እንደደበቅነው ተደርጎ የተረበ ትችት እንጂ ሌላው የሚደነት ዕሁፍ ነው። ጽሁፉን ተከትለው የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት የሚደውሉ ከፍሎች ቁጥር ለበሐፊህ አታከርት ነበር የሞለው። በሐፊህ ጊዜ ስታጣኝ እንድትመለከታቸው አንዳንዶቹን መገማባልሃለች። እንዲያውም እኔ ራሴ በጣም ጠቃሚ የሆኑትንና አሁኑኑ ብታያቸው ይሻላል ያልኳቸውን መርጨ አምጥቼልሃለሁ።»

ሃሪ ዴትገ ከንግግር ጋር ጠረጴዛው ላይ አስተምጧቸው የነበሩትን ወረቀቶች አነሳቸው።

ኤድዋርድ ወረቀቶቹን ወዲያው ለቀም አደረጋቸው።

«አንደኛው የፕሬዚዳንቱ የፕሬስ በሐፊ የሽግ ዊስተን ሲሆን ፕሬዝዳንቱ ራሳቸው የደስታ መግለጫ መልእክት ማትረባቸውንና ወደ ሰንደን ከመሂዳቸው በፊት በጥይት ሐውስ የራት ግብዣ ፕሮግራም

እንደያዙልህ የሚገልጽ ነው።››

ኤድዋርድ መልእክቱን አነበበና ‹‹እንዴት ታየሞለህ ሃሪ?›› ሲል ረዳቱን ጠየቀው።

‹‹ፕሬዚዳንቱ ሰሞኑን ብዙ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ስላለባቸው ጊዜ ያጥራቸዋል። እንተን ለማስተናገድ ከሆነ ግን የፈለገውን ጊዜ መስዋእት ያደርጋሉ። ያንተ ውሳኔ ነው የሚጠበቀው።››

ኤድዋርድ አሁንም የመገረም ገፅታ ይነበብበታል። ‹‹በዚች አለም በተነደለው ተዳዳ ሁሉ መጠቀም ያስፈልጋል›› አለ። ከዚያም በድጋሚ ወደ ታይም መጽሔት እያመለከተ፣ ‹‹እና ዕሁፉንና ፎቶውን ረክተህበታል?›› ሲል ረዳቱን ጠየቀው።

‹‹በጣም›› ብሎ ሃሪ ጥቂት ዝም አለና ‹‹በመጠኑ የሚያሳስበኝ ግን ማንነትህ ይህን ያህል የሁሉም የመነጋገሪያ ጉዳይ መሆኑ እንዳንድ ከፍሎች በእንቅስቃሴህ ላይ እንዲያንጎራበቡና የለት ተለት ተግባርህን እንዲከታተሉ ያደርጋል የሚል ሃሳብ ነው። ለመሆኑ ትናንት በተነጋገርንበት ጉዳይ ላይ ልታስብበት ሞክረሃል?››

አሳታሚው ግንባሩን ቋጠረ። ‹‹የሰጠኸኝ ምክር ማለትህ ነው? አዎ፣ አስበሰበታለሁ›› ካለ በኋላ ተሸክርካሪ ወንበሩን ወደፊት ወደኋላ እየናጠ የረዳቱን አይን የጎረጥ ተመልክቶ ‹‹ልክ ነህ›› አለ፣ ‹‹ምክርህን ለመቀበል ወስኛለሁ። ድርጊታችንን እናቆማለን። . . . ግን አንድ ይቀረናል፣ አንድ ታላቅ ተግባር።››

‹‹ይህ አንድ ነገር ለመሳካቱም ቢሆን እርግጠኛ አይደለሁም አለታ?››

‹‹አኔ ግን እርግጠኛ ነኝ›› አለ ኤድዋርድ ሳያወላውል። ‹‹የምንዘው ሽቅብ እንጂ ቁልቁል አይደለም። አንድ ጊዜ እኪር የሠረለት ሰው በሎድረስ እንደገጠመን ሽንፈት በመሰለ ነገር አይደለም ተልዕኮውን የሚደመድመው።››

‹‹ግን በሎድረስ መሸነፋችንን ግን ያውታል?››

‹‹እኔ አውታለሁ፣ ሃሪ። ስራናን የምጽፈውና የማበታው በድል መሆን

አለበት። እንድ የመጨረሻ፣ ግን ከበፊቶቹ ሁሉ የበለጠ ታላት የድል ሞገድ ይቀረኛል።›› ፊቱ በፈገግታ ወግግ አለ። ‹‹ምን እንደማደርግ ጠንቅቁ አውቃለሁ ሃሪ። በምንተሰኛት ላይ መሉ እምነት ይኑርህ።››

ሃሪ በረጅሙ ተነፈሰ። ‹‹እንደፈለግህ።››

‹‹የመጨረሻው ነውኮ።›› ታል ግባ፣ ‹‹ይልቅስ ለመጨረሻው ተግባር በፍጥነት እንንቀሳቀስ።››

‹‹መልካም›› ነበር የሃሪ መልስ።

‹‹ፓጋኖን እንደገና ፓሪስ እንዲሄድ ንገረው። እንዲያውም ከኔ ጋር አገናኘኝ። ከኩፐር ጋር አንድ ውይይት እንዲዘጋጅልኝ ልነግረው አፈልጋለሁ፣ ነገ ማታ ፓሪስ በላንካስተር ሆቴል።››

ሃሪ ሽምቅቅ አለ። ‹‹አለቃ፣ ጥቂት አስብበት። ያቺ ወፈ የጠማት ቪክቶሪያ ዊስተን ያለችው ፓሪስ እንደሆነ አትርሳ። ብታይስ?››

‹‹ልታየኝ አትችልም!›› አለ ኤድዋርድ ነጠቅ አድርጎ። ‹‹በላንካስተር ሆቴል የምቆየው አንድ ምሽት ብቻ ነው። ከሆቴሉ ደግሞ አልወጣም። ከመሰለህ ልጅቷን ለንደን ሂዳ እስክደውልላት እንድትጠባበቅ ማዘዝ እችላለሁ።››

‹‹ይሽ ጥሩ።››

‹‹በነገራችን ላይ፣ የመጀመሪያው ነገር መጀመርያ። መጀመሪያ ከፓጋኖ ጋር አገናኝኝ። ስትወጣ ደግሞ እግረ መንገድህን ለነገ ዒት ጉዞ የፓሪስ ቲኬት እንድታሲዝልኝ ለኢስቲል ትነግርልኛለህ።›› ሃሪን እየተቅለሰለሰ ተመለከተው። ‹‹እውነቴን ነው የምልህ ሃሪ፣ የአሁኑ ሥራችንን ዳር ማድረስ አለብን። ጉድ አንድ ሰሞን ነው።››

* * *

እንትልፏን ሳትጨርስ የስልኩ ጩኸት ተሰቀሳት። እንደምንም ብድግ ብላ አነሳችው።

‹‹ሄሎ።››

‹‹ሃይ ቪክ፣ ኒክ ሃኝ። እንትልፍሽን ረበሽኩሽ?››

‹‹የለም፣›› አለች ቪክቶሪያ። ‹‹በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ያንተን ድምፅ መስማት አይረብሸኝም። ግን ምነው? አዲስ ነገር አለ?››

‹‹ለጥያቄሽ መልስ የለኝም። አዲስ ነገር አለም፣ የለምም። ባለፈው ያደረግነው ውይይት አፈጻጸም አሳረካኝም።››

‹‹እንዴት ነበር የተፈፀመው?››

‹‹ኤድዋርድ እኒያን ሁሉ አቢይ ዜናዎች እንዴት ከሰው በፊት እንደሚያገኛቸውና በህይወት የሌለ ብራድሾን የዜናዎቹ አቅራቢ አድርጎ እንደሚያሳትም ያላመንሽበት ነገር መኖሩን ነበር የነገርሽኝ። እኔ ደግሞ በሳምንትና በአሰር ቀናት ውስጥ ለንደን ሰለምመጣ በነገሩ እንደማስብበትና ሾለክ ብየ ወዳንቺ ፓሪስ መጥቼ እንደምንነጋገርበት አውግቼሽ ነበር። አንቺ ደግሞ. . .››

ቪክቶሪያ አቋረጠችው። ‹‹እኔ ደግሞ ‹ይሀን ጥያቄ ለመመለስ ያለ አረፍት እደክማለሁ። የፈለገው ይምጣ ብየህ ነበር።››

‹‹የደወልኩልሽ ለዚህ ነው። አሰካሁን ምን ሰራሽ?››

‹‹የደረስኩበት ነገር የለም። ነገሩ ድፍንፍን ያለ በመሆኑ ወዴት እንደማመራ ተወናብዶብኛል።››

‹‹ምናልባት ልረዳሽ እችል ይሆናል›› አለ ራምሲ። ‹‹በነገርሽኝ ሃሳብ ላይ በጥሞና አስቢበታለሁ።››

‹‹ቶጥል!›› አለች በጉጉት።

‹‹ያንቺ ግምት ኤድዋርድ ከአንድ የሽብር ፈጣሪ ቡድን አባል ጋር ግንኙነት ፈጥሯል የሚል ነው። ግምትሽ እውነት ባይመስለኝም ሌላ አማራጭ ስለሌለኝ በሃሳብሽ ተስማምቻለሁ ልበል። አለቃችን ከፋኖ ጋር ግንኙነት ካለው ያ ፋኖ የካርሎስ ቡድን አባል መሆን አለበት አላለሁ። በትርቡ የተፈፀመ ሽብርኝን ለማነሳሳስ አትም ያለው ቡድን የካርሎስ ብቻ ነው። በዚህ እንደማትስማሚ አውቃለሁ።››

‹‹በዚህ ነጥብ ላይ ማንኛውንም አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ። እሽ ካርሎስ ነው እንበል። ምንም እንኳ ኤድዋርድ በወታደር አስፈልጎ ሊያሰቃዩው አለመቻሉን ቢነግረውም. . .››

‹‹የኔ እመቤት፣ አንቺ ራስሽ ስለኤድዋርድ ያለሽን ግምት እንቀበል ካልን ኤድዋርድ ማለት ተጣፊ ሰው ነው ብለን መደምደም አለብን። በዚህም መሰረት ካርሎስ የዜናዎቹ ምንጭ የሆነ ሰው ስለሆነ ሊያሰቃዩው አልሞከረም፤ ለፖሊስ ጠቆምኩበት ያለውም ውሸት ነው እንበል።››

‹‹ሞጣል!›› አለች፡ በትረካው እየተሳበች።

‹‹እንግዲህ ስሚኝ። አንድ ታላቅ ታሪክ ያዘለ ዜና ልሰጥሽ እችላለሁ። ለጊዜው ግን ከአንድ ሰዓት በፊት ምን እንደደረሰብኝ ልንገርሽ። እዚሁ ሀንፃ ውስጥ ጥቂት ውሃ እየወሳሰድኩ ነበርኩ. . .››

‹‹አሱማ ልማድህ አይደል›› ስትል አቋረጠችው።

‹‹. . .ድንገት ካርሎስ በጠለፈኝና ባንጋረኝ ወቅት የሆነውን ሁሉ ለመግፍ ወሰንኩ። እና መግፍ ጀመርኩ. . . ለጋዜጣ እንዳይመስልሽ ልፅፍ ያሰብኩት›› ካላት በኋላ ራምሲ ጥቂት እንደማፈር ብሎ ‹‹አየሽ ካርሎስን በተመለለ ገፀ-ባህርይ ላይ የሚሽከረከር ልቦለድ ድርሰት ለመግፍ ነው ውሳኔየ።››

‹‹በጣም ማሩም ኒክ›› አደነቀች ቪክቶሪያ።

‹‹አድናቆቱ ስራየን ስጨርስ›› አላት፤ ‹‹ያም ሆነ ይህ እውነተኛውን ታሪክ በማምሰለሰልበት ወቅት አንድ ነገር ተፈጠረ።››

‹‹ምን?››

‹‹ልብ በይ፤ ካርሎስ ካንጋረኝ በኋላ ሊለቁኝ ሲሉ ከድጥሮቹ እንደሻቸው በሚቀጥለው ቂት ቡድኑ ወደ አዲስ ስፍራ እንደሚዛወር ሲናገር መሰማቱን ላንቺና ለኤድዋርድ ነግሬአችሁ ነበር። ግን አሁን ታሪኩን መግፍ እስክጀምር ድረስ ትዝ ያላለኝ አንድ ያልነገርኳችሁ ነገር ታወሰኝ።››

ቪክቶሪያ መነጋገሪያውን ይበልጥ ወደ ጆሮዋ አስጠግታ በጭንና

ማጸመጫን ተጠለች። ‹‹ቮጥል! ቮጥል!›› አለችው ራምሲን።

‹‹'ወዴ ቁጥር 10 እንሳወራለን። መሰንበቻችንን እዚያው ማድረግ አለብን' ይል ነበር ፋኖው። በርግጥ እንዳቸውም በኔ ፊት ሚስጥር መናገራቸውን ከምንም የቆጠሩት አይመስለም፣ ምክንያቱም አይኔን በጨርቅ በመሸፈናቸውና እንደሸፈኑኝም ስለሚያስወጡኝ ፓሪስ ውስጥ የት አካባቢ እንዳለሁ ላውት እንደማልችል በነበራቸው እምነት ነው።›› ራምሲ ንግግሩን ጥቂት ቆም አደረገ። ‹‹አንቺ ግን ታውቂአለሽ ቨሂ። የት እንደወሰዱኝ ተከታትለሻል።››

‹‹ሪዮ ማርቱል ጎዳና ቁጥር 12 ላይ ኮሚፕኝ ሀንግ›› አለች ቨክቶሪያ ቀበል አድርጋ።

‹‹በዚያው ጎዳና ቁጥር 10 ሀንግ አይተሻል?››

‹‹ከ12 ቀጥሎ ያለው ነዋ።››

‹‹ታላቅ ዜና ቨሂ፣ ታላቅ ታሪክ. . . ግን ላንታመን እንችላለን።››

ቨክቶሪያ ስሚቷ ንር ነበር። ‹‹እንታመናለን! ያለጥርጥር!›› አለች።

‹‹እዚያ ስፍራ አካባቢ መታየትሽን አልደግፈውም ነበር፣ ግን በብራድሾ ፍለጋሽ መቀጠልሽን ካላቆምሽ. . .››

‹‹በጭራሽ አላቆምም።››

‹‹እንግዲያውስ ቁጥር 10 ድረስ ተጠጉተሽ ተከታተይ። ግን አንድ ሰው ማስከተል አለብሽ። ሲድ ሉታስን ወይም ከሱ ሰራተኞች አንዱን። ለዚህ ታል ግቢልኝ።››

‹‹አንድ ሰው ጨምሬ ለመሄድ እሞክራለሁ›› አለች። ማስከተል እንደማትችል ግን ልቧ ያውቀዋል። ፍላጎቷ በማሷ አንድ ጠንካሪ ነገር ልትሰራ የምትችል ጠንካሪ ሰው መሆኗን ማስመስከር ነው።

‹‹አካባቢውን በደንብ ተመልከች›› አላት ራምሲ፣ ‹‹ግን በማም እንዳትጠጊ፣ አደራ። እንቺን ማጣት አልፈለግም።››

‹‹ታስብልኛለህ?›› አለችው የሞኝ ሰው አይነት ደስታ እየፈነጥላት።

መልስ ከመስጠት ተቆጠበ። ኮስተር እንዳለ፣ «ልብ አድርጊ፣» አላት፣ «ሦስተኛድጂው ካርሎስን አይደለም።»

«የማሳድደው ታላቁን ታሪክ፣ ታላቁን ዜና ነው።»

«በርቺ» አላት፣ «ይቅናሽ።»

* * *

ፓሪስ ዶፍ ዝናብ ይበልጥ ባዘበደው የተሟለመለመ ምሽት ተጸፍናለች። በቻምፕስ ኢሊሲ ጎዳና ከዋናው መንገድ ብዙም ሳይርቅ ላንኸተር ሆቴል አዘትቱን ሞዴማ ከውስጡ በሚገኙት ክፍሎች ብርሃን ሊቋቋም በእምቢተኝነት የቆመ መስሎ በታላቅ ግርማ ሞገስ ይታያል። የሁሉም ክፍሎች መስኮቶች ከውስጥ የሚበራውን መብራት ያንፀባርቃሉ፣ በሶስተኛው ፎቅ ከሚገኝ አንድ ክፍል መስኮት በስተቀር።

በዚህ ሞዴማ ክፍል በተለይ ከመኝታ ክፍሉ በሚንጨለጨለው የራስጌ መብራት እገዛ እየተረዳ ጉስ ፓጋኖ አዲሱን የፊት መከለያ ከራሱ አስክ እንቱ ድረስ ለኤድዋርድ አርምስቱድ ያጠልቅለታል። «ስንት ናቸው ነበር ያልከኝ?» ሲል ጠየቀ ኤድዋርድ በመከለያው የአፍ ስንጥቅ።

«ላራስ ኩፐርና ኩማ ብቻ ናቸው።»

«የማዝናቸው ምን እንደሆነ ገምተዋል?»

«የለም፣» አለ ፓጋኖ። «ይህን የመሰለውን ተልእኮ ሲያቀርቡና ሲያዝዙ የሚገባው እርስዎ ብቻ መሆን አለብዎ።»

«በል ተዘጋጅቻለሁ» አለ ኤድዋርድ

ፓጋኖ የመኝታ ክፍሉን በር እንደከፈተ ሁለቱም ወደ አነስተኛ ሳሎን ገቡ። ሳሎኑ ከመኝታ ክፍሉ ይበልጥ የጨለመ ከመሆኑ የተነሳ ኤድዋርድ በገባበት ቅጽበት ያሉትን ሰዎች ማንነት መለየት ተርቶ አይኑን ቢዘነክሉት እንኳ ማዬት አልቻለም። የኋላ ኋላ ግን ሰዎቹን በአንደኛው የክፍሉ ጠርዝ በኩል ሶፋ ላይ ተቀምጠው አያቸው።

ከፓጋኖ ጋር ወደነሱ ሄዶ ኩፐርንና ኩማን እጃቸውን በመጨበጥ

ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ ከፌት ለፊታቸው በተዘጋጀለት ደረት መንበር ላይ ተቀመጠ።

‹‹እስካሁን ላደረጋችሁልኝ ፀሉ ሳላመሰግናችሁ አላልፍም›› አለ ኤድዋርድ በመጀመሪያ። ‹‹ይሀን ያለ ምንም መሰናክል ተልእኮአችሁ ይከናወናል ብየ አልገመትኩም ነበር።››

‹‹በሎድረስ ስለገጠመን ችግር እዝናለሁ።›› ኩፐር ይቅርታ ጠየቀ። ‹‹የጳጳሱ ጠባቂዎች ቁጥር ከጠበቅነው በላይ ስለሆነብኝ ጣጣ ውስጥ እንድንዘፈቅ አልፈለግሁም። ከመሸነፍ፣ ጥሎ ማለፍ።››

‹‹ውሳኔአችሁ ትክክለኛ ነበር›› አለ ኤድዋርድ፣ ‹‹ሊሎች ተልእኮዎቻችሁ ግን እንዘን የማይመጣላቸው ነበሩ።››

‹‹እትድ ነዋ›› አለ ኩፐር ነጠት አድርጎ። ‹‹ሆደረሰው ጉዳት ከቁጥር የሚገባ አይደለም። እስካሁን በፈጸምናቸው ተልእኮዎች የሰድስት ሰዎች ህይወት የጠፋ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከኛ ወገን የከፈልነው መስዋእትነት የአንድ ሰው ህይወት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በእንዲህ አይነቱ ተግባር ላይ እጅግ አነስተኛ ጥፋት ነው። ለከፈሉት ግንዘብ ትክክለኛ ዋጋ እንደከፈልንም ተሰፋ አለኝ።››

‹‹በትክክል›› አለ ኤድዋርድ። ከዚያም ከድምፁ ጥቂት ዘና ሊል እየሞከረ ‹‹ተልእኮዎቹን ለምን እንደፈለግንችውና አላማየ ምን እንደሆነ እስካሁን ሳትገምቱ አንዳልቀራችሁ እርግጠኛ ነኝ›› አለ።

‹‹ግምት ብቻ እንጂ እውነተኛ አላማዎን እስካሁን አናውቅም፣ ልናውቅም አልሞከርንም። ፍላጎታችን እይደለማ። የኛ እርካታ ትዕዛዘዎን ከመፈጸምና ደስ መሰኘትዎን ከማረጋገጥ ላይ ብቻ ነው። የሚከፍሉት ግንዘብ ዳጎስ ያለ ሰለሆነ አላማችን ትዕዛዘዎን መፈፀም ብቻ እንደሆነ ይኖራል። ለከፈሉን ግንዘብ እናመሰግንዎታለን›› አለ ኩፐር።

‹‹እናመሰግንዎታለን›› አለ ኩማ ተበል አድርጎ።

‹‹ግሩ ነው›› አለ ኤድዋርድ። ‹‹አንድ ሌላ ተልዕኮ አዘጋጅቼላችኋለሁ። ግንኙነታችንን በማዘዋት ተመሰጋግነን የምንለያበተው ይሀን የመጨረሻ

ተልእኮ ስትፈጽመልኝ ይሆናል።››

‹‹አንድ የመጨረሻ ተልዕኮ።›› አለ ኩፐር በረጅሙ ተንፍሶ። ‹‹ጥሩ፣ መቼም እርስዎን ራስዎን በግንባር እዚህ እንዲገኙ ያደረገዎ ከበፊቶቹ የላቀ ተልዕኮ በመሆኑ መሆን አለበት።››

‹‹ከበፊቶቹ ሁሉ የላቀ›› አለ፣ ኤድዋርድ እጆቹን ወደ ኮቱ ኪሶች እየከተተ። ከዚያም አንድ የተጣጠፈ ወረቀት ካወጣ በኋላ ተስ አያለ ገለጠው።

‹‹ተልዕኮዎችን ሁሉ በወረቀት አስፍሬ አላውቅም። ይህኛውን ግን ራሴ ነኝ በግል ታይፕ ያደረግሁት። ምክንያቱም የተልእኮው እንትስታሲ በሁሉም ላን ግልጽ እንዲሆን ፈልጌ ነው። አንድ ጊዜ ካነበባችሁት ቀዳድጄ አቃጥለዋለሁ። ይዝውላችሁ። ለኔ ጉዳይ ከሁሉም የላቀ ተልዕኮ ነው።››

ሁለቱ ፋኖዎች ዕሁፉን ባንድነት ካነበቡት በኋላ ኩፐር በግሉ በድጋሚ አነበበው። ከዚያም ወረቀቱን በጥንቃቄ አጣጥፎ ለኤድዋርድ ከመለሰለት በኋላ ‹‹የምንችለው አይመስለኝም›› አለ። ‹‹ልናደርገው አንችልም። በኛ መስመርና አትም ስር አይደለም። ሲበዛ ከባድ ተልእኮ ነው።››

ኤድዋርድ ክላይ ክላይ ይተነፍስ ነበር። ‹‹የግድ ማድረግ አለባችሁ። ሊሎችን አድርጋችሁ የለም?››

‹‹ይዝኛው ጥሁም የተለየ ነው።››

‹‹መቼም የተልእኮውን አላማ አትታወሙም›› አለ ኤድዋርድ በጥርጣሬ።

‹‹እንዴ በጥጹም፣ እኛ ተልእኮው ወይም በተልእኮአችን የሚጠፋው ሰው ጉዳያችን አይደለም። ችግራችን ይህ አይደለም። ችግራችን ይዝኛው ተልእኮ ከአትግሽን በላይ መሆኑ ብቻ ነው።››

‹‹ክፍያውን እጥፍ ባደርግላችሁም?›› አለ ኤድዋርድ በቁጭት። ‹‹አስር ሚሊዮን ዶላር ይጠብቃችኋል።››

ኩፐር ራሱን በአሉታ ነቀነቀ። ‹‹በፈለገው ግንዘብ ቢሆን አንችልም።

መሰረታዊው ችግራችን የትክክል ጥያቄ ነው። ያሰን አይኑቹን ተልእኮ ለማከናወን ትጥቁ የለንም። አውሮፕላን ማግኘት ይኖርብናል። አውሮፕላኑን ብናገኝ የሚያስፈልገንን አብራሪ ከየት እናመጣዋለን? በርግጥ እኛ ብቻ ሳንሆን የፈለገው ቡድንም ቢሆን የሚፈልመው ተልእኮ አይደለም. . ›› ኩፐር ጥቂት በማመንታት ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

‹‹ግንም አያችለውም። ክካርሎስ በስተቀር። ካርሎስ ግን ጂፐን ውስጥ ለዚህ ጉዳይ የሚጠቅምበት አውሮፕላን አብራሪ እንዳለው ሰምቻለሁ። ካርሎስና የሱ ቡድን ምናልባት ሊታዘዙልዎ ይችሉ ይሆናል። እንደሚችሉም እርግጠኛ ነኝ። ሌላ ቡድን ግን በጭራሽ አይሞክረውም፣ እኛም እንችለዋለን ብየ ልሞሽዎ አልፈልግም።››

ኤድዋርድ ከኩፐር ገለፃ አንድ ጭብጥ ሳይዝ አልቀረም። ‹‹ግን በርግጥ ካርሎስና ቡድኑ ተልዕኮውን ሲፈጽሙ ይችላሉ ብላችሁ ታምናላችሁ?››

‹‹እንደሚችሉ አፌን ሞልቼ አረጋግጥልዎታለሁ። ነፋቱ ግን ቢችሉም ፈታድኛ አይሆኑም።››

‹‹ለምን?››

ኩፐር አላማኝ በሆነ ግለፅ አነጋገር ያብራራ ጀመር። ‹‹ነገሩ እንዲህ ነው። እኔና ተከታዮቼ ብንሆን ኖሮ አላማችን ግንዘብ በመሆኑ ጥቅም ለሚያስገኙልን ተልእኮዎች ሁሉ እንዋዲታለን። እና በኛ በኩል ብዙዎቹ እንቅስቃሴዎቻችን የሚከናወኑት በገቢ ምንጮቻቸው ነው። ካርሎስንና ድርጅቶቹን በተመለከተ ግን ሁኔታው የተለየ ነው። የግንዘብ ሰዎች እንዳይመስሉዎ። አማኞች ናቸው፣ ሀይማኖቸውን የሚሰጪለት እምነት ያዘው የተነሱ ወግ አጥባቂዎች ናቸው፣ የርስዎን ግንዘብ ከምንም አይቆጥሩትም። እንደ ሃይማኖት የሚያምኑበት አላማቸውን ለማራመድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፍጡራን ናቸው። እርስዎ ሊያስፈጽሙ ከሚፈልጉት ተልእኮ ጀርባ ያለውን አላማ ሲመረምሩ የፖለቲካ ጎን ስለሚያጠበት የፈለጉትን ግንዘብ ቢከፍሉዋቸው እሽ አይሉዎትም።››

ኤድዋርድ በፊት ሽፋኑ የእይን ቀዳዳ ኩፐርን በእትኩሮት ይመለከተው ነበር። ‹‹ተልእኮአቸውን የማድ እንዲፈጽሙ የሚገፋፋቸው አላማ

ባቀርብላቸውስ?››

‹‹ምን አይነት አላማ?››

ኩፐር በቅጽበት አድናቆትና ጉጉት የተሞላዬበት ገፅታ ይነበብበት ጀመር።

ኤድዋርድ አሁንም ኩፐርን አተኩሮ መመልከቱን እንደቀጠለ ነው። ‹‹መጀመሪያ እናንተ የካርሎስ ቡድን ሊታወሙው በማይችል ሁኔታ ትዕዛዜን የሚቀበልበት ግዴታ ውስጥ የሚያስገባው አንድ ሰው እንድትጠልፉልኝ እጠይቃችኋለሁ። እናንተ ይህን ሰው ትጠልፉልኛላችሁ፣ ሰውየውን ለመልቀቅ የካርሎስ ቡድን የምትጠይቁት ደግሞ የኔን ተልዕኮ እንዲፈፅም ማዘዝ ነው። ሰውየው በዚህ ደቂቃ ዩት ቢታ ሊጠለፍ እንደሚችል አውቃለሁ። ይሀን ሰው ለመጥለፍ አስር ሚሊዮን ዶላር እከፍላችኋለሁ።››

ኩፐር በጉጉት አይኑን አፈጠጠ። ‹‹ግን ማንን ነው የምንጠልፈው?››

ኤድዋርድ ምራቁን ዋጠ። ‹‹ካርሎስን ራሱን።››

ክፍሉ ውስጥ ያሉት ሶስት ሰዎች አይኖቻቸውን ኤድዋርድ ላይ ተክለው።

ኤድዋርድ አሁንም ምራቁን ዋጥ አደረገ። ‹‹ካርሎስን አጥናችሁ ትይዙልኛላችሁ›› አለ በድጋሚ። ‹‹ካርሎስን ለማግኘት ሲል የካርሎስ ቡድን እኔ ያዘዝኩትን ከመፈጸም አማራጭ አይኖረውም። ምን ይመስላችኋል?››

12

ከሶስት ዓመታት በፊት በውጥረቱ ብቻ የሚያስበረግግ ጠብደል ሳለ የግዛውንና አሁን ግን በሰውነት መከሳት የተነሳ ካሥርቱ ሊመስል ትንሽ የቀረውን ኮቱን ለብሶ ከሪዩ ማርቱል ቁጥር 12 ሀንግ ብት አለ።

በትጽበት ግራ ተጉን ተገላመጠ። ራት ብሎ በመንገዱ ዳር ከምትታየው ሱት በደረቱ ሴት በስተቀር አካባቢው አረሞ ብሏል።

በሰፈሩ ዐጥ ማለት በመርካት ይመስላል፣ ካርሎስ ከንዑሁ አየር ትንሽ ከማገለት በኋላ በቀጥታ ኩርባው አጠገብ ወደቆመች ሲትረን አውቶሞቢል አመራ። መኪናዋ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ግን ካርሎስ አውቶሞቢሏን የፓሪስ ከተማ ታክሲ ለማስመሰል የተከለለላት የኪሎ ሚትር መቆጣጠሪያ በርግጥ መኖሩን ማረጋገጥ ነበረበት። አዎ፣ በርግጥ የርሱው ናት።

ጊዜ ሳያጠፋ ካርሎስ የኋለኛውን በር ከፍቶ ዘው ብሎ ገባ። ሾፌሩ ከካርሎስ መመሪያ እስኪሰጠው በመጠበቅ ሳይሆን አይተርም እንደ ድንጋይ ድርት ብሎ እንደተቀመጠ ነው። ወፈር ያለ ኮት ለብሶ ረጅም የሱፍ ፎጣ ከአንገቱ እስከ አፍንጫው የጠመጠመው ሾፌር እንደተለመደው ሰፈሙን ከፍያውን ጆሮው ድረስ አጥልቋል። እንደ ልማዱ ሳለ።

‹‹ብርድ የመታህ ትመስላለህ›› አለ ካርሎስ።

ሾፌሩ በአምንታ ራሱን እየነቀነቀ መሃረብ አውጥቶ በድምሚ ሳለ።

‹‹ባል እንሂድ ጂን›› ካርሎስ አዘዘ። ‹‹ወደ ዳኅል አውሮፕላን ጣቢያ በቱርክ አየር መንገድ ነው የምበረው። ታዲያ አትቸኩል። ሰፈ ጊዜ ስላለኝ

እንዲያውም የሚነበብ ነገር ለመግባት መንገድ ላይ መቆማችን አይተውም።››

ሾፌሩ አሁንም በአምንታ ራሱን ነቅንቆ ሳለን በእንድ እጁ በያዘው መሪተ ሊቆጣጠር የሚሞክር እየመሰለ በለላ እጁ ሞተሩን አስነሳ።

ጉዞ ተጀመረ። ሆነግ ቁጥር 12 እንደደረሱ ሾፌር ማርሽ ቀያሮ መሪውን በሁለት እጅቱ ከያዘ በኋላ ወደ ግራ በመሣር መኪናዋን በከባድ ፍጥነት ከመንገዱ አውጥቶ ጥቅጥቅ ዶለማ ከሞጠው ጠባብ መንገድ ውስጥ ድንገት ቸጥ አደረጋት።

በድንገተኛው ፍጥነትና በተከተለው ድንገተኛ አቋቋም ከመደገፈያው ጋር የተጋጨው ካርሎስ ሚዛኑን ለመጠበት በፅኑ መታገል ነበረበት። ‹‹አንተ የውሻ ልጅ! ምናባትክ እያደረግህ ነው?››

ካርሎስ በድጋሚ ጂን ላይ ሲሥነበት ሲል ሾፌሩ አስክ አፍንጫው የጠመጠመውን ፎጣ አውልቆ ወደኋላ ሦር ሲል ባየው ግዕታ ተገርሞ አፉን እንደከፈተ ቀረ። አሽከርካሪው የራሱ ሾፌር ጂን ሳይሆን አይቶት የማያውቅ እንግዳ ሰው ነው። ሾፌር እጁን ወደፊተኛው መተመጫ መደገፊያ ሰደደ። እጁ ድምፅ የለሽ አውቶማቲክ ሽጉጥ ደትኗል። ሽጉጡን ካርሎስ ማንባር ላይ እያነጣጠረ ‹‹አፍህን ዝጋ›› አለው ‹‹ብትንቀሳቀስ ትበላሻለህ››

በዚያው ቅጽበት የአውቶሞቢሏ የኋላ መሣኪያ ሽፋን ተበርግዶ ተከፍቶ ከውስጥ አንድ ሰው ተፈንጥሮ ከወጣ በኋላ ሽፋኑን በኃይል ሲዘጋው ሌላ ሁለተኛ ሰው መጥቶ ሁለቱም በግራ ቸኑ የኋላ በሮች ተንደርድረው በመግባት ካርሎስን ከጎንና ከጎናቸው አደረጉት።

‹‹ምንድን ነው?. . .›› ካርሎስ ንግግሩን ከመጀመሩ የተደቀነበት ሽጉጥ ከግንባሩ ሲነሳ እእምሮ የሚያስት ፈሳሽ የጠጣ የጥጥ ዲራዎ ባፍና ባፍንጫው ተጠቀጠቀበት። ካርሎስ ሲፈራገጥ ቢሞክርም የሁለቱን ሰዎች ጉልበት ሊቋቋም አልቻለም። ሾፌሩ አደንዛዥ ፈሳሽ የጠጣውን ዲራዎ ይበልጥ ባፍና ባፍንጫው ቀዳዳዎች ወደ ውስጥ ጠቀጠቃቸው። በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ የካርሎስ መጥፈርፈር ቆሞ ከግራና ቸኝ ጠላፊዎቹ ባንዴ እንድ ላይ ዝንጥፍ ብሎ አሸለበ። በዚያው አፍታ ለላው ጠላፊ ልምድ ባካበቱ እጆቹ የካርሎስን ደረትና ጀርባ ፈትሾ ከብብቱ ስር ያገኘውን አውቶማቲክ ሽጉጥ

ማረክ።

ሁለቱ ጠላፊዎች ካርሎስን ከወንበሩ አውርደው ወለል ላይ አንደመቱት።

‹‹እንንካ›› አለ አንደኛው።

ሾፌሩ መኪናዋን በመጣችበት በመመለስ ወደ ሪዮ ማርቱል ጎዳና በጥድፊያ ሲንዝ ድንገት ከኋላ ወንበር አንድ ድምፅ ሥሀ ብሎ ‹‹አቁም. . .›› አለው፤ ‹‹ያው መጣ።››

ከመንገዱ ወዲያ ማዶ የአንድ ሀንባ ጥላ ስላረፈበት በግልፅ የማይታይ የተዘጋ ሱቅ በር ተከፍቶ የአንድ ሰው ቅርፅ ከወጣ በኋላ ወደ አውቶሞቢሉ ይሮጥ ነበር። ሰውየው ከመድረሱ በፊት ከሾፌሩ ጎን የፊተኛው የሮኝ በር ተከፍቶለት ዘው ብሎ ከገባ በኋላ ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ምልክት ሰጠ። ይህ ሰው ጉስ ፖጋኖ ነበር።

ሾፌር ነጻጅ መስጫውን እየረገጠ፤ ‹‹ክቱጥር 12 ያየን የለም?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹ማንም›› ፖጋኖ አረጋገጠ። ከዚያም ፖጋኖ ወደ ኋላ ዞር ብሎ ‹‹ሆነ ኩማ?›› አለ።

‹‹ሀልሙን እየቀጨ ነው›› አለ ኩማ። ቀጥሎም ወለል ላይ የተዘረረውን በድን አካል በእግሩ እየረገጠ ከልብ በመነጨ ፈገግታ ግንባሩን ወጣ አድርጎ ‹‹ልጅት፤ ለአስር ሚሊዮን ዶላር የቀጠሙት ወንድ መሳይ ጉረኛ ይህ ነው›› አላቸው ሳይጥሮቹን።

አውቶሞቢሏ ፍጥነቷን ጨምራ ከሪዮ ማርቱል ጎዳና ወጥታ ተጓዘች።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ አንዲት ቀይ ፌኖ አውቶሞቢል ሪዮ ማርቱል ጎዳና ላይ ታዩች። ፌኖዋ አውቶሞቢል በከፍተኛ ፍጥነት ስትከንፍ ለተመለከታት የኒፖጋኖን ሲትረን እያሳደደች መሆኗ ያስታውታል። አሽከሪካሪዋ ቪክቶሪያ ዊስተን ነበረች።

* * *

ካርሎስ ወደ አእምሮው ተመልሶ አይኑን ሙሉ ለሙሉ መክፈት

እንደቻለ ዙሪያውን ሲቃኝ ሁለት ሰዎች ከፊት ለፊት ቆመው እንደሚመለከቱት አስተዋለ። ወዲያው ድግሞ ከአንድ ደረት ወንበር ጋር በጥብቅ መጠፈሩን፣ ከጉዱ ወደኋላ ተዘንጥሎ ከወንበሩ መደገፊያ ጋር መተብተቡን፣ ቲሸሞምሞሚዮቹ ከወንበሩ የፊት እግሮች ጋር መታሰራቸውን ተገነዘበ።

ካርሎስ ምላሱ በአደንዛዥ ፈሳሽ ንያል ጎልድፍበት እንደልብ አላንሣር ቢለውም የግዱን አንድ ጥያቄ ሊሰንዘር ቻለ። «እነማን ናችሁ?» ግራ ቀኙን በድጋሚ ቃኘ። ያለው ሞዶማ በዋጠው ሳሎን ውስጥ በመሆኑ በውል ለመለየት ተሳነው እንጂ ከፍሉ ውስጥ፣ በተለይ ከበስተጀርባው ሌሎች ሰዎች መኖራቸውን አላጣውም። ሁለተኛ ጥያቄ እንደምንም ሰነዘረ።

«የት ነው ያለሁት?»

«የትም ብትሆን አይጥንትህ» አለ ከሁለቱ ሰዎች ረዘም ያለው፣ ከካርሎስ ፊት ለፊት ባለ ወንበር ላይ እየተቀመጠ። «ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አብረን ስለምንቆይ ራሳችንን ብናስተዋውቅህ አይከፋንም። እኔ ኩፐር፣ ይሸው ደግሞ ኩማ ይባላል።»

ካርሎስ የወትሮ ድምፁ ሲመለስለት ታውቆው። «ዋ፣ ለዚህ ድፍረት በኋላ የምትከፍሉት ዋጋ እንዳይከብዳችሁ፣ እናንት ወራዶች።»

«እሱ የኔ ችግር አይደለም» አለ ኩፐር፣ «መጨነት የሚገባህ አንተ ትመስለኛለህ። ካልተባበርከን በስተቀር።»

የካርሎስ አይኖች የበለጠ አተኩሩ። «ካርሎስ ከማንም ጋር ተባብሮ አያውቅም፣ ራሱ ካልፈለገ። እኔ ደግሞ የምተባበረው ከማንም ዶላር አሳዳጅ የትጥረኞች ጥርቅም ጋር አይደለም። ብትለቁኝ ይበጃችኋል፣ አለዚያ. . .»

«አለዚያ ምን?»

«አለዚያማ እያንዳንድሽን እንደወረቀት አሰቦጫጭትሻለሁ።»

ኩፐር ብድግ ብሎ ወደፊት በመጠጋት የካርሎስን ጉሮሮ በእጁ አንቆ ሞርትቅ አደረገው። ካርሎስ አይኑን አፍጥጦ ማንቋረር ሲጀምር ኩፐር ለቀት አደረገውና «ከልብህ አሳምጠኝ አንተ ወራኛ። ከቀባሣሪው አፍህ

በስተቀር ሁሉም ነገር በቁጥጥሬ ስር ነው። እኛን እንደ ወረቀት ሊታሰሱቅ ይትርና የራስህን ሞንትሳት ልበትንልህ ነው። እስክሬንህን በማጥሽ እንድ ቁራጭ ለሞፍርችህ በፖስታ ልልክላቸው ነው። ካለው በኋላ በፊት ለፊቱ በኩራት እየተንጎራደደ ‹‹ካሁን በኋላ ይህን ጉራ ስትለፋደድ እንዳልሰማ። ትተባበረናለህ ወይ ትሞታለህ። ምረጥ፣ የምሰጥህ የአንድ ደቂቃ ጊዜ ብቻ ነው።››

ካርሎስ ሁኔታዎችን በሚገመግም አስተያየት ኩፐርን ከተመለከተው በኋላ መሸነፉን ተቀበለ። ‹‹የምትፈልጉት ምንድን ነው?››

‹‹ቡድንህን›› አለ ኩፐር፣ ‹‹ሞፍርችህን አንድ ተልዕኮ እንዲፈጽሙልን እንፈልጋቸዋለን። እኛ ቡድንህን እንፈልጋለን፣ ቡድንህ ደግሞ ያንተን ደህንነት ይፈልጋል። አንድ የምናከናውነው ልዩ ተልዕኮ አለን። ለዚያ ተልዕኮ ያንተ ቡድን እንዲፈፅመው እንፈልጋለን። ይህ ነው ሳንተ በደህና መለቀት የኛ ቡድን የሚያቀርበው የመያዣ ዋያቄ። ተልዕኮአችንን ቄፍሮችህ በተሳካ ሁኔታ መፈፀማቸውን እንዳረጋገጥን በሰላም እንለቅሃለን፣ ለነርሱ መልሰን እናስረክብሃለን።››

ካርሎስ ከንፈሩን ሽብሽብ እንዳደረገ ኩፐርን መመልከቱን በመቀጠል ‹‹ምን እንዲደረግላችሁ ነው የምትፈልጉት?›› ሲል ጠየቀ። ‹‹በውነቱ እኔ ልረዳችሁ አልችልም። የምትፈልጉትን ለማስፈፀም ብልሀት ብትሆኑ ኖሮ እኔን ሳይሆን የቢታቾቹን ሚኒገር እንደሚኖርባችሁ ማወቅ ነበረባችሁ።››

በዚህ ጊዜ ኩማ ወደፊት ተጠግቶ ጎንበስ አለ። ‹‹ማንን ነው የምናነጋግረው?››

‹‹እኔ እንጃ። ምናልባት ወኪሉን። እኔ በማልኖርበት ጊዜ ሉሎች ተክታዮቼን የሚመራው እሱ ነው። ሮበርት ጀክሊን ይባላል።››

‹‹የት እናገኘዋለን?›› ጠየቀ ኩፐር። ‹‹ሪዩ ማርቲል በተደበቃችሁበት ሀንባ?››

‹‹የለም›› አለ ካርሎስ። ‹‹ጀክሊን ኢስታንቡል ነው ያለው። ኩርዝ ህዝባዊ አርነት ግንባር ጋር ለማላችን ጉዳይ አንድ ትድመ ዝግጅት በማተናጀት ላይ ነው።››

ኩግ ከካርሎስ ኪስ ውስጥ አውጥቶት የነበረውን የቱርክ አየር መንገድ ቲኬት እያሳየ ‹‹ከሱ ጋር ለመገናኘት ወደ ቱርክ በመንዝ ላይ ኖረሃል?›› አለው።

‹‹አዎ።››

‹‹ኢስታንቡል ላይ በምን መንገድ ልናገኘውና የመያዣ ጥያቄውን ልናቀርብለት እንችላለን?›› ኩፐር ነበር ጠያቂው።

‹‹ልታገኙት አትችሉም። ኢስታንቡል ላይ አድራሻ የለውም።››

‹‹እንጉ ግን ኢስታንቡል የምትሄደው እሱን ልታገኝ ነበር›› አለ ኩፐር ‹‹ቀጠሮአችሁ የት ላይ ነበር?››

ካርሎስ በእልህ ጥርሶቹን አንቀረጨጨ። ‹‹ኧረ ባካችሁ እኒህን ሰባጎሎች አላለልኝ?››

‹‹ወቅቱን ጠብቀን›› አለ ኩፐር። ‹‹ከጃክሊን ጋር የተቀጣጠርከው የት ቦታ ነበር?››

‹‹መስጊድ ውስጥ. . . ሰማያዊ መስጊድ ውስጥ. . . ነግ. . . ጧት. . . በአምስት ሰዓት።››

‹‹መስጊዱ ውስጥ. . . በተለይ የትኛው ስፍራ?››

ካርሎስ መልስ ላለመስጠት አትማምጦ ነበር። አፋጭቶቹን ሲያይ ግን ከገፅታቸው መረታት እንዳለበት አነበበ። ‹‹ከመስበኪያው ባንኮኒ ፊት ለፊት።››

‹‹ይህን በኋላ በዝርዝር ታብራራልናለህ›› አለ ኩፐር፣ ‹‹ለጊዜው ግን ጃክሊንን በምን ምልክት እንለየዋለን?››

‹‹ሞሪት። ቀኝ ጉንጩ ላይ ሞሪት አለበት።›› ካርሎስ ኩፐርንና ኩግን መመልከቱን ቀጠለ። ‹‹ግን እናንተን ሊያነጋግራችሁ እንደማይፈቅድ ማወቅ አለባችሁ።››

‹‹ባንዴ›› አለ ኩፐር፣ ‹‹ከካርሎስ የተላከ የመያዣ መልእክት

ሲደርሰው፣ በራስህ እጅ የተጻፈ ደብዳቤ ሲያነብ እጁን ይሰጣል። ከጎናችን ብትሰለፍ ይሻልሃል ካርሎስ፣ የነገን ዕለታዊ ከፈለግህ።››

ካርሎስ በረድ ማለት ጀመረ። ፊቱ በመጠኑ የፈገግታ ምልክት ታየበት። ‹‹ምን ይደረግ፣ ምርጫ የለኝም›› አለ።

ኩፐር ብድግ ብሎ ኩባ ወዲያዛቸው የቱርክ አየር መንገድ ቲኬቶች እያመለከተ ‹‹እኒህን ቲኬቶች ለጋጋኖ ስጥ›› አለ፣ ‹‹አሁኑኑ የካርሎስን ደብዳቤ አስፅፈን እንደጨረስን ወደ ኢስታንቡል እንድሚንዝ ንገረው። ለምን እንደዘገየ ለአለቃችን እንዲያስረዳ ጨምረህ ንገረው›› ካለ በኋላ ሰዓቱን ተመለከተ። ‹‹ቀልጠፍ ካለ በዘጠኝ ሰዓቱ አውሮፕላን ለመሳፈር ጊዜ አለው። ዛሬውኑ ኢስታንቡል ላይ እንዳገኘው አፈልጋለሁ።››

* * *

ቱርክ ርዕሰ ከተማ ኢስታንቡል ላይ ከከተማዋ ውጭ በሚገኘው የሲልኪይ አውሮፕላን ማረፊያ ከአውሮፕላኑ እንደወረደ ጉስ ጋጋኖ እስቱድሞ ተዘጋጅተውለት የነበሩት መኪናና ቫሲፍ የተባለው ሾፌሩ ተቀበሉት። ኢስታንቡል ሂልተን ሆቴል አሊጋ ከያዘ በኋላ ምሽቱን ከተማዋን በመጎብኘት አሳለፈ። በተለይም በተለምዶ ሰማያዊ መስጊድ በተባለ ስም በሚጠራው የሱልጣን አህመድ መስጊድ ቅጥረ ግቢና ሀንፃ መወሰኒ መግቢያ ላይ ጉብኝት ብቻ ሳይሆን ዝርዝር ጥናት አካሂደ።

በማግስቱ ጧት በጥሮግራሙ መሠረት በአረብ አስልምና ተከታይ አለባበስ ማንኑን ለውጦ አማኞች ሀንፃው ውስጥ በተለይ ጫማቸውን አውልቀው ከሚያስተምጡበት ስፍራ ሊሎች ፀሎተኞችን በመከተል በእግር ሽራብ ወደ ውስጥ ገባ።

በመስጊዱ አፃራማ ውስጣዊ ክፍል ቱርኮችና ጥቂት የውጭ ዜጎች እዚህ እዚያ ተበታትነው በጉልበታቸው ተንበርክከው በግንባራቸው ተደፍተው ይፀልያሉ።

ጋጋኖ ድንጓት ከኋላው እንድ ድምፅ ሰማ። ሾፌሩ ቫሲፍ ነበር።

‹‹እንግዳ ነገር አይታይም አይደል?›› አለ ቫሲፍ።

ጋጋኖ እዚህ የመጣው ለጉብኝት መሆኑን ማሳወቅ እንደሌለበት ተገነዘበ።

«የታክሲ የመስበኪያው ባንኮኒ?» ሲል ጠየቀ።

ቫሲፍ ወደቀኝ በማመልከት ከአናቱ ላይ አንድ ባንኮኒ የሚታይበት መስኮት የሌለው የእብነበረድ ክፍል አሳየው። «ከዚያ ባንኮኒ ላይ ነው ለባኪው ዐስታቸውን የሚያንበለበሉት።»

«አሳህ ይስጥህ» አለ ጋጋኖ፣ «አውን ብቻየን ሆኜ መፀለይ አለብኝ። መኪናዋ ውስጥ ጠብቀኝ።»

ሾፌሩ ከመስጊዱ ሲወጣ ባይኑ ከተከተለው በኋላ ጋጋኖ መለስ ብሎ ባንኮኒውን ይታኝ ጀመር። በባንኮኒው ተከፋች ጥግ አንድ ወንድ ሰው ለፀሎት ተንበርክኳል። ጋጋኖ የሚፈልገውን ማግኘቱ ተሰማው። ሰዓቱን ተመለከተ። ከአምስት ሰዓት ሶስት ደቂቃ አልፏል። ጋ. . እድግ የሚፈላለጉ ሰዎች ተጠሮ ከዚህ ማለፍ የለበትም። ጋጋኖ ረጋ ባለ ርምጃ በሲጋጅዎቹ ላይ እየተንዘዘ ወደ ሰውየው አመራ። ከሰውየው ጥኝ ጎን እንደደረሰም እንደ ፀሎተኛ በርከክ ብሎ ግንባሩን መሰሉ ላይ ደፋ አደረገ። ወዲያው ግን ከአንገቱ ሀር ብሎ ሰውየውን ለአጥቃ ተመለከተው። የጥኝ ጉንጩ ቂጠት በግልፅ ይታያል። ጋጋኖ ጊዜ ሊያጠፋ አልፈለገም። «አንተ ነክ ሮበርት ጃክሊን?»

ጃክሊን ጆሮውን ተጠራጠረው። «ማነህ አንተ?»

«የካርሎስ መልእክተኛ» ነበር መልሱ።

«እንዴት?»

«ካርሎስን የጠለፈ የአንድ የጋሪስ ቡድን ወኪል ነኝ። አለታህን ይዘነዋል። የመያዣ ጥያቄአችንን ካሚላችሁ ካርሎስ በደህና ይመለስላችኋል። መያዣውን ልገልፅልህ ነው፣ አመጣዜ።»

ጃክሊን ትንሣት ንትንት ሳይል አዳመጠ። «ግን የምታወራው እውነት መሆኑን በምን አውታለሁ?»

‹‹ከራሱ ከካርሎስ የተላከ ደብዳቤ አሳይሃለሁ። የእጅ ጽሁፉን ትለየዋለህ?››

‹‹አዎ።››

‹‹ጥሩ መልእክቱን አስነብብህና እሱን የጠለፍንበትን መያዣ እነግርሃለሁ። ፓሪስ ካሉት ጓደኞችህ ጋር ተወያይተህ ውሳኔ ላይ እስክትደርስ ጊዜ እንሰጥሃለን። ጥያቄአችንን ለመመለስ ፍቃደኛ ከሆናችሁ እኔንና አለቃዮን ሂልተን ሆቴል ቦስፈረስ ምግብ አዳራሽ ውስጥ ነገ ልክ በስምንት ሰዓት ተገኝተህ ታነጋግረናለህ። ተግባብተናል?››

* * *

የካርሎስ ቀኝ ክንድ ከሆነ ሰው ጋር ሊገናኝ ጥቂት ደቂቃዎች ይቀሩታል። ከኢህ ደቂቃዎች በኋላ የሚቀጥለው ተልእኮ ይከናወን አይከናወን እንደሁ ሊያውቅ ነው። ነገር ግን ሁሉም ነገር ሮበርት ጀክሊን በሚያቀርበው የውሳኔ ቃል ላይ የተመረኮዘ ነው። በኢስታንቡል ሂልተን ሆቴል ከመኝታ ክፍሉ ወደ ቦስፈረስ የምግብ አዳራሽ የሚያመራው ኤድዋርድ አርምስቲድ በትርቡ ሊፈፅመው ስላቀደው ታላቅ ተልዕኮ እውን መሆንና አለመሆን እያምሰለሰለ በሃሳብ ተውጧል።

በምግብ አዳራሹ በተለይ ለሶስቱ ሰዎች በትድሚያ በተዘጋጀው ክብ ጠረጴዛ ፓፓኖና ሮበርት ጀክሊን ቀድመው በመግኘት የኤድዋርድን መምጣት ይጠባበቃሉ።

አለቃውን ግና ከሩት በትህትና ለመቀበል ከተቀመጠበት የተነሳው ፓፓኖ ኤድዋርድ ከስፍራው ደርሶ ከመቀመጡ በፊት ‹‹ሚስተር ሮበርት ጀክሊን ማለት እሱ ነው›› ሲል አስተዋወቀ፣ ‹‹አሳቹው ደግሞ ሚስተር ዋልተር ዚምበርማ ይባላሉ።›› ጀክሊን ከወንበሩ ለመነሳት ሳያጨነት ቀኙ እንዳለ እጁን ዘርግቶ ከተደራዳሪው ጋር ተጨባበጠ።

‹‹ብዙም እንዳላሰጠበቅኋችሁ ርግጠኛ ነኝ›› አለ ኤድዋርድ እየተቀመጠ።

‹‹የለም›› ካለ በኋላ ጀክሊን ከንፈሩን ሽርመም አድርጎ ኤድዋርድን በፈገግ ተመለከተው።

‹‹ያጠለቱት የፊት ሽፋን በጣም ተራ፡ ሲበዛ መናኛ ነው፡፡ ለወደፊቱ ደህንነትም ነው የምመክርም፡፡ ግን ነጥቦችን ይህ አይደለም፡፡ ማንም ይሁኑ ማን ጉዳየ አይደለም፡፡››

የሆቴሉ አስተናጋጁ ቀርበ የሚፈልጉትን ካዘዙ በኋላ ነበር ድርድሩን የጀመሩት፡፡ ‹‹እዚህ ቦታ ሰስታችን ለምን እንደተሰበሰብን ሳትገምት እንዳልቀረህ እርግጠኛ ነኝ›› አለ ኤድዋርድ ስብሰባውን ሲከፍት ወደ ጃክሊን እየተመለከተ፡፡

‹‹ከካርሎስ ደብዳቤና ጓደኛም ከነገረኝ ለመረዳት ችያለሁ›› አለ ጃክሊን፡፡

‹‹ልታደርጉት ትችላላችሁ?››

‹‹ከሞላ ጎደል ሁሉም ነገር ከኛ የተነሳ አይደለም፡፡ በርግጥ አሁን የጠየቃችሁንን አይነት ባይሆኑም ይበልጥ አደገኛ የሚባሉ ተልእኮዎችን ያለምንም እንቅፋት እናከናውናለን፡፡ የናንተ ጥያቄ ግን ያልተለመደ ነው፡፡››

የኤድዋርድ ፊት ኩምትር ሲል ያስታውታል፡፡ ‹‹የጠየቅሁት አስተያየትህን አይደለም›› አለ እንደተቆጣ፡ ‹‹ታደርጉታላችሁ ወይስ አታደርጉትም?››

ጃክሊን በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ‹‹ካርሎስ በደህና እንዲመለስልን እንፈልጋለን፡፡››

‹‹እንግዲያውስ ታደርጉታላችሁ›› አለ ኤድዋርድ፡፡

‹‹ግዴታችን ነው›› አለ ጃክሊን፡፡ ‹‹ጉራስ ከሚገኙት አቻዎቼ ጋር ተነጋግሬበታለሁ፡፡ ተስማምተዋል፡፡ የጠየቃችሁትን እናደርግላችኋለን፡፡ ተልዕኮው ቀላል ባይሆንም ልናደርገው እንችላለን፡፡ ደግሉ ደግሞ የሚያስፈልጋችሁ ብልጥ ሰው ጃንን ውስጥ በኛ ስር ይገኛል፡፡ ለተልዕኮአችሁ ዝግጁ ነው፡ የሚጠይቀው ዋጋ ከተሟላለት፡፡››

‹‹ዋጋው ካርሎስ ነው፡፡›› ኤድዋርድ ነበር፡፡

‹‹ለኛ በርግጥ ዋጋችን ካርሎስ ነው። ለጀኖኖዊው ቁልፍ ሰው ግን ካርሎስ ጉዳዩ አይደለም። ጀኖኖዊው ስራውን ሲፈጽም በግሉ የሚተበለው የተመሰነ ገንዘብ በዋስትና እንዲያዝለት ይፈልጋል። ምናልባት አንድ ሚሊዮን ዶላር ይጠይቅ ይሆናል፣ ብቻ ትክክለኛውን የገንዘብ ልክ ልናገር አልችልም። ግን የሚጠይቀው ገንዘብ የሚከፈለው ከሆነ ይተባበረናል። ተልዕኮውን ለማከናወን ደግሞ የግድ እሱን ማሳተፍ አለብን።››

ኤድዋርድ በሃሳብ ሊጨነቅ አልፈለገም። ‹‹የሚጠይቀውን ገንዘብ ልክ ግወቅ አለብኝ፡›› አለ።

ጃክሊን ያስተረበውን ምግብ ሲጎራርስ ከቆየ በኋላ፣ ‹‹በዚያ ላይ፡›› አለ፣ ‹‹ጀኖኖዊው ለጥቂት ቀናት ልዩ ልምምድ ሲያደርግ ለመሰንበት ጠይቋል።››

‹‹በዚህ በኩል ምንም ችግር የለም›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹ጥሩ›› አለ ጃክሊን፣ ‹‹እንግዲህ በተልዕኮው ዋዜማ ከቶኪዮ እዚህ መጥቶ ከኛ ጋር መገናኘት ይኖርበታል። እኛን ሳይሆን አርስዎን ለማነጋገርና ለሚፈልመው ተግባር የሚጠይቀው የገንዘብ ክፍያ በሚስቱ ስም ባንክ ውስጥ መቀመጡን ለማረጋገጥ በትድሚያ አርስዎን ለማግኘት መጠየቁ አይቀርም። በፈለጉት ቦታ ቀርበ ሊያነጋገርዎ ይችላል።››

‹‹ከአሜሪካ በሚነሳበት ወቅት እንነጋገራለን›› አለ ኤድዋርድ ተበል አድርጎ።

‹‹በጣም ጥሩ›› አለ ጃክሊን፣ አፉን እየጠራረገ።

ኤድዋርድ ንግግሩን በመቀጠል ‹‹ይኸ ጓደኛየ›› አለ ወደ ፓጋኖ እየጠቆመ፣ ‹‹ፓሪስ ላይ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሙሉ ካንተ ጋር ያቀናብራል። ባፈው'ት ወደ ፓሪስ ይመለሳል።››

‹‹እኔም ነግ ፓሪስ እገባለሁ። ሚስተር ፓጋኖ ከኛ ጋር በስልክ የሚገናኝበትን መንገድ ያውቃል›› ካለ በኋላ ጃክሊን ኤድዋርድ ላይ እንዳፈጠጠ ‹‹ለመሆኑ በፕሮግራሙ ላይ ለውጥ አለ?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹ያው የባፈ ሳምንት ነው›› አለ ኤድዋርድ። ‹‹ሰኑዩና ደቂቃው

እቅጩን መሆን አለበት፡፡››

‹‹እትጩን ይሆናል›› አለ ጃክሊን፡ ኤድዋርድ ሳያ ማፍጠጡን ለአፍታ እንኳ ሳያቋርጥ፡፡ ‹‹ተልዕኮው በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቅ መያዣው ይለቀቅልናል፡፡ ማለት ካርሎስ፡፡ ለመሆኑ ያኔ ካርሎስን እንዴት ነው የምናገኘው?››

ኤድዋርድ ራሱን በእምንታ ከፍ ዝቅ አደረገና ‹‹የተልዕኮአችሁ ውጤት መሳካቱን ካረጋገጥኩ በኋላ በአንድ ሰዓት ውስጥ የጋሪሉ ወኪላችሁ ኪጋንና የሰልክ ጥሪ ይደርሰዋል፡፡ ጋጋና የካርሎስን መለቀቅና የት እንደምታገኙት ይነግራችኋል›› ካለ በኋላ የሚከተሉትን ቃላት በጥንቃቄ አስተመጣቸው፡፡ ‹‹የበኩላችሁን ፈፅሙ፡፡ የበኩላችንን እንፈፅማለን፡፡››

ጃክሊን በመገረም ይመስላል፡ ከልቡ ፈገግ አለ፡፡ ‹‹የጠለፋ መሰረቱ መተማመን ነው›› አለ፡ ‹‹እርስ በርሳችን ሰንጠላለፍ እንኳ፡፡››

* * *

ከጋሪሉ የኒውዮርክ ሪኮርድ ጽህፈት ቤት የዝግጅት ክፍል ቢሮ ያወጣቻቸውን የፎቶ ፋይል አቃፊዎች እንደተሸከመች ቪክቶሪያ ዊስተን በክፍሉ መካከል ወደሚገኘው ሰፊ የማንበቢያ ጠረጴዛ ወስዳ ካስተመጠቻቸው በኋላ በፎቶዎቹ መካከል የምትፈልገውን ሰው ምስል አግላብጣ ለመፈለግ እያም ተቀመጠች፡፡

ቪክቶሪያ የካርሎስ ቡድን አባል፡ ምናልባትም ካርሎስ ራሱ ሊሆን ይችላል፡ ከተደበቀበት ሀንፃ ሲወጣ ባልታወቁ ሰዎች ተጠልፎ ሲወሰድ ተከትላ ካየችና ተጠላፊውም የተወሰደበትን ቦታ ከተመለከተች አራተኛ ቀኗ ሆኗል፡፡

ከዚያ እለት ጀምሮ ቪክቶሪያ ከመቼውም የበለጠ እረፍት አጥታ ስትዋትት ነበር የሰንበተችው፡፡ ላለፉት ሶስት ተናት ለጥቂት ደቂቃዎች ሳንድዊች ቢጤ ለመትመስ ወይም ገላዋን ለመለታለት፡ ቡተረፈ ከእኩለ ሌሊት አስከ ንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት እንትልፍ ካልሆነ በስተቀር መላ ጊዜዋን ሪዩ ጃኮብ በተባለው የካርሎስ አባል ተጠልፎ በተወሰደበት ስፍራ

ጠርዝ ላይ መዚናሞ ውስጥ ተንሲታ ጠላፊምቹ ሲወጡ ለመመልከትና ማንነታቸውን ለማወቅ ስትጠባበቅ ሰንብታለች። ባራም ይሆን አሰልቺ ስራ ሞለችበት። ፍላጎቷ የጠላፊዎቹን ማንነት ለማወቅ የነበረ ቢሆንም ዛሬ ግን ሃሳቧን እንድትቀይር የሚያደርጋት አንድ ነገር ተፈጥሮባታል።

ቪክቶሪያ ቱድሞውንም በካርሎስ ስውር መኖሪያ አካባቢ እንድታንጣለብ ያደረጋት አለታማ ሚስተር ኤድዋርድ ከሁሉ ቱድሞ በሚያሳትማቸው ትኩስ ዜናዎች በካርሎስ ቡድን መከከል ግንኙነት ይኖር እንደሁ ለማጣራት ራምሲ በሰጣት ምክር ተመርታ ነበር። ነገር ግን በካርሎስ መኖሪያ አካባቢ ክትትል ስታደርግ ባልጠበቀቸው ሁኔታ ጠለፋ ሲፈፀም፣ አንድ ሰው ከካርሎስ ህንፃ በሚወጣበት ወቅት ባልታሰቡ ሰዎች ሲታፈን ለማየት በቃች። ከዚህ ጊዜ በኋላ አላማዋ የኢያን ያልታወቁ ጠላፊዎችና የተጠላፊውን ሰው ማንነት በማወቅ ላይ አነጣጠረ። ይህ አላማዋ ተሳክቶ ሰዎቹን ማወቅ ከቻለች ደግሞ የቱድሞዎቹን ሽብር ፈጠራዎች የፈለገ ሰው ቢያቀርባቸው የአለምን የዜና ስርጭት ታምቡር በኃይል በመምታት በአጭሩ የጉሬሰ ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ዜና በራሷ ስም ቀርቦ ታላቅ ሰው እንደሚያሰኛት በጽኑ አምናለች።

ይሁንና ምንም እንኳን ለአራት ተናት ጥበቃዋን ተስፋ ሳትቆርጥ ብትቀጥልም ጠላፊም ተጠላፊም ከገቡበት የመጻህፍት መጋዘን ህንጻ አንድም ሰው ብቅ ሳይል ሰንበተ። ምናልባት ለእንትልፍ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄዳ ሳለ በሙድትት ሊሊት ወጥተው ይሆናል ብላ ገመተች። ባራ በአራተኛው ቀን በተለይ ከሰዓት በኋላ ጥበቃዋ ይበልጥ አስቸጋሪና እንዲያውም አደገኛ እየሆነ መጣ። ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ አካባቢው ባሉ ሱቆች ሳይቀሩ በተጀጋሚ ስላዩዋት በማንነቷ ላይ የጥያቄ ምልክት አስቀምጠውባታል። ከዚያም በተጨማሪ አንድ ቢታ ተግተር ወይም ተጎልቶ መሞሉ፣ ከመኪና ወርዶ በእግር ወዲያ ወዲህ መንጎራደዱ ከቱርኩሞኒስት አስክ ማጅራቷ መጋለሚያዎቿን ይጠዘጥዛት ጀምሯል፣ ዛሬ ከሰዓት በኋላ እንዲያውም ራሷን ስታ ልትወድት ምንም አልቀራትም።

በጀቃኝ ተሸንፋ ያለምንም ውጤት ጥሪቷን ልታቋርጥ መወሰን እንደጀመረች አንድ የበለጠ ጠቃሚ ነገር ልትሰራ እንደምትችል ታመነት።

በመለፋው ወቅት በተለይ ከሪዩ ማርቱል ሀንጻ ሲወጣ የተመለፈው ሰው መልክ በማይረሳ ሁኔታ በአእምሮዋ እንደተቀረፀ ነው። ይሆን ሰው በድጋሚ ለማየት ብትታደል በደንብ እንደምታውቀው ታምናለች። ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠላፊው ካርሎስ ይሁን ወይም ሌላ የሱ ሞፍራ መለየት ትችላለች።

የካርሎስ ፎቶግራፍ በዜና መዚል ቢሮዎች ፋይል ውስጥ እንደሚገኝ አስተድማ ታውቃለች። እንዲያውም አንዳንዶቹን የካርሎስ ፎቶዎች በራሷ እጅ አይታለች። እናም አሁን በካርሎስ ስም ስር የወጡ ፎቶዎችን ከአቃፊዎቹ ፋይሎች መካከል ማግኘት ከቻለች ባለታሪቱ ሰዎች የተጠለፈው ሰው ካርሎስ መሆን አለመሆኑን እንደምትለይ አልተጠራጠረችም።

ይህ አዲስ ሀሳብ ነበር ለአራት ቀናት በመጸሀፍት ቤቱ ሀንጻ አካባቢ ጠላፊና ተጠላፊን ለማወቅ ያደረገችውን ፍሬ አልባ አድካሚ መንቀዋለል በመተው ወደ ፓሪስ የሪኮርድ ቢሮ ሂዳ የሽብር ፈጣሪዎችን ፎቶ ለማገላበጥ እንድትወስን ያደረጋት።

የመጀመሪያውን አቃፊ ገልጣ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ሽብርተኞችን ፎቶዎች በዝግታ ትመለከት ገባች። የመጀመሪያውን ገጽ ገልብጣ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ፣ አራተኛ. . ሁሉንም ገጾች ተመልክታ ጨረሰችና እንደገናውን አቃፊ ከደነችው።

በሶስተኛው አቃፊ ውስጥ የካርሎስን ፎቶዎች አገኘች። አንድ ብቻ ሳይሆን አራት የካርሎስ ፎቶዎች በረድፍ ይታያሉ። ከልጅነቱ እንስቶ በተለያዩ ጊዜያት ከተነሳቸው ፎቶዎች የተወሰዱ ነበሩ። ነገር ግን ከአራቱ አንዳቸው እንኳ በሞራሽ በሪዩ ማርቱል የተጠለፈውን ሰው አይመስሉም።

እንደ እድል ሆኖ አይኗ አምስተኛው ፎቶ ላይ ተተከለ። የትርብ ዘመዷን ወይም ጓደኛዋን ያህል የምታውቀው ሰው ፊት ነበር። ጥቁር ፀጉር፣ ብላት ያለው ቅንድብና ሽፋሽፍት፣ ሰፊ አፍንጫ፣ ወፍራም ከንፈሮች፣ የተሸረጎዱ ጉንጮች፣ ቀጠን ያለ መልክ። እዎ፣ እዚህኛው ላይም እንደ ሌሎቹ አራት ፎቶዎች ከስሩ «ካርሎስ» የሚል ጽሁፍ ይነበብበታል። «ከጣም በትርብ ጊዜ የተወሰደ ምስል» ይላል።

ዘርፋፋ ኮት ለብሶ ከሪዩ ማርቱል ሀንጻ ቁጥር 10 የወጣው፣ በሲትረን

መኪና የተጠለፈው፣ ሪዩ ጀኑብ በሚገኝ የመሃፍት መጋዘን በምርኩ የታሰረው ሰው ትክክለኛ ማልባሮ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች ቪክቶሪያ የእርምጃ ድምጽ በመስማቷ ሠር ስትል የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሲድ ሉታስ ወደኋ ሲመጣ አየችው።

"ምን እየሰራሽ ነው ቪኪ?" አላት ሉታስ ትከሻዋን ቸብ አደረገ። "የምረዳሽ ነገር አለ? የካርሎስን ፎቶ አገኘሽ?"

"እም። ግን ካርሎስን በአካል አይተኸው ታውቃለህ፣ ሲድ?"

ሉታስ ከት ብሎ ሳቀባት። "እኔ ባየውማ መላው አለም አየው ማለት ነው።"

ቪክቶሪያ ሰውየውን ትክ ብላ ለመመልከት የፊቷ ይመስል ከአይኑ እየሸሸች በንግግራቸው ርዕስ ላይ ምን ያህል ደረጃ ልታመጣለው እንደምትችል አሰበች።

"ስማኝ ሲድ፣ ግን በካርሎስ ላይ አንድ የምትዕፈው ነገር ብታገኝ - አንድ ቁልፍ ቢያጋጥምህ ምን ታደርጋለህ?"

"ስለ ካርሎስ?" አላት ግንባሩን ቁጥር አድርጎ።

"እም፣ ለምሳሌ የተደበቀበትን ቦታ ባጋጣሚ ብትደርስበት ወይም ይህን የመሰለ ነገር ብታገኝ።"

ሉታስ ትከሻውን ነቀነቀ። "ይህማ መና ነው።"

"ግን ምን ታደርጋለህ?"

"እንዲህ ያለ ነገር ላገኝ አልችልም ቪኪ።"

"እንዲያው ብታገኝስ?"

"እንዴ፣ ያው በቀጥታ ለፈረንሳይ ፖሊስ መጠቆም ነዋ።"

"ይህንን ነው የምታደርገው?"

ሉታስ ቅንድቡን ሸብሸብ አድርጎ እያትማማ የቀረበለትን አማራጭ

በጥሞና አሰበበት። «አይ. . . መቼም ኤድዋርድ ለትክሰ ወራ ምን ያህል እንደሚጓጓ ስለማውቅ መጀመሪያ ነገሩን ለእሱ አንግረዋለሁ» ካለ በኋላ ከትከሻው ሰበቅ ብሎ «ግን ለምን በተን ሀልም እንታጦለን? እንዲያው ለነገሩ ይህን ሃሳብ ከምን አመጣሽው? አውንም ያረጀውን የሽበር ፈጠራ ሪፖርት እየቆፈርሽ ነሽ? አየሽ የምረዳሽ ነገር ካለ. . .»

ሉቃስ ንግግሩን ከመጨረሱ በፊት ቪክቶሪያ ከተቀመጠችበት ተነሳች። ታላት የእርካታ፣ የእፎይታ፣ የድል አድራጊነት፣ የኩራት ስሜት ሰውነቷን ወጥሮ ተራራ ያሳክላት መሰላት። እየተጥለቀለቀች ሉቃስን ጉንጩ ላይ ላመችውና «ከምፈልገው በላይ እንደረዳሽኝ አታውቅም ሲድ፣ በጣም አመሰግናለሁ» ብላ አቃፈምቹን እየተጣደፈች አንድ ላይ ደራርባ ግራ ከመጋባቱ የተነሳ ጠንክሮን መጠራጠር በጀመረው የቢሮ ታላፊ ፊት አስቀ መጠቻቸው። «ደጋግሚ አመሰግናለሁ።» ከእንግዲህ ምን እንደምታደርግ ከማንም በላይ ራሷ ታውታለች።

* * *

ሃሪ ዴትዝ አለቃውን ከእንቅልፉ እንደቀሰቀሰው ግና ከድምፁ አውቆታል። ነዝር ግን ኤድዋርድ ነገሩን ሰምቶ ከብደቱን ሲረዳ ከእንቅልፉ በመቀስቀሱ እንደሚያጉረመርም ሃሪ ዴትዝ አላጣውም።

የስልኩ ጥሪ የተደረገው በኤድዋርድ የግል ስልክ መስመር በተለይ እጅግ በጥብቅ ሚስጥርነት በሚገለገልበት የግል የጥናት ክፍሉ ነበር። ኒውዮርክ ሪኮርድ ጋዜጣን ከወረሰ ጀምሮ ኤድዋርድ የሚሰቱን ንዝንዝ ለመሸሽ ብቻ ሳይሆን የሚሰራውን ሰራ ከአደ አይኖች አግልሎ ለማሉ ለማድረግ ሲል ሰራውንም ሆነ መኝታውን በዚህ የተገለለ ክፍል ውስጥ አድርጓል። ከቱርክ ጉዞው በኋላ የደከመ ሰውነቱን ለማሳረፍ ሲል ይተኛ እንጂ እንደወትሮው በሆን ጥሮ ሃሪ ዴትዝ በደወለበት ሰዓት ኤድዋርድ ከመኝታው ተነስቶ ሰስራ ተቀጣጅቶ ጨርሶ ነበር።

«ምንድን ነው እሱ?» አለ ኤድዋርድ እየተድተሰተሰ።

«በደንብ ነትተግል ኤዲ?» አለ ዴትዝ ለአለቃው የበለጠ ጊዜ ለመስጠት በማሰብ። «አላስቸግርህም ነበር አለታ፣ ግን በጣም ጠቃሚ ጉዳይ

ሆኖብኝ ነው።››

‹‹ነትቻለሁ። ምን ችግር አለ?››

‹‹አሁን ከፓሪስ ተደውለውልኝ ነበር። ከዚያች ልጃችን ከቪክቶሪያ ዌስተን። በማም ከመጓጓቷ የተነሳ ትንፋሿን እንኳ መቆጣጠር አትችልም። በስሚ የሚወጣ ታላቅ ዜና አግኝሁ ትላለች።›› ሃሪ ንግግሩን ጥቂት ቆም አደረገ፣ ‹‹ካርሎስ ሲጠለፍ አየሁት ትላለች።››

ሃሪ ዴትዝ ንግግሩ አለቃው ጆሮ ላይ የመብረቅ ያህል እንደሚፈነዳበት እየታወቀው ነበር የተናገረው።

‹‹ምን?›› አለ ኤድዋርድ። «እንዴት ቻለች?››

‹‹እኔ እንጃ›› አለ ሃሪ ፈጠን ብሎ፣ ‹‹ብዙም አላስጨነቅኋትም፣ ለማየት ግን እርግጠኛ ነኝ።››

‹‹ግን እንደጠለፈው አውቃለች?››

‹‹የለም፣ ያልታወቁ ሰዎች ነው ያለችኝ።››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹አታውቅም፣ አለች። ስለኩፐር ወይም ስለኩፐርና ስለእኛ የምታውቅ ነገር ቢኖራት ኖሮ ባልደወለችልኝ ነበር።››

‹‹ልክ ነህ።›› ኤድዋርድ ተስማማ፣ ‹‹መደረጉን እንጂ ግን እንዳደረገው አታውቅም ማለት ነው።››

‹‹በትክክል። ታሪኩን በስሚ አትመን እንድናወጣ ትፈልጋለች። በብዙ ትግል አሳመንኳት። ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት ነገሩን እንተ ልታውቀው እንደሚገባና ምናልባትም ታሪኩን ቢጋዜጣችን ከማተማችን አስቀድሞ እያ የበለጠ ዝርዝር መረጃ እንድታገኝ ልታገዛት ስለምትችል ያንተን መልስ እንድትጠባበቅ መከርኳት። እያ ግን ነገሩን ለማንም ሳታወጣ ያንተን መልስ እንደምትጠብቅና እግረ መንገዷንም የካርሎስን ጠላፊዎች ማንነት ለማወቅ ከመጸሀፍት ቤቱ መጋዘን ሳትርቅ ማደኗን እንደምትቀጥል

ነው የምትናገረው፡፡››

‹‹ከውካሞ ውሻ!›› አጉረመረመ ኤድዋርድ፡፡ ‹‹አንድ መጥፎ መሰናከል ልትፈጥር. . . እንዲያውም ጠቅላላ እቅዳችንን ልታበላሽ የምትችል ረጉም ነች፡፡››

‹‹እኔንም ያስፈነቀኝኽ ይኸው ነው፡፡ አንቦን አስካነጋገር መስመር ላይ እንድትጠብቀኝ አድርጌአለሁ፡፡ አሁኑኑ መልሽ እንደምደውልላት ታል ግብቼላታለሁ፡፡ ምን ብየ ልንገራት?››

የኤድዋርድ መልስ ፈጣን ነበር፡፡ ‹‹ባስቮኳይ ወደ አሜሪካ እንድትመለስ እዘዛት››

‹‹ስለካርሎስ ጉዳይ ስትጠይቀኝስ?››

‹‹ካርሎስ በተጠለፈበት ቦታ ሆኖ ነገሩን የሚያሣራ ሰው እንደምንመድብ ንገራት፡፡ ታዲያ ታሪኩ በግል በዩ ስም እንደሚታተም ታል መግባቴን ቸምር ንገራት፡፡ ግን ባስቮኳይ ኒውዮርክ መመለስ እንዳለባት፡ ያየችውን ነገር በዝርዝርና ከራሷ አፍ ለመስማት በግንባር ላነጋግራት እንደምፈልግ አስታውቃት፡፡›› ጥቂት ዝም ብሎ ቆየ፡፡ ‹‹ከዚያ በኋላ የሷን ጉዳይ ምን እንደማደርገው እወስናለሁ፡፡››

‹‹ግን ተጠራጣሪ ሆና እንትስታሴአችን ላይ እንድታነፈንፍ አልፈልግም›› አለ ሃሪ እየቀፈፈው፡፡

‹‹ግዴለህም ሃሪ፡ የሷን ነገር ለኔ ተውልኝ፡፡››

13

የዶክተር ሻርፍ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ደወል የሚቀጥለው ታካሚ መምጣቱን እንዳስታወቀ ኤድዋርድ አርምስቱድ ከተቀመጠበት ባለመደገፊያ ወንበር ብድግ አለ። «የተመደበልኝ ጊዜ ያበቃ መሰለኝ» አለ በተሰላቸ ድምፅ።

ከጠረጴዛው ወዲያ የተቀመጠው ዶክተር ሻርፍ ወደ ኋላው ለጠጥ እያለ «የተመደበልህ ጊዜ ማብቃቱን እኔ እስክነግርህ ድረስ ብትታገስ ምናለበት ኤድዋርድ?» አለ።

መቶ ጊዜ ደጋግሞ የነገረው ነጥብ ይመስል ከልክ ያለፈ ተቆናጥሮ፣ «ግና ሳንጨርስ. . .?»

ኤድዋርድ ግን የሃኪሙን ንግግር ለማዳመጥ የሚጨነቅ ሰው አልነበረም። የተንጠለጠለውን ኮቱን አውርዶ በመልበስ ለመውጣት ትዕግስት እንደሌለው አስታወቀ።

ዶክተር ሻርፍ ከውስጡ ፈገግ እያለ ኤድዋርድ ምን ያህል አስቸጋሪ ሰው እንደሆነ፣ በተለይም ከትርብ ጊዜ ወዲህ እየጨመረ በመጣው የግትርነት አመሉ ምክንያት ምን ያህል የጤንነቱን ጉዳይ እንኳ ቸል እንዳለ ያስብ ጀመር።

ዶክተር ሻርፍ ጊዜ ሳያጠፋ ብድግ አለ። «ፕሬዚዳንቱ ለራት ግብዣ ቤተ-መንግስት እንደጠሩህ ሰሰማ በጣም ነበር የተደሰትኩት፣» አለ፣ «ታላቅ ክብር አገኘህ። ግን ሲያንስህ ነው። ከግብዣው መልስ ላይህ እፈልጋለሁ።

በምን ሁኔታ እንጻሳለፋችሁ ማወት አለብኝ፡፡››

‹‹ስራም አላጣሁ›› አለ ኤድዋርድ በተጣደፈ ቃና፡፡ ቀጥሎም ‹‹ለዚህ አይነቱ ማውደልደል ፋታ ያለኝ ሰው አይደለሁም›› ካለ በኋላ የሽኩሙን መደነት አስተውሎ ‹‹ፕሬዚዳንቶች ይሸማለሉ፣ ይሻራሉ፡፡ ለአራት አመት የተመረጠ የኮንትራት ፕሬዚዳንት አብረዝኝ ዳቦ ቁረስ ቢለኝ የትኛውን ክብር ሊጨምርልኝ? የኔ ስራና ሙያየ ያኝናፀፈኝ ክብር ከዚህ ሁሉ የላቀ ነው›› ብሎት ከበሩ ወጣ፡፡ ቀጥሎም ‹‹ብዙም አታስብ›› አለው አንጥረን መለስ አድርጎ፡፡

የሰነ ልቦናው ሀኪሙ ‹‹ሽረ ራስህ ብዙ አታስብ›› ሲለው ፈለጎ ከአፉ ላይ መለሰው፡፡ ቢሮውን ዘግቶ በሩ ላይ ተደግፎ እንደቆመ በሃሳብ ተዋጠ፡፡

ሃሳብ ላይ የጣለው የኤድዋርድ አርምስቱድ ሁኔታ ነበር፡፡ ኤድዋርድ የሰነ ምግባር ለውጥና የመንፈስ ሁከት ምልክት እየታየበት ከመጣ ውሎ አድሯል፡፡ ይህ ምልክት ደግሞ የሚመጣዘን ችሎታንና ከሰዎች ጋር ያለ ግንኙነትን ሚዛን የሚያጣባ የሂፖማኒክ ሀመም ሳይሆን እንዳልቀረ ባለሙያው ሃኪም ተጠራጥሯል፡፡

ዶክተር ሻርፍ በዝግታ እየተራመደ ሄዶ መንበሩ ላይ ሲቀመጥ ሁሉ በአእምሮው የሚገመግመው ኤድዋርድ ስለሚታይበት ምልክት ነበር፡፡ ኤድዋርድ ላለፉት ሳምንታት ለሚሰቱ፣ ለልጁ፣ ለትምህርትና ለሰራተኞቹ ያለውን አመለካከት ሲገልፅ የሚታይበት ምልክት ያለጥርጥር ሂፖማኒክ እንደጀመረው ያስረዳል፡፡ ለሌሎች ሰዎች ያለው ግምት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ጠቅላላ ሁኔታው ጥርጣሬና ትብብብነት የተሞላበት ሆኗል፡፡ በራሱ ግትር ፍልስፍና ለመመራትና የሌሎችን ምክር ሳለመቀበል በሚያሳየው አደም ጨካኝነትና ጠብ አጫሪነት ይንፀባረቅበት ጀምሯል፣ የሚሯሯጠውም ለግል ጥቅሙ ብቻ መሆኑን የተለያዩ ድርጊቶቹ ይመሰክራሉ፡፡ በተለይ የዛሬው አነጋገሩ፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትን ያህል ታላቅ ሰው ያቀረበለትን የራት ግብዣ አልተበልም ማለቱ፣ ከዚህ የበለጠ ጠቃሚና ኃያል ሰው መሆኑን ማመኑና በራሱ እንደበት መናገሩ ያለበትን አጠቃላይ የአእምሮ ችግርና ለውጥ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ ኤድዋርድ

የራሱን አለም በአእምሮው ፈጥሮ፣ የአእምሮው አለም ንጉስ ሆኖ መኖር የጀመረ ወፈፌ መሆኑን ገመገመ—ዶክተር ሻርፍ።

ኤድዋርድ ይህን የአስተሳሰብ መዛባት ማሳየት የጀመረው መቼ እንደሆነ ራሱን ይጠይቅ ጀመር—ዶክተሩ። ነገር ግን ይህን ጥያቄ ለመመለስ ራሱን ማስጨነቁን እንደ ጀመረ የሰልኩ ደወል አባነነው።

ዐሐፊው ነበረች የደወለችለት። ከበሽተኛ ጋር ስለነበር ስልክ ሊያነጋግር እንደማይችል ነግራ የተቀበለችለት መልእክት ነበራት። «ኪም ነስቢት የተባሉ ሴት ደውለው ነበር። ጊዜ ሲያገኙ መልሰው እንዲደውሉላቸው ጠይቀዎታል። ስልክ ቁጥራቸውን ራስዎ እንደሚያውቁ ነው የነገሩኝ።» አለችው ዐሐፊው።

ዶክተር ሻርፍ በሃሳብ እንደተዋጠ ስልኩን ዘጋው። ኪም ነስቢት ለምን እንደደወለች ጠርጥሯል። ጥርጣሬው ትክክለኛ ከሆነ ደግሞ መደወሏ አደገኛ ቢሆንም ጠቃሚ ተግባር እንደሚሆን አምኗል። እናም ለኤድዋርድ ከማስረዳቱ በፊት ሰዒ መልሶ ለመደወል ውሳኔ ላይ ለመድረስ ኦኮተው። መቼም ኪም ነስቢት የደወለችው ስለኤድዋርድ ሊታዋየው ፈልጋ እንደሚሆን አልተጠራጠረም።

በመጨረሻው ግን ከማስታወሻው ቁጥሩን ፈልጎ ደወለላት። ኪም ስልኩን ያነሳችው በፍጥነት ነበር።

«ካርል ሻርፍ ነኝ። መልእክትሽ ደርሶኝ ነው የምደውልልሽ። እንዴት ሰነበትሽ?»

«እንደምነህ ዶክተር?» ካለችው በኋላ ጥቂት ሳት ብላ፣ «የኔን ሁኔታ ላታውት ትተራለህ?» አለችው።

ጥርጣሬው ትክክለኛ መሆኑን ተረዳ። የምታወራው ስለኤድዋርድ መሆኑን አረጋገጠ።

«ልረዳሽ የምችል ከሆነ የገጠመሽን ሳትደብቂ ንገሪኝ» አላት።

«የሁለታችንም የጋራ ወዳጅ ስለሆነ አንድ ሰው ምክር ልጠይቅህ

አፈልጋለሁ።››

‹‹የምችል ከሆነ ምናለበት። ግን ሰውየው ማነው?››

‹‹ኤድዋርድ አርምስቲድ። ለመሆኑ አሁንም ትገናኛላችሁ?››

ሃኪም መልስ ለመስጠት አቅማማ።

ለመልስ መቸገሩ ሳይገባት አልቀረም፣ ኪም ነስቢት ሳት አለች። ‹‹በርግጥ ከኔ ጋርም እንገናኛለን። አልፎ-አልፎ እንደሚሳሸንኝ ሳታውቅ አትቀርም። አሁን ግን እንደወትሮው አያዘወትርም። ራሱን ሲያስፈልገው አንዳንድ ቀን ብቻ እንጂ ለኔ አሰቦ ጠይቆኝ አያውቅም። የምመካበት ሰው ሊሆንልኝ አልቻለም።››

ዶክተር ሻርፍ በኪም ሰበካ የሚነዳ ሰው ሊሆን አልፈቀደም። ‹‹ብረዳሽ ደስ ይለኝ እንደነበር ሳታውቂልኝ አትቀሪም›› አለ፣ ‹‹ግን ስለኤድዋርድ ጉዳይ አንስቼ መወያየት አግባብ አልመሰለኝም። እም፣ እንደንገረሽ የግል ሀኪሙ ነኝ። እና የሰነ ምግባር ጉዳይ የማክማቸውን ሰዎች ሚስጥር እንዳላወጣ ያግደኛል።››

‹‹እ፣ የት ሂድክብኝ›› አለች ኪም ፊጠን ብላ። ‹‹የሱን ሚስጥር አውጣልኝ አላልኩም። የኔንና የሱን ችግር ሁለታችንንም እኩል ስሚያውቀን ሰው አዋይቼ ምክር ማግኘት ብቻ ነው የኔ ፍላጎት። በምን መልክ ልተርበው እንደሚገባኝ የሚመክረኝ ሰው ፍለጋ ነው የደወልኩልህ›› ካለች በኋላ ጥቂት ዝም ብላ ቆየችና ‹‹ጤንኛ አይደለም፣ ታውቃለህ?›› አለች።

ዶክተር ሻርፍ ንግግራቸውን የሚያቆምበትን መንገድ ይፈልግ ጀመር። በለላ በኩል ደግሞ ከራሱ በኩል ምንም ሃሳብ ሳይሰነዝር የምትናገረውን ሁሉ ሊያጸምጣት ፈለገ። በኤድዋርድ ላይ እሱ ራሱ ላደረገው ሻምፖ ከሴትየዋ የሚሰማው ሞብዋ ተጨማሪ መመዘኛ ሊሆንለት እንደሚችል ገመተ። ‹‹ጤንኛ እንዳልሆነ ትገምቻለሽ?›› ሲል ነገሯን እንድትቀጥል ገፋት።

‹‹ትጠራጠራለህ? እስካሁን እንዴት አላወቅህም? አእምሮው አነጣጠ ችግር አለበት። ይህች አለም በቁጥጥሩ ስር ያለች ይመስለዋል። ፍላጎቱ፣ ምኞቱ፣ ሃላፊ ሁሉ ስልጣን ነው። ለስልጣን ካለው ጥማት የተነሳ አልጋ ላይ

ተኝቶ እንኳ ድንገት ስሜቱ ተዘንቶ ከማን ጋር እንደተጋደመ ረስቶ ቁም ይላል። በሚያደርገው ጥድፊያ ከራቱ የቆመውን ሁሉ እየደፈጠጠ መንገ ይፈልጋል። እኔንማ መተከሻው ነው ያደረገኝ . . .

‹‹መጀመሪያ ላይ ደህና ነበር። አባቱ በሞተበት ጊዜ በእፍላ ፍትር አዘውትር እየተመላለሰ ይጠይቀኝ ነበር። ቆይቶ ግን እኔ አልበቃው አለህ። በመላው አለም ያለውን ሰው ሁሉ ፈለግ። የአለምን ህዝብ በስሩ ለማድረግ፣ ለመግዛት ተመኘ።››

‹‹እገናለሁ፣ ኪም›› አለ ዶክተር ሻርፍ ነጠት አድርጎ፣ ‹‹ለማንኛውም ያለሱ ፈቃድ ስለኤድዋርድ መሠያየት ባልችልም ባመቸኝ ጊዜ ብት ብለኝ ብታነጋግረኝ ፈቃደኛ ነኝ። በሚተጠለው ሳምንት ሲመጣ ዝርዝሩን ለራሱ እስክነግረው ድረስ ሚስጥሩን ባታውጅ ይመረጣል።››

‹‹ታል አልተነፍስም ዶክተር።››

‹‹እመሰግናለሁ ኪም። በሰላም ያግኛት።››

ስልኩን ዘጋው። ከሙያው በማይጠበቅ ጎጸና ቢራመድም እርምጃው ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆነ ተሰማው። ከንግዲህ በሳምንት የሰሰት ቀን መደበኛ ፕሮግራም ይዘ እንዲታከም ለኤድዋርድ መንገር እንዳለበት ወሰነና ደወለ። ደውሎ ተላላኪውን ጠራው። የሚተጠለው በሽተኛ የሚገባበት ሰዓት ደርሶ ነበር።

* * *

ከዶክተር ሻርፍ መልስ ኤድዋርድ በቀጥታ ወደ ቢሮው ነበር የሄደው። አስቸጋሪዎቹን ሰራዎቹን አስራ አንድ ሰዓት ላይ አግባደደ። መሸትሸት ሲል ሁልም ነገር በቁጥጥር ስር እንደዋለና በእትድ መሰረት በመንገ ላይ እንዳለ ተሰማው።

ቪክቶሪያ ዊስተን አለቃዋ የካርሎስን አጠላለፍ ከራሷ አፍ ሊሰማ ስለሚፈልግ ወደ ኒውዮርክ እንድትመለስ ያተረበላትን ትዕዛዝ በደስታ በመቀበሏና ሃሪ ዴትዝ ስለነገረው ከንግዲህ ያቺ ነገር እያሸተተች የረበሸች ሞቅኩ ለወሬ ችግር እንደማትፈጥር አረጋግጧል። በዚህ መንገድ የኮገር

እንቅስቃሴ ከመጋለጥ መዳኑን ካረጋገጠ በኋላ ኤድዋርድ ጠቅላላ ጊዜውን ያጠፋው በትርቡ ሊፈፀም ላቀደው ታላቅ ታሪክ የሚደረጉት ቅድመ ዝግጅቶች በእቅድ መሠረት መከናወናቸውን በመከታተል ላይ ነበር። ፓጋኖ ወደ ፓሪስ ተመልሶ እንቅስቃሴውን በዝርዝር አሰረድቶታል። የካርሎስ ሞፍሮች አለታቸውን በሰላም ለማስፈታት ሲሉ የተጠየቱትን ሁሉ በቅልጥፍና በመፈፀም ላይ ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ቶኪዮ የሚገኘው ቁልፍ ሰው፥ የሁክ ማፀጸ የተጠየቀውን ተልዕኮ ለመፈፀም ፈታኙን በመሆን ልምምዱን ጀምሯል፥ በትርቡም ወደሚፈልግበት ቦታ ለመሣጣት ጉዞ ይጀምራል።

እንግዲህ ያን ታላቅ ታሪክ ለመሰራት የሚፈለጉ ነገሮች በሙሉ ያለ እንክን መዘጋጀታቸው ከተረጋገጠ ኤድዋርድ ካሁን በኋላ የሚቀረው ታላቁ ታሪክ ከተሰራ በኋላ በሪኮርድ ጋዜጣ በምን መልኩ ታትሞ ወጥቶ መላውን አሜሪካና ጠቅላላውን የአለም ህዝብ ግንጥጥቅጥ እንዳለበት ከረዳቶቹ ከሃሪ ዴትዝና ከማክ አሊስተር በተረበለት አስተያየት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት ነው፥ ይህን ጉዳይ ግን በይደር ይዞታል።

እናም መሸትሸት እያለ በሄደ መጠን ኤድዋርድ ብቸኝነት ተሰማዉነው፥ የደስታ ብቸኝነት። ሰውዋ አስፈለገው። በተለይ ተቃራኒ ጾታ። ሃና መቼም አትታሰብም። እንዲያውም ለራት እንኳን ሰራ ስለሚበዛበት እንዳትጠብቀው ደውላ እንድትነግራት ፀሐፈውን አዝዟል።

እና እንግዲህ ምሽቱን አብራው የምታሳልፈው ኪም ነስቢት መሆኗ ነው። ወደፊ እየመጣ መሆኑን አስተድሞ ደውሎ ነግራትና ልክ አሰራ እንድ ሰዓት ከአስር ላይ የሳሎኗን በር ከፍቶ ገቡ አለ።

ኪም ኤድዋርድ ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን ቀይ ሃር ተሚስ ለብሳለች። መምጣቱን በስልክ ከሰማች ጀምሮ ራሷን ስታስውብ መቆየቷ ለእይነ ሰውር እንኳ አይጠፋውም። በጉር አበባጠጅና የፊት ቀለም ትቢ ብቻ ሳይሆን የሽቱዋ ጠረን በሳሎኗ በር የሚያልፋትን የአፓርታማው ነዋሪዎች ሳይቀር ሳብ፥ ሳቡ የሚል ይመስላል። በዚያ ላይ እንደወትሮዋ በእጅዋ የውስኪ መለኪያ አልጨበጠችም። ተሚሏን ማውለት፥ የሰራ አካላቷን

መደባበስ፡ እጅጉን ሰጥቃ ስትስለመሰም መመልከት፡ እጅ እግሯ እንደ በረሮ አንቱና ዝርግትግት ብሎ ሲሰራቂ ማየት. . . ኤድዋርድ ኪምን ከዚህ በፊት አይቷት ያውቅ እንደሁ እስኪጠራጠር ድረስ ማረክችው።

ሰተት ብሎ ወደቧ ሄደና እትፍ አድርጎ ጨመጨማት። «በጣም ናፍተሽኛል፡ ኪም» አላት፡ «በጣም አስፈልገሽኛል።»

«አይሆንም» ነበር መልሷ።

«ትሰሚኛለሽ? አስፈልገሽኛል።»

«ትሰማኛለህ?» ሥዕሯ በጥያቄ፡ «አይቻልም።»

ሊጸብሳት የነበረው እጁ ሰብሰብ አለ። በተላለ ልክ ሊያስረግጣት እንደሚችል ልቡ ቢያውቀውም፡ በጉልበቱ ሊያስገድዳት አልፈለገም። ለረጅም ጊዜ የፈለገውን ነገር ተከልክሎ፡ ያሻውን ነገር እምቢ ተብሎ፡ የከጀለውን ነገር ተንጉሎ፡ ያቀደው ነገር ተሰናክሎ የሚያውቅ ሰው በመሆኑ እቧም የተመኘውን ነገር በፈታድኝነት እንድትሰጠው ፈለገ።

«ምን ሠነሻል?» አላት፡ «አትፈልጊኝም?»

«አፈልግሃለሁ» አለችው፡ እጅጉ ከንዱ ላይ አረፈ። «ግን አሁን አይደለም። በትድሚያ እንኒጋር።»

ትዕግስቱ ባይኖረውም ደስ ይበላት ብሎ የምትናገረውን ለማዳመጥ ወሰነ። ቀስ በቀስ እያሚሚቱ ስሚደን እንዲያግልላት እንደምትፈልግ ጠረጠረ። «እሽ» አላት እየተትበጠበጠ በረጅሙ ተንፈሰና፡ «እንኒጋር። ዛሬ ምን ስትሰሪ ዋልሽ?»

«ወንር ቤት። ቱለቪሽን ስከታተል። ጥቂት. . . ጥቂት ስጠጣ።»

ራሱን ሊቆጣጠር ሞከረ። «መጠጥ ማብዛት የለብሽም።»

«አንተስ የት ነበርክ?» ስትል ጠየቀችው። «ላምንት ሙሉ ብት አላልክም።»

«በጣም ሥራ በዝቶብኝ ሰንበትኩ። የማንተሳትስው...» ብሎ ሲናገር

በታይም መጽሔት ስለሱ የተፃፈው ታሪክ ትዝ አለውና ‹‹ሰፈ የክሙኒኬሽን ሚኒት እየመራሁ ነኝ›› አላት።

‹‹ግን ለሊስትም ሰዎች ጊዜ ሊኖርህ ይገባል። . . ለምሳሌ ለኔ ጥሪት ጊዜ ማስተራፍ አለብህ።››

‹‹አመሳገኝ እንጂ ኪም? ትናንት ጋሪስ፡ ዛሬ ኢስታንቡል፡ ነገ ደግሞ ማን ያውቃል። አየሽ ያለኔ መንቀሳቀስ የማይችል በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ አለ።››

‹‹ከዚህ ህዝብ መነከል አንዱ እኔ ነኝ። እንጀት ካለህ ጊዜ ባሳጣህ። ብቸኝነቱን አልቻልኩትም።››

በረድ እያለች እንደመሳቅ ስለታወቀው ይመስላል፡ ሰውነቱ እንደገና ሲግል ተሰማው። ‹‹ጊዜማ ፈልጌ ይኸው መጣሁ።›› እንደገና ሁለቱንም እጆቹን ሰዶ ባንዳኛው ጡቶቿንና አንገቷን፡ በሌላው ወገቧንና መቀመጫዋን ያሻሸ ገባ። የውስጥ መታንታዋን ለማውረድ በመጣደፍ ላይ እንዳለ ድንገት በጎይል ነጥቃው ከሁለቱም እጆቹ ተላቀቀችና ፈተት ብላ ቆመች።

‹‹አይሆንም›› አለች፡ ‹‹ከ. . ንግዲህ አይደረግም. . . የምጠይትህን እሽ እስካላልክኝ ድረስ. . ››

ቱጣው በትዕበት ገነፈለ። ‹‹ምኑን ነው እሽ የምለው?››

‹‹. . እንደወትሮህ ቶሎ ቶሎ ለመሳሳት ታሪ እስካልገባህልኝ ድረስ። አሁን አሁንስ እንደ ጥራጊ ቆጠርከኝ። እኔምኮ. . እኔምኮ የሰው ልጅ ነኝ.....››

አላስጨረሳትም። ‹‹ሁኚ ያልኩሽን መሆን ያለብሽ ሰው ነሽ›› ሲል ባረቀባት። ‹‹እኔ ሁኚ ከምልሽ ውጭ ምንም አይነት ሀልውና ያለሽ ሰው አይደለሽም። ኧረ ለመሆኑ አኔን እንዲህ ለማሰናጨት የደፈርሽው ማነኝ ብለሽ ነው? ማንም ይሁን ማን በዚህ አለም የሚኖር ሰው ሁሉ ህይወቱ ያለችው በኔ እጅ ነው። የአሜሪካ ኮሬዝዳንት ቢሆን እንኳ። . . ጭ! ሰዎች ለሚያዩት፡ ለሚሰሙት፡ በራሳቸው ላይ ለሚደርሰውና ለሚፈፀመው ሁሉ ሞተሩና ባትሪው እኔ ነኝ። ሁሉም ነገር በኔ ትከሻ ላይ ያረፈ ነው›› አለ

ከተፈላሰፈባት በኋላ ወደፊት ተረብ ብሎ አይኑን እጉረጠረጠባት። ‹‹እኔ ዜና ነኝ፤ ዝባሽ? ዜና የምሰራ እኔ ነኝ። ህይወት የምዘራ እኔ ነኝ። ታሪክ የምሰራ እኔ ነኝ። የፖለቲካውን ባቡር መሪ የጨበጥኩ ሾፌር እኔ ነኝ። ምድርን የማሽከረክር እኔ ነኝ። የመላው የሰው ልጅ ህይወት በመጻፌ ውስጥ ነው።››

ፈራችው። ‹‹የለም ኢዲ፣ እንዲህ አትናገር። እውነት አይመስለኝም። በርግጥ ዝነኛ ሰው ነህ፣ ግን. . .››

ከርኗን በንይል አፈፍ አደረጋት። ‹‹ማን እንደሆንኩ የምትነግሪኝ አንቺ አይደለሽም! ማንነቴን ጠንቅቄ አውቀዋለሁ። መጽሔቶች አጣላኸው አሰኪ። ምንተስኖት ማለት እኔ ነኝ።››

‹‹አትሞኝ ባክህ›› አለችው፣ ‹‹እባክህ. . .››

ከርኗ የተቆረጠ እስኪመስላት ድረስ ጭምት አድርጎ ጠመዘዛት። ‹‹ኤድዋርድ ሞኝ ነው የምትይው አንቺ ብቻ ነሽ. . .››

‹‹ኧረ ጆሮህን ክርክረህ የሚሉህን ስማ?›› ስትል ሰሚቸች። ‹‹ሁሉም አውቆብሃል። ዶክተር ሻርፍ እንኳ ሲናገር. . .›› ካለች በኋላ አረፍተ ነገሩን ሳትጨርስ ከአፏ መለሰችው።

የሚወድቅባት እስኪመስል ድረስ ከፊት ለፊቷ ተጠግቶ ድርቅ እንዳለ ቁልቁል ተመለከታት። ‹‹ዶክተር ሻርፍ?›› አለ። ‹‹ተገናኝታችሁ ኖሯል..?››

‹‹የለም. . . በሮራሽ. . ደጥፁም።››

ጆሮ ማንዲ ላይ በጥፊ አነባረራት። ‹‹ተገናኝታችኋል አይደል?››

‹‹የለም›› አለች ከው እንዳለች።

እንደገና በጥፊ አሰሳት።

‹‹ደውየለት ነበር›› ብላው አረፈች። ‹‹ስላንተ ተጨንቄ ስለነበር አነጋገርኩት።››

‹‹ሻርፍ ስለኔ አነጋገረሽ?››

‹‹አ. . .ዎ፡፡››

‹‹እና ምን አለሽ?›› አንራ ኤድዋርድ፡፡

ከንፈሮቿን ግጥም አደረገች፡፡ ደጋግሞ ወለወላት፡፡ በጥፊ፡ በእይበሉብሽ፡ በጥፊ በእይበሉብሽ፡፡ እንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት ጊዜ፡፡ መንጋጋዋን፡ ጉንጮዋን፡ ጆሮ ግንዷን፡ መንጭላዋን፡፡

‹‹በኔ ሞት. . .በኔ ሞት አ.ዲ›› ስትል አለቀሰች፡፡ ‹‹ላንተ ስል ነውኮ ለራስህ ደህንነት ነበርኮ የደወልኩለት. . . ያነጋገርኩት. . .››

አሁንም ሊያቀምሳት ነበር፡፡ ፊቷን በእጆቿ ሸፈነችበት፡፡ ወዲያው ደግሞ ከእንባዋ ጋር ደም ሲፈስ ተመለከተ፡፡

‹‹ንገሪኝ!›› ሲል አዘዘ፡፡ ‹‹ምን አለሽ?››

‹‹በርግጥ ያንተን መታመም አምኖበታል፡፡ ጤነኛ አለመሆንህን ያነሳሁበት እኔ ነበርኩ፡፡ እሱም ደግሞ በትርቡ መትበጥበጥ መጀመርህን ነገረኝ፡፡ እና እሱም እንደኔ ያንተ ነገር አሳስቦታል፡፡ ስሞትልህ አ.ዲ. . . በኔ ሞት ከእንግዲህ እንዳትመታኝ፡፡››

ኤድዋርድ እንደተቆጣ አንበሳ በጣቱ ጥፍር መሬመድ እስኪጸጸው ድረስ ወደ ላይ ለጠጥ ብሎ ከብሽቀት በሚመነጭ ፈገግታ ተመለከታት፡፡ ‹‹ይኸ ኖሯል የምታጫውችኝ ነገር. . . ሻርፍ ትበጥብጥ እንዳለኝ ልትነግሪኝ፡ አንቺ ደግሞ ሞኝ ብለሽ በፊት ለፊቴ ልትለፋደድ፡፡››

‹‹አይደለም አ.ዲ. . . እስኪ ስማኝ. . .?››

‹‹መጋኖና ሽርመጫ!›› አለ ኤድዋርድ፡፡ ‹‹ማንነታችን ከሞንሮቫ ባለጨዎች ተነግረንኮ! ሃ. . .ሃ››

‹‹ስማኝ አ.ዲ. . .›› እየተርበተበተች ተማፀነችው፡፡

እሱ ግን በትጽበት ሀር ብሎ በገባበት በር ተንደርድሮ ወጣ፡፡

* * *

‹‹ታዲያ ይኸ ምን ችግር ሊፈጥር ይችላል?›› ሃሪ ዴትዝ ጠየቀ፡

ኤድዋርድ በኪም ነሰቢት መኖሪያ የገጠመውን በዝርዝር ሲያጫውተው ከዬየ በኋላ። ኤድዋርድ ከኪም ቤት እርር ብሎ ከወጣ አንድ ሰዓት እንኳ አልሆነም። በቀጥታ ሃሪ ዴትዝን ፎር ሲዝንስ በተባለው ሆቴል እንዲመጣ አድርጎ ሁኔታውን አብራራለት።

‹‹ሻርፍ በጢንቱ ላይ ችግር አለ ብሎ አምኗል። ጢንቱ እንዳሳሰበውም ነግሯታል። ስለዚህ እንደዚያች ጋዜጠኛ እንደ ዊስተን ልጅ እንትስታሴየን እየተከታተለ ወሬ ፍለጋ ሊያነፈንፍ ይችላል። እኛ ደግሞ የዚህን የታላቁን ታሪክ ጎማ ማሽከርከር በጀመርንበት ባሁኑ ወቅት በመንገዳችን ላይ የሚንጎማለት ሰው እንፈልግም።››

‹‹ትክክል ሳትሆን አትቀርም፣ አለታ።››

‹‹ፍፁም ትክክል መሆኔን አውቃለሁ›› አለ ኤድዋርድ ኮስተር ብሎ፣ ‹‹አደጋ አደጋ ይሸተኛል። ሻርፍ አንድ አደጋ ነው።››

‹‹ታዲያ ምን ብናደርግ ይሻል ይሆን?››

‹‹አስቀድመን ሻርፍን ከጎዳናችን ጠርገን ማስወገድ። ልክ አሁን ከኔ እንደተለየህ ሻርፍ ቢሮ በሊሊት ገብቶ ጉዳይ የሚፈፅም ሰው ታፈላልግልኛለህ።››

‹‹ችግር የለም›› አለ ሃሪ ዴትዝ ቀበል አድርጎ።

‹‹ያ ሰው ቢሮው ውስጥ ገብቶ በቀጠሮ ፋይል ውስጥ ከተቀመጡ ካርዶች፣ ገንዘብ ከተከፈለባቸው ደረሰኞች፣ መድንኒት ከታዘዘባቸው ወረቀቶችና ከሊሎችም ውስጥ የኔ ስም ያለባቸው ሁሉ ማውጣት አለበት።››

‹‹ችግር የለም›› አለ ሃሪ፣ እንደገና።

‹‹ከዚያ ቀጥሎ ሻርፍ የሚሉትን ሰው ከመንገዴ አጠፋለሁ።››

‹‹ማለት፣ ሀይውቱን?››

‹‹አይ፣ የሱ ሀይወት. . . በተሰብ አለው። ለልጅቱ ይቆይላቸው። ግን ለጊዜው ከመደበኛ ተግባሩ እንዲገለል አደርጋለሁ። ምናልባት ነገ ሥራ ሊገባ ሲንከወከው በመኪና አስገጨዋለሁ። የሱን ነገር ለኔ ተውልኝ። ብቻ

አንተ የምትመለምልልኝ ሰው ሊሊት በፎው ውስጥ ስራውን በብቃት እንዲወጣ የሚጠይቅህን ገንዘብ ሳትከራከር አሽገው።››

* * *

ኤድዋርድ እርምስቱድ አሰረኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው ውብ መኖሪያው ለመሄድ ያደፋፈረው ሚስቱ ሃና ከእንቅልፏ አትነቃም የሚለው እምነቱ ብቻ ነበር። ራት ላይ እንደማይገኝ ስላስታወቃት የራሷን ራት ጎራርሳ እንደምትተኛ ገምቶ ነበር። ሀመሚንና አስም በጤንነቷ ላይ ያለውን ቸልተኝነት እያነሳች ስትነዘንዘው የሚሰማበት ጆሮም ሆነ ፍላጎት አልነበረውም። በእውቅ ባሰራው የሚስጥር ክፍሉ ገብቶ በሚወደው የግል ጠረጴዛው ላይ በጋዜጠኝነት ታሪክ ውስጥ እስካሁን ያልተመዘገበውን ያን ታላቅ ዜና፣ ያን ታላቅ ታሪክ ያን ጉድ፣ ያን ተዓምር ለብቻው ሆኖ ሊያረትት፣ ለሪኮርድ ጋዜጣ የመጀመሪያ ገፅ ከርዕሱ እስከ ሃተታው ሊዘግብ ይፈልጋል።

ከመተላለፊያው ከሪደር በተንጣለለው ላሎን እስክ ምግብ ክፍሉ ድረስ አንድም የህይወት ምልክት አልገጠመውም። ‹‹ጥሩ›› አለ ኤድዋርድ ለራሱ። ሃና ባትተኛ ኖሮ የምትገኘው በተሽከርካሪ ወንበሯ እንደተጎለተች ላሎን ውስጥ ግዙፉን ቴሌቪዥን ስትመለከት ነበርና።

ከምግብ ክፍሉ ወደ ግል ክፍሉ ወደሚወስደው ጠባብ መተላለፊያ ሲያመራ በመኝታ ክፍሎች በኩል ማለፍ ነበረበት። ሃና መኝታ ክፍሏ ውስጥም ብትሆን ካልተጥ ዝም ብሎ ሊያልፋት እንደማይችል ስለተሰማው በሲጋጃው ላይ በእግሩ ጣት የሚራመድ እስኪመስል ድረስ ቀስ እያለ አዘገመ። ሆኖም የሃና መኝታ ክፍል በር ክፍት መሆን ብቻ ሳይሆን መብራቶቹም አልጠፉም። ልቡ ኩምትር ያለ መሰለው። ሃና እልተኛችም፣ እንዲያውም እሱን እየጠበቀች ሊሆን ይችላል። አመ፣ ልክ በበሩ ትይዩ ሲደርስ ተሽከርካሪ ወንበሯ ላይ እንደተጎዠረች አይኖቹ ከጎድጓዳ አይኖቿ ጋር ግጥም አሉ።

‹‹እስካሁን አልተኛሽም?›› አላት በበጎ ልቡ እየሰገግት ‹‹ጥቂት ማረፍ አለብሽ።››

‹‹እንተም እንዲሁ›› አለችው፣ ‹‹አንተን እየጠበቅሁ ነው ያልተኛሁት። ደህና አልነበርክ እስካሁን ያዘገየህ?››

አነጋገሯ የለበጣ መሆኑን ጠረጠረ። ‹‹ሃሪ ዴትዝ ራት ጋብዞኝ ነው። አንድ የምንነጋገርበት ጉዳይ ነበረን።››

‹‹ከዚያ በፊትስ?››

‹‹ከዚያ በፊት ደግሞ የት ልሆን ኖሯል? ያው ቢሮ ነዋ. . .››

‹‹ከቢሮ የወጣኸው አስራ አንድ ሰዓት ላይ ነው።››

ኤድዋርድ ጥርሱን አፋጨ። ይቺ ጨርሳሳ ደግሞ ማስቸገር ልትጀምር ነው። በሆነ መንገድ ከቢሮ ከወጣ በኋላ ከሃሪ ዴትዝ ጋር ከመገናኘቱ በፊት በመካከሉ የት እንደነበረ ደርሳበታለች። እና መካድ ሳይሆን ማመን ነው የሚያዋጣው። ትክክል መሆኗን በማመን ለቱጣዋ ማጎብደድ የተዘጋጀበትን ንትርክ ባጭሩ መትጨት። ከዚያ በኋላ ምን ልታወራ ትችላለች?

እፀ ግን ይትርታ ለመጠየቅ አፉን ከመክፈቱ በፊት ቀደመችው።

‹‹ከቢሮ ወጥተህ ወደዚያች ጋለሞታ አፓርታማ ነበር የሄድከው ኤድዋርድ።››

‹‹ልክ ነሽ›› አላት እጅቹን አቆላልፎ፣ ‹‹ዘንግቼው ነው ያልነገርኩሽ። ከሀዘኗ መፅናናቷን ለማየት ሃሪ ዴትዝን ከመገናኘቱ በፊት እግረመንገዴን ጎራ ብየ ነበር።››

‹‹ከአንድ ሰዓት በላይ ነበር ቤቷ ውስጥ የቆየኸው።››

‹‹በመድኃኒአለም ሃና፣ ም ልትይ ነው? ኪምኮ ዘመዶችን ማለት ናት። በአባቱ ሞት ሲበዛ አዝናለች። ከአባቱ ሞት ጀምሮ ሁለት ይሁን ሶስቱ ለማስተዛዘን ቤቷ ሂጀለሁ።››

‹‹ሁለት ይሁን ሶስት ደርዘን ጊዜ›› አለች ሃና ኮስተር እንዳለች ‹‹ለማስተዛዘን ሃ. . .ሃ››

‹‹አንቺ ለዋላ›› ሮጎ ኤድዋርድ። ‹‹ታሰልይኝ ኖሯል? በትክታተይኝ

ነዋ የከረምሽው?››

ሃና የወንበሩን የእጅ ማሳረፊያ ጥብት እድርጎ እንደያዘች ‹‹ሁሉንም አውቀለሁ›› አለች በቁጣ በተሰባበረ ድምፅ። ‹‹የራሴ መረጃ አለኝ። ስታዋርደኝ፣ ስታሳለኝ ዝም ብየ አላይም።››

‹‹ደስ ያለኝን ሁሉ ማድረግ እችላለሁ›› ሲል አጓራባት፣ ‹‹እኮ ምን ይሁን?››

‹‹ብዙ የማደርገው ነገር ይኖራል፣ ከፈለግሁ። አባትህ በእጄ ተዘፍቶ ሳለ የደረሰለት አባቴ መሆኑን ፈሳህ? ያን የአራጣ እጅ ደግሞ አባቴ ከነሙሉ ለኔ ነው ያወረሰኝ። ከሃብትህ ሁሉ ቢያንስ ግማሹ የአባቴ፣ ማለትም የኔ ውርስ ነው። ግማሽን ደግሞ በሰማኒያ ሚስትነቴ ከመጠየት አልከለከልም፣ ገባህ? ድርጅቶችህን በሙሉ በሃራጅ ሽጪ ራቴትህን ማስተረት እችላለሁ›› ካለች በኋላ ትንፋኟን ለመቆጣጠር ጋብ አለችና ተጠለች። ‹‹እኔ ግን እንተን አይደለሁም ኤድዋርድ፣ ይህን ሁሉ አላደርግም። አንተ ደግሞ፣ ራሀራሀና ከሁሉም በላይ ሰክን፣ ተስ ያልክ እንድትሆንልኝ ነው ፍላጎቴ።››

‹‹የፈለግሁትን ከመሆን የሚያግደኝ የለም›› አለ ንዴት የሚያወራጨው ኤድዋርድ። ‹‹በመንገዴ እየተልመሰመሰሽ ጋራጣ እንዳትሆኝብኝ ነግሬሻለሁ፣ ጸጋመኛ በማላውቀው ሰው ስታሰልፈኝ ብደርስበት የለሁበትም። ልብ አድርጊ ሃና፣ ብትጠነቀቂ ይሻልሻል።›› ከንግግሩ ጋር ወደኋላ መለስ ብሎ የመኝታ ክፍሉን በር በኃይል ወርውሮ ዘግቶባት ወጣ።

እንዳበደ ወደ ግል ክፍሉ ተንደርድሮ ወፈር ያለውንና ምትክ የሌለውን የበር ቁልፍ ከኪሱ እያወጣ ነገሮችን ሊገመግም ሞከረ። በጉሠው ላይ መሰናክል እየፈጠሩ ያስቸገሩት ሴቶች መሆናቸው አስገረመው። መጀመሪያ ያቺ ሞትኩ ለወሬ ቪክቶሪያ ዊስተን፣ ተጥሎ ቲሞራዋ ገላ ለሞት ኪም ነስቢት ከገዛ ራሱ የግል ሀኪም ጋር ተባብራ ልትሸጠው። አሁን ደግሞ ይቺ ሞት እምቢ በገዛ ቤቱ ተኮምጣ በሰላይ የምታሳድነው ያነሳት ይመስል፣ ይባስ ብላ ሃብት ወራሽ ነኝ እያለች ደነፋችና አረፈችው።

የሃናን ድርጊት መላልሶ አመነገርከው። በኪም ነሰቢት ቤት በገባ በወጣ ቁጥር በሰላይዋ አደን እንደተመለከተችው ሲረዳ ሽምቅት አደረገው። ከዚም

ነሰዚትን ጠየትሀ ብላ በትኖት ብትንጨረጨር ጉዳዩ ባልነበር። ግን የቀጠረችው ሰላይ የኤድዋርድን ውስ የብክሥሁሰ ከሆነ ሊሎች እንትስታሴምቹን፣ የሚገናኛቸውን ሰምች ለምሳሌም እንደ ጉሰ ፓጋኖ ያሉትንና እንዲያውም ያደረጓቸውን ውይይትች ሁሉ ሰምቶ እንደሆንስ? በዚያ ላይ የሃና ሰላይ እስካሁን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ከትትሉን ሊቀጥል ይችላል። በተሰይ የሚቀጥሉትን ቀናት እንትስታሴምቹን የሚከታተል ከሆነ ውጤቱ አደገኛ መሆኑ ነው። ስለዚህ በአፋጣን አንድ ነገር መደረግ አለበት።

መብራቱን ሳያበራ በሮለማው ክፍል እንደተጥተረ በሃሳብ ተውጦ ቀረ።

በመጨረሻው አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ለሃና ፍቅር ማሳየትና ባንጀቷ መግባት፣ አንጀቷን በልቶ የልብን መሰራት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ሆኖ ታየው።

አዎ፣ እንዲያውም ጧት ቁርጷን እሱ ራሱ ሰርቶ ያቀርብላታል። ያሳርሳታል፣ እጅዋን ያጥባታል፣ አሷን ይጠርግላታል። እናም ሃና ያ ቁርስ በዚህ ምድር የምትመገበው የመጨረሻ እህል ይሆናል። ላትነሀንዘው፣ በዚህ ወጣህ በዚያ ግባህ፣ ላትሰው ትሰናበታለች። ከተሸከርካሪው ወንበሯ ትወርድና፣ ከመኝታ ክፍሏ ትወጣና ወደ ዘላለም ቤቷ ትሸኛለች። እንትሩትነቷ ያከትማል። ከዚያ ወዲያ ሰላይም ከትትሉን ያቆማል።

ኤድዋርድ በመንቻካዋ ሚስቱ ላይ በወሰነው ውሳኔ እመርቂነት ረክቶ በራሱ ሥሌነት ራሱን እያደነቀ ፈገግ ብሎ መብራቱን አበራው።

* * *

የኒውዮርክ ሪኮርድ ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ ኦሊ ማክ አሊስተር ከዋናው አዘጋጅና አሳታሚ በታዘዘው መሰረት ያመጣውን አታፊ ለአለታው አስረክበ ከፊት ለፊቱ ወንበር ላይ ቁጭ ብሏል።

ሚስተር ኤድዋርድ አርምስቱድ በበኩሉ ምክትል አዘጋጁን አታፊውን ይዞ ቢሮው ድረስ እንዲመጣ ያዘዘው አማራጭ በማጣቱ እንጂ ፍላጎቱ አታፊው በሚስጥሩ በግል በተካፈለው በሃሪ ዴትዝ እንዲተርብለት ነበር።

ሃሬ ዴትዝ ግን ዛሬ ምን ችግር እንደገጠመው አልታወቀም፡፡ ኤድዋርድ ለአንድ ሰዓት በትዕግስት ቢጠብቅም ለሰራ አልገባም፡፡

በትዕዛዝ የቀረበው አቃፊ በተለይ ተጠቃለው የቀረቡ የዚህ ሰሞን የሀገር ውስጥ ዜናዎችን ይዟል፡፡ ማክ አሊስተር ይሆን አቃፊ በተለይ ለምን ይህ እንደተረበ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡

ኤድዋርድም ሚስጥሩን ለምክትል አዘጋጁ ለማካፈል የሚሞኝ ሰው አልነበረም፡፡

‹‹እስኪ ከሰሞኑ ምን አዲስ ነገር እንዳለ እንይ›› አለ ኤድዋርድ በረጅሙ ተንፍሶ አቃፊውን እየገለጠ፡፡

በመጀመሪያው ወረቀት ላይ ለከንቲባነት ስለታጨ አንድ ሰው ዕሁድ በማንበቡ ‹‹ይኸ ደግሞ ዜና መሆኑ ነው?›› አለው ምክትል አዘጋጁን፡፡

‹‹ሰውየው ደራሲ ስለሆነ በምርጫው ውድድር ላይ መነጋገሪያ ይሆናል በማለት ስለሱ ልንዕፅ አስበናል፡፡››

‹‹ባካችሁ አሊ፤ ለእንዲህ አይነቱ የመንደር ወሬ ወረቀት አታብላሽ›› ካለው በኋላ ሆን ብሎ ብዙ ገጾችን ገለበጠ፡፡

‹‹ውሻ ነካሹ ሰው?›› አለ ኤድዋርድ አንድ ገፅ ላይ ባነበበው ነገር ተገርሞ፡፡ ‹‹ምነው ቀልዱን አበሳችሁት አሊ?››

‹‹በውነት የተደረገ ነው፡፡ በጎሳውን ድብን አድርጎ በላው፤ ሰውየው፡፡ ግን ይህን እንኳ አናትመውም፡፡››

‹‹በሞራሽ እንዳታትመው›› ካለ በኋላ ኤድዋርድ አውንም ፈላኑን ገጽ ግልበጣ ቀጠለ፡፡ የሚያነበውን ገረፍ-ገረፍ እያደረገ ስለነበር ወደ መጨረሻው ተቃረበ፡፡

በመጨረሻ ልቡ የሚፈልገውን በማግኘቱ አይኑን አፈጠጠ፡፡ ‹‹ይኸ ደግሞ ምን መሆኑ ነው?›› አለ የተሰማው ውስጣዊ ስሜት በፈቱ መለዋወጥ እንዳይታወክበት፤ በመሰረ አነጋገር፡፡ ‹ደስ ልቡና ሀዚም የመረና ሣድት ደረሰበት፡፡ ጉዳቱ አደገኛ ነው፡፡› ይህ ደግሞ ከየት የተገኘ ወሬ ነው?››

ማክ አሊስተር ምንጭ ጠቅሶ በዶክተር ሻርፍ ላይ ስለደረሰው አደጋ ዘረዘረለት።

‹‹ለመሆኑ ስለ ጉድው ባለመኪና የታወቀ ነገር አለ?››

‹‹ሰሌዳ ለመመዝገብ እንኳ በትርብ ሰው አልነበረም። መኪናዋ ደግሞ እንደጂት ትበር ነበር አሉ። ይኸ ሁኔታ ነው አደጋው ሆን ተብሎ የተፈጸመ መሆኑን ያስጠረጠረው።››

እርካታው እንዳይታወክበት እያመቀ ኤድዋርድ ማንበቡን ተጠለ። ‹‹ሀም. . . ዶክተር ሻርፍ? ይሀን ስም ሰምቼው አላውቅም፣ እንተስ አሊ?››

‹‹ኧረ የለም፣ ግን ሪፖርተር ልከን ማንነቱን ልናጣራ እስበናል። ምናልባት ይህ ሰው ያከመው የነበረ አንድ ታዋቂ ሰው ካለ ይህንኑ አስመልክተን ልንፅፍ ተነጋግረናል።››

ኤድዋርድ ፈገግ በሚመስል ገፅታ ከንፈሩን ወደአፍንጫው መሰድ አደረገ። ‹‹በንዲህ ያለው ፍሬቢስ ስራ የሪፖርተሮቻችንን ጊዜ አታባክኑ። ታያለህ የሀኪሙ ከሲኒክ የት ሰፈር እንደነበር? እንብብና ፍረድ። በዚያ ጉራንጉር የሚያክም ሰው ምን አይነት ታዋቂ ሰው ሊያክም ይችላል? እሱ ራሱ መናኛ ዶክተር መሆን አለበት። ደምበኞቹም መናኛዎች ናቸው።››

ብዙም ሳይቆይ ኤድዋርድ አታፈሙን አጥፎ ሰምክትል አዘጋጁ መለሰ። ምክትል አዘጋጁም በአክብሮት ጎንበስ ብሎ ሲወጣ ኤድዋርድ ለአፍታ የዚያ ሀኪም ገፅታ በአእምሮው መጣበት። ያ ውሻ ከድቶት ሚስጥሩን አጋልጧል። ሆኖም ያ ኩፍንቺላ ባይሞት ተመኝለት። ግን ቢሞትም የጁ ነው።››

ያም ሆነ ይህ አንድ ተጸጸ ተደፈነ።

አንግዲህ የተረው ከምሳ በኋላ የሚደፈነው ሁለተኛው ተጸጸ ነው።

* * *

ከምሳ በኋላ ስራ ከተጀመረ አንድ ሰዓት አልፎታል።

ቪክቶሪያ ዊስተን የቢሮውን በር ከፍታ በገባችበት ወቅት ኤድዋርድ

ወረቆቱው ላይ የተከመሩ ገቢ ደብዳቤዎችን በመመልከት ላይ ነበር።

"ዜና ይስጥልኝ ሚስተር ኤድዋርድ።" ጎንበስ ብላ ሰላምታ አቀረበች።

ከፊት ለፊቱ ባለው ወንበር ላይ እንድትቀመጥ ምልክት ሰጥታ በመቀመጥ ላይ ሳለች ኤድዋርድ ሲጋራውን እያቀጣጠለ በአይኖቹ ይከተላት ነበር። ቪክቶሪያ ዊስተን ከላይ እስከ ታች በጋሪሰ ልብሶች ተሰብጣለች። ቆንጆና ትርፀ መልካም መሆኗን አስተዋለ። ግን ትኩስና በጥያቄ የተሞላች መሰላም ታየችው። አስቸጋሪ ሰው ልትሆንበት እንደምትችል ገመገመ።

"ጉዞው እንዴት ነበር? ማለቴ ከጋሪሰ?" ጠየቃት ለነገር መንደርደሪያ።

"ደህና ነበር። ጥቂት ባይዘገይ ኖሮ ትናንት መግባት እችል ነበር።"

"ብቻ ያም ሆነ ይህ ጥቂት እረፍት እንዳደረግሽ ተስፋ አለኝ። መንገዱ አሰልቺ ነው።"

"እስከዚህም አልደከመኝ" አለች ቪክቶሪያ።

"በስራሽ ምን ያህል እንደረካን ልነግርሽ እፈልጋለሁ። ያቀረብሻቸው ዘጣዎች ሁሉ እጅግ በጣም የተዋጣላቸው ነበሩ። በዚያ ላይ አውሮፓ ውስጥ ሽብር ፈጠራዎች በተፈፀሙ ቁጥር በቦታው መገኘትሽ የሚደነቅ ነው።"

"በዚህ እንኳን እናንተን ልረዳችሁ አልቻልኩም" አለች ቪክቶሪያ።

"እኔ በቦታው መገኘት ብችልም ሁልጊዜ ከኔ ቀድሞ ነበር ዜናው የሚደርሳችሁ።"

"ፈጣን በሆነና ተወዳዳሪ በሌለው የዜና ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ ብዙ ጊዜ ይህ ያጋጥማል፣ ቪክቶሪያ። ግን ዜናውን የበለጠ ለማጠናከርና ስህተት ያለበት ወሬ እትመን እንዳናወጣ ድጋፍ ለመስጠት ያንቺ በወቅቱ እየተገኘሽ ጭብጡን ማተበል ሲበዛ አስደስቶናል።"

"እኔ እምለው ሚስተር ኤድዋርድ. . .?"

"ጀመረች እንግዲህ ሲል አሰበ ኤድዋርድ። ማስቸገሯን ልትተዋል

ነው።››

‹‹እኔ ያልገባኝና ትር ያሰኘኝ በዚህ ወቅት ወደ ኒውዮርክ እንድመለስ መደረጉ ነው። ሰሚስተር ሃሪ ዴትገ እንደነገርኩት በአንድ ተደናቂ ክስተት ላይ ከመቼውም የላቀ ዜና ላተርብ ተዘጋጅቼ ነበር። ያን ዜናየን ደግሞ ያለጥርጥር እርስም ይፈልጉታል. . ››

‹‹በርግጥ የዜናውን ሞብቸ ማተማችን አይቀርም›› ሲል አሟረጣት። ‹‹ነገር ግን በመጀመሪያ ካንቺ ጋር በግንባር መነጋገሩን አምኜበታለሁ።››

‹‹በመሃሉ ዜናው ከእጃችን አምልጦ በህዝብ ጆሮ ቢገባስ?›› ተቃወመች ቨክቶሪያ።

‹‹እታሰቢ ቨክቶሪያ፡ ልክ ነገሩን እንደሰማነው ከሰራተኞቻችን አንዱን በነገርሽን ቦታ ክትትል እንዲያደርግ መድበናል። ይህ በእንዲህ እንዳለ እኔ ደግሞ የበለጠ ለማወቅና በነገሩ ከመግፋቱ በፊት ትክክለኛውን ሁኔታ ካንቺ ለመስማት ፈለግሁ። ተደማጭነታችንንና ዝናችንን ዝቅ የሚያደርግ ስህተት እንድንሰራ አልፈቅድም። በእጅር ጊዜ ስማችንን ለማንሳትና አደሰ ተግባሮችን ለማስመገብብ በቅተናል፡ በእኛ የሚተርብ አብይ ዜና ደግሞ እስካሁን ሙቱ በሙቱ እውነተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። በሀገራችን ሁሉም የሚተናብን ከመሆናችንም በላይ በሽያጩ ከአጠባችን የሚደርስ ጠፍቷል። ይህ ተሰሚነታችንና አስተማማኝ የዜና ምንጭነታችን በአንድ ያልተረጋገጠ ወሬ የተሳሳተ አደጋ ላይ መውደቅ የለበትም። እና. . ››

‹‹ግን›› ተቃውሞዋን ቀጠለች። ‹‹እኔ ራሴ በዐይኑ ነበርኩ። ነገሩ ሲፈፀም አይቻለሁ። ካርሎስን ሲጠልፉት በአይኔ ብረት ተመልክቻለሁ።››

‹‹በአይንሽ?›› ኤድዋርድ የሲጋራውን ሞስ ተማ አደረገው። ‹‹ይትርታሽን እጠይቃለሁ፡ ቨክቶሪያ። የምከራከርሽ በእንዲህ አይነቱ ነገር ላይ የረጅም ዘመናት ልምድ ስላካበትኩና አንቺ ደግሞ አዲስና ብዙም ያልሰራሽ በመሆንሽ ነው። በበኩሌ ብዙ የነፍስ ግድያ ክሶችን የተከታተልኩና በአንድ ነፍሰ ገዳይ ላይ አምስት የአይን ምስክሮች አምስት የተለያየ ቃል ሲሰጡ የሰማሁ ሰው ነኝ። ማለቴ ሁላችንም ብንሆን የሰው

ልጅ እስከሆን ድረስ. . .››

‹‹ይመኑኝ፣ ሚስተር ኤድዋርድ፣››

‹‹እምንሻለሁ፡፡ ግን ተፈጥሮየም ቢሆን ነገርን በዚህ መልኩ እንድመለከተውና እጁን ከማስገባቱ በፊት ጥንቃቄን እንዳስተድም ያስገድደኛል፡፡ ለዚህ ነው አንቺን በትድሚያ ለማነጋገር የወሰንኩት፡፡ ስለዚህ እስኪ ባትፈርጅብኝ ከመጀመሪያው እንጀምርና በሪዩ ማርቱል ጎዳና ሆነሽ ሁኔታውን ትከታተይ ነበር. . . . ከዚያስ?››

‹‹ካርሎስ የተደበቀበትን ህንፃ እከታተል ነበር፡፡››

ኤድዋርድ ሲጋራውን ከአፉ አላቀቀ፡፡ ‹‹ቆይ እስኪ፣ ቪክቶሪያ፡፡ ስለካርሎስ ያለን የመጨረሻው መረጃ ኒክ ራምሲ በተጠለፈበት ወቅት ከካርሎስ ቂፍርኖች እንደኛው ከ12 ቁጥር እንደሚዛወሩ ሲናገሩ መስማቱን ኒክ ራምሲ የሰጠን ጮብጥ ነው፡፡ እሱንትም ሁኔታው ለፖሪስ ፖሊስ ጠቁሚ ፖሊሶች ቁጥር 12 ህንፃ ሲፈትሹ ያገኙት ነገር አልነበረም፡፡ ካርሎስ ለቆ ነበር፡፡››

‹‹ግን የገባው ብዙም ሳይርት፣ ከሚቀጥለው ህንፃ መሆን ይርሽበታለሁ›› አለች ቪክቶሪያ ተበል አድርጋ፡፡

‹‹እንዴት ደረሰሽበት?››

‹‹እንዴ፣ ከ. . .›› ካለች በኋላ ቪክቶሪያ አለታዋን ተመለከተች፡፡ ‹‹የነገርኩም መስሎኝ ነበር፡፡ ምናልባት ረስቼው ይሆናል›› ካለች በኋላ ኒክ ራምሲ ዋሽንግተን እንደተመለሰ በእንድ አጋጣሚ ባደረጉት የስልክ ግንኙነት አንድ የረሳውን ነገር ማስታወሱን ጠቅሶ የካርሎስ ቂፍራ መኖሪያቸውን እንደሚያዛውሩ ሲናገር የሚዛወሩት ወደ ቁጥር 10 መሆኑንም ጭምር እንደነገራት ለአለታዋ አብራርታ ራሷ ባደረገችው ክትትል ከበፊቱ የካርሎስ መኖሪያ ጎን ቁጥር 10 ህንፃ መኖሩን አስቀድማ አስተውላ ስለነበር ይህንኑ ህንፃ አጥብቃ ትከታተል እንደነበር አስረዳች፡፡››

‹‹የምትገርሚ ነሽ፣ ቪክቶሪያ፡፡ ግን ልጅነትም ነው መሰለኝ፡፡ ፖሪስ ውስጥ 10 ቁጥር ስያሚ የተሰጣቸው አያሌ ህንፃዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ

ዘንግተሻል። ሰውየውም ሲናገር ቁጥር 10 ይበል እንጂ በደርዘን ከሚቆጠሩት የፓሪስ ጎዳናዎች ውስጥ ወደ የትኛው ቁጥር 10 እንደሚሄዱ የሰጠው ፍንጭ የለም።››

‹‹ይሆናል›› አለች ቨሮኒክ። ‹‹ሃቁ ግን ቁጥር 10 ሲል የሪዩ ማርቱልን ቁጥር 10 ማለቱ ነው። ደግሞስ ካርሎስ በሊሎች መንገዶች እየተዘዋወረ ራሱን ለምን ያጋልጣል? ጎረቤት ወደሚገኝ ህንፃ ፊቱት ማለት ይበልጥ አስተማማኝ መሆኑን ያጣዋል? በርግጥም እንደደረስኩበት የተሳሳቱት ወደጠረጠርኩት ህንፃ ሆኖ ተገኘ።››

‹‹እንዴት እርግጠኛ ሆንሽ?››

‹‹ምክንያቱም ካርሎስ ራሱ፣ መሪያቸው፣ ከህንፃው ሲወጣ አየሁት።››

ኤድዋርድ ከሲጋራው ማነስት። ‹‹ቨሮኒክ፣ ካርሎስ እሱ መሆኑን እንዴት አወቅሽ? ከዚህ በፊት ሰውየውን በአካል አይተሽው ታውቂያለሽ?››

‹‹በርግጥ አላውትም›› ካለች በኋላ በፓሪሱ የሪኮርድ ወኪል ቢሮ የሽብር ፈጣሪዎችን የፎቶ ፋይል አገላብጣ የካርሎስን የትርብ ጊዜ ፎቶግራፍ ከተመለከተች በኋላ ከተጠላፊው ሰው ጋር በትክክል እንደሚመሳሰሉ መደምደሚን አስረዳች።

ኤድዋርድ በአስቸጋሪዋ ጋዜጠኛ ተወጥሮ ቢያዝም በቀላሉ ሊበገርላት አልፈለገም፣ አይችልምም።

‹‹ግን ካርሎስ ተጠለፈ ብለሽ እንድታምኚ ያደረገሽ ምንድን ነው?›› ሲል በፈዘዘ አስተያየት ጠየቃት።

ቨሮኒክ ካርሎስ በተጠለፈበት ወቅት የሆነውን ሁሉ በዝርዝር አብራራች። በመጨረሻ ‹‹ካርሎስ ከሁለቱ ሰዎች ጎን ከኋላው መቀመጫ ላይ በታይም ወዲያውት ክለይን ተሰወረ። ያለ ጥርጥር ጠላፊዎቹ ወደታች ተብረው መኪናዋ ወለል ላይ አስተኝተው በጉልበታቸው ረግጠው ይዘውታል፣›› አለች።

‹‹ግን ይህ ሲደረግ ያየሽው ነገር የለም?›› ጠየቃት አለቃ።

‹‹የለም. . . ይሆን በርግጥ አላየሁም፣ ግን ሊላ ምን ሊሆን ይችላል?››

ኤድዋርድ እጁን አልሰጠም፡፡ ‹‹ምናልባት ከኋላው መቀመጫ ያለው ካርሎስ ቢሆን እንኳ መኪናዋ ሊላ ሰው ለመጫን ጠባብ ባልሽው መንገድ በገባችበት ወቅት አንድ ጎን ተዛውሮ እንደሆነስ?››

‹‹ይሆን ይሆናል፡፡›› ቪክቶሪያ አማራጩን መቀበል ነበረባት፡፡ ‹‹ግን የተደረገው ያ አይመስለኝም፡፡››

‹‹የተደረገው ያ አይመስልሽም፡፡›› ደገመው ኤድዋርድ ቃሉን፣ ‹‹ለዚያስ?››

‹‹ከዚህ በኋላ መኪናቸውን በመኪናየ ተከትየ ሪዮ ጃኑብ ድረስ ከኋላቸው ተጓዝኩ፡፡ ሊላው የፋኖ ቡድን፣ ካርሎስን የጠለፈው የፋኖ ቡድን የመሸገው በሪዮ ጃኑብ መሆኑንም አየሁ፡፡››

‹‹ይህ ሊላው የፋኖ ቡድን ያልሽው ቡድን ካርሎስን ጠልፎ ወደመሸገበት ስፍራ ሲያስገባ ተመለከትሽ?››

‹‹የለም. . . ይህንም አላየሁም፡፡ መኪናየን የማቆምበት ቦታ መፈለግ ነበረብኝ፡፡››

‹‹ከጠለፋው ቡድንስ ያየሽውና የምትለይው ሰው የለም?››

‹‹ሁለት ሰዎች ከመኪናዋ ሲወጡ አይቼ ልከተላቸው ፈልጌ ነበር፣ ግን መኪናየን አቁሜ እስከመለስ ተሰወሩብኝ፡፡››

‹‹በተለይ የፋኖ ቡድኖች ያሉ ሽብርተኞችን ፎቶዎችን ብናቀርብልሽ እኒህን ሁለት ሰዎች ልትለይልን ትችያለሽ?››

‹‹አይ. . አይመስለኝም፡፡›› በአሉታ ራሷን ነቀነቀች፡፡

‹‹ግን አንድ የፋኖ ቡድን ካርሎስን ጠልፎ ለመያዙ እምነት አለሽ? እንዴት ደፈሩት?››

‹‹አይታየኝም፡፡››

‹‹እኔም አይታየኝም›› አለ ኤድዋርድ በተጠቃለለ አነጋገር፡፡ ‹‹እጅግ

ያጠራጥራል። ሲበዛ የማይታመን ነው። ከካርሎስ ጋር እንዲህ ያለ ተልድ የሚሞላውት ፋኖ ይኖራል ብየ አላምንም። ግን ለማንኛውም ነግሩን መከታተሉን አላቆምም።››

ቪክቶሪያ ለመውጣት ዝግጁ አልነበረችም። ‹‹እኔን መልሰው እንደሚልኩኝ ተሰፋ ነበረኝ። እባክዎ ራሴ እንደጀመርኩ ራሴ ተከታትየ ልጨርሰው?››

ኤድዋርድ ሲጋራውን ሙቦርከሻው ላይ አጠፋው።

‹‹ዕናትሽን አደንቃለሁ፣ ቪክቶሪያ። በዚህ ጉዳይ ላይ ግን አግባብ አይመስለኝም። ጉዳዩን በግላችን እንገፋበታለን። ላንቺ ደግሞ እዚሁ የምትሰሪው ብዙ ጉዳይ አለን።››

‹‹እንዳላችሁ እርግጠኛ ነኝ።› እያለች ከጎኗ ያስቀመጠቻቸውን ቦርሳና የገናም ልብስ አንስታ ብድግ አለች። ‹‹ግን አዝናለሁ።››

‹‹ነገሩ ዳር ከደረሰ የዜናው ባለቤት አንቺ እንደምትሆኝና አስተዋፅኦውን እንደምትጋሪ ታል እገባልሻለሁ። በይ የላፊን እረፍት አድርጊ። ስራ የምትገቢው ነገ ይሆናል። ቤትሽ የሚያደርስሽ መኪና አዝዘልሻለሁ።››

‹‹አመሰግናለሁ።››

ቪክቶሪያ ከአለቃዋ ቢሮ ስትወጣ ብዙ ሃሳብ ተመሰቃቅሎባት ነበር። የተደረገውንና በአይኗ ያየችውን ነገር አለቆቿ አጣጥለውባታል። እንዳልተሳሳተች እያወቀች መሳሳቷን እየተናገሩ አደናቁረዋታል።

ማንነቷን እንዴት ታሳያቸው? ትክክለኛነቷን እንዴት ታረጋግጥላቸው?

ድንገት አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰች። አሁኑኑ በአገር አቋራጭ ጋሪስ ለመደወል ወሰነች።

* * *

ከአስራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ሃሪ ዴትዝ ቢሮው ውስጥ እንደተቀመጠ አንድ ያልተጠበቀና አእምሮውን የበጠበጠ የስልክ ጥሪ

ይደረግለታል። በጥሞና ካዳመጠ በኋላ ‹‹የለም፣ እኔ በውነቱ ስለዚህ ጉዳይ ምንም የማውቀው ነገር የለም። አለቃችን ምናልባት ያውቅ ይሆናል። እስኪ ሚስተር ኤድዋርድ ቢሮው ውስጥ መኖሩን ልይ። ካለ ከሱ ጋር ብትነጋገር እመርጣለሁ። ስልኩን አትዝጋው›› ብሎ መነጋገሪያውን አስተመጠና እየተጣደፈ ወደ አሳታሚው ቢሮ የሚያስገባውን የግል በር በችኮላ ያንኳኳ ጀመር።

‹‹ጥሪ አለን አለቃ. . .›› አለው ከመግባቱ፣ ትንፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ እያለ። ከዚያም ኤድዋርድ በጥያቄ አስተያየት እንደሚመለከተው ሲገባው ‹‹ከፖሪስ ቢሮአችን ኃላፊ፣ ከሲድ ሉቃስ ተደውሏል። ምናልባት አንተ ብታነጋግረው ይሻላል።››

‹‹ሲድ ሉቃስ?›› ካለ በኋላ ኤድዋርድ የጠረጴዛውን ሰዓት ተመልክቶ ጊዜው ፖሪስ ላይ ሊሊት እንደሚሆን ገመገመ። ‹‹በዚህ ሰዓት? ምን ተፈጠረ?››

‹‹እሱው ይንገርህ፤ አለቃ›› አለ ሃሪ ዴትዝ። ሃሪ ዴትዝ ከአለቃው ጠረጴዛ ትይዩ በሚገኘው ወንበር ላይ ሊቀመጥ ሣራ የተጋባው ኤድዋርድ ደግሞ ስልኩን እንስቶ ወደ ሃሪ ዴትዝ የሚያጎናጽፈውን መስመር ተመኘው።

‹‹ሲድ?››

‹‹ሚስተር ኤድዋርድ፣ እርስዎን ለማስቸገር እንኳ አላሰብኩም ነበር። ሚስተር ዴትዝ ናቸው ሊረዱኝ እንደሚችሉ የነገሩኝ።››

‹‹ነገሩን ልወቀው?››

‹‹ከአስር ደቂቃዎች በፊት ቨክቶሪያ ዊስተን ደውላልኝ ነበር። ለካ ኒውዮርክ ተመልሳለች። እኔን ለታገኘኝ ስላልቻለች መልእክት ትታልኛለች፣ ነገሩ ጠቃሚ መሆኑን ባልገምት ብዙም ባልተቸገርኩ።››

‹‹እኮ ልስማው?›› አለ ኤድዋርድ አላስችል ብሎት።

‹‹መልእክቷ እንደደረሰኝ መልሺ ብደውልላት ቢሮዋ ውስጥ የለችም። ስለዚህ ሚስተር ሃሪ ዴትዝን እንዲያገናኙኝ ጠየቅሁ። እሱ ደግሞ ሚስተር

ኤድዋርድን አነጋግር አለኝ፡፡››

‹‹አለሁ›› አለ ኤድዋርድ ከመቅኩሉ የተነሳ ጥርሱን እያንቃረጨጨ፡፡ ‹‹ደሙላ ምን አለች?››

‹‹መልዕክቱን ባነበው ይሻላል፡፡ ‹‹በጣም ጠቃሚና ታላቅ ታሪክ ተዚታትኖ በደረሰኩበት ወሳኝ ወቅት ላይ ወደ ኂውሮረክ አንድመለስ ታዝዣለሁ፡፡ ታሪኩ እውነት መሆኑን ያመነበት ባይኖርም ድርጊቱ ግን በትክክል ተፈፅሟል፡፡ የሽብርተኞችን ፎቶምቹ ባስመረምር ስለአንድ ሰው አንሰቹ እንዳዋየሁህ ትዝ ይበልህ፡፡ ያ ሰው አሁን የት አንዳለ አውቃለሁ፡፡ ነገሩን ራስህ መከታተል ያለብህ ይመስለኛል፡፡ ከአንድ ሰዓት በኋላ ቤቱ እገኛለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ በፈለግኸው ሰዓት ብትደውልልኝ ዝርዝሩን እነግርሃለሁ፡፡ ቪክቶሪያ ዊስተን፡፡› ከመልእክቱ ጋር የቤቷን የስልክ ቁጥርም ትታለች፡፡›› ሲድ ሉታስ ንግግሩን ትቶ ጥቂት ከቆየ በኋላ ተጠለ፣ ‹‹በርግጥ የምትናገረው ስለካርሎስ ነው፡፡ ያለበትን ታውታለች፣ ያ ደግሞ እጅግ በጣም ጠቃሚ መንደርደሪያ ነው፡፡ ዝርዝር ያለችውን ነገር ባሁኑ ደቂቃ ማግኘት አለብኝ፡፡ እርስዎ ከረዱኝ ጥሩ፣ አለዚያም ጥቂት ቆየት ብየ ለራሷ ደውየ እደርስበታለሁ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ እርስዎ የሚያውቁት ነገር ይኖር ይሆን?››

ኤድዋርድ ትንፋሹን ዋጥ አደረገ፡፡ ‹‹ሲድ፣ በውድትት ስለተረበሽክ አዝናለሁ፡፡ ነገሩ ትርኪ-ምርኪ ነው፡፡ እርግጥ ዛሬ ከወይዘሪት ዊስተን ጋር ተገናኝተናል፡፡ ሁሉንም ነገር በክብካ ነግራኛለች፡፡ ራሷ ተሳስታ ሊሎችን ሁሉ ልታሳስት እንደነበር አስረድቻታለሁ፡፡ ማሰረዳት ብቻም ሳይሆን ለራሷ አረጋግፀላት፣ ተማምነን ነገሩን እንድትረሳው ነግሬአት ነበር፡፡››

‹‹ታዲያ ምናባቷ ነው ያለ ሰዓት የምትረብሸኝ?››

‹‹ጀማሪ ሪፖርተሮች ሁሉም እንዲህ ይሰራቸዋል›› አለ ኤድዋርድ በደረቱ እየሳቀ፡፡ ‹‹ባንድ ምሽት ዝነኛ ጋዜጠኛ ተብላ ከሁሉም ሙያተኞች አናት ላይ ቁጢጥ ልትል ትፈልጋለች፡፡ ካርሎስን የመሰለ ሰው በማየቷ ብቻ የካርሎስን ሞራ የያዘች መስሏት በስሜት ፊረስ ትጋልባለች፡፡ ካርሎስ ግን አሁን ያለው አጥሪካ ውስጥ መሆኑን ከታመነ ምንጭ ደርሰንበታል፡፡ ይኸ ነው ነገሩ ባጭሩ፡፡ የቪኪን ወሬ እርሳው፡፡ ሁሉንም ነገር እርሳው፣ ሲድ፡፡››

‹‹መልካም ሚስተር ኤድዋርድ፣ ሳላመሰግን አላልፍም። ስላስቸገርኩም ይቅርታ። ግን ደውልልኝ ብላኛለች፣ ምን እንደምላት እሄ እንጃ. . .››

‹‹ምን አስደወለህ። አርፊህ ወደ መኝታህ። የማድ ልደውል ካልክ ደግሞ ቀጥል። ያም ሆነ ይህ ግን ለጅቷ የተባጠረችው በሊለ ነገር ላይ በመሆኑ አዝናለሁ።››

ኤድዋርድ ስልኩን እንደዘጋ ካቀረቀረበት ቀና ሲል ሃሪ ዴትዝ ለጠጥ ብሎ ተቀምጦ ጉንጉት በሚነበብበት ገፅታ ሲመለከተው አየ። ‹‹ምነው ደግሞ እንዲደውል ፊት ሰጠኸው አለታ? እግዚአ፣ ምናልባት ልታሳምነው ብትችልስ?. . . ምናልባት ለፖሊስ ጠቁሞ ቢያስከብባቸውስ. . .? እንዲያ ከሆነኮ ፖሊሶች የሚይዙት ካርሎስን ብቻ ሳይሆን ኩፐርንና ጠቅላላውን ቡፍራ። ኧረ ይኸ ብቻ አይደለም. . . እኛም እንገኛለን እንጂ. . .››

‹‹ሃላብ አይግባህ ሃሪ›› አለ ኤድዋርድ ‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን ዛሬ ማታም ሆነ መቼም ማታ ከሲድ ሉታስ የስልክ ጥሪ አትተበልም።››

‹‹እንዴት?››

‹‹ሃሪ›› አለ ኤድዋርድ ሳቅ እያለ። ‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን ትሞታለች። አሁኑኑ አሳይሃለሁ።››

14

‹‹ለማነጋገር ችግር የለብህም?››

‹‹ላንቺ ከሆነ ምን ችግር አለ?›› አላት ራምሲ ቪክቶሪያ ደውላለት ከመጀመሪያው የሰላምታ ልውውጥ ተጥሶ ሳቀረበችለት ጥያቄ ሲመልስ፡፡

‹‹በደንብ ስማኝ ኒክ. . . . .››

‹‹ሄይ፣ ምን ሆነሻል? የተጣደፍሽበት ነገር አለ፡፡››

‹‹በጥድፊያ ልፈንዳ ነው፡፡ የምደውልልህ ኒውዮርክ ሆኜ ነው. . .››

‹‹እንዴት? ከጐሪስ መስሎኝ. . .ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ?››

በተቻላት መጠን በፍጥነት ልትናገር ሞክረች፡፡ ‹‹ኒክ የጠቆምከኝ ነገር በተጥታ ከክርስቶስ ጋር አገናኘኝ፡፡ ሊሎች ፋጥኖች ሲጠልፉት አየሁ፡፡››

‹‹በአይንሽ? እንዴት ጠለፉት. . .? እንዴት ደፈሩ?››

‹‹እኔ እንጂ›› ካለች በኋላ አጠቃላይ ሁኔታቸውን እንደደረሰችበት ለአለቆቿ ሪፖርት ማድረጓንና በምላሹ ግን ባስቸኳይ ወደ ኒውዮርክ እንድትመለስ መታዘዟን ነገረችው፡፡ ‹‹ታሪኩ በትክክል ከተረጋገጠ ከብራድሾ ጋር ስምሽን አወጣዋለሁ ይለኛል ኤድዋርድ›› አለችው፡፡

‹‹ከብራድሾ ጋር? የሊለ. . .››

‹‹ብራድሾ የሊለ መሆኑን ታውቃለህ፣ እኔም አውቃለሁ፡፡ አለቆቻችን ግን ሽፍጣቸውን እንዳወቅንባቸው አልተረዱም፡፡ ወይኔ. . . እንዴት አይኔ

ታውሮ ኖሯል? አፍንጫየ ላይ ተቀምጠ፣ እውነተኛው ሃት ምነው ፈዝዞ ከረምኩ? ከሽብር ፊጠራው ሞገድ ጀርባ ያለው ማን መሰለህ? ማን መሰለህ እኒያን ሁሉ አብይ ዜናምች ለኢውዮርክ የሚጽፈው ሞገደኛ. . .››

‹‹እያዳመጥኩሽ ነው›› አሳት ራምሲ መስመር ላይ። ዋሽንግተን ያለው ኒክ ራምሲ ፊቱን ኮስተር አድርጎ መነጋገሪያውን ከጆሮው ጋር አጣብቆ ለመስማት አቆበቁቦ ታያት። ‹‹ቀጥይ ቪኪ›› አሳት።

ምንም ነገር ሳታስቀር፣ በአእምሮዋ የሚንላላውን በሙሉ ዘከዘከችለት። ከጊዜ በኋላ ነገሮችን አብላልታ የደረሰችበትን መደምደሚያ በእርግጠኝነት ነገረችው።

‹‹ይኸው ነው ሃቁ ኒክ›› አለችው ስታጠቃልል። ‹‹ከዚህ ውጭ ምንም ነገር የለም።››

ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም ዝም አሉ። ‹‹ኤድዋርድ አርምስቱድ›› ሲል አጉተመተመ ራምሲ በመጨረሻው፣ ‹‹እና እምነትሽ ማርክ ብራድሾ ማለት ኤድዋርድ አርምስቱድ ራሱ ነው፣ ፋኖዎቹን አደራጅቶ ያን ሁሉ ሽብር ፈጠራ ያስፈጸመው፣ መፈፀሙን ስለሚያውትም አስቀድሞ ለሀትመት የሚያበቃው፣ በጥቅሉ ለተፈጸመው ወንጀል ሁሉ ተጠያቂው ማርክ ብራድሾ፣ ማለትም የፋኖዎች ፋኖ ኤድዋርድ አርምስቱድ ነው የሚል ነው፣ እ?››

‹‹አትጠራጠር!›› ነበር ቁርጥ ያለው መልስ።

‹‹ግን ለምን. . .ለምን ብሎ እንዲህ ያደርጋል? ማለቴ ገንዘብ እንደ ድቡሽት የቆለለ ከበርቴ ነው. . .››

‹‹ግን ገንዘብ እንጂ ስም አልነበረውም። ይህንን ባንድ ወቅት አንተ ራስህ ነግረኸኝ ነበር። ኤድዋርድ ስም ፈላጊ ሰው ነው። የስልጣን ጥም አንገብግቦታል። ደግሞም፣. . . እኔ እንጂ. . . ጥቂት ወፈፍ ሳያደርገው አልቀረም።››

‹‹ይሆናል›› አለ ራምሲ፣ ጥርጣሬ ግን አሁንም አልለቀቀውም። ‹‹ግን ሊሆን አይችልም። በርግጥ ጥሩ መደምደሚያ ላይ ደርሰሻል። ግን ይደረጋል የማይባል ነገር ይመስላል። እግዜር ያሳይሽ፣. . . ኤድዋርድን

ያህል ሰው ቅጥረኞችን ተከራይቶ ከሽብር ፈጣሪዎች ጋር ተሞውሎ፣ እኒያን ሁሉ ወንጀሎችና ነፍስ ግድያዎች ፈፀመ ተብሎ እንዴት ይታመናል?››

‹‹የማያታመን ነገር የለም ኒክ። ያተረብኩት ማጠቃለያ ከመላምት የመነጨ ሳይሆን ሎጂክ ነው። ሎጂኩ ደግሞ ቁልጭ ካለ ሃት የበተለ እንጂ በአየር ላይ የተንጠለጠለ ነገር አይደለም። ታዲያ ከዚህ ሎጂክ ሌላ ምን አይነት ማጠቃለያ ይወጣለታል ኒክ?››

‹‹ሌላስ አይወጣለትም።›› ራምሲ አመነ።

‹‹ግን ማጠቃለያሽ እውነት ሆኖ ተገኘ እንበል። ነገሩን ምን ልታደርጊው ትችያለሽ? ማሰቱ እንድም የተጨበጠ ማሰረጃ አስካላገኘሽለት ድረስ ምን የምትሰውሮው ነገር ይኖራል?››

‹‹ፖሊስ ጣቢያ ሄጀ ምርመራ እንዲያደርጉ አመለክታለሁ።››

‹‹ከቢሮአቸው አስወጥተው ይወረውሩሻል። ይህን ኢታውቂም?››

‹‹አውቃለሁ›› አለች ቪክቶሪያ ቅሬታዋ እየተነበበ። ‹‹ማስረሻ ያስፈልገኛል። የደወልኩልህም ለዚሁ ነው። እርዳታ እሻለሁ። እኔን ብትሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበር?››

ራምሲ ተመሰጠ። ‹‹የመጀመሪያው ተግባሬ በግሌ ራሴ ክትትሉን መቀጠል፣ በጥንቃቄ የጀመርኩትን መግፋትና እንቅስቃሴያን መለስ እያልኩ መመርመር ነው። ቪክ አውነትን ፈላጊና ግዕድን አውሮ እንድ ናቸው፣ የሚቆፍሩትን ክቡር ነገር ለማግኘት ይበልጥ በጥልቀት በማሰ መጠን በህይወታቸው ላይ ሊደረመስ የሚዘበዘው አደጋ ይበልጥ እያሰጋና እየበዛ ይመጣልና። በርግጥ ኤድዋርድ በነገሩ ካለበት፣ እስካሁን በአንቺ እንቅስቃሴ ላይ የጥያቄ ምልክት አስተምሮበት ይሆናል። ምናልባትም ኒውዮርክ እንድትመለሽ ያደረገው በዚሁ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እና. . . በድርጊትሽ ገፋሽበት ማለት፣ ይበልጥ ኤድዋርድን ተጠጋሽ ማለት፣ ኤድዋርድ እንቺን ለማስወገድ. . ለማጥፋት እንዲገደድ አደረግሽ ማለት ነው።››

‹‹ጥሩ ማስጠንቀቂያ›› አለች ቪክቶሪያ። ‹‹ግን የሚተማመው እርምጃ፣

እኔን ብትሆን ምን ታደርጋለህ?››

‹‹ሀም. . .›› አለ ራምሲ. ተመስጠውን በመቀጠል፡፡ ‹‹እንግዲህ ማስረጃ ትፈልጊያለሽ፡፡ በውነቱ ከየት ቦታ በምን ሁኔታ ማስረጃ እንደምታገኝ አይታየኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ሁለት ምንሥኙን ልትጠቀሚ ትችያለሽ፣ ሁለቱም ለኤድዋርድ ተረቢታ ያላቸው፡፡ ግን. . . ይህ የኔ ግምት ነው. . .. ሁለቱም ከኤድዋርድ ጋር ተረቤታ እንጂ ፍትር የላቸውም፡፡ አንደኛዋ ሚስቱ ሃና ናት፡፡ ለብዙ አመታት በተለይም ከአንድና ከሁለት አመታት በፊት ጀምሮ ኤድዋርድና ሚስቱ ሆድና ጀርባ ናቸው፡፡ ሌላዋ ኪም ነሰቢት ናት፡፡ ምን ይመስልሻል?››

‹‹ጥሩ ሃሳብ ነው፡፡ ኪም ነሰቢት ማለት ያቺ የብሮድወይ ተዋናይ? የኢዝራ አርምስቱድ ትምጥ የነበረችው?››

‹‹ይህን ብቻ ነው የምታውቂው?››

‹‹ይህን ብቻ፡፡››

‹‹ኤድዋርድ ከእባቱ ወርሶ አስተምጧታል፡፡››

‹‹ምን ታሸፋለህ?››

‹‹ታዲያ አሁን እንደሰማሁት ኪም ደስተኛ አይደለችም፡፡ ኤድዋርድ አጣጥሏታል የሚል ወሬ ይናፈሳል፡፡ በርግጥ አሁን እሷ ሰለሱ ምን እንደምታስብ አላውቅም፡፡ በታማኝነቷ ልትተማመል ትችላለች፡፡ ወይም በኤድዋርድ ያኮረፈችና ብቀላ የሻታት ትሆን ይሆናል፡፡ ከተሳካልሽ በሁለቱ ሴቶች ድል ትመቻለሽ፡፡››

‹‹ካልተሳካልኝስ?››

‹‹ካልተሳካልሽማ ከሁለት አንዷ የምታደርጊውን ሁሉ ለኤድዋርድ አሻውላ ጉድ ታደርግሻለቻ፡፡››

‹‹የፈለገው ይሁን›› ስትል ቆራጥነቷን አረጋገጠችለት፡፡

‹‹ሊላው›› አላት ከመሰነባበቻው በፊት ‹‹እኔ ከነገ በስቲያ ከፕሬዝዳንቱ ጋር ለንደን መጓዜ ነው፡ ካስፈለግሁሽ አቴናየም ሆቴል ደውለሽ

ታግኝኛለሽ። በተረፈ አሜሪካ ውስጥ ሊተባበርሽ የሚችል አንድ ሰው ልጠቁምሽ። ዋይት ሐውስ በተመንግስት በፕሬዝዳንቱ ረዳቶች ቢሮ ይሰራል። ሲ ርዘንብሎም ይባላል። እንዲያውም ከአባትሽ ጋር በጣም ይግባባሉ። ሰውየው የኔም የትርብ ጓደኛ ነው። ኮሌጅ ውስጥ አንድ መኝታ ክፍል ነበር የምንኖረው። ችግር ቢገጥምሽ ከኔ የሚመረጥ ሊታደግሽ የሚችል ሰው የለም። ካንቺ ጋር ስሰራ እንደነበርና አብረን ያሳለፍነውን ሁሉ አሜጋውቸዋለሁ። ችግር ላይ ከወደቅሽ ሳትደብቂ ሚስጥሩን በሙሉ ልትነግረው ትችያለሽ። ግን ምን ጊዜም ቢሆን ከሁሉ በፊት እኔን ለማግኘት ሞክሪ።››

‹‹እሽ፣ በል መልካም ጉዞ፣ ኒክ።››

‹‹ሰኔ እትጨነቂ። የሚያሳስበኝ ያንቺ ነገር ነው። ጠንቃቃ መሆን አለብሽ።››

‹‹በጣም።››

‹‹ታዲያ ማስረጃ ቁፈራሽን መቼ ነው የምትጀምሪው?››

‹‹ነገውኑ ኒክ። በደቂቃ ውስጥ።››

* * *

እንደፎከረችው ጊዜ ሳታጠፋ የኪም ነስቢትን አድራሻ አግኝታ ከደወለችላት በኋላ በግል ተገናኝተው ለመነጋገር የአምድር ጊዜ ቀጠሮ ወሰዱ።

ቨክቶሪያ፣ ኪም ነስቢት መኖሪያ አፓርታማ ሄዳ ከአለቃዋ ቅምጥ ጋር ያደረገችው ውይይት አላረካትም። የሚያረካም አልነበረም። ኪም የኤድዋርድን ሰብዕና፣ ሰስልጣን ሲል ራሱም ቢሆን የሰው ሕይወት ከማጥፋት እንደማይመለስ የተረዳችውን ለቨክቶሪያ ብታስረዳትም በመጠጥ ኃይል ከመድከሟ የተነሳ ቨክቶሪያ የአለቃዋን ሚስጥር በማስረጃ ለማስደገፍ ለምታደርገው ጥረት የሰጠቻት ምንም እገዛ አልነበረም። በመጨረሻ ቨክቶሪያ ከምንም ይሻላል በማለት ከቦርሳዋ ማስታወሻ ደብተር አውጥታ ጫር ጫር ካደረገች በኋላ ለኪም እየሰጠች ‹‹አድራሻየን የሰልክ ቁጥሬን

ብሰጥሽ?›› አለቻት፡፡ ‹‹ሁልጊዜም ከስራ ሰዓት ውጭ ከቤት አልወጣም፡፡›› ከዚያም የሴትዮዋን ትኩረት ከገጽታዋ ልትገመግም እየሞከረች፣ ‹‹የተነጋገርንበት ነገር በተላለ የምትረሽው አይመስለኝም፡፡ ሲመሽሽ ይበልጥ ብታነጋግሪኝ ደስ ይለኛል›› አለች፡፡

‹‹ምናልባት›› አለች ኪም በመጠጥ ጀብርራ ‹‹ደህና ሁኚ፡፡››

የቪክቶሪያ የመጨረሻ ተስፋ ሃና አርምስቱድ መሆኗ ነው፡፡ ኪም ነበቢት በስካርም ይሁን በፍርሃት አይታወትም፣ ጠብ የሚል መረጃ ልትሰጣት አልቻለችም፡፡ የሃና ጉዳይ ደግሞ የተለየ ነው፡፡ ኤድዋርድ ከሚስቱ ጋር መሸነፉን ራምሲ የነገራትን ስታስታውስ ልቧ በተስፋ ይንጠረበባል፡፡ ይሁንና ባለ ምንም ቢሆን ባል ነውና የባሏን ገመና አውጥታ ለክፉ ልትሰጠው አትፈትድም ይሆናል፡፡ ይህን ስታስብ ቪክቶሪያ፣ ራምሲ የመከራት ትዝ ይላታል፣ እውነትን ፈላጊና ማዕድን አውሎ አንድ ናቸው... እናም እጓዝሂ ጥንታቱ የተሞላበት መሆን እንዳለበት ይሰማታል፡፡

ነገር ግን ምንም ቢሆን ቁፋሮዋን ላለማሰለስ ለራሷ ታል ገብታለችና ሳትውል ሳታድር ኤድዋርድ አርምስቱድ መኖሪያ ቤት ሂደች፣ ሃናን ፍለጋ፡፡

የበሩን የመጥሪያ ደወል ሰምታ በሩን ትከፍታለች ብላ የጠበቀቻት ሃናን ራሷ ነበር፡፡ በሩ ሲከፈት አንቲን ብት ያደረገችው ግን ነጭ የነርስ ካባ የደረበች አንዲት ጀርመናዊት የምትመስል ሆኖ ጠጭጣፋ ፊት ያላት ወፍራም ሴት ነበረች፡፡

‹‹አቤት?›› አለች ወፍራሟ ሴት፡፡

‹‹የሚስተር ኤድዋርድ ሰራተኛ ነኝ›› አለች ቪክቶሪያ፡፡ ‹‹ሃና አርምስቱድን ለማነጋገር ነበር፡፡››

‹‹አዝናለሁ ወይዘሪት፡፡ ዛሬ የሚቻል አይደለም፡፡ ሴትዮዋ ዛሬ ማንንም እንዳያነጋግሩ ሀኪም በጥብቅ አዝዟል፡፡››

‹‹የግል ጉዳይ ነው፡፡ ግዴለምትም ራሳቸውን የሚመለከት ነገር ስለሆነ.....››

‹‹የለም ወይዘሪት፣ ዛሬ ማንንም አላስገባም፡፡ የዶክተሩን ትእዛዝ መጣስ

አልችልም፡፡››

‹‹ሴትየዋ ታመዋል ማለት ነው?››

‹‹ከከርስ በኋላ በሻጋታ መርዝ በአደገኛ ሁኔታ ተጎድተው ነበር፡፡ ሀኪም ባይደርስላቸው ኖሮ ባልተረፉ፡፡ የጨጓራ ቧንቧ አስገብተውላቸዋል፡፡››

‹‹አሁን ግን እያሰጋቸውም?››

‹‹መድኃኒዓለም ይመስገን፡፡ በቋፍ ላሉ ሐኪሞች ደረሱላቸው፡፡ አሁን ራሳቸውን እያወቁ ነው፡፡ መልስ መስጠት ጀምረዋል፡፡ ግን በጣም እንደተጎዱ ናቸው፡፡ ከማንም ጋር እንዳይነጋገሩ ሐኪም ከልክሎአቸዋል፡፡››

ቪክቶሪያ በሃና መተረፍ የተሰማትን ደስታ ልትደብቅ አልቻለችም፡፡

‹‹የግል ማስታወሻ ጽፌ ብተውላቸው በሻቸው ይሰጡልኛል?››

‹‹ችግር የለም›› አለች ነርሷ፡፡

በጥንቃቄ ጻፈች፡፡ *‹‹በባለቤትም ሰር የምሰራ ጋዜጠኛ ነኝ፡፡ አራሳቸውን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ለብቻም የማነጋግርም ጉዳይ አለኝ፡፡ እጅግ በጣም ጠቃሚና አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ማስታወሻም ሆነ የኔን ስም ባለቤትም እንዳያዩብኝ፣ አደራዎ የጠበቀ ነው፡፡ አመሰግናለሁ፡፡ ቪክቶሪያ ዊስተን፡፡››* ከስሟ ጎን የአጋርታማዋንና የስልኳን ቁጥሮች አስተምጣ ወረቀቱን ካጣጠፈች በኋላ፣ ‹‹አደራው ከሳቸው ሌላ ማንም እንዳያነበው፣ የኔ እመቤት›› በማለት ለነርሷ ሰጠቻት፡፡

ከዚህ በኋላ ቪክቶሪያ ምናልባት ኤድዋርድ ወደ ላይ ሲወጣ እንዳያገኛት በመጥራት በአሳንሰሩ ከፎቅ ለመውረድ የነበራትን ሃሳብ ቀይራ በደረጃዎች ወረደች፡፡ አወራረዱ የተዋከበ ነበር፡፡ ሲድ ሉታስ ከፓሪስ ከደወለላት እንዳያጣት ቤቷ ገብታ መጠባበቅ ነበረባት፡፡

ይሁን እንጂ ጥድፊያዋን ቀንሳ በዝግታ እንድትወርድ ያደረጋት ሌላ ሃሳብ ደግሞ ብልጭ አለባት፡፡

አዎ፣ ካሁን በኋላ የካርሎስ ጉዳይ ለቪክቶሪያ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ

ነገር ነው።

ቪክቶሪያ አሁን የምታድነው ከፋሞም በላይ የፋሞምን ፋሞ ሆኗል።

* * *

ሽሪ ኔዘርላንድ በተባለው ሆቴል በሚገኘው የመኝታ ክፍሉ ውስጥ ሃሪ ዴትዝ የስራ ልብሱን እንደለበሰ ሁለቱንም ትራሶቹን ከአልጋው የራስጊ እንጨት ላይ አሰደግፎ በጀርባው በከፊል ተንጋሎ ነገ የሚወጣውን ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ የመጀመሪያ እትም እያገላበጠ ያነባል። ተኮናትኑ ጋዜጣ እስትሪእስት በዓምዶቹ ምን ሊያወጣ እንደተዘጋጀ አስቀድሞ ማወቅ ተግባሩና ፍላጎቱ ቢሆንም በላፊው ምሽት ግን ለሚያነበው ነገር ብዙም የሚጨነቅ ሰው አልነበረም።

ከአልጋው አጠገብ ያለው ስልክ ከአንድ ሰዓት በፊት ማታጨለል ሲባባው እስካሁን ፀጥ እንዳለ መቅረቱ ሃሪ ዴትዝን ከመጠን ያለፈ ሳያሳስበው አልቀረም። የጉብ ጋጋኖ ጥሪ ከተጠሮው ካለፈ ደቂቃዎች አልፈው ሰዓት እየተቆጠረ ነው። ሃሪ ዴትዝ ደግሞ ራሱ ብቁ ሆኖ ከሊሎችም ብቃትን የሚጠብቅ ሰው ነው። የጋጋኖ መዘግየት አንድ ስህተት ተፈጥሮ ካልሆነ በስተቀር ምንም ምክንያት ሊቀርብለት የሚችል ነገር ነበር። ጊዜ ባዘገመ መጠን የሃሪ ሞንቀትም እየጨመረ መጣ። የእላ እላ ግን ስልኩ አቃጨለ። ለሃሪ ዴትዝ የስልኩ ድምጽ ብቻውን ትልቅ የምስራች ነበር። ጊዜ ሳይሰጥ ብድግ አደረገው።

"ጋጋኖ ነኝ።"

ሃሪ ጉጉትም እፎይታም እንደተቀላቀለበት፣ "አለቀ?" ሲል ጋጋኖን ጠየቀው።

"ወይ ማለት?" አለ ጋጋኖ የራሱን ሞንቀት ሲያጋልጥ፣ "እንኳን ሊያልቅ ገና አልተጀመረም።"

ሃሪ ኩተንጋለለበት እንዴት ተፈንጥሮ በቂው እንደተኮመጠ ራሱም አያውቀውም። "ምን ምን አልሽኝ?"

"ሞትኩ ሰወሬ በተጥታ ወደ አጋርታማዋ ነው የምትሄደው ብለህ

የነገርኮኝ መስሎኝ ነበርኩ።››

‹‹ነበር። ምክንያቱም መሄዴን በማረጋገጤ ነው። የመኪናውን ጋራዥ ሳይተር ሂጀ ተመልክቼዋለሁ። ከአንድ ሰዓት ተኩል በፊት መኪና ማውጣቷን አረጋግጫለሁ። በተጨማሪ ወደ አፓርታማዋ ነበር የምትሄደው።››

‹‹አይ፣ አይመስለኝም›› አለ ፓጋኖ፣ ‹‹የሚያደርጋትን ሰው መዝሊያዋ አካባቢ ከነመሳሪያው አስተምሀኋው ነበር። በፍፁም ሲያገኟት አልቻለም።››

‹‹ሙስጥ ገብቶ ነበር?››

‹‹ሁለቴ። ደሞ ለመግባት ምንም ችግር አልነበረም። የበሩ ቁልፍ በዘንር ማስያዣዋ እንኳ በቀላሉ ይከፈታል። ያለ ድካም ገብቶ ነበር፣ ሙስጥ ግን ማንም የለም። ጥቂት ሲጠብቅ ቆየና እንደገና ሞከረ። አሁንም ባዶ። ግን የሄደችው ወደ አፓርታማዋ ለመሆኑ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነህ?››

‹‹ሊላ ወዴት ትሄዳለች?›› አለ፣ ሃሪ ወሽመጡ ተቆረጠ። ‹‹ምን እንዳዘገያት አልገባኝም፣ ግን መግባቷ አይተርም።››

‹‹ታዲያ ሰውየአችንን ምን አድርግ ልበለው?››

‹‹ከአፓርታማው ወጥቶ ጥቂት ፈተት ብሎ አስክትመጣለት ሊጠብቅ አይችልም? ከዚያ በኋላ ተከትሏት ሊገባ ይችላል።››

‹‹ይኸ አያዋጣም። ነገሩን እሱም ራሱ አስቦት ነበር፣ ግን በዚያ ፎት አስተማማኝ የመመልከቻ ሰፍራ የለም።››

‹‹እንግዲያውስ ቤቷ ውስጥ ገብተህ አስክትመጣልህ ጠብቃት በለው።››

‹‹እሽከ›› አለ ፓጋኖ ሳት ብሎ። ‹‹ሶስትና አራት ጓደኞቿን አስክትላ ብትጣሰስ? ሰውየአችን አለተለት ማለት ነው።››

‹‹ወይ ጣጣ›› አለ ሃሪ፣ ‹‹እንግዲያውስ እስካሁን ሲያደርግ የነበረውን ይተዋል። ግማሽ ሰዓት ይጠብቅና ይመለስ። ልጅቷን አግኙት አስኪያደ ርግላት ድረስ በየግማሽ ሰዓቱ እየተመላለሰ እንዲያያት አፈልጋለሁ።››

‹‹እንግረዋለሁ።›› የፓጋኖ አንጋር ከማትማማት የመነጨ ነበር።

‹‹ግን . . በየግማሽ ሰዓቱ ተመላለሰ ማለት በየግማሽ ሰዓቱ ይበልጥ ራሱን ስው አይን ውስጥ አስገባ ማለት ነው። ስጋቱ ከፍተኛ ነው። በዚያ ልክ የምንከፍለውም መጨመሩ ነው።››

‹‹ዳግመኛ ስለ ክፍያ እንዳታነሳብኝ!›› አለ ሃሪ ደሙ ፈለቀ። ‹‹በእሰር እጥፍ ቢጨምርብህ እንኳ አይንህን እንዳታሽ። የምንፈልገው ስራውን እንዲፈጽም ብቻ ነው። አሁን ወደ ቢሮ መሄድ አለብኝ። ሁለተኛ ስትደውልልኝ የልጅቷ ነገር መጠናቀቁን፣ ላንዲና ለመጨረሻ መሰናበቷን እንደምታረጋግጥልኝ እጠብቃለሁ። የምልህን ሰምተህልኛል?››

‹‹በጎይልና በግልጽ›› አለ ፓጋኖ ስልኩን የደወለበት ዋነኛ ምክንያት፣ ክፍያውን አስጨምሮ ከሮማሪው ላይ ለግሉ ኮሚሽን ለማሸረፍ የነበረው ምኞት በመሳካቱ ውስጡ እየፈነደቀ።

‹‹በል እንደጨረስክ ቢሮ ደውልልኝ።›› ሃሪ ዴትዝ በቁጣ ደሙ እንደፈላ ስለኩን በጎይል ጥርትም አድርጎ ከዘጋው በኋላ ሁልጊዜም በሚያደርገው ነገር ላይ መሉ እምነት ከሚሰማው ከኩሩው አለቃው ከኤድዋርድ አርምስቲድ ጋር ለሚጠብቀው የምሽት ስብሰባ ወደ ቢሮው ለመሄድ ከአልጋው ተነሳ።

* * *

ኪም ነስቢት እንቅልፍ ለመተኛት ሞክራለች፣ ወይም ተኝታለች። እንዴት እንደሆነ በውል አልታወቀም አላት። ከተጋደመች አንድ ሰዓት አልፏታል፣ መሉ በመሉ የነቃችው ግን ዛና አሁን ነው። የመጠጡ የሀረ ድምር እንደጠቅሮው የታመመኝ አይደለም። ራስ ምታቱ፣ መጋጠሚያ መቆርጠሙ፣ አይን መሞሰምሰሙ፣ ከንፈርና ምላስ መድረቁ . . ሁሉም በልክ ነበር።

ከአልጋዋ ተነስታ ከሁለት ነገሮች መካከል የትኛውን መውሰድ እንዳለባት ታመነታ ጀመር፣ አስፒሪን ወይም መጠጥ?

መጠጥን መረጠችና ጠርሙስና መለኪያ ፍለጋ ሄደች።

በውስኪዋ ላይ በረዶ ከጨመረች በኋላ መለኪያዋን እንደጨበጠች

በሳሎኑ መዲያ መዲህ ትንሳፈዳድ ጀመረ። ከተጫዋኝነው ብቸኝነድ ጋር ስላስተያየቸው ሳይሆን አይተርም፣ ሳሎኑ የስታዲዮም ያህል ሰፍቶ ታያት። የመተላለፊያውን ኮሪደር መብራት ስታብራ ሁለት የነገ ጧት ጋዜጦች . . . ሪከርድና ታይምስ ከመልእክት ማስተመጫው ሳጥን ተንሸራተው መሰሉ ላይ አየቻቸው። እንደምንም አጎንብሳ ካነሳቸቸው በኋላ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አገላብጣ ሊታነባቸው ወደሶፋው አመራች። ሶፋው ላይ ተመሰታትለው የተተመጩትን ሁለት ትራሶች ስትመለከት እንድ ትውስታ ተቀሰቀሰባት።

እንድ እንግዳ መጥቶ እንደነበር ትዝ አላት። ቱጥሎም ደግሞ እንግዳዋ ሰለኤድዋርድ ሊታነጋገራት የመጣች የሪከርድ ጋዜጣ ሰራተኛ ጠጣት ቆንጆ መሆኗን አስታወሰች።

ቱሮ አለችና ከውሰኪዋ እየተንኔጌች ከእንግዳዋ ጋር ስለተነጋገረችበት ጉዳይ ማሰላሰል ያዘች። ልጅቷ ኤድዋርድ በተለይ በአለም አተፍ ሽብር ፈጠራዎች ላይ ስለሚያወጣቸው ትክሰ ዜናዎች እንስታ ኤድዋርድ ራሱ ከእኒያ ሽብር ፈጣሪዎች ጋር የተያያዘ የግል ግንኙነት ሳይኖረው እንደማይተር መጠራጠሯን ነግራታለች። ኪም ራፏም ኤድዋርድ ማለት የለየለት አረመኔ የስልጣን ጥመኛ ስሚትና ምኞቱ እውሬ ያደረገው ደንታ ቢስ መሆኑን ለጋዜጠኛዋ አረጋግጣላታለች። ከዚህ በስተቀር ከወጣቷ ጋዜጠኛ ጋር ምን እንደተነጋገረች ኪም ሊታስታውሰ አልቻለችም።

መጠሚን ጨልማ እንደገና እስክ እቶ ሞላችውና ጉንፈኒ የሚችለውን ያህል ተሳንፎታ ጸሃመኛ በሳሎኑ መንገራደድ ጀመረች። አሁን በሃሳቧ የመጣባት ግን ኤድዋርድ ነበር። እውነትም የለየለት አረመኔ ነው፣ ኤድዋርድ። እንዲህ ብቻዋን የተዋት ለግል ጥቅሙ ብቻ የሚዋከብ ሰፍሳፋ ቢሆን ነው። አንዳች ነገር ከምድር ቢያጠፋው ተመኘች። የተንጣለለውን ሳሎኗን ግራ ቀኝ ስትታኝ ደግሞ ከናሳሰቲክ፣ ከእንጨትና ከቆርቆሮ ከተሰሩ ቲሳቴስ በስተቀር የህይወት ዘር ማየት ባለመቻሏ ቱሮድ ጨመረ።

ብቸኝነት! በምድር ካሉ በሽታዎች ሁሉ የከፋው ብቸኝነት በቢሊዮን ከሚቆጠረው የሰው ልጅ ዘር ነጥሎ እዚህ ፊረስ በሚያስጋልብ ሳሎን ውስጥ እያንገዋለለ ከራሷ ጋር ያነጋገራታል፣ ልትመልሰው በማትችለው ጥያቄ

ይወዋታል፤ ብዙ ሃሳቦችን አእምሮዋ ውስጥ አምቆ አፏን ከራሷ ጋር ያሟግታታል። ራሷን እየከሰሰ ያንገላታታል።

ድንገት ሰው አሰፈሰጋት፣ ሲጋና ደም የለበሰ ሰው። የምታውቀው ሰው፣ ኤድዋርድ አርምስቴድ ብቻ ነው።

ትናንት በጥፊ ቢመለውላትም፣ በእጮኮታማው እንዴ እብድ እያንዣ እየተወራጨ ቢሄድም፣ ዛሬ በአእምሮዋ ድቅን አለባት። ፈለገችው። ሪሃብ አንጀት ሲያጥጥ ምግብ ማማረጥ እንደማይቻል ሁሉ ብቸኝነት ሲከብድ ደግሞ እንደሰይጣን የሚያስጠላም ቢሆን እንኳ የሚያውቁት ሰው ይናፍቃል።

እናም ኤድዋርድን እንደገና መደፈ ሊያመጣ የሚችል ስትራቴጂ ታሰላስል ጀመር።

አንድ ሃሳብ መጥቶ ኮረኮራት። ከጥቂት ጊዜ በፊት መጥታ የነበረችው በኤድዋርድ የግል ህይወት ግልታ ግብታ መሬ የምታነፈንፍ ጋዜጠኛ ትዝ አለቻት።

ለኤድዋርድ ስልክ ለመደወል ያቺ ጋዜጠኛ በቂ ሰበብ ትሆናለች። ኤድዋርድን በስልክ አግኝታ አንድ ውለታ ብትጥልበት፣ ቢታስጠነቅቀው፣ ከሰራተኞቹ አንዷ ከጀርባው በግል ጉዳዩ ላይ አደገኛ ክትትል እያደረገችበት መሆኗን ብትነግረው በኪም ተቶርቋሪነት ልቡ እንደሚነካ፣ ከሻርፍ ጋር በመነጋገሯ ያጠፋችውን ጥፋት እንደሚያካክሰላት ቁልጭ ብሎ ታያት። ከዚያ በኋላ ኤድዋርድ ለህይወቱ ማን እንደደረሰ ያያል፣ ተቶርቋሪው በመሆኗ ይቅርታ ያደርግላታል፣ ተመልሶ ይጠይቃታል፣ ይህ ሳሎንም እንደገና በሰው ይጎበኛል።

ጠረጴዛዋ ላይ የውስኪ መለኪያዋን አስተምጣበት የነበረውን ወረቀት አነሳችው። እንግዳዋ ስሚንና አድራሻዋን ለኪም ስትሰጥ የጻፈችበት ወረቀት ነበር። የእንግዳዋ ጋዜጠኛ ስም ቪክቶሪያ ዊስተን መሆኑን አነበበች።

በቀጥታ ወደ ኤድዋርድ የግል ክፍል ደወለች።

"ሄሎ አዲ" አለች ስልኩ እንደተነሳ፣ "ኪም ነኝ።"

‹‹ኤድዋርድ አይደለሁም፡፡›› መለሰላት አንድ ድምጽ፡፡ ‹‹ሃሪ ዴትዝ ነኝ፡፡››

‹‹የደወልኩት የኢዲን የግል ቁጥር ነበር፡፡ ኢዲን አፈልጋለሁ፡፡››

‹‹እሱ ቢሮ እየሰራሁ ነኝ፡፡ እስኪ በትርብ እንዳለ ይጠብቁ፡፡››

‹‹ሂድና እይልኝ›› አለችው ትእዛዝ በተቀላቀለበት ቃና፡፡

ኤድዋርድ ቢሮ ያለው የስልክ መነጋገሪያ የእጅ መዳፍ ሳያርፍበት አልቀረም፣ ፀጥ እንዳለ ታውቃት ኪም፡፡ ፀጥታው ግን ፍፁም አልነበረም፡፡ መነጋገሪያው ላይ ያረፈው መዳፍ በመጠኑ ሽርተት ብሎ ይሆናል፣ አንድ ድምጽ ከርቀት ሲናገር ተሰማት፡፡ ድምፁ ቁጣ ነበረበት፡፡

‹‹ኤሞ ምነው. . . ምን እንደምትመልስ ነግሬሀ አልነበረም?. . . የለም በላት፡፡››

የኤድዋርድ ድምጽ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ የሃሪ ዴትዝ ድምጽ ጥርት ብሎ ቀረበላት፡፡ ‹‹ተዘዋውሬ ፊለግሁት ኪም፡፡ በትርብ የለም፡፡››

ኪም በቁጣ ተሞ አለች፡፡ ‹‹አንተ ውሻ! አጠገብህ ነው ያለው. . . የሚናገረውን ሰምቸዋለሁ፡፡ አሁኑኑ እንዲያነጋግረኝ ብትነግረው ይሻላል፡፡ ለራሱ የሚበጀው ትልት ነገር አለኝ፡፡ ጓላ እንዳይቆጨው!››

ስልኩ ጥቂት ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ የሃሪ ዴትዝ ድምጽ እንደገና ተሰማ፡፡ ‹‹እዚህ አካባቢ የለምኮ. . ኪም፡፡››

‹‹ይተወው፡፡ ወንዳገረድ፡፡ ዋጋውን ያግኛል›› ብላ ተንጠራርታ ስልኩን ዘጋች፡፡ ለአምስት ደቂቃም ያህል ሶፋው ላይ ተለጥጣ እንደተኮመጠች የልቧን አመታት ልታረጋጋ ሞከረች፡፡ በግልጽነት የተረበሸችን ወጣት ልታሰወጋ ያደረገችው ሙከራ ባለመሳካቱ ራሷን ታዘበችው፡፡ ‹ዋጋውን እሰጠዋለሁ ይህን በስባሳ› አለች ለራሷ፡፡ ‹ብቃ የጅን ያግኛል፡፡››

ንጄድ ፊቷ ላይ የሚንሳፈፈውን ፍጆግ ለማስገደድ ከመጠጡ ደጋግማ ሳበችለት፡፡

ከንግዲህ የሚጠበቅባት አንድ ነገር መሆኑ ተሰማት፣ ብቸላ፡፡

የብሎሳሞን ንድፍ ካወጣች በኋላ የመለኪያ ማስተመጫ የነበረውን ወረቀት እንደገና እንስታ አነበበችው።

ኤድዋርድ አርምስቱድን በጥርጣሬ የምትከታተለው ወጣት ጋዜጠኛ ስም በጉልህ ተነበባት። *ቪክቶሪያ ዊስተን።*

እም ያች ልጅ፣ ስለኤድዋርድ አንድ ሚስጥር የምትፈልግ ሴት። ግን ኪም ምን ልትነግራት ትችላለች?

ትኅንት ከኤድዋርድ ጋር በጠበ ስትወጣብ ኤድዋርድ የተናገራቸው ታላት መለስ ብላ አሰበቻቸው። *«ዘና የምለው እዳ ነኝ። ታሪክ የምሰራ እዳ ነኝ። ምድርን የማሽከረክር እዳ ነኝ...»*

እንዲህ ያሉ ሀረጎች ነበሩ ከኤድዋርድ የባረቁባት። ግን እኒህ ታላት ኤድዋርድ ሽብር ፈጣሪዎችን ለማንሳቀስ ፍንጭ የሚሰጡ ይሆኑ ይሆን? ይሆናሉ ወይም እይሆኑም። ለቪክቶሪያ ዊስተን የሚጠቅሙ፣ ልዩ ትርጉም ያላቸው ሐረጎች ይሆኑ ይሆን? ይሆናሉ ወይም እይሆኑም።

ኤድዋርድ እንደሰራላት ልትሰራለት፣ እንደተሟላተባት ልትሟላትበት ልታሰላጋው ፈልጋ ነበር፣ ኪም። ግን የያዘችው ሞብዋ ወደ ቪክቶሪያ ዊስተን ለማቅረብ እጅግ ደካማ ሆኖ አገኘችው።

«ኤዲያ፣ ጃነብ ይግባ፡ አለች፣ና ኪም ነገሩን ሁሉ ትታ ብስጭቷን ለማቅለል ከመጠጡ መደጋገምን መረጠች።

በመጨረሻም ሁልጊዜ እንደምታደርገው ለእንትልፍ መጥሪያ፣ ለአልጋ መጠጫ ጋዜጣ ልታነብ ወሰነች። መጀመሪያ እጅዋ ያነሳው ሪከርድ ጋዜጣን ነበር። ለጋዜጣውና ለኤድዋርድ ያላትን ጥላቻ ለመግለጽ ሪከርድን ዙዮትዮት አድርጋ ወረወረችው። ይህን ስታደርግ ኤድዋርድ ባያት ደስ ባላት። ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣን ብድግ አደረግችው፣ አሁንም ኤድዋርድ በኖረ ኖሮ ምን ያህል በንዴት ይጨስ እንደነበር እየታያት የታይምስ ጋዜጣን የመጀመሪያ ገጽ ማንበብ ጀመረች። ሚቹ የኤድዋርድ አባት ኢዝራ አርምስቱድ ሐንድ ገጽ ንባብ ከሐንድ ሙሉ ፓንፓዮ ይመረጣል፡ ያላት የነበረው ትዝ አላት። ጋዜጣውን ገጽ በገጽ አገላበጠች። ስድስተኛው ገጽ

ላይ ሰትደርስ የአንድ ርዕሰ ሀረግ ትኩረቷን ሳበው። ቃሉ ‹‹ሥሓምር ዘኢ›› የሚል ነበር። ‹‹ዘጠና ቆሰሉ›› ይላል ርእሱ ሲጠቃለል።

በርዕሱ ስር ያለው እጅር ዝርዝር ዜና በዶክተር ሻርፍ ላይ የደረሰውን ከባድ አደጋ አረዳት። ያ ደግ ለሰው አሳቢ ዘኢም ብዛት ያላቸው ቀደ ጥናቶች እየተደረጉለት መሆኑን አነበበች። የጉዳተኛው ዲግሪዎችና የክብር ሽልማቶች ዝርዝር ጭምር ሰፍሯል። በማጠቃለያውም ጉዳቱን ያደረሰው አሽከርካሪ ከአደጋው በኋላ በፍጥነት በማምለጡ ተጠያቂው ማን እንደሆነ እስካሁን የተደረሰበት ፍንጭ አለመኖሩን ፖሊስ ከሰጠው መግለጫ ለመረዳት መቻሉ ያሳዝናል።

አደጋ . . . ያልተደረሰበት ተጠያቂ፣ ዝግንን አላት፣ ኪም።

ከአደጋው በፊት ከዶክተር ሻርፍ ጋር ያደረገቻቸው ንግግሮች ትዝ አሏት። ዶክተሩ ቱስለኛ ለኤድዋርድ ሁኔታ ያሳይ የነበረው መጨነት ታወሳት። በመጨረሻም ስለኤድዋርድ ከጂ ጋር መነጋገሩን ለኤድዋርድ እንዳትናገር አደራ ብሏት ነበር፣ ዘኪሙ። እሷ ግን አደራዋን ጥሳ የዘኪሙን ሚስጥር አውጥታ ለኤድዋርድ ነግራዋለች። በመጠጥ ኃይል ተገፋፍታ፣ በሰካር መንፈስ ተነሳስታ፣ በደደብነት ተነሳስታ የዘኪሙን ሚስጥር አውጥታ ለወንዳገረዱ ውሽማዋ አተብላለች። ይህን በመስማቱም ነበር ኤድዋርድ ደም ቡልት አስኪላት በጥፊ የጠፈጠፋት።

እናም አሁን ኤድዋርድ ዶክተሩን ለመግደል መሞከሩ ታወቃት። አዎ፣ ነገሩ ይኸው ነው። የተከሰተው ድንገተኛ እጋ አይደለም፣ ሆን ተብሎ የተፈጸመ የግድያ ሙከራ እንጂ። በሻርፍ ላይ ለደረሰው አደጋ ተጠያቂው ማን እንደሆነ እሷ ብቻ ታውቃለች። በአእምሮዋም ቅንጣት ጥርጣሬ የለም። ግን ለምን? ለምንድን ነው ኤድዋርድ ግድያውን የታሳው? ምክንያቱም በግል ባህርዩ ክትትል እያደረገ ለጤንነቱ ቢጨነትም እግረ መንገዱን ማንነቱን. . . ምናልባትም ወንጀሎቹን ሊያጋልጥበት ይችላልና።

ወንጀሎቹን፣

ኪም እንደግና ቪክቶሪያ ዊስተን ስለ ኤድዋርድ ወንጀለኝነት እንስታ

ማስረጃ እንደምትፈልግበት ያወሳችላት ትዝ አላት።

ያ! አሁን ግና ደረሰችበት። ቪክቶሪያን በማስረጃ አስታጥቃ ኤድዋርድን ልታስወጋ ወሰነች።

ከሶፋው ብድግ ስትል ከጠባችው መጠጥ ብዛት የተነሳ ጥምብዝ ብላ መስከሯ ሚዛኗን ጠብቃ መቆም አትቻት፣ እንደምትንገዳገድ ታውቃት። ራሷን አለመሳቷና የምታደርገውን እንደምታውቅ ግን ተሰምቷታል። ግን ሰው እንዴት ባንድ ወቅት ሰካራምም የሚያደርገውን የሚያውቅም ሊሆን ይችላል? የለም፣ በርግጥ ሊሆን አይችልም! ኪም ግን ሁለቱንም ነበረች።

አሁኑኑ መኝታ ቤቷ ገብታ ፒጃማዋን አወላልቃ የውጭ ልብስ ልትለብስ አሰበች። ከዚያስ?

በቀጥታ ወደ ቪክቶሪያ ዊስተን።

* * *

በተወችላት አድራሻ እየተመራች ቪክቶሪያ ዊስተን መኖሪያ አፓርታማ በር ላይ እንደደረሰች ኪም በሩን አንኳኩው ብላ በመዳፏ ጠፈጠፈችው።

መልሱ ቅጽበታዊ ነበር። «ማነው?»

«እኔ ነኝ፣ ኪም ነስቢት። በክርስቶስ አስገቢኝ?»

በሩ ተከፍቶ ቪክቶሪያ ወዲያውኑ ብብቷን አፈፍ ባታደርግ ኖሮ ኪም ነስቢት በሩ ስር በተዘረረች ነበር።

«ወይዘሪት ነስቢት. . . አልጠበትሁም ነበር።» ቪክቶሪያ እንግዳዋን በሁለት እግሯ እንደቆመች ለማየት ባለንይሷ መደገፍ ነበረባት።

«ላነጋግርሽ እፈልጋለሁ. . .ብዙ ነገር አምጥቼልሻለሁ. . .» እየተወላከፈች ተኮላተፈች ኪም። «ስለ ኢዲ፣ ስለ ኤድዋርድ አርምስቱድ ብዙ የምነግርሽ አለኝ። አየሽ. . . የሰው ልጅ ህይወት በእጁ ነው ያለው ይለሻል። ዜና የምሰራ እኔ ነኝ ይለሻል። ምናልባት ከመንበዴም ጋር ይሠናል ዜና የሚሰራው። እኔ እንጃ። ግን አንድ ሰው ደግሞ ሊያስገድል ሞክሮ ነበር፣ ሀኪሙን። ለጤንነቱ ስላሰበለት ለምን ይከታተለኛል ብሎ።

ግን . . ግን ጠጥቶሙ . . ሞሞ ቢሆኑ . . እንኳ እሳ ነው የጠጣሁት። መጀመሪያ ልቅመሞ . . .

ቪክቶሪያ በሩን . . . . . በመጨረሷ በፊት ለሊት መኝታዋ እንደ እሳ . . . . . ጎጣጣፊ ሶፋዋ ወስጻ አስቀመጠቻት። «ቡና ጣፍላሽ?» አለች ቪክቶሪያ። «ጥቁር ቡና ነው የምትወስጂው?»

«የተገኘውን።» ሳቅ አለች ኪም።

ቪክቶሪያ ቡና ለማፍላት ወደ ማብሰያ ክፍል ከጣቸች ደቂቃ እንኳ አልሞላም። . . . . . ትክል ግራ ቀኝ ስትወላወል ዙያ ሶፋው ላይ ልብሽ ብላ ተኛች። ዘንቺው እጅዋ ራሷን አንተርሳ በላይኛው በጉሯን ወደ ጎላዋ ለመሳብ ስትጣጣር ከመድከሚ የተነሳ እጅዋ አይኖጅ ላይ እንዳረፈ ቀረ።

እጅዋ ያሳረፈችባቸውን አይኖቿን ከድና ለማረፍ ፈለገች። የሰራ አካላቷ የሚያቀርብላት ጥያቄ እረፍት ብቻ ነበር። እረፍት፣ ዘለአለማዊ።

ገልበጥ አለችና ዝርግትግት ብላ በጀርባዋ ተኛች። እንቅልፍ እንዳይወስዳት ለመሚገት ብትጥርም ወዲያውኑ እጅዋን ሰጠች። በማታውቀው ቤት ተኛችና አረፈችው፣ ያለ ያሉኝታ።

የእንቅልፍ ጨለማ ዋጣት።

ያ የእንቅልፍ ጨለማ የሳሎኑ በር በተሰታ ሲከፈት እንኳ አልተገፈፈም። ከማብሰያ ቤቱ በር ተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኘው የሳሎን በር በስፋት መከፈቱን ተጠሰ። ወዲያው ደግሞ የአንድ ሰው ቅርጽ ታየ። ሰውየው በከፈተው በር ልጥፍ እንዳለ ልምድ ባካበተ ወጥኛ አረማመድ ግድግዳውን እየታከከ ወደ ውስጥ አመራ። ሰኮንድ በማይሞላ ጊዜ ሰውየው ዙሪያውን ቃኘ። በዚያው ሰኮንድም በንቃታቸው ከድመት ጋር የሚመሳሰሉት አይኖቹ በሶፋው አልጋ ላይ በተጋደመው ሰው ላይ አረፉ። አሃ ያችውና . . . በመጨረሻው ተገኘች። ሶፋው ላይ እንቅልፏን ትለሸልሻለች፣ ተራሳጊዋ።

ጠጋ ብሎ አስተዋላት። ጉዳዩን ከመፈጸሙ በፊት በጉልበት ሊገናኙት አሰበ። ከማሰናበቱ በፊት ፍላጎቱን ሊያረካባት ተመኘ። ወዲያውኑ ግን እንዲህ ያለው ተግባር ከሙያው ውጭ መሆኑ፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ድርጊት መሆኑ ተሰማው። ሰውየው በሙያው ኩራት የሚሰማው ሲሆን ሙያው ደግሞ ተልኮውን ያለአንዳች እንከን ከፍጥነት ጋር መወጣት እንዳለበት የሚያስገድድ ነው።

ይህኛውን ተልእኮ መወጣት በጣም ቀላል ተግባር ነው፣ በውነቱ።

ድምጽ በማያሰሙት የሚዳ ቲኒስ መሣሪያዎቻ ሚጣምቅ እየተራመደ ወደ መኝታዋ ግርጌ ተጠጋ። በዚያው ወቅትም ቀኝ እጁ ከኪሱ ውስጥ እጅግ በጣም ዘመናዊውን ድምጽ አልባ ሽጉጥ አወጣ።

አቀባበለ። ጠቋሚ ጣቱን ምላጩ ላይ አሳረፈ።

ቀኝ እጁን ወደ አልጋው ግርጌ ወሰደው። ሽጉጡ የቀኝ እጁ ተጥጥላ ነበር።

በትክክል ግንባሯ ላይ አነጣጠረ።

ምላጩን ሳበው።

ሱ. . . . . ሽ!

ሴትዮዋ ከወደ ራሷ ነጠረች. . ሁሉም ሰዎች እንዲህ እንደሚ ያደርጋቸው ያውቃል፣ ሰውየው። . . ወዲያው ግን እንደበፊቱ ዐጥ አለች።

ዘላቂ ይሁን ጊዜያዊው እንቅልፍ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ሰውየው ኢላማውን ዝቅ አድርጎ በድጋሚ ምላጩን ሳበው።

ሱ. . . . . ሽ። ሙሉ ለሙሉ ደረቷን ቦትርኮ ገብቷል ጥይቱ።

ከሁለተኛው ምት የሚወጣው ደም ልብሷን ማበስበስ ጀምሯል። ዞር አለና እንዳመጣጡ በዝግታ ሳይሆን ለእምነት በሚያስችገር ፍጥነት በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘጉቶ እንደጥላ ውልብ ብሎ ጠፋ።

ይህ ከሆነ ደቂቃ እንኳ አልተቆጠረም፣ በተቃራኒ አቅጣጫ ያለው በር

ተከፍቶ ቪክቶሪያ ከግብስያ ቤቱ ቡና በማትረቢያ ከስኒና ከስኳር እቃ ጋር ይዛ ብት አለች። ያልተለመደ ድምጽ የሰማች መሆኑን ጠርጥራ ስለነበር እንግዳዋ በስካር እንድ እቃ ሳትሰብር እንዳልቀረች ገምታለች።

ሳሎኑ እንደበፊቱ ነው። ወደ ውጭ የሚያስወጣው በርም እንደተዘጋ ነው። ልባ ረጋ ስላለላት ቪክቶሪያ ወደ ሶፋው አመራች።

ኪም ነሰቢት ጧ ብላ ተኝታለች።

ቪክቶሪያ መጀመሪያ የገባት ነገር አልነበረም። ወዲያው ግን የሆነውን ስትረዳ ቪክቶሪያ የያዘችውን የቡና ማትረቢያ በቱሚ ለቀቀችው። በፍላጎቱ ወደኋላ የሚንደረደረውን እግሯን በመጨረሻ ያቆመው ከጀርባዋ የገጫት ግድግዳ ነበር።

ልትጮህ ሞከረች። ከአንደበቷ የወጣው ግን ምንኑ የማይታወቅ ሰላላ ድምጽ ነበር።

አስክሬን ከታቀፈው ሶፋ መሸሿን በመቀጠል እንደምንም የጨኸት ድምጽዋን ፈለጋ አግኝችው። እራታዋን እያቀለጠች ወደ በሩ ተንደርድራ ሄደች። እራታዋን እያቀለጠች ከቤቷ ወጣች።

* * *

በሰማይ ጠቀስ የአርምስቱድ ሀንባ ስድስተኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው ቢሮው ኤድዋርድ ከፊት ለፊት ከተቀመጠው ረዳቱ ከሃሪ ዴትዝ ጋር የመጀመሪያውን ቡናቸውን አስቀርበዋል። ኤድዋርድ ሞኑ ላይ ያስቀመጠውን የእለቱን የሪከርድ ጋዜጣ ቅጅ ሶስተኛ ገጽ ያነባል።

‹‹ማውጣታችሁ ትክክል ላይሆን አይቀርም›› አለ ኤድዋርድ።

ነገሩ ጥያቄ አልነበረም፣ ሃሪ ግን መልስ ሊሰጥ ፈለገ። ‹‹ማተሙ የግድ አስፈላጊ ነበር›› አለ በረጅሙ ተንፍሶ፣ ‹‹አለባ ተጠራጣሪዎች እንሆን ነበር።››

‹‹ልክ ነህ›› አለ ኤድዋርድ እራሱን በአምንታ እየነቀነቀ። ‹‹ምስኪን ኪም። ግን ሰውየው እንዴት ሊሳሳት ቻለ?››

«አይፈረድበትም» አለ ሃሪ ምክንያት ሲያቀርብ፡ «የሚመታትን ሴት ከዚህ በፊት አላያትም፡፡ ክፍሉ ውስጥ የሚያሟትን ሴት እንዲመታ ብያ ነበር የተነገረው፡፡ ኪምን ሶፋ ላይ ተጋድማ ሲያይ ሊጠራጠር አይችልም፡፡ ያቺ ርኩስ ግን ባጋጣሚ ማብሰያ ክፍሏ ውስጥ ኖራለች፡፡፡»

«ይህ ማለት ግና ያልተጠናቀቀ አንድ ሰራ ይቀረናል» አለ ኤድዋርድ ቀበል አድርጎ፡፡

«መሆኑ ነው፡፡፡»

«ለመሆኑ ሞትክ ለወሬ አሁን የታባቷ ግባች?»

«ከመኖሪያዋ ጠፍታለች፡፡ የት እንደገባች የታወቀ ነገር የለም፡፡»

«መታወቅ አለበት፣ ሃሪ፡፡፡»

«አታመልጠንም፣ አለች፡፡፡»

ኤድዋርድ ከበናው ፉት አለለት፡፡ «ኧረ ለነገሩ ኪም ግን እዚያ ቤት ምናባቷ ታደርግ ኖሯል?»

«ምን አውቅላታለሁ?. . . .ግን ለተፈጠረው ሰሁት በጣም አዝናለሁ፡፡፡»

«እኔ ግን የተሰማኝ ስሜት ሃዘን ይሁን ምን መለየት አትቶኛል» አለ ኤድዋርድ ከተቀመጠበት እየተነሳ፡፡ «ለወሬ ሳይሆን አይቀርም እዚያ የሄደችው፡፡ ምናልባትም የምታውቀውን ሚስጥር ከመለፍለፏ በፊት ሳንቀድማት አልቀረንም፡፡፡» ፈጣን ብሎ የሲጋራ ባኩ ይከፍት ጀመር፡፡ «ምን ጊዜም አኪር ለኛ እንደሆረ ነው ሃሪ፡፡፡»

* * *

ቪክቶሪያ ዊስተን በለጋው የህይወት ዘመኗ የምትገኝ ወጣት እንደመሆኗ ሞት ራሱ ቀርቶ ሃሳቡ እንኳ ለአእምሮዋ እጅግ የራቀ ነገር ነበር፡፡ ባለፈው ጊዜ ግን ቪክቶሪያ ሞትን ለሁለተኛ ጊዜ ልትመለከተው በቃች፡፡ ከደቂቃ በፊት ሚስጥር ሊታባፍላት የነበረች ብትሰክርም ደስተኛነቷ ከገፅታዋ የሚያስታውቅባት ፍልቅልቅ ሴት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ለዝንተ

አለም የተኛ አስከሬን ሆኖ ጠብቃታለች።

ይህኛው ከስተት ደግሞ ፓሪስ ላይ በካርሎስ ጠፌ አጥባይ ላይ ከደረሰው የበለጠ የሚዘገንን ሆኖ አገኘችው።

የኪም ነስቢትን አስከሬን ከተመለከቱት ብዙም ሳትቆይ አንድ አስፈሪ ጥርጣሬ በሃሳቧ መጣ። ነፍሰ ገዳዩ የአፓርታማውን ነዋሪ ሴት ማለትም ራቧን እንዲገድል ሳይሆን እንዳልተረና ኪም ነስቢት ተኗ ደርሶ በሳሎኗ በመገኘቷ በጥይት መመታቷን ጠረጠረች።

በርግጥ ፖሊስም ወንጀሉ የተፈፀመው ለሰርቶት በመሣ ሊባ መሆን እንዳለበት ተንትኗል። ይህን ግምት ቪክቶሪያ ብታምንበት ኖሮ ፍርሃቷ በተለለላት ነበር። ነገር ግን አላመነችበትም። የኪም ነስቢት ገዳይ ለሰርቶት ምንም ጊዜ አላጠፋም። ሳሎን የገባው ለእንድ አላማ ብቻ ነበር፣ ለግድያ። በመሆኑም ገደለና በትጽበት ተሰወረ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ቪክቶሪያ ያመነችው ይህንን ነበር። አሁንም እምነቷ ይኸው ነው። ቪክቶሪያ ዊስተንን እንዲገድል አንድ ትጥረኛ ተልኮ እንደነበር ጥርሱን ያገጠጠ ሃት ሆኖ ታይቷታል። እድል ሆኖ ከሞት ተርፋለች፣ ያ ሞት ግን በማንኛውም ጊዜ ተመልሶ ሊነበኛት እንደሚችል ፊርታለች።

እናም ደመ-ነፍሷ ነግሯት፣ ከአይታ መሰወር እንዳለባት፣ ከምትታወቅበት አድራሻዋ መሸሽ እንደሚገባት፣ ምን ማድረግ እንዳለባት እስከምትወስን ድረስ ተደብቃ መቆየት እንዳለባት ደመ-ነፍሷ መከሯት ትናንት ማታ አፓርታማዋን ለቃ ተሰወረች። ባንድ ወቅት አባቷ ለሥራ ጉብኝት ኒውዮርክ መጥተው ሳለ አብራቸው መጥታ ለብዙ ቀናት አርፈውበት የነበሩበት ሮያልተን የተባለውን ሆቴል አስታውሳ ስሚን ቀይራ ባርባራ ፓሪ በተባለ ስም ተመዝግባ ሁለት የፖሊስ መኮንኖች አጅበዋት ገባች።

የእንትልፍ ኪኒን ብትወስድ እንኳ የትናንቱን ለሊት ያነጋችው እንዳፈጠጠች ነበር። የሞት ጋሻ ጃግሬ ትከሻዋ ላይ ቁጢጥ ብሎ መቼ ከዚች አለም እንደሚያሰናብታት ለመወሰን የሚያሰላስል ሊመስላት ነበር ያደረው። ጋሻ ጃግሬው የሚታያት ኤድዋርድ አርምስቱድን ተመስሎ ነው።

ትዝታ መለስ ሲሉላት ከተትዛን ለማንም መወሰኗንና የታዘቧቸውን ብቻ ለመፈፀም መዘጋጀቷን በኤድዋርድ አስታውቃ ያትርታ ልትለምነው ታስባለች። እሱ ተግባሩን ከተወ እሷም የጀመረችውን ከትትል እንደምትተው ልትነግረው ትፈልጋለች። ሠዲያው ግን ኤድዋርድ ከእርምጃው በፍፁም ንትንት ሊል እንደማይፈትና ይታወቃል።

እናም ሞት ትርብ መሆኑ ሲታያት በፍርሃት ትንዘፈዘፋለች። ትናንት ሊሊቱን ፈርን ትራፊ ውሰጥ ተብራ በእንባ ስትታጠብ ነበር ያነጋችው። በዚህ ሁኔታ መሞት ምን ያህል የሚያሳዝን ግፍ ነው? ከሚያፈቅሩት ሰው ጋር አንድ ሊሊት እንኳ አትፍትፍ ብሎ ለማደር ሳይታደሉ፣ ወልዶ ለማሳደግ ሳይበቁ፣ የሚያዝዙበት ቤት ሳያደራጁ፣ ወግ ማዕረግ ሳያደርሱ፣ ጠብ በማይል ስራ፣ ሊላው በሚወደስበት ሰራ እንደተዋከቡ አፈር ሊሉን... ...ለማትነት ሊቀሙ...?

የለም፣ የለም፣ የለም። አይደረግም። አይሞከርም። እንዲህ በማፍስ አይከጀልም።

ትዝት ሲያነሳ ሲጥላት አድሮ ንጋት ላይ አንቅልፍ አሸለባት። የነቃችው ከጧቱ አራት ሰዓት ከሃያ ላይ ነበር።

ሊሊቱ በሰላም ነጭቶ ቱርፊን ከጥፊ ድረስ አስመጥታ የጧቱን ጋዜጣ እያነበበች መመጣብ በመቻሏ ሽእቦራሪያ ፍርሃቷ በመጠኑም ቢሆን ተለል አለላት። ሞት ፈቅ ብሎ ታያት። እንዲያም ሆኖ ግን የሚተጥለው ርምጃዋ ምን መሆን እንዳለበት መርጣ ያውን መውም መወሰን አቃታት። ለማንኛውም ግን ቀኑን መሉ ልታሰብበት ወሰነች። ስጊዜው ግን ወላጆቿ ምናልባት በልጃቸው አፓርታማ ስለተፈፀመው ወንጀል እንብበው ከሆነ እንዳያስቡ ደውላ ልታረጋጋቸው አሰበች። ለአባቷ ሞሽንግተን፣ ለእናቷ ኢቫንስተን ደውላ ደህንነቷን ነገረቻቸው። ተጥላም ለኒክ ራምሲ ደወለች። ደህንነቷን ለማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ምን እንደሚዘጋት ምክር ለመጠየቅ። ኒክ ግን ጧት ሶስት ሰዓት ላይ ወደ ለንደን የሚነዝ እንደመሆኑ ባራ ስራ እንደማይገባ ተነገራት። መልእክት ልትተውለት አልፈለገችም።

እናም ይህን ፈታኝ ወቅት ያለእንዱት ርዳታ ያለማንም እገዛ ብቻዋን

ልትጋፈጠው እንደተገደደች ተረዳች።

እዚህ ድረስ አጅበው ካመጧት ሁለት ፖሊሶች በስተቀር የቪክቶሪያን አድራሻ ማንም አያውቅም። ቪክቶሪያ ትናንት ማታ መኖሪያዋን ለቃ ወደዚህ በመጣችበት ወቅት ከፖሊሶች ጋር የተነጋገረችውን አስታወሰች። ዛሬ አጋርታ-ማዋን የሚጠብቀው ፍላሽር-ቲ የተባለው ተረኛ የፖሊስ መኮንን የሚደወሉላትን ስልኮች እያነሳ ስትደውልለትም የተቀበላቸውን መልእክቶች ይነግራታል።

በዚህም መሰረት ከትናንት ማታ ወዲህ የተደወሉ ስልኮች እንዳሉ ለማወቅ ወደ አጋር-ተማዋ ደወለች።

አራት መልዕክቶች እንዳሏት ፍላሽር-ቲ ገለፀላት። ሶስቱ ከመገናኛ ብዙሃን ነበሩ። ሁለቱ ከቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ አንድ ከሬዲዮ። ቪክቶሪያ ሶስቱንም መልእክቶች ቀዳዶ እንዲጥላቸው ለፍላሽር-ቲ ነገረችው።

አራተኛው መልእክት ከወይዘሮ ሃና አርምስቱድ ነበር።

ሃና አርምስቱድ ልታገኛት ትፈልጋለች!

ቪክቶሪያ ከሊሊቱ ወዲህ ቀርቶ የነበረው የፍርሃት ሙጣጭ እንደተን ሲበን ተሰማት። ልቧ በልበ-ሙሉነት ተንጠረበበ። በዚያ አፍታ አንድ ቶራጥ ውሳኔ ላይ ደረሰች። ከንግዲህ መሮጥ፣ መሸሽ የለም። ቆሞ መጋፈጥ ብቻ። መጣል ወይም መውደት። ፊት ለፊት መጋፈጥ!

ለሃና አርምስቱድ ደወለች።

ለስልኩ መልስ የሚሰጣት ድምጽ ደካማ ይሆናል ብላ ጠብቃ ነበር። ድምፁ ግን የጠራ ነበር።

‹‹አቤት፣ ማን ልበል?››

‹‹ወይዘሮ አርምስቱድ? ቪክቶሪያ ዊስተን ነኝ። መልእክትዎ ደርሶኛል።››

‹‹በጣም ጥሩ፣ ላገኝሽ እፈልጋለሁ።››

«ብቀጥታ ልምጣ?»

«የለም፣ የለም ወይዘሪት ዊስተን። ባለቤቱ እንዲያይሽ እንደማትፈልጊ ከተውሽልኝ መልእክት አንብቤአለሁ። እሱ ደግሞ አሁን ላንድ ጊዜ በት መጥቶ አንዳንድ እቃዎችን ይዞ አዳራን ከከተማ ውጭ እንደሚያሳልፍ መልእክት ደርሶኛል። ስለዚህ መጥቶ እስኪሄድ መታገስ አለብን። ማለት እስከ ከሰዓት በኋላ።»

«እጠብቃለሁ፣ ወይዘሮ አርምስቱድ።»

«እስክደውልልሽ ጠብቂ። ለመሆኑ የት ነው የምደውልልሽ?»

«ሮያልተን ሆቴል ነው ያለሁት። ስሚም ባርባራ ጋሪ ነው።»

«አሃ» ካለች በኋላ ሃና፣ ሰጥቲት ጊዜ ወጥታ ሰፈነ።

«ፈርተሽ ነው ወይዘሪት ዊስተን? ባለቤቱ እንዳያገድልሽ ሰግተሻል?»

«መቼስ. . . .»

«እም፣ አይፈረድብሽም» አለች ሃና ኮስተር ብላ፣ «በይ እስክደውልልሽ ጠብቂ።»

* * *

ሃና አርምስቱድ ለቪክቶሪያ በደወለችበት ወቅት ጊዜው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር።

«አሁን ልትመጭ ትችያለሽ» አለች ሃና። ቪክቶሪያ በታክሲ ተሳፍራ ወደ አለቃዋ ባለቤት መኖሪያ ስትሄድ የጉጉትና የምኞት ሃሳብ ተመሰቃቅሎባት ነበር። ወደ መኖሪያው ስትደርስ ነበር የጉጉትና የምኞት ሃሳብ በጥርጣሬ ተተክቶ የረበሻት። ምናልባት ሃና አርምስቱድ ከባለቤቷ ጋር ተመሳጥራ እያን ለማማናትና ጉድ ለማድረስ የወጠነችው ደባ ይኖር ይሆን? አይደረግም አይባልም፣ ግን አይመስልም፣ አለች ሰራሏ። እናም ማመንታቱን ትታ የበሩን ደወል በድፍረት ተጫነችው።

የመግቢያው በር ወዲያውኑ ተከፈተ። የከፈተችው የሊሊት ልብስ

የለበሰች በተሽከርካሪ ወንበር የተቀመጠች ጠና ያለች ሴት ነበረች። ‹‹ሃና አርምስቱድ ነኝ›› አለች ሴትየዋ። ቪክቶሪያ ሴትየዋን አስተዋለቻት። ሃና ሰውነቷ ከእድሜ ጋር በበሽታው መሸሽ ብሎ ለቷል። ጠቅላላ ገጽታዋም ድቅት ያለ ነው። ይሁንና ብሩህ ከሆኑት አይኖቿ ላይ እንዳች ንቃት፣ እንዳች ኃይል ይነበባል፣ ከናፍሯም ግና ብዙ ሊንቀሳቀስ የሚችል መሆኑ ያስታውቃል።

‹‹አንቺ አይደለሽም ቪክቶሪያ ዊስተን?›› አለች ሃና።

ቪክቶሪያ ዊስተን በአምንታ ራሷን ነቀነቀች።

‹‹አትጨነቂ›› አለች ሃና። ‹‹ማንም የለም። ብቻችንን ነን። ግዚ።››

ቪክቶሪያ ባትወድም አማራጭ አልነበራትምና ተሽከርካሪውን ወንበር እየተከተለች ወደሳሎን አመራች።

‹‹ከአንድ ሰዓት በፊት መጥቶ ሂዷል›› አለች ሃና ቪክቶሪያን ወደኋላ ሽቅብ እየተመለከተቻት። ‹‹ሌቱን ሙሉ ብቻችንን ልንነጋገር እንችላለን።››

‹‹አመሰግናለሁ፣ ወይዘሮ አርምስቱድ።››

‹‹ሃና ብለሽ ጥሪኝ። እኔም ቪክቶሪያ አልሻለሁ። አየሽ፣ ሙያዬታችን የግል እስከሆነ ድረስ በመጀመሪያ ስማችን ብንጠራራ ይበልጥ ተግባቡቦን እናመሻለን።›› እንዲህ እየተናገረች ሃና እንግዳዋን ከግሞቲያው አጠገብ ባለ ተለል ያለ ወንበር ላይ እንድትቀመጥ በእጇ ጠቆመቻት። ቪክቶሪያ ስትቀመጥም ሃና ተሽከርካሪ ወንበሩን ነድታ ከፊት ለፊቷ ሆነች።

‹‹መልካም›› አለች ሃና፣ ‹‹ጊዜ አናጥፋ። ለምን ነበር የፈለግሽኝ? በመልእክትሽ እጅግ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ያልሽውስ ምን ነበር? መቼም ያለጥርጥር ባለቤቱን የሚመለከት ነው።››

‹‹አዎ፣ ሚስተር ኤድዋርድን የሚመለከት ነው።››

‹‹ስጋት እንዳያድርብሽ፣ ከልብሽ ግልጽ ሆነሽ እንድታነጋግሪኝ እንድ ነገር ልንገርሽ›› አለች ሃና፣ ‹‹እኔ ባሌን እንደባል የምቆጥር ሴት እንዳልመስልሽ። በርግጥ ከጅምሩ እንስቶ ማለቱ አይደለም። የጠላሁት

ከትርብ አመታት ወዲህ ነው። ከትርብ ሳምንታት ወዲህ ግን ከጥላቻ አልፈን አጥፊና ጠፊ እየሆነን መጥተናል። አንዳንድ ጊዜ እንደአውራ አስኪሰራው ድረስ ከሰው ጋር አብሮ የመኖርን ነገር እርግፍ አድርጎ ትቶታል። በግልጽ ልንገርሽና ምግባሩ ሁሉ የእብድ ሰው ሆኗል። አሁን ባጠቃላይ ሳንጠራራ እማንላቀትበት ደረጃ ላይ የደረስን ባልና ሚስት ነን። ይህንን አውቀሽ ትንጣት ላትሰጊ ሚስጥርሽን ግለጭልኝ።››

ቪክቶሪያ በዚች ጨዋና ደግ እመቤት አነጋገር ልቧ ተነካ። ‹‹ኧረ ምንም አልሰጋሁ፣ ሃና።››

‹‹እንግዲያውስ ቱጥይ፣ ምን እግር ጣለሽ?››

‹‹ባለቤትም አንድ አለም አቀፍ የሽብር ፊጠራ በድን እንደሚያንቀሳቅሰ ስለጠረጠርኩ. . . .››

ከሃና ፊት ምንም እንግዳ ነገር አልታየም። ከቧ የሚጠበት ጥያቄ ብቻ ጠየቀች። ‹‹በታይም መጽሔት ሽፋን ላይ ምስሉ የወጣ፣ ምንተስኖት ተብሎ የተሰየመ በዘመናችን ከታወቁ አሳታሚዎች ሁሉ ይበልጥ የተደነቀና በእርአያነቱ የመናገሪያ ርእስ የሆነ፣ የዘንድሮውን የኖቤል ሽልማት የሚነጥቀው የለም የሚሉት ታላቅ ሰው፣ የሽብርተኞች መሪ?››

‹‹ነገሩ እንደማይታመን ይገባኛል. . .›› ከማለድ ቪክቶሪያን ሃና አቋረጠቻት።

‹‹የለም፣ የለም፣ ቱጥይ፣ እኔ የፈለግሁት እዚህ መደምደሚያ ላይ እንድትደርሽ ያደረገሽ ጭብጥ ምን እንደሆነ ማወቅ ነው። ማስረጃ አለሽ?››

‹‹ሁኔታዎችን ከመገምገም የመነጨ›› አለች ቪክቶሪያ ፊጠን ብላ፣ ‹‹ግን በማይካድ ሁኔታ የሚያሳምን።››

‹‹ለመስማት ቸኩያለሁ፣›› አለች ሃና።

‹‹እኔም ከልቡ አዳምጦ ከጎኔ ለሚቆም የተሰማኝን ለማስረዳት ቸኩያለሁ።›› ቪክቶሪያ የግላ ራሷ አሰሪ የሆነውን አሳታሚ በገሙቱት ርካሽ ተግባር እንድትጠራጥረው ያደረጓትን ነገሮችና የወሰደቻቸውን

ግምግምት በሙሉ ዘርግፋ ለተጠርጣሪው ባለቤት ተረከቻላት። የኤድዋርድ ትኩስ ዜና አቀራረብ በጋዜጣውና በቴሌቪሽን ማዘጋጃዎቹ እንዴት የሌሎች ቁንሮ እንዳደረጉት፣ ነገር ግን ዜናዎቹ ሁልጊዜም የሚቀርቡት በምድር ላይ በሌለ ማርክ ብራድሾ በተባለ ሰው መሆኑን፣ እያንዳንዱ ዜና በተፈፀመበት ቅጽበት እሷ ወይም ጓደኛዋ ኒክ ራምሲ በቦታው እንደነበሩ፣ ባንድ ወቅት የኤድዋርድ መረጃ አቀባይ የሆነ ጉስ ፖጋኖ የተባለ ሰው በጓላ ጠለፋ በተካሄደበት አካባቢ አውሮፖ ውስጥ አይታው ሾልኮ ውስጥ ገብቶ እንደተሰወራት፣ መገኛብ ላይ ግን ጀምስ ፈርግሰን በተባለ የሽፋን ስም መመዝገቡን፣ ከጊዜ በኋላ ፖሪስ ውስጥ በዚሁ ስም ከአንድ ፕሮፌሰር የሎርድስ ከተማን ካርታ እንደወሰደና ወዲያውኑ በዚሁ ከተማ ጳጳሱን ለመጥለፍ ሙከራ እንደተደረገ ዘረዘረችላት። ቨክቶሪያ ትረካዋን በዝርዝር ማስረዳቷንና ለአለቆቿ ሪፖርት ማቅረቧን፣ የተሰጣት ምላሽ ግን ሁኔታውን እንዳትከታተል ሆነ ተብሎ ወደ ኒውዮርክ እንድትመለስ የተረበ ትእዛዝ መሆኑን አብራራች።

ነገሯን ስትጨርስ ቨክቶሪያ የሃና ምላሽ ምን እንደሚሆን አቆብቁባ ትጠብቅ ጀመር።

ሃና ትረካውን ያዳመጠችው ለአፍታ እንኳ ሳታቋርጥ በከፍተኛ ተመስጦ ነበር። ቨክቶሪያ ነገሩን ስትጨርስ እንኳ ወዲያውኑ ከተመስጦዋ አልተመለሰችም።

በመጨረሻው ከሽክሽክታ ትንሽ ከፍ ባለ ድምጽ የተሰማትን ትናገር ጀመር። «አዎ» አለችና በረጅሙ ተነፈሰች። «ከትርብ ጊዜ ወዲህ ከአንድም ሁለቱ እኔም እንዳንቺው ሳልጠረጥር አልቀረሁም። ለኤድዋርድ ዝነኝነትና ለሚያማበሰብሰው የተትረፈረፈ ገንዘብ ሌላ ምንም ማብራሪያ ሊቀርብለት አይችልም። . . »

«ዜናዎችን ራሱ ይሰራል ከሚለው መደምደሚያ በስተቀር» ጠየቀች ቨክቶሪያ ተበል አድርጋ።

«ዜና ፈጠራ. . . ሥ. . . ሥ» አለች ሃና ከመጠን ያለፈ ተገርማ። «ግን ይገርምሻል ሃሳቡ በሮራሽ አልዋጥልሽ ብሎኝ ከአእምሮዬ አውጥቼው

ነበር። ትናንት ነው እንደገና ያመንኩት።››

‹‹እንዴት ትናንት?›› ቪክቶሪያ ጆሮዋን አቆመች።

‹‹ትናንት ጧት ያለወትሮው ቁርሱን ራሱ ሊሰራ ተጭነጭ ያለ ጀመር። ያልተለመደ በመሆኑ መለማመጥ ይሁን ወይም ለኔ ማሰብ ነገሩ አልገባኝም ነበር። ምግቡን አትርቦልኝ ቢሮ ሄደ፣ እኔም ቁርሱን በላሁ። ብዙም ሳልቆይ ግን የሰራ አካላቱ ሊከዳኝ ተሰማኝ። እንደምንም ወደ ሰልኩ ቀርቤ ሃኪሜን መጥራት ባልችል ኖሮ ወዲያውኑ ራሴን እስት ነበር፣ ግንም ሳይደርስልኝም ሕይወቱ አልፋ ነበር።›› ንግግሯን ገታች ሃና። ‹‹የለም ቪክቶሪያ፣ የተመረዝኩት በሻንታ አልነበረም። ባለማወቅም ሆነ በማወቅ ምግቤ ላይ መርዝ ተጨምሮ ነበር። ደሞ በማወቅ ነበር የተጨመረው. . . በገዛ ባለቤቴ።››

ቪክቶሪያ የኤድዋርድን ሰብእና አስቀድማ የተማነዘቸች ሰው ባትሆን ኖሮ የሃናን አነጋገር ለማመን በተቸገረች ነበር።

‹‹ግን ለምን እንዲህ ያለ ተንኮል አሰቡብሽ? በርግጥ ግንኙነታችሁን አላውቅም. . .››

‹‹ትናንቱን ማታ ባንድ ነገር ተነታርከን ነበር። ለረጅም ጊዜ ቤት ሳይመጣ ያመሸው ከኪም ነሰቢት ጋር ውሽምነት በመጀመሩ መሆኑን እንዳወቅሁበት ነግሬው ነበር።››

ቪክቶሪያ የኪም ነሰቢት ስም በሃና ከንፈር ሲጠራ በመስማቷ ከመጠን ያለፈ ተገረመች። ‹‹ግን የሁለቱን ግንኙነት እንዴት ደረሱበት?›› ብላ ከመጠየቅ ሌላ የምትናገረው አልነበራትም።

‹‹የግል ሰላይ ቀጥሮ ኤድዋርድን ለብዙ ሳምንታት እንዲከታተለው አድርጌ ነበር።››

‹‹ታዲያ በሰላይ ሲከታተሉ እንደነበሩ ለባለቤትም ነግሩዋቸው?››

‹‹በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ እንዲገባው አደረግሁ።›› ቪክቶሪያ ነገሩን ለአጭር አሰላለሳ የምትናገረውን ታል አስቀድማ መረመረች። ‹‹ሃና፣ ሰውየው ሊገድሉም ያሰቡት ሌላ ሴት መያዛቸውን ስላወቁባቸው አይደለም።

በህይወትም የመጡት የሚሰጥር እንትስታሲያቸውን በመከታተልዎ ነው።››

‹‹አልገባኝም›› አለች ሃና።

‹‹በሚሰጥር ተከታተሉዋቸው ማለት በህይወታቸው የተደበቁ እንትስታሲአቸውን አወቁባቸው ማለት ነው። በሚሰጥር የሚገናኙዋቸውን ሰዎች—ወንጀለኞችና ሽብርተኞች ሊሆኑ ይችላሉ—አዩባቸው ማለት ነው። አጠቃላይ ተግባራቸውን ደረሱባቸው ማለት ነው። ስለዚህ ከመጨረሻው ሃት ላይ ከመድረሰዎ በፊት ማቆም ነበረባቸው።››

‹‹ሃትን የያዘች መንገድ ትተዋናለች እንጅ አትዘጋም›› አለች ሃና በቀስታ፣ ‹‹ይህን ሁሉ አሳሰብኩም ነበር። ያም ሆነ ይህ እኔን በመርዝ ለመግደል ሞክሮ እንደነበር ግን አይጠረጠርም። ታዲያ ምን ልሁን? ማሰረጃ ማቅረብ እስካልቻልኩ ድረስ ምን ላደርገው እችላለሁ? አሁን ሰው ምን እንደሚደርገው አሳውቅም ነበር። ዛሬ ቧት በኢንተርኮሜ የተደረገውን፣ የኪም ነስቢትን መገደል ከጋዜጣ ሳነብ አንቺ ደግሞ መጀመሪያ የተውሽልኝ መልእክትና በኋላም እንቺን ፊሽሽን ከፖሊሶች ጋር በቁሊቪኒን ላይሽ ብዙ የተወሳሰበ ነገር ተገናዘብኝ፣ ከግድያው ጀርባ የኤድዋርድ እጅ እንዳለበት በጽኑ አመንኩ። በኢንተርኮሜ ነስቢትን ያስገኛት አንድና አንድ የጋራ ተጠሪ ኤድዋርድ አርምስቴድ ነው። ኪም ቅምጡ ነበረች። አንቺ ደግሞ እኔን የጣዛ ባለቤቱን ለማንገር እስከመሞከር እንትስታሲውን የምትጠራጠሪ ሰራተኛ ነሽ። ግድያውን ያለመው በማንኛችሁ ላይ እንደሁ ወይም ለመግደል የፈለገበትን ምክንያት አላውቅም።››

‹‹እኔም ሙሉ በሙሉ መገመት አያዳግተኝል›› አለች ቪክቶሪያ። ‹‹ነገር ግን ለመግደል የፈለጉበትን ምክንያት ተረድቻለሁ። በሆነ መንገድ ባለቤትም ድርጊታቸውን እንደተጠራጠርኩና ከኪም ነስቢት ማሰረጃ እንደምፈልግ ተረድተዋል። ስለዚህ እኔን ከመንገዳቸው ለማስወገድ ትጥረኛ ላኩብኝ፣ ትጥረኛው ግን ኪምን ገደለ። ምናልባት እኔም ማብሰያ ክፍል መኖሬ ቢታወቅ ኖሮ እሳየ ከኪም ነስቢት አይለይም ነበር።››

‹‹ያም ሆነ ይሁ›› አለች ሃና፣ ‹‹መርዝ ከበላሁ በኋላ የተውሽልኝ ማስታወሻ በኢንተርኮሜ ከደረሰው አሳቻኝ ነገር ጋር ተገጣጠመ። ለዚህም

ነበር በእርግጥ እንደገፍሽው በጣም አሳስቢ ጉዳይ ሳይኖርሽ እንደማይተር ያመንኩት። በዚያ ላይ ሰውየው የመጣው በእም ህይወት ላይ ስለነበር ነፍሴን ለማቆየት ስል ምናልባት አንቺ እንድ ጠቃሚ ጉዳይ ትነግሪኛለሽ ብየ ነበር።››

‹‹ታዲያ አሁን ሚሰጥሩ ተገለጠልዎ አይደል?››

‹‹ተገለጠልኝ።›› ሃና በአምንታ ራሷን ዝዝግታ ከፍ-ዝት አደረገች። ‹‹ከንግዲህ አንለተውም። ቪክቶሪያ ደግሚ ልንገርሽ። ሰውየው የከፋ ውሻ ሆኗል። በባህርዩ የከፋ ውሻ፣ በማዕረጉ የወትሩ የከፋ ውሾች፣ የአደገኛ ወንበዴዎች መሪ።››

‹‹ትክክል ብለዋል››

‹‹በዚህ ምን ያህል እርግጠኛ ነሽ?››

‹‹መቶ በመቶ።››

ሃና እንግዳዋን አተኩራ ተመለከተቻት። ‹‹ግን ማረጋገጫው የለሽም።››

‹‹እም፣ የለኝም። የመጨረሻ ተስፋየም እርስዎ ይረዱኛል የሚል ነበር።››

ሃና ቸኩላ አልተናገረችም። ስለእንድ ነገር የምታስበውን ሃሳብ ለመቋጨት ታስላስል ይመስል ቀና ብላ አይኗን ጣራው ላይ አንጓለሰችው። በመጨረሻውም ተናገረች። ‹‹ልረዳሽ እችላለሁ።›› አነጋገሯ አዋጅ የመልፈፍ ያህል ነበር። ‹‹ጥርጣሬሽ እውነት መሆኑን ወይም ባዶ ጥርጣሬ መሆኑን እንድታረጋግጭ ልረዳሽ እችላለሁ።››

‹‹እውነት?›› ቪክቶሪያ ከተቀመጥሽበት እንዴት ተነሳሽ ቢሏት መመለስ አትችልም። ኤሊክትሪክ የያዛት ይመስል ተስፈንጥራ ብድግ አለች።

ሃና እጅዋን አንስታ ከሳሎኑ ወደሚያስወጣው ኮሪደር እያመለከተች፣ ‹‹ተከተይኝ›› አለችና ወንበሩን እያሽከረከረች ወደ ኮሪደሩ ሄደች። ቪክቶሪያ ተከተለቻት።

በመጀመሪያው መኝታ ቤት በር ላይ ሲደርሱ ሃና ቪክቶሪያን

እንድትቆም ምልክት ሰጥታ ወደ ውስጥ ገባች። በዚህ መኝታ ቤት ከአልጋው ራስጊ የቆመ ረጅም የብረት ዘንግ ነበር። ሃና ዘንጉን እንደ ምርኩዝ በመገልገል ከተሸከርካሪው ወንበር ብድግ ብላ በእግሯ መቆም ቻለች። ከዚያ ወደ ቁም ሳጥኑ አምርታ ከመስታወቱ በስተግራ ከታች በኩል የሚገኘ አንድ መሳቢያ ከፈተች። ከመሳቢያው ውስጥ አንድ በተላሉ የሚገኝ የማይመሰል የተደበቀ ነገር ስትፈልግ ቆይታ ወዲያው የምትፈልገውን በማግኘቷ መሆን አለበት በእርጋታ ፈገግ አለች። ሃና ያገኘችው ነገር ምን እንደሆነ ቪክቶሪያ ባታውቅም ሃና ከመሳቢያው ያወጣችው ነገር አንድ ሳይሆን ሁለት መሆኑን ሴትዮዋ እቃዎቹን ወደ ተሟያ ኪስ ስትከት ገምታለች።

ሃና፣ ቪክቶሪያ ወደ ቆመችበት ቦታ ተመልሳ ከሄደች በኋላ፣ «ነይ ከኔ ጋር» አለቻት፣ «ማሰረጃ ማግኘት ከተቻለ የምናግኝበትን ብቸኛ ስፍራ ላሳይሽ ነው።»

ዘንጓን እንደተመረኮዘች ሃና በጉጉት የምትጽምጠውን እንግዳዋን አስከትላ ወደ ኮሪደሩ አመራች። ሁለተኛውን የመኝታ ክፍል ካለፉ በኋላ አንድ መዝጊያው ከሌሎች ክፍሎች መዝጊያዎች ሁሉ የተለየ ክፍል በር ላይ ሲደርሱ ሃና ቆመች። «የውሸው የግል ጥናት ክፍል» አለች ሃና፣ «እዚህ ክፍል ውስጥ እንድገባ አይፈቀድልኝም። እንድ ጊዜ ብቻ ያለ ፍቃድ ሳያየኝ ገብቼ ነበር። አሁን ሁለተኛየ መሆኑ ነው።» ይህን ተናግራ እጅጉን ወደ ኪዷ ሰዓ ከመሳቢያው ካወጣቻቸው ሁለት ነገሮች አንደኛውን አወጣች። «እዚህ ክፍል የሚያስገባ ቁልፍ ያለው እሱ ብቻ ይመስለኛል፤ ኤድዋርድ። ምትክ ቁልፍ እንዳይሰራ ከልክሎ ነበር። እኔ ግን በድብቅ ይህንን ሁለተኛ ቁልፍ አሰራለሁ።» ከዚህቸው ንግግሯ ጋር ደግሞ በሩን ትከፍት ጀመር። «ይህን ቁልፍ ከሱ ደብቁ ያሰራሁት በዚያ ወቅት እጠረጥረው ስለነበር ሳይሆን ለሱ ስለማስብ ነበር። እዚህ ክፍል ብቻውን ከውስጥ ቆልፎ ለብዙ ሰዓቶች ይሰራ ስለነበር ለጤንነቱ አስብ ጀመር። አንድ ቀን ድንገት ልቡን እንኳ ቢያመው በሩን ከፍቶ ለእርዳታ ሊደርስለት የሚችል አይኖርም በማለት በሚስጥር አናጢ አስጠርቼ ይህን ቁልፍ አሰራሁ። እም፣ ይህ ቁልፍ የተሰራው ለድንገቶች ጉዳይ ነበር። ያሁኑ የኛ ጉዳይ ደግሞ ድንገተኛ

ነው።››

ቁልፉን በመክፈቻው ቦታ አስገብታ ባለ ኃይሏ ዞር ስታደርገው በሩ ያለምንም ድምፅ ወዲ ውስጥ ተከፈተ።

‹‹ይህ ክፍል ሁልጊዜም የኤድዋርድ የግል ጥናት ክፍል ጭርሶ?›› ጠየቀች ቪክቶሪያ።

‹‹አዎ፣ ግን ሁሌም ክፍቱን ነበር›› አለች ሃና። ‹‹የስፓኙ ንጉስ ሳን ሴባስቲያን ውስጥ ከመጠለፋቸው ጥቂት ላምንታት ተደም ብሎ ኤድዋርድ ልዩ ቁልፉን አሰርቶ ማንም እንዳይገባ ከመከልከሉ በፊት ሁልጊዜም ተበርግዶ ነበር የሚውለው።››

ሁለቱ ሴቶች እርስ በርሳቸው በእትከሪት ከተያዩ በኋላ ወዲ ውስጥ ገቡ።

ቪክቶሪያ ክፍሉ ውስጥ እንደገባች ዙሪያዋን ትገላመጥ ጀመር። ደብዘዝ ባለ ውሃ ሰማያዊ ቀለም የተቀባውን ክፍል በተለይ ልዩ የሚያደርገው ከማሞቂያው ላይ የሚታየው የናፖሊዮን ቦናፓርት ምስል ነው። በተረፈ ክፍሉ ወዲ ተጠኚው የግል መታጠቢያ ቤት የሚያስገባ በር ያለው ሲሆን በእንደኛው ማዕዘኑ በኩል የቪክቶሪያዊ ቤተ መፃህፍት ጠረጴዛና ከጎኑ በኤሌክትሪክ የሚሰራ የታይፕ ፅሀፈት መሣሪያ አለው።

ሃና በታይፑና በጠረጴዛው መካከል ወዳለው ደረት ወንበር አመለከተች። ‹‹ከሞላ ጎደል ሁል ጊዜ ማታ እዚህ ክፍል ይገባና እዚያ ወንበር ላይ ተቀምጦ ታይፕ ያደርጋል›› አለች ሃና፣ ‹‹በርግጥ በእይኔ አይቼው አላውቅም፣ ግን እንደነገርኩሽ እንደሚያደርግ አውቃለሁ፣ በተለይ ጋዜጣውን ከአባቱ ከወረሰ በኋላ ለብዙ ላምንታት።››

ቪክቶሪያ በአድናቆት ብዛት ሊላ አለም ውስጥ ያለች መስሏት አይኖቿ ታይፑ ላይ እንደተተከሉ ቀሩ።

‹‹የሽብር ፈጠራዎቹን ታሪኮች ሲፅፉ የነበሩ ይመስለዎታል?›› ጠየቀች፣ እንደተገረመች።

‹‹ሃሳብሽ ገብቶኛል። ማወቅ የፈለግሽው የባለቤቱ የብዕር ስም ማረክ

ብራድሾ መሆኑን አይደለም?›› አለች ሃና፣ ‹‹አበቂ እናራጋግጥ፡፡ ከዚያም ወደ አንድ ጎን ዞር ብላ ከተቃራኒ አቅጣጫ ባለው ግድግዳ በኩል ከአንድ መንበር በስተጀርባ ወደሚገኝ ነገር በእጅዋ አመለከተች፡፡ ‹‹ታያለሽ?››

ቪክቶሪያ ከፍሉ በገባችበት ወቅት ዙሪያዋን ብትታዘብም እስካሁን ያላየችው መጠኑ መካከለኛ የሆነ የአንድ ታዳጊ ወጣት ፎቶ በመስታወት ተቀምጦ ተመለከተች፡፡ ይህ ያማረ የወታደር ዩኒፎርም የለበሰ የአስር ወይም የአስራ አንድ አመት ልጅ ምስል ትክክለኛ ትጅ ይመስላል፡፡

‹‹የኢድዋርድ የልጅነት ፎቶ ነው፡፡›› አብራራች ሃና፣ ‹‹ቦርሳው ያለው ከፎቶው ጀርባ ግድግዳው ጥግ ነው፡፡››

ቪክቶሪያ ሃናን በጥያቄ አስተያየት ተመለከተቻት፡፡ ‹‹ቦርሳው?›› ስትል ጠየቀች፡፡

‹‹አዎ፣ ማሰረጃው›› አለች ሃና፡፡ ‹‹ማስረጃ ካለ በርግጥ የምናገኘው እዚያ ቦርሳ ውስጥ ይሆናል፡፡›› ከንግግሯ ጋር ሃና እጅዋን ወደ ተጠቂሷ ኪስ ሰዳ ቁራጭ ወረቀት አወጣች፡፡ ‹‹ቦርሳው የሚከፈተው በቁጥር ነው፡፡ ተመሳሳይ ቁልፍ ላሰራ ከአናጢ ጋር በገባሁበት ወቅት ቁጥሩን አግኝቼ በሌላ ወረቀት ገልብጬው ነበር የወጣሁት፡፡ እዚህ መንበር ላይ ቁጢና ፎቶውን ስታነሽው ቦርሳውን ታገኛለሽ፡፡ ማሰረጃ ካለ ቦርሳው ውስጥ ማግኘት አለብን፡፡ ለዚህ ነው ልረዳሽ እችላለሁ ያልኩሽ፡፡ መልካም እድል ሳይሆን መልካም እውነት እንዲገጥምሽ እመኝልሻለሁ፡፡››

ቪክቶሪያ ለአፍታ በሃሳብ ተመሰጠች፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለች ያነበበችው አንድ ነገር ከዘመናት በኋላ ዛሬ ትውስ አላት፡፡ አንዲት የኒው ኢንግላንድ ትምህርት ቤት መምህርት ሽክስፒር የታወቀባቸውን ተውኔቶቹን ራሱ አልፃፋቸውም የሚል ንድፍ ሃሳብ ኮስተር ብላ ታራምድ ነበር፡፡ ንድፈ ሃሳቧ ማረጋገጫ ስትጠየቅ ማስረጃው በስትራፎርዱ ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው የሼክስፒር መካነ-መቃብር እንደሚገኝ ወጥራ ትወተውታለች፡፡ ይባስ ብላ የሼክስፒራን መካነ-መቃብር ከፍታ ማስረጃዎቹን ለማውጣት ለብዙ አመታት ያለመታከት ትጠይቃለች፡፡ በመጨረሻው መቃብሩን እንድትከፍት ፈቃድ ይሰጣታል፡፡ መምህርት ግን ታመነታ

ጀመር። ‹‹አእምሮዋ በጥርጣሬ ተሞላ›› ብላለች ከጊዜ በኋላ ሃውትሮን የተባለች ጓደኛዋ ስለዚ ስትፅፍ፣ ‹‹የመታብሩን ድንጋይ ስታነሳ ከውስጥ ምንም ማስረጃ ባታገኝ የምትደነግጠው ድንጋጤ አስቀድሞ ልቧን መታው።›› በዚህም መሰረት በብዙ ድካም ያገኘችውን ፈትድ በራሷ ፍትድ ሽራ መታብሩን ላለመክፈት ወሰነችና አረፈችው።

በእኒያ የተመሰጠ ሴትንዶች ቪክቶሪያ ቦርሳዋን ስትከፍት ምንም ማስረጃ ባታገኝ የምትደነግጠው ድንጋጤ አስቀድሞ ልቧን መታው። ማስረጃው ከቦርሳው ካልተገኘ እብዱ እሷ እንጂ ሚስተር ኤድዋርድ እንዳልሆነ ሲታሰባት ከወዲሁ በመንፈስ ፅንቶት ልታብድ ምንም አልቀራትም።

‹‹እኔ. . . . እኔ እንጀልኝ›› አለች ቪክቶሪያ ዝግ ብላ።

‹‹የመጨረሻው እድልሽ ይኸው ነው›› አለች ሃና።

‹‹ሁለታችንም እውነቱ ላይ መድረስ ይገባናል።››

ቪክቶሪያ በትካዜ አንገቷን አቀረቀረች። ወንበሩን እንስታ ከኤድዋርድ የልጅነት ፎቶ በታች ካደረገች በኋላ ወንበሩ ላይ ቆመች። ፎቶውን ከተንጠለጠለበት ለማንሳት ብዙም አልተቸገረችም።

ሰማያዊ ቦርሳ ታየ።

‹‹ይኸው›› አለች ቪክቶሪያ ቦርሳውን ይዛ ከወንበሩ ከወረደች በኋላ።

ሃና ከወረቀቱ ላይ የመከፈቻውን ቁጥሮችና የአህያራቸውን አቅጣጫ ለቪክቶሪያ ትነግራት ጀመር። ቪክቶሪያ እንደተናገረችው አድርጋ ስትጪርስ የቦርሳውን ክዳን ብድግ አደረገችው። ቦርሳው ተከፈተ። እጅጉን ወደ ውስጥ አስግብታ በጣቶቿ ስትደባብስ አንድ ትልቅ ኤንቬሎፕ አገኘች። መጀመሪያ ኤንቬሎፑን ለማውጣት ፍላጎት አልነበራትም። ይሁንና ቦርሳው ውስጥ ሌላ ምንም ነገር ስላልነበር ቡናማውን ኤንቬሎፕ ቁልቁል ተመለከተችው። ቦርሳው ላይ የተፃፈ አድራሻ የለም። በእርሳስ የተፃፈ ቁጥ ብቻ ይነበባል። ቁጥ የነገው እለት ነበር።

‹‹ይኸ ብቻ?›› አለች ቪክቶሪያ ቅስሟ ተሰብሮ።

‹‹ከውስጡ ምን አለሙ?›› ሃና ነበረች።

ቨሮኒካ ኤንቬሎፑን ከፈተች። ከውስጡ ሰባት መረጃዎች ነበሩበት። መረጃዎቹ በማም ዘርዝር ባለ ርቀት በታይፕ የተጻፉ መስመሮች ይታዩባቸዋል።

ከላይ ርዕሱ ተፅፏል።

ከርዕሱ በታች ‹ማርክ ብራድሾ› የሚል ሃረግ ይነበባል።

ቨሮኒካና ሃና ሳን ለሳን ሆነው ታሪኩን ያነቡ ጀመር። የመጀመሪያውን ገፅ አንብበው እንደጨረሱ ሁለቱ ሴቶች፣ ትንፋሻቸው ቁርጥ-ቁርጥ እያለ እርስ በርሳቸው ተያዩ።

‹‹ጉድ›› አለች ቨሮኒካ ‹‹ሃና. . .››

ሃና ትንተባተባ ነበር። ‹‹እኔ አላምንም. . .››

‹‹ምነው አይታመን! . . .›› ይህ ሃረግ የተነገረው ከቨሮኒካም ሆነ ከሃና አልነበረም። ድምፁ የመጣው ከጀርባቸው ከቆመ ሶስተኛ ሰው ነበር። ሁለቱ ሴቶች የሰሙትን ባያጠራጥሩ ኖሮ ባለበት እንደ ትክል ድንጋይ ደርቀው በቀሩ። ይሁን እንጂ ጆሮአቸውን ባለማመናቸው ወደ ኋላቸው ዞር አሉ።

ኤድዋርድ አርምስቱድ ከበሩ ግባ ብሎ ቆሞ በፈገግ ፈገግታ ሲመለከታቸው ሲያዩ ምን ይበሉ?

ኤድዋርድ ፈገግታው ሳይለየው ወደ ሴቶቹ ያመራ ጀመር።

‹‹ወይዛዝርት›› አለ ኤድዋርድ ‹‹እንደለመዳችሁት ሁል ጊዜ የነገን ዜና ዛሬ ማንበብ አትችሉም።››

ኤድዋርድ ከሚሰራበት ጠረጴዛ ትይዩ ቆም ብሎ ወደ ታች እየተመለከተ የስልክ ማዘዣውን መስመር ከግድግዳው ነቀለው። ከዚያም በኩራት እየተጀነነ ከሆንኮት የተነሳ እርስ በርሳቸው ወደ ተያቀፉት ሴቶች በዝግታ መራመዱን ቀጠለ።

አጠገባቸው ሲደርስ ፈገግታው ወደ ሳቅ ከፍ ብሎ ነበር። ኩራት ላያለየው፣ ዝግታውም ሳይተር፣ በጥንቃቄ ወረቀቶቹን ከሚንዘፈዘፈው የቪክቶሪያ እጅ ተቀበለ።

«ይሀን ፊልጌ ነው ተመልሽ የመጣሁት» አለ። «ቶሎ ለመውጣት ስላደፍ ረስቼው ሄጄ ነበር።» ወረቀቶቹን በጥንቃቄ አጣጥፎ በካፖርቱ ኪስ ከከተታቸው በኋላ «አሁን ደግሞ» አለ፣ «ማነሽ አንቺ . . አም ሃና፣ ተመሳሳዩን ቁልፍ በፍታድሽ ብትሰጭኝ።»

ድንጉጥነው ከስተት የምታደርገውን አስረስቷት ስለነበር ሃና ያለምንም ተቃውሞ ቁልፉን ለባለቤቷ አሰረከበች። ኤድዋርድ ከከፍለ ለመውጣት ሠር ብሎ መራመድ ሲጀምር ግን ድንገት ወደ ሀይወት ተመለሰችና በሁለት እጇ ካፖርቱን መሳቡኩ እድርጋ በመያዝ «ኤድዋርድ፣ አትችልም!» ስትል ጮኸች።

ኤድዋርድ ካፖርቱን ከሃና እጅ ለማስለቀቅ ብዙም ኃይል አልጠየቀውም። ምንጊዜ አደረጋትና «የኔ እመቤት» አላት፣ «ተራውን ይጠብቃል እንጂ ከሞት የሚተር ማንም የለም። ያንቺና የሷ ጓደኛሽ ተራ ደርሷል።»

በመጨረሻም በሩን ዘጋባቸው። አበቃ! የሞት ደወል የመሰለ ድምፅ ተሰማ። ክፍሉ በውሎ ተዋለፈ።

15

በመጨረሻ አይነጋ የለ ነጋ።

ሃና ቀስ በቀስ እየነቃች አይኗን መግለጥ ስትችል ያለችበትን ቦታና ለምን እዚያ እንደተገኘች ለማወቅ ጥረት ሲከንዳት ማስተዋል ነበረባት። ማታ የተከሰቱት ነገሮችና በእስር ያሳለፈችው ሌሊት ትውስ አሏት። አሁን ግን ሰውነቷ በድካም ከመዛሉ የተነሳ የፍርሃትና የሞንተት ስሜት አልነበረባትም። ራሷን ወደ አንድ ጎን ዞር ስታደርግ ቪክቶሪያ ከጎኗ ቆማ ቱልቱል እንደምትመለከታት አየች፡

‹‹እ. . . እንቅልፍ ወስዶኝ ኖሯል›› አለች ሃና፣ ‹‹አንችስ?››

‹‹ለአጭር ጊዜ›› ቪክቶሪያ፣ ‹‹እዚያ ወንበር ላይ።››

ሃና ከፍሉን ታንች። ‹‹የሆነውን ሁሉ እንደገና ባጭሩ ብትነግሪኝ?›› አለች። ‹‹የዛፈው ታሪክ። ዛሬ የሚፈፀመው ታሪክ። አሁንም ለአለምሮዬ እንግዳ ነው። ዝርዝሩን ረስቼዋለሁ። የ. . . የፕሬዝዳንቱ አውሮፕላን ...››

የፕሬዝዳንቱ አውሮፕላን በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ሲበር ከሌላ አውሮፕላን ይጋጫል፡›› አለች ቪክቶሪያ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ። ‹‹ግጭቱ የፕሬዝዳንቱ አውፕላን እንዲፈነዳ ያደርገዋል። ከአደጋው የሚተርፍ ሰው አይኖርም። ፕሬዝዳንቱ፣ የፕሬስ ፀሐፊያቸው ዜማ ዊስተን፣ የኒውዮርክ ሪኮርድ የዜና ወኪል ኒክ ራምሲ፣ ሁሉም ይሞታሉ። ባጠቃላይ በአውሮፕላኑ የተሳፈሩ ከአንድ መቶ የሚበልጡ መንገደኞች በመሉ ይሞታሉ።››

‹‹ይህን የዛፈው ኤድዋርድ ነው።››

‹‹ከዚህ በፊት እንደተፈፀመ እደጋዎች ሁሉ ይህኛውም ከአንድ ሰዓት ብዙም በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይፈፀማል፡፡››

‹‹በስንት ሰዓት?›› ሃና ጠየቀች፡፡

‹‹የኤድዋርድ ፅሑፍ እንዳስታወቀው ነገሩ ከጧቱ በ3፡32 ተፈጽሟል፡፡ ማለት ይፈፀማል፡፡››

‹‹አሁን ስንት ሰዓት ነው፡ ቪክቶሪያ?››

ቪክቶሪያ መረጨባው ላይ ያለውን ሰዓት ተመለከተች፡፡

‹‹ልክ ሁለት ሰዓት ከዘር ስምንት ደቂቃ፡፡››

ሃና ሽምቅት አለች፡፡ ‹‹እንዴት? በምን መንገድ ሊፈፅመው ይችላል?››

*ፅሑፉ ዝርዝር መግለጫ አልሰጠም፡፡ ርዕሱ በርግጥ ሆን ተብሎ በተፈፀመባቸው የአውሮፕላን ግጭት ተገደለ ነው የሚል፡፡ በዕሁፉ መሠረት የተደረሰበት ዝርዝር መረጃ የለም፡፡ አደጋውን ያደረሰው አውሮፕላን አብራሪ ከቁም ነገር አልተቆጠረም እንጂ ከሳምንት በፊት እንድ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ፅፎ የነበረ፡ በሁለተኛው የአለም መርኃት ወቅት የጂፓን አየር ኃይል መኮንን የነበረ ሰው ሳያሆን እንደማይቀር ገምቷል፡፡ ይኸው አብራሪ በ1945 ፕሬዚዳንት ሩዝቬልተን ለመግደል ተመድቦ ነበር፡፡ ያኔ ተልእኮው ባለመሳካቱ የተነሳውን ክብሩን ለማደስ ሲላ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሲገድል ቆርጦ ተነስቷል፡፡ አውሮፕላኑን ሚሪላንድ ከሚገኘው እንድሬው አውሮፕላን ማረፊያ አስነስቶ ወደ ለንደን ለመብረር ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ድንበር 120 ማይል ርቀት ላይ የፕሬዝዳንቱ አውሮፕላን ጉዞ በጀመረ በአርባኛው ደቂቃ አካባቢ አግኝቶ ይገጨዋል፡፡ ፅሁፉ ከዚያ በኋላ የሚያትተው በአደጋው ያልታሰቡ ተብለው ስለሚታመንባቸው ስለ ፕሬዝዳንቱና በአውሮፕላኑ ውስጥ ስለተሳፈሩ ተንገሮች ነው፡፡ ይህን ነበር ጊዜ አግኝቼ ላነብ የቻልኩት፡፡››

ሃና በቪክቶሪያ ትረካ በመላብ ላይታወቃት ከተንጋለለችበት ቀና ብላ ተቀምጣ ነበር፡፡ ‹‹ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ነው›› አለች፡ ‹‹ይህን አደጋ ሲያስብ ኤድዋርድ በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸውን ፋኖምኖ ላይተጥር አይተርም፡፡›› በመረረ ሃዘን አንገቷን ደፋች፡፡ ‹‹ትክክል ፕሮናል ቪክቶሪያ፡

ኤድዋርድ አብዷል።››

‹‹ያሀን ሁሉ ያቀናበረው ግን በእብድ ሳይሆን በትክክለኛ፣ ግን በአረመኔ አእምሮ ነው።››

‹‹የለም አብዷል›› አለች ሃና፣ እንደገና።

ቪክቶሪያ በደከመ እግሯ ወዲያ ወዲህ ትራመድ ጀመር። ‹‹ግን እኛ ምን የምንሆን ይመስልዎታል? ኤድዋርድ ምን ያደርጉን ይሆን?››

‹‹የሚያደርግንማ በግልፅ ነግሮን አይደል የሄደው። ቂት ላይ . . . ማለትም አሁን ባስፈለገው ደቂቃ ከቅዋሬኛች እንዱ ወይም ሁለቱን ልኮ በሩን ያስከፍትና ወደ አስፈላጊው ስፍራ ያስወስደናል። ከዚያማ ያው የኪም ነሰቢትን ጽዋ ያስጎነጨናላ . . . ››

‹‹ግን ለመግደል ቢፈልጉ ኖሮ ትናንት ማታ ለምን ተውን?›› ጠየቀች ቪክቶሪያ።

ሃና ራቧን ነቀነቀች። ‹‹የለም፣ ኤድዋርድ እንዲህ የዋዛ ሰው እንዳይመስልሽ። በገዛ ቤቱ አስከራን አስተምሮ ለሚፈጽመው ወንጀል ፍንጭ በመስጠት የሚሞኝ ሰው አይደለም። እንድ ባለሞያ ልኮ ከዚያ ስፍራ ያስወጣንና የልቡን ይሰራል።››

‹‹በረንዳው ላይ ዘብ እያለ ማን ደፍሮ ይገባል?››

‹‹ምናለች በይኝ ዘቡ በስፍራው አይኖርም። ባንድ ዘዴ ከአካባቢው እንደሚያነሱት አትጠራጠሪ።››

የቪክቶሪያ አይኖች በጭንቀት ክፍሉን ግራና ቀኝ ቃኙ። ‹‹አንድ ማምለጫ መኖር አለበት ሃና።››

‹‹ማምለጫ እንደሌለ ልብሽ ያውቀዋል›› አለች ሃና ተስፋ እንደቆረጠች። ‹‹ማታ ኤድዋርድ ከመጣ በኋላ ለማምለጥ ስንፍጨረጨር ያጠፋነው ጊዜ ትዝ አይልሽም? ሌላ ሰው መጥቶ ጎትቶ እስኪያወጣን ድረስ ምንም ማምለጫ የለንም።››

ቪክቶሪያ ወዲያ ወዲህ መንጎራደዱን አቆመች። ለ. . .ለኔ እንኳን

ግድ አልነበረኝም ሃና። በእውነት ለራሴ አላሰብኩም። ያንቺ ነገር ነው ያስጨነቀኝ።››

‹‹ለኔ ሃላፊ አይግባሽ።. . .››

‹‹ከዙሴም በላይ በሚንተት ሊያሳብደኝ የደረሰው ግን በዚያ አውሮፕላን ውስጥ ያሉ ሰዎች እጣ ነው።. .አባቴ፣ ከልቤ የምወደው ፍትረሻየ፣ ፕሬዚዳንቱ እና ሌሎችም ንፁህ ሰዎች። እንዲህ ያለ፣ በሚራሽ፣ በታሪክ ተመዝግቦ አያውቅም። ሃና በፍፁም መደረግ የለበትም።››

‹‹አልነበረበትም›› አለች ሃና፣ ልቡ በተነካ ሰው ታና።

‹‹ግን እዳጋው የሚፈፀም ይመስልዎታል?››

‹‹ለምን አይፈጸም? ምን አግዶት? እኛ እንደው ራሳችንን ለማትረፍ እንኳ የምንበታ አይደለንም።›› አይኖቿን ጨፈነች። ‹‹ሁላችንም ዋጋ የለንም።››

* * *

ይህ ከሆነ ከአራት ሰዓት በፊት አንድ እጅግ አስደናቂ ነገር ተፈፅሞ ነበር። ኤድዋርድ አርምስቱድ በጉስ ፓታኖ መሪነት ሮድ ደሴት ውስጥ በኒውፖርት ጸርቻ ከሚገኝ አንድ ሳሎን ውስጥ ሲገባ ይህ ድርጊት በአለም ታሪክ ከተፈፀሙት ሁሉ በአስፈሪነቱና በሚስጥራዊነቱ ተመጻዳሪ እንደማይገኝለት ተሰምቶት ነበር።

ኤድዋርድ በሰው ሰራሽ ፀጉርና ሪዝ ራሱን ለውጦ ጥቁር መነፅር ካደረገ በኋላ በተከራየው መለስተኛ አውሮፕላን ኒውፖርት እንደደረሰ ጉስ ፓታኖ ሰሊጻ የለላት ዶጅ መኪና ይዞ ከተጠበለው በኋላ ወደዚህ ሲፈርስ ያዘመመ ቤት አመጣው። ይህን አሮጌ ቤት አንድ የካርሎስ ቡድን መኪል የተከራየው ሲሆን ለመመሸጊያነትና ለእንትስታሴያቸው በመጎሻነት ሊገለግልበት መስኗል።

ጉስ ፓታኖ ኤድዋርድን ሳሎን ውስጥ አስገብቶት ሲወጣ ‹‹ሁለም ነገር ችግር የለበትም። እዚህ አካባቢ የውጭ ሰዎች መጥተው አያውቁም።

ማዕጸን ጥቂት ራት ካሰ የግል አውሮፕላን ማረፊያ ወደ ባሃም እንዲበር እናደርጋለን። ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው፣ ጊዜው ደግሞ እየሮጠ ነው። ስለዚህ ውይይታችሁ አጠር ማለት ይኖርበታል። እሱ ግን ስራቸውን ከመቀጠላቸው በፊት ከርስም ጋር የግድ መነጋገር እንዳለበት አምኖበታል» አለ።

«እሽ» አለ ኤድዋርድ።

«የሚፈልገው ምን እንደሆነ አውቀዋል?»

«ችግር የለም።»

«እሽ እዚህ ይጠብቁኝ። ይዤው እመጣለሁ።»

ጋጋኖ ከክፍሉ ሲወጣ ብቻውን የቀረው ኤድዋርድ ዙሪያውን በአድናቆት ይቃኝ ጀመር።

ብዙም ሳይቆይ አንድ ሰው ሲገባ በመስማቱ ለተውኔቱ ክብብ ተዋናይ ሰላምታ ለማቅረብ ዞር አለ። ክፍሉ ውስጥ ገብተው ወደሱ የሚያመሩት ግን አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሰዎች ነበሩ። የመጀመሪያው ከኢስታንቡሉ ድርድራቸው ወዲህ ያላገኘውና ካርሎስን መከሎ ጠቅላላውን እንቅስቃሴ የሚመራው ሮበርት ጀክሊን ነበር። ሁለተኛው የተውኔቱ መሪ ተዋናይ ደግሞ አጠር ብሎ ደጋን እግሩ በእድሜ ጠና ያለው ጃፓናዊ ቆዳ ኩት የለበሰው አውሮፕላን አብራሪ ማዕጸ ነው።

«ሚስተር ዋልተር ዚምበርግ ማለት እሳቸው ናቸው» አለ ጀክሊን በትህትና ሲያስተዋውቅ። «በራሪው መኮንን የሱክ ማዕጸ በሁለተኛው የአለም ጠርነት የጃፓን ልዩ ተዋጊ ኮር አብራሪና የነፈው የርስም ተልእኮ ተጠሪ።»

ኤድዋርድ ለሰላምታ ከዘረጋው እጁ ጋር እርግጠኛ ያልሆነ ፈገግታ ለአብራሪው አሳየው። ማዕጸ በዘኩሉ የኤድዋርድን እጅ ሞት ባለ ሰላምታ ሲጨብጥ ከሚታይበት ፈገግታ የተነሳ ከላይኛው መንጋጋው ውስጥ ያሉት የወርቅ ጥርሶቹ እንኳ ሙሉ ለሙሉ ይታዩ ነበር።

«የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው አስከዚህም ነው» አለ ጀክሊን «ደግሉ

እኔ ጀንትኛ አማርቹ ስለምናገር እተረጉምለታለሁ።››

‹‹ጥሩ›› አለ ኤድዋርድ። በአብራሪው የመርት ጥርስ ተግርሞ ነበር። ‹‹የዚህን ሁሉ መርት ሙዮ እንዴት ቻለው?››

‹‹ከወጻጅቹ የተሰጠው የትድሙ መርነት ገፀ በረከት ነው።››

‹‹እሽ›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹እዚህ የመጣበትን ምክንያት ሳስረዳ። አብራሪ መኮንን የሱክ ማፀጳ የ721ኛው አየር ጓድና ሚያዝያ 17 ቀን 1945 በአሚሪካ የአውሮፕላን ተሸካሚ ላይ እደጋ ለመጣል ተልከው የነበሩት አጥፍዮ ጠፊ አብራሪዎች ብርጌድ አባል ነበረ። ማፀጳ በተለይ በዚያ እለት ፕሬዚጳንት ሩዝቬልት በተመልካችነት ተኮምጠውበት እንደነበረ የሚታመንበትን ድልድይ በሚያበረው ሱይሲ 441 ተዋጊ አውሮፕላን በ520 ጋውንድ ቦምብ ለመደብደብ ተመድቦ ነበር።

‹‹ቆይ እስኪ›› አለ ኤድዋርድ። ‹‹ይህ የሆነው መቼ ነበር?››

ሚያዝያ 17 ቀን 1945።››

‹‹ታዲያ ያኔኮ ፕሬዚጳንት ሩዝቬልት ሞተው ነበር። ስልጣን ላይ የነበሩት ፕሬዚጳንት ትሩማን ነበሩ።››

ጃክሊን በተታውሞ እጅን አወላወለ። ‹‹ይህን የምናውተው እኔና አርሰም እንጂ በወቅቱ ፕሬዚጳንቱ መሞታቸውን ማፀጳ አያውትም ነበር። ጥፉ ነጥብ ግን ማፀጳ ተልእኮውን መፈፀም አልቻለም። በመጨረሻው ደቂቃ የመጨረሻውን በረራ እያደረገ ቱልቱል በሚውዘገዘግበት ወቅት ራሱን ሳተ። አጥፍዮ መዋሩትን፣ ማለት አውሮፕላኗን ኢላማዋ ላይ ከስክሶ መሞትን ፈራ። ቶኪዮ የምትኖር እሙኛ ነበረችው። በሀይወት ወደቧ መመለስን መረጠ። ስለዚህም ተልእኮውን ሰርዞ ድልድዩን ሳያጠፉ አውሮፕላኑን ወንዙ ውስዋ አሳረፈው። ከዚያ በኋላ ከነጥሱ ተማርኮ በጠላት እጅ ሰር ገባ። መርነቱ እንዳሰቀም ከእሰር ተፈቶ ወደ አገሩ ተመለሰና የሚፈሊጋትን እሙኛውን ሊያገኝ ቻለ። ይህንና ተልእኮውን ሰርዞ እጁን ለጠላት በመስጠት በፈፀመው አሳፋሪ ድርጊት ውርደት ላይ ከመውደቅና አንድም

ጠቅሚ ስራ ሳይዝ ከመንከራተት በስተቀር ያተረፈው ነገር አልነበረም። ከዚያ ጊዜ አስከሁን ድረስ ሚስቱና ልጅቱ በድህነት ሲማቅቁ ነው የኖሩት። ሚስቱ ሽባ ነች። ማፀዳ ራሱ በሀያውቱ ሊቆይ የሚፈልገው ለአንድ ነገር ሲል ብቻ ነው። ለዚተሰበ ኑር አንድ ዋስትና የሚሰጥ ነገር ሊያግኝላቸው እንደተመኝ ነው እድሚውን የገፋው። እንደበፊቱ ያለ የአጥፍቶ መጥፋት ተልዕኮ እንደገና እንዲፈፅም ቢላክ ለዚተሰበ የኑሮ ዋስትና የሚሰጥ ክፍያ ካገኘ ያለ ማወላወል እንደሚፈጽም አበክሮ አስታውቆ ነበር። ካርሎስ ይህን በሰማ ጊዜ ማፀዳን አነጋግሮ ሰውየው አንድ ቀን ያስፈልግኝ ይሆናል በማለት የተወሰነ ገንዘብ እየደጎመ አስቀምጦት ነበር። ይኸው ቀኑ ደረሰ።››

ኤድዋርድ ደረት ፊጊታው የማይለየውን ሶስላ ዶሮ መሳይ ጅጉናዊ አተኩሮ መመልከቱን እንደተጠለ ነበር። በሸሙየው ላይ ሙሉ ለሙሉ እምነት እንዳልጣለ ያስታውቅብታል። ‹‹እንደ መጀመሪያው ይዝኛውንም ተልእኮ ባይፈጽምስ?››

‹‹ያህን አይጠራጠሩ›› አለ ጃክሊን። ‹‹ፍላጎቱ ለዚተሰበ ችግር መድረስ ብቻ ነው። በዚያ ላይ ከራሱ አፍ እንደሚሰሙት የነብር ጉዳይም አለ። እንዲያውም ኪሱ ውስጥ በማሞሪ ይዟል።››

‹‹ምን ይዟል?››

‹‹በቡድሃ ሃይማኖት ተልእኮ እንዲሳካ የመልካም እድል መግለጫ አርማ።›› ኤድዋርድ መርካቱን በመመልከት ጃክሊን ወደ ማፀዳ ዞር ብሎ በጀጋንኛ ያናገር ጀመር። ሁለቱ ሰዎች የጂጋንኛ ቃላት ከተለዋወጡ በኋላ ጃክሊን ወደ ኤድዋርድ መለስ አለ። ‹‹እሱ፣ አሁኑኑ ወደ ተልእኮኖ ልሂድ ነው የሚለው። የተረው የተኮንግሩትን አንድ ሚሊዮን ዶላር በቶኪዮው ዳይ-ኢቺ ኩባዩ ባንክ በሚሰቱ ሰም ማስተመሪያዎን ማረጋገጥ ብቻ ነው።››

‹‹ተቀምጠሀል›› አለ ኤድዋርድ የባንኩን ደረሰኝ ከጃኬቱ ኪስ እያወጣ። ‹‹ይኸው የደረሰኙ ፎቶ ኮፒ። ዋናው ቅጅ ቶኪዮ ያለው መኪላችሁ ስሚሰቱ ባሬውት ይሰጣታል።››

ጃክሊን የደረሰኙን ፎቶ ኮፒ ከኤድዋርድ ተቀብሎ ለጂጋናዊው አብራሪ አሳየው። ማፀዳ ደረሰኙን ካንበበ በኋላ ከልቡ በተደሰተ ሰው ገጽታ ፈገግ

ሲል አሁንም ድርድሮቹ የወረት ጥርሶቹ ሙሉ ለሙሉ ታዩ። ከዚያም ማፀዳ ጀመረ።

‹‹እተረጉምልዎታለሁ›› አለ ጃክሊን። ‹‹ረክቷል። አመሰግናዎታል። ግን ቅድም እንደነገርኩዎ ተልእኮው የከብር ጥያቄም እንዳለበት እንዲያውቁለት ይፈልጋል።››

የኤድዋርድ አስተያየት ግን አሁንም ተጠራጣሪነትን ያስነብባል ‹‹አሳቻ ሰው ነው። በርግጥ ይሳካለታል?››

‹‹ያለ ጥርጥር። በዚያ ላይ አዲሱን ጀት ተዋጊ አላማ ለማስመታት በቂ ልምምድ ሲያደርግ ሰንብቷል። ይልቅስ በነገርኩዎ መሠረት በሰዓት ለመንቀሳቀስ አውሮፕላን ማረፊያ መሬድ አለብን።››

ጃክሊን አሞራን ጃጋኖቭ ከንዴ ላይ ይዞ ከከፍሉ ለመውጣት ሲያመሩ ጃጋኖቭው ወረት ጥርሶቹን እያስገለፈጠ ዞር አለና ለመጨረሻ ጊዜ በሚሰናበት ሰው አንጋገር ‹‹ቴና ባንዛይ›› አለ።

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ኤድዋርድ ከፓጋኖ ጋር ከከፍሉ ወጡ። መኪናቸው ላይ ሲደርሱ አርምስቱድ ‹‹ከኔ ጋር ወደ ኒውዮርክ ትመለሳለህ። አልረሳህም አደል?›› ሲል ፓጋኖን ጠየቀው።

‹‹አልረሳሁም።›› ፓጋኖ ነበር።

‹‹እኪህልህ ሁለቱ ቁልፎች›› አለ ኤድዋርድ።

‹‹አንደኛው ሰዎችህን አፓርታማ ውስጥ ለማስገባት። ሁለተኛው እግል ከፍሊ ውስጥ። ልክ ኒውዮርክ እንደገባን ቁልፎቹን ለሰዎችህ ትሰጣለህ።››

‹‹ሁሉን ነገር አዘጋጅቼ ጨርሻለሁ አለኮ አያስቡ።››

ኤድዋርድ መኪናዋ ውስጥ ገባ። ‹‹አንድም ምልክት መኖር የለበትም። አደራ።››

‹‹በሮራሽ አይኖርም። አስክሬኖቹ ሮራሽ ሊኖኑ አይችሉም።›› ፓጋኖ መኪናዋ ውስጥ ገባ።

ኤድዋርድ ፓጋኖን ሳሽም አደረገው። ‹‹ጉስ?››

‹‹አዚት?››

‹‹የሴዮቹን ነገር እንግዲህ ላንተ ትቼዋለሁ።››

‹‹በኔ ይሁንብም ነው። የምልም። ልክ እንደ ኪም ነስቢት ያለ አንዳች ምልክት ነው የምፈልመው። ዘና ይበሉ፣ አለች። ጄጋናዊው ታላቁን ታሪክ ያከናውናል። የተረውን ታሪክ ለኔ ይተውልኝ።››

በኤድዋርድ መኖሪያ የግል ክፍል የታጎሩት ሁለት ሴቶች የማይተረው እስኪፈፀምባቸው ዝም ብለው ከመጠባበቅ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም።

ሁለቱም ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። ሁለቱም በደረሰባቸውና በተስፋ መቁረጥ ስሜት በአካልም ሆነ በሀሊና ደንዝዘዋል።

ቪክቶሪያ ጠቅላላ ተልፂ ያለው ጠረጴዛው ላይ ባለው የጠረጴዛው ሰዓት ላይ ነበር። እይናቿ ደቂቃ ቆጣሪውን ይከተላሉ። በመጨረሻ በረጅመ ተነፈሰችና ‹‹አሁን ጉዞ ጀመሩ›› አለች።

ሃና ከተዋጠችበት ሰመመን ብንን ያለችው በዚህ ወቅት ነበር። ‹‹እነማን?››

‹‹ከማሪላንድ የሚነሳው የፕሬዚዳንቱ አውሮፕላን አሁን በረራውን ጀምሯል። ሰዓቱ ልክ ሶስት ነው። አጥፍቶ ጠፊው ጄጋናዊም በዚህ ደቂቃ ሳይነሳ አልቀረም።›› ቪክቶሪያ ንግግሯን በተጥታ ለሃና ለማድረግ ይመስላል፣ ወንበሩ ላይ ተስተካክላ ተቀመጠች። ‹‹ባለቤትም አሁን ይሆናል ወደኛ ሰው የሚልክት።››

‹‹ይሆናል›› አለች ሃና።

ቪክቶሪያ ከብዙ ሰዓቶች በፊት የክዳት የመንፈስ ጥንካሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለሰላት ትመስላለች። ‹‹በሚመጡብን ጊዜ. . . ሃና እሽ ብየ አልወጣላቸውም። መሞቱ ካልቀረ ለምን እንደ በግ እነዳላቸዋለሁ? ወደ ታች ፎቅ ሲያወርዱን እንደምንም ርዕዱ ለማምለጥ እሞክራለሁ።››

‹‹መንገድ ላይ በጥይት ይመቱሻል።››

‹‹ይምቱኝ›› አለች ቪክቶሪያ ከትከሻዋ ሰበት እያደረጋት። ‹‹የኔ እጣ

ምንጊዜም መሞት ነው። እየሮጥኩ ከሞትኩ ግን እነሱ ሊያዙ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ምናልባት እርስዎ ሊያመልጡ ይችሉ ይሆናል።››

‹‹በእኔህ እግሮቼ ነው የማመልጠው ቪክቶሪያ?›› አለች ሃና አንጀት በሚበላ ትካዜ እግሯን ቁልቁል እየተመለከተች።

‹‹እንደ በግ እየተነዱ ወደ መታረጃቸው፣ ወደ አሸዊትዝ እንደተወሰዱት ሬዳት የለሽ አይሁዶች እዚህ ተዘፍዝፈን ወደ መታረጃችን እስኪጎትቱን መጠበቅ የለብንም። በሚቻለን ሁሉ መሟት አለብን። ከዚህ መውጫ የለም ብየ አላምንም።››

‹‹ማታ የደከምነውን ረሳሽ ቪክቶሪያ? ምንም መውጫ የለም።››

ቪክቶሪያ ከተቀመጠችበት እየተነሳች ዙሪያዋን ተገላመጠች። ‹‹መስኮት. . ከተፈጠርኩ መስኮት የለለው ክፍል አይቼ አላውቅም።በሆነ ዘዴ ተሸጥኖ ይሆናል እንጂ ቢያንስ አንድ መስኮት መኖር አለበት።››

‹‹ከእኔ አታውቂም፣ ቪክቶሪያ። መጀመሪያውኑ ሲገነባ ያለ መስኮት መሆኑን አይቻለሁ። በዚህ ተስፋ ቁረጭ።››

‹‹አንድ ከባድ እቃ ወይም እንደድጅኖ ወይም መዶሻ ያለ ነገር ብናገኝ ኖሮ ግድግዳውን ለመንደል እንጠቀምበት ነበር።››

‹‹ኤድዋርድ እዚህ ክፍል ዲጂኖና መዶሻ ምን ሊያደርግለት ያስቀምጣል? እንደዚያ ያለ እቃ ክፍሉ ውስጥ ቢኖር እንኳ ቶልፎብን በወጣበት ወቅት ያወጣው ነበር። እንዲህ ያለ እቃ ትኑ የሚሄድ ሞኝ ሰው አይደለም።

ቪክቶሪያ በኤሌክትሪክ የሚሰራውን ታይፕ ተመለከተችው። ‹‹ይህን ማንሳት ብችል ኖሮ ከግድግዳው ጋር እያጋጨሁ አፈርስበት ነበር።››

‹‹ግድግዳውን እንዲህ ተላል አድርገሽዋል? በኮንክሪትና በብረት የተገነባ ህንፃ ነው።››

ቪክቶሪያ ወደ ሃና ጠጋ ብላ አሰማች። ‹‹እንዲያው ምንም መፍትሔ የለም ነው የሚሉኝ?››

‹‹ምንም መፍትሔ፡፡››

‹‹ይህን ቤት መቼም ብቻውን ሊያንቀሳቅሱት አይችሉም፡፡ አልጋ የሚያነጥፍ ቤት የሚያፀዳ ሰራተኛ ቢጠም የለም?››

‹‹አንድ ጥሩ ተመላላሽ ሰራተኛ ነበረችኝ፡፡ ከሳምንት በፊት ኤድዋርድ ካልወጣች ሞቼ እገኛለሁ ብሎ አስወጣብኝ፡፡ ከዚያ በኋላ አንድ የፅዳት ሰራተኛ ራሱ በግሉ ቀጠረ፡፡ ይህች ሰራተኛው ታዲያ በሳምንት ሁለት ቀን ያውም ለሶስትና አራት ሰዓቶች ብቻ ነው፡፡ ለዚያውም እንግሊዘኛ መግባቢያውን በትጉ መናገር እንኳ የማትችል የኦቲማላ ሴት ናት፡፡››

‹‹መቼ መቼ ነው ታዲያ የምትመጣው?››

‹‹ዛሬ አትመጣም፡፡ ያሳዝናል ቪክቶሪያ፡፡ ይህ ቤት ግራ የሚያጋባ ቤተሰብ መኖሪያ ነው፡፡ ኤድዋርድ ቤቱን ገጸም አድርጎት ነበር የሚኖረው፡፡ ሆን ብሎ፡፡››

‹‹እንዲያው ሚስተር ኤድዋርድ ስራዎን በሚስተር የሚከታተል ክፍል ሊኖር ይችላል የሚል ጥርጣሬ አልነበራቸውም?››

‹‹ኧረ በሞራሽ፡፡ ምድር ቤት ያለው ዘብ በቂ ነው የሚል እምነት ነበረው፡፡ በተጨማሪም የውጭ ሰው ወደዚህ ክፍል ጥርጎ ጠትላላ ሀንግው እንዲገባ የሚያደርግ ማንኛውንም አይነት ስራ እንዲሰራ አይፈትድም፡፡›› ሃና ንግግሩን አቋርጣ ትክዝ አለች፡፡ ‹‹የሀንግው ተቋራጭ እዚህ ክፍል እንዲያስገባለት የጠየቀው የሞሶ መቆጣጠሪያ ብቻ ነበር፡፡ ኤድዋርድ በሀይወቱ እንደ እሳት የሚፈራው ነገር የለም፡፡››

ቪክቶሪያ በትጽበት አይኗን አፈጠጠች፡፡ ‹‹የሞሶ መቆጣጠሪያ? የት?››

‹‹እዚሁ ነዋ . . .››

የቪክቶሪያ አይኖች በጣራው ተንገዋለሉ፡፡ ‹‹እስካሁን አላየሁትም፡፡››

‹‹አዎ፡ በተላለ አይታይም፡፡ ኤድዋርድም እንዳይታይበት ነው ሆን ብሎ በማዕዘኑ በኩል በእንጨት ከፈኖ እንዲከለልለት ያዘዘው፡፡››

ቪክቶሪያ ወደ ማዕዘኑ ጠጋ ብላ ስትመለከት ዝርግ ሳህን መሰየ ከብ

የሶስ መቆጣጠሪያ ነጣ ባለ ቡናማ ቀለም በጉልህ ተለያት። ‹‹እዚያ አካባቢ አንድ ክብ ብረት ነገር ይታየኛል።››

‹‹እሱ ነዋ ታዲያ የሶስ መቆጣጠሪያው።››

‹‹አገልግሎቱ ምንድን ነው?››

‹‹እንዴ . . .ያው መሥሠህ ነዋ። እሳት ወይም ሶስ በአካባቢው ከኖረ።››

‹‹መሥሠህ?›› ቪክቶሪያ አልገባትም። ‹‹እንዴት?››

‹‹የቤቱ ነዋሪዎች እንዲጠነቀቁ በንይል ይደውላል። ግን ይህ አይነቱ የሶስ መቆጣጠሪያ ከሌሎቹ ውስብስብና ዘመናዊ ነው። ለቤቱ ነዋሪዎች በሚደውልበት ጊዜ መቆጣጠሪያውን ላስገባው ኩባንያም እንዲሁ ምልክት ያቀብላል። ኩባንያውም መልእክቱ እንደደረሰው ወዲያውኑ በትርብ ለሚገኝ እሳት አደጋ መከላከያ ብርጌድ ያሳውቃል።››

‹‹ሃና›› ላይታወቃት ሥጋት ቪክቶሪያ። ‹‹በቃ ማምለጫችን እሱ ነው።››

ሃና ምን ያህል ግራ እንደተጋባች መገመት አያዳግትም። ‹‹አልገባኝም.....››

‹‹ችግር ላይ መሆናችንን የውጭ ሰው እንዲሰማልን እንገለግልበታለን። መጀመሪያ እዚህ የእሳት መቆጣጠሪያው ደወል ይደውላል፣ ለኩባንያው መልእክት ያቀብላል። እርዳታ ይደርስልናል . . .››

ሃና ምን ትበል? ‹‹እሳት? እንዴ ልክ ነሽ። ግን ደግሞ አደገኛም ነው። እሳቱ ራሱ አመድ ቢያደርገንስ . . .››

‹‹እሳቱን መቆጣጠር አያቅተንም። ደሞስ ከሞት በላይ ምን ይመጣብናል? ልብ ያድርጉ የሚጠብቀን ሠሮ ሠሮ . . .››

‹‹ሠሮ ሠሮ ሞት ነው›› አለች ሃና ተበል አድርጋ። ‹‹እንዴት ያለ መጥፎ ሌሊ ነው ቪኪ። እርዳታ ለመጥራት አማራጭ የሌለው ዘዴ።››

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቪክቶሪያ ተግባሯን ቀጥላ ኖሯል። መጀመሪያ ተቀምጣበት የነበረውን ወንበር አንስታ ከእሳት መቆጣጠሪያው ትይዩ አደረገችው። «ክብራት ይኖር ይሆን?»

«ኤድዋርድ አያጣም። ካለች በኋላ ሃና የባሷን ጠረጴዛ ትመለከት ጀመር። ያገኘችው ነገር ግን አልነበረም። ቀጥላ መነበያውን ከፍታ ትበረቅቅስ ገባች። አረንጓዴ የክብራት ባነ አገኘች። ጊዜ ሳታጠፋ ለቪክቶሪያ አቀበለቻት።

ቪክቶሪያ ወንበሩ ላይ ዘላ ከወጣች በኋላ በእግሯ ጣቶች ቆማ በምትችለው መጠን ወደ ላይ እየተለጠጠች አንድ እጅዋን ወደ ጭስ መቆጣጠሪያው ሰደ ልትደርስ የምትችለውን ርዝማኔ ለካች። «መቆጣጠሪያውን መንካት ቀርቶ መቅረብ አልችልም። ሲበዛ ሩቅ ነው። ለ,ያገኘው የሚችለው አውኑኮ አሳት ብቻ ነው። . ሃና፣ ያን ጋዜጣ ጋዜጣውን ከጠረጴዛው ያምጡልኝ።»

ሃና በምትችለው ጥሞነት እንደታዘዘችው አደረገች።

«ግሩም» አያለች ቪክቶሪያ ጋዜጣውን ለሁለት ቀዳ በሰያፉ በረጅሙ ጠቀለለችው። «ከአንድ ሜፍ በክብራት ለክሽ መቆጣጠሪያውን አሰነሳዋለሁ። ያኔ ያሰብኩት ይፈፀማል።» ከንግግሯ ጋር ክብራት ሜረች።

«ተጠንቀቂ ቪክቶሪያ!» ሃና ተናገረች።

የተያያዘውን ክብራት ቪክቶሪያ ከወረቀቱ ጋር ከማገናኘቷ ወረቀቱ በነበልባል ዐግ አለ። ነበልባሉ ትልቅ፣ ሰፊ፣ ቀይና ይበልጥ የጠነከረ እየሆነ በመጣ መጠን ቪክቶሪያ እንደገና በእግሯ ጣቶች ቆማ በተቻላት መጠን እየተንጠራራች ወረቀቱን በእሳት መቆጣጠሪያው ሳህን ላይ አደረገች። ነበልባሉ ወደታች እየወረደ ከመቆጣጠሪያው እየራቀ የቪክቶሪያን እጅ መጠጋቱ አልቀረም። ይሁን እንጂ በነበልባሉ ፋንታ መቆጣጠሪያውን የሚያጥነው ጭስ ብዛት ደግሞ እየጨመረ ሄደ።

«ኧረ ተጠንቀቂ!» ሃና ጮኸች።

ቪክቶሪያ የሃናን ምክር የምትቀበልበት ልብ ተርቶ የምትሰማበት ጆሮ

ሊናራት እንደማይችል ግልፅ ነው። መቆጣጠሪያውን ብቻ ደመነፍሷን ‹‹ደውል፣ ባክህ ደውል!›› እያለች ትለምን ጀመር።

ድንገት፣ በሚነዝር ሃይል፣ ደወሉ አስተጋባ። ከድምፁ ከፍተኛነት ጋር ደወሉ የሚያሰማው ለረጅም ጊዜ ነበር። በዚያው ቅጽበት መቆጣጠሪው ለሰራው ኩባንያው መልእክት በማስተላለፍ ላይ መሆኑን የተረዳው የቪክቶሪያ ፊት ፈተ-ፈቷ ከሚያበራባት ነበልባል ጋር ተዳምሮ ምን ያህል እንደሚያበራ መገመት ይቻላል። ወዲያው ግን የወረቀቱ የመጨረሻ ጫፍ እየነደደ እጅጉን ማማናት ሲጀምር በተሰማት ሀመም የተረዙን ጋዜጣ በትጽበት ጥላ ከልከ ያለፈ ሥዝች። በዚያው ሴኮንድም ከወንበሩ ዘላ ወረደች።

ሃና የቪክቶሪያን ትከሻ ጮምት አድርጋ ደሃ ወደ አንድ አትጣጫ አመለከተች። ‹‹ቪክቶሪያ . . . !››

ቪክቶሪያ የወረቀቱ ነበልባል እጅጉን ባታጠለበት ወቅት በደመነፍስ ስትወረውረው ወደ ላይ ሽብ ተደርጎ በተቋጠረ ቱይ መጋረጃ ውስጥ መውደቁን አልተመለከተችም ኖሯል። መጋረጃው አትር ደቡቦት በነበረው የወረቀት ነበልባል እየተያያዘ መጀመሪያ ደማት ቱይ በኋላም መርጮማ የእሳት አሎሎ ከውስጡ መትፋት ሲጀምር እሳቱም እየሰፋና እየተስራፋ ሂደ።

‹‹ያጥፉት . . . ቶሎ እናጥፋው!›› ቪክቶሪያ ሥዝች። የምትሆነው ያጣችው ሃና የመጋረጃው ነበልባል እየተንረደ እየተወረወረ ክፍሉን ሲሞላው ተመለከተች። ‹‹የለም፣ ቪክቶሪያ፣ ልናጠፋው አንችልም፣ . . በታ እንደታፈን ነደን ማለቃችን ነው።››

ሃና ተስፋ በቶረጠ ሞንቀት ቪክቶሪያን ሙሞቱ እድርጋ ያዘች። ወዲያው ግን አንድ ሃሳብ መጣባት። ‹‹በዚህ በኩል ነይ። መታጠቢያ ክፍሉ እንግባ . . .የእሳት አደጋ ሰራተኞች ሲናገሩ ሰምቻለሁ . . . መታጠቢያ ክፍል ግቢ፣ ግንዳው ውስጥ ተቀመጭ . . .ውሃውን ልቀቂው።››

ሞሁ ክፍሉን ሞልቶ አይን ቢወጉ እንዳይታይ አድርጎታል። ቪክቶሪያ

አጎንብሳ በትንሿ የበር መተላለፊያ ሃናን እየተከተለች ትንዝ ጀመር።

ሁለቱም ግንዳው ውስጥ ኩርትም ብለው ተቀመጡ። መታጠቢያ ክፍሉን ከውስጥ ዘጉት። «ሮስ ሮስ ይሸተኛል» አለች ቪክቶሪያ። «ሮስ እየገባብን ነው። ሮስ መጀመሪያ አፍኖ ባይገድለን እንኳ እሳቱ ያጥንናል። ውሃውን ልልቀቀው ይሆን?»

«ቆይ ቆይ» አለች ሃና። «ያ የመጨረሻው ርምጃችን ይሆናል። ስሚ ቪክቶሪያ።»

ሁለቱም ዐጥ ብለው የሚያቋርጠውን ቀጭን የሮስ መቆጣጠሪያ ደወል ያጸምጡ ጀመር።

«መቆጣጠሪያው፣ እየሰራ ከሆነ» አለች ሃና በሮስ በታፈነ ትንፋሽ፣ «እስካሁን የእሳት አደጋ ማዘዣ ሰራተኞች መልእክቱ ደርሷቸው ይሆናል። ከደረሳቸው ደግሞ በአፋጣኝ እዚህ ይመጣሉ።»

«ያርግልን» አለች ቪክቶሪያ፣ ሳል አላናግር እያላት። «እንጂ፣ በጊዜ የሚደርሱልን አይመስለኝም።» ሰንሰለቷን ተመለከተች። «ስምንት ወይም አስር ደቂቃ መልእክቱ ሳይተላለፍ አይቀርም።»

ይህ በእንዲህ እንዳለ በታጠሉው መስፋፋት የመታጠቢያ ክፍሉ የመስታወት በር እየተንቋቋ፣ እየተወላወለ መጥቶ በመጨረሻው የእሳቱ ወላፈን ሁለቱን ሴቶች መግረፍ ጀምሮ ነበር። በተወላወለው የመስታወት በር የሚገባው ሮስ መታጠቢያ ክፍሉን አፍኖ ትንፋሽ መተናነቁን እየጨመረ ነው።

ቪክቶሪያ ከመታጠቢያ ክፍሉ የሳመና ማስቀመጫ አጠገብ አንድ የውሃ መምጠጫ ስፖንጅ አየች። ስፖንጁን እንስታ ከኪሷ መሃረብ ካወጣች በኋላ የግንዱውን ውሃ መክፈቻ አዙራ ተዝለግላ ውሃ እንዲፈስ አደረገች። ከሚፈሰው ውሃ በታች ስፖንጁንና መሃረቡን ይዛ ጥቂት እንደቆየች ቧንቧውን መልሳ ዘንቅና ውሃ የመጠጠውን ስፖንጅ በሃና ፊት ላይ አስቀመጠች። ቀጥላ ርጥቡን መሃረቧን በራሷ አፍና አፍንጫዋ ላይ ጨመቀችው።

አይኖቿ እየተጠቀጠቀ የሚመጣውን ሮስ መቋቋም አቅቷቸው እንባ

ማንቀርዘዝ ከመጀመራቸውም በላይ ሳሉን አልቻሉችውም።

ድንገት ከሚንበለበለው እሳት የዘለጠ ከባድ ድምፅ በመሰማቱ ጆሮዋን በጎንዱው መስታወት ላይ ለጠፈች።

ድምፁ በግልጽ የሚለይ፡ ከፍተኛና ኃይለኛ ሲሆን በመጨረሻው የመታጠቢያ ክፍሉ በር ጆሮ በሚሰቀጥጥ ከባድ ድምጽ ተሰብሮ የአንድ ጅረት ፋፋቱ የሚያህል ውሃ ወደ ክፍሉ ገባ። ወዲያው ደግሞ የሚንቀለቀለው እሳት በውሃ እየጠፋ ይመስላል ቸሰስ የሚል ድምፅ ተከተለ። ቪክቶሪያ ወደ ሃና ዞር ብላ ልታትፋት ሞከረች። ሃና ግን ዝልፍልፍ ብላ ራሷን ስታ ልትወድት ደርሳለች።

ቪክቶሪያ በድስ በጠቆረው የመታጠቢያ ክፍል መስታወት በኩል ሁለት ምስሎች የምታይ መሰላት። አዎ፡ ፈታቸውን የከለሉና የእሳት መከላከያ ኮት የለበሱ ሰዎች መታጠቢያ ክፍሉ ውስጥ እየገቡ መሆኑን አመነች። በደስታ ጩኸቷን እያቀለጠች የመታጠቢያ ክፍሉን በር ከፈተች። «እዚህ! እዚህ ነን!» ነበር ከአፏ ሊወጣ የቻለው ሃረግ።

ቪክቶሪያ በደመነፍስ ወደ ውጭ ለመውጣት ስትንደረደር እንደኛው የእሳት አደጋ ሰራተኛ ባይደግፋት ኖሮ በአደገኛ ሁኔታ በወደቀች ነበር። እሷ ግን ትንፋሿ ሃና መለስ ላይልላት ወደ ኋላዋ እያመለከተች «እዚያ ውስጥ ናቸው. . . እሳቸውን እርዱ!» ጮል ነበር።

በደጋፊ ኮሪደሩ ላይ እንደደረሰች ዞር ስትል ሌሎች ሰራተኞች ሃናን ከመታጠቢያ ክፍሉ አውጥተው ወደ ሁለተኛው መታጠቢያ ክፍል ሲወስዷቸው ተመለከተች። ሰራተኞቹ ሃናን ኤድዋርድ መኝታ ክፍል ወስደው በጥንዱ አልጋ ላይ ሲያጋድሟት አየች።

ቪክቶሪያ የሞት ሞቷን ወደ መኝታ ክፍሉ ተንደርድራ ስትገባ ሃና ተገለፍልፋ አንጎበሰው በሚያክሙዋት ሰዓት ወንድና አንዲት ሴት ባለሙያዎች ተከባ ነበር።

ከሃኪሞቹ መካከል በተለይ ሬዙ የተንዥረገገ አንድ ሰው ወደ ቪክቶሪያ አመራ። «አንቺ ደህና ነሽ ወይበሪት?»

ቪክቶሪያ መሳቧን አቁማ ነበር። ደነና መሆኗን በእምንታ ምልክት ገለፀችለት።

ሀኪሙ በእውራ ጣቱ ወደ አልጋው እየጠቆመ «አይሆሽ» አሳት ቪክቶሪያን «እናትሽ ምንም አይሆኑም። ሮስ ሳምባቸውን አፍኖት ነበር፣ ግን እየወጣላቸው ነው። በወትሮ ነው የአሳት አደጋ ተከላካዮች የደረሱላችሁ።»

ቪክቶሪያ የአምንታ ምልክት ማሳየቷን በመቀጠል ወደ አልጋው ተመለከተች። የሃና አይኖች ያለወትሮአቸው ጎላ ብለው በመነፈጥፈጣቸው ቪክቶሪያ እሷን የሚፈልጉ መሰሏት። ወዲያውኑ ወደአልጋው ተጠግታ ሃና እሷን ወደ ራሷ ለማቅረብ ስትሞክር አየቻት። ቪክቶሪያ በፍጥነት ጎንበስ አለችና «አይዞዎ፣» አለቻት።

ሃና ለመናገር እየተጣጣረች ስለነበረች ቪክቶሪያ ጆሮዋን በፀሸተኛዋ ከናፍር ላይ ጣል አደረገች። «ቪክ. . .» አለች ሃና የማጂን። «አደራሽን እንዳታስገድይው. . . እሱ. . . እሱ በሽተኛ ነው፣ . . .የተለከፈበት ነገር አለ።»

ቪክቶሪያ አውንም በአምንታ ራሷን ከፍ ዝቅ አድርጋ ቀና ብላ ዙሪያዋን ተገላመጠች። ብዙ ሰዎች እዚህም እዚያም ይጣደፋሉ። እዚህ መኝታ ቤት ሀኪሞች ሃናን ከበው በህክምና ይዋከባሉ፣ እዚያ ደግሞ የእሳት አደጋ ተከላካዮች በኮሪደሩ ውዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ። ቪክቶሪያ ቦርሳዋን አፈፍ አድርጋ አንስታ በኮሪደሩ በኩል ወደ ላሎን ትሮጥ ጀመር። እንደ እድል ሆኖ ወደ ላሎኑ ስታመራ ያያት የእሳት አደጋ ሰራተኛም ሆነ ፖሊስ አልነበረም።

ከአፓርታማው ውጭ በረንዳው ላይ ብዙ የእሳት አደጋ መኪኖች ከብ ሰርተው በነገር ይወጣገባሉ። ቪክቶሪያ በፕሬዚዳንቱ አውሮፕላን ላይ ስለሚታጣው አደጋ ለመኮንኖች ልትገልጽ አሰበች። ይሁን እንጂ ለነሱ ሚስጢሩ እስኪዘረዘር፣ ማስረጃ እስኪጠቅስና ተከራክረው እስኪያምኑ የሚታጠለውን ጊዜ ግመተች። በጥያቄና መልስ ታለምልልስ የምትታሰርበት ጊዜ እንደሌላት አምና ወደ ደረጃው አመራችና ቁልቁል ትመርድ ጀመር፣

እንዳትወድቅ እየተጠነቀቀች።

ሰንድን መመልከት አልነበረባትም። የመጨረሻው ቀውጢ ደቂቃ እየደረሰ መሆኑን ደመ-ነፍሷ ነግሯታል።

* * *

‹‹ምን ልታዘዝ የኔ እመቤት? ለመሆኑ ምነው? ተጨንቀሽ ያደርሽ ነው የምትመስይው።›› ከብዙ ፋሚሊ በኋላ፣ ብዙ መንገድ ሮጣ፣ ብዙ መንገደኞች በሁኔታዋ ተገርመው አፋቸውን ይዘው ተመልከተዋት በመጨረሻ ትንፋሿ እየተናነቃት የገባችበት አንድ የአልኮል መጠጥ ሽሮሰሪ ባለቤት የቪክቶሪያን ተንደርድሮ ዘው ማለት ሲያይ እብድ ናት ብሎ ሳይደመድም አልተረፈም።

‹‹ከእሳት አመለጥኩ›› አለች ቪክቶሪያ ትንፋሿ እንደተናነቃት፣ የተመሰቃቀለ ጠጉሯን፣ የበለዘ ፊቷንና የተቀዳደደ ቆሻሻ ልብሷን ማብራራት እንዳለባት ተሰምቷት።

‹‹ስልክ ፊልጌ ነበር. . .››

‹‹ከፊት ለፊትሽ አለልሽ።››

ወደ ስልክ መደወያው ሳጥን አመራች። ከውስጥ ዚጋችና ከሠርሳዋ ያገኘቻቸውን ዝርዝር ሳንቲሞች ጨምራ መጀመሪያ የሞሽንግተን ዲ.ሲ.ን የማዞሪያ ቁጥር ተጥሎም የዋይት ሀውስ ቤተ-መንግስትን ቁጥር አዞረች። የማዞሪያው ስልክ ተነስቶ አንድ የሴት ድምጽ ተቀበላት። ቪክቶሪያ ከማን ጋር አገናኙኝ እንደምትል ግራ ገብቷት ታመነታ ጀመር። ምናልባት አውሮፕላኑ ባንዳንድ ምክንያቶች ዘግይቶ ለጉዞ አልተነሳ ይሆናል። ምናልባትም አባቷ እስካሁን ከዋይት ሀውስ አልተነሱ ይሆናል።

‹‹ኧማ ዊስተንን ማነጋገር እፈልጋለሁ፣ የፕሬስ ዘሐፊውን።››

‹‹አገናኝዎታለሁ›› የሚል መልስ ተሰጣት። ወዲያው ደግሞ ሌላ የወጣት ሴት ድምፅ ተረበሳትና፣ ‹‹የፕሬስ ጸሐፊ ቢሮ›› አላት።

‹‹ሚስተር ዊስተንን እባክዎ?››

‹‹አዝናለሁ፣ ለሳምንት ያህል ከዚማ ውስጥ አይኖሩም። መልእክት

ካለም. . .››

‹‹ጉዳዩ በጣም አስቸኳይ ነው። የኮሬዚዳንቱን ሀይወት ይመለከታል። የማነጋግረው ሌላ ሰው. . .›› የወጣቷ ሴት ድምፅ አንድም የመደናገጥ ቃና አይታይበትም። ‹‹እስኪ ከሞይት ጋውስ አኮሬሽን ጋላፊ ጋር ላገናኝም። ይጠብቁ።››

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ለስለስ ያለ የወንድ ድምፅ መስመር ላይ ተሰማ።

‹‹ፍራንክ ሂሊፋንት ነኝ። ምን ልርዳ?››

‹‹የኮሬስ ዐሐፊው ልጅ ነኝ. . .››

‹‹የሚስተር ዊስተንን ስልክ ልስጥሽ?››

‹‹ሞክሬ ነበር›› አለች ቪክቶሪያ የጊዜው ሩጫ እያበሳጫት። ‹‹እርስዎን አነጋግሬ ብለውኝ ነው። ጉዳዩ በውነት በጣም አስቸኳይ ነው። የኮሬዚዳንቱ ሀይወት አደጋ ላይ ወድቋል። በማንኛውም ደቂቃ የአኮሬሽን ጋላፊው ልጅቷን ለማረጋጋት ይመስላል ንግግሯን አቋረጣት።

‹‹አሁን ስኮሬዚዳቱ ሀይወት የምናስብበት ወቅት አይደለም፣ ወይዘሪት ዊስተን። በሰላም ወደ ለንደን በመጓዝ ላይ ናቸው። ለወዲፉቱ የተጠነሰሰባቸው ነገር ካለ ግን አንድ ሪፖርት ለማዘጋጀት ዝግጁ ነኝ። መሉ ስምሽንና አድራሻሽን የደረስሽበትን ሁኔታ ሞምር ብትነግሪኝ ለምርመራ መንደርደሪያ እናደርጋቸዋለን።››

ቪክቶሪያ ሳግ እየተናነቃት ነው። ያ ዶለዝ እንደማንኛውም ተራ ባለጉዳይ እየተመለከታት ነው። የማይታመን እልቂት ተጠንስሶ፣ የመፈፀሚያው ደቂቃ ደርሶ እያለ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ርምጃ የሚወስድ ጠፋ። የቢሮ ውጣ ውረድ ምን ጊዜም ለአጣዳፊ ጉዳዮች ማነቆ እንደሆነ ነው። ነገሮችን በቀላሉ አለማመን በእለት ተለት ተደጋጋሚ ስራ ከመሰላቸት ጋር ተዳምሮ ለብዙ አስቸኳይ ጉዳዮች ጋሬጣ ሆኗል።

ቪክቶሪያ በንዴት ብዛን ብላ ስልኩን ልትዘጋ ስትል አንድ ስም

በአእምሮዋ መጣ።

ሲ.ሮዝንብለም።

ኒክ ራምሲ ለመጨረሻ ጊዜ ባነጋገረችው ወቅት እንድ ፈጣን ምክር ወይም ርዳታ ባሻሽ ጊዜ ዋይት ኃውስ ደውለሽ ሲ. ሮዝንብለምን እንዲያገናኙሽ ጠይቂ. . . ያላት ታውሳት።

‹‹እንግዲያውስ ሲ.ሮዝንብለምን ላነጋግር?›› ጮኸች።

‹‹ማን?››

‹‹ሚስተር ሮዝንብለም። የፕሬዝዳንቱ ቢሮ ረዳት. . .››

‹‹እንድ ጊዜ እመቤት፣ ማውሳውን ልመልክት. . . እም ሰልኩ አለኝ። ላገናኝሽ እሞክራለሁ።. . .››

ሴኮንዶች በረሩ። ‹አገናኘኝ፣ አገናኘኝ› በአፏ ሳይሆን በልቧ ተማፀነች፣ ቪክቶሪያ። በልተት ያለች ሴት መሳይ ድምጽ ቀረበ።

‹‹ሚስተር ሮዝንብለም ቢሮ።››

‹‹ሂሎ ያዳምጡኝ። በጣም አስቸኳይ ጉዳይ አለኝ። ሚስተር ሮዝንብለምን ማነጋገር አለብኝ። ቪክቶሪያ ዊስተን እባላለሁ. . .››

‹‹አሁን ወጣ አሉ። ከአንድ ሰራተኛ ጋር፣ ለቡና ሳይሆን አይቀርም። ከማማሽ ሰዓት በፊት እንደሚመለሱ እርግጠኛ ነኝ።››

የቪክቶሪያ ጭንቀት መገመት አያስቸግርም። ‹‹እባክዎ አንድ ሙስታ ይዋለልኝ። እንደነገርኩዎ እጅግ በጣም አስቸኳይ ነገር ነው። . . . የህይወትና የሞት ጥያቄ ሆኖብኝ ነው። ሰውየው ምናልባት ከነንግው አልወጡ ይሆን? ሊደርሱባቸው ይችሉ ይሆን?››

ፀሐፊዋ ኮስተር ብላ መለሰች። ‹‹ይሆኑ ይሆናል ግን ባግኛቸው ማን ፊለገም ልበላቸው? ዊስተን አለኝ. . .?››

‹‹ቪክቶሪያ ዊስተን። የኒክ ራምሲ ጓደኛ ይበሉልኝ። ሰለኔ ያውቃሉ. . . እባክዎ ፈጠን ይበሉልኝ?››

‹‹ስልኩን አይዝጉት›› አለች ፀሐፊዋ፡፡

የቪክቶሪያ ሞንትሳት ሊፈነዳ ደረሰ፡፡ በክንዱ ያሰረችው ሰዓት ደቂቃ ቆጣሪ በእሮጮ ጊዜ ከዐታው ለቋል፡፡

በመጨረሻ ቀዝቀዝ ያለ ድምጽ ከወዲያኛው መስመር ተሰማት፡፡ ‹‹ወይዘሪት ዊስተን?››

‹‹አ. . .አም፡፡››

‹‹ርዘንበለም ነኝ፡፡ ለገጠመሽ ችግር አዘናለሁ፡፡ በመጨረሻም በድምጽም ቢሆን መገናኘት መቻላችን ደስ ብሎኛል፡፡ በርግጥ ስለእንቺ ከኢክ ራምሲና ከድኑ አባትሽ ሰምቻለሁ፡፡ እንዲያውም ራምሲ ልትደውልልሀ ስለምትችል በጥሞና አነጋግሪት ብሎኝ ነበር፡፡ ለመሆኑ ችግር. . .?››

‹‹በጥሞና ይዳምጡኝ!›› ቪክቶሪያ ተማፀነች፡፡ ‹‹ሮሬዚዳንቱ፣ አባቴ፣ ኒክ ራምሲ፣ ሁሉም የለንደን መንገደኞች በማናቸውም ደቂቃ ሊሞቱ ነው፡፡ አንድ ሴራ እንደተደገሰ ደርሰንበታል፣ አሁን በእንትስታሲ ላይ ያለ የግድያ ሴራ እንደተደገሰ ደርሰንበታል፣ አሁን በእንትስታሲ ላይ ያለ የግድያ ሴራ አለ. . . ምን ያህል አውነተኛ ነሽ እንዳይሉኝ. . . መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ›› በማለት ታሪኩን ባጭሩ አብራራችለት፡፡

ቪክቶሪያ ከማዶው መስመር የሚያነጋግራት ሰው እምት ያለ ትንፋሽ ሲሙጥ ይሰማታል፡፡ ‹‹ከልብሽ ነው? መሉ ለመሉ አረጋግጠሻል?››

‹‹ወይኔ. . .አም፣ አም፣ አም፡፡ ይመኑኝ፡፡››

‹‹አምንሻለሁ፡፡ ለመሆኑ ይህ መቼ ነው እንደሚፈፀም የሚገመተው?››

‹‹አሁን፡፡ በማናቸውም ደቂቃ. . . በደቂቃ ውስጥም ሊሆን ይችላል፡፡››

‹‹እንግዲያውስ በተጣደ ከአውሮፕላኑ ጋር ራስሽን በመስመር ባገናኝሽ ይሻላል፡፡ አየሽ፣ ነገሩ ፈጠን ይላል፡፡ ልታስጠነቅቂያቸው ትችያለሽ፡፡ ለመሆኑ የት ነሽ?››

‹‹ኒውዮርክ፣ በሀዘብ ሰልክ ነው የምደውለው፡፡ ማዲሰን ጎዳና፡፡››

‹‹ስልኩን አትዝጊው›› አለ ሮዝንብለም በጥሞና፡፡ ‹‹እዚያው ሆነሽ ጠብቂ፡፡››

ቪክቶሪያ ከስልኩ መደወያ ሙሎ ሁለት ሰዎች ወረፋ እየጠበቁ መሆናቸውን የተረዳችው ግና አሁን ነበር፡፡ ስልኩን እንደ ያዘች መቅረቷን ሲረዱ ከሁለቱ ሰዎች አንደኛው በቁጣ በሩን ይደበድብ ጀመር፡፡ ቪክቶሪያ መቼም ንቅንቅ የምትል ጉድ አልሆነችም፡፡ የኋላ ኋላ ሁለቱ ሰዎች የግሮሰሪውን ባለቤት ጠሩ፡፡ ባለቤቱ ጊዜ ሳይፈጅ መጥቶ በቁጣ የበሩን እጀታ ይዞ መዝጊያውን ይንጠው ጀመር፡፡

ቪክቶሪያ መዝጊያውን በሳም በጥቂቱ ከፈት አደረገች፡፡

‹‹እመቤት፣ ይሂኩ የቤትሽ ስልክ አይደለም፡፡›› ባረቀ ባለግሮሰሪው፣ ‹‹ትሙዋ እንደሁ ሙሎ ሰዎች ይደውሉበት፡፡››

‹‹አልችልም!›› ሥነሽች ቪክቶሪያም በልበ መሉነት፡፡ ‹‹የአሜሪካን ፕሬዚዳንት እያስቀረብኩ ነው፡፡ ይልቅስ ፀጥታ ባትነሱኝ፡፡›› በሩን ጥርቅም አድርጋ ዘጋች፡፡

በስልኩ መስመር ላይ ድምጽ መጣ፡፡

ቪክቶሪያ መነጋገሪያውን ጆሮዋ ላይ ልጥፍ አደረገች፡፡

‹‹አዎ እኔ ነኝ፡፡››

‹‹ሮዝንብለም ነኝ፡፡ ጠብቂ ቪክቶሪያ፡፡ በቀጥታ ከአውሮፕላኑ ልናገናኝሽ ነው፡፡››

* * *

ከአንድሪው አየር ኃይል ካምፕ ከተነሳ ሃያ ሁለት ደቂቃ የሆነው (አየር ኃይል አንድ) የሚል መጠሪያ የተሰጠው 747 ጄምቦ ጀት አውሮፕላን ባሞጠሞጠ አፍንጫው በሰማያዊ አትላንቲክ ውቅያኖስ ከደመናው በላይ ሠዉን እየተዘፈ ወደ ለንደን የሚያደርገውን ጉዞ ተያይዞታል፡፡

በአውሮፕላኑ ውስጥ የፕሬዚዳንቱ ቢሮ የፕሬስ ፀሐፊ የሆኑት ኸግ ዊሰተን የስልክ ጥሪ ለመቀበል በፕሮቶኮል ከተቀመጠበት ቦታ ተንስተው

ወደ አውሮፕላኑ የኮሙኒኬሽን ክፍል ያመራሉ። ከፍሉ ውስጥ እንደገቡ የአውሮፕላኑ የኮሙኒኬሽን ኃላፊ ጠረጴዛ ላይ ያለውን ነጣ የስልክ መነጋገሪያ አመለከታቸው።

‹‹ማነው እሱ?››

‹‹እኔ እንጃ። የሚወተው ካልተገለፀ ስፍራ በሞይት ጋውስ የኦፐሬሽን ክፍል በኩል የተገናኘ አስቸኳይ ጥሪ መሆኑን ብቻ ነው።››

ኸግ ዊስተን በጥሪው ግራ ተጋብተው ላያበቁ መነጋገሪያውን ከማንሳታቸው የምታናግራቸው የገዛ ልጃቸው መሆኗን ሲረዱ በመገረም የሚናገሩትን አጡ።

‹‹ቨኪ፣ ምን ተፈጠረ?››

በሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቿ ልጅ ለአባት ማብራራቷን ጀምራ እንድ ደቂቃ እንዳለፈ አባት አቋረጧት።

‹‹እንድ ሴኮንድ እንኳ እንዲባክን አልፈልግም፣ ቨኪ። ትረካሽን ራምሲን አትርቢ ያጓምጥሽ. . . እኔ ግን ሁኔታውን በተጥታ ለፕሬዚዳንቱ ልንገር። ራምሲ ከዚህ በፊት የሚያውተው አለው ብለሻል። ስለዚህ ዝርዝሩን ለሱ ታብራሪለታለሽ። ምናልባት ፕሬዚዳንቱ የሚያነሱት ጥያቄ ቢኖራቸው ራምሲ ይመልስላቸዋል። መስመር ላይ ጠብቂ። ኒክ ይተርብልሻል።››

ኸግ ዊስተን ስልኩን እንደተክፈተ አስቀምጠው ወደ ተሳፋሪዎች ክፍል ሲገቡ እንድ አስተናጋጅ ከፊት ለፊታቸው አገኙ።

‹‹ስማ፣ ወደ ፕሬስ ክፍል ሄደህ ኒክ ራምሲ የተባለው ሰው አሁኑኑ እዚህ ድረስ እንዲመጣ ትነግርልኛለህ።›› አዘዙ ኸግ።

የአውሮፕላኑ አስተናጋጅ በፍጥነት በደርዘን የሚቆጠሩ ዘጋቢዎችና የአምድ አዘጋጆችን ወዲያዘው የአውሮፕላን የኋላ ክፍል ሄደ። ከጋዜጠኞች ማማሸቹ ካርታ ይጫወታሉ፣ ሊሎች ያነባሉ፣ እንዳንዶቹ ያናውላሉ። የደቂቃ ማማሸ እንኳ ሳይቆጠር ኒክ ራምሲ ወደተጠራበት በሩጫ ሄዶ

ከፕሬስ ፀሐፊው ፊት ለፊት ገጭ አለ።

‹‹አቤት?››

‹‹ኒክ፣ ልጄ መስመር ላይ ትጠብቅሃለች፣ ከኒውዮርክ።››

‹‹ቨኪ?››

‹‹ኤድዋርድ ሊገድላት ሲል ከሞት ተረፈች። ኤድዋርድ በአንድ ሽብርተኛ የሚነዳ አውሮፕላን ልኮ ሁላችንንም ሊፈጀን በመንኮላኮስ ላይ ለመሆኑ የተጨበጠ ማስረጃ አግኝታለች። ኧረ ለመሆኑ ኤድዋርድ እንዲህ ያለ ነገር ሊያደርግ ይችላል?››

ራምሲ አላመነታም። ‹‹አዎ ያደርጋል።›› አለ።

‹‹ታምንበታለሃ በቨኪ ማስጠንቀቂያ?››

‹‹የተናገረችው ቨኪ ከሆነችና ማሰረጃው ካላት በርግጥ አምንበታለሁ።።።››

‹‹ነገሩ የሚደረገው በዘጠኝ ደቂቃዎች ውስጥ ነው ትላለች። እንዲያ ከሆነ አውኑኑ ለፕሬዚዳንቱ ባሳውቅ ይሻላል። ቨኪ ዝርዝሩን ለመንገር መስመር ላይ ናት። በተቻለህ ፍጥነት ገለፃዋን በማስታወሻ አስፍረህ ፕሬዚዳንቱ ክፍል ድረስ። እኔንም እዚያ ታገኛለህ።››

ራምሲ መልእክቱን ተቀብሎ፣ ስልኩን ዘግቶ ወደ ፕሬዚዳንቱ ክፍል እየተወረወረ ሲሄድ ከስድሳ ሰከንዶች ብዙም አይበልጥም።

ፕሬዚዳንቱ ከቆዳ በተሰራው ተሽከርካሪ ወንበር የእጅቻቸውን መደፎች ጠረጴዛው ላይ አድርገው ተቀምጠዋል። ከጎናቸው በአውሮፕላኑ የአሜሪካ ጦር ከፍተኛ መኮንን በመሆን የተሳፈሩት ጀኔራል ጄድሰን፣ ከፊት ለፊታቸው ደግሞ ኸግ ዊስተን ቆመዋል።

ፕሬዚዳንቱ ሰላምታም አላቀረቡም። ‹‹የዊስተን ልጅ በቲ ማስረጃ እንዳላት አምነህበታል?››

‹‹ጥያቄ የለውም፣ ሚስተር ፕሬዚዳንት›› ካለ በኋላ ራምሲ፣ ቨኪቶሪያ ስለአዲጋው መፈፀም የደረሰችበትን ማስረጃ ባጭሩ ዘረዘረ።

‹‹እንዴት?››

አሁንም ራምሲ ሚስተር ኤድዋርድ ከሽብርተኞች ጋር እየተደራደረ የፈፀማቸውን ወንብድናዎች ይህ የአሁኑ እትዱም የበፊቶቹ ወንጀሎች ተተጥላ መሆኑን በሚያሳምን መረጃ እያስደገፈ አብራራ።

‹‹ለመሆኑ ይህስ መቼ ነው የተወሰነብን?››

የራምሲ አይኖቹ የግድግዳውን ሰዓት ተመለከቱ።

‹‹በስምንት ደቂቃዎች ውስጥ፣ ሚስተር ፕሬዚዳንት።››

ፕሬዚዳንቱ ወንበራቸውን ወደ አንድ ጎን ቦር አድርገው ጀኔራል ጁድሰንን ተመለከቱ። ‹‹ለመሆኑ ለዚህ በረራ የተመደበው ጥበቃ ምን ያህል ነው፣ ጀኔራል?››

‹‹ምንም ጌታዮ። የወታደራዊ ደህንነት አደረጃጀትን ዝቅ ለማድረግ በቅርብ አመታት የወሰዱን ፖሊሲያችንን ሳያውቁ አይቀሩም። በዚህም ምክንያት የሲቪል በረራ ተመስለን ለመጓዝ ነው እትዳችን። ለማንቸውም አሁን የመጀመሪያው ተግባራችን በርግጥ የተጠቀሰው አውሮፕላን በሽብርተኞች እጅ መግባቱን ማረጋገጥ ነው።››

‹‹ባስቸኳይ አረጋግጡ›› አሉ ፕሬዚዳንቱ፣ ነፈሱን ሰልካቸውን ለጀኔራሉ ገፋ እያደረጉለት። ‹‹ነገሩ እውነት መሆኑ ከተረጋገጠ የሚተገበሩ ተግባራችሁ በክልሉ ውስጥ በእየርም ይሁን በአውሮፕላን ተሽከርካሪ መርከበኞችን ላይ የኛ ተዋጊ አውሮፕላን መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ይሆናል። መልስ የምታገኘው በሴኮንድ መሆን አለበት። ምክንያቱም ርዳታ ሊደርስልን የማይችል ከሆነ. . .››

ፕሬዚዳንቱ ንግግራቸውን ከመጨረሳቸው በፊት ጀኔራሉ ሰልኩን አንስቶ ከብሔራዊ የወታደራዊ እዝ ማዕከል ጋር ተገናኝቶ ነበር።

* * *

ጋይለት ዮሱዝ ማዕዳ አይኑ ከአጠገቡ ያለውን ኮምፒዩተር ያነባል። የሚያበረው አውሮፕላን እንደ ጅራታም ኮከብ እየተወረወረ ሽቅብ

በመምህሟ ላይ ነው። የበረራውን ፍጥነት ባንድ በኩል ከባህር ወለል በላይ ያለውን ክፍታና የንዞውን ትክክለኛ አቅጣጫ በሌላ በኩል በሞገዩተሩ አስልቶ አጥፍቶት ከሚጠፋው አውሮፕላን ጋር የሚጋጭበትን የጊዜና የቦታ መጠን ደርሰበታል። በመጨረሻም ደቂቃዎች ፊት ለፊት የሚመለከተው ራዳሩ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ከልል 35,000 ሜማ ከባህር ወለል በላይ የሚበረውን የፕሬዚዳንቱን 747 አውሮፕላን ያሳየዋል። ከዚያ በኋላ የሚተረው በ70,000 ሜማ ክፍታ የሚበረውን የራሱን አውሮፕላን በተሳሳ ወደ አላማው ማብረር ነው።

በአያንዳንዱ ሴኮንድ በረራ ወደ አላማው እየተጠጋ፣ እየተጠጋ፣ የህልፊት ሀይሙቱን ቅርበትም እንዲሁ እያስጠጋ፣ እያስጠጋ በመሄድ ላይ መሆኑን ቢረዳም ማፀዳ ፊጥጋታ አልተለየውም። ከሁሉም በላይ በሀይሙቱ ሲመኘው የነበረውን ሊያገኝ ነው። በቶኪዮ ባንክ የተቀመጠለት ሚሊዮን ዶላር ቢተስበት ከጎስቋላ ወደ ትምጥል፣ ከእከክ ወደ ድሎት ሊያሻጋግርለት ነው። በዚያ ላይ እድሜ ልኩን ከሰው ቢታች ያደረገው የተገፈፈ ክብሩ በዚህኛው ጀብዱ ሲመለስለት ነው። ደሀንና ማፀዳ በፈፀመው ጀብድና ባንክ በተቀመጠለት ገንዘብ እየተምነሸነሸ አለሙን የሚቀዋ ሰው ሊሆን አይችልም። ይህን በማሰብ ላይሆን አይቀርም ማፀዳ እግሩ ወደ ጉድጓድ በማዝገም ላይ ቢሆንም የተጥለቀለቀ ፊጥጋታው ያልተለየው።

ይህ የመጨረሻው በረራ እንደ ሀልም ነበር የሚታየው። ቁንጮት የለ፣ ግራ መጋባት የለ። እንደ ሀለተኛው የአለም ጠርነት ተልእኮው በራዳር መመራት፣ ከጠላት ጥቃት መሸሽ፣ የጠላት ሚሳይሎችን መሸወድ የሚሏቸው ነገሮች አያስጨንቁትም። ባሁኑ ወቅት እሱና አውሮፕላኑ ራሳቸው ሚሳይል ሆነው እየተወረወሩ ናቸው፣ ጠላትን ለመምታት።

ለጥቂት ደቂቃዎች የማፀዳ ሃሳብ ወደ ቤተሰቡ ወጀጅ አሰ። ስጊዜው የሚሰማቸው ሃዘንና ስዘለቂታው የሚኖራቸው ደስታ ታየው። ባለቤቱ በባለቢድ ሞት፣ ልጆቹ አባታቸውን በመቀማታቸው የሚሰማቸው ሃዘን በእእምሮው መጣበት።

ባዚህ ቅጽበት ድንገት፣ ኮምፕዩተሩ መጀመሪያ የማስጠንቀቂያ ምልክት

ከሰጠው በኋላ ራዳሩ ከፊት ለፊቱ 150 ማይል ርቀት ላይ አንድ ምስል አሳየው፡፡ የፕሬዚዳንቱ አውሮፕላን ለእይታ መቅረቡን ወድያውኑ ተረዳ፡፡

ማዕጸ አይኑን ከራዳሩ ሳይነቅል ኪኮ የተባለችው ባለቤቱ ከሶስት ልጆቻቸው ጋር የተነሳችውን ባለቀለም ፎቶግራፍ ከኪሱ አወጣ፡፡ ፎቶግራፉን በመጨረሻው የአፍቅሮትና የስንብት አይን ተመለከተው፡፡ የመጓጉ አመኩን ሲያወጡ ሳይቀር በእይነ-ህሊናው ታዩት፡፡ ተጥሎም የመጨረሻው ቅጽበት በእጁ ነውና ማዕጸ ፎቶውን ሞኑ ላይ አስተምጠ የፕሬዚዳንቱን አውሮፕላን ይበልጥ በግልፅ ማየት ወደሚችልበት አቅጣጫ አውሮፕላኑን ዘወር አደረገው፡፡

አየር ኃይል አንድ የተሰኘው የፕሬዚዳንቱ አውሮፕላን ከርቀት ቢሆንም በራዳሩ ብቻ ሳይሆን በአይኑ ማየት በሚችልበት ደረጃ ቀረበ፡፡ ወርቃማ ጥርሶቹን በሚያፍለቀልቅ ፈገግታ ሳት እያለ ማዕጸ ወደ ኢላማው አውሮፕላን የሚከሰክሰውን የመቆጣጠሪያ ዘንግ ወደፊት ለመግፋት ይዘጋጅ ጀመር፡፡

* * *

ከፕሬዚዳንቱ ክፍል ትይዩ በሚገኘው የስብሰባ ክፍል ሶስቱም ሰዎች በሶስቱ መስኮቶች አሰግገው ወደ ውጭ እየተመለከቱ የመጨረሻውን የውድመት ሴኮንድ ይጠባበቃሉ፡፡ ፕሬዚዳንቱ ባንደኛው፣ ዝግ ዌስተን በሁለተኛው፣ ኒክ ራምሲ በሶስተኛው መስኮት፡፡ ከተከፈተው በር ወዲያ አራተኛው አባላቸው ጀኔራል ጁድሰን የአውሮፕላኑ ራዳር እጥፉ ጠፈሙን አውሮፕላን አትርበ ሲያሳይ ተመልከተው በድንጋጤ ከው ብለዋል፡፡ በስብሰባው ክፍል ላሉት ሶስት ሰዎች ግን ከጠራው ሰማይ በስተቀር የሚታዩቸው ነገር አልነበረም፡፡

የአውሮፕላኑ አብራሪዎች ረዳቶቻቸው ሚስጥሩ አልተነገራቸውም፡፡ ሊሎች መንገደኞችም የሚያውቁት ነገር የላቸውም፡፡ ጉዳያቸውን ሲሰሙ በድንጋጤ ደርቀው ከመሞት በስተቀር ምን መፍትሔ ሊያመጡ ይችላሉ?

የአውሮፕላኑ የኮሙኒኬሽን ማዕከል ከብሔራዊ የደህንነት ጠኪል ቢሮ የተቀበለውን መረጃ ጠቅሶ በሰላይ ሳተላይት አማካኝነት ንብረትነቱ ያልታወቀ ተሞኒ መሳይ አውሮፕላን ህዋ ላይ መታየቱንና በከፍተኛ ፍጥነት

ወደ አየር ኃይል እንድ በመጠጋት ላይ መሆኑን ማስጠንቀቂያ አቀብሏል። ተመሳሳይ ምላሽ ለመስጠት በመሞከር ላይ መሆኑንም ጨምሮ ገልጿል።

የጀኔራል ጄድሰን እጅግ በጣም አስቸኳይ ጥሪ በበኩሉ ከጥቂው እዝ በትርብ ከሚገኘ የመከላከያ ኃይል ጋር ተገናኝቶ የአሜሪካ ሽፋን ሰጭ ተዋጊ አውሮፕላኖች እንዲዘጋጁ እንዲያደርግ ቢያስጠነቅቅም አደጋው የሚፈፀምበትን ትክክለኛ ቦታና ጊዜ መለየትም ሆነ በወቅቱ ደርሶ አደጋውን ለመመከት ያለውን እቅም አስቀድሞ መተንበይ አዳጋች ነበር።

ውጤቱን አስቀድሞ መናገር አስቸገረ። የሁሉም ተስፋ እጥፍ ጠፈው እብድ በሉላ እብድ ቢጠፉ የመሰናክል ቀቢፅ-ተስፋ ብቻ ሆነ።

ኒክ ራምሲ ብቻ አደጋው ይፈፀማል ብሎ ማመን አልሞጥልህ አለው። የምሁር አእምሮው ቢሞት የሚያጣቸውን ነገሮች ዘረዘረለት። ላለማፍቀር፣ ከቪክቶሪያ ጋር ፍቅርን ላለመጋራት፣ የመጀመሪያውን መጽሐፍ ላይጨርስ በእንጥልጥል ለማስተረት፣ ጸጋመኛ አፕራቲፍ እየጠፉ የሀይወትን ክብደት ላለማትለል፣ ልጅ ወልዶ ላለመሳምና ስምን ላለመተካት እንዴት ይሞታል? በጭራሽ አይደረግም።

የድምፅ ማጉያው ጩኸት ነበር ራምሲን ከሃሳቡ የመለሰው። ጀኔራል ጄድሰን የራዳሩን ርቀት ቆጣሪ እያነበበ «ወቸ ጉድ፣ መቶ ማይል ቀረው እኮ. . . ሰማንያ. . . ስድሳ. . .» ይላሉ የአጥፍቶ ጠፈውን ቅርበት ሲገልፁ።

የጀኔራሉ ድምፅ በማጉያው መርገብገቡን ግና ሳያቆም ራምሲ ከቁጥር ውጭ በሆነ መወራጨት እየተንደረደረ ስብሰባው ክፍል ገብቶ አይኑን ጎልጉሎ በመስኮቱ ወደ ውጭ ይመለከት ጀመር። ሰማዩ ግን አሁንም ባዶ ነው። በዚያው ደቂቃ ግን ራምሲ የጀኔራሉ ጩኸት ጆሮው ላይ ባረቀበት። «ወይኔ፣ እዩት እዚያ ላይ! ከጎጀዋ እንደምትወጣ የሊሊት ወፍ ዘሮ ሊልበን ወደታች እየወረደ ነውኮ!»

ራምሲ ልቡ ከደረቱ ዘሎ የሚወጣ እስኪመስል ድት ድት እያለ ቀና ብሎ ሲመለከት ትልት ብርማ ቀለም ቆርቆሮ ማየት ቻለ። ብርማው ቆርቆሮ የማፀዳ አውሮፕላን ነበር። አውሮፕላኑ የሚታየው እጅግ ወደ ሰማይ ርቆ ቢሆንም በረራው ግን በቀጥታ ወደነሱ አቅጣጫ ነበር። ደሞ የፍጥነቱ ነገር፣

ቱልቱል ሲውሀዝ። በተረበ መጠን ለአይን እየጎላ ሄደ። በመጨረሻው የአውሮፕላኑ ቅርፅ ብቻ ሳይሆን ሞዴሉም በግልህ ይታይ ጀመር።

‹‹ወይኔ፣ ልክ እንደሚሳይል ነው› የሚመረመረው።›› ጀኔራሉ በሞንተት መስኮቱን በቡጢ ደለዙት። ‹‹በሰዓት ሁለት ሺ ማይል ተምዘግዝጎ ደረሰብን።››

‹‹አልቆልናል በታ›› አሉ ፕሬዚዳንቱ፣ ከንፈራቸውን ከመንከስ ሌላ የሚያደርጉትን እጥተው።

በዚህ ጊዜ ራምሲ በአይኑ ጠርዝ አንድ ሌላ ብርማ ቆርቆሮ፣ እንዲያውም ሁለት ቆርቆሮዎች ታዩት። ወዲያውኑ ቱልቱል እየተመለከተ ሮጫ።

‹‹እዩ . . እዚያ ታች እዩ››

‹‹አሃ፣ ኤፍ 15 የረጅም ርቀት ተዋጊዎች።›› ጀኔራሉ ነበሩ። ‹‹የሻ ተዋጊዎች!››

‹‹ጋ፣ አያችሁ!›› ፕሬዚዳንቱ ባረቱ። ሁሉም ሰዎች የተራቀቁት የመካከለኛ ርቀት አየር ለአየር ሚሳየሎች ከሁለቱ ሽፋን ሰዎ አውሮፕላኖች ሲወነጨፉ ተመለከቱ። መብረቅ በሚመስል ፍጥነት ሚሳይሎቹ ወደ አጥፊው አውሮፕላን ተወነጨፉ።

ራምሲ አፉን ቧ አድርጎ ከፍቶ አጥፊው አውሮፕላን ከላዮቹው ላይ ተዘብዝ ከራሱ አውሮፕላን ጋር ሊነካካ ጥቂት ሲቀረው መንትዮሽ የሚመስሉት ሚሳይሎች ደግሞ አጥፊውን አውሮፕላን ሊነኩ ጥቂት ሲቀራቸው ለዩ።

የትኛው ይሆን መጀመሪያ ጠላቱን የሚያጋየው? የሞት ጥላ ባንደኛው ላይ ማረፉ መቼም አይቀርም።

ከሁለት አንደኛው በርግጥ ተፈፀመ። የትኛው እንደተፈፀመ ግን ራምሲ ለተወሰነ ጊዜ ሊያውት አልቻለም። የተሳፈረበት አውሮፕላን እንደቁመማ ተንዘፈዘፈ። በዚያው ቅፅበት ሰማያዊው ሰማይ ብቻ ወደ ግራጭ የብርቱካን ቀለምና ቅርፅ ተለወጠ። አጥፊው አውሮፕላን መጀመሪያ ወደ ኃያል

ነበልባልነት ተለውጠ ኃላም ተከሚሂድቅ ወደ ውትያጥስ ሲመድት ለመለየት ለራምሲ ጥቂት ጊዜ ሳይወስድበት አልቀረም።

እየር ኃይል አንድን በኃይል እንዲንቀጠቀጥ ያደረገው በአጠገቡ የተፈጠረው ፍንዳታ ኖሯል። አውሮፕላኑ መንቀጥቀጡን ባያቆምም ቀስ በቀስ እየተስተካከለ ንሥሩን ቀጠለ። ያለማቋረጥ ወደ ለንደን . . .

* * *

ከእየር ኃይል አንድ ጋር ያደረጓቸውን የስልክ ንግግር ከማጠቃለሷ በፊት ቪክቶሪያ አንድ የምትናገረው ነገር ተርታት ነበር። «ለአንተና ለእባቱ እዐልያላችኋለሁ» ካለች በኋላ በመጨረሻው አንድ ቃል አመለጣት። «ኒክ አፈቅርሃለሁ» አለች። ይሁንና ራምሲ የተናገረችውን ከመስማቱ በፊት ስልኩን መዝጋቱ ታወቃት።

ስልኩን በስፍራው ካስቀመጠች በኋላ እንኳ ቪክቶሪያ በመደወያው ሳጥን እንደተጥለረች ቀረች።

ያልተጠናቀቀ ስራ፣ አንድ የሚቀረው ስራ፣ አንድ ሌላ የስልክ ጥሪ ማድረግ አለባት።

ለሻምበል ዚሞቲ ከራውፎርድ፣ ለኒውዮርክ ከተማ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል መደወል አለባት። ራምሲን ባነጋገራችበት ጊዜ የሚተላለፉ ተግባሯ ምን እንደሆነ ጠይቃት በዚያ የጥድፊያ ንግግር ምን እንደምታደርግ ነግራው ነበር። ራምሲ ግን «ኤድዋርድን ብቻሽን እንዳትጋፈጭው» ሲል አስጠንቅቋታል። ተጥሎም የሻምበል ከራውፎርድን አድራሻ ሰጣት። ሻምበሉ በተለይ የራምሲ ጓደኛ ነበር። «ሁሉንም ሳትደብቂ ንገሪው። ምን መደረግ እንዳለበት እሱ ያውቃል» ብሏታል።

ሻምበሉን አግኝታ ሪቢን ካስተዋወቀች በኋላ ታሪኩን በሙሉ አብራራችለት።

«አጣዳፊ እርምጃ እንድንወስድ መጨረሻ ላይ የነገርሽኝ ብቻውን ያስገድደኛል።» አረጋገጠላት ከራውፎርድ። «ለተተሩት ወንጀሎች እርግጠኛ ማስረጃ ማግኘት አለብን። በትድሚያ ግን እየር ኃይል አንድ

አሁን በምን ውኔታ ላይ እንዳለ ማወቅ ይኖርብናል። ያም ሆነ ይህ አንቺና የኤድዋርድ ባለቤት በግድያ ሙከራ ክስ መመስረት አለባችሁ። አሁኑኑ ወደ ኤድዋርድ መኖሪያ ሀገሃ ልትሂድ ከቻልሽ እኛንም አዚያው ታገኝናለሽ።››

ከግሮሰሪው እንደወጣች ታክሲ ይዛ ወደ ኤድዋርድ ሀገሃ ስትጓዝ ሞንተቲ መጨረሻው ደረጃ ላይ ደረሰ። ቢያንስ አራት የሚሆኑ የፖሊስ መኮንኖች በኤድዋርድ ሀገሃ መግቢያ በር ዙሪያ ቆመው ታዩዋት። ተጥሎ ምን እንደሚሆን ልታስብ ሞከረች።

‹‹እንዴ፣ ምን ችግር አለ?›› አላት የታክሲው ሾፌር የፖሊሶቹን ትርምስና የቪክቶሪያን ተማድሮ መውረድ አስተውሎ።

‹‹ብዙ ችግር›› አለች ቪክቶሪያ። ‹‹ጋዜጣ አንብበህ ትረዳለህ።››

አንድ ወንዳወንድ የፖሊስ መኮንን ወደ ቪክቶሪያ ጠጋ ብሎ ‹‹አንቺ ነሽ ቪኪ ዊስተን? ከራውፎርድ ነኝ። ሁላችንም እንደምታይው ስፍራችንን ይዘናል። ኤድዋርድ ቤቱ ውስጥ ያለ ይመስልሻል?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹የዛሬውን አደጋ በማሳተም ላይ ስለሚሆን ያለጥርጥር ቢጋዜጣው ዝግጅት ቢሮ ነው የሚገኘው፣ ስድስተኛ ፎቅ ላይ ልመስዳችሁ እችላለሁ።››

‹‹የለም፣ እንቺ እንኳ እዚያ አካባቢ ባትገኝ ነው የሚሻለው። እደግሻ ነው።››

‹‹ግን ኤድዋርድን እንዴት ትለዩታላችሁ?››

ሻምበል ከራውፎርድ በክናፍሩ ግማሽ ፈገግ ብሎ ‹‹የሱ መልክ ላለፋት ሳምንታት የሁላችንም አይን ያረፈበት መልክ ነበር። ‹ምንተስኖት› ነበር አይደል ታይምስ መጽሔት የሰጠው ስያሜ? እንዴት ይጠፋኛል?››

ሻምበሉ ወታደሮቹን ወደ ሀገሃው ሲያሰማራ ቪክቶሪያም ሻምበሉን ይቅርታ ጠይቃ ወደ ስድስተኛ ፎቅ ለመውጣት አሳንሰሩ ውስጥ ገባች። ‹‹የግድ መገኘት አለብኝ፣›› አለችው።

ሻምበል ከራውፎርድ ስድስተኛ ፎቅ ላይ ከግማሽ ወታደሮች ጋር እንደደረሰ የቀሩት ወታደሮች ከደረጃው እየወጡ እስኪመለሱለት ይጠባበቅ

ጀመረ። እንደደረሰለትም በር አካባቢ ቁመው እንዲጠባበቁ ትዕዛዝ ሰጥቶ ማማሾቹ ፖሊሶች ሬክርድ ዝግጅት ክፍል ውስጥ እንዲገቡ በእጅ ምልክት ጠቆማቸው።

ቪክቶሪያ ዝግጅት አዳራሹ ተንደርድራ ስትገባ ከራውፎርድና ወታደሮቹ ተከተሏት። የዝግጅት አዳራሹ በሰራተኛ ጠም ብሎ የሞላ ሲሆን ቪክቶሪያና ፖሊሶቹ በወጣ አዳራሹን አልፈው በስተጀርባ ወደሚገኘው የባለስልጣኖች ቢሮ አመሩ። ቀስ በቀስ አዳራሹ ውስጥ እንቅስቃሴ ደኅዶ ይሰራ የነበረው ሰራተኛ አንድ በአንድ ከእንቅስቃሴና እያሰለ የፖሊሶቹን መግባት ሲመለከት ስራውም እንዲሁ ቀጥ አለ።

ቪክቶሪያ የራሷን ጠረጴዛ በማለፍ ላይ ሳለች በኢንጣሚ ሰልኳ ሲፈነዳ ሰማችው። ትታው ልትሄድ ከመነታች በኋላ አነሳችው። ሮዝንበለም ነበር ከሞይት ጋውስ። አየር ኃይል አንድ ከአደጋው ሙትረፉን አበሰራት። ሰልኩን ገና ሳትዘጋ ቁጥጥር ያሉት ጠንቅቃቹ በእፎይታ ሲፍታቱ ታወቃት።

የምስራቹን ለሻምበል ከራውፎርድ አበሰረችለት። «እንግዲህ የቀረን ጸጣመኛ እንዳይፈፀም ቁንጮውን መምታት ነዋ. . .» አላት ከራውንፎርድ ፊገግታ ሳይለየው።

ወደ ኤድዋርድ ቢሮ ጉዞው ቀጠለ። ቪክቶሪያ ሁለንም ፖሊሶች ቀድማ ወደ አሳንሟሩ በሐፊ ወደ ኢስቲል ቢሮ እንደገባች ኢስቲል አንገቷን ከታይፑ ቀና አድርጋ ስራዋን ያቋረጠችችን ጋዜጠኛ በተሰላቸ አስተያየት እየተመለከተች «ምን ፈለግሽ?» በትል ጠየቀቻት።

«ሚስተር ኤድዋርድ ይኖራሉ? » ቪክቶሪያ ጠየቀች።

«አሉ፣ ግን ከሚስተር ዣሪ ዴትዝ ጋር ሳይሆኑ አይተሩም። እስኪ ልደውልላቸው. . .»

ከራውፎርድ ዘው ብሎ ገባ። በዚህ ወቅት «እጅሽን እንዳታንሽ አመቤት። አለታሽን የምንፈልገው በድንገት ለማግኘት ነው» አለ ከራውፎርድ፣ ቪክቶሪያ የኤድዋርድን ቢሮ እንድትከፍት በራሱ ምልክት

እየሰጣት።

ቪክቶሪያ በሩን በርግዳ ስትከፍት ፖሊሶቹ በትጽዕት ተድመዋት ወደ አሳንሣሪው ቢሮ ገቡ። ተከትላ እንደገባች ሻምበል ከራውፎርድ «እዚህ ማንም የለም» ሲል ሰማችው።

በዚያው አፍታ ከኤድዋርድ ወደ ሃሪ ዴትዝ ቢሮ የሚያሳልፈው የውስጥ ለውስጥ መገኪያ ተከፍቶ ኤድዋርድ አርምስቱድ ወረቀቶችን ታትር ገባ። ቢሮው ውስጥ ያሉትን እንግዶች ሳያስተውል ከጀርባው ተከትሎት ወደሚገባው ረዳቱ ወደሃሪ ዴትዝ ዞር ብሎ ከት ብሎ ይስቅ ነበር። ቪክቶሪያ ሊላ ሰስተኛ ሰው በክፈል እየታያት መሆኑና ሰውየውም ጉስ ፖጋኖ ሳይሆን እንደማይተር ጠርጥራለች። ኤድዋርድ ግን ሳቁን ሳያቆም ከኋላው ካለው ረዳቱ ጋር መነጋገሩን እንደተጠለ ነው።

«ተሰምቶ የማይታወት ፍንጸታ። ጃክሲን ግሮቱ ሲፈፀም ሰማዩ እንደ መብረቅ የተሰነጠቀ መስሎ ነበር አለኝ። ታሳቱ ሰራ ተሳካ። ከንግዲህ.....»

«አለታ» ሃሪ ነበር። «ሽረ ዞር ብለህ እያቸው...»

ሻምበል ከራውፎርድ ወደ አሳንሣሪው አመራ። «ኤድዋርድ አርምስቱድ በወንጀል ሴራና በማድያ መከራ በቁጥጥር ስር ውለሃል።»

በዚህ ወቅት ቪክቶሪያ ከፖሊሶቹ ፊት ወጥታ ከሻምበሉ ጎን ገቡ አለች። ኤድዋርድ የአይን መኖር ሲያይ አይኑ ተጓልጉሎ ሲወጣ ደረሰ።

«አመለጥክ፣ እኔና ሃና። እና ሁሉንም ተናገርን።» ቪክቶሪያ በእልህ ምላሷ ቢተሳሰርባትም ንግግሯን ተጠለች። «ባሬ ምንም ታሪክ አልተሰራም። ምንም ዜና የለም። የሰማችሁት ፍንጸታ የገዛ ራሳችሁ ትዋረኛ በሚሳይል ሲመታ ነበር። አየር ኃይል እንድ በሰላም በመንገዝ ላይ ነው።»

ኤድዋርድ የሰማውን ማመን አቅቶት ራሱን በእሱታ ይነቀንት ነበር። ተጥሎም አይኖቹ እንደፈጠጡ ከቪክቶሪያ ወደ ፖሊሶቹ ተንከራተቱ። እግሩም ወደኋላ እያፈገፈገ የገባበትን በር ፍለጋ ይዟል።

«መብትና ግዴታውን እንብቡለትና ሙሰዱት፣ ልጅት።» የከራውፎርድ

መመሪያ ነበር።

«አይቻልም» ኤድዋርድ በንዴት ሥኒ የተጠጋውን መዝጊያ በርግዶ ከፍቶ ወደኋላ መንደርደሩን ተጠለ።

በዚህ ጊዜ ሻምበል ከራውፎርድ በደመነፍስ ሽጉጡን አውጥቶ ወንጀለኛው ላይ አነጣጠረ። ይሁንና ቪክቶሪያ በትጽበት የሻምበሉን ክንድ ሥምት አድርጋ ያዘች። «የለም. . . የለም፣ አይሞትም። ባለቤቱ. . . ይሞም ቢወጣም ማምለጫ በር የለም። አእምሮውን ስለሳተ ነው።»

ኤድዋርድ በሃሪ ዴትዝ ቢሮ በኩል አልፎ ወደ ኮሪደሩ ሲያመራ በተበረገዱት በሮች በኩል ለፖሊሶች ይታዩቸዋል።

«አልሰደውም» ሻምበል ወንጀለኛን ተከትሎ ሲሮጥ ቪክቶሪያም ተከተለች። በመጨረሻ የተጠጉት በህንፃው ሜፍ በረንዳው ላይ ነበር። ኤድዋርድ የምትከተለውን ሴት ሥር ብሎ ሲመለከት የተኛ እጅን ጠምጣ ጣት በሚያንገራግር መልእክት ተስቦ «አንቺ. . . አንቺ ውሻ! ሞትኩ ለወሬ . . . ከንግዲህ ሪፖርተሬ ሆነሽ የምትሰሪ መስሎሻል. . . የክፍለ ዘመኑን ታላቅ ታሪክ ታላቅ ዜና ታጨናግፊብኝ አንቺ ጠልጣላ እኮላሪ. . . አሁን ሁላችሁም. . . ለቀት አድርጉኝ. . . ሽማግሌ አባቴን ማማናት አፈልጋለሁ! የማነጋግረው ነገር አለኝ!»

ከንግግሩ ጋር የበረንዳውን ባንኒ ዘሎ ረግፎ ወደ ላይ ከተፈናጠረ በኋላ ቁልቁል መውረድ ጀምሮ ከአይን ተሰወረ።

ቪክቶሪያ ጩኸቷን ብትለቀውም ሰውየው ግን ተሰውሏል። ቪክቶሪያና ከራውፎርድ ወደ በረንዳው ባንኮኒ ሂደው ከሰድስት ፎቅ በታች የሚታየውን እውራ ጎዳና ቁልቁል ተመለከቱ። ቪክቶሪያ መመልከቷን አለማቆሟን ሲመለከት ከራውፎርድ ክንዷን ያዝ አድርጎ እያቦራት «ሲበዛ ሩቅ ነው፣ መራቱ። ምን እንደምትጠብቂ አልገባኝም?» አላት።

«ሞቷል በቃ?»

«አበቃ።»

ከበረንዳው ተነስተው ወደ ሃሪ ዴትዝ ቢሮ በመመለስ ላይ እንዳሉ

ኤድዋርድ ክፍቱን በተወው በር በኩል ካለው ኮሪደር አካባቢ የተኩስ ድምፅ በመስማታቸው ለእፍታ ደንግጥ ብለው ቆሙ።

ሁለቱ ፖሊሶች ተኩሱ በተሰማበት አቅጣጫ ሲሮጡ ሻምበሉና ቪክቶሪያም ተከተሏቸው። ከሁለቱ ፖሊሶች መካከል አንደኛው ከሃሪ ዴትዝ ቢሮ ሲወጣ ቪክቶሪያንና አለቃውን ሻምበል አግኝተው። «እዚህ የነበረው ሰው ነው. . . ራሱን ገደለ. . . የጣዘ ሞንትላቱን አትምሰታል» አላቸው።

ከራውፎርድ በጥያቄ አስተያየት ወደ ቪክቶሪያ ተመለከተ። «ማነው ደሞ እሱ?»

«የኤድዋርድ ልዩ ረዳት፣ ሃሪ ዴትዝ።»

ከራውፎርድ ከልቡ ሳቀ። «የፍርድ ቤትን የስራ ጊዜ እየቆጠቡ ናቸው።»

በመጨረሻው የሃሪ ዴትዝ አስከሬን ተነስቶ፣ ሻምበል ከራውፎርድ ከሀንግው በመውጣት ላይ እንዳለ ቪክቶሪያ ከንዱን ያዝ አደረገችው።

«ሻምበል» አለች ቪክቶሪያ፣ «የኤድዋርድ መፈጥፈጥ. . .»

«ምን ሆነ?»

«እንዳየኸው ድንግተኛ አደጋ ነበር።»

ከራውፎርድ ጋዜጠኛዋን ለረጅም ጊዜ ሲመለከታት ቆየ። ከዚያ ከትከሻው ሰበት አለ። «ይሆናል። የፊለማሽውን ስም ልትሰዱው ትችያለሽ። በመጨረሻ የራስሽን ብቸኛ ታሪክ ለማግኘት በትተሻል። እውነትም ሞትኩ ለወሬ።»

* * *

ታሪኳን ዕፋ ከማሳተሚ በፊት ግን ቪክቶሪያ አንድ የቀራት ተግባር ነበረ። በቀጥታ ፓሪስ ደወለች።

ስልኩን የተቀበላት ሲድ ሉታስ ነበር። ወዲያውኑ ካርሎስ ስለሚገኝበት ሁኔታ ጠየቀችው። ሉታስ ግን አቋረጣት። «ቪኪ፣ አንድ ሚስጥር

ልንገርሽ። ኤድዋርድ አርምስቱድ የካርሎስን መጠለፍ ማየትሽን ካለማመኑም በላይ እኔ እንኳ ራሴ ታሪኩን እንድከታተል እንደማይፈልግ በዝርዝር ነግሮኛል።››

አዲሱን ታሪክና የኤድዋርድን አሟሟት ልታብራራለት ካሰበች በኋላ ጊዜው አሁንም ለያ ወርት መሆኑን አስተዋለችና በተታራኒው ወሰነች።

‹‹ሲድ›› አለች ለጊዜው። ‹‹ኤድዋርድ እንድትከታተል ያልፈለገው የካርሎስ ጠላፊዎች የራሱ የኤድዋርድ ትጥረኛ ሽብርተኞች በመሆናቸው ነው።››

‹‹ምን! ምን አልሽኝ?››

‹‹ትሰማኛለህ? ማብራሪያ አትጠይቀኝ። ጊዜ ያጥረኛል። ቂት ስለሁለም ነገር ትደርስበታለህ። ብቻ እመነኝ፣ ኤድዋርድ ሽብር ፈጠራን መነገጃ አድርጎት ነበር የከረመው። ይልቅስ የኤድዋርድን ፖሊሶች ትጥረኞችና ካርሎስን እንዲፈለጉ ጠቁምልኝ። የቀረውን ታሪክ ነገ ራሴ እንደማብራራልህ ቃል እገባለሁ። አሁን ግን በፈጠረህ አንድ ነገር አድርግ። በተቻለህ ፍጥነት።››

‹‹የምትናገሪው አንድ ሃሰት ቢኖበት ቨኪ፣ . . ኤድዋርድ ከሥራ ያስወጣኛል፣ ፖሊሶችም በዋላ አይለቁኝም።››

‹‹እንዲያውም ትሸለማለህ ሲድ፣ በኔ ይሁንብህ። ይልቅ ባሁኑ ደቂቃ ያልኩህን አድርግ። እሽ?››

‹‹እሽ ቨኪ፣ ባፈውኑ ጋማቸውን አሳብታቸዋለሁ። ሪዮ ጀነሽ ቁጥር ሶስት አይደለም ጠለፋት ያልሽኝ?››

‹‹ትክክል።››

‹ሞተ ነገሩ› አለችና ቨክቶሪያ ወንበሯን ወደ ጠረጴዛው አስጠጋችው። ‹ከንግዲህ ታሪኩ ይፃፍ።››

የምትፅፈው ታሪክ በነገው ጋዜጣ የመጀመሪያ ገፅ መሪ ዜና ሆኖ የሚወጣ ነው።

ብዙ ሰዓቶች ፃፈች። ሰራተኛው እየወጣ አዳራሹ ባዶውን እየቀረ፣ ዐጥ እረፍ እያለ ነው። ቪክቶሪያ ታሪኳን ዕፋ በጨረሰችበት ወቅት ጊዜው ለአይን ያዝ ማድረግ ጀምሮ ነበር። ሰርዛ ደልዛ ያወጣችው የመጨረሻ ረቂት ወዲያውኑ ለታይፕ ቀረበ። «ምንተስኖት» ተብሎ የተጠራው የጉራሴ ንጉስ በመሃያ ብታቱ ክፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ተብሎ በታመነበት ወቅት የተከሰተው ድንገተኛ ውድቀት፣ ሀይውቱ፣ ድልቂቱ፣ ለዜና ያለው ዝንባሌ፣ የማይዘነጉት አብይ ዜናዎቹ።

በመጨረሻ ከወንበሯ ተነሳች። በተጥታ የሄደችው አሊ ማክ አለስተር ቢሮ ነበር።

ካቀረቀረበት ቀና ብሎ እያት አለ። «ጨረስሽ?»

«ሁለንም» አለች ቪክቶሪያ ጽሁፉን ጠረጴዛው ላይ እያስተመጠች።

«ደህና እደር።»

* * *

ስምንት ቀናት አለፉ።

አገሩ የሚመለስበት ቀን ምሽት ደረሰ። በማንቸውም ደቂቃ ሊመጣ እንደሚችል ስለምታውት ቪክቶሪያ ቤቷን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ለማስዋብ የማታደርገው ጥረት አልነበረም።

የከረመችበት አፓርታማ ሲታደስ በተለይም ኪም ነስቢት የሞተችበት ሶፋ በአዲስ ሶፋ ሲለወጥ መመልከቱ ብቻውን ልዩ ርካታ ሰጥቷት ነበር ያመሸው።

ግላሞን ተጣጥላ ቅባትና ሽቶውን ተቀባብታ ከፓሪስ ያመጣችውን አዲስ የለሲት ልብስ ለባብሳለች። ከንግዲህ የሣፊውን የደስታ፣ የፈንጠዚያ ምሽት ስትምነሽነሽ ለማሳለፍ የቀራት ቀን ላይ ግዚታ ካስተመጠችው ጠርሙስ ሻምፓኝ እየተመተመች ራምሲ እስኪመጣ መጠበቅ ብቻ ነው።

የአዲሱን የሶፋ አልጋ ትራስ ተደግፋ ጠርሙሱን ከፈተችና በመለኪያ እየቀዳች ትተማምስ ጀመር። ግማሽ ሰዓት ሳይሞላት አራተኛውን መለኪያ

ማታ ጀምራ ነበር።

የበሩ ደወል ድምፅ በተሰማበት ወቅት አምስተኛዋ ላይ ደርሳለች። መለኪያዋን ኮሞዲኖዋ ላይ አስቀምጣ ወደ በሩ ተንደረደረች። እሱ መሆኑን ስለምታውቅ ማንነቱን ለመጠየቅ አልተጨነቀችም።

ኒክ ራምሲ ታይፕና የቢሮ ቦርሳ ተሸክሞ ፈገግ እንዳለ ወደ ውስጥ ከገባ በኋላ እቃዎቹን አስቀምጦ ቪክቶሪያን እቅፍ አድርጎ ወደ ላይ ካነሳት በኋላ መልሶ ወለሉ ላይ አቆማት።

እንደተታቀፉ ተጨማጨሙ።

‹‹ደህና መጣህ፣ ኒክ?››

‹‹እድሜ ላንቺ›› አለ ራምሲ። ‹‹ልብስሽን ብታወልቂ ባታወልቂ ደንታየ አይደለም።››

‹‹አወልቃለሁ›› አለች እየተፍለቀለቀች።

እሱም ጃኬቱን አወለቀ። ‹‹ለመሆኑ አንድ መለኪያ ሻምጋኝ አስተርፈሽልኛል?››

‹‹እዚህ አለልህ›› አለች በላዶ እግሯ ወደ ጠረጴዛው ሂዳ ከሻምጋኙ በለላ መለኪያ እየቀዳች። ይህ በእንዲህ እንዳለ ራምሲ ከራቫቱን አውልቆ የሸሚዙን ቁልፎች በመጭመት ላይ ነበር። ‹‹አየሽ ቪኪ. . .?››

‹‹ላፊ አዳርህ እዚህ ነው›› አለችው አጽርጣ። ከለበ ሳቀ። ‹‹እንዲህ ደፍረሽ ትጠይቂኛለሽ ብየ አላሰብኩም ነበር።›› ሸሚዙንና ሱሪውን አወለቀ። ‹‹የት ነው መታጠቢያ ክፍልሽ? አሃ. . . እየሀት እትነሽ፣ ቶሎ እመለሳለሁ።››

ራምሲ ወደ ገላ መታጠቢያው እንደሄደ ቪክቶሪያ አልጋው ላይ በጀርባዋ ተንጋላ ናፍቆቷን የምትወጣበትን ደቂቃ ትጠብቅ ጀመር።

ከብዙ ጊዜ ወዲህ እንዲህ ቀለል ብሏት አታውቅም።

አምስተኛዋ መለኪያ ፈልጣ ስድስተኛ ቀዳች። ቀጥሎም እንትልጥ

የተመጣጣኝ ስለመሰላት ስድስተኛውን ጨለማ ሰባተኛው ላይ ገባች።

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ራምሲ በውስጥ መታንታ ብቻ ከመታጠቢያው ክፍል ብቅ አለ። «ቪኪ!»

መልስ አልሰጠችውም። በአልጋው ዙሪያ ተራምዶ ቁልቁል ተመለከታት። ከጎኗ ብርድ ልብሷ ላይ ተኝታ አይኗን ከድናለች። አተነፋፈሷም ከዝለት የተነሳ በተከፈተው አፏ ነበር። ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዷታል።

ሳትም ብስጭትም እየከጀለው ራምሲ ብርድ ልብሱን ገለጥ አድርጎ ከጎኗ ተኛ። ለዛሬ እሱም መንገደኛ ስለሆነ አይናቹን እንደከደነ ድካሙ ያለ እንቅልፍ እንደሚወስደው አላጣውም። ጧት ደግሞ ሁለቱም በህይወታቸው ከመቼውም የበለጠ ደስተኞች ሆነው ገላ ለገላ ተዋህደው እንደሚነቃ ያውቃል።

ተፈፀመ

የተርጓሚው ሌሎች የትርጉም ሥራዎች

ጉድ ሲናፕ

Des perfume

Patrick SÜbkind

መጽሐፍ አንብቦ ፊልሙን ማፈላለግ የወግ ነገር ነው። ለምሳሌ የKunderaን ‹‹The unbearable lightness of being›› ካነበብኩ በኋላ ፊልሙን አፈላልጌ አይቻለሁ። የFyodor Dostoevskyን ‹‹The Gambler››ን እንዲሁ፣ ከእነዚህ ሁሉ የተለየብኝ ‹‹ጉድ ሲናፕ›› (Des perfume) ነው። መጀመሪያ ፊልሙን ‹‹The Perfume›› በሚል ርዕስ አየሁት፣ ወደድኩት፣ መጽሐፉ ከፊልሙ በላይ እንደሚሆን አልተጠራጠርኩም። አፈላለግኩ፣ አፈላለግኩ . . . አጣሁት። በመጨረሻ ግን ‹‹በፈረስ የፈለግሁት . . .›› እንዲል ከእናት ቋንቋው ከጀርመንኛ ወደ ቋንቋዬ አማርኛ ተመልሶ ቤቱ ድረስ መጣ። አንብቤ ጨረስኩት፣ በእርግጥም ግሙቱ ይዞልኝ ኖሯል፣ መጽሐፉ ከፊልሙ በላይ የላቀ ነበር፣ ደገምኩት. . . .

. . . . ‹‹ጉድ ሲናፕ›› የሰው ልጅ ሕልውና አጭንቅ ቋፍ ተንጠልጥላ ሁለመና በጠረን ኃይል ሥር የሚወድቅበትና መሥዋዕት የሚቀርብበት፣ እንኳን ሊሞከር ታስቦ የማያውቅ ድንቅ ሥራ ነው። ይኼን መጽሐፍ አንብቦ ሌሎችን ላይጋብዙ ማለፍ የማይቻል ቢሆንብኝ ‹‹እነሆ›› አልኳችሁ። አንብቡትና መጽሐፉን ከእኔ ጋር አጣምራችሁ ፍርዳችንን ወዲያው - - -

ዓለማየሁ ገላጋይ
ደራሲና ሐያሲ

አመዳፋሽ

የተላከችው በግዙፍ ግብራኃይል የማይከናወን እጅግ አደገኛ የሆነ ግዳጅ እንድትፈፅም ነበር። በጠላት እጅ በወደቀ ክልል ገብታ፣ ቁጥር ስፍር የለሰው የጠላት ወታደር ሰፍሮ እንደጉንዳን በሚርመሰመሰባት እጅግ ቁልፍ የወደብ ከተማ ላይ ቁጢጥ ብላ፣ ከመኖሪያ ኢኮኖታማዋ ስር ዳናሞን ለመያዝ ያደፈጡ የሚያስፈሩ አዳኖቿን ከምንም ሳትቆጥር በመገናኛ ራዲዮዋ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ምስጢራዊ መረጃዎችን ለወገን በማስተላለፍ ታላቅ ጀብዱ ፈጽማለች. . . . .መጨረሻዋስ?

* * *

"ጋ ምን ያህል የምትፈልገው ሰላይ ቢሆን ነው ይህ ሁሉ ሽብ-ረብሀ?"

"እኔ ብቻ አይደለሁም፣ መላው ጀርመን በመብራት የምትፈልገው ሰላይ ነው።"

"ይኸን ያህል ጠቃሚ ሰላይ ነው ማለት ነው?"

"ወዳጀ ጊልበርት፣ በወገንም ሆነ በጠላት መስፈርት የአንድ ሰላይ ዋጋ የሚተመነው በሰላዩ ሰላይነት አይደለም፣ በጨበጠው መረጃ ከብደት እንጂ።"

* * *

"ሰላይህን በጥምር ስለላ ተግባር በምትጠረጥርበት ጊዜ የምትገለገልበት አንድ መሠረታዊ መርህ አለ። ሰውዬው ብልጫ ያለው መረጃ እያቀበለ ያለው ለማንኛው ነው? ላንተ ወገን ወይስ ለተቀናቃኝህ? ላንተው ወገን ከሆነ ሰውዬውን ቀጥል ትሰዋለህ። ለጠላትህ ወገን ከሆነ ግን. . . . "

* * *

"ጽናትና ከሀዲት. . .ሰላይና ጥምር ሰላይ. . . ባንዳና የውስጥ አርበኛ የገዘ ልብ የማይታመንበት . . የሥነ-ልቦና ጦርነት ቋያ የሚቀሰቀሰብት. በዓይነቱ የተለየ. . . . ."

ዶላስ ኒውስ።

"በሴራና በልብ ሰቀላ የተሞላ! . . . . . አስጨናቂ ስለላ!"

ጆን ባርካሃም ሪቪውስ።

"ጋብ በማይል እደጋ የታጨቀ. . . . . እጅግ በጣም ማሩም መጽሐፍ!"

ኪን ፎሊት።

"ዘጥቂት ታዋቂ የስለላ መጻሕፍት አንዱ! . . . . . "

ቺካጎ ትሪቡን።

"አመዳፋሽ. . . . . ደራሲውን ከማይተዉ ድንት ደራሲያን ጎን የሚያስቀምጥ ብርቅ ሥነ-ጽሑፍ!"

ሎስ አንጀለስ ዴይሊ ኒውስ።

እፎይታ

«እንደ እፎይታ ገጽ በገጽ ልብ የሚያንጠለጥሉ መጻሕፍት ጥቂቶች ናቸው።»

ሉምል ቤር

እፎይታ - ፈረንሳዊው ደራሲ አሌክሳንደር ዱማስ (1802-1870) በመላ አውሮፓ «የድርሰት ሩብራክ» ተብሎ እንዲጠራ ያደረገ ብርቅ መጽሐፍ ነው።

እፎይታ - እውቅ ሐያሲያን «የዱማስን ድርሰቶች የተቸ አልነበረም፣ የለም፣ ሊኖርም አይችልም» ብለው ዋቢ እንዲያመሰሉት ያደረገ ተአምረኛ ድርሰት ነው።

እፎይታ - ደራሲውን «የሥነ-ጥበብ ቲንሬ» ካሰኙት ሥራዎቹ ውስጥ የጎላውን ድርሻ የያዘ ስሜት ሞጋች ልቦለድ ነው።

እፎይታ - ፈረንሳውያን ነሥኙት፣ ደራሲውን በአንድ ወገኑ ከጥቂር በመወለዱ እንዳያንቋሽሹት ጨንቋቸው «ባርነቱን አስረሳን እኮ» እንዲሉ ያስገደደ አፍ የሚያስይዝ መጽሐፍ ነው።

ከጀመሩት የማያስቀምጡት እጅግ አንጊ፣
ከሀሊና ፍፁም የማይጠፉ ዘመን አይሽሬ ድንቅ መጽሐፍ!

ማገዷ

‹‹አስደናቂ...የማያቋርጥ ሴራ.....››

ዊኪታ ፎልስ ታይምስ፡፡

* * *

‹‹በጥራት የተዘጋጀ ፍጹም አዝናኝ!.....ተንልሙ የማይከደን!››

ፕብሊሸርስ ዊክሊ፡፡

* * *

‹‹ከምርጦችም የሚመረጥ.....!››

ዘ ኒውዮርክ ታይምስ፡፡

‹‹በእያንዳንዱ ገጽ ልብ [illegible] !...››

ሃያሲ ሸርለ ኤደር፡፡

እርሺንግ ቫላስ

በድርሰቶቹ ፍቅር የተጠመደው የዓለም ህዝብ ብዛት በሚሊዮን [illegible] አንባቢዎቹ ሁለት ሚሊዮን ቅጂ ልብ አንጠልጣይ ልቦለዶች ያስነበበው አሜሪካዊው ደራሲ እርሺንግ ዋላስ በሞት ከመለየቱ በፊት በዓለማችን ከሚገኙ አምስት ምርጥ ደራሲያን አንደኛው ነበር፡፡

አሳብ አሳታሚ
Asbab Publishers
[illegible]

[illegible]

ዋጋ 172.00 ብር ብቻ